@Amharicbookstore

# ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

## የሕይወት ታሪክ

## ማ ስ ታ ወ ሻ

ዘነበ ወላ

የመጀመሪያ ሕትመት ሚያዝያ 2006
አዲስ አበባ

የመጀመሪያ ሕትመት ሚያዝያ ፪፻፫ ዓ.ም
© ዘነበ ወላ ወጋ
***

ኢሜል Zenebewola @ Yahoo.com
Zenebewola @ Gmail.com
***
የመ.ሣ.ቁጥር 25360 ኮድ 1000
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
***

የፊት ገጽ ፎቶ በደምሰው ኃይለሚካኤል
የሽፋን ዲዛይን አለባቸው ስቱዲዮ
ኢሜል allebachew@yahoo.com

## መታሰቢያ

ግብርናን እንደ ዘር ብንቆጥረው የዚህ መጽሐፍ ባለታሪክና ደራሲው የገበሬው ዝርያ ይሆናሉ:: ጋሽ ስብሐት በአባቱ፣ ደራሲው በአያቱ የአርሶ አደሩ አብራክ ክፋይ ናቸውና::

ግብርና ከዓለማችን ሕዝብ ሕይወት ጋር ስናቆራኘው ዐሥር ሺህ (10,000) ዓመታትን አስቆጥሮ እንዳደገና እንደተመነደገ ድርሳናት ይመሰክራሉ:: የኛዎቹ አርሶ አደሮች ከዚህ የዘመናት ምጥቀት በጨለፉት ዕውቀት እናት አገራችንን የሺህ (3,000) ዓመታት በቅብብሎሽ ይዘዋት እንደዘለቁ ከመጣፍም፣ ከሊቅ አፍም የምንረዳው ነው::

«ተግባርና ሳይንስ ዓለምን ይለውጧታል::» ይላል ስመጥሩ ሩሲያዊ ደራሲ ማክሲም ጎርኪ:: ሀገራችንን በተግባርም ሆነ በሳይንሳዊ ምርምር ውጤታማ ለመሆን እንቅስቃሴ ያደረጉትን አርሶ አደሮችና ድንቅ ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶችን ማሰብ ፈለግሁ:: «በከዳሽ ከንደ ትከዳኝ፣ ምላሴም ከትናጋዬ ትጣበቅ» ብለው አርሶ አደሮቻችን ጠላት በመጣ ቁጥር ለዘመናት ሞተውለታል:: በአሁኑ ጊዜ «ከዝቅተኛው አዘቅት ውስጥ» የሚገኙትን አርሶ አደሮቻችንን ሕይወት አገራችንን ለመለወጥና «ዘርተን ለመቃም ወልደንም እንድንስም» ለሚጥሩ ተመራማሪዎች ከተግባራቸው ግዝፈት አኳያ ይህችን አነስተኛ ድርሰቴን መታሰቢያ ትሆናቸው ዘንድ ሳበረክትላቸው በታላቅ አክብሮት «ኖር» እያልኳቸው ነው::

ዘነበ ወላ
አሃዱ በሦሺህ ዓመት ጉዞአችን ላይ ተበረከተ

## «በየኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር...»

ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ጽፌ ለማጠናቀቅ ከሞት ጋር ስንሽቀዳደም ለሥራዬ መሳካት ሕይወት የዘሩብኝ በርካታ ወዳጆቼ ናቸው:: ከእያሌዎቹ ጥቂቶቹን የቡድናችንን አባሎች ሳስተዋውቃችሁ:: ባለቤቴ ወይዘሮ ዐለሚ በላቸው ማንበር ቀደሚ ናት:: የዕረፍትና የመኝታ ጊዜዋን ይህንን መጽሐፍ በኮምፒዩተር በመጻፍ የበኩልዋን አድርጋለች:: በመጀመሪያው ህትመት ወይዘሮ ሱ ኤድዋርድስ ተንቀሳቃሽ ኮምፒዩተር (Portable computer) በማዋስ ሥራችንን በቤታችን ውስጥ እንድናጠናቅቅ አግዘውኛል:: መጽሐፉ ከታረመ በኋላ በትልቅ ኮምፒዩተራቸው አስፈላጊውን ማስተካከልና ማተም እንድናከናውን ቢሮአቸውን ወለል አድርገው በመቀበል የድርሰት ሥራችን እንዲሳካ አድርገውልናል::

የዚህን መጽሐፍ ጅምር አውግቼአቸው የበኩላቸውን ለማድረግ ቃል ገብተውልኝ መሠረት ዶክተር ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር ከሞት ጋር ለምናደርገው እሽቅድምድም የብርሃን ፍጥነት እንዲኖረን የህትመት ካፒታል በመስጠት አበረታተውናል:: ለዚህ አስተዋጿቸው ምሥጋናችን የላቀ ነው::

የሚያስፈልጉኝን ዶክመንትና ፎቶግራፎች በመለገስ ወዳጆቼ ስንዱ አበበ፣ ስዩም ተፈራ፣ የሴፍ ገብረ እግዚአብሔር፣ ማርታ ገብረ እግዚአብሔር፣ ኢፍሬም ሐጎስ፣ ኃይሉ ታምራት፣ ዶክተር ኢያሱ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር፣ ሲራክ እንዳለ፣ ደምሰው ኃይለ ሚካኤል፣ ትድስት ነፍሰ የሐንስና መንን ክፍሌን ምስጋናዬ ይድረሳችሁ::

የመጽሐፌን ረቂቅ በማንበብ ሃሳብ በማዋጣት ሊገኙ የሚገባ ተደቆዎችን በማስታወስ የበኩላቸውን ካበረከቱ ጓደኞቼ መካከል እስክንድር ከበደ፣ ሙሴ ኃይሉ፣ ሰለሞን ታደሰ ጎሳ፣ ወልደገብርኤል አብተ ባለውለታዎቼ ናቸው:: በተጨማሪም ለአዲሱ ሕትመት የአርትኦት ሥራ ከሠራሁ በኋላ አይተውት ሙያዊ አስተያየት ለሰጡኝ የጋራ ወዳጆቻችን ለሆኑት ጋሼ ሳህለሥላሴ ብርሃነ ማርያም፣ ኃይለመስከት መዋዕል፣ መምህር መሠረት አበጀን ከልብ አመሰግናለሁ::

የህትመት ወጪዬን ለመሸፈን እንዲረዳኝ ዲኤችገዳ ኢንዱስትሪያል ግሩፕ እና ወንድሜ አማኑኤል ሀዲስ እገዛቸውን በመቸራቸው የአምላክ ቸርነት ይድረሳቸው::

ከእነዚህ ወዳጆቼ ጋር በየኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር በሰያሜን ጉሮሮ አተንት ይሰንቀር የምንባልበት ጊዜ እነሆ ደረሰ:: ከጓደኞቼ መካከል ሰለሞን በዚህ ፌስታ ላይ ለመታደም አልታደለም:: መጽሐፉ እንደተጠናቀቀ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል::

የወዳጆችንን ነፍስ የሳሊበላን ዕድቅ፣ መጽሐፉን ሙሉ ለማድረግ በማደርገው ጥረት በሃሳብም፣ በምስልም፣ በገንዘብም ሊረዱኝ የሚተሳኑ ዕድሜ ከጤና ጋር ይስጥልኝ.

@Amharicbookstore

እንግባባን ሆዬ!

በልጅነቴ ለመጀመርያ ጊዜ ፎቶ ተነስቼ ሲያሳዩኝ "ይህን ነው የምመስለው?!" ብዬ ገረመኝ። ፎቶውን ግን አምኜዋለሁ። ሌሎቹን እንስቶ አይቼዋለሁዋ! ካሁን ሲያዩኝ ይህን ነው 'ምመስለው።

ሌላ ቀን ደግሞ ድምፄን በቴፕ ሰማሁትና እሁንም ገረመኝ። ሰዓገር እኔ የምሰማው ሌላ፣ የቴፕ ድምፅ ሌላ!

ዘመናት አለፉ (ቀን መቁጠሪያው ግን አመታት አለፉ ይላል) እኔም ሆንኩ ዘነብ ደህ የምታነሉት መፅሀፍ ገና በሆነብኝን እንኳ ሳይመጣ፣ እሱ ስለ ህይወትና ስለ ስነፅሁፍ እንዲወለሉት ሁኔታዎችን አመቻቸ።

ሰናወሉ... ሰናወሉ... ሰናወሉ... ሳናስበው ይሄ መፅሀፍ ብቅ ማለት ጀመረ። ተናገርኩ የመዘገበ፣ ፃፈ። በሰዎች እምነት አመት እድሜዬ ይሄ ዘነብ በሚከተሉት ምእራፎች እንደምታነሱት በቃላት ፎቶ እንስቶኝ አየሁ። ላካ በድጋ እኔን ሲያዩኝ ይህን እመስለሁ?! ገርሞኛም እናንቱ!!

አብሬኝ ሁኝ ስለ ህይወት ተአምራት እየተገረመኝ ሁ በቃል የተሳሉውን ፎቶዬን ታዩ ዘንድ በእንግብሮት እጋብዛለሁ።

ዘነብ ወለ ያዘጋጀውን የህይወቴን አልበም እየከፈታችሁ ነው። መልካም እይታ! ለሁሉም ለሁሉም እንኳ በረከት!... በመጨረሻም የገረመኝ — የዘነብ ወለ ብእር እንደ ሲኒማ ወለል እድርጎ ያሳየናል።

የዘነብ አገሮች (ጋሞ የሚባሉት) አብሮቻው የሌለውን፣ የሚያከብሩትን የሚያደንቁትን ሰው ሲያስታውሱት << ኢዚ ገደንታ ሰገ ኢሃ ሱንጎ ዴንሳ ሀኢካ ኢዛሶ ኤቃይስ!>> ይላሉ። "እሱ በሌለበት ስሙን ስነገውሩ፣ ተነስቶ ቆሞ <ኖር!> እንደሚለኝ ነው" እንደ ማለቱ ነው። ፎቶግራፌን ካፈጠረ በጋሞ ስርአት ተነስቼ እጄ እንሳሻለሁ። በዚያውም ለዘነብ አገሩና እናቴ፣ ለእኔ ወለ ወጋንና ለወይዘሮ ወርቅነሽ ባጎ፣ እሱን ወለደው ለሰጡን ወላጆቹ እና እማዬ (ትእዛዝ ያግዜር ቢሆንም) በእንግብሮት ተነስቼ እጄ እንነሳቸዋለን...

መልካም ንባብ!

[illegible]

ሰ ባሰት ለኪቢ

፳፫/፪/፺፫

# ክፍል አንድ

# ስብሐት ለአብ

"እስ በውስጣችን...
እውነት ፍፁም ሆኖ የምታበራበት
ደግሞም ማወቅ ማለት
ከውጭ ያለውን ጊዜ ከመፈለግ
ከውስጥ ያለውን እንዲበራ ማድረግ"

ገብረ ክርስቶስ ደስታ

@Amharicbookstore

# የሕይወት ታሪክ

1ኛ ስም — ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር
2ኛ የትውልድ ቀን — ሚያዝያ 27ቀን1929(28) ዓ.ም
3ኛ የትውልድ ስፍራ — ርባ-ገረድ አድዋ (ትግሬ)
4ኛ ትምሕርት 1940 -1944 ተፈሪ መኮንን 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
1944 _ 1948 ተፈሪ መኮንን 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
1948 _ 1952 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ቢ.ኤ በማስተማር ሙያ (Education)
1953 _ ዌስተርን ሚሺጋን ዩኒቨርስቲ (ዩ.ኤስ.ኤ)
1956 _ ዩኒቨርሲቲ ድ' ኤክስ ማርሰይ (ፍራንስ)

5 የሥራ ልምድ
1935 _ 1939 እረኛ
1946 _ 1947 የተፈሪ መኮንን ዓላማ The T.M.S Ensign የተባለ መጽሔት አዘጋጅ
1953 _ 1956 አሰፋ ወሰን ትምህርት ቤት የእንግሊዘኛ መምሕር
1958 _ 1960 ትምሕርት ሚኒስቴር ስኮላርሺፕ ክፍልና የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ባልደረባ።
1960 _ 1962 የኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር የእንግሊዝኛው
1962 _ 1967 ዓለም የሕዝብ ግንኙነት አማካሪዎች።
ሀ. ሥራ አስኪያጅ
ለ.. 1965 _ 1966 "መነን መጽሔት ሥራ አስኪያጅ 'ETHIOPIA MIRROR' CONTRIBUTTING EDITOR

-----------------------------

*ይህ መረጃ እራሱ ጋሼ ስብሐት ጽፎት ተተይቦ እኔጋ የደረሰ ነው። ይሁን እንጂ ከ1966 እስከ 2004ዓ.ም ያለውን መረጃ አላካተተም። (ሀሐፊው)*

## ክፍል አንድ

### ስብሐት ለአብ

ገጽ


1. ሞትን እንቅደመው .................... 13
2. ልጅነት .................... 34
3. ዶቃው .................... 45
4. ወርቃማ ዓመታት .................... 53
5. ኮሌጅን በጠስናት .................... 61
6. "ብር አምባር ሰበረችልዎ".......... 70
7. የኔታ ስብሐት .................... 79
8. "የተወለድኩብሽ ያደግኩብሽ ሀገር" ... 86
9. ሚጢጢ ተአምረኛ ደሴት.......... 105
10. ሀገሬ እንክል ሳም.................. 109
11. ማሪያን ላቤላ ፍራንስ .............. 121
12. የዕድሜ ልክ እውነት.............. 127
13. ያለፈውን ታሪክ ፍለጋ .............. 143
14. ባለመትረየሱ .................... 150
15. ነጂና ተነጂ.................... 152
16. "አካኪዩ" .................... 158
17. ፍቅሩን በዕንባው አየሁ.............. 164
18. ዜና መልሕቁ ናት.............. 169
19. ድብቋ ፍቅረኛ .................... 172
20. እነሆ ባህር ማዶ መሻገሩ ቁርጥ ሆነ...174
21. ስዊዝ.................... 179
22. ከወጣቷ ጋር መፈጣጠም .......... 185
23. አለቆቹ .................... 189
24. የክብር ሕግጋት .................... 193
25. አልአሚን.................... 197
26. ሻህራዛድ.................... 198
27. አጫጭር መልዕክቶች.............. 217


## ክፍል ሁለት

### "ይናገራል ፎቶ "

@Amharicbookstore

## ክፍል ሦስት

### ማዕደ ጥበባት


ገጽ

28. መጻሕፍት ስሁሉም................. 225
29. ጥበበ ሰይጣን ቤት..................... 228
30. ባርነትና ነፃነት ........................ 236
31. ዓይኔን አበራልኝ ..................... 241
32. ጋዜጦች ላይ መዝራት .............. 252
33. ድርሰተ ስብሐት ..................... 263
34. ገፀ ባሕርያቱ ........................... 269
35. ተርጓሚዎቹ ............................. 274
36. ንባበ ስብሐት ........................... 278
37. ለአንባብያን ክብር ..................... 339
38. "ዶሴታንቴ"................................. 341
39. ማኅበሩ .................................... 346
40. መልዕክተ ስብሐት (ለፀሐፍት)...... 348
41. ሀያሲያን.................................. 361
42. የሕፃናት ሥነ ጽሑፍ ................. 364
43. የተነበቡልኝ ድርሰቶች.............. 369
44. 'ሲጋራ ፍራንክ' ........................ 374
45. ልደት ...................................... 378
46. ያስተዋልኳቸው ገፀ ባህርያት ........ 380
47. የስብሐት በረከቶች.............. 386
48. የመጨረሻው ጽሑፎቹ .............. 387


## ክፍል አራት

### መሰነባበቻ


ገጽ

49. የመጨረሻዎቹ ሰሌታት......................388
50. ስንብት.................. 413
51. መልዕክተ ቴክኖሎጂ .................... 428
52. ልደትና ሞት ........................ .... 431
53. የሐዘኑሉቱ መልዕክት ................. 438


## ክፍል አምስት

### ዘና እንበል


ገጽ

54. ከሳቅ ሞት ያድነን......................... 440
55. "ፈገግ ነን"....... .... .......... 464


ይድረስ ለተከበራችሁ አንባቢያን

በያላችሁበት

ተሳከ ከዘነበ ወላ

አዲስ አበባ ቀርቀስ

«እኔ የምሞተው በሚወዱኝ ሰዎች ልብ ውስጥ መረሳት ስጀምር ነው:: ሥጋዬ ሞተ ብለሽ አትዘኝ:: በልብሽ ረስተሽኝ በአፀደ ሥጋ ከምንከላወስ ሞቼ ብታስታውሺኝ ለኔ ምርጫዬ ነው::»

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

ጋሼ ስብሐት በአፀደ ሥጋ ተለይቶን አርባው እንደሞላ ሰሞኑን አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ አነበብኩ:: በመንፈስ ግን በምንወደው ሁሉ እኛ እስካለን ጊዜ ድረስ አብሮን አለ::

ሳልስቱ እንደወጣ ማስታወሻ በሚል ርዕስ በእርሱ የሕይወት ታሪክና ኪነጥበባዊ ክህሎቱ ላይ የጻፍኩትን መጽሐፍ ማንበብ ጀመርኩ:: የመጀመሪያው ሕትመት ከወጣ ድፍን 11 ዓመታት ተቆጥሯል:: እኔ ላይ 11 ዓመታት ተጨምረዋል::

ማስታወሻ ጋሼ በሕይወት ዘመኑ የኖራትን የ65 ዓመት ታሪኩን ነው የያዘው:: ተጨማሪውን 11 ዓመታት ለማከል ነው ይህንን መጽሐፍ ቁጭ ብዬ ማንበብ ያስፈለገኝ:: ሕሊናዬን ግን አንድ ፈተና ሰቅዞ ያዘኝ:: በደህናው ጊዜ ከጋሼ ስብሐት ጋር ተገናኝተን በምንጫወት ጊዜ «ምን ያደርጋል ደራሲ መሆን? የተጻፈው አልተነበበም፣ ስለዚህ ደራሲያንን ለመፍጠር አንባቢውን ለማበራከት ብለህ አትጻፍ:: እስኪ የተጻፈው ይነበብ» ይለኝ የነበረው ሃሳብ ሕሊናዬ ውስጥ አስተጋባ:: ስለዚህ የተጻፈው ይበቃል፣ መጻፍም አይኖርብኝም፣ የሚል ስሜት ተጠናውቶኝ ውስጤን ፈተነው::

በሌላ በኩል ማስታወሻን ሳነበው ድፍረቴ በጣም አስደንግጦኛል:: በሐረር ልጆች አባባል እኩል ነው 'የተሳፈጥኩት'፣ ይህንን ስፋጣዬን በአሁኑ ዕድሜ ላይ ሳስተውለው ምን ነካኝ? ስል እራሴን ታዘብኩት:: ዕድሜዬን ሳሰላው ከእርሱ ጋር ስንገናኝ 30ዎቹ ውስጥ ገብቻለሁ:: አሁን ሃምሳዎቹን አልፌአለሁ:: ዕድሜ ቸርነቱ ለማስተዋል የሚበጅ መሆኑ ነው:: የጋሼ ስብሐትን ዕንፍ የለሽ

ቸርነትም እዚህ ጋ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ እሱ ድንቅ አርቲስት ነው፡፡ ይህንን ክህሎቱን **ልጅነት** በተባለው ሥራዬ ላይ አሳይቶኛል፡፡ «ሰውና እንጨት ተሰባሪ ነው፡፡ እንዴት እንዳረምኩህ ልብ ብለህ ተመልከት፡፡ ሁሌም አብረን አንኖርም አንድ ቀን እንተላለፋለን፡፡ በዚህ ቀበዐ ራስህን ችለህ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ ልብ አድርግ» ይለኝ ነበር፡፡

ማስታወሻን አሁን እየነበብኩት ለምን እንደ ሌላው ሥራዬ አልደሰትኩም፡ ስል እራሴን እጠይቃለሁ፡፡ እንደኛው ይህ ሥራ የራሴ እንደሆነ አንባቢም አቀናባሪውም እንዲገባው እስከ መሰረቤን እንደ ምልክት እንደተወው አምናለሁ፡፡ ልክ እንደ ሌላ ሥራው ሁሉ ጥርት አድርጎ አርሞ ቢሰጠኝ፡ ሥራው የእኔ ሳይሆን የእርሱ ይሆን ነበር፡፡ ስለዚህ በገዛ የሕይወት ታሪኩ እንዳማረበት ከነማድፈቱ ተወኝ፡፡ ዛሬ በራሴ ላይ ነቅቼ መጽሐፉን እንደ አዲስ የአርትኦት ሥራ ሠርቼ ጋሼና አንባቢዬ እንደልባችሁ እንድትጨዋወቱ ትቻችኋለሁ፡፡

ጋሼ ስብሐት ሲያርፍ ምናልባትም ስምንት ወር ገደማ ሲቀረው አንድ ባልንጀራዬ ከባህር ማዶ ጋሼን አስፈርሜ ማስታወሻን እንድልክለት መልዕክት ላከብኝ፡፡ መጽሐፉ አራተኛ ሕትመት ላይ ስለቆመ ገበያ ውስጥ የለም፡፡ ለልጆቼ ካስቀመጥኩት አንዱን ኮፒ ወስጄ ለባሕረኛው ያሬድ ሳህሉ ብሎ እንዲፈርምለት ሰጠሁት፡፡ ይህን ሳደርግ ያስተዋለች አንዷ ሸሪካችን ለምን አሁን ለአምስተኛ ጊዜ አታሳትመውም አለችኝ፡፡ እኔም ከዚህ በኋላ አንድ ስድስት ወር ቆይ ብለን ተነጋግረን በተጨማሪም እጄ ላይ ያሉትን አዳዲስ መረጃዎች ጨምሬ አሳትመዋለሁ አልኳት፡፡ ይሁን እንጂ ጋሼ እንደሚለው ሰውና እንጨት ተሰባሪ ነውና ሞት ቀደመኝ፡፡ አሁን ይህን ሥራ በአዲስ መልክ መሥራት ስጀምር የተፈጠሩብኝን ውስን ክፍተቶች ለመሙላት የራሴን አስተውሎት አክዬበታለሁ፡ በተጨማሪም የጋራ ወዳጃችን ኃይለ መለኮት መዋዕል ቀደም ብሎ ስለ ጋሼ ስብሐት ለአብ የሚያውቀውን አስተውሎቱን በራሱ ቋንቋ እንዲገልጽ በማሰብ አጭር ቃለ ምልልስ አድርገናል፡፡ እነዚህን ሃሳቦች አስፈላጊ ናቸው ብዬ ባሰብኳቸው ምዕራፎች ግርጌ ላይ አስፍሬያቸዋለሁ፡፡

እዚህ ጋ የተከበራችሁ አንባቢዎቼ በተለይ የቅርብ የሆናችሁ ጋሼ በጣም የሚወዳትን የኔወርቅ እንደሻውን ባለቤቱን አሌክስን ብታናግር ወይም ከስንዱ አበበ ጋር ብታወራ ይሄን ታገኝ ነበር፤ ወይም ባልንጀራውን አረፋዓይኔ ሐጎስን ሥዩም ተፈራን፣ ሰብስዛር ሳሙኤል፣ ሰውነቸው ተረፈን ብታገኝ የሚልህ ይኖራል፡... የመሥሪያ ቤቱ ባልደረቦችም፣ ወንድም እህቶቹ... ሲባል መጽሐፉ ከልክ በላይ ይሰፋና ጠበብት እንደሚሉት Scholar's Biography እንዳይሆንብኝ ሰጋሁ፡፡

ይህንን ስጋት በቅርቡ በአጠናቀቅኩት አዲስ ሥራ በተግባር ተከስቶ አስተውየዋለሁ፡፡ ይህንን ከ1990 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ያጠናሁትን ጉዳይ እንዳጠናቀቅኩ ለሁለት ወዳጆቼ አስነበብኩ፡፡ ወጣቱን ትውልድ እንዲወክልልኝ ግሩም ዘነበን ሳስነብብ አዛውንቶችን እንዲወክልልኝ ለጋሼ ሳህለሥላሴ ብርሃነ ማርያም አስነበብኩ፡፡ የሁለቱም አስተያየት ገንቢ ነበር፡፡ ግሩም ደስ ተሰኝቶ እንደ ሽልማት ቻይና ሬስቶራንት ራት ጋበዘኝና ይስተካከሉ ያላቸውን ነጥቦች አንስቶ በተረፈ "አሪፍ ነው" አለኝ፡፡ የጋሼ ሳህሌ አስተያየት አጭርና ግልጽ ነበር፡፡ "መጽሐፉን የጻፍከው በሙያው ለሚመራመሩ ሳይንቲስቶች ነው" አለኝ፡፡ ስለዚህ ይህን አዲስ መጽሐፍ ለሁለት ከፍዬ ማስነበቡን ወደድኩ፡፡ አንደኛው አብዛኛው አንባቢ ቢያነበው ማለፊያ ነው ያልኩትን 57 ምዕራፍ አሳትመዋለሁ፡፡ በመጠንም 500 ገጽ ይወጣዋል ብዬ እገምታለሁ፡፡ የአያሌዎቹ ምስክርነትና ምርምር ያለበትን ደግሞ በመስኩ ለተሰማሩ ምሁራን በምዕራፎችም ሰፍቶ በገጽም ዳጎስ ብሎ እንዲታተም አዘጋጅቼዋለሁ፡፡ ይህንኑ ችግር ላለመድገም ነው ቀደም ብዬ ያነሳኋቸውን ባልንጀሮቹን የሥራ ባልደረቦቹንና ቤተሰቦቹን አነጋግሬ ማከሉን የገደፍኩት፡፡ የተከበራችሁ አንባቢዎቼ ይህማ ያስፈልገናል የምትሉ ከሆነ ተርፎ ከሚቀረው ዕድሜ አንድዬ ካልነፈገኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሌላ መጽሐፍ ማዘጋጀት እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም ባለታሪኩ በሌለበት ሌሎች ሰዎችን አነጋግሮ መጽሐፍ መጻፍ እንደሚቻል በአቶ ዱጉማ ሁንዴ ገዳ (ዲ.ኤች.ገዳ) ላይ የጻፍኩት መጽሐፍ ማለፊያ ትምህርት ሰጥቶኛል፡፡ ጋሼ ስብሐት ላይም ሃሳቡ በስፋትና በጥልቀት መኖሩን አውቃለሁ፡፡ እኔ ባይሞላልኝ መጪው ትውልድ ይከውነዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ይህን መጽሐፍ ስጽፍ በዕቅዴ የያዝኩት አብዛኛው ሕዝብ የሚያነበውን Popular Biography የተባለውን ዘርፍ ነው፡፡ ቀደም ብዬ እንዳልኩት የእኔንና የኃይለ መለኮትን ሃሳብ ሳክል የዘርፉን ሕግጋት ጥሻለሁ፡፡ ደግነቱ የጣስኩት የሥነ ጽሑፉን ሕግ እንጅ ወንጀለኛ መቅጫውን ባለመሆኑ ዕድለኛ ነኝ፡፡ የሥነ ጽሑፍን ሕግ መጣስ እያስከስስም ግን ያስተቻል፡፡ ያን ደግሞ የለመድኩት ሲሆን፡ ለመቀበልም ዝግጁ ነኝ፡፡

@Amharicbookstore

በተጨማሪም የተቀረውን 11 ዓመታት የሕይወት ሒደቱን እንደ ምዕራፎቹ ቅደም ተከተል አክዬላችኋለሁ። እንዲሁም አዲስ ፎቶግራፎች ጨምሬያለሁ። የቀድሞው ማስታወሻ መጽሐፍ ጀርባው ላይ ጋሼ ስብሐት የፌስታል ቦርሳውን ይዞ አንድ መጽሐፍ እያነበበ ሲያዘግም የሚያሳይ ስዕል እህቴ ማህሌት ወርቁን አስዬ መጸሐፉ ላይ ታትሞ ወጥቶ ነበር። በሕትመት ወቅት ስዕሉ ጎልቶ ባለ መውጣቱ ልብ ላላለው አይታይም። ልብም ያለው ያለ አይመ ስለኝም። ይህ ስዕል ሲሳል ጋሼን «የማንን ደራሲ መጽሐፍ እያነበብክ ማዝገም ትፈልጋለህ?» ብዬ ጠይቄው ነበር።

«የዊልያም ሼክስፒርን ማክቤዝን» ነበር ያለኝ። ማክቤዝ ጭፍግ ደም በደም የሆነ ታሪካዊ ድራማ ነው። ለምን ይህንን መረጥክ ብዬ በወቅቱ አልጠየቅኩትም። ፍላጎቱን ብቻ ነው ያስፈ ፀምኩለት። አሁንም ከጀርባ ባስገባው ደብዘዞ ላታዩት እንደምትችሉ በመገመት በፎቶግራፍ ምዕራፍ ውስጥ አካትቼዋለሁ። አስተውሉና እናንተም ቀዝማችሁበት በህሊናችሁ ሸንጎ ዳኙት። በሁለት ምዕራፎች ላይ ታሪኩ ብቻ አንባቢዎቼ'ጋ እንዲደርስ በማሰብ የባለታሪኮቹን ስም ገድፌዋለሁ። አንደኛው እነሆ ባህር ማዶ መሸገሩ ቁርጥ ሆነ እና ስዊዝ ባለታሪኳ አገር ውስጥ ስለሌለች የእሷንም ሆነ የባለቤቷን ስም ቀይሬ እሱ እንዳሜወተኝ ሳይሆን በተገቢው ቋንቋ አርሜ አቅርቤዋለሁ። ሁለተኛው አለቆቹ በሚል ርዕስ የነገረኝን እንዳልኩት ስማቸውን አስቀርቻለሁ። በአንድ ወቅት በሥራ መስኩ ይደረስበት የነበረውን አመቃ ሲያወጋኝ «ጡረታ ወጥቼ ይህቺኑ እንዳገኝ ያደረገኝ አንድ ስሙ የደቡብ የሆነ የማኅበራዊ ዋስትና ሠራተኛ አስተካክሎልኝ ነው እንጂ ይህቺንም አላገኝም ነበር ብሎኛል። እኔም የምጽፈው ግለ ታሪክ ነውና የግል ማህደሩ ውስጥ የከተቱበትን 'እፌንስ' አይቼ ለማካተት ጥሬ አልሰመረልኝም። ለማንኛውም ምን አይነት የሥራ ኃላፊዎች እንደነበሩት ይህቺ ምዕራፍ እንደነገሩም ቢሆን ታሳያለች ብዬ ስም ሳልጠቅስ አካትቻታለሁ። ከእኔ ጋር እሱ በሚወደው አባባል እንሰነባበት። ይህቺን አባባል ደጋግሜ አስጠንቼዋለሁ። ጽፌም ሰጥቼዋለሁ። ግን ይጠፋውና ትዝ ስትለው "ድገምልኝ" ይለኛል።

ጋሞዎች እንደእርሱ እራሱን ሆኖ ለታየ የቀለም ቀንድ፣ ተግባራዊና ህያው ሰው እንዲህ በማለት አክብሮታቸውን በሌለበት ይገልጻሉ። እኔም 'በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ' እንዲሉ የራሱን የጋሼን ስም አካትቼ አባባሉን ልበልላችሁ«ጋሼ ስብሐት ኔ ባይንታ ሶን ኔሱንሳ ዴንሳሺ ህኢካ ቦንቾን ኔስ ኤቃይስ!» ትርጓሜው «ጋሼ ስብሐት አንተ በሌለህበት ቦታ ሁሉ ስምህን አሁንም ሳነሳ በአክብሮት ቆሜ ነው»። ማለት ነው። ባህሉን ሙሉ ላድርግላችሁ። ይህንን አባባል ብዬ አክብሮቴን ስገልጽ የሚሰማ ጋሞ ባጭሩ ያከበራችሁትን አብረዋችሁ እያከበሩ እንዲህ ይላሉ። «ኔስካ እሲ ኢቆ!» ትርጓሜው «አንተም የተግባር ሰው ሆነህ በሌለህበት እንዲህ ሰው ኖሮ የሚልህ ሁን!» ማለት ነው። ሁላችንንም ለዚህ አክብሮት ያብቃን አሜን! መልካም ንባብ!

ዘነበ ወላ
መጋቢት ፪ሺ፮
አዲስ አበባ ቂርቆስ



፩

# «ሞትን እንቅደመው»

*"ተረት ተረት"*
*"የላም በረት"*
*"አንዲት ሴትዮ ነበረች"*
*"እሺ!"*
*"ስትኖር ስትኖር ታመመችና ሞተች፣ ተቀበረች፣*
*ይሀ የሁላችንም የሕይወት ታሪክ ነው"*

*ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር*
*ሌቱም አይነጋልኝ ገጽ 24*

እነሆ! ቀዳሚና ተከታይ፣ የአላፊውና የመጪው ትውልድ አባል ሆነን ተገናኘን፡፡ ጋሼ ስብሐት የአላፊው ትውልድ አባል ለመሆን በመጨረሻዋ የሕይወት ጠርዝ ላይ ይገኛል፡፡ የእኔም ትውልድ ይከተለዋል፡፡ ሕይወት እልፍ አእላፍ ዘመናትን ያሸጋገረችው በቅብብሎሽ ነው፡፡ እንደ ጊዜ በምትሃትዋ በውስጣችን ለዘመናት ፈስሳለች፡፡ ወደ ፊትም ሂደቱ እንደዚሁ ይቀጥላል፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን "ዘነበ!"
"አቤት ጋሼ?"
"ሞትን እንቅደመው?"
"እሺ፤ ግን እንዴት?"
"ከማውቀው የማስታውሰውን ሁሉ ልንገርህ።"
"ማለፊያ።"
"የሚጣፈውንም፣ የማይጣፈውንም ነው የምነግርህ።"
"እየያዝኩ ነው።"

እንቀጥል። ሔንድሪክ ቫን ሉን (Hendric Van Loon) የሚባል የደች ዘር አሜሪካዊ ደራሲ The wandering Jew የሚባል ልበለድ ጽፏል። በአጭሩ ላጫውትህ። በእኛ ቋንቋ ስትተረጉመው ከርታታው ይሁዳ ልትለው ትችላለህ። ይሁዳው ሲፈርድበት፣ ሊፈታትነው ከማይችለው፣ ቀና ብሎ ሊያየው ከማይገባ ሰው ጋር ለዘለዓለሙ ተቀያየመ።

@Amharicbookstore

ነገሩ እንዲህ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ጎልጎታ ጉብታ ሊሰቅሉት መስቀል አሸክመው እየገረፉ ይወስዱታል:: እየተንገዳገደ፣ እየተወላገደ ደፋ ቀና ሲል፣ ይሁዳው አየውና «ምን እዚህ ትሽመደመድብናለህ? ፈጠን ብለህ ሂድ ቀርፋፋ» አለው::

ኢየሱስም ቀና ብሎ አየውና «እኔስ እየሄድኩ ነው:: አንተ ግን እስከምመለስ እዚሁ ትቆየኛለህ» አለው::

ያ ክርታታ ይሁዳ አሁንም በዓለማችን በሕይወት አለ:: በልዩ ልዩ ሀገር እየተዘዋወረ ይኖራል:: አይሞትም:: ኢየሱስ ወደ ዓለማችን ዳግም እስኪመጣ ይጠብቀዋል:: የዚያን ጊዜም ዕድለኛ ከሆነ ነው የሞትን ፅዋ የሚጠጣት:: እስከዚያው ድረስ ግን መንከራተቱን ይቀጥላል ለረጅም ጊዜ አብረውት የኖሩት ሰዎች ተገርመው «አንተ አታረጅም? አትሞትም እንዴ?» ሲሉት «ቢቃ አውቀውኛል ማለት ነው» ይልና ሀገር ቀይሮ የርግማን ኑሮውን ይቀጥላል:: አንተ ራስህ የአረብ መልክ ያለው ሰው ካጋጠመህ ተጠራጠር:: ምናልባት ክርታታው ይሁዳ ሊሆን ይችላል:: እኔ እንኳን አንድ ቀን ተረት ሰፈር አይቼዋለሁ» አለ ጋሼ::

ያ ክርታታ ይሁዳ እሱ ራሱ ጋሼ እንዳልሆነ ምን ማረጋገጫ አለኝ? ጋሼ በአፀደ ሥጋ ዕድሜው ከሰባት አሰርት እልፍ ይበል እንጂ፣ በኔ ግምት በንባብ እንደዚህ እንደ ክርታታው ይሁዳ ከሁለት ሺ ዓመታት በላይ ኖሯል፣ ስል አስባለሁ:: በንባብ ርዕስ ጉዳይ አውግተን ምናባዊ ጥልቀቱን ሲያሳየኝ ይርቅብኝና አለማንበቤን እንድገነዘብ ያደርገኛል:: አስተሳሰቡን ሳስተውል ጥልቀቱ ያስደንቀኛል:: ርቀቱ እንደ ምትሃት ያፈዘኛል:: አንድ ሰው እስከዚህ ድረስ ያውቃል ስል እገረማለሁ::

ጋሼ ሲያወጋኝ «እንዲት ሚጢጢ የሆነች የአንትሮፖሎጂ መጽሐፍ አንብቤያለሁ:: ጊዜው ቆይቷል:: ጭብጡ ግን እዚህ ውስጥ አሁንም አለ» ጭንቅላቱን በጣቱ እየነካ::

«ከአሰር ሰዎች መካከል አንዱ በውድም በግድም አብረውት ያሉትን ሰዎች መምራት ነው የሚፈልገው:: ሌላኛው ሰውዬ መምራትም መመራትም አይፈልግም:: አፈንጋጭ ነው:: ፈላስፋ፣ ሳይንቲስት፣ ደራሲ፣ ወይም የአንድ ጥበብ ሊቅ ነው:: ሁሌም ራሱን እንጂ ሌሎቹን አያያቸውም:: አብረውት ቢኖሩም፣ ባይኖሩም ሁሌም ብቻውን ነው:: የተቀሩት ስምንቶቹ ግን መንጋ ናቸው:: የሚመራቸው፣ አለዚያም የሚነዳቸው መሪ ያስፈልጋቸዋል» ብሎኛል::

ይህ ሰው ለእኔ በሁለተኛው ደረጃ ላይ የሚገኝ አፈንጋጭ፣ በሰው ዱር ውስጥ እየኖረ በራሱ ዓለም ውስጥ የመነነ ሰው ነው:: በምናባዊ ሂደቱ ርቋል:: ማጋነን ቢመስልም ከመጻሕፍት ዓለም ካነበበው ይልቅ ያላነበበውን መቁጠሩ ነው የሚቀለው::

@Amharicbookstore



በሶስት ቋንቋዎች ያነባልም፣ ይጽፋልም:: በእንግሊዘኛና በአማርኛ ይጠበባል:: ፈረንሣይኛ አሳምሮ ይችላል:: የአፍ" መፍቻ ቋንቋውን ትግርኛን ጨምሮ በአራት ቋንቋዎች ይናገራል:: በእነዚህ ቋንቋዎች ስለ ሥነ ጽሑፍ፣ ፍልስፍና፣ ሥነ ልቦና፣ ሥነ መለኮት፣ ታሪክና ወታደራዊ ሳይንስ አንብቧል:: ይህንን ጥበብ እንደ አስፈላጊነቱ ወደ አማርኛ እየመለሰ በጋዜጦችና፣ በመጽሔቶች ላይ ጽፏል:: በአጠቃላይ ጋሼ በሁለት እግሩ የሚሔድ ነፍስ ያለው፣ ድንቅ ሙሉ ቤተ መጻሕፍት ነው:: በበርካታ ኢትዮጵያውያን አንባቢዎች ዘንድ ባዕድ የሆነውን የባሕር ዓለም የጋሼ ነፍስ ጠልቃበታለች:: ስለዚህም በእሁኑ ሰዓት ገዝፎ የሚታየኝ ከደራሲነቱ ይልቅ ድንቅ አንባቢነቱ ነው::

በ1960ዎቹ የዩኔስኮ ዳይሬክተር የነበረው እምቦዋ ሲናገር «በአንድ የአፍሪካ መንደር የሚኖር ሽማግሌ ሞተ ማለት፣ አንድ ሙሉ ቤተ መጻሕፍት ተቃጠለ ማለት ነው» ብሏል::

እንደ አባባሉ የእኛ የአፍሪካውያን ቤተ መጻሕፍት አባቶቻችንና እናቶቻችን ናቸው:: እዚህ እኔ ባለሁበት አካባቢ ላለን አፍሪካውያን ጋሼ ተልኮልናል:: እናንተ አካባቢ ያሉትን አዛውንትና ባልቴቶች ልብ ብላችሁ በማስተዋል ፈልጓቸው:: በቅርብ ርቀት ታገኙዋቸዋላችሁ:: የሙጥኝ በሏቸው:: ከማለፋቸው በፊት የሚያቀብሏችሁን ሁሉ እንዲያካፍሏችሁ ጣሩ:: ካለፈው ትውልድ የተቀበልነውን ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፉን ባሕል እናድርግ:: እንዲህ አድርገን ነው ዘርተን ለመቃም፣ ወልደን ለመሳም ታድለን ሙሉ ሰው የምንፈጥረው::

ጋሼ ይህንን ስሜቴን በመረዳቱ የአንድ መጽሐፍ ርዕስ አንስቶ « The old man and the sea?ን አንብበኸዋል?» ይለኛል::

«ምን ማለትህ ነው እኔ እኮ መርከበኛ እያለሁ አንብቤዋለሁ» ስለው::

«አ Sailor! እኔ እኮ ያላነበብከው መስሎኝ ላጫውትህ ነበር:: ጭብጧ ደስ አትልህም? ያንን ሁሉ ታሪክ በጥቂት ገፀ ባህርያት ሲያጫውትህ አረፍ ደራሲ ነው ኧርነስት ሄምንግወይ:: ስለ ባህር ካነሳን ካልቀረ Moby Dickን አንብበሃል?

«ስለቋንቋ ክብደት አትጨነቅ:: ለምን ሩብ ብቻ አይገባህም? ደጋግመህ ማንበብ አለብህ:: እንዲያ እያልክ ነው ከደራሲው ቋንቋ ጋር ሐሳብ ለሐሳብ የምትግባባው:: እንደገና መጀመር አለብህ:: ለማንኛ ውም መጽሐፉን አግኝተህ እስከምታነበው የማውቀውን ላጫውትህ» ይልና ይጀምራል::

«አንቱ ደግሞ ደስ ያለህን ርዕስ ምረጥና ጠይቀኝ:: «እዚህ» ጭንቅላቱን እየጠቆመኝ «አረፍ ቤተ መጻሕፍት አለልህ:: ጠይቀኝ:: ማንበብ፣ ማገላበጥ ሳያስፈልግህ የማውቀውን ሁሉ ላጫውትህ፣ ላስተምርህ ዝግጁ ነኝ» ይለኛል::

አንድ ቀን አዘውትሮ የሚይዛትን ፌስታል ገለጥ አድርጌ «ዛሬ የሚነበብ አልያዝክም?» አልኩት።

The History of Jesus Christ የሚል መጽሐፍ ግንጣይ ከፌስታሉ አውጥቶ አሳየኝ «የተቀረውስ?» አልኩት።

«መጽሐፉ በጣም ትልቅ ነው። ያንን በዚህ ፌስታል ውስጥ ይዤ በየሔድኩበት ላነበው ሞከርኩ። ክብደቱን አልቻልኩትም። ስለዚህ በየቀኑ የማነበውን ያህል እየገነጠልኩ ይዤ እሄዳለሁ። ሸክሙም ቀለል አለልኝ። አሁን ልጨርሰው ጥቂት ነው የቀረኝ። አንብቤ እንዳጠናቀቅኩት ማተሚያ ቤት የሚሠራ አንድ ወዳጄ አለ፤ ለእርሱ እሰጠውና እንደገና ይጠርዝልኛል።»

የብር ፌስታል ከእጁ አይጠፋም፤ ይህም በርሳው መሆኑ ነው፤ በፌስታሉ ውስጥ ማስታወሻ ደብተር፣ ጅምር ጽሑፎች፣ አንድ መጽሐፍ ይይዝበታል፤ በማስታወሻው ብዙ ጊዜ በእንግሊዝኛ ሲጽፍ በአማርኛም የሚከትብበት ጊዜ አለ፤ ይህ መጽሐፍ እየተፃፈ እያለ የእፎይታ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ፌስታሉን፣ በአነስተኛ የጉዞ ቦርሣ ተክቶለታል፤ ብዙም ሳይቆይ እሷንም በቆንጆ የቆዳ ቦርሳ ለወጡለት፤

ጋሼን ምንጊዜም የማየው ንባብ ጀምሬው እንዳልጨረስኩት እንደ ሚያጓጓኝ መጽሐፍ ነው። ሁሌም ተገናኝተን ስንለያይ እንደጓጓሁ ነው። ባገኘሁት ቁጥር አዲስ ነገር ሳይነግረኝ አይቀርም።

ይህንን ሲያደርግ እኔን ለማስደነቅ ፈልጎ አይደለም። በአጋጣሚ በዕለቱ የምንወያይበት ርዕሰ ጉዳይ የሚፈጥረው ነው። ይህንን ታላቅ የዕውቀት ክምችቱን ያዳበረበት ጥበብ ማንበብ፣ ማንበብ አሁንም ማንበብ ነው።

ጋሼ መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን ሰዎችንም ያነባል። ይህ ሕሊናው በመጻሕፍት ጥበብ የደረጀ ሰው፤ የዚያኑ ያህል የማያውቃቸው ርዕሰ ጉዳዮችም አሉ። በዚህ ወቅት፣ እዚያው በዚያው «በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ምንም የማውቀው ነገር የለም። እስኪ አንተ የምታውቀውን ያህል አጫውተኝ?» ይልና የሠራ አካላቱ ጆሮ ይሆናል። በሕሊናው የተጠራቀመው የዕውቀቱ ክምችት በማንበብ ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ጋር በመወያየት በመማርም ጭምር ነው። ጋሼ ስብሐት ይጽፋቸው የነበሩትን ሥራዎቹን ማንበብ ምንጩ መጽሐፍት ብቻ ሳይሆኑ ሰዎችም እንደነበሩ አስታውሳለሁ፤ በተለይ ብላታ ዴሬሳ አመንቴና አቶ ሥዩም ስብሐት፣ እትዬ በሰሙ ኃይሌና አባ ኪዳነማርያም... ከምንጮቹ የሚጠቀሱ ናቸው፤

@Amharicbookstore



«አንዳንዴ የምነግርህ ብቻህን ስትሆን የምታብሰለስላት ነች። አንዷ ይችትልሀ። ይህችን ልብ በል፣ በሻህን-ሻህ (የኢራን ንጉሥ) ጊዜ የተነገረች ነች። ንጉሡ ቀርሱን በልቶ እንደጨረሰ፣ ገበታው ከፍ ይላል። ይህንን ጊዜ ይህችን ቃል ለመናገር ዕድሜው የሚፈቅድለት አንድ ሰው ይመጣል። ለምሳሌ አንተ ንጉሥ ብትሆን ለእንዳንተ ዓይነቱ ወጣት በእኔ ዕድሜ ውስጥ ያለ ነው የሚመረጥልህ። ብዙ ጊዜ ከሥጋ ዘመዶቹ አጎቱ ወይም ያስተማረው መምህር ይህንን መልዕክት እንዲያስተላልፍለት የሚመረጠው። ዓለምን የሚገዛው ምንጊዜም አደጋ ላይ ነው። ንጉሥ ስለሆነም ሰውን እንደ ቅንጫ ሊቆጥር ይችላል። ይህንን አደጋ ለመከላከል ያ የተመረጠ ቀስቃሽ መጥቶ በረጅሙ ዘንግ ኳ! ኳ! ያደርጋል ወለሉን። ንጉሡ ቀና ብሎ ነቅቶ ጆሮውን ይከፍታል።

ቀስቃሹም «ሟች መሆንህን አትርሳ!» ብሎት ይወጣል።

«ለምን ማለት ጥሩ ነው። ግዝ ነዋ። ይህ ሰውዬ እኮ ሰው ሆኖ እንጂ ያለው ሥልጣን ያምላክን ያህል ነው። አንቂው ወይም ቀስቃሹ ደግሞ ከአምላክ ሥልጣን ተሰጠህ እንጂ ሰው ነህ ሲለው ነው። ሰው መሆንህን አትርሳ። ስትለው ሰው ፈራሽ መሆኑን ያስታውሳል። አንተ ስትሆን ብቸኛ ስለሆንክ በስድስት ወር አንዴ ቢነግርህ ይበቃሃል። ንጉሡ ግን በቀን በቀን ያስፈልገዋል። አየህ፣ በመስጠት ሳይሆን በሞትና በሕይወት ፍርድ ላይ እየው። ንጉሥ መልክህን አይቶት ብታስጠላው በጥቅሻ ብቻ ይገላግልሃል። ይህንን ፈተና እንዳያልፍ አንቂው ይጠቅመዋል፤ እልሃለሁ። አንተም ፈራሽ መሆንህን አትርሳ... እኔም ጭምር... »

«እኛም ሟች ነን። ከመሞታችን በፊት ግን ሟች አምላክ እንሁን፣ ሞትን እንቅደመው» ይልና ከመጣፍም ከሊቅ አፍም ባከማቸው ዕውቀት ይዞኝ እልም ይላል።

በውስጤ አባባሉን እያብሰለሰልኩ ለሁለታችንም ሻይ ቀዳሁ። ጀንበር ከጠለቀች ሻይም ቡናም መጠጣት አይፈልግም። አሁን ግን ጊዜ ስለሆነ ግብዣዬን ተቀበሉኛል።

ሩሲያዊው ደራሲ ማክሲም ጎርኪ ሲናገር «አንድ ሰው መኖርን ካወቀበት ሁሉም ይጠላዋል፡ ይመቀኘዋል፡ ካላወቀበት ሁሉም ይንቀዋል» ይላል። ጋሼ ሰዎች ሲኮንኑት መኖርን አሳወቀበትም በሚል ስሜት ነው። እርሱ ደግሞ እነርሱን እርሳቸው ነው የሚለኝ።

ጀምበር ስታዘቀዝቅ ወደ ሰፈሩ ለመሄድ እየተነሳ «ሆ! በጣም ቆንጆ ቀን አሳለፍን። አማልክቱ ያለምክንያት አይፈጥሩህም። ሲፈጥሩህም፣ ሲያሳውቁህም ምክንያት አላቸው። ያሳወቁህን ሁሉ ለተተኪው ትውልድ እንድትዘራ ያደርጉሃል። ልጄ አማልክቱ ምንም የሚያባክኑት ነገር የለም። በአገር ቤት ገበሬዎች በሬዎችኝ ለርሻ ሲጠምዱ ያረጀውን በሬ፣ ከወይፈን ጋር ነው የሚጠምዱት። ወይፈኑ ሁሉንም ተምሮ ከአረጀው በሬ

ይማራል። እኔና አንተን ማን እንደጠመደን አላውቅም። ሳይሀ፣ ስስማህ ደስ አልከኝ። አብረን መጓዝን ፈቀድኩ። የት እንደምንደርስ ከወዲሁ መተንበይ አልችልም። ሕይወት ግን ቀንበሯን አኑራብን እነሆ እያረስን ነው» ይላል።

ከዚህ መምህር፣ ደራሲና አርታኢ ከሆነው ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ጋር ሕይወት ያስተዋወቀችን በርቀት ነው። እኔ መርከበኛ ሆኜ በቀይ ባሕር ላይ ስቀዝፍ እሱ ደግሞ በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ውስጥ አርታኢ ሆኖ ይሠራል።

ሕይወት ተጽፎ የተጠናቀቀውን የዕውን ዓለም ምዕራፍ ገለጠች፤ ገጸ ባሕሪዎችዋ ስንተውን ከአንድ ወጣት መምህር ጋር አገጣጠመችኝ፤ ከከባችን ገጠመ፤ እኔ ደቀ መዝሙሩ፣ ወጣቱ መምህሬ ሆነ፤ በ1980 ዓ.ም አሥመራ ከተማ በሚገኘው የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ቴክኒክ ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል ለትምህርት ገብቼ ነበር፤ ወጣቱ መምህር ሰይፈ ሠማ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን ተቀብሏል፤ የመመረቂያ ጽሑፉን በስብሐት አጫጭር ልቦለዶች ላይ ነው የሠራው፤

ከፍተኛ የሆነ የስብሐት ሥራዎች ተፅዕኖ ነበረበት፤ ይህንን ተፅዕኖ በመርከበኞች ተማሪዎቹ ላይ አጋባብን፤ ስብሐት የዘወትር መዝሙራችን ሆነ፤ መምህሬ አንዳንዴ በራሱ ላይ እየነቃ በሰጠን ኮርስ ላይ የሌሎች ደራሲያን ሥራ ቀላቅሎ አስተምሮናል፤ በወቅቱ የጋሼ ስብሐትን አጫጭር ልቦለዶች በሙሉ በክፍል ውስጥ ስላነበብናቸው ውስጣችን ገዝፏል፤

ወቅቶች ተለዋወጡ፤ የነበረው እንዳልነበረ ሆነ፤ በዚህ ወቅት እኔ አዲስ አበባ መጥቼ የሕይወቴን ሌላ ምዕራፍ በትውልድ ሰፈሬ ቂርቆስ ጀምሬያለሁ፤

አንድ ቀን ምሽት ሬድዮ አደምጣለሁ፤ የኪነጥበባት ምሽት ነው፤ ስብሐት በዚያ ወፍራም ድምጹ ዝግ ብሎ 'ፈርኦን ሲሶ ዝና' ሲል ርዕስ የሰጣትን አጭር ልቦለዱን ያነባል፤ በየመሐሉ ያዝ ሲያደርገው ከራሱም ያክልበታል፤ ይስቃል፤ አንብቦ እንደጨረሰ ጋዜጠኛዋ ሰሎሜ ደስታ ጋሼን ስለ ሕይወቱ ጉዳይ ታነጋግረው ጀመር፤ በወቅቱ ተደስቼ ማዳመጤን አስታውሳለሁ፤...

ከዕለታት በአንዱ ቀን በወርሐ ሰኔ 1985 ዓ.ም ከደራሲና ጋዜጠኛ ተስፋዬ ገብረአብ ጋር ተዋወቅን፤ ያስተዋወቀን የጋራ ወዳጃችን ደራሲ መስፍን ሀብተማርያም ነው፤ በጨዋታችን መሐል «ሥራ አለህ?» አለኝ ተስፋዬ፤ እንደሌለኝ ነገርኩት፤ የፕሬስ ድርጅት

@Amharicbookstore



አባል እንድሆን ጋበዘኝ፤ ተስማማሁ፤ በወቅቱ እሱ የዚህ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ነበር፤

የኔ ሕይወት ምዕራፍ አካሔድ ከዚያን ዕለት አንስቶ ተቀየረና ከባሕር ወጥቼ የብስ ላይ ጉብ አልኩኝ፤ መርከበኝነትን ለዘለዓለሙ ተሰናብቼ የጋዜጠኞች ቡድን አባል ሆንኩ፤

በዚህ አጋጣሚ ነው የዚህ ድርሳን ባለታሪክ ከሆነው ሰው ጋር በአካል የተዋወቅነው፤ ማንም አጨባብጦ አላስተዋወቀንም፤ አብሮ መሥራቱ፣ በአንድ ቤተ መጻሕፍት አብሮ ማንበቡ፣ ቡና መገባበዙ አቀራረበን፤ ቆይቶም ምሣ አብረን መብላት ጀመርን፤ አብሮ መዋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ እኔ ቤት ማደርንም መብታችን አደረግነው፤

ኮከባችን ገጠመ፤ በጣም ጥሩ ሕሊናዊ ጥምረት በመካከላችን ተፈጠረ፤ ከርሱ መማር እንደምፈልግ ገባው፤ ፈቃደኝነቱን ሲያወጋኝ 'በል 'One man university' እንመስርት፤ 'When the student is ready the master arrives' አለኝ፤ ለሁለታችንም የሚመቸን ቀን ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ሆነ፤ ለመወያየቻን 'ዙሉ ካስል' ስል የሰየምኳትን ቤቴን በማዕከልነት መረጥን፤ ይች መጠለያ ከቤት ዝቅ፣ ከማዕድ ቤት ከፍ ያለች ነች፤ ታላቁን እንግዳዬን ለማስተናገድ ተዘገጃጀች፤ በወቅቱ ወንደላጤ ስለነበርኩ ለምሣ የሚያስፈልገንን ምግብ ዓርብ ማታ እቀቅላለሁ፤ ቅዳሜ ስባት ሰዓት ቤት እንደርሳለን፤ ጋሼ አልጋ ላይ ጋደም ሲል እኔ ሱሩ (የጋሼ ማቢያ) ለማሞቅ ጉድ ጉድ እላለሁ፤

በመርከበኝነት ሕይወት ያተረፍኩት አንድ ማለፊያ ነገር ራስን መርዳት ነው፤ የማበስለውን ማፍጠት ይመገባል፤ እጃችን ከረጠበ አትክልትና ፍራፍሬ ይታከልበታል፤ ለበርካታ ጊዜያት ጊዜ ቆጥበን ወደ ውይይታችን እንድንገባ የማዘጋጀው ምግብ የእንቁላል ስልስ፣ አልያም የሥጋ ጥብስ ነው፤ ጋሼ ስብሐት ሥጋ አይወድም፤ የዕንቁላል ስልሷን ግን ማፍጠት ይመገባል፤ ስልሱ የቀረበበትን ድስት ሲጠርጋት የመዒጠጥ ያክል ነው፤ በዚህ ጊዜ "እረ ድስቴን እንዳትሸነቁርብኝ" እለውና እንሳሳቃለን፤

ከመሥሪያ ቤታችን ወደ ቂርቆስ ስንጓዝ "ዛሬ ምሣ እንቁላል ስልስ ነው?" ይለኛል፤

"አዎን!" ስለው የአስር ማንቲም ቃሪያ ገዝቶ በኪሱ ይይዛል፤ አሁን ይህን መጻፍ ስጀምር "እንቁላል ስልስ ሳዘጋጅ ቃሪያ መግዛቱን ለምን ዘነጋሁ?" ስል ራሴን እጠይቃለሁ፤ ይህንን ስህ ተቴን ሳላርም ትዳር መሰረትኩና ከመጥቤትነት ተሻርኩ፤

በግል ባሕሪያችንም በጣም ተቀራርበናል፤ አንዳችን የአንዳችንን ምስ አማምረን እናውቃለን፤ ማጣት ኪሳችንን ሲፈታትሸው "ስንት ይዘሃል?" ተባብለን ለውይይታችን መድመቅ የየበኩላችንን

እናዋጣለን፡፡ ለትራንስፖርትም ሆነ ለጥቃቅን ወጪዎቻችን ገንዘብ እንለጋገሣለን፡፡

በጨዋታ ላይ ብዙውን ጊዜ አድማጭ ነው፡፡ ማውራት የሚጀምረው ጥቂት አልኮል ከተጎነጨ ነው፡፡ በዚያ ሰዓትም ቢሆን ተራውን ጠብቆ ማውጋቱን አሣምሮ ተክኖታል፡፡ የማይጥመው ጨዋታ ከገጠመው "ርዕስ ለውጥ" እስከማለት ይደርሳል፡፡

ከምሣ በኋላ ምን እንደሚፈልግ አሣምሬ አውቃለሁ፡፡ ከመጠጥ ካቲካላ ይመርጣል፡፡ ስምንት ሰዓት ላይ አንዷን ቡትሌ መቀምቀም ከጀመረ ጀንበር ሲያዘቀዝቅ ያጠናቅቃታል፡፡

ሲጠጣ ከመለኪያው ላይ አንዴ ፉት ይልና ውሃ በላዩ ላይ ይጎነበጭታል፡፡ ይህንን ለምን ማድረግ እንዳስፈለገው ጠይቄው፣ "መስከሩን እንጂ ነገ ራስ ምታቱን አልፈልገውም፡፡ ስለዚህ ውሃው እያካለሰ ለካሬጋ ያደርሰኛል፤ ለነገም ከራስ ምታት ይከላከልልኛል" ብሎኛል፡፡ አልኮል መጠጣት በጣም ይጠላል፡፡ መስከር ግን ይወዳል፡፡ በሕይወቱ አንዴ ተጎንጭቶት የጣመው መጠጥ ሻምፓኝ ነው፡፡ ያቺም ከሐና ይልማ ጋር በሕግ ሀብትሽ በሀብቴ ተባብለው የተጋቡ ዕለት የተጎነጨት እንደሆነች አውግቶኛል፡፡

ጋሼ ስብሐት በእርጅና ላይ ሲቀልድ አንድ አሜሪካዊ ያጫወተውን ነገረኝ፡፡ "መጀመሪያ ስም ትረሣለህ፡፡ ከዚያ መልክ፣ በመቀጠል ዚፕ መዝጋት፣ ሲለይልህ ዚፕ መክፈቱንም ትተውዋለህ፡፡"

በአሁኑ ሰዓት ጋሼ ስብሐት መልክና ስም ይዘነጋል፡፡ አንድ ቀን "በአባትህ ዘነበ ለማንም እንዳትነግርብኝ ይህ የቢሮ ደባልህ ስሙ ማነው?" ብሎኝ ነግሬዋለሁ፡፡ በመርሣት የሚወዳደረው ያለ አይመስለኝም፡፡ የዚያኑ ያህል በፍፁም የማይረሣቸው ርዕሰ ጉዳዮች አሉት፡፡ እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ትዝ እንዲሉት ሌላ ሊከረከረው የሚችል ጉዳይ መፈጠር አለበት፡፡ በፍጹም የማይረሣው ቀልዶችን ነው፡፡ አንድ ቀልድ ሲያጫውተኝ ማን እንዳወራለት፣ የት እንዳወራው አውግቶኝ ነው ወደ ቀልዱ የሚገባው፡፡ በነዚህ ጊዜያት በኔና በጓደኞቼ መካከል የሚቀርና አስፈላጊም ከሆነ በአደባባይ ከወዳጆቻችን ጋር የምንቋደሳቸውን ቀልዶች አጫውቶኛል፡፡

ቀልድ መስማት ደስ ይለዋል፡፡ በሌላ ቀን ቀልድ የነገረው ሰው አጠገቡ ካለና የመጨዋወቻ ጊዜ ከሆነ "እባክህን ያችን ቀልድ ለእነሱም አውጋቸው" ሲል ይጋብዛል፡፡

ጋሼ ስብሐት ቀልዶ ማሳቅ፣ ተቀልዶለት መሳቅ ብቻ ሣይሆን ቀልደውበትም ይስቃል፡፡ አንድ ቀን በሱ ላይ የተቀለደ ቀልድ

@Amharicbookstore



ከዕለታት አንድ ቀን ጋሼ ስብሐት በከተማ አቶብስ ይጓዛል፡፡ አንድ ሌባ ጠጋ አለና ኪሱ ገባ፡፡ ጋሼ ስብሐት ቀድሞ ነቅቶ ኖሮ "ምነው?" አለው፡፡ ሌባውም ደንገጥ ብሎ "ውይ! የእኔ ኪስ መስሎኝ ነው!" ሲል መለሰለት፡፡

ጋሼ ስብሐት የሚወርድበት ፌርማታ አካባቢ ሲደርስ እየተራመደ ሌባውን በጥፊ ጭው! አደረገው፡፡ "ሌባውም ምነው?" ሲለው "ውይ የኔ ፊት መስሎኝ ነው" አለው፡፡

ይህንን ስነግረው ሣቀና«ቢቃ በሕይወት እያለሁ ተረት ልሆን ነው?» አለ፡፡ መሰሎት እንጂ ሕይወቱ ተረት ከመሆን አላመለጠችም፡፡ በርካታ አድናቂ ወጣቶች አሉት፡፡ ግጥም ገጥመውለታል፣ ቅኔም ተቀኝተውለታል፣ ተቀኝተውበታልም፡፡ ሸራ ወጥረው በብሩሾቻቸው ምትሀት የሕይወቱን ገፅ ስለውታል፡፡ ይህ ሁሉ ጉዞው ወዴት ይሆን...?

ለአንዳንድ 'ድንበር ዘለል' ተቆርቋሪዎች እንደበቱ ፈጣን መልስን ያውቅበታል፡፡ አንድ ጊዜ ከአንድ ወጣት ጋር ሲጨዋወቱ «ጋሼ ስብሐት እንእገሌ እኮ ታዋቂ ደራሲ የሆኑት ባንተ Idea ነው» ሲለው፡፡

«አንተ የምትለው ደራሲ ሁሉንም Idea ካልወሰደ እስኪ አንተ የተቀሩትን ውሰድና እንደርሱ ድንቅ ደራሲ ሁን» ብሎታል፡፡

አንድ ወጣት ጋዜጠኛ ሊያነጋግረው ወደሚኖርበት አካባቢ ዘለቀ፡፡ በቃለ ምልልሳቸው ወቅት ወጣቱ ጥያቄውን ያነሣና ማድመጡን ዘነጋው፣ ጋሼ ስብሐት መመለስ ሲጀምር ወጣቱ ከአፉ ነጥቆ ይጨርስበታል፡፡ ይኼኔ ጋሼ ተገነዘበና «ሻይ ትፈልጋለህ?» አለው፡፡ ወጣቱ ግብዣውን ተቀበለው፡፡

ጋሼ ስብሐት ተነሣና የሻይ ማንቆርቆሪያና ብርጭቆ ይዞ መጣ፡፡ መቅዳት ጀመረ፡፡ ሻዩ ብርጭቆውን ሞልቶ ጠረጴዛ ላይ መፍሰስ ጀመረ፡፡ ወጣቱ ይህንን አይቶ «ኧረ ጋሼ ሻዩ ፈሰሰ» አለ፡፡

«አንተም እንደዚህ ሻይ ነህ፡፡ በምትጠይቀኝ መረጃ ታጭቀሃል፡፡ ለምን እኔን ታደርቀኛለህ?» ሲል ገስጾታል፣ ብሎ አንድ ጓደኛዬ አውግቶኝ፣ ጋሼን አድርጎት እንደሆን ጠየቅሁት፡፡ «እንደመሰለኝ ሻይ እስከማፍላት በብርጭቆ ቀድቶ እስከማፍሰስ አልሄድም፡፡ ተረቱን ግን ሳልነግረው አልቀረሁም» ብሎኛል፡፡

ቀጠሮ አክባሪ ነው፡፡ ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመው በቀር ማንንም ቀጥሮ አያቀርም፡፡ ለበርካታ ጊዜያት አያሌ ሰዎች ቀጥረውት እንደቀሩበት አጫውቶኛል፡፡ በቀጠሮ ረገድ በተለይም የአዲሱን ትውልድ አባሎች ያማርራቸዋል፡፡

በተቀጠረበት ቦታ ቀድሞ ይገኛል፡፡ ወዳጆቹን ሲጠብቅ እያነበበ ነው፡፡ ከለቅሶ ቤት በቀር የትም ቦታ ለእርሱ ማለፊያ የማንበቢያ ሥፍራ ነው፡፡

ባሕሪው አይከብድም፡፡ ሸበት የወረረውን ገፁን ያየ ይፈራዋል፡፡ ውሎ ሲያድር ማንንም በቀላሉ በፍቅር የማጥመድ ኃይል ተፈጥሮ ለግሳዋለች፡፡ የማንንም ሰው የሕሊና ነፃነት ያከብራል፡፡ የማንንም አስተያየት ለመንቀፍ አይቸኩልም፡፡ አንደበቱ ቁጥብና ዝምተኛ ነው፡፡ አንድ ቀን ጥሩ አድማጭነቱን ሳወጋው እንዲህ አለኝ፡፡ «አዎን፣ እግዜር በጻፈው ቴአትር ውስጥ እኔ ማየትና ጆሮ በመሆን ማድመጥ ደስ ይለኛል፡፡ ብዙውን አፍ መሆን ነው የሚፈልገው፡፡»

በጨዋታ መሐል፣ ክርክር ተነስቶ ሲሟሟቅ የሚያምንበት ጉዳይ ከሆነ ይሳተፋል፡፡ በሕይወቱ አምርሮ የሚጠላው ምክር ነው፡፡ ማንንም ሲመክር አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ ምከረኝ ባይ ከመጣ "እሺ! ካስፈለገ" ይልና ያመነበትን እውነት ይተነፍሳል፡፡

ሐና ይልማ በሕይወቱ ምዕራፍ ውስጥ ከተከሰተች በኋላ ጋሼ ስብሐት ሽቅርቅር እንደነበር በቅርብ የሚያውቁት ሁሉ አውግተውኛል፡፡ ለርሱም በዚያን ወቅት ስለነበረው አለባበስ አንድ ጊዜ አንስቼበት "እኔ ዘነጥኩ አልዘነጥኩ ግድ የለኝም፡፡ እሷ ግን ዘናጭ እንድትሆን እፈልጋለሁ" አለችኝ፡፡ "እሺ፣ እየገዛሽ አምጪልኝ፣ እለብሳለሁ አልኳት፡፡" ቀደም ብሎ የሚያውቁት ሰዎች ያንን ጊዜ ያስታውሱታል፡፡

አሁንም ብስክሌት መጋለብ ይችላል፡፡ መኪና መንዳት ግን አይችልም፡፡ አንዴ መንጃ ፈቃድ ለማውጣት አንድ ጓደኛው እያለማመደው አዋሳ ድረስ ነዱ፡፡ አርፈው፣ ለስላሳ ጠጥተው ልምምዱን ለመቀጠል ካረፉበት ሆቴል መኪናውን አስነስቶ ሲወጣ ከበሩ ጋር ተጋጨ፡፡ ክፉኛ ደነገጠ፡፡ ልምምዱም በዚሁ ቆመ፡፡ «ለምን?» ብዬው «ሾፌር እንደሆን ሐና አለችልኝ» ሲል መልሶልኛል፡፡

ባንክ ገንዘብ የማጠራቀም ባህሉን ጀምሯል፡፡ ከአንድም ሁለት የባንክ ደብተር ቢኖረውም፣ በሁለቱም ደብተሮቹ ውስጥ አስር፡ አስር ብር ብቻ ነው ያለው፡፡ «ይቀመጡ፣ በደንብ እየወለዱልኝ ነው» በማለት ቀልዶልኛል፡፡

@Amharicbookstore



ስለ ሁለተኛው ትዳሩ ጠይቄው እንዲህ አጫወተኝ፡፡ «አ! » ብሎ ሳቁን ለቆ «ሶቅራጥስ ፈላስፋ ነው፡፡ ሚስቱ ደግሞ ጨቅጫቃ ነች፡፡ አንዳንዴ ወይዘሮ ይሉኝታና አቶ ይሉኝታ ቢስ ይጋባሉ፡፡ ሶቅራጥስ ሲፈላሰፍ ነው የሚውለው፡፡ ትዳርዋን ለምትወድ ሴት ደግሞ ይህ ዓይነቱ አካሄድ የሚጥም ሕይወት አይደለም፡፡ የሶቅራጥስ ሚስት ሲበዛ ጨቅጫቃ ነበረች፡፡ ታዲያ ሶቅራጥስን ደቀ መዛሙርቱ ስለትዳር ጠይቀውት ሲመልስ «ትዳር መመሥረት ጥሩ ነው፡፡ ዝምተኛና ሰላማዊ ሚስት ካጋጠመችህ ደስተኛ ሕይወት ትኖራለህ፡፡ ከጨቅጫቃዋ ጋር ሕይወት ካቀረኘችህ ደግሞ ፈላስፋ ትሆናለህ» አላቸው፡፡ «እኔም ሁለተኛው ትዳሬ ፈላስፋ አድርጎኛል፡፡»

ስለማኅበራዊ ሕይወታቸው አንስቼ «አንተም ዕድር፣ ባለቤትህም የሴት ማኅበር አታጡም» ብለው «አ! ምን ነካህ? የኛ ቤት እኮ የሁለት ወንበዴ ቤት ነው» ብሎኝ እየሣቀ «ይልቅ ጎረቤት እያላዘነ ያስቸገረንን አንድ ውሻ የትምወርቅ ርቦት ነው ብላ በሊሊት ፊትታ አመጣችው፡፡ የኛ ውሻ ሆነ፤ ማላዘኑን ተወ፡፡ ስሙንም ዶጊ አሉት፡፡ ሲለዩ... የምትባል ድመትም ነበረችን፡፡ ተረት ሰፈርን ትተን ሁላችንም በየፊናችን ከተበታተንን በኋላ አንድ ቀን ከኩሻን ልጎበኝ አክስቷ ቤት ሄጄ ምን አለችኝ መሰለህ፡፡ «ዶጊን አግኝተኸው ታውቃለህ?...» ሳቀ፡፡ ሌላ ቀን ደሞ « ዶጊን ካገኘኸው ሰላም በልልኝ» አለችኝ፡፡"

ልቅሶ የመድረስ ባሕሉ የለውም፡፡ የታመመም አይጠይቅም፡፡ ከወዳጆቹ መሐል ሌላ አስታዋሽ ሰው ሊወስደው ከመጣ ግን ዘመድ ለሞተበት «እግዜር ያጽናዎትን!» የታመመንም «እግዜር ይማርዎት!» ሲል ከልቡ ነው፡፡ እግረ መንገዱን በደረሰው ለቅሶ ላይ እንዴት እንደተንቀሳቀሰ ሲያጫውተኝ «በዕድሜ አንተን ሳክል እዚህ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን ለምን እንደመጣሁ እንጃ ያካባቢው ሰው ማርገጃው ላይ ተሰብስቦ ያረግዳል፡፡ ጠጋ ብዬ ሳደምጥ ያስለቀሷ ሙሾ አወራረድ ሳበኝ፡፡ ወዲያውኑ እምባዬ መጣ፡፡ በጣም አለቀስኩ፡፡ ተንሰቀሰቅሁ፡፡ ሟቿ መሐን ነበረች፡፡»

ቂመኛ አይደለም፡፡ ከምር የጠላቸውን ሰዎች ከዓመታት በፊት አንስቶ አጫውቶኛል፡፡ ምክንያቱንም ዘርዝሮልኛል፡፡ ረጅም ጊዜ ካለፈ በኋላ ጥላቻውን ለመመዘን እነዚህኑ ሰዎች አነሳሁበት፡፡ «ሂድ እባክህ! እኔ እኮ ቂም የሚባል ችግር የለብኝም፡፡ ለጊዜው ችግሩ ያናድደኝና እናገራለሁ፡፡ ቆይቶ ግን እረሳዋለሁ፡፡ በታናሽ ወንድሜ ተወልደ ብርሃን ላይ የደረሰውን ልንገርህ፡፡ ከአሥመራ ዩኒቨርሲቲ

ተዛውሮ እዚህ እያለ በጠዋት ቢሮው ገባ፡፡ የዕለት ሥራውን ሊጀምር ሲል ከኮሪደሩ የተኩስ ድምጽ ሰማ፡፡ ተንሥቶ ወጣ፡፡ ተኳሹ ተወልደን እንዳየው አለመና ተኮሰበት፡፡ ተወልደ ሲሸሽ እናቱን መታው፡፡ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተኛ፡፡ እዚያ እያገገመ እያለ የደርግ መንግሥት የባሕል ሚኒስትር አድርጎ ሾመው፡፡ በዚያን ወቅት አንድ ጣሊያን ውስጥ ያለ ዩኒቨርሲቲ እየተመላለሰ ያስተምር ስለነበር እግረ መንገዱንም ለሕክምና ደርግን አስፈቅዶ ወደ አውሮፓ ሔደ፡፡ እሱ የባህል ሚኒስትር ሆኖ በተሾመ በወሩ እነ መለስ ደርግን አሸንፈው አዲስ አበባ ገቡ፡፡ ወደአገሩ ለመመለስ እንደሚፈልግ እዚያው ጣሊያን እያለ ይህን መንግሥት ጠየቀ፡፡ እንዲመጣ ፈቀዱለት፡፡ ተወልደን ያን የተኮሰበትን ሰውዬ በሕግ ይፈልገው እንደሆን ጠየቁት፡፡ «ተውት፣ ከእኔ ጋር ፀብ የለውም፡፡ አጋጣሚ ነው ያገናኘን» ብሎ ይቅር ለእግዜር ብሎታል፡፡

«ልብ አድርግ፡፡ የተኮሰበትን ሰውዬ ታናሽ ወንድሜ ይቅር ሲል እያየሁ እኔ ደግሞ በትንሽ ነገር የተጋጨኋቸውን እንዴት ይቅር ማለት ይሳነኛል? እርሣቸው!! » ብሎኝ «እ» አለ፡፡

“እ” ምን አልኩት፡፡ የሚያክለው ሐሳብ ሲኖረው እ! ይለኛል፡፡ ለኔም ወደሚቀጥለው ወግ መሸጋገሪያ ስለምትሆነኝ የውስጡን ማያ በማድረግ ቃልዋን እንደ ጥያቄ እጠቀምባታለሁ፡፡

“ይኸውልህ ‘ሴይለር’ ይህ ዓይነቱ ይቅር ባይነት ከዘርህም የምትወርሰው ይሆናል፡፡ ይህንን ስልህ ምክንያት አለኝ፡፡ ይኸውም ወንድ አያታችን ኅይታይ ሐለቃ ተወልደ መድሕን ገብሩ አንድ መራር ገጠመኝ አላቸው፡፡ አቦይ ተወልደ መድሕን የእናቴ አባት ናቸው፡፡ አሥመራ አጠገብ ፀረ-ማርያሞች ክርስቲያን ነን እያሉ ማርያምን መጥላት እንዴት ይሆናል? ብለው ለማጣራት ከቤታቸው በዓድዋ በኩል አድርገው ወደተባሉበት አሥመራ አካባቢ ሔዱ፡፡ ሰዎቹን አግኝተው አነጋገሯቸው፡፡ ሰዎቹም «እኛ ፀረ-ማርያም አይደለንም፡፡ እንዴት የጌታችን እናት ሆና እመቤታችንን እንፃረራለን?» አሏቸው፡፡ ነገር ግን በኛ እምነት አታማልድም ነው የምንለው፡፡ እኛ ያለአማላጅ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በቀጥታ ነው የምንገናኘው፡፡ አማላጅ አያስፈልገንም አሏቸው፡፡ ወንጌሉ የሚለውን እያስነበቡዋቸው፡፡ ሰዎቹን እምነታቸውን ሲጠይቁ ፕሮቴስታንት መሆናቸውን ነገሯቸው፡፡ አስተማሩዋቸው፡፡

ዓድዋ ላይ የመጀመሪያዋን የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱት ኅይታይ ሐለቃ ተወልደ መድሕን ናቸው፡፡ እኝህ አያቴ አንድ ልጃቸው ሴት አውል ሆነ፡፡ አንድ ምሽት የለመዳት ሴት ቤት አጥር ዘሎ ሲገባ ባለቤትየው እቤት ውስጥ ነበርና ጠመንጃውን

@Amharicbookstore



አልሞ ተኩሶ ገደለው፡፡ ገዳዩን አገሬው ይዞ ለአባትየው አቀረበላቸው፡፡ «ቢፈልጉ በዱላ፣ ቢፈልጉ በጠመንጃ፣ ቢፈልጉ በሥለት መግደል ይችላሉ» አሉዋቸው፡፡

አቦይ ተወልደ መድህን ግን ይህን አላደረጉም፡፡ ሰውዬውን ይዘውላቸው ሲቀርቡ አይተውት አዘኑ፡፡ የልጃቸውንም ጥፋተኝነት አምነዋል፡፡ ሲናገሩ፣ «እኔ ይኼን ሰውዬ በደመኝነት አልፈልገውም፡፡ ነገር ግን እዚህ እኛ ባለንበት አገር ባይኖር እመርጣለሁ፡፡ ለምን፣ እኔ ይቅር ለእግዜር ብል እንኳ ቤተዘመዶቼ ይምሩታል ብዬ አልገምትም፡፡ ስለዚህ ይህችን አገር ለቅቆ ይውጣ» አሉ፡፡ ሰውዬውም ዓድዋን ጥሎ ወጣ፡፡

የጋሼ ስብሐት ነብስ አሁንም ቆንጆን ታደንቃለች፡፡ ውብ ወጣት በታክሲ ውስጥ ካጋጠመችው፣ ወይም እግረ መንገዱን ካያት፣ ልጂቱ ሳታየው በደንብ ያስተውላታል፡፡ ይህንን ሲያደርግ በርካታ ጊዜ አይቼዋለሁ፡፡

“እንዴት ናት?” ስለው፡

“ሥጋ የለበሰን አበባ ማስተዋል ደስ አይልህም?”

ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ቢጋራ ወዳጃቸው ጥበበ ተርፋ ቤት መጅሊስ ተቀምጠው ያወጋሉ፡፡ በጨዋታው መሐል ጋሼ ስብሐት ሽንት ቤት ደርሶ ይመለሳል፡፡ እንደ መደንገጥ ብሎ ዓይኑ ፈጧል፡፡ አብረውት የተቀመጡት ይህንን አላስተዋሉም፡፡ ደራሲ መስፍን ሀብተ ማርያም ጋሼ ስብሐት እንደተመለሰ መታጠቢያ ቤት ይሔዳል፡፡ በተመለከተው ትዕይንት ደንግጧል፡፡

ጋሼ ስብሐት አጠገብ ሲቀመጥ “እ! ታዲያስ እኔ ያየሁትን ውበት አየህ?” ሲለው መስፍን ልቡን ያነበበውን ያህል ነው ማለቱን አውግቶኛል፡፡

አንዲት ወጣት ከወገቧ በላይ ራቁቷን ሆና ፀጉሯን ለመታጠብ እየተዘገጃጀች ነው፡፡ ያጎጠጎጡ ጡቶቿን ከለል ሳታደርግ መታጠቢያ ቤቱን ጠቆመችው፡፡ በፍጥነት ተጠናቅቆ ይመለሳል፡፡ በእሱ ቤት ያየውን ውበት ማንም አላየውም፡፡

ጋሼ ስብሐት ቁመቱ አንድ ሜትር ከ66 ሴንቲ ሜትር ነው፡፡ ፓስፖርቱ ላይ 1ሜትር ከ69 ሴንቲ ሜትር እንደሆነ አጫውቶኛል፡፡

“ዕድሜህ እየጨመረ ሲሔድ ቁመናህ ሰብሰብ እያለ ነው” ስለው፡

“እ!” አለኝ፡፡ ምን ታደርገዋለህ በሚል ስሜት ትከሻውን እንደ እስክስታ ወራጅ እየሰበቀ፡- ወዳጅነታችንን በ1985 ዓመተ ምሕረት ማብቂያ ግድም ስንጀምር ዕድሜው 57 ዓመት ነበር፡፡ ክብደቱ 49

ኪሎግራም ሲሆን፡ ሰባት ዓመታት ያህል አልፈው ክብደቱ 52 ኪሎግራም ደርሷል፡፡ ይህ ክብደት በሕይወቴ በጣም ከፍተኛው ጊዜ ነው፡፡

መልኩ ውብና ፀይም ነው፡፡ የወጣትነት ውበቱ ዛሬም በአዛውንትነት ገጽታው ላይ አሻራውን ትቷል፡፡ ወጣትነቱን በምልሰት ሲቃኝ ስንትና ስንት ቆንጆጂት በጉርምስናው ወቅት ነሁልለውለት ይሆን? እላለሁ፡፡ በፀባዩ ዓይናፋር በገቢውም እምብዛም ስለነበር እንደ አብዛኛው ወጣት ድንግልናውን በ21 ዓመቱ ለሴተኛ አዳሪ ነው ያስረከበው፡፡ ጢም ማብቀል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ረዛም ነው፡፡ ጢሙም አሁን ከጥቁረቱ ንጣቱ ያይላል፡፡

ፀጉር አስተካካይ ቤት ሄዶ አያስተካክልም፡፡ ይፈራል፡፡ "ለምን?" ብዬው «እኔ እንጃ፣ ከዚያ ስወጣ አናቴ የሚቆሳስል ይመስለኛል፣ ቆረቆር፣ ቋቁቻ፣ ምናምን ቢያመኝስ?» ሲል ስጋቱን አጫውቶኛል፡፡

ቀደም ብሎ ሐና እንዲሁ ሥራዋ የፀጉሩን ውበት መጠበቅ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እፍቃሪዎቼ ያስተካክሉለታል፡፡ የዛሬዎቼ እንደ ፍቅራቸው የማስተካከሉ ጥበብ ስለማይሰምርላቸው ሲመደምዱት ምን ጊዜም ገመምተኛ ይመስላል፡፡ አናቱም እንደ ነብር ገላ ይዥጎረጎራል፡፡ ሰውዬው ግን ምንም ቢመስል ደንታ የለውም፡፡

በአሁኑ በአዛውንት ዕድሜው በሁለት ነገሮች ብዙም አይጨነቅም፡፡ እሱም ገንዘብና ልብስ ናቸው፡፡ ከተገኘ ንጹሕ ቢለብስ ይደሰታል፡፡ ከጠፋ ባይፈልውም ቢሆን አካሉን ይሸፍናል፡፡ ይህንን እምነቱን 'ኮተት' በሚል ርዕስ በጻፈው አጭር ልቦለድ ውስጥ አንፀባርቆታል፡፡

ከኔ ጋር ስንተዋወቅ ከሁለት አቅጣጫ የገንዘብ ምንጭ ነበረው፡፡ በአዲስ ዘመን እና ሔራልድ ጋዜጦች ላይ በሚጽፋቸው ወጎች 800 ብር ይከፈለዋል፡፡ ከማኅበራዊ ዋስትናም የጡረታ አበሉ 380 ብር ነው፡፡ በወር ከ1000 ብር በላይ ቢያገኝም ገንዘብ በቅቶት አያውቅም፡፡ "ጋሼ ስለ ገንዘብ አጠቃቀምህ ብትገልጽልኝ?" አልኩት በአንድ ወቅት፡፡ "ደሞዜን እንደ ተቀበልኩ ዱቤዎች አሉ፡፡ የመጠጥና የምግብ ቤት ዕዳ፡፡ ይህ እንደ ጉድጓድ ነው፡፡ ለቤተሰቤ የማገኘው እስካሁን ይበቃል፡፡ የወደፊቱን እንጃ እንጃ እንዲህ ነው የምሔደው፡፡ ልጅ ሆኜ ርበኝ ስለማውቅ በኔ እምነት የመጀመሪያው ጥያቄ ሆድ ነው፡፡ ተረት ሰፈር ነው የምኖረው፡፡ ካለኝ ፉጃጋን እያየሁት ላልፈው አልችልም፡፡ ሲርበው እሰጠዋለሁ፡፡ ከኔ የባሰበት ካለ አላልፈ ውም፡፡ አንዲት ሚስኪን አለች፡፡ የተራበች፡፡ ሥርታ መመለስ የማትችል፡፡ የኔን ልጅ ዋሱን ያመው ስለነበር ማዘር ቴሬዛ ሊያሳድጉት ወስደውታል፡፡ እኔም ለዚህች ሴትዮ በወር 20 ብር ልሰጣት ወሰንኩ፡፡ መንገድ እየሄድን ነው፡፡ መአት ሲኦል ውስጥ

@Amharicbookstore



ነው ያለነው፡፡ ሁሉንም ማገዝ አትችልም፡፡ ይሁን እንጂ ያንን ሁሉ ለማኝ ይህ ከተማ እየጠበቀ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብ ባይኖር እኛ እንኖርም ነበር ሲል አንድ ለማኝ ሰምቼዋለሁ እልሃለሁ፡፡ እኔም የዚያ ሲኦል አካል ነኝ፡፡ ስለዚህ የሙሴን ሕግ እናከብራለን፡፡..."

በዚህ የገንዘብ አጠቃቀሙ ብዙም ዘና ሳይል በዕለታት ዕድሜ ውስጥ ወደ ማጣት ይመለሳል፡፡ ከወዳጆቻችን መካከል አንዱን ካገኘ ለዛሬ የምትበቃውን ገንዘብ ብቻ ይጠይቃል፡፡ እኔ በተገኘሁበት ማንም የለኝም ሲለው አልሰማሁም፡፡ ከልቡ ከሚወደውና ከሚያቀርበው ሰው ካልሆነ በስተቀር በፍጹም አይጠይቅም፡፡ አጠያየቁ የከፋንም ቢሆን ያስወጣል፡፡

ከዓይኑ ስውራንና ከአካል ጉዳተኞች ላይ ሎተሪ የመግዛት ባሕሪ አለው፡፡ አንዴ ሎተሪ ሲገዛ አግኝቼው "አንተም በዚህ ታምናለህ?" አልኩት፡፡

"ሊደርስህ ይችላል፡፡ ለምን አትሞክርም፡፡ ዕድሉ ሲያጋጥመን እኛ እንነሳተፋለን፡፡ ደግሞ እኮ አባ ኪዳነ ማርያም መጣፍ ገልጠውልኝ ኮከቤን ሲቆጥሩት ሎተሪ እንድገዛ አዘውኛል" ሲለኝ፡

"እስካሁን ወጥቶልሃል?"

"አባ ግዛ አሉኝ እንጂ ይደርስሃል አላሉኝም እኮ!" ብሎኝ ወደ ቤተ መጻሕፍት ቤት ገባ፡፡

ሲራመድ ዝግ ብሎ ነው፡፡ የሚቸኩል ሰው ካጋጠመው ገለል ብሎ ያሳልፈዋል፡፡ አንዴ መንገድ ተገናኘንና «ፍጠን!» አልኩት፡፡ ገለል አለልኝና « አንተ ፍጠን እኔ ሩጫዬን ጨርሻለሁ» አለኝ፡፡

ፀሐይዋን ለመከላከል ሹራብ አናቱ ላይ ያደርጋል፡፡ ይህ ድርጊቱ የፍልስጥኤም ነፃ አውጪ ግንባር መሪ የነበረውን ያሲር አራፋትን ያስታውሰኛል፡፡ ጀንበር ስትጠልቅ ያንኑ ሹራብ ይደርበዋል፡፡ አየሩ ከቀዘቀዘው ከሱቅ የአስር ማንቲም ፌስታል ገዝቶ አናቱን ያለብ ሳል፡፡ ለምን ይህንን ማድረግ እንዳስፈለገው ጠይቄው ጥሩ ሙቀት እንደሚሰጠው አጫውቶኛል፡፡ በቅርቡ ዝንጉርጉር መለዮ ማድረግ ጀምሯል፡፡

በወጣትነቱ ወቅት እስከ ጉልምስናው የማንበቢያ መነጽር ይጠቀም ነበር፡፡ ከአንዴም ሁለት ሶስቴ በሌቦች በመመንተፉ፣ የማንበቢያ መነጽሩን መጠቀም አቆመ፡፡ አሁን በአዛውንትነት ዕድሜው የመነጽሮቹን መሰረቅ አንስቼበት «እንኳንም የወሰዷቸው! ከሸክም ነው የገላገሉኝ፡ እንጂ እጅግም መነጽር የሚያስፈልገኝ አይደለሁም፡፡»

ጋሼ ስብሐት በሕይወቱ አንድ ሦስቴ ማጅራት መቺዎች አጋጥ መውታል፡፡ ዕድለኛም ስለሆነ ኪሱን በሰላም አስመትቶ ተላልፈዋል፡፡

የጋሼ ስብሐት አባት፣ አያትና ቅድመ አያቱ ... አሥራ አራት ትውልድ ድረስ ቀሳውስት ናቸው፡፡ እሱም በልጅነቱ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ነበር፡፡ አዲስ አበባ እንደመጣ የተማረበት ትምህርት ቤት በፕሮቴስታንቶች ይመራና ይተዳደር ስለነበር ያ አጋጣሚ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በእጅጉ እንዲተዋወቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህ ታላቅ መጽሐፍ የገበየው ዕውቀት ለፈጠራ ሥራው በጥልቀት ጠቅሞታል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዕምነት ደረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚቀበላቸውም፣ የማይቀበላቸውም ምዕራፎች አሉት፡፡ እግዚአብሔር የለምም፣ አለምም አይልም፡፡ በሕይወቱ መጨረሻዎቹ ዓመታት እምነቱን እንደገና ወደ አርቶዶክስ መልሷል።

ጋሼ ስብሐትን ለዓመታት የማስተዋል ዕድል የገጠመው ሰው በአስተሳሰቡ በነፃነት አሳቢ (Free thinker) መሆኑን ይረዳል። ከማንም የሚረባውን ይወስዳል። ከፍልስፍናው፣ ከፈጠራው፣ ከማይገነሱ ... እንደ ሱፊ፣ እንደ ቡድሀ፣ እንደ ግሪክ አማልክቱ፣ እንደ እስላምና ክርስቲያን ሲኖር ይስተዋላል። በሕይወት ጉዞው ቀለል ባለ አኗኗሩ ማሀትማ ጋንዲን እንደተቀበለ ይገለጽልዎታል። ሰውዬው ግን ተከታይ ነኝም አይደለሁምም አይልም።

ለዓመታት አብሮት የኖረ ሳል አለበት፡፡ ስለዚህ አፍ ማበሻ ወረቀት ከኪሱ አይጠፋም፡፡ "ሳሉ መቼ ነው የጀመረህ?" አልኩት፡፡

"ማዳም ሁሴን፣ ከኢየቶላ ሆሚኒ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ ነው የጀመረኝ፡፡ ለነገሩ ጉንፋን አይደለም፡፡ እኔ ያኔ ጉንፋን መስሎኛል፡፡ ጠርነቱ ሲያበቃ ነው የምድነው አልኩ፡፡ ጠርነቱ አለቀ፡፡ ሳሏ ግን አልዳነችም፡፡ እስከሁንም አለች፡፡ ምንም አይደለም አሁን እንኳን ጉንፋን አይደለችም ጨዋታ ናት፡፡ አዲስ አበባ የትም ይስማማኛል፡፡ ለእኔ ነው ከተማዋ የተሠራችው፡፡ ምክንያቱም አፍንጫዬ አያሸትም።"

በሚጠጣው ባሕላዊ መድኃኒት ምክንያት ሰውነቱ ተቆጥቶ አንዳንዴ በጣም ያሳክከዋል፡፡ ይህንን ለምን እንደሚያደርግ ጠይቄው "አለርጂ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ሕመም ተራውን ሰው አይዘውም" አለና አስቆኝ "የምጠጣው መድኃኒት አለ ብዬሃለሁ፡፡ ያንን ስወስድ ነፍሴ ትደሰታለች፡፡ ግን 'አለርጂ' ሆኖብኝ ያሳክከኛል፡፡ በዚህ ምድር ላይ ሳትከፍል በብላሽ የምታገኘው ምንም ነገር የለም፡፡



አየህ፣ ምን ባላደርግ እንደማይተወኝ ባደርግ እንደሚተወኝ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ማከኩ በጣም ስለሚጥመኝ አብሬው እኖራለሁ፡፡"

"ስለ ምንም አልጨነቅም፡፡ እኔን የሚያስጨንቀኝ ልጆቹ አጠገቤ ካሉ ነው፡፡ ኩኩሻ በአምስት ዓመቷ አድጋ ጨርሳለች፡፡ ለምሳሌ መንገድ ላይ ፀጉሬን ባበጥር «ተው ነውር ነው» ትለኛለች፡፡ ዜና ግድ የላትም፡፡ ሲያስኛት ደግሞ የሚሰማትን የምትናገርበት ጊዜ አለ፡፡ ከኤልሣ ጋር ተነፋፍቀን ነው የምንገናኘው፡፡ ኢያሱ ባሕር ማዶ ነው፡፡ ሌላውን እርሳው... ለተመልካች ይደብር ይሆናል፡፡ እኔ ግን ተስማምቶኝ እየቀጠልኩ ነው፡፡"

የድርሰት ሥራውን ጠበቅ አድርጎ እንዳይዘው ኑሮ ልጓም ሆናበታለች፡፡ የሁለት ቸር (የሁለት ብኩን) ቤት ሆኖ የሁለተኛው ትዳሩ ሕይወት የገንዘብ እጥረት በጣም አለበት፡፡ በዚህም ምክንያት ጥበብን እንደ ውሽማው ነው የሚያያት፡፡ በአጠቃላይ ሕይወቱ መረጋጋትና ሰላም ስለሌላት ሰውየው ተዓምር ነው የሚያሰኝ ዓብይ ሥራ መሥራት አልቻለም፡፡

እንዳለመታደል በእኛ አገር ለደራሲያኑ ቀድሞ በመክፈል እንዲጠብቁ የማድረግ ባሕሉ የለንም፡፡ በባሕር ማዶዎቹ ይህ ባሕል ሥር የሰደደ ነው፡፡ ይህ ባሕል ሩሲያውያን ባይኖራቸው ኖሮ ምናልባት ዶስቶዬቭስኪን የሚያክል ደራሲን በጅምር ሥራው ብቻ ዓለም ባጣቸው ነበር፡፡ የዚያን ዘመን የሩሲያ አሣታሚዎች ግብ 'አክክልኝ ልክክልህ' ቢሆንም በረከቱ እኛ ድረስ ደርሷል፡፡

ጋሼ ስብሐት የመጻፍ አምሮቱን ለመወጣት በጋዜጣና መጽሔት ላይ ይጽፋል፡፡ በአንድ ወቅት ከወጣት ደራሲያን ጋር ሲወያይ፣ አንዱ ተነሣና «ለእኛ ለወጣቶች ምን የሰጠኸን ዕውቀት አለ?» ሲል ጠየቀው፡፡

ጋሼ ስብሐትም "ለወጣት ደራሲያን አስጠርጌ የማቀብላቸውን ዕውቀት ድህነቱ አገደው፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ሁለት ዓመታት እግረ መንገድ በሚባለው ዓምዴ ላይ የማውቀውን ሁሉ እየጣፍኩ ላቀብላቸው እየሞከርኩ ነው፡፡ በግድ ይጠረዝ ካልተባለ ከዚያ በርካታ ቁምነገሮችን መገበየት ትችላለህ" ብሎታል፡፡

...ቀደም ባሉት ዓመታት የካቲት፣ መነን፣ አዲስ ሪፖርተርና፣ ቁምነገር መጽሔቶች ላይ በፈጠራውም በኢ-ልቦለዱም ተጠቧል፡፡ በቅርቡ በእንግሊዘኛው The Sun በአማርኛው ምዕራፍ ጋዜጣ ላይ ይጽፍ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እፎይታ ጋዜጣና መጽሔት ላይ እየጻፈ ነው፡፡ በመቀጠል አዲስ አድማስ፣ ኔሽን ...ጋዜጦች ላይ አያሌ ሃሳቦችን

@Amharicbookstore

ዘርቷል። የሕይወቱን መጨረሻ ጽሑፎች የጻፈው አዲስ አድማስ ላይ ነበር።

አንድ ቀን ይህች አገር በልማቱ መስክ ደርጅታ የሚነበብ ነገር ልጆችዋ ቢፈልጉ ደራሲ ሰብሐት ገብረ እግዚአብሔር በሕትመት ልማናት ላይ የዘራቸው የጥበብ ሥራዎቹ ከየጋዜጠቹና መጽሔቶች ላይ አፏራውን እያራገፍን መሰብሰብ ያስፈልገን ይሆናል። በአማርኛም በእንግሊዘኛም ለሕትመት ይበቃሉ፤ እርሱም በስሙም በተግባሩም ተረት ከመሆን ድኖ ሕያው ባሕሪ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

በባሕር ማዶዎቹ በየጋዜጣውና በመጽሔቱ ላይ የተጻፉትን ሥራዎች ሰብስቦ ለኅትመት ማብቃት የተለመደ ባሕል ነው። ማርክ ትወይንን፣ ቻርልስ ዲክንስን፣ ፡ አልቤር ካሙን ለአብነት መጥቀስ እንችላለን።

ጋሼ ሲናገር «አማልክቶቼ ለእኔ ያደላሉ። ዕድለኛ ነኝ» ይላል። አባባሉ በብዙ መልኩ እውነትነት አለው። አንዷን ልጥቀስ። ቀደም ብዬ እንዳልኩት እርሱ መዝሬት ነው ተግባሩ። አድናቂዎቹና ወዳጆቹ አሰባስበውለት 'ጺያፉን' አለዝበውም ሆነ እሱ ራሱ እንደወረደ የጻፈውን ለሕትመት በቅቶለታል። ይህንንም በሕይወት ቆሞ ለማየት በቅቷል።

በተከታዩ ሰኞ ዕለት በቀጠሮ ስንገናኝ ጋሼ ሰብሐት ዘንጧል። ቡና ዓይነት ቆዳ ጃኬት፤ ኮሌታ የሌለው ሸሚዝ፤ ከፋይ ሱሪና ቡና ዓይነት ጫማ ተጫምቷል። እሱ፣ እኔ እና ባለቤቴ ዐሐይ ሆነን ፕሬስ ክበብ ሻይ ጋብዞን እየጠጣን "ጋሼ ፋሽን መከተል ጀመርክ እንዴ?" አልኩት።

"እ! እ! እርሱ ተከተለን እንጂ እኛስ አንከተለውም" አለኝ።

"እዚህ ውስጥ ብቻህን አትፈራም?" አልኩት ሰፊ ከፋይ ሱሪውን እያሳየሁት።

"ማን? እኔ ወንዱ!" አለና ሳቁን ለቀቀው።

ጋሼ ሲናገር «ሀሊናና ሆድ አያረጅም» ይላል። እውነቱን ነው። በርግጥም ራሱን ጋሼ ሰብሐትን ሳየው ቆዳውም ፀጉሩም አረጀ እንጂ ሰውዬው ሰብሐት ነፍሱ ምንጊዜም ወጣት ነች። ከማንኛውም አዛውንት በላቀ ሁኔታ የወጣቶችን ሕይወት በጥሩ ሁኔታ ይረዳል።

@Amharicbookstore



በመንገድ ላይ ሲጓዝ ከወጣት ጓደኞቹ ጋር ከሆነ የመንገዱን ግራ ይዞ፣ በስተቀኝ በኩል የሚጓዘው እሱ ነው። ከእኔም ጋር ከዕለት ውሎዎችን ስንመለስ በመኪናዎቹ መተላለፊያ ላይ የሚራመደው እርሱ ነበር። "በዚህ ዕድሜህ አንድ ጎልስዋገን ብትገዛ ጥሩ ነበር" አልኩት።

"አልፈልግም" አለኝ።

"ለምን?"

"ማሽን ከሕዝብህ ያለያይሃል።"

የጋሼ ሰብሐት የዘር ሐረግ ከትግሬው ሦስት አራተኛ ሲሆን፣ በእናቱ እናት በኩል ሩብ የአማራ ደም አለበት። በአባቱ ደሞ አንድ ስምንተኛ ጎጃሜ ነው። በመጀመሪያ ትዳሩ ከኦሮሞ፣ በሁለተኛ ጋብቻው ከወሎዬ ጋር ተቀላቅሏል። በሁለቱም አቅጣጫ ዘሩን ዘርቷል። ሦስት ሴትና ሁለት ወንድ ልጆችን ወልዷል።

ሕይወቱ የታነፀበት ባሕል፣ ወግ በመሐል አገር የአማራው ሥርዓት ሲሆን፣ ሥነ ልቦናው የእንግሊዞች እንደሆነ ይናገራል።

አንድ ቀን ርዕሳችን ዘር ማንዘር መቁጠር ሆነ። በጨዋታው መሐከል አጼ ምኒልክን አነሣና «ዘነበ፣ ያንተ ዘር ጋሞ ነው። የኔ ደግሞ ትግሬ። ምኒልክ መጣና የምንግባባበትን የአማርኛን ቋንቋ፣ ለዜግነታችን ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን፣ ከዚያም በላይ ባንዲራን ሰጠን። የነጮች ባሪያ ከመሆን አዳነን። ምኒልክ ባይኖር ኖሮ በምን ዓይነት ቋንቋ እንግባባ ነበር?»

ነሸጥ ሲያደርገው በአሜሪካዊው ዋልት ዊትማን ግጥም ራሱን ይገልጻል።

Do I contradict myself?
Very well then. I contradict myself
I am more than one. I am many
I am myriads I am a universe

***

እንተርጉመው።

ያልኩትን ተቃረንኩ እንዴ?
እንኳንም ተቃረንኩት።
ከአንድ በላይ ነኝ፤ ብዙ ነኝ
እልፍ አእላፍ ነኝ፣ ሙሉ ዓለም ነኝ

***

በጆን ዶን ሲመጣ ነብሱን እንዲህ ይተርካል፡፡

No man is an island
At most he is a promontary
Every man's death reduces me.
Send not to ask for whom the bell tolls
It tolls for thee

***

ማንም ሰው ደሴት አይደለም
ግፋ ቢል ሰርጥ ቢሆን ነው
የማንም ሰው መሞት እኔን ያጎድለኛል
የቀብር ደወል የሚደወለው ለማን ነው ብለህ አትጠይቅ
የሚደወለው ላንተ ነው፡፡

ይህ ነፍሱ ዓለም የሆነች ሰው፣ ይህ የማንም ሞት ያጎድለኛል ብሎ የሚያስብ ሰው ታመመ፡፡ ...

ከጋሼ ጋር ስለሞት ለአያሌ ጊዜያት አውግተናል፡፡ በአንድ ወቅት ሲያጫውተኝ «ሞት መምጫው አይታወቅም፡፡ ያከስቱ ልጅ ስታጫውተኝ ሞት የሚገርመኝ መደምደሚያችን ነው፡፡ ሰዎች ደግሞ በየት በኩል ሸንቁሮን ይገባ ይሆን ብለን ስንጠነቀቅ እንኖራለን፡፡ የሚከዳኝ ሳምባዬ ወይስ ኩላሊቴ ይሆን? አልያስ ልቤ?... እያልን እንጨነቃለን፤ እንጠበባለን፡ ሞት ግን አገባቡን ቀይሮ ይመጣና ሒሳብ ያዘጋናል፡፡»

በሌላ ጊዜ «ከእንቅልፌ ነቅቼ እንደምነሳ ከዚያም እንደምተኛ ሁሉ ከሞት በኋላም ነቅቼ የምነሳ ነው የሚመስለኝ» ብሎኛል፡፡ ይህን አባባሉን እያብሰለሰልኩ "ቀጣይ ሥራዬ ያንተን ሕይወት መጻፍ ነው፡፡ ቶሎ ተነሳና ምዕራፍ በምዕራፍ እያነበብን እናስተካክለውና የጎደለም እየጨመርን በሐሳብህና በሐሳቤ እምናዳብርበት ሁኔታ እንፈጥራለን" አልኩት፡፡

"ከሆነልህ ደስ ይለኛል!!" አለኝ፡፡ ሙሉ ፈቃደኝነቱን በሚያሳይ ስሜት፡፡ ብዙ ተጨዋወትን፡፡ ከዚያን ዕለት ቀደም ብሎ እሱ ነው ብዙ እሚያጫውተኝ፡፡ የእኔ ተግባር እርሱን በጥያቄ መኮርኮር ነበር፡፡ የዚያን ዕለት ይደክመዋል ብዬ ስለገመትኩ አጫዋችነቱን እኔ ነበርኩ የያዝኩት፡፡ ጀምበር ስታዘቀዝቅ ወደ ሰፈሬ ለመሔድ ተነሳሁ፡፡

እየጨበጥኩት በጄ ጨመቅ አደረግኩት፡፡ እሱም ጨመቅ በማድረግ አፀፋውን መለሰልኝ፡፡ ሆኖልኝ ታሪኩን እንደምጽፍለት

@Amharicbookstore



በእጆቻችን ስንጠቃቀስ ነው፡፡ በቆምኩበት ቁልቁል ሳይ ከፋይ ቡና ዓይነት ጫማው ክሩ ተፈቷል፡፡ ይህ „የዘወትር ልማዱ ነው፡፡ ምንጊዜም አንድ ቦታ ሄዶ ሲገበዝና ጫማውን አውልቆ መደብ ላይ ሲቀመጥ፣ ወይም ማታ ቤቱ ገብቶ ሲተኛ የጫማውን ክር ፈቶ ኪሱ የመክተት ባሕርይ አለው፡፡ ይህ ጋዋን ወይም ቱታ ለብሰን እቤት መዋላችንን የምንገልፅበት ስልት መሆኑ ነው፡፡ በዚሁ ሰሞን የጫማውን ክር አሥሮ እኔ ቤት በመምጣት አብረን ያችን ታሪክ በተዋጣ መልኩ እንደምንሠራው አስቤ ፈገግ አልኩ፡፡ በሕይወቴ ነገን በፍጹም የማያምን ሰው ማንን ታውቃለህ ብባል ልጠራ የምችለው አንድ ሰው ጋሼ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔርን ነው፡፡ ይህን ተፈጥሮን ያለማመን ጠባዩን አጋብቶብኝ እኔም ዛሬን እንጂ ነገን ሳላምን እዚህ ደርሻለሁ፡፡

"ከሆነልኝ ደስ ይለኛል" እንዳለ አጠቃላይ የሕይወቱን ምዕራፍ አጫውቶኛል፡፡ መጽሐፉን ጽፌ እንዳጠናቀቅኩ መጀመሪያ ያስነበብኩት ራሱን ነው፡፡ አስተያየቱን በገዛ እጁ ጽሕፈቱ በመጽሐፉ ቢሮ ላይ አኑሬላችኋለሁ፡፡ በክፍል አንድ ልጅነቱን፣ ወርቃማ ዓመታቱን፣ የኪሊጁን፣ የፍቅሩን፣ ትዝውን፣... ሰውየው ስብሐትን ታገኙታላችሁ፡፡ በክፍል ሁለት እንደ ፋታ ማግኛ ከወዳጅ ዘመድ የሰበሰብኳቸውን ፎቶግራፎች ትመለከታላችሁ፡፡ በመጽሐፍ ሦስት ማዕደ ጥበባት በክፍል አራት በመሰነባበቻ የምንላችሁ አለን፡፡ ክፍል በክፍል አምስት ዘና እንበል ላይ ተሳስቀን አልባቱ ላይ እንደርሳለን፡፡ ደራሲውን ስብሐትን ታገኙታላችሁ፡፡ በመጨረሻም አስጀምሮ ላስጨረሰን... እንባባላን፡፡ እናም የእኔን ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ሕይወቱን ከነብትርዋ ይሸውላችሁ፡፡ የናንተን እንጂ እንጂ እኔስ ሞትን ከስብሐት ጋር እንዲህ ቀደምኩት፡፡ ደንቴም እንዲህ አድርጎም መቅደም የለ!!

የጋሽ ስብሐትን ስብዕናና ኪነጥበባዊ ክህሎቱን አሳምሮ የሚገልጽልኝ ደበበ ሰይፉ ነው፡፡ ደበበ እንደዚህ ይለናል፡፡ «ደራሲ ደራሲ ከመሆኑ በፊት አንባቢ ነው፡፡ ደራሲ ደራሲ ከሆነ በኋላም አንባቢ ነው፡፡ የሕይወት ትጠ ልንም ያነባል፡፡ ዕድሜ ልኩንም ያነባል፡፡ እነሆ ዕድሜ ልኩን አንብቦ በሺዎች ዓመታት ከኖረው ደራሲ ስብሐት ጋር ልተዋችሁ ነው መልካም ንባብ!

***

፱

## ልጅነት

በትግራ ጠቅላይ ግዛት፣ በአድዋ አውራጃ፣ ርባገረድ በምትባል መንደር ውስጥ ነን፡፡ ከርባገረድ ማዶ ሰማይን ለመንካት የምትን ጠራራ ተራራ አለች፡፡ የተራራውን ስም ማሪያም ፎ ይሉታል፡፡ ማራም ፎ ሁሌም በክረምት ጉም ትለብሳለች፡፡ እዚህ መጥተን አድገን ወልደን አንድ ቀን ታናሽ ወንድሜን ተወልደ ብርሃንን ከትውልድ መንደራችን በሩቅ የምትታየው ተራራ ለምን ማሪያም ፎ እንደተባለች ጠይቄው እንዲህ አለኝ፡፡ «አባቶቻችን ሲያወሩ እንደሰማሁት አንዱ ጥልያን ማነች ይህች ተራራ?» ሲል ተወላጆቹን ይጠይቃል፡፡ ማሪያም፤ ሲሉ ይመልሱለታል፡፡ «ማራም ፎ! አለ ጥልያኑ፡፡ ፎን የጨመረው ለአድናቆት ነው፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተራራዋ ስያሜ ማራም ፎ ሆኖ ቀረ፡፡

እኔ ተወልጄ ባደግኩባት መንደር ሦስት ቤቶች አሉ፡፡ የቤቶቹ አሠራር ታሪክ እንዲህ ነው፡፡ አያቴ ምህረቱ ገብረ ዮሐንስ ሲያርፉ ርስታቸውን ሁለት ልጆቻቸው ተከፋፈሉት፡፡ አንዱ የአጎቴ ሲሆን፣ ሁለተኛው የእኔ ወላጆች ቤት ነው፡፡ ሌላኛው የእኔ የክርስትና አባት የአቦይ ገብሩ ቤት በቅርብ ርቀት አለ፡ እነዚህ ቤቶች እሳት ይጫጫራሉ፣ ዕቃም ይዋዋሳሉ፡፡

ከመንደራችን ወረድ ብሎ ርባገረድ የምትባል ወንዝ አቋርጣው ታልፋለች፡፡ ትርጓሜውም በአማርኛ የገረድ ወንዝ ማለት ነው፡፡ አረንጓዴውን መስክ፣ ሸንተረሩን፣ የባላገሩን ጎጆ በምናባችሁ ሳሉት፡፡ የአዕዋፉን ዝማሬ፣ የከብቶቹን ጩኸት፣ የእረኛውን ዜማ፣ ያለመታከት ከመሬት ጋር የሚታገለውን አርሶ አደር ሕይወት በልቦናችሁ አብሰልስሉት፡፡ እዚህ ባላገር ውስጥ ነው ሚያዚያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም የተወለድኩት፡፡

አባቴ መምሬ ገብረ እግዚአብሔር ገብረ ዮሐንስ፤ እናቴ ወይዘሮ መዓዛ ተወልደ መድሕን ይባላሉ፡፡ ሁለቱንም ሕይወት ያጣመራቸው

@Amharicbookstore



እንዲህ ነው፡፡ አባቴ ሚስታቸውን፣ እናቴም የመጀመሪያ ባሏን ሞት ነጥቋቸዋል፡፡ ሁለቱም ከመጀመሪያው ትዳራቸው ልጆች አፍርተዋል፡፡ እኔ በዚህ ሁለተኛ ጋብቻቸው የመጀመሪያ ልጃቸው ነኝ፡፡ ስብሐት ለአብ አሉኝ፡፡ አዲስ አበባ መጥቼ የአራዳ ልጆችን ሕይወት ስቀማምስ በክርስትና ስሜ መጠራቱ ረዘመብኝ፡፡ ስለዚህ ስሜን ስብሐት ብዬ አሳጠርኩት፡፡ ለአብን እስከ ዘለዓለሙ ልሰናበታት ግን አልቻልኩም፡፡ ምክንያቱም ከገጠር ዘመዶቼ ሲመጡ፣ ከታናናሾቼም ከታላላቆቼም ጋር ተነፋፍቀን ስንገናኝ የሚጠሩኝ ስብሐት ለአብ ብለው ነው፡፡ ምንም አይመስለኝም፡፡ እንዲያውም የልጅነት ስሜቴን ይከረክሩዋታል፡፡ ጨዋታችንንም ያደምቅልናል፡፡ በአሁኑ ዕድሜዬ ወጣቶች ፈርምልን ይሉኛል፡፡ እኔም ስብሐት ለአብ እያልኩ ነው የምፈርምላቸው፡፡

እንደሚታወቀው የተወለድኩት ፋሽስት ኢጣልያ አገራችንን በወረረቻት ወቅት ነው፡፡ ነፍስ ማወቅ ስጀምር አንዳንድ ነገሮችን መስማት ጀመርኩ፡፡ እጅግም መራር ስላልሆኑ ብዙዎቹን አላስታውሳቸውም፡፡ አንዷ ግን አሁንም ትዝ ስትለኝ ታስቀኛለች፡፡

አንድ ቀን አቦይ የክርስትና አባቴን ልጅና ታላቅ ወንድሜን አያ ገውን አስከትለው በመንደራችን ውስጥ አሁን ትዝ የማይለኝን ሥራ በጋራ ይሠራሉ፡፡ የክርስትና አባቴ ልጅ ስሙ ገብረ እግዚአብሔር ነው፡፡

በዚያን ሰዓት አንድ የጣሊያን ‹ቴኔንቴ› ቡድን ወደ መንደራችን ይመጣል፡፡ ባንዳዎችን አሠልፎ ሲደርስ አባቴ ከልጆቻቸው ጋር በሥራ ላይ ናቸው፡፡ የጣሊያኑ ቴኔንቴ አመጣጡ ለሰላም ነው፡፡ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ሰብስበው ይወስዱና እስከ አራተኛ ክፍል ያስተምሩዋቸዋል፡፡ ከዚያም በተላላኪነት፣ በፖስተኛነት፣ በተለያዩ አነስተኛ ሥራዎች ይመድቡዋቸዋል፡፡ ይህንን ምልመላ ለማካሄድ ነው ጥልያኑ መንደራችንን መጎብኘት ያስፈለገው፡፡ አባቴ አጠገብ ሲደርሱ ቆም ብለው ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡ ማንነታቸውን አባቴን ጠየቃቸው፡፡

«ገብረ እግዚአብሔር እባላለሁ፡፡» ብለው ወደ ልጆቻቸው እያመለከቱ፣ «እነዚህ ልጆቼ ናቸው፡፡ ይኼ ገው ይባላል፣ ይኼኛው ደግሞ ገብረ እግአብሔር ነው» ይሉታል፡፡

ጥሊያኑም ተገርሞ “አባትም ልጅም ገብረ እግዚአብሔር?” ሲላቸው

“ቢሆንስ?! እና ምን ትሆናለህ?!” አሉና ዱላቸውን ወደ ላይ አነሱበት፡፡ ጥልያኑ በጣም ግቀና አልፎአቸው ሄደ፡፡

አባቴ ምህረያ ገረዝጊሄር ረጅምና ቀጭን ቁመና ነው ያላቸው፡፡ በባህርያቸው በጣም ቁጡ ቢሆኑም ቶሎ ይበርድላቸዋል፡፡ በሰላም ወቅት ተጫዋች ናቸው፡፡ ቀልዱን ያውቁበታል፡፡ ተግባራቸው ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው በቤተክህነት ትምህርታቸው ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ፣ በሌላው ገበሬ ናቸው፡፡

የባላገር ቄስ እንደ ከተማው ቄስ ሙሉ በሙሉ ሥራው ቅስና አይደለም፡፡ ዘወትር እሑድ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከበዓላት ውጪ አራሽ ነው፡፡ አባቴን አሁን ሳስባቸው የሚያስገርሙ ገጠመኞች በልጆቻቸው ነፍስ ውስጥ አኑረዋል፡፡

ትንሽ ልጅ ሆኜ ማረስ እለማመዳለሁ፡፡ አቦይ ማረሻውን ለቅቀውልኝ እንዴት ማረስ እንዳለብኝ እየመሩኝ ዘና ይላሉ፡፡ እንደ ተለመደው አንድ ቀን ማረስ ጀመርኩ፡፡ ትንሽ ተጓዝኩ፡፡ ይሁን እንጂ ማረሻውን መሬት ውስጥ ሰቅስቄ መውጋት አልቻልኩም፡፡ በዚህ ጊዜ በሬዎቹ ችግሬን ሳይረዱ ማረሻውን ጎተቱት፡፡ ማረሻው ከአፈሩ ወጣና የበሬውን እግር ወጋው፡፡ «ወይኔ አባቴ ገደሉኝ» ብዬ በጣም ክው አልኩ፡፡ እሳቸው ግን «አይዞህ ልጄ» አሉና ቀንበሩን ከበሬዎቹ ላይ ፈተው ወደ መንደራችን ተመለስን፡፡ የዚህን ተቃራኒ ደግሞ ላጫውትህ፡፡ አቦይ ገረዝጊሄርን በደንብ እንድታያቸው፡፡

አንዳንዴ የማያስቆጣ ነገር እርር ድብን ሲያደርጋቸው አጋጥሞኝ በልጅነት ልቤ ውስጥ ተቀርፆ ቀርቷል፡፡ አንዴ እንጨት ሲፈልጡ ይሁን ሌላ ሥራ ሲሰሩ የለበሱት ነጠላ ከትከሻቸው ላይ ወርዶ ጫፉ መሬት ዘፍ አለ፡፡ ወደላይ መልሰውት ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡ ነጠላው አሁንም መሬት ላይ ወደቀ፡፡ ቀና አድርገውት ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡ ነጠላው እንደገና መሬት ዘፍ አለ፡፡ ይኼኔ ተናደዱና «መውደቅ ከፈለግህ ይኸውልህ!» ብለው ከትከሻቸው ላይ አውርደው መሬት ጥለው ደህና አድርገው ረገጡት፡፡

አባቴ ባላገር ውስጥ መንገድ ይጓዛሉ፡፡ ስንቅ አልያዙም፡፡ በጣም ራባቸው፡፡ ወሩ ጥር ስለነበር በሚጓዙበት መንገድ ከርቀት የሠርግ ዘፈን ይሰማል፡፡ በዚያ ሰፈር አቦይ አይታወቁም፡፡ በአገሬው ተወዳጅ የሆነችውን የሠርግ ዘፈን እያወረዱ ሰተት ብለው ወደ ሠርግ ቤቱ ገቡ፡፡ ቤተኛው ተቀበላቸው፡፡ እሳቸውም ዘፈኑን ማውረዱን ቀጠሉ፡፡ የሠርግ ዳሱ በጣም ደመቀ፡፡ አንድ ወጣት አፈፍ ብሎ ይነሳና «እባክህ አንተ ወንድሜ፣ ለኔ ዋና ሚዜዬ ሁንልኝ!!» ሲል ተማፀናቸው፡፡

«እሺ ምን ከፋቶኝ» ብለው ቁጭ አሉና የራባቸውን ያህል በሉ፡፡

@Amharicbookstore



እናቴ አጭር፣ ወፍራም ነች፡፡ በባህሪዋ የአባቴ ተቃራኒ ነች፡፡ ዝምተኛ ናት፡፡ ልጆቿ ስንጠራት ወለላይ ብለን ነው፡፡ ያልመሰላትን ማንም ቢናገራት «ቅ!» ነው የምትለው፡፡ ድንቄም እንደማለት ነው፡፡ ይህ ለእርሷ ብዙ ተናገረች ማለት ነው፡፡ ባለሞያ ፈታይ፣ ጠንካራ ሠራተኛ ነች፡፡ ልጆቿን በጣም ትወዳናለች፡፡ ወለላይ ስታዝን፣ ስትጨነቅ አይቼ አላውቅም አቦይ ያውቁባት ይሆናል እንጂ፡ እንዴ እኔ የአንድ ወደል አህያ ጭራ ስነካ ሆዷን በርግጫ አፈረሰው፡፡ «ወለላይ!» ብዬ ጮህኩ፡፡ ፈትለክ ብላ መጣች፤ ያ ሁሉ ውፍረት የሌለ ያህል፡፡ «ሁለተኛ ያህያ ጭራ ትነካና ወየውልህ!» አላለችም፡፡ «ልጄን! ልጄን!» ብላ አቀፈችኝና የአህያውን እርግጫ አበረሳችኝ፡፡ እኔ በተራዬ ከወለድኩ በኋላ ነው በዚያች ሰዓት እናት ማን እንደሆነች ያየሁት፡፡

ሌላ ቀን ግን አበዛሁት፡፡ ምን እንዳደረግሁ ዛሬ አላስታውስም፡፡ ግን በወለላይ ቤት የሚያስገርፈኝ ጥፋት ነው፡፡ ተቆጣች፡፡ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ እናቴ ስትቆጣ የዚያን ዕለት አየኋት፡፡ አባቴ እንደመጡ ጥፋቴን ነግራቸው «ግረፉት!» አለቻቸው፡፡ ይኼውልህ እርሷን ፈርተው አቦይ ገረፉኝ፡፡ በሕይወቴ የዚያን ዕለት ብቻ የአባቴን እጅ ቀመስኩ፡፡ አንድም ቀን ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ተገርፌ አላውቅም፡፡

ሚጢጢ ሆኜ እኔና ወለላይ መንገድ እንሔዳለን፡፡ የባላገር መንገድ ጠባብ ስለሆነ ጎን ለጎን ስለማያስኬድ ኋላና ፊት ሆነን ነው የምንጓዘው፡፡ እሷ በረጅሙ እየተራመደች እኔ ሱክ ሱክ እያልኩ እከተላለሁ፡፡ መንገድ ላይ ድንጋይ አነሣችና «አንተም አንሳ» አለችኝ፡፡ አነሳሁ፡፡ የተወሰነ ርቀት እንደሔድን የድንጋይ ቁልል ከአለበት ስፍራ ደረስን፡፡ ወለላይ የያዘችውን ድንጋይ ቁልሉ ላይ አኖረችው፡፡ እኔንም እዚያ ላይ እንዳስቀምጥ ነገረችኝ፡፡ ቁልሉን አልፈን ስንሄድ የድንጋዩን ቁልል ምስጢር እንድትነግረኝ ጠየቅኋት፡፡ ስታጫውተኝ «እምታየው በታ ላይ ለወደፊቱ ቤተ ክርስቲያን ይሠራል፡፡ እንዲህ አይነት ሥራ ሲታሰብ ለአካባቢው ነዋሪ ይነገረዋል፡፡ ስለዚህ ሕዝብ ከየተነሣበት ድንጋይ እየያዘ እየመጣ ቁልሉ ላይ ድንጋዩን ያኖራል» አለችኝ፡፡ አለና ጋሼ ስብሐት ትኩር ብሎ እያየኝ "እየህ ይህ ሕዝብ አንድ ሲሆን፣ ንጉሥ ወይም አምባገነን መሪ አያስፈልገውም፡፡ ኔቨር! ሕዝብን በነፃነት ከአስተዳደርከው እንኳን ቤተ ክርስቲያን የፈለግከውን ሌላ ነገር ሁሉ አማምሮ ይገነባል፡፡ ለሕዝቡ የሚያስፈልገው ነፃነት ብቻ ነው፡፡ ነፃነት ብቻ...!

እህ... አዎን አንተን፣ እኔን እንደሰው የሚቆጥሩን ወላጆቻችን፣ ዘመዶቻችን፣ የምንኖርበት ማኅበረሰብ ብቻ ናቸው፡፡ በተረፈ ባለንበት ሁላችንም ለመንግሥቶቻችን እስታቲስቲክስ ነን፤ ቁጥር ነን፡፡

ቤተክርስቲያን ስንል አልነበረም? አንድ ጊዜ፣ አንዱ ይነግና የማይሆን ቦታ ይገኛል፡፡ በምሳሌ ማስደገፍ እንችላለን፡፡ ከንደኛው ሚስት ጋር መርፌና ክር ሆነው ተገኙ፡፡ ይኼኔ ባል ውሽማን ሊገድለው አሳደደው፡፡ ውሽማ እንዳይሞት ይሸሻል፡፡ ሮጦ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ደወል ይደውላል፡፡ ጉዳይ ይቆማል፡፡ እዚያ አካባቢ ዝርም አይል፡፡ በዚህ ጊዜ ለመግደል ግሎ የነበረው ባል ይቀዘቅዛል፡፡ ፋታ ስለሚኖር ሽማግሌ ተሰብስቦ ይቅር ለእግዜር ይባላል፡፡

አየህ የደወልን ኃይል? እንዲህ ነው የባላገር ሥልጣኔ፣ የሥልጣኔ ከተማ ገብቶ ሲበላሽ ማየት አይገርመንም?

አንዳንዴ፣ እንዲያውም ብዙ ጊዜ፣ አካባቢያችን በድርቅ ይመታል፡፡ በአንድ ወቅት አቦይ ወደ ሽሬ ተሰደዋል፡፡ ሽሬ ሁልጊዜ የጥጋብ አገር ነው፡፡ በጊዜው እህል የሚባል ነገር ቤታችን ውስጥ የለም፡፡ ወለላይ ደግሞ በእግዚአብሔር ጥልቅ እምነት አላት፡፡ ነግሬሀለሁ ባለሙያ ፈታይ ናት፡፡ የዚያን ሰሞን ልቃቂቶችዋን ይዛ ገቢያ ሄደች፡፡ አንድ ሰውዬ መጡና ፈትሉን አዩት፡፡ «ቆንጆ ፈትል ነው» ብለው ዋጋውን ጠየቋት፡፡ እንዲከፍሏት የጠየቀችው ገንዘብ ከጠበቁት በታች ሆነ፡፡ «ለዚህ የሚገባው እንዲህ ነው» ብለው ከጠየቀችው በላይ ከፈሏት፡፡ ተደሰተች፡፡ ባዶውን ቤቷን በልቃቂቷ ገቢዋ እህል ሸምታ ሞላችው፡፡ ሰውዬውም ከዚያ በኋላ ደንበኛዋ ሆኑ፡፡

ወለላይ በየሶስት ዓመቱ ነው ልጆቿን የወለደችን፡፡ አራት ወንድ፣ ሁለት ሴት ልጆችን ከማሕፀኗ አፍርታለች፡፡ ከመጀመሪያ ትዳርዋ አንድ ወንድ ልጅ ወልዳለች፡፡ አቦይ ከመጀመሪያ ባለቤታ ቸው አምስት ልጆች ወልደዋል፡፡ ወላጆቻችን በአጠቃላይ አስራ አንድ ልጆችን በመጀመሪያውም ሆነ በሁለተኛ ትዳራቸው አፍርተዋል፡፡ አባት እናታችንን ጨምሮ እዚያ ጎጆ ውስጥ የምንኖረው አምስት ልጆቻቸው ብቻ ነን፡፡ የተቀሩት ከመጀመሪያ ትዳር የተወለዱት ታላላቆቻችን ግን በዚያን ወቅት ወደተለያዩ አገሮች ሄደው የራሳቸውን ኑሮ ጀምረዋል፡፡



እኔ ለእናቴ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ፡፡ ተወልደ ብርሃን እንደተረገዘ ሁት በቃህ ተባልኩ፡፡ የኔ የክርስትና ሐባቴ የአቦይ ገብሩ ባለቤት ስም በትግርኛ እነይ ትዕበ ይባላል፡፡ ትርጓሜው ትደግ ማለት ነው፡፡ ፍስሐን ወልዳ ሁቷ ወተት ማፍሰሱን ስላላቆመ እርሷን እንድጠባት ተፈቀደልኝ፡፡ እነይ ትዕበን እየጠባሁ እስከ አራት ዓመቴ ቆየሁ፡፡ ወይስ አምስት አመት እስኪሞላኝ ጠባሁ? ትውስታዬ በዚያ ርቀት አታስተማምንም፡፡

በቤታችን ውስጥ ኩራዝ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ አይለኮስም፡፡ የምድጃው እሳት ሲከስም፣ አልያም ራት ልንበላ ስንል ነው የሚበራው፡፡ ወይም ወለላይ ቀን በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ በዝቶባት ከዋለች እና እንጀራ መጋገር ከፈለገች በኩራዙ ብርሃን ትሰራለች፡፡ ከቤት እቃዎች አንዲት በርጩማ ብቻ ቤታችን እንደነበረች ትዝ ይለኛል፡፡ ቀን ወለላይ ሥራ ስትሠራ ትቀመጥ በታለች፡፡ አቦይ ከእርሻ መልስ አረፍ ብለው እሳት የሚሞቁት በዚህችው በርጩማ ላይ ተቀምጠው ነበር፡፡ ይህችን በርጩማ እኔ ነኝ ነፍስ አውቄ ወደ ርባገረድ ስመለስ በሌላ መደገፊያ ባለው ወንበር ለአቦይ የቀየርኩላቸው፡፡ ለወለላይ ግን ምንም አልወሰድ ኩላትም፡፡ እኔ ልጇ እበቃታለሁ" አለና ፀጥ ብሎኝ ጥቂት ቆዘመና...

ለታላቁ ለአያ ገው ጥልቅ ፍቅር አለኝ፡፡ በዚያን ወቅት እርሱ ጎረምሳ ነው፡፡ ሁጪ ወጥቼ መዋል ከቻልኩ ጀምሮ አብሬው እውላለሁ፡፡ እሄደበት ሁሉ ያስከትለኛል፡፡ በወቅቱ እኔ ለጥጃ እረኝነት ደርሻለሁ፡፡ ስለማናቸውም ነገር ያስተምረኛል፡፡ ትግል እንዴት መግጠም እንዳለብኝ አሰልጥኖኛል፡፡ ይኼ ልምምድ ካለፈ ዕለታት፣ ወራት፣ ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ አንድ ቀን የእኛ ሠፈር ልጆችና የሌላ መንደር ልጆች ይዋጣልን ተባባሉ፡፡ ጎረምሶቹ ማን ማንን እንደሚያሸንፍ ይተዋወቃሉ፡፡ ፀባቸውም አይጀመር እንጂ፣ ከተቀሰቀሰ በቀላሉ አይበርድም፡፡ ደንባቸውም አረፍ እንደሆነ አስታውሳለሁ፡፡ የምር ስለሚጋጠሙ፣ የሚጣሉት ጎረምሶች ዱላቸውን መሬት አስቀምጠው ትግል ይገጥማሉ፡፡ ትግሉን ቀድሞ የጣለው ጎረምሣ ዱላውን ያነሣና የወደቀውን ይገርፈዋል፡፡ ተመቺው "ማረኝ" ብሎ ካለቀሰ ደብዳቢው ያቆማል፡፡ ይኼ ለጎረምሶቹ የሚሠራ ደንብ ሲሆን፡ ለእኛ ለሡጫጬቹ ግን ታግለህ መጣሉ ብቻ በቂ ነው፡፡ የዚህን ዕለት ከየሰፈሩ ወኪል የሚሆን ሡጫጭ ተመረጠና ሰፈራቸውን ወክለው እንዲፋጠሙ ተወሰነ፡፡ ከዚያኛው ሰፈር አንድ ልጅ ተመረጠ፡፡ ከእኛ ሰፈር አያ ገው እኔን እንድጋጠም መረጠኝ፡፡

ተጋጣሚዬን ሳየው በጣም ፈራሁ፡፡ እንደዚያን ሰለት የተርበ-ተበትኩበት ቀን ትዝ አይለኝም፡፡

"ታሸንፈዋለህ" አለኝና ኢዮ ገው ገፋ አደረገኝ፡፡

ምንም ብፈራ እንቢ አልፈልግም ልለው አልቻልኩም፡፡ እንደ ፈራሁ አልቀረልኝም፤ ትግሉን ገጠምኩ፡፡ ታገልን፣ ታገልንና ጣልኩት፡፡ በጣም ገረመኝ፡፡ ግን ፍርሀቱ አሁንም አልለቀቀኝም፡፡ በጭራሽ ከፍርሀቴ ነፃ ሳልሆን ርባገረድ ገባሁ፤" አለ፡፡ ፍርሃቱ ምን ዓይነት ጭንቀት በሰራ አካላቱ እንዳደረሰበት በአኳኋኑ እያሳየኝ ቀጠለ፡፡ "በመንደርህ ማን ማንን ያሸንፋል ትባባልና ትሞካከራለህ፡፡ እርስ በራሳችንም እንተዋወቃለን፡፡ በዚህ የልጅነቴ ወቅት የምታስገርም ገጠመኝ አለችኝ፡፡ የአቦይ ገብሩ ልጅ ፍስሐ የእኔ እኩያ ነው፡፡ እሱ እኔን ያሸንፈኛል፡፡ እኔ ተኽሉን አሸንፈዋለሁ፡፡ ተኽሉ ደግሞ ፍስሐን ያሸንፋል፡፡ ይኼንን ሁኔታ በልጅነቴ ሳሰላስለው ተኽሉ ያሸነፈውን ፍስሐን እንዴት እኔ አላሸንፈውም? ስል እገረማለሁ፡፡ ይህች ጥያቄ መልስ ሳይገኝላት ውብ የነበረችው የልጅነት ወቅት አለፈች፡፡" አለኝ ፈገግ ብሎ ጢሙን በጣቱ እያፍተለተለ፡፡ "ትዝታ ትዝታን ይጠራል፡፡ ተረኛዋ ትዝታ መጣች፡፡ ልቀጥልልህ ነው፡፡

ከአብሮ አደጎቼ ጋር በብዙ ቀዳዳ ማን ይሸናል እንባባልና የምንጫወታት ጨዋታ አለችን፡፡ አንድ ሐረግ አለች መሬት ለመ ሬት እየተጎተተች የምትበቅል፡፡ ይህችን ሐረግ ቅጠልዋን ስትበጥሳት ነጭ ወተት ይወጣታል፡፡ ወተቱን በመሸኛ ቀዳዳችን ላይ ጠብ እናደርገዋለን፡፡ ወተቱ መሸኛችን ላይ ይደርቃል፡፡ በበነጋታው በልዩ ልዩ ቀዳዳዎች እንሸናለን፡፡ ከጓደኞቼ ጋር በተራ እየሸናን የማን ቀዳዳ እንደበዛ እንቆጥራለን፡፡ አንዱ በሦስት፣ በአራት፣ በአምስት እያለ ይቀጥላል፡፡ ነገ በበለጠ በብዙ ቀዳዳዎች ለመሽናት ወተቱን መሸኛችን ላይ ጠብ እናደርጋለን፡፡ ተነገ ወዲያ እስከ ዘጠኝ ቀዳዳዎች እንሸናለን፡፡ እኔም በዚህ የቁጥር ብዛት መሽናት ጀመርኩ፡፡ በሚቀጥለው ቀን የበለጠ እንዲበዛልኝ በማሰብ ወተትዋን በደንብ ብልቴ ላይ አፍስሼ አደርኩ፡፡ ሲነጋ ሽንቴ ወጥሮኝ ተነስቼ ብለው ብሠራው እንቢ አለኝ፡፡ ሲጨንቀኝ «ኢዮዮ!» ብዬ ተጣራሁ፡፡ ኢዮ ገው እየሮጠ መጣና «ምን ሆንክ?» አለኝ፡፡

"ሽንቴ እንቢ አለኝ" አልኩት፡፡

ወረንጦውን አወጣና በርከክ ብሎ ሲጎትጣት ሽንቴ ቷ! ብሎ ራቱን አለበሰው፡፡ ይኼንን ሳስታውስ ኢዮ ገው ትዝ ይለኛል፡፡ ኢዮ ገው እዚያው ርባገረድ የአባታችን መሬት ብቸኛ ወራሽ ሆኖ በግብርናው ገፋበት፡፡ ሌሎቻችን እንደየዕጣችን ለመኖር በሠፊዋ



ኢትዮጵያ ተዘራን፡፡ ኢዮ ገው ጎልምሶ ትዳር መስርቶ ታሞ አረፈ፡፡ ጥሩ ጨዋታ አዋቂ እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ በጣም የምወደውን ኢዮዮ ገውን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው የተለየሁት" ብሎ ተከዘ፡፡ በፀጥታ እንደተዋጥን ፈገግ አለ፡፡

መምህረይ ገብረ ዮሐንስ ኢዮቴ ናቸው፡፡ የአቦይ አባት፡፡ እሳቸው አሁን በምነግርህ ገጠመኝ ውስጥ ባይከሰቱ ኖሮ በአሁኑ ሰዓት መተዳደሪያዬ ምናልባት ሌብነት ይሆን ነበር ስል አስባለሁ፡፡

እንዴት? ማለት ጥሩ፡፡ ኢዮቴ መምሬ ገብረ ዮሐንስ መልካቸው ቀይ መሆኑ አሁንም ትውስ ይለኛል፡፡ በዕድሜ በመጣባቸው መዘዝ ታውረዋል፡፡ ዕድሞ ውስጥ ነው የሚተኙት፡፡ ዕድሞ ከሣር ጎጆዎችን አጠገብ ከድንጋይ የተሠራ ባለአራት ማእዘን መጠለያ ነው፡፡ እዚያ ውስጥ በኢዮቴ ራስጌ በገንቦ ሙሉ የዋንዛ ደረቅ ፍሬዎች አሉ፡፡ ፍሬዋን ሚጢጢ ቴምር በላት፡፡ እንደ ዘቢብ ሲበሏት ትጣፍጣለች፡፡ ግርጌያቸው ወደበሩ ነው፡፡ እንደማያዩ ስለማውቅ ብዙም አልተጨነቅኩም፡፡ ልክ ገንቦዋን ከፍቼ ከዋንዛው ልዘግን ስል አፈፍ አደረጉኝ፡፡ አቤት ድንጋጤዬ!!! ለካ ተሳስቻለሁ፡፡ ያኔ ውሪ ስለነበርኩ ኢዮቴ በጆሮአቸው ሕያው መሆናቸውን ረስቼ ስገባ እያንኮሻኮሸኩ ነው፡፡ እሳቸው ግን መደንገጤና መሸበሬ ገባቸው፡፡ ሲያኩሙኝ፣ የልጃቸው ልጅ ነኝና ከዋንዛው ቆንጥረው ሳይሆን በደንብ ዘግነው ሰጡኝ፡፡ ዋንዛዋ በዕለትዋ ጣፍጣ ተበልታ ብታልቅም ድንጋጤዋ ግን አብራኝ አድጋ ሌብነትን ከላዬ ላይ አራገፈችው፡፡

እቃ፣ እቃ በደንብ ተጫውቻለሁ፡፡ ለዚያውም ባልኛ ሚስት" አለና ጋሼ ስብሐት በግንባሩ ላይ በስተቀኝ በኩል ያለችውን ጠባሳ አሣየኝ "በግምት የሰባት ዓመት ልጅ እያለሁ ነው የተፈነከትኩት፡፡ በዚያን ጊዜ የታናሼ ታናሽ ዮሴፍ ሕፃን ነው፡፡ ይድሃል፡፡ እርሱን እንድጠብቅ፣ እንዳጫውተው ታዝዣለሁ፡፡ ግን በሚያስተማምን ሁኔታ ልጠብቀው አልችልም፡፡ ይህንን ሁኔታ ቤተሰቦቼ ቀድመው ተረድተው አንዲት የሩቅ ዘመድ በዕድሜ ግን እኩያዬ የሆነች ሴት ልጅ ቀጠሩ፡፡ ደሞዝዋ በመኸር ወቅት የተወሰነ ቁና እህል ለቤተሰቧ ይከፈላል፡፡ ይህቺ ልጅ እንደመጣች እኔ ዮሴፍን ከመጠበቅ ነፃ ሆንኩ፡፡ እኔ፣ ልጅቱና ዮሴፍ እቤት ውስጥ ስንውል ወላጆቼ ወደ እርሻ ተግባራቸው ሄዱ፡፡ እኔና እርስዋ መቅረታችንን ሳይ አንድ ነገር አማረኝ፡፡ ለመንኳት፡፡ ዮሴፍ በወቅቱ ነብስ አያውቅም፡፡ ወንድ ከሆንክ አይደለም የሰባት ዓመት ልጅ፣ የሁለት ዓመት ልጅም ብትሆን ያምርሃል፡፡ እሷም ሳያምራት አይቀርም፡፡ «እሺ ግን በአንድ ነገር እንስማማ» አለችኝ፡፡

@Amharicbookstore

«በምን?» አልኳት።

«ጭንቅላትህ ተዘቅዝቆ እግርህን እሽኮኮ ብዬ ከዚህ እስከዚያ ድረስ ተሸክሜ ልውሰድህና ሳንመለስ እሺ» አለችኝ።

ተስማማሁ። ተዘቅዝቄ እንጠልጥላኝ መንገድ ጀመርን። ትንሽ እንደሄደን አንድ እግሬ አመለጣት በጭንቅላቴ መሬት ላይ ተተከልኩ። ግንባሬ ላይ ተፈነከትኩ። ሁሉም ነገር ቀርቶ ቁስሌን ማስታመም ጀመርኩ።

"ልቀጥልልህ" አለኝ ጋሼ፡ ይህችኛዋ ገጠመኜ የልጅነትን ልበገርነት የምታሳይ ነች። አንዲት ዘመዳችን ሞታ ወለላይ ለቅሶ ተቀምጣለች። ለቀስተኛ ከየአካባቢው ይጎርፋል። ልክ እኛ ግቢ አጥር አጠገብ ሲደርሱ ማልቀስ ይጀምሩና ወደ ውስጥ ይገባሉ። እናቴ የሞተችበት ልጅና እኛ እየተጫወትን ነው። ለቀስተኞቹ ለቅሶውን ደርሰው ከቤት ሲወጡ ልጁን ካዩት «ይኼውልሽ የሟችቷ ልጅ» ብለው ከንፈራቸውን በሐዘን ይመጥጣሉ። እኔም ይህንን ሳይ ጊዜ ምነው ወለላይ ሞታ ለእኔም እንዲህ ባዘኑልኝ ስል መመኘቴን አስታውሳለሁ።

ሌላኛዋ ገርነት መጣች። አንዳንዴ እቤት ውስጥ ጨዋታው ሲደራ ዝፈን ይሉኛል። እዘፍናለሁ። አንድ ጊዜ፣ (አቦይ እንጀራ ለማሳደድ ሽሬ ሄደው ሳይሆን አይቀርም) እናቴና ዘመዶቹ ባሉበት ሳልጠየቅ መዝፈን ጀመርኩ። እንደመሰለኝ ራሴን ስጠረጥረው «ጎሽ የኔ ልጅ!» ብለው እንዲያሞጋግሱኝ ፈልጌያለሁ። የዘፈንኳት ዘፈን ትርጓሜዋ 'እትዬ ዘውዲቱ፣ ሊጋሽዬም አቅምሺያቸው' ነው የምትለው። በዚህ ጊዜ ወለላይና እንግዶችዋ «አንት ምናምንቴ! አትጠፋም ከዚህ?!» ብለው አባረሩኝ። ብሎ ፈገግና "ይህቺ እንግዲህ ትንሽ ሲዞርብህ የምታጋጥምህ ዓይነት ናት። የገሃዱን ዓለም ኑሮ ዓይንህን ገልጠህ ስታስተውል ደግሞ የሰው ልጆች ሲባሉ የትም ቢሆን፣ ጤናማዎቹ ሰዎች በአበዱ ሰዎችና በውሾች ላይ በጣም ይጨክኑባቸዋል። ይህ ለእኔ አሳዛኝ የሕይወት ፈተና ነው። ርባገረድ ውስጥ ውጫጭ ዞኚ የማልረሣት አንዲት እብድ ነበረች። ቆንጆ ነች። ትልልቅ ሰዎች ሲያወሩ እንደሰማሁት፣ ተድራ፣ የሀርግ ግብግቦ ዘፈን አብቅቶ ጫጉላ ቤት እየተስተናገደች እያለች፣ ከዚያ ሁሉ ሆታ በኋላ ድንገት እሷ ብቻዋን ሆና ከብቻዋ ጋር ተፋጠጡ። በዚህ ድንገተኛ ብቸኝነት አበደች። አንዳንዴ ዘነበች እብደቷ ሲለቃት፣ እያለቀሰች እንዲህ ታንጎራጉራለች «ወይኔ፣ ይህን ውበቴን ሳልጠቀምበት አፈር ልሆን ነው ወይ?!» እያለች ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች። ሲሻላት እኛ ውጫሌጮቹ እንጠራትና «ወይ!» ስትለን



«እንትን አለሽ?» እንላታለን። እሷም "አዎና! ያውም ምን የሚያክል ወፍራም ቀይ!" ትለናለች።

በዚያው በልጅነቴ ወቅት በሩቂቱ በአድዋ ከተማ አንድ አስተዋይ እብድ እንደ ነበሩ ሲነገር ትውስ ይለኛል። እኚህ ሰውዬ ብቻቸውን ቆመው እያለ፣ ከኋላቸው አንድ ልጅ ሲስቅ ሰሙ። ዘወር ብለው ቢያዩ ሌላ ሰው የለም።

«ልጄ ከማን ጋር እየሳቅክ ነው?» ይሉታል።

«ብቻዬን!» ሲላቸው፣

«ልጄ! በስማም በል። እኔንም ሲጀምረኝ እንዲህ ነበር» አሉት።

እኛ ቤት የፊደል መምህራችን አባታችን ናቸው። ፊደልን በእኛ ባህል ስትማር ሀሁን ብቻ ሳይሆን፣ ከሃይማኖትም ጋር ያስተዋውቁሃል። ይህ ደግሞ ሌላ መንፈሣዊ ብርሃን ነው። እንየው?

በአገራችን በሰንበት ዕለት አቅራቢያችን ወደሚገኝ ቤተ ክርስቲያን እንሔዳለን። አባታችን ፀሎተ ሥርአቱን አስተምረውናል። ክርስትናን ያወቅኩት በዚህ ወቅት ነው። ሌላ ትዝታዬ የእስልምናና የክርስትና ግንኙነት ነው። በአገሬ የሽመና ሥራ የሚሠሩት እስላሞች ናቸው። እናቴ ፈታይ ስለሆነች የሸማኔ ደንበኛ አላት። ሸማኔውም እኛ ቤት በየጊዜው ሲመጡ አስታ ውሳቸዋለሁ። እኛም በተለያዩ ጊዜያት ሸማኔው ቤት ተልከናል። አንድ ቀን እኔና የታላቄ ታላቅ አደይ አስካሉ ሸማኔው ቤት ተላክን። አደይ አስካሉ መልዕክቱን ታደርሳለች። የሸማኔው ባለቤት ራቅ ብለው ወጥ ያበሳስላሉ፡ ሴትዮዋ ድስታቸውን ለማማሰል ከፈቱት። ሥጋ ወጥ ነው የተጣደው። አደይ አስካሉ ብድግ አለችና «ና! እንሂድ» ብላኝ በሩጫ ወጣች። ተከተልኳት። መንገድ ላይ እየሄድን ምን እንዳስደነገጣት ስጠይቃት «ሴትዮዋ የሚሠሩት ወጥ የእስላም ሥጋ እኮ ነው» አለችኝ።

በእስልምና ላይ ሌሎች አንድ ሁለት ገጠመኞች አሉኝ። በአንድ ወቅት ወለላይ ወደተወለደችበት ማይምሻም ወደሚባል አካባቢ እንሔዳለን። በስተግራ በኩል አዲ እስላም የሚባል ሰፈር አለ። የእስላም አገር ማለት ነው። እዚያ አንድ አነስተኛ የገጠር ከተማ አለ። አዲ እስላም ስንደርስ ያየሁት የልብሶችና የጨርቆች የቀለማት ብዛት በወቅቱ የፈጠረብኝ ግርምት አሁንም ያስደንቀኛል። የሰውም ብዛት ያንን ያህል ነው ያስገረመኝ። ቀደም ብሎ የእኛን የገጠር ገበያ አይቻለሁ። አዲ እስላም ግን ከቀለማቱ ጋር ተዓምር

እንደሆነብኝ ውስጤ ቀረ። እስልምናና እኔ እንዲህ ነበር የተዋወቅነው።

እኔ ልጅ ሆኜ ስሰማ በዚያን ጊዜ ገንዘብ አደራ የሚሰጠው ለእስላሙ ነው። የእስልምና ተከታዮች ታማኝ ናቸው። አያክዱም። እስላሞቹ በቁጥር ጥቂት ቢሆኑም በወቅቱ በነበረው ኅብረተሰብ መካከል በሀብት ከፍ ያሉት እነሱ ናቸው።" አለና ካቲካላውን ፉት አለ። ውሃውን ተጎነጨና "የርባገረድን ሕይወት ነፍሷን ይዘሃል? ወደ መደምደሚያችን እየወሰድኩህ ነው። በልጅነቴ በጣም የምወደው እንቅልፍ ነው። ተኝቼ የነጎድጓድ ድምፅ መስማት ደስ ይለኛል። አሁንም ተኝቼ አውሮፕላን ሲበር ስሰማ ያንን ስሜቴን ይጠራዋል። ይሁን እንጂ የባላገር ኑሮ እንደልብ የሚተኛበት አይደለም። ቤተሰቡ ሁሉ ቢጥርና ቢግርም በጣም ድሆች ነበርን። በጠቅላላ የምንችለውን ያህል ሁሉ ሰርተን የድህነት ሰንሰለትን መበጠስ አልቻልንም። የእኔን እንቅልፍ ወዳድነት የምታውቀው ወለላይ የወደፊት መኖሪያዬ ባላገር ሣይሆን ከተማ እንደሆነ ጠቆመችኝ።

ድህነት ስልህ የከፋውንም በዚያው በሕፃንነት ዕድሜዬ ውስጥ አይቻለሁ። አሁን ሰውዬውን ረስቻቸዋለሁ። የልጁን እናት ነው የማስታወሳቸው። አንዲት ላም ብቻ ነበረች፣ ያለቻቸው። ትታለባ ለች። ልጁ ራበውና ከእርጎዋ ላይ ሰርቆ ተጎነጨላት። እናት ከውሎዋቸው መጥተው እርጎዋን ሲያዩ ተሰርቆላታል። ልጃቸውን ጠርተው ጠጥቶ እንደሆነ ጠየቁት። ልጁ ካደ። «በል ቶሎ የዶሮ ላባ አምጣልኝ» ብለው እንዳመጣላቸው አፉን አስከፈቱት። ዶሮ ላባዋን አፉ ውስጥ ከትተው ጉሮሮውን ኮረኮሩት። ልጁ አስመለሰው። እርጎዋ ወጣች። «ይቻት ወተቴ» አሉ እናት። አለና በብስጭት እጁን አወናጭፎ «ድህነት እዚህ ድረስ አስጨክኖ ልጃቸውን ብላልኝ ጠጣልኝ ከማለት ይልቅ የልጅህንም ሆድ ያስፈትሻል። የእኔ ወንድሞችና እህቶች ከድህነታችን መከፋት በቀር ከወላጆቻችን ሙሉ ፍቅር እየተሰጠን ነው ያደግነው።

ትልቅ ሰው ከሆንን በኋላ ከታናሼ ታናሽ ከዮሴፍ ጋር እንጨ ዋወታለን። «ዮሴፍ ያህቺ ወለላይ ከልጆቿ ሁሉ አብልጣ እኔን በጣም የምትወደኝ ይመስለኝ ነበር። ያንተስ ስሜት እንዴት ነበር?" አልኩት።

«እኔም ወለላይ ከሁላቸሁም አብልጣ እንደምትወደኝ ነበር የሚሰማኝ» አይለኝ መሰለህ ጆ! አየህ፤ እናቴ የምትበድለኝ ቢሆን ኖሮ ሴትን ጠልቼ ተጣምሜ አድግ ነበር። ሁላችንም ወላጆቻችን የሰጡንን ስንቅ ይዘን ነው መኖርን የምንጀምረው፣ ስንቁ መራር ወይም ጣፋጭ ሊሆን ይችላል። የእኛ ስንቅ ጣፈጠ። የእናቴን

@Amharicbookstore



ምክርና ፍቅር በልቤ ጥፌያት በአሥር ዓመቴ ገደማ ርባገረድን የኋሊት ትቼ ወደ አዲስ አበባ ከታላቅ ወንድሜ ለጋሼ አስፋው ጋር ኑሮ ጀመርኩ።

***

፲

## ዶቃው

በባላገር ማለዳ ከወፎች እኩል ነው የምትነቃው። ትልልቆቹም ሆኑ ትናንሾቹ ልጆች በዚህ ጊዜ ነቅተው የዕለት ተግባራቸውን ለማከናወን ይሰማራሉ። የማለዳን ጤዛ፣ ቁሩን፣ የተሲያት ግለቱን እንደ አመጣጡ ከሕይወት ጋር መጋተር በባላገር ግዴታ ነው።

የሰውን ልጅ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የምታውቀው እናቱ ነች። እናቴም እኔን ልጇን እንዲሁ ጠንቅቃ ታውቀኛለች። የባላገሩ ሕይወት ከእኔ እንቅልፍ ወዳድነት ጋር እንደማያዋጣኝ አውቃለች። ስለዚህ አንድ ቀን ታላቁን ምክሯን ለገሰችኝ። «ስብሐት ለአብ ልምከርህ። እንቅልፍ እንደልብ መተኛት ከፈለግክ አዲስ አበባ ሂድና ተማር። እንደልብ እየተኙ የሚኖሩበት አገር አዲስ አበባ ነው። የሌሊቱ ቁር፣ የከሰዓት በኋላው ንዳድ አያገኝህም፣ ጭቃ አትረግጥም። ተስማምቶህ መኖር የምትችለው አዲስ አበባ ነውና ሂድ፤ ወንድሞቼ አሉ፤ ያሳድጉሃል። ለሐጎስ ደግሞ ንገረው። እኔ እርሱን እናታችን ሞታ እንደ እናት ነው ተሸክሜ ያሳደግኩት። አሁን አንተን ልጄን ስልክለት ደስ ብሎት ያስተምርሃል። ስለዚህ ሂድ አዲስ አበባ» አለችኝ።

ከፊቱ በመለኪያ ተቀድታ የተቀመጠችውን ካቲካላ ፉት አላት። አንድ ጉንጭ ውሃ ከለሰባትና "በእኔ ግምት የአስር ዓመት ልጅ እሆናለሁ። በዚያኑ ሰሞን የእናቴ የበህር ልጅ ጋሼ አስፋው ከአዲስ አበባ ወደ ርባገረድ ቤተሰቦቹን ሊጠይቀን መጣ። ቢስክሌት እየነዳ ነበር የመጣው። ለእኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት የቴክኖሎጂ ውጤት ነበረች። በጣም ተገረምኩ፤ እኔ ብቻ አይደለሁም የተደነቅሁት መንደርተኛውም ጭምር ነበር የተገረመው። በትግርኛ የሰይጣን

ፈረስ (ዓረቢያ ሸይጣን) ብለዋት ነበር፡፡ ቀደም ብሎ የሚያውቁት ትሬንታ ኳትሮ በአራት ጎማ ነው የሚሄደው፡፡ ይህቺ ግን ምትሃት ስለሆነችባቸው ነው በሁለት ጎማ መጋለቢ የሰይጣን ፈረስ ያሰኛት፡፡

ጋሼ አስፋው ርባገረድ አጭር ጊዜ ሰነበተ፡፡ ከወላጆቼ ጋር አዲስ አበባ ይዞኝ እንዲሔድ ወሰኑ፡፡ በሚነሳበት ወቅት አብሬው ለመሄድ እኔም ቤተሰቦቼን ተሰናበትኩ፡፡ መለያየት የሚሉት የሕይወት አሠቃቂ ምዕራፍ በዚህ ጊዜ በእኔም ነፍስ ውስጥ ተከሰተ፡፡ እንደልብ እምበላበት፣ እምተኛበት አገር ለመድረስ ጉዞ ጀመርኩ፡፡

ከርባገረድ ዓድዋ ነበር መጀመሪያ የምንሔደው፡፡ እዚያ የወለላይ ታናሽ እህት አለች፡፡ አክስቴ ትበርህ (ታበራለች) ትባላለች፡፡ እርሷ ጋ አስራ አምስት ቀን ገደማ ተቀመጥን፡፡ ከርባገረድ ዓድዋ ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በእግር ተጉዘን ደረስን፡፡ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ትልቁ ከተማ ነው፡፡ አሁን ሳስታውሰው ዓድዋ በወቅቱ የአገር ቤት መንፈስ ነበር ያለው፡፡ የነዋሪው ቋንቋ፣ አለባበስ፣ ወግና ባህሉ እኔ ከማውቀው ማኅበረሰብ ብዙም የራቀ አልነበረም፡፡ ከተማው እጅብ ብሎ በቆርቆሮ ቤቶች ማሸብረቁ አስገርሞኛል፡፡

በዚያን ጊዜ የዓድዋ ከተማ ነዋሪ ደጋግሞ የሚዘፍናት አዲስ ዘፈን ነበረች፡፡ በዚያ ማኅበረሰብ አስተሳሰብ አንድ ሰው ሲያጠፋ፣ አንድ ዓይነት ነውር ነገር ሲሠራ ይነጠምበትና ሁሉም እየተቀ ባበለ ይዘፍንበታል» ጉሮሮውን አሳስሎ አፀዳዳና ዘፈንዋን በትግርኛ እንዴ ተወጣት፡፡

"እምባዬ ምባዬ ምባዬ
ዬይ ኀለዬ (ወይ ልጂዋ)
አብ ርባ ርባ ርባ ጥዑም ዘረባ" ብሎ አዜመልኝና ታሪኩን አጫወተኝ፡፡ "እምባዬ የሚባል ሰውዬ የሚስቱን እናት ወንዝ ዳር ድንገት ወሸማቸው፡፡ ይህችን ነውር የሕዝቡ ዓይን የሆኑ አዩበት፡፡ ገጣሚዎቹ ደግሞ ተጠበቡበት፡፡ በዜማ ተቀናብራ የዓድዋ ከተማ መማማሪያ ሆነች፡፡

ዓድዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ሻይ ጠጣሁ፡፡ እቤት የጣፈጠኝ መጣ ፈጥ! እቤት እንዴት ደስ አለኝ!" አለ ጭንቅላቱን ይዞ፣ አሁንም ያ ጣዕም የፈጠረበትን ስሜት በመዝረም እያብሰለሰለ፡፡ ትንሽ ቆይቶ

እርሱም ወጉን ቀጠለ፡፡ "ስለ ሻይ ርባገረድ ሳለሁ በወሬ ነበር የማውቀው፡፡ ዓድዋ መጥቼ መልኩና ጣዕሙን ሳይ ዝናው እውነት እንደሆነ አረጋገጥኩ፡፡ ርባገረድ ስንኖር ወለላይ እቤት ውስጥ ለራሷ ቡና ስታፈላ አውቃለሁ፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ ቡናን ስለማ ውቀው ሽታውም መልኩም ብዙ አላስገረመኝም፡፡ ሻዩ ግን ልዩ ሆነብኝ፡፡

@Amharicbookstore



ጤናማ እብደት ደግሞ አለልህ፡፡ ይህንን የምነግርህ ያክስቴ ልጅ እያታው፣ ኖራው የነገረችኝን ነው፡፡ በዚያን ዘመን ሻይ ብርቅ ነው፡፡ ሻይ ጠጥተህ ታውቃለህ? እየተባባለ መንደርተኛው ይጠያየቃል፡፡ የቀመሱት አጋንነው ይናገሩለታል፡፡ እቤት ቃናው! ደሞ ሲያዩት ሲያምር! ሲጣፍጥ! ይባልለታል፡፡ በሠፈራቸው እማማ ውዴ የሚባሉ ባልቴት ነበሩ፡፡ እማማ ውዴ ባላቸው ሞተዋል፡፡ ልጅም የላቸውም፡፡ ለመኖር ግን በቂ ገንዘብ አላቸው፡፡ ቤታቸውም ደህና ነው፡፡ ብቻ የሰፈር ልጆች እማማ ውዴ ምን እንደሚሠሩ ለማየት አንድ ቀዳዳ በግርግዳቸው ላይ በስተዋል፡፡ እማማ ውዴ ቤታቸው ውስጥ ሻይ እያፈሉ ነው፡፡ በእማማ ውዴ ቤት ግን ማንም አይያቸውም፡፡ ብርጭቆአቸው ውስጥ ሻይ ቀዱ፡፡ ውጫሬጮቹ እያዩ ተጎሻሸሙ፡፡ እማማ ውዴ ሻዩው ውስጥ ግማሽ ማንኪያ ስኳር ጨምረውበት አማሰሉት፣ ቀመሱት፡፡ ፉት ያሉትን ሻይ ከዋጡት በኋላ አፋቸው ውስጥ የቀረውን ቃናውን ያጣጥሙታል፡፡ "እይ ሲጣፍጥ! ግን ስኳር በዝቶበታል" ልጆቹ ውጪ ሆነው ምራቃቸውን ይውጣሉ፡፡

እማማ ውዴ ግን ብቻቸውን ከብቻቸው ጋር ሆነው ስኳር አበዛሁበት እንዴ? ይሉና ትንሽ ሻይ ይጨምራሉ፡፡ ይቀምሳሉ፡፡ ሻይ በዛ፣ ስኳር አነሰ፡፡ ሩብ ማንኪያ ስኳር ጨምረው የቀዱበትን አማስለው ይቀምሱታል፡፡ ስኳር ስለበዛበት ሻይ ይጨምሩበታል፡፡ እንደገና ይቀምሱታል፡፡ ስኳር ስላነሰው ሌላ ሩብ ማንኪያ ይጨም ሩበታል፡፡ በበዛ ባነሰ እያሳበቡ በብዙ ብልሐት ሞሉዋት፣ ያችን ብርጭቆ ሙሉ ሻይ በስኳር ጥጥት፣ ጭልጥ! ብቻቸውን ሆነው፡፡ ሁራዎቹ እያዩዋቸው፡፡ ይሉኝታን ፈርተው፣ ተሸቆጥቁጠው፣ የገዛ ሻይና ስኳራቸውን በራቸውን ዘግተው ለብቻቸው ሲጠጡ ማየት አንድ ዓይነት እብደት ማየት ነው፡፡ እማማ ውዴ ግን ጤነኛ የኅብረተሰብ አባል ናቸው፡፡ ሠርተው የሚኖሩ፣ ራሳቸውን የሚችሉ እመቤት ናቸው፡፡

ከዚያ ሁለት ሳምንት ዓድዋ ሰንብተን በትሬንታኳትሮ ተሳፍረን ወደ አስመራ ተጓዝን፡፡ ትሬንታኳትሮ እንደዛሬው ጊዜ የጭነት መኪና በቁልፍ አልነበረም ሞተሩ የሚነሣው፡፡ ከፊት ይከፈትና በአንድ ቆልማማ ብረት ያዞሩታል፡፡ ሞተሩ ሲነሣ ያጓራል፡፡ ከዚያም ሰዎቹ ይጫኑና ይጓዛሉ፡፡

አስመራ የጋሼ አስፋው አጎት ነበሩ፡፡ በጣም የሚያምሩ ረዥም ቀይ ሰውዬ ናቸው፡፡ ካደግኩም በኋላ ሽማግሌ ሆነው አይቻቸ ዋለሁ፡፡ ያ ልጅ ሆኜ ደስ ያለኝ ውበታቸው አብሮአቸው ነበር፡፡ አስመራ እንደገባን እሳቸው ያረፍንበት ሆቴል መጡና ቁርስ

«ፍሬታታ አምጣላት» ብለው አስተናጋጁን አዘዙት፡፡ በኋለኛው ሕይወቴ እንዳወቅሁት ፍሬታታ በጣሊያንኛ የተጠበሰ ዕንቁላል ማለት ነው፡፡ ፍሬታታውን በላሁ፡፡ እንደ እዚያ የሚጣፍጥ ምግብ የለም፡፡ እስካሁን እንኳን!" አለና ፍሬታታዋን ትንሹ ስብሐት ጣፍጦት ሲበላ እየታየው ሳቁን ለቀቀው፡፡

ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ይመጡና ፍሬታታ ያዙልኛል፡፡ እበላ ለሁ፡፡ እየጣፈጠኝ፡፡ ፍሬታታንና እኒያን የሚያምሩ አዛውንት ወዳ ጄን ተሰናብተን ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመርን፡፡

አዎን፡፡ አሁንም ጉዞው በትሬንታኳትሮ ነው:: የዚያን ጊዜ የሕዝብ ማመላለሻ አቶቡስ በደንብ አልገባም፡፡ ስለዚህ እንኳንም በትሬንታ ኳትሮ ተጓዝን!

ለምን? እንዴ! አስብ እንጂ፡፡ ልጅ ነበርኩ፡፡ ያጋጠመኝን ሁሉ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ ስለዚህ ትሬንታኳትሮ ቀስ ብሎ ስለሚሄድ አካባቢውን በደንብ እንድጎበኝ ዕድል ሰጥቶኛል፡፡ የአላማጣን ጠመዝማዛ መንገድ በዝግታ ስንወጣው ይታይህ፡፡ ሾፌሩን አሁንም አስታውሰዋለሁ፡፡ ጣሊያናዊ ነበር፡፡ ክንዱ ድረስ ሸሚዙን ጠቅልሎታል፡፡ ጋሼ አስፋው ደግሞ ጣሊያንኛ በደንብ ያውቃል፡፡ ያጫዋውታሉ፡፡ ሲያስኙቸው እኔንም ያጫውቱኛል፡፡

ጋሼ አስፋው በዚያን ጊዜ የት መሥሪያ ቤት እንደሚሠራ አላስታውስም፡፡ ሙያው የሂሳብ ሠራተኛ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የሂሳብ መኪና ስላልነበረ የሂሳብ ሥራውን የሚሠራው ሰው ነው፡፡ በራሱ ጭንቅላት ቀንሶ፣ ደምሮ፣ አባዝቶና አካፍሎ ያለምንም ስሕተት ቁጭ ያደርጋል፡፡ በዚህም ችሎታው በጊዜው ጥሩ ደሞዝ ነበረው፡፡ በወቅቱም ችሎታውን ሰዎች ሲያደንቁለት ሰምቻለሁ፡፡

ሁለት ሳምንት ያህል ከፈጀብን በኋላ በየመንገዱ እያደርን አዲስ አበባ ገባን፡፡ እንደልቤ የምተኛባት፣ እንደልቤ የምበላባት፣ ተምሬ እማውቅባት፣ ወልጄ የምስምባት፣ ለክፍያ ጥፌም የምታወቅባት ከተማ ገባሁ፡፡

ከጋሼ አስፋው ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ኖርኩ፡፡ ወንደላጤ ስለነበረ አልደላኝም፡፡ እሱ ከጓደኛው ጋር ነበር የሚኖረው፡፡ በየጊዜው ቤቱ የተለያዩ ሴቶች ይመጣሉ፡፡ ማታ እሱ አልጋ ላይ ተኝቼ ስጠብቀው እንቅልፍ ይወስደኛል፡፡ ጠዋት ስነቃ ጓደኛው አልጋ ላይ ራሴን አገኘዋለሁ፡፡ የሆነች ሴት አያለሁ፡፡

"ልጅህ ነው እንዴ?" ብላ ትጠይቃለች ሴትዮዋ::

@Amharicbookstore



"አዎን፡፡ እኔን አይመስልም?" ይላታል፡፡ ትንሽ ተቀላልደው ወንድሙ እንደሆንኩ ነግሯት ትሄዳለች፡፡ ይህቺን ሴት ድጋሚ ሳላያት ሌላኛዋ ተረኛ ትመጣለች፡፡ "

ይህንን አዲስ ሕይወት ሳልጠላውም፤ ሳልወደውም ጋሼ አስፋው ከአጎቱ ከአባባ ዛፉ ጋር ተነጋግረው እሳቸው ጋ እንድኖር ተወሰነ፡፡ አባባ ዛፉ መሐንዲስ ናቸው፡፡ የታናሽ ወንድማቸውን ልጅ ዳምጤ ምህረቱን ያሳድጋሉ፡፡ ዳምጤ ዛፉ እየተባለ ነው የሚጠራው፡፡ የአባባ ዛፉ ባለቤት እማማ ኪዳን ደግና ጥሩ ሰው ነበሩ፡፡ ቤተሰቡ ተስማማኝ፡፡ ከዳምጤ ጋርም ከበባችን ገጠመ፡፡ አቤት ቀልድ ሲያውቅ! ሁሌም አብረን መሳቅ ነው፡፡ አባባ ዛፉና እማማ ኪዳን ልጅ አስተዳደጉን ስለሚያውቁበት ደስተኞች ነን፡፡ ብዙ ዘመዶች የወገናቸውን ልጅ እናሳድግ ብለው አምጥተው ያሰቃያሉ፡፡ እንደ እንጀራ ልጅ መከራህን ነው የሚያበሉህ፡፡ ኩርኩምና መላላክ ይበዛል፡፡ የአባባ ዛፉ ቤት ግን እንደ እናትና አባቴ ቤት ደላኝ፡፡

እማማ ኪዳን ከአገር ቤት ከወጡ ብዙ ዓመታት ሆኗቸዋል፡፡ አገራቸው ይናፍቃቸዋል፡፡ እኔ ደግሞ በተቀባይ የልጅ አእምሮዬ በርካታ የአገር ቤት ጨዋታዎችን ይገኙ ነው የመጣሁት፡፡ እማማ ኪዳን ይጠሩና «ዝፈንልኝ» ይሉኛል፡፡ እዘፍንላቸዋለሁ፡፡ አንዳንዱ እርሳቸው ልጅ በነበሩ ጊዜ እየዘፈኑት ያደጉ ስለነበር አገራቸው ትዝ ብሏቸው ይተክዛሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በሁለታችን መካከል ጥልቅ ፍቅር ሰፈነ፡፡ በጣምም ስለወደዱኝ ስሜን ስብሐት ለአብ ማለታቸውን ትውትና 'ሻቺሬ' አሉኝ፡፡ በአማርኛ ዶቃ ማለት ነው:: እ! ጌጥ ሆንኳቸው::

"የአጎቴ ዛፉ ቤት አራት ኪሎ አካባቢ ነበር፡፡ በወቅቱ ማንም ሰው የግል ሬዲዮ ስላልነበረው አደባባይ ላይ የሬዲዮ ማይክሮፎን ተተክሏል፡፡ እዚያ ሄደን ወሬ ሰምተን መጥተን እኔና ዳምጤ ለቤተሰቡ እናወራለን፡፡ ጋዜጠኛ መሆን ጀመርን ማለት ነው፡፡ ሰዓት አባባ ዛፉ ነበራቸው፡፡ ከኪሳቸው አውጥተው ያያሉ፡፡ እኛ ግን እማማ ኪዳን አባባ ዛፉ ሳይኖሩ አራት ኪሎ ሄደን ሰዓት አይተን እንድንመጣ ይልኩን ነበር፡፡ ከዳምጤ ጋር አብሬ ወደ ከተማዋ እወጣለሁ፡፡ እሱ በሁለት ዓመት ስለሚበልጠኝ እና አዲሳባ ስለተወለደ፣እኔ የርሱ ደቀመዝሙር ሆንኩኝ፡፡ ያስቀኛል፡፡ ጨዋታ ያውቃል፡፡ ክፋት የሌለበት ተንኮል ፈጥሮ ማውራት እሱን ራሱንም ያስቀዋል፡፡ አማርኛውን ለእኔ እንዲገባኝ አድርጎ ሲተረጉመው ያስቀኛል፡፡ ለምሳሌ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ አቤሴሎም የሚል ስም አለ፡፡ እርሱ ሲተረጉምልኝ ~አቢሽልሆም (ትልቅ እቃቸው) ማለት ነው ብሎ በወቅቱ አስቆኛል::"

አለና በረጂሙ ተነፈሰ፡፡ በፍጥነት ካቲካላዋን ተጎንጭቶ ውሃዋን ተጉመጠመጠ ዋጠና "ዳምጤ ሞቷል! በደርጉ ጊዜ የአየር ኃይል ትራፊክ አዛዥ ነበር፡፡ የእነርሱን የጠር ኤሮፕላኖች ውረዱ፣ ተነሱ የሚለውን ትዕዛዝ የሚሰጠው እሱ ነበር፡፡ ምንም የእረፍት ጊዜ ኖሮት ስለማያውቅ ተገናኝተን አናውቅም፡፡ እንዳልም አንድ ጊዜ ተገናኝተን ለጥቂት ሰዓታት አብረን ሳቅን፡፡ ልጅነታችንን አነሣንና አወጋን፡፡ ይህ ቀን ለኔና በጣም ለምወደው ጠባቂ ወንድሜ የመጨረሻ ጊዜ ሆነ፡፡ በልብ ሕመም ድንገተኛ ሞት ይህችን ዓለም ተሰናበታት፡፡" አለና ፀጥ አለ፡፡

ከዚያማ ሕይወት ሂደቷን ቀጠለች፡፡ ሕይወት ልጅ ሆነህ ደግሞ የተለያዩ ልጆችን ታስተዋውቅሃለች፡፡ አንዳንዶቹ ሊያስደስቱህ የሚላኩልህ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ሳያውቁትም ቢሆን ሊያሰቃዩህ የተፈጠሩ ይሆናሉ፡፡ የአባባ ዛፉ ባለቤት እማማ ኪዳን የእህታቸውን ልጅ ከእኛ ጋር ያሣድጉ ነበር፡፡ ዋህድ ትባላለች፡፡ ቀይ ቆንጆ ልጅ ነች፡፡ በማላውቀው ምክንያት ጠምዳኝ ነበር፡፡
"አፍንጫህን ትሬንታኪትሮ ደፍጥጦታል" ትለኛለች፡፡
እኔን ወደ ኋላ ተመልሰህ ስታየኝ ባላገር ነኝ፡፡ ከተማ ስገባ 'ኮምፕሌክስ' ሰዎች ይንቁኛል የሚል ስሜት ነበረብኝ፡፡ የመጨረሻ አሰቀያሚ እንደሆንኩ ይሰማኝ ጀመር፡፡ ሐናን እስካፈቀርኳት ጊዜ ድረስ ስሜቱ አብሮኝ የኖረ ይመስለኛል፡፡ በሕይወቴ ውስጥ ሕድአት ተከሰተች፡፡ ሕድአት ትርጓሜው እርጋታ ማለት ነው፡፡ ያክስቴ ልጅ ሕድአት አባቷ ሞተው እንደኔ ጋሼ ሐጎስ ቤት ነው ያደጎችው፡፡ ሉል ገብሩም እዚያው ቤት አለች፡፡ ቆንጆ ሳቂታና ተጫዋች ነች፡፡ እኔ ደግሞ ከሴቶች ጋር መጫዋት፣ መሳቅ እወዳለሁ፡፡
አንድ ቀን ሉል እየሳቀች "አቤት ስብሐት! ስትስቅ ዓይኖችህ እንደ ከከብ ነው የሚያበሩት!" አለችኝ፡፡
ወዲያው ዳንኩ፡፡ ያቺ ቀይ ቆንጆ ከረዳ ዋህድ ያሳደረችብኝ የደፍጣጣነት በሽታዬ ታከመ፡፡ ሉል በሽተኛውን ማዳንዋን አታውቀውም፡፡ በሽተኛው ለካ እሱ ራሱም ሳያውቀው ለአስቀያሚነቱ ፈውስ ፍለጋ እየተንከራተተ ኖሯል፡፡ እምዬ ማርያም ሉል ገብሩን ላከችና ሕመምተኛውን ፈወሰችው፡፡

ከዚያማ ኑሮን ቀጠልናት፡፡ ሕይወት ትጓዛለች፡፡ እኛም ጥላዋ ሆነን አብረን ነጎድን፡፡ ሚጢጢው እኔም የአዲስ አበባውን ሕይወት ለመደው፡፡ የእኔ እናት ወለላይን "ያሳደገችኝ እናቴ ናት" የሚላት ጋሼ ሐጎስ መጣ፡፡ ከልጅነት መንደር ከርባገረድ ወለላይ ስትሸኘኝ



እንዳሳደገችው ውለታውን ለመመለስ እኔን እንዲያሳድገኝ አደራዋን ያስተላለፈችለት ሰውዬ ነው ጋሼ ሐጎስ፡፡ እኔም አደራውን ሳልነግረው ሊያሳድገኝ ወሰደኝ ነው። እነ ሕድአትን፣ ሉልንና ኤፍሬምን ያወቅኳቸው፡፡ በዚያ ጊዜ ስዊድሽ ሚሽን (ሽሮ ሜዳ አካባቢ) ትምህርት ቤት ገባሁ፡፡
አጎቴን በሁለት ጎኑ ነው የማየው። በአንድ ጎኑ ሳደንቀው፣ በሌላ ጎኑ እንቀዋለሁ፡፡ በማደንቀው ልጀምርልህ፡፡ እሱንኳ እንደ አባት ሆኖ ስለራሱ አጫውቶን አያውቅም፣ ከወንድሜ ከተወልደ ብርሃን በተባራሪ የሰማሁትን ነው የማጫውትህ፡፡
አያ ሐጎስ ሕፃን እያለ አስመራ ይማር ነበር፡፡ በወቅቱ ኤርትራን የሚያስተዳድሩ ጣሊያኖች ነበሩ፡፡ ሙሶሊኒ በዘመኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ነበር፡፡ ሕፃናቱን አያ ሐጎስን ጭምር ጣሊያኖች ሰብስበው ለሙሶሊኒ ፎቶ ሰላምታ ያሰጧቸው ነበር፡፡ መሬት ጥለው ባነጠፏት በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ እንዲተፉ ያደርጉም ነበር፡፡ የሐጎስ ተራ ደረሰ፡፡ በሙሶሊኒ ፎቶ ላይ ምራቁን ተፍቶ ለኢትዮጵያ ባንዲራ ሰላምታ ሰጠ፡፡ አሰሩት፡፡ አሰቃዩት፡፡ ይህ የደረሰበት እንግዲህ የአስርና የአስራ አንድ ዓመት ልጅ ሆኖ ነው፡፡ በዚህ አደንቀዋለሁ፡፡ የራሱ እምነት ስላለው፡፡ በኋላም (እኔ ባላጣራሁት መንገድ) ትምህርቱን እንዲቀጥል ፈቅደውለት ለክረምቱ እረፍት ወደ ዓድዋ ሲመለስ እናቱ ሞተዋል፡፡ ይሁን እንጂ 'ሳይደግስ አይጣላም' እንዲሉ አበው፣ የእኔ እናት፣ የእሱ የብዙ ታላቅ እህት፣ እናቱ ሆና አሳደገችው።
ጋሼ ሐጎስ ለልጆች የምሕረት፣ የፍቅር ዓይን አልነበረውም፡፡ ልጆች ለእሱ ሰው ሳይሆኑ ካልተመቹት የሚገረፉ ናቸው፡፡ የብቻዬን ልናገርና፣ አንዳንዴ አንድ ነገር ሲጠፋ፣ ከማጣራቱ በፊት በኩርኩም ኳ! ወይም በጥፊ ጧ! ያደርገኛል፡፡ ጉዳዩ የምናልባት ምናልባት ዕድል ፈቅዶልኝ እውነቱ ላይ ከደረሰበት፣ "መጀመሪያ አትነግረኝም ነበር?!" ብሎም ወደ ጉዳዩ ይሄዳል፡፡ ነገም ግን እንደ ትናንትናው ነው፡፡ በንዲህ ዓይነት እብደት ነው ሁላችንንም ያሳደገን፡፡

አቤት! እርሱ ቤት እግዜር ሲልከኝ በእትዬ ዘርትሁን ካሰኝ፡፡ ሳቅና ጨዋታ ነበር ከእሷ ጋር ያሳለፍኩት ሕይወት፡፡ እኔ የባላገር ቀልድ ሳወራላት ትስቃለች፡፡ ከማሕፀኗ እንደወጣ ልጅ ብቻ ሳይሆን ልክ እንደ እኩያ ጓደኛዋ የትልቅ ሰው ሕይወትም ታጫውተኛለች፡፡ በኋላ እንድጥፍ ፈግዜሩ መርጠኛል አደል? እቺ አባባል አባ ኪዳነ ማርያምን አታስታውስህም? ደስ እያለኝ እንደ ተረት እሰማታለሁ፡፡ ለምሳሌ እትዬ ዘርትሁን እንደ አጫውተችኝ ወንደ

@Amharicbookstore

ላጤው ወንድሚ ጋሼ አስፋው እሳት የላሰ አራዳ ነበር፡፡ በጊዜው በውቤ በረሃ ውስጥ ከታወቁት ሦስት ወይም አራት ዳንሰራዎች መካከል አውራው ነው፡፡ እንደደሰነ፣ እንደተጫወተ፣ እንደጠጣ፣ ደስ ያለችውን ሴት እንዳቀፈ ኖረ፡፡ እኔ በልጅ ዓይኔ ሳስታውሰው ደሞ ረጅምና ኀባጣ ነው፡፡ በኋላ የአጥንት ካንሰር ታሞ ሞተ፡፡ ጋሼ አስፋውን ሳስበው ሞት እርሱን የሚኀበኘው በመጠጥ ወይም በሲጋራ ሰበብ ነው ብዬ ነበር፡፡ ሞት ግን እኛን በክንፉ አሣፍሮ ለመውሰድ በርካታ መንገዶች አሉትና፣ ጋሼ አስፋውም በአጥንት ካንሰር ተሸኘ፡፡ የት ጋ ነበርኩ?... ውሉን አስያዘኝ፡፡

እ! እትዬ ዘርትሁን እንዲህ የምወዳት ሸርኬ ነበረች፡፡ እንካ ሲኒማ ግባ ብላ ገንዘብ ትሰጠኝ ነበር፡፡ አቤት! ደግሞ እትዬ ዘርትሁን መልኳም ቁመናዋም ሲያምር! ድምፅዋ ደግሞ እንዴት ያምራል መሰለህ!

በትዬ ዘርትሁን ላይ ሌላ የማጫውትህ አለ፡፡ አንድ ቀን ሳሙና በውሃ እያፈላች ልብስ ታጥባለች፡፡ እንደመሰለኝ ደግሞ ከጎኑ ወጥ በሌላ ምድጃ ጥዳ ሽንኩርት እያቁላላች ነው፡፡ ይህንን የጥድፊያ ተግባሯን ስታከናውን ጋሼ ሐጎስ መጣ፡፡ እንዳያት "ምን ነካሽ? ልብስ ማጠብና ምግብ ማብሰል አብሮ ጎን ለጎን ይሠራል?" ብሎ ከመንገር ይልቅ እንዴት! አለና በጥፊ አጮላት፡፡ አቤት የተናደድኩት ንዴት! ይሄ ከርሱ የማልጠብቀው ነበር፡፡ እሷም ጥፊዋን ቀምሣ ቻለችው፡፡ ዕለታት አለፉ፡፡ ከሌሎች ሴቶች ጋር አንሶላ እንደሚጋፈፍ ወሬ ሰምታለች፡፡ አንድ ቀን የገዛ ሽጉጡን ከትራሱ ሥር ላጥ አድርጋ አነጣጠረችበት፤ ቃታ ሳበች፡፡ ተተኮሰ፡፡ ለጥቂት ሳተችው፡፡ ከዚያ በኋላ ጋሼ ሐጎስ በፍቅሯ ከነፈ፡፡

ጋሼ ሐጎስ የልጅነትን ዕድሜ የመገንዘብ ችግር ነበረበት፡፡ በኤምባሲ ሥራ ከግሪክ አገር ለዕረፍት መጣና ምግብ ተሰብስበን እንበላለን፡፡ በልቼ ከጠገብኩ በኋላ «እንካ የእህቴ ልጅ» ቢለኝ፤ «ጠግቤያለሁ!» እያልኩት አጎረሰኝ፡፡ ሁለተኛ ሊደግመኝ ሲል «ጠግቤያለሁ!» አልኩት፡፡ የግድ እንደገና ሊያጎርሰኝ ሞከረ፡፡ «በቃኝ!» አልኩት፡፡ እንደመሰለኝ ከመናደዱ የተነሣ ከንፈሩ ይንቀጠቀጣል፡፡ በንዴት ፍጥጥ ብዬ ሳየው ዓይኑን ሰበረ፡፡ ከዚያ በኋላ ሆን ብዬ ለፍተሻ ዓይኑን አየዋለሁ፡፡ ዓይኑን ይሰብራል፡፡ ነፍሱ ነፍሴን ፈራቻት አልኩና፣ ለራሴ ካቅራራሁ በኋላ፣ ጋሼ



ሐጎስን መፍራት ረገፈልኝ፡፡ አልፈራውም፣ ግን ብሞክርም ልወደው አልቻልኩም፡፡ ሲበዛ ያሳዝነኛል'ንጂ፡፡ "

ጋሼ ሐጎስ ስንተኛ ፀሐፊ እንደሆነ ረሣሁት፣ ጃንሆይ ሾመውት ወደ ግሪክ አገር የኤምባሲ ባልደረባ ሆኖ ሄደ፡፡ ጃንሆይንም፣ "ልጆቼን አዳሪ ትምህርት ቤት ያስገቡልኝ" ሲል ለመናቸው፡፡ እሳቸውም ፈቀዱልን፡፡ እኔም ቀጣዩ የሕይወቴ ምዕራፍ ወደሆነው ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ገባሁ፡፡

***

፬

# ወርቃማ ዓመታት

እኛ ትናንትና መጥተን ወደ ነገ እንጓዛለን፡፡ ያለፈው ኑሮዋችንም ሰሙን ቀይሮ አብሮን ይጓዛል፡፡ ሲያሚው ትውስታ ወይም ትዝታ ይሆናል፡፡ በትዝታ መርከብ እንንሳፈፍ፡፡

የትምህርት ቤት፣ የአስተማሪዎችና የተማሪዎች ትውስታዎቼ ዛሬም በውስጤ ሕያው ናቸው፡፡ ወደኋላ መለስ ብዬ የአእምሮዬን ቀሻ ስጎበኝ ትዝታዎች በደማቋ ጨረቃ ብርሃን፣ በጉልህ ከዋቦች ውበት ታጅበው ይታዩኛል፡፡

ጃንሆይ በዚህ ብርሃን ድባብ ጎልተው ይታዩኛል፡፡ በመጀመሪያ ስማቸው ይጠራ በነበረው በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ነው የተማርኩት፡፡ ትምህርት ቤቱን ጃንሆይ ከአባታቸው በወረሱት ርስት ላይ፣ በገዛ ገንዘባቸው ነው ያሰሩት ሲባል እንሰማ ነበር፡፡ እየተመላለሱ በአባታዊ ዓይን እያዩ ይጎበኙን ስለነበረ፣ የሰማነውን ሁሉ እናምናለን፡፡

ጃንሆይ አራት መቶ የምንሆን አዳሪ ተማሪዎችን በወር አንድ ጊዜ አመሻሽ ላይ ጨለማው ለዓይን ያዝ ሲያደርግ ብቅ እያሉ ይጎበኙን ነበር፡፡ የወራቱን ፍራፍሬ አስጭነው ይመጡ ነበር፡፡ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ መንደሪን ወይም ወይን ይሆናል ያመጡልን፡፡

በራት ሰዓት ነበር የሚደርሹት፡፡ ከፀሎት በፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ምዕራፍ ይሰበካል፡፡ ሰባኪው አባ ጠዪም፣ ሸውራራ ነበሩ፡፡

@Amharicbookstore

ሁሌም የሚሰብኩት የአብርሐምን ታሪክ ነበር፡፡ የማት ቀዮር በመሆንዋ ይሰለችናል፡፡ ሥላሴዎች እንዴት አብርሃምን እንደጎበኙት ያወጉንና ማሳረጊያቸው፣ ጃንሆይ የእኛ የተማሪዎቹ እንግዳ በመሆናቸው የሥላሴዎቹ ተምሳሌት አድርገዋቸው በመተረክ ያሟርጋሉ፡፡ ራት መብላት እንጀምራለን፡፡ ጃንሆይም እየተዘዋወሩ አንዳንዶቻችንን ያነጋግሩናል፡፡ ያነጋገሩትን አይረሱም ይባል ነበር፡፡ አቤት ሲመጡ የሚሰማን ደስታ!

እሳቸው መጥተው እኛን መጎብኘት ደስ እንደሚለን እሳቸውም ወደኛ መምጣቱ ሳያስደስታቸው አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ልጆች ይወዳሉ፡፡ ነብስ ካወቅኩ በኋላ ስለ ጃንሆይ ስሰማ ከልጆቻቸው ልዑል መኮንንን በጣም ይወዱት ነበር፡፡ ጃንሆይ የተከሡ ዕለት በእግር በፈረስ ልዑል መኮንን ተፈልጎ መጥቶ ቢሮዋቸው ወይም ባሉበት ቦታ እንዲያጫውታቸው ይደረጋል፡፡ ከአንድ ሩብ ሰዓት በኋላ አካባቢው በሳቅ ያውካካል፡፡

አቤት ልዑሉ የሞተ ዕለት ለቅሶዋቸው፡፡ ምናለ የዚያን ዕለት ባላየኋቸው፡፡ የጃንሆይ ሐዘን የዚያን ዕለት ነው ገዝፎ የታየኝ፡፡ ለቀስተኛው፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ በግራና በቀኝ ሆነው እንባውን ያፈሳሉ፡፡ እሳቸው በመካከል እያለፉ ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሲጓዙ አየኋቸው፡፡ አቤት የዚያን ዕለት እንዳሳዘኑኝ! የምር ልጅ ስለሚወዱ የፍቅራቸውን ያክል ሐዘናቸውም መራር መሆኑ ይታይ ነበር፡፡

ከተወለድን በኋላ ሁለተኛ አባት መምረጥ የሚቻል ቢሆን የኔታ ገብረ መድህን አባቴ እንዲሆኑ ነበር የምመርጠው፡፡ ለምን? 'ከአነጋገር ይፈረዳል፣ ከአያያዝ ይቀደዳል' አሉ አበው፡፡ የኔታን ላሳይህ? በዚህ ትውስታዬ ዋሻ በጨረቃዋና በከዋክብቱ ብርሃን የኔታ ገብረ መድህን በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየፃፉ ግዕዝ ሲያስተምሩን ይታዩኛል፡፡ 'እኒህ ሰውዬ ቅዱስ ናቸው' የሚለውን ስሜት ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳደሩብኝ የኔታ ገብረ መድህን ነበሩ፡፡ በኋለኛው ህይወቴ፣ በጉርምስና ዕድሜ "ለልበ ንጹህ፣ ሁሉ ንጹህ ነው" የሚለውን የአረብኛ ምሣሌ ሳነብ፣ ለራሴ ' ልክ እንደ የኔታ ገብረመድህን' አልኩ፡፡ ብልግና የሚባል ነገር በእሳቸው ቤት በጭራሽ የለም፡፡ በጭራሽ!" አለና በሐሣብ እልም አለ፡፡

የመጀመርያ ቀን ግዕዝ ሲያስተምሩን በግስ እርባታ አስጀመሩን፡፡ ነፍሀ ማለት ነፈሰ ማለት ነው፡፡ ግሱ ሲረባ ነፍሀ፣ ይነፍህ፣ ይንፋህ፣ ይንፋህ ነው፡፡ ትርጓሜው በአማርኛ ነፈሰ፣ ይነፍሳል፣ ይነፍስ ዘንድ፣ ይንፈስ ማለት ነው፡፡ በሚቀጥለው የትምህርት ክፍለ



ጊዜ ሲያስተምሩ ገና ጠመኔዋን ሲያነሱ "የኔታ ነፍሀ አልገባኝም?" አላቸው አንድ ተንኮለኛ ተማሪ፡፡

የኔታ ወደ እሱ ሳይዞሩ፤ እንደ ልማዳቸው እንደ ሕንድ ጭንቅላታቸውን እየወዘወዙ "ምን ያቅታል?" አሉ "ነፍሀ፣ ይነፍህ፣ ይንፋህ፣ ይንፋህ" አሉ፡፡

ተማሪው ሁሉ በሳቅ አውካካ፡፡ ወደ ጠያቂው ዞሩና፣ ምንም ዓይነት ቁጣ ወይም ተግሳፅ በሌለበት ድምፅ "እህ! ይንፋህን ፈልገህ ነው? በል ይንፋህ!" አሉትና ወደ ሰሌዳቸው ተመለሱ፡፡

የኔታ ገብረ መድህን ሲቆጡ አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ እሳቸው ሲፅፉ እኛ ስንገለብጥ እንንጫጫለን፡፡ ጫጫታው ከልክ በላይ ሲሆን፣ ወደ እኛ ይዞሩና፣ ራሳቸውን እየወዛወዙ "ዝንጀሮዎች! ኢትዮጵያ እናንተን አፈራች!" ብለውን ወደ ሰሌዳቸው ይመለሳሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ጫጫታው በኃይል ከመጠን በላይ ይሆናል፡፡ ይኸን ጊዜ ጠመኔያቸውን አስቀምጠው ወደ እኛ ዞረው፤ "እኔ እዚህ ክፍል አላስተምርም" ብለውን ከክፍላችን ይወጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ክፍሉ በፀጥታ ይዋጣል፡፡

በላቸውና አንድ ሁለት ትላልቅ ልጆች ይወጡና የኔታን ይቅርታ ለምነው፣ "አይለመደንም" ብለው፣ መልሰው ያመጧቸዋል፡፡ የግዕዝ ትምህርታችን ይቀጥላል፡፡ በሚቀጥለው የግዕዝ ክፍለጊዜ ግን ይቅርታ መለመናችንን ረስተን ያው ውጫጭ ነንና መንጫጫታችን አይቀርም፡፡ የኔታ ግን ሺ ጊዜ ይቅርታ አድርገውልናል፡፡

አንድ ቀን የኔታ ፈተና ይፈትኑናል፡፡ በለጠ በአጠገቡ ሲያልፉ ጠራቸው፡፡ ተጠጉት፡፡ የፃፈውን እያሳያቸው "የኔታ ይሄ ልክ ነው?" አላቸው በሹክሹክታ፡፡ "እዚህጋ አንድ ረስተሃል! " አሉና ቦታውን በጣታቸው ጠቆሙት፡፡ በለጠም ትዝ አለችውና መልሷን ወረቀትዋ ላይ አሰፈራት፡፡

የኔታ ገብረ መድህን ይህን ያህል የዋህ፣ ገር፣ ቸርና ለሕፃናት ተገቢ ትክክለኛ መምህር ነበሩ፡፡ የሚወልደንን አባት አንመርጥም፡፡ ከተወለድን በኋላ ሁለተኛ አባት መምረጥ የምንችል ቢሆን ኖሮ እኔ የኔታ ገብረ መድህንን ነበር የምመርጠው ያልኩህ ለዚህ ነው፡፡

ጋሼ ስብሐት ፈገግ ብሎ እያየኝ "አንድ ቀን ቴዎድሮስ ትናንት እሁድ ያየሁትን ብነግርህ አታምንም፡፡ "የኔታ ገብረ መድህን የ-ሐንስ ቤተክርስቲያን አጠገብ እንዲት ቆንጆ ሻዮሊን አቅፈው ሲሄዱ አየሁዋቸው" አለኝ እየማለ፡፡ አላመንኩትም፡፡ ግን የኔታ ገብረመድህን ሻዮሊን ይዘው ቢሄዱ ምን አለበት? አንድ ደስ ያላቸው ቦታ ላይ ቁጭ ብለው ሻዮሊናቸውን ቢጫውቱስ? ማን ይከለክላቸዋል?

"በግድ በገና ወይም መሰንቆ መሆን አለበት?" ብሎኝ መልሴን ጠበቀ፡፡

እዚህ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ሦስተኛ ክፍል ነው የገባሁት፡፡ እንደ ዕድለኝነት የምቆጥረው ከተለያየ ዘር ከተውጣጣን ኢትዮጵያውያን ጓደኞችን ስላፈራሁኝ ነው፡፡ እኔ በተወለድኩበት አገር እያለሁ በዓለም ላይ ያለ የሰው ዘር ትግሬ ብቻ ነበር የሚመስለኝ፡፡ ዓዲ እስላም ስሄድ ምን ዓይነት ልዩ ልዩ ነገሮች እንዳጋጠሙኝ ነግሬሃለሁ፡፡ አሁን ደግሞ ከልጅነቴ አኳያ አዲስ አበባ ውቅያኖስ ሆነችብኝ፡፡ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ደግሞ ባህር ሆነ፡፡ ትንሽዬ ኢትዮጵያን ፈጠረልኝ፡፡ አማራ፣ ጉራጌ፣ ሶማሌ፣ ጋሞ... ከሆኑ ጓደኞች ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የምወደውም የምጠላውም አለ፡፡

ይኼውልህ! ሆዳሙ ዘለቀ ብቅ አለ፡፡ በዚያን ጊዜ እንደዛሬው ሁሉ የአንድ ክፍል ተማሪዎች በአንድ ዕድሜ ላይ አልነበርንም፡፡ ዘለቀ የክፍላችን ልጅ ቢሆንም አብዛኞዎቻችንን በዕድሜ ይበልጠናል፡፡ እንግዲህ ማክሰኞና ሐሙስ ቁርስ ዳቦ፣ ዕንቁላል ጥብስ ከሻይ ጋር ይቀርብልናል፡፡ ቦዩ የዕንቁላሉን ፍርፍር በሳህን ላይ አውጥቶ ያልፋል፡፡ ዘለቀ ዙሪያውን ይገላመጥና ቶሎ የአንዳንዱን ልጅ የዕንቁላል ፍርፍር ሳህን ሳብ አድርጎ ምራቁን ተፍቶበት በፍጥነት እቦታው ይመልሳል፡፡

ዕንቁላሉ ላይ የተተፋበት ልጅ መብላቱን ትቶ ይነጫነጫል፡፡ ዘለቀ የራሱን ዕንቁላል ይጨርስና እንደገና ይገላመጣል፡፡ ከዚያ በፍጥነት ያልተበላውን ዕንቁላል ወደ ፊቱ ይስብና ባዶውን ሳህን ወደ ልጁ ፊት ይመልሳል፡፡ የተበላበት ልጅ አንጀቱ ሲያርር ዘለቀ ሆዳሙ ሁለት ቁርስ ይወጥቃል፡፡ ማክሰኞና ሐሙስ የዕንቁላል ቁርሳችን በዚህ ዓይነት ግብር ይጠናቀቃል፡፡

አቀማመጣችን በሁለት ተርታ ነው፡፡ ስድስት በዚያኛው ወገን፣ በዚህ ደግሞ ስድስት ልጆች እንቀመጣለን፡፡ አንድ ማታ ራታችንን በልተን ጠግበን ሙዞችንን ልንልጥ ስንል ዘለቀ እንዲህ አለ "እንወራረድ፡፡ አስራ ሁለት ሙዝ ብቻዬን በልቼ እጨርሳለሁ፡፡"

ተወራረድን፡፡ ራቱን ጥግብ ብሎ እንደበላ እናውቃለን፡፡ ጉዳዩ በቅርብ ስለሚመለከተን አሥራ አንዳችንም ትኩር ብለን እያየነው ነበር፡፡ የመጀመሪያዎቹን አራት ሙዞች እየተደሰተ ልጦ እንከት አደረጋቸው፡፡ የሚቀጥሉትን ሲልጥ ቀስ፣ በጣም ቀስ፣ እጅግ በጣም ቀስ እያለ ሄደ፡፡ ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንተኛው ጋ ሲደርስ ግንባሩ ላይ ላብ ቸፈፍ አለ፡፡ ፊቱን ስናየው ከመደሰት ወደ ማማረር፣ ከዚያም ወደ ማቅለሽለሽ ተለዋወጠ፡፡ በከፍተኛ መስዋዕትነት አስራ

@Amharicbookstore



አንድ ሙዝ ፈጀ፡፡ አንዲት ቀረች፡፡ ላጣት፡፡ በብዙ ቀስታና ስቃይ ጥቂት በጥቂት እየጎረሰ ግማሽ ሙዝ በላ፡፡ ግማሽዋ ስትቀረው ከእጁ ለቀቃት፤ ወደቀች፡፡ ተሸነፈ" አለና ዘለቀ በዓይነ ሕሊናው እየታየው ሳቀ፡፡ እንባውን በሶፍት ወረቀት እያበሰ "እንዲህ እያስገበረንም እኛ ውራዎቹ ዘለቀን አንጠላውም፡፡ እንዲያውም እንወደዋለን፡፡ ዘለቀ በአሁኑ በአዛውንትነት ዕድሜዬ እንግዳዬ ሆኖ ቤቴ ቢመጣ መኝታዬን ለቅቄ መሬት ተኝቼ የማስተናግደው ሰው ነው፡፡"

ሙት! አሁን ትዝ ሲለኝ ዘለቀ ይወደናል፡፡ ሌሎች ልጆች ሊመቱን ካሉ ያግዘልናል፡፡ በዕድሜ ቢበልጠንም ወንድማችን ነው፡፡ ነበሩ'ንጂ፡፡ እነ ግርማ ጭራቁ፡፡ የውጭው ጠላት፡፡ በጉልበቱ አገር አሳጣን፡፡ በአጠገቡ ስናልፍ በኩርኩም ኳ! ያደርገናል፡፡ እኔና ተስፋዬ ግሡሡ ጠላቶቹ ነበርን፡፡ ተስፋዬ እንደምታውቀው ቀይ ነው፡፡ "ክሉ፣ ክልስ አህያ መልስ" ይልና ኳ! ያደርገዋል፡፡ አንድ ቀን ምግብ ቤት ቁርስ እየበላን ሳለ "ዛሬ ግርማን ማናፈጥ አለብኝ" አልኩ፡፡ ምናልባት ከተስፋዬ ጋር እንዴት ላናፍጠው እንደምችል ተማክረን ይሆናል፡፡ ጊዜው ይርቃል፡፡ ተስፋዬ በዚያን ጊዜ ሲኒማ ይገባ ስለነበር እንዴት መግጠም እንዳለብኝ አሳየኝ፡፡ አደፋፈረኝ፡፡ ከግርማ ጋር መጋጠሚ ቁርጥ ሆነ፡፡ ይህንን ያህል ስዘጋጅ ግርማ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ አንድ ቀን ልክ ከምግብ ቤት ስንወጣ "እናትክን!" አልኩና ከደረጃ ዘልዬ እላዩ ላይ ተከመርኩበት፡፡ አንዴ ቷ! አደረኩት፡፡ ደነገጠ፡፡ ገላጋይ መካከላችን ገባ፡፡ ምንም ሳይመታኝ ዳንኩ፡፡ ከዚያ በኋላ ከግርማ ጭራቅ ጋር ተከባበርን፡፡ ልቀጥልልህ" አለኝ፡፡ የሚያስደስተውን ሲያወጋ "ልቀጥልልህ" የሚለው ባሕሪ አለው፡፡

ጃንሆይም እኛን ልጆቻቸውን በደንብ አጥግበውን ተንከባክበውን ስለሚያሳድጉን ከመፍሳት አልፈን በጉልበት ከሚበልጡን ጋር እንዲህ እስከ መግጠም እንደርሳለን። የፈስ ነገር ካነሳን አንድ ልጅ ነበር። በዕድሜም በክፍልም ይበልጠኛል። አብረን ነው የምንማረው። ይህ ልጅ ከክፍል ጓደኞቹ ጋር "ከምትገምቱት በላይ እፈሳለሁ፣ ብትፈልጉ ቁጠሩ።" ብሎ ማንዛረጡን ጀመረ። ቆጠሩ፣ ሰማንያ ስድስት ጊዜ መድፉን አይተኩስ መሰለህ?" አለና ጋሼ ስብሐት ባለፈ ትዝታው ሳቀ። "ጃንሆይ በሥጋ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በመንፈስም ሙሉ ሊያደርጉን የደከሙ መሪ ነበሩ።"

በዚያን ጊዜ በኛ ዕድሜ በጣም የሚወደደው የታርዛን ፊልም ነበር፡፡ ታርዛን የነብር ቆዳውን አገልድሞ ራቁቱን ነው የሚሄደው፡፡ ሰውነቱ በስፖርት የዳበረ አካል ነው ያለው፡፡ ታርዛንና ጓደኛው ጦጢት በጫካው ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ጠላት ሲመጣባቸው ከዛፍ ዛፍ

በሐረግ ተንጠላጥለው ሽው ይላሉ፡፡ የአዕዋፉን፣ የአራዊቱን ቋንቋ አሳምረው ያውቃሉ፡፡ ይኼን ስናይ እንደ ታርዛን ነው መኖር እንላለን፡፡ ታርዛን ጩቤ ነው የሚታጠቀው፡፡ ከአንበሳ፣ ከነብር፣ ከአዞ፣ ከዘንዶ፣ ወይ ከእኩይ ሰው ጋር ሲጣላ በጩቤ ወግቶ ይገድለዋል፡፡

ታርዛን ጩቤውን ሲሰካባቸው (ማናቸውም ቢሆኑ) ሲኒማ ቤቱ በጭብጨባ፣ በጩኸትና በፉጨት ይቀልጣል፡፡ እኛም የታርዛን 'ቲፎዞዎች' በትምህርት ቤታችን ዳርቻ ላይ ወደ በቀለው መለስተኛ ጫካ እንገባና በገመድ ወይ በልጥ ሐረግ ሠርተን ከአንዱ ዛፍ ቅርንጫፍ ወደ ሌላው ዛፍ ቅርንጫፍ እንዘላለን፡፡ ታርዛን ለመሆን፡፡

አንድ ቀን ቴዎድሮስ፣ አርአያ፣ ገበየሁ፣ ሳህሌና ገብረ ኢየሱስ ተማከሩ፡፡ ተዘገጃጅተው እንደ ታርዛን በደን ውስጥ ለመኖር ጠፍተው ወደ እንጦጦ ጫካ ሸፈቱ፡፡ ለአራት ቀናት ማንም ሳያገኛቸው፣ እነርሱም ሳይመለሱ ሰነበቱ፡፡ አሁን ሳስበው ዳይሬክተራችንና አስተማሪዎቻችን እንዴት ተጨንቀው ነበረ ይሆን? እላለሁ፡፡

በአምስተኛው ቀን እነ ቴዎድሮስ "ታርዛንነቱ ይብቃን" አሉ፡፡ "ከሚርበንና አውሬም ከሚበላን ትምህርት ቤታችን ብንመለስ ይሻለናል" ብለው መጡ፡፡ ጉድ ተባለ፡፡ ይቅርታ ለመኑ፡፡ ይቅር ተባሉ፡፡" ብሎ ጢሙን እያፍተለተለ ተከዘና "አሁን ሳስበው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ጀዝዊቶቹ የተሟላ ዕውቀት ነበር የሚያቀርቡልን፡፡

ግዕዝ፣ አማርኛ፣ እንግሊዘኛ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ጂኦግራፊና ሌሎቹን የቀለም ትምህርት ዓይነቶች ብቻ አልነበረም የሚያስተምሩን፡፡ የእንጨትና የቴክኒክ ሥራም ይጨምር ነበር፡፡ የአናጢ ትምህርት መምህራችን ፈረንሣዊ ካናዳዊ ነው፡፡ ሻርፖንቲዬ ይባላል፡፡ ትርጉሙም አናጢ ማለት ነው፡፡

ለምንፈልግ ተማሪዎች በሳምንት አንድ ቀን ማታ የሙዚቃ ማድመጥ ፕሮግራም አለን፡፡ የነሞዛርትን፣ የነቤይቶቨንን፣ ወዘተ 'ክላሲካል' እናደምጣለን፡፡

ፍላጎቱ ላላቸው ተማሪዎችም የመጻሕፍት እድሳት ያስተምራሉ፡ በዚህ ትምህርት ቤት ነው እንግሊዝኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ የሌላ አገር ሰዎች በተቃለለ እንግሊዝኛ የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብ የጀመርኩት፡፡ ካደግኩ በኋላ ያገኘኋቸውን ታላላቅ ደራሲያን ሥራዎች በዚህ ትምህርት ቤት ቤተ-መጻሕፍት ነው የተዋወቅኋቸው፡፡ የልቦለድ ፍቅር በዚያው አደረብኝ፡፡ እኔም የዚሁ ትምህርት ቤት ልሣን በነበረው ተፈሪ መኮንን 'ኢንሣይን' በሚባል ጋዜጣ ላይ መጻፍ ጀመርኩ፡፡ የጋዜጣዋም አዘጋጅ ሆኛለሁ፡፡ በወቅቱ የአስራ አንደኛ



ክፍል ተማሪ ነበርኩ፡፡ ነገር ግን እኔ የማነብበትን ጊዜ የሚሻማብኝ ሥራ እጠላለሁ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሰለቸኝ፡፡ ስለዚህ ለአስተማሪዬ ችግሬን ነገርኩ፡፡ ገባነለኝ፡፡ ደራሲ መሆን እንደምችል የገባኝ ምናልባት ያኔ ይሆናል፡፡

በትምህርት ቤታችን ሰባት የመጫወቻ ሜዳዎች ነበሩ፡፡ ሁለት የመረብ ኳስ፣ ሌላው የቅርጫት ኳስ፣ ወዘተ ናቸው፡፡ እኔ ታዲያ አልፎ አልፎ ካልሆነ ሁሉም ውስጥ የለሁበትም፡፡ ቦይ ስካውት ነበርኩ፡፡

ከእኛ ትምህርት ቤት ጥቂት ደቂቃዎች ተጉዘን እቴጌ መነን ትምህርት ቤት አለ፡፡ እዚያ የሚማሩት ሴቶች ልጆች እንደ እኛ እነሱም አዳሪዎች ናቸው፡፡ እንዳልከው ከሆድ ጥያቄ ቀጥሎ የፆታ መስተጋብር ነውና የተፈሪ መኮንን ተማሪዎች ስለ እቴጌ መነን ተማሪዎች እናስባለን፣ እናልማለን፣ እናወራለን፡፡ ወሬው ደግሞ አይሰለችም፡፡ እንዲያውም ደስ ይለናል፡፡ እነሱም ይቀኙልናል፡፡

"ቲሪሪም፣ ቲሪሪም የሚለው ታንቡሩ
ተፈሪ መኮንን ግባልኝ በበሩ" እያሉ

እየዘፋፈኑ ወደእኛ ይናፍቃሉ፡፡ እንደ አጋጣሚ ይሆንና እኛ የተፈሪ መኮንን ልጆች እቴጌ መነን ውስጥ እህት ወይም የአክስት፣ የአጎት ልጅ አልያም የሰፈር ልጆች ይኖሩናል፡፡

የአክስቴ ልጅ እዚያ ትማር ነበር፡፡ እሷ ስትነግረኝ "ከቁርስ በኋላ ተሰልፈን የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርን ዘምረን ወደየ ክፍላችን እንገባለን፡፡ ስንማር እናረፍድና እረፍት እንድንወጣ ደወል ይደወላል፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ ባቡር መንገድ እሚያሳየው ዋናው በር ጋ ለመድረስ እንሽቀዳደማለን፡፡ የቀደምነው ልጆች አላፊ አግዳሚውን በሚያሳይ ቦታ እንቆማለን፡፡ የተቀደሙት ከኋላ ቆመው እየተንጠራሩ ብጥስጣሽ ትርኢት ያያሉ" ብላኛለች፡፡

'ውስጡን ለቄስ' ሆኖ ነው እንጂ እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ ግን ይህቺ ሁሉ እንዲህ ያሰፈሰፈች ቡቃያ ሔዋን ዋና ዓላማዋ ክብርዬ በዚህ ሲያልፍ ለማየት ነው፡፡ ከሚጎማለለው ወንዳ ወንድ ውበቱ የምኞትና የሕልም ስንቅ ልትሰንቅ ፈልጋ ነው፡፡

"ያውና መጣ!" ይባባል በልብ፡፡ ወጣቱ ከአሜሪካን አገር ቻርልስ አትላስ የተባለ የሰውነት ግንባታ ባለሙያ የሚያሳትመውን መጽሔት እያጠና፣ ልምምድ እያደረገ ድንቅ የሆነ የሴት ልጅ ልብ የሚያጠፋ ገላ ገንብቷል፡፡

እየቀረባቸው ሲመጣ ኳሱን አውልቆ ባንድ እጁ ከትከሻው በስተኋላ አንጠልጥሎ የደረቱንና የክንዶቹን የዳበሩ ጡንቻዎች

@Amharicbookstore

የሚያሳይ ጉርድ እጅጌ ሸሚዝ ለብሷል፡፡ እየተንቀባረረ በፊታቸው ሲያልፍ፣ እንደ ቄጤማ እንደ ባህር ዛፍ በሚወዛወዝ ድምፅ፡

*"ባሰራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ፋብ ጉዳይ*
*ለምን ትመጣለህ፣ እንደ ነብሰ ገዳይ?"*

እያሉ ይዘፍኑለታል፡፡ ፀሐይዋና የትምህርት ፕሮግራሙ የሚያሳዩት ጊዜ ገና ከሟቱ አራት ሰዓት ቢሆን ነው፡፡ ጎረምሳው ብርቅዬ ገላውን እያጎማለለ ካለፈ በኋላ በርሱ ትርኢት ሙቀት ለጥቂት ፈንድታ የነበረችው አበባ ሔዋን ተመልሳ ሚጢጢ እምቡጥ ትሆንና ወደየጨዋታዋ ትበተናለች፡፡ እኛም አዳሞቹ እንደዚያው፡፡

በዚህ ውብ ተወዳጅ የልጅነት ጊዜዬ አንድ ነገር የጎደለኝ ነበር፡፡ ወለላይ ትናፍቀኛለች፡፡ ትዝ ስትለኝ መኝታ ቤት እገባና አልጋዬ ላይ ተደፍቼ ስቅስቅ ብዬ አለቅሳለሁ፡፡ ናፍቆቱ፣ በዚህ መንሰቅሰቅ ይከፈልልኛል፡፡

እነሆ ይህንን አብሮኝ ያረጀ ትዝታዬን ሳወጋህ ዕድሜዬ ከስድሣዎቹ ፊቅ ብሏል፡፡ በእነዚያ ወርቃማ ዓመታት ታፈራኋቸው ጓደኞቼ በአሁኑ ጊዜ ብዙዎቹን አላገኛቸውም፡፡ አልፎ አልፎ ከአንዳንዶቹ ጋር እንገናኛለን፡፡ ሕይወት ሰምሮላቸው ዘርተው የቃሙ፣ ወልደውም የሳሙ አሉ፡፡ የዚያኑ ያህል ሕይወት አክንባሎዋን ደፍታባቸው የቡሔ ዳቦ የሆኑም አስተውያለሁ፡፡

ከብዙ ዓመታት በኋላ ግርማ ጭራቅ ያ አንበሳ ጉልበቱ ከድቶት በከራንች እየተሽመደመደ ሲሄድ አገኘሁት፡፡ የልጅነት ቂሜ ፀሐይ እንዳረፈበት ጤዛ ተኖ፣ በይቅርታ ተተካና በጣም አዘንኩ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከአብሮ አደጎቼ ሲያስፈልገን ተፈላልገን የምንገናኘው ከተስፋዬ ገሠሠ ጋር ነው፡፡ የዚያን ዕለት ቀኑን ሙሉ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ስናወጋ እንውላለን፡፡ ብዙ ጊዜ ሳይሆን አልፎ አልፎ የማገኘው ዘውዱ ወሰኔን ነው፡፡ ዘውዱ በጃንሆይ ዘመነ-መንግሥት ዘረ-ቱጃር ነበር፡፡ ያውም የወሎ መሀመዶች ልጅ ነው! በአሁኑ ጊዜ ግን ደህይቶዋል፡፡ ሁሌም ሲያገኘኝ የሚለኝ አንዲት ቃል ናት፡፡ መጀመሪያ እንዳየኝ ይጠመጠምብኛል፡፡ እኔም አፀፋውን እመልስለታለሁ፡፡ ከዚያም "ስብሐት ዘ ግሬት! አሁን ለኢትዮጵያ ከአንተ በቀር ማን አላት?! አንድ አንተ ብቻ እኮ ነህ ያለህት" ይለኝና ጥቂት ቆይቶ "በተጨማሪም እኔ!" ይለኛል፡

@Amharicbookstore



፳

## «ኮሌጅን በጠስናት»

ውስጥህን የሚያበራልህ አስተማሪህ ነው፡፡ በሐቅ ወይም በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ አይተኸው የማታውቀውን እውነት የሚያሳይህ አስተማሪህ ነው፡፡ እሱ ስላስተማረህ አንተን ተአምረኛ ሰው እንድትሆን ያስችልሃል፤ የተማረ አቅሙ ውስጥህ ካለ፡፡ እንዲህ ዓይነት ድንቅ የሆኑ አስተማሪዎች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት ተዓምረኛ አስተማሪ ያጋጠመኝ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ገብቼ ነው፡፡ የታሪክ መምህሬ ነበር፡፡ ሚስተር ሶሎዱኺን ይባላል፡፡ ቁመናው ረጅም፣ ዓይኖቹ ሰማያዊ ሲሆኑ መነፅር ያደርጋል፡፡ አገሩ ሩሲያ ነች፡፡

ስለ ሕይወት ታሪኩ በጣም ትንሽ ነው የምናውቀው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪ ሆኜ ሳገኘው በዚያን ወቅት ሩሲያ ውስጥ ቦልሼቪክ አብዮት ፈንድቷል፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስተር ሶሎዱኺን በጊዜ ከሩሲያ ካልወጣ አብዮታውያን ሊገድሉት ሆነ፡፡ እንደ ደርጋውያን እርምጃ ሊወስዱበት እንደሚችሉ ጠረጠረ፤ ስለዚህ ተሰደደ፡፡ የከበለለባት አገር ከሩሲያ ጋር በዘር፣ በባህልና በጂኦግራፊ አህትማማች ናቸው፡፡ እዚያም መፅናኛው የምትሆን በዕድሜ የምትበልጠው ሴት አጋጠመችው፡፡ የሁለቱም ዕጣ ፈንታ አቀራረባቸውና፡ ከአገሩ እንዴት እንደወጣ ነገራት፡፡

"እዚህም ኮሚኒስቶች ገና ሥልጣን አልያዙም እንጂ በብዛት አሉ" አለችው፡፡

"ገና ሥልጣን አልያዙም ስትዪኝ፣ መያዛቸው አይቀርም ማለትሽ ነው?" ሚስተር ሶሎዱኺን ጠየቀ፡፡

"ምን ነካህ? ያገርህና የአገሬ ታሪክ እኮ በጣም ይቀራረባል፡፡ ይመሳሰላል፡፡ እኔና አንተም የነዚህ አገሮች ዜጎች በመሆናችን ወደ የትም ወለምዘለም ሳንል የማዕበሉ ወቅት ያልፍ፡ እንደሆን እዚሁ ተደብቀን እንየው?"

"የሚያልፍ አይመስልሽም ግን?"

የሚያሳይ ጉርድ እጅጌ ሸሚዝ ለብሷል፡፡ እየተንቀባረረ በፊታቸው ሲያልፍ፣ እንደ ቁጤማ እንደ ባህር ዛፍ በሚወዛወዝ ድምፅ፡

*"ሳስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሩብ ጉዳይ*
*ለምን ትመጣለህ፣ እንደ ነብሰ ገዳይ?"*

እያሉ ይዘፍኑለታል፡፡ ፀሐይዋና የትምህርት ፕሮግራሙ የሚያሳዩት ጊዜ ገና ከሟቱ አራት ሰዓት ቢሆን ነው፡፡ ጎረምሳው ብርቅዬ ገላውን እያጎማለለ ካለፈ በኋላ በርሱ ትርኢት ሙቀት ለጥቂት ፈንድታ የነበረችው አበባ ሔዋን ተመልሳ ሚጢጢ እምቡጥ ትሆንና ወደየጨዋታዋ ትበተናለች፡፡ እኛም አዳሞቹ እንደዚያው፡፡

በዚህ ውብ ተወዳጅ የልጅነት ጊዜዬ አንድ ነገር የጎደለኝ ነበር፡፡ ወለላይ ትናፍቀኛለች፡፡ ትዝ ስትለኝ መኝታ ቤት እገባና አልጋዬ ላይ ተደፍቼ ሰቅስቅስ ብዬ አለቅሳለሁ፡፡ ናፍቆቴ፣ በዚህ መንሰቅሰቅ ይከፈልልኛል፡፡

እነሆ ይህንን አብሮኝ ያረጀ ትዝታዬን ሳወጋህ ዕድሜዬ ከሰድሣዎቹ ፊቅ ብሏል፡፡ በእነዚያ ወርቃማ ዓመታት ታፈራኋቸው ጓደኞቼ በአሁኑ ጊዜ ብዙዎቹን አላገኛቸውም፡፡ አልፎ አልፎ ከአንዳንዶቹ ጋር እንገናኛለን፡፡ ሕይወት ሰምሮላቸው ዘርተው የቃሙ፣ ወልደውም የሳሙ አሉ፡፡ የዚያኑ ያህል ሕይወት አክንባሎዋን ደፍታባቸው የቡሔ ዳቦ የሆኑም አስተውያለሁ፡፡

ከብዙ ዓመታት በኋላ ግርማ ጭራቅ ያ አንበሳ ጉልበቱ ከድቶት በክራንች እየተሽመደመደ ሲሄድ አገኘሁት፡፡ የልጅነት ቂሜ ፀሐይ እንዳረፈበት ጤዛ ተኖ፣ በይቅርታ ተተካና በጣም አዘንኩ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከአብሮ አደጎቼ ሲያስፈልገን ተፈላልገን የምንገናኘው ከተሰፋዬ ገሠሠ ጋር ነው፡፡ የዚያን ሰሰት ቀኑን ሙሉ በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ስናወጋ እንውላለን፡፡ ብዙ ጊዜ ሳይሆን አልፎ አልፎ የማገኘው ዘውዱ ወሰኔን ነው፡፡ ዘውዱ በጃንሆይ ዘመነ-መንግሥት ዘረ-ቱጃር ነበር፡፡ ያውም የወሎ መሀመዶች ልጅ ነው! በአሁኑ ጊዜ ግን ደህይቷል፡፡ ሁሌም ሲያገኘኝ የሚለኝ አንዲት ቃል ናት፡፡ መጀመሪያ እንዳየኝ ይጠመጠምብኛል፡፡ እኔም አፀፋውን እመልስለታለሁ፡፡ ከዚያም "ስብሐት ዘ ግሬት! አሁን ለኢትዮጵያ ከአንተ በቀር ማን አላት?! አንድ አንተ ብቻ እኮ ነህ ያለሀት" ይለኝና ጥቂት ቆይቶ "ቡተጨማሪም እኔ!" ይለኛል፡

@Amharicbookstore



# ፳

## «ኮሌጅን በጠስናት»

ውስጥሀን የሚያበራልህ አስተማሪህ ነው፡፡ በሐቅ ወይም በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ አይተኸው የማታውቀውን እውነት የሚያሳይህ አስተማሪህ ነው፡፡ እሱ ስላስተማረህ አንተን ተአምረኛ ሰው እንድትሆን ያስችልሃል፣ የተማረ አቅሙ ውስጥህ ካለ፡፡ እንዲህ ዓይነት ድንቅ የሆኑ አስተማሪዎች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት ተዓምረኛ አስተማሪ ያጋጠመኝ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ገብቼ ነው፡፡ የታሪክ መምህሬ ነበር፡፡ ሚስተር ሶሎዱሂን ይባላል፡፡ ቁመናው ረጅም፣ ዓይኖቹ ሰማያዊ ሲሆኑ መነፀር ያደርጋል፡፡ አገሩ ሩሲያ ነች፡፡

ስለ ሕይወት ታሪኩ በጣም ትንሽ ነው የምናውቀው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪ ሆኜ ሳገኘው በዚያን ወቅት ሩሲያ ውስጥ በልሼቪክ አብዮት ፈንድቷል፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስተር ሶሎዲሂን በጊዜ ከሩሲያ ካልወጣ አብዮታውያን ሊገድሉት ሆኑ፡፡ እንደ ደርጋውያን እርምጃ ሊወስዱበት እንደሚችሉ ጠረጠረ፤ ስለዚህ ተሰደደ፡፡ የኮበለለባት አገር ከሩሲያ ጋር በዘር፣ በባህልና በጂኦግራፊ እህትማማች ናቸው፡፡ እዚያም መፅናኛው የምትሆን በዕድሜ የምትበልጠው ሴት አጋጠመችው፡፡ የሁለቱም ዕጣ ፈንታ አቀራረባቸውና፣ ከአገሩ እንዴት እንደወጣ ነገራት፡፡

"እዚህም ኮሚኒስቶች ገና ሥልጣን አልያዙም እንጂ በብዛት አሉ" አለችው፡፡

"ገና ሥልጣን አልያዙም ስትይኝ፣ መያዛቸው አይቀርም ማለትሽ ነው?" ሚስተር ሶሎዱሂን ጠየቀ፡፡

"ምን ነካህ? ያገርህና የአገሬ ታሪክ እኮ በጣም ይቀራረባል፡፡ ይመሳሰላል፡፡ እኔና አንተም የነዚህ አገሮች ዜጎች በመሆናችን ወደ የትም ወለምዘለም ሳንል የማዕበሉ ወቅት ያልፍ እንደሆን እዚሁ ተደብቀን እንየው?"

"የሚያልፍ አይመስልሽም ማን?"

"አይመስለኝም።"

እውነትም እንዳለችው ሁሉቱም በየሄዱበት የሚፈነዳባቸው የኮሚኒስት አብዮት በቡልጋሪያ ፈነዳ፡፡ ሚስተር ሶሎዱሂንና ከለላ የሰጠችው ወዳጁም ለአደጋ ተጋለጡ፡፡ ሁለቱም ከቡልጋሪያ ተሰደው ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አዲስ አበባ ገቡ፡፡

ሚስተር ሶሎዱሂን በዩኒቨርሲቲ ኮሌጃችን የታሪክ መምህር ሆኖ ተቀጠረ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በትዝታዬ ውስጥ የሚገኙት የሚስተር ሶሎዱሂን የተለያዩ ሥዕሎች ላሳይህ።

ታሪክ ስንፈተን የተርም ፈተና ወቅት ነበር፡፡ በዓመት ሦስት ተርም ነው የነበረው፡፡ ያን ጊዜ እኔ ደግሞ መጻሕፍት ቤት ውስጥ ያገኘኋቸውን ልቦለዶችና ሌሎች መጻሕፍት ጊዜዬን እየተሻሙት ስለነበር፣ ከተሰጠን ስድስት ጥያቄዎች መመለስ የቻልኩት አንዷን ብቻ ነበር፡፡ ሌሎቹን ነካክቼ ከማጨመላልቀው ቢቀርብኝ ይሻላል ብዬ ባዶ ተውኳቸው፡፡

አሁን በእርግጠኝነት ውጤቱን አላስታውሰውም፡፡ የፈተናዬ ውጤት ከመቶ ሰባ፣ ወይም ሰባ አምስት ነበር፡፡ ሥራዬን አሳምሬ ስለማውቀው ማግኘት የነበረብኝ 20 በመቶ ቢሆን ነው፡፡ ስለዚህ የተሳሳተ ስለመሰለኝ የፈተና ወረቀቴን ይዤ ሚስተር ሶሎዱሂን ቢሮ ሄድኩ፡፡ የማይገባኝን ማርክ እንደሰጠኝ ስነግረው እንዲህ አለኝ፣

«የኔ ፈተና ዓላማው ተማሪው ላቀብለው የሞከርኩት የታሪክ መንፈስ ገብቶታል ወይ? ነው፡፡ መንፈሱ ምን ያህል እንደገባህ ከአንዷ ጥያቄ አመላለስህ ተረድቻለሁ፡፡ የተቀረው ጥያቄ፣ አንብብ የተባለውን አንብቧል ወይ? ምን ያህልስ ያስታውሳል? ነው፡፡ እሱም ያስታውቃል፡፡ ስለዚህ አንተ ከፍተኛ ማርክ አልኩው እንጂ የሰጠሁህ የሚገባህን ነው" አለኝ፡፡

ይህንን እያለኝ ሚስተር ሶሎዱሂን ሲፅፍበት የቆየውን 'ፋውንቴን ፔን' የሚባል ቀለም የሚመጥ የዘመኑን ብዕር ሊከድን ሲል የከዳኑን ቀዳዳ ሳተው፡፡ በሶስተኛው ሙከራ ከደነው፡፡ ዓይኑን አየሁት፡፡ ደነገጥኩ፡፡ ለካስ አንድ ዓይኑ 'አርቲፊሻል' ነው፡፡ እውነተኛ ዓይን እንዲመስል ተደርጎ በጥበብ ቀለም በመሠራቱ ከርቀት ለሚያየው ሰው፣ ሰው ሠራሽ መሆኑ አያስታውቅም" አለና አትኩሮ አየኝ፡፡

ጢሙን በቁዘማ እየላገ በጣም ተክዞ "መምህሬ አንድ ዓይና ነው፡፡ መልስ የማላገኝላቸውና ምንጊዜም አብረውኝ የሚኖሩ ጥያቄዎች፡፡ ዓይኑን ምን አጠፋው? በእንርሱ የትርምስና ዘመን በትንሽ ጠብ በሚነሣ ፍልሚያ ምክንያት? ወይስ ጠላቶቹ 'ቡቶርች' ሰቅለው ሲገርፉት? እግዜር ይወቅላቸው!" አለና በረጅሙ ተነፈሰ፡፡



የሁላችንንም የታሪክ ፈተና ውጤት ሚስተር ሶሎዱሂን በጥቁር ሰሌዳው በምናውቀው የእጅ ጽሕፈታቸው በአንድ ወረቀት ላይ ፅፈው ይለጥፉታል፡፡

1. Super geniuses ከመቶ እስከ ዘጠና አምስት ያመጡ ናቸው፡፡ ከእነሱ ስም ዝርዝር በኋላ
2. Geniuses እነዚህም በቁጥር ይገለፃሉ፡፡
3. Excellent work...የስም ዝርዝር
4. Good...
5. Normal Pass... የተቀረነው ተማሪዎች የሁላችንም ስም ዝርዝር

ከላይ ከአንድ እስከ አምስት ያስፈርኩት የሚስተር ሶሎዱሂን የርዕማን ሊቃን ጠበብትና የሌሎች የስም ዝርዝሮች እንዲህ እንደነበሩ በምናብ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ትውስታዬ ግን በዚህን ያህል የጊዜ ርቀት እርግጠኛ መሆን እንዴት ይቻላል? እያለችኝ ነው፡፡

አንድ ቀን ከክፍል ውጪ ሚስተር ሶሎዱሂንን ከበነው ቆመን በታሪክ፣ በስነጽሑፍ ላይ እንወያየለን፡፡ እሱ በአፍ መፍቻ ቋንቋው አንብቦት እንደ ወተት፣ ማር ጥሞት አሁንም እየደጋገመ የሚያነሡ ውን አሌክሳንደር ፑሽኪንን ጠይቀነው እንዲህ አለን፡፡

"አይቱ የናንተ አገር ሰው ከሆነው ከፑሽኪን ጋር ብታስተያዩት ሼክስፒር የሚያለቅስ ሕፃን ነው።"

ስለ ፑሽኪን ከንቱ አሟሟት፣ ገና በጎልማሳነቱ በማይረባ ምክንያት በፍልሚያ ስለመቀጨቱ፣ በዚህ ጥልቀትና ብስለት ላይ አስር ዓመት ቢጨምር ኖሮ የሚፅፋቸውን የቃላት ምትኃቶች በምናብ እያስጎበኘን ሲተርክልን ከቆየ በኋላ የክፍላችን ልጅ ፍኖትን በወዲያ ማዶ ስታልፍ አይትና እንዲህ አለን "Gentlemen ሴት ልጅ 'ሱፐር ጂኒዬስ' ናት ብዬ በመፃፌ በጣም አዝናለሁ፡፡ ይኸዋ፤ ይህች ልጅ ሱፐር ጂኒዬስ ሆና አገኘኋት፡፡ ሱፐር ጂኒዬስ ናት ብዬ ከመመስከር ሌላ ምርጫ የለኝም፡፡ ያሳዝናል" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ "እንዲህ ዓይነት የወንድ አቋም በኋላኛው ዘመን 'የወንድ ትምክህተኝነት' ተብሎ ሲዘለፍ ሰምተናል፡፡

ሚስተር ሶሎዱሂን ታሪክ ሲያስተምረን ልክ የትናንትናን ያህል ቀርቦ ወለል ብሎ ጎልቶ ይታየኛል፡፡ ሰዎች ጽሕፈት እንዴት እንደፈጠሩ ሲነግረን በጥቁር ሰሌዳው ላይ በፍጥነት በጠመኔ ግመል ሰራ፡፡ አጠገቡ አራት የቆሙ መስመሮች፡፡ አግድም አንድ መስመር ይሰርዛል፡፡

ነጋዴ ነው ጽሕፈትን የጀመረው፡፡ በኋላ ካህናቱና ደባትሩ ወረሱት፡፡ በጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ወይም በከብት ቆዳ ላይ ይህንን

@Amharicbookstore

ሠርተህ የሳምንት መንገድ ርቆ ወደሚነግድ ጓደኛህ ትልክለታለህ፡፡ ይህም አምስት ግመል ላክልኝ ማለት ነው፡፡

መቶዎችና ሺዎች ዓመታት ካለፉ በኋላ አንዱ "ሱፐር ጂኒየስ ብልጭ ይልበትና" ብሎ ሚስተር ሶሎዱሂን የግመሉን ቁመቱን ያጠፋና ራሱና አንገቱ ብቻ ሲታየን "ይኸው ግመል፡፡ አሁንም ሺዎች ዓመታት ካለፉ በኋላ የሚቀጥለው "ሱፐር ጂኒየስ" ከግመሉ ራስና አንገት ይኸው የናንተን የግዕዝ ፊደል ገ የሚባለውን ፈጠረ፡፡ ገ ገመል፡፡

ለምዕራባዊው ዓለም የመጀመሪያ የሆነውን ልበለድ በግጥም የጻፈው ደራሲ ጊልጋሜሽ ስለተባለው ገጸ ባሕርይ ዙፋኑን ትቶ የሞት መድኃኒት ፍለጋ ስለሄደው ሚስተር ሶሎዱሂን እንዲህ ይነግረናል፡፡

ጊልጋሜሽ የፍቅር አምላክ የሆነችው ኢስታርቴ ከሰማይ ወርዳ አብረኸኝ እደር ስትለው ተንቀባረረባትና "እኔ ለአደን እንጂ ለሴት ጊዜ የለኝም" ብሎ አሳፈራት፡፡ እሷም ጊልጋሜሽን እንዲገድልላት ኤንኪዱ የተባለ የአውሬ ጠጉር የለበሰ ግዙፍ ሰው ፈጠረችና ጊልጋሜሽ ለአደን የሚሄድበት ጫካ ውስጥ ለቀቀችው፡፡

ጊልጋሜሽና ኤንኪዱ ጫካ ውስጥ ተገናኝተው ግማሽ ቀን ሙሉ ተዋጉ፡፡ ጊልጋሜሽ አንድ ፎቅ ቤት የሚያክል ቋጥኝ አንስቶ ይወረውርበታል፡፡ ኤንኪዱ ትልቅ ዛፍ ነቅሎ ይወረውርበታል፡፡ በመጨረሻ ጊልጋሜሽ ያሸንፍና ኤንኪዱን እንደ ምርኮ ይዞት ወደኡር ከተማው ይመለሳል፡፡

ጊልጋሜሽና ኤንኪዱ የልብ ጓደኛሞች ሆኑና አብረው አደን መሄድ ጀመሩ፡፡ አደኑ እንደ ማር ጣፈጣቸው፤ ቆይቶም ሱስ ሆነባቸው፡፡

አሁን ደግሞ ኢስታርቴ ጊልጋሜሽን ለማጥፋት ሁምባባ የተባለ ሰው መሳይ አውሬ ፈጥራ እዚያው ጫካ ውስጥ ለቀቀችው፡፡ ጊልጋሜሽና ኤንኪዱ ከሁምባባ ጋር አንድ ቀን ሙሉ ሲዋጉ ውለው ድል አደረጉት፡፡

ሚስተር ሶሎዱሂን ከአሌክሳንደር ፑሽኪን ይበልጥ በጣም የሚጠቅሰው ዊሊያም ሼክስፒርን ነበር፡፡ "የሥነ ልቦና ሱፐር ጂኒየስና ከዚያም በላይ የነበረው ሼክስፒር እንደሚለው፤ ገሃነም ራሱ እንኳን ንቀት ካሳየናት ሴት እኩል ንዴት የለውም፡፡ ሴትዮዋ አምላክ ስትሆን ደሞ ጊልጋሜሽን እንዴት እንደቀጣችው እዩልኝ፡፡" እንደ ከረምቦላ ጨዋታ በስፖንዳ ጊልጋሜሽን ስትመታው ኤንኪዱ ላይ እያኮሳ እየመነመነ አስነባብቶ የሚገድል በሽታ ላከችበት፡፡

@Amharicbookstore



የኤንኪዱ አሰቃቂ አሟሟት ጊልጋሜሽን እስከወዲያኛው ለወጠው፡፡ ኃያሉ ንጉስ ጊልጋሜሽ ዙፋኑን ለቀቀ፡፡ መንኖ ወጣና የሞት መድኃኒት ፍለጋ ሄደ...

ሚስተር ሶሎዱሂን እያስተማረን አራት ወርቃማ ዓመታት በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ኖርን፡፡ ከትምህርት ዓለም ወጥተን ወደ ሥራው ዓለም ተሰማራን፡፡ በዚህ ጊዜ ከሐና ጋር ቤተሰብ መሠረትናል፡፡ የኮሚኒስቶች አብዮት በዚህች ቅድስት ምድር ላይ ፈነዳ፡፡ ውቃቢው አብዮት በፈነዳ ቁጥር የሚበረግገው ሚስተር ሶሎዱሂን ጓዙን ቀረቃቀበ፡፡ ባለውለታው ባለቤቱን አስከትሎ ለዓመታት ካስተናገደችው አገር፤ ጓደኛቸውን ገልጠው እንዲያዩ ካስተማራቸው ተማሪዎቹ ተለይቶ ከአዲስ አበባ በአውሮፕላን ተሣፍሮ ወደ አውስትራሊያ ኮበለለ፡፡ እኔ አሁን ሳስበው ለባለቤቱ እንዲህ ሳይላት አይቀርም፤

"የእኔና ያንቺ ዕጣ እንዲህ ሆኖ ይቅር? ልክ እንደ ነገደ ይሁዳ ዕጣችን አልሆነም? ሁልጊዜም መባረር፤ ምንጊዜም መሰደድ፡፡"

እሷን ስጠረጥራት እንዲህ ሳትለው አትቀርም "እኔ በበኩሌ የትም ብሔድ ምድራቱ እንደሆን ምድር ናት፡፡ ሁልጊዜም በሔድኩበት ይገፍህ የምሔደው አገሬ አንተ ነህ" ብላው ይሆናል...እንደገና ወደ እኔ 'ዲፓርትመንት' ልመለስልህ?

አንድ የእኛው አገር ሰው የEducation Departement Dean ሆነ፡፡ ዶክተር ነው፡፡ አሁን ስሙ ጠፋኝ፡፡ ገጠመኙ ብቻ ነች ውስጤ የቀረችው፡፡ ከእርሱ በፊት ለነበረው ዲን አማርኛ መናገር እችላለሁ በቂዬ ነው፡፡ የአማርኛ ሊቅ መሆን አልፈልግም አልኩት፡፡ በምትኩ ሌላ ትምህርት እንድማር ፈቀደልኝ፡፡ ተምሬ ጨረስኩ፡፡ ልመረቅ ስል ይህ አበሻው ዶክተር ጠራኝና ያንን የቀየርኩትን የትምህርት አይነት አለመውሰዴን ነገረኝ፡፡ ቀደም ብዬ ከዚያን ጊዜ ዲን ጋር ተነጋግሬ ኮርስ አስቀይሬ ማጠናቀቄን ነገርኩት፡፡ "በፍፁም አይሆንም፡፡" ሲል ችክ አለ፡፡ የፍልስፍና መምህራችን ሚካኤሊደስ ይባል ነበር፡፡ ሄጄ ነገርኩት፡፡ እውነተኛ ፍልስፍና ነበር ያስተምረን የነበረው፡፡ እዚያው እኔ ባለሁበት ለዶክተሩ ደወለለት፡፡ ያኛው ምን እንደሚል ባልሰማም ይህኛው "እንዴት አይመለከትህም? ይህ አገር እኮ ሶቭየት ራሺያ አይደለም!" ብሎት ስልኩን ዘጋ፡፡ እንደ በፊቱ እንድቀጥል አመቻቸልኝ፡፡ ምንም ሳልቸገር በሰላም ትምህርቴን ጨረስኩ፡፡

ሚካኤሊደስ ቀጥተኛና ዲሲፕሊን አክባሪ ጀዝዊት እንደነበረ አስታውሳለሁ፡፡ አንድ ጊዜ ለንደን ውስጥ የመኪና መንገድ ለመሻገር ቆሟል፡፡ አጠገቡ ሁለት ጀዚዊቶች ምንኩስናቸው የሚከለከ

ለውን ብልግና ሲያወሩ ሰማ፡፡ አንዳቸውን በጥፊ አጮለውና፣ በራሳቸው ቋንቋ በፈረንሣይኛ ገሰፃቸው፡፡

ቢያስፈልግ ነዋ! በመጀመሪያ የጆዝዊት እምነት ተከታይ አለመሆን፡፡ ከሆኑም ደንብ ማክበር እንዳለባቸው ሊያስተምራቸው ነው ወገራው ያስፈለገው፡፡

ተስፋዬ ገሠሠ አብሮኝ ነበር፡፡ ሌሎችም አሉ፡፡ አንደኛ ተራ ተማሪ የነበረው ተስፋዬ ኮሌጅ ስንገባ ቢራቢሮ ሆነ፡፡ በሄድክበት ሣቅ ከሰማህ ተመልከት፣ እዚያ አካባቢ ተስፋዬ አለ፡፡ አንዴ ምግብ ቤት ብድግ አለና ጠረጴዛው ላይ ቆመ፡፡ ንግግር አደረገ፡፡ የእዜኔ ምን እንዳለ አሁን አላስታውስም፡፡ ተማሪው ከዳር እስከዳር በሣቅ አውካካ፡፡

ከሰለሞን ዴሬሣ ጋር ኮሌጅ ነው የተዋወቅነው፡፡ ገና እንደ ተዋወቅን ከነባችን ገጠመ፡፡ ማንበብ፣ መወያየት፣ ውቤ በረሃ ሄዶ መደነስ፣ ሲኒማ አብሮ መግባት ተጨማሪ የጓደኝነት ማጠናከሪያ ሆኑ፡፡ የእኔና የእርሱን ጥምረት ተመሳሰሎ መፈጠር ልልህ እችላለሁ፡፡ የምንጋራቸው በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ ስለ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ያለን አስተያየት አንድ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ ፍልስፍናን ከሚካኤሊዴስ በስተቀር ሌሎቹ አላስተማሩንም ልልህ እችላለሁ፡፡ የተማርነው ቴዎሎጂን በፍልስፍና ቋንቋ ነው፡፡

ፍልስፍና ማለት ሐቅን ፍለጋ በጭንቅላትህ ብርሃን መጓዝ ነው፡፡ ስትነሳ የት እንደምትደርስ፣ ምን እንደምታገኝ አታውቅም፡፡ ስትሄድ ስትሄድ... ቆይተህ አንድ የራስህ ጭብጥ ላይ ትደርሳለህ፡፡ እነርሱ ግን በፍልስፍና ቋንቋ ያስተማሩን የካቶሊክ ሃይማኖትን ነው፡፡ እኛም ነቅተንባቸው ነበር፡፡ ያውም ከዩኒቨርሲቲ ወጥተን ሳይሆን እዚያው እየተማርን ነው፡፡... ባክህን ተወው ፍልስፍናን፡፡ ሰለሞንን ልጨምርልህ፡፡

ቅድም ተመሳሰሎ መፈጠር አላልኩህም? አንድ አዲስ ነገር ሲያጋጥመን ያንን ነገር እንዴት እንደምንቀበለው ይመሳሰላል አቀባበላችን፡፡ ሁለታችንም በፍቅር እናምናለን፡፡ በእርግጥ በፍቅር የማያምን የለም፡፡ የእኛ ግን ሆፍ ያለ ይመስለናል፡፡ የሰማናቸውን ቀልዶች እንለዋወጣለን፡፡ ቀልድን መጋራት የበለጠ ያቀራርባል፡፡

በኮሌጁ ውስጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የለንበትም፡፡ የለንበትም ባንልም አንገባበትም፡፡ ዞር ብለን ስናስተውለው እኔም ሆንኩ ጓደኞቼ እዚያ ውስጥ ብንገባም፣ ባንገባም ምንም ለውጥ አናመጣም፡፡ ቁጥሩንም አናነሰው፡፡ በዚህ በኩል ግን ጊዜያችንን ለምንወደው ነገር ብናውለው እንችላለን የሚል እምነት ነበረን፡፡

@Amharicbookstore



በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ውስጥ የዐመፅ ባሕሉን የሚዘሩባቸው ሌሎች አፍሪካውያን ናቸው፡፡ ጃንሆይ ስኮላርሺፕ ሰጥተዋቸው አብረውን የሚማሩ ነበሩ፡፡ አንድ ጊዜ የኮሌጃችን ተማሪዎች ጃንሆይን ሊያነጋግሯቸው ተሰልፈው ወደ ፓርላማ ሄዱ፡፡ ንጉሡ ተቀብለው በሰላም አነጋገሯቸው፡፡ ተማሪዎቹ ወደ ኮሌጅ ሲመለሱ ፓርላማ ግርግዳ ላይ በትልቁ 'የሚከራይ' የሚል ጽሑፍ ለጠፉበት፡፡ የፕሮፓጋንዳ ጨዋታ ብትሆንም ደስ ብላኛለች፡፡

በወቅቱ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁንም፣ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትንም የሚያስተዳድሩት ጆዚዊቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጃንሆይ ከጆዚዊቶች ጋር ግንኙነት ነበራቸው፡፡ እሳቸው ትምህርታቸው በፈረንሳይኛ ነበር፡፡ የእኛ ትምህርት ቤት ዲሬክተር የነበሩትና ሌሎቹ አስተማሪዎቻችን የካናዳ ፈረንሳዊ ጆዚዊቶች ናቸው፡፡ ኮሌጁን የቀረቀሩትም እነሱ ናቸው፡፡ ሁሉም ነገር በፕሮግራም የተከፋፈለ ነበር፡፡ ሴቶቹ መኝታ ቤት አካባቢ መሄድ ክልክል ነው፡፡ እኛ ደግሞ ጎረምሳ ነን፡፡ ይህ አይነቱ ሥነ ሥርዓት ነብሳችንን ያበሳጫታል፡፡

ውቤ በረሃ አምሽተን ወደ ዩኒቨርሲቲ እንመጣለን፡፡ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት በኋላ መግባት ክልክል ነበር፡፡ አንዱ ጆዝዊት በር ላይ ይቆማል፡፡ እኛን ላለማስገባት፡፡ ይኼኔ አንዱ ተማሪ ይሸፋፈንና በድንጋይ ይለዋል፡፡ ጆዚዊቱ እግሬ አውጪኝ ይላል፡፡ ተማሪውም ሹልክ ብሎ በሰላም ወደ መኝታ ቤቱ ይገባል፡፡ እራሳችንን አሁን ስንጠረጥር እንዲህ ዓይነቱ ዐመፅ ውስጥ አንጠፋበትም፡፡

ዩኒቨርሲቲ የኪስ ገንዘብ አይሰጠንም፡፡ ምግብ፣ መኝታና ዩኒፎርም ይችለናል፡፡ ስለዚህ ገንዘብ ይቸግረኛል፡፡ ከዩኒፎርሙ ሌላ የምቀይረው ልብስም የለኝም፡፡ አንድ ሞራንሲ የሚባል ነበር፡፡ ሁሌ ሲያየኝ ያች ዩኒፎርም አትቀየርም፡፡ ጠራኝ፡፡ ሙሉ ኮትና ሱሪ ዩኒፎርም አወጣና ሳያስፈርመኝ በነፃ ሰጠኝ፡፡ ልብስ መቀየሬን ግን ሌላው ተመልካች አላየልኝም፡፡

የመጨረሻ ዓመት የኮሌጅ ተማሪዎች ተመርጠን በልዩ ልዩ ርዕስ ተከራከርን፡፡ ይኸውም ከማይንስ፣ ከትምህርትና ከሕግ ወዘተ ተውጣጣን፡፡ እኔ የትምህርት ክፍልን ወክዬ ነው የተከራከርኩ፡፡ ሙግቱ የተካሄደው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ነበር፡፡ ጃንሆይም የዚያን ዕለት ተገኝተዋል፡፡ ዳኞችም ተሰይመዋል፡፡ በወከልነው የሙያ መስክ ላይ ተሟገትን፡፡ ተስፋዬ ገሠሠ አንደኛ ወጣ፡፡ እኔ ስንተኛ እንደወጣሁ አላስታውስም፤ ግን ንግግሬን ጃንሆይ ወደውልኝ ኖሯል፡፡ ዳኞቹ እንደ መሰለኝ በዚያን ጊዜ

የጣሉኝ ወይም ነጥብ ያስቀረጠብኝ አንዱ ምክንያት ኮቱ አልተቆለፈም ነው ያሉት።

በወቅቱ ጃንሆይ ናቸው የትምህርት ሚኒስትር። ተጠባባቂው ከበደ ሚካኤል ነበሩ። ጃንሆይ አቶ ከበደን ዩኒቨርሲቲ ልከው ነው ያስጠሩኝ። አቶ ከበደ ቤተመንግሥት ወሰዱኝ። አዳራሽ ውስጥ ስገባ ጃንሆይ ሩቅ ናቸው። በመሐላችን ቀይ ምንጣፍ ተነጥፏል። በግራና በቀኝ በኩል ክብር ዘበኞችና ትላልቅ ሰዎች ቆመዋል። ወደ እሳቸው ስሄድ እያነስኩ፣ እያነስኩ ሄድኩ፣ እሳቸው ደግሞ እየገዘፉብኝ ሄዱ። እኔ የባላገር ልጅ ነኝ። የቤተ መንግሥቱን ሥነ ሥርዓት ስለማላውቅ ዝም ብዬ እየሄድኩ ነው። ወደሳቸው። አንዱ ከኋላዬ መጣና አንገቴን አንቆ ሊደፋኝ ነበር። እኔም ለመከላከል መከትኩ። እንደመሰለኝ እሳቸው የሰጡት ምልክት ሳይኖር አይቀርም። ተወኝ። እንጃ የእኔ ምክሯ ከምን ሊያድነኝ? አፈርድሜ ነበር የሚያስግጠኝ። ያም ሆነ ይህ በሰላም አጠገባቸው ደረስኩ። እንደመሰለኝ እጅ ነሣሁ። ትንሽዬ ሳጥን ከፈቱና እንካ አሉኝ። ቆንጆዬ ሰዓት ነች። ተመልከት የእጄን ቅጥነት። ከዚህች ቅጥነት ጋር የምትስማማ ሰዓት ተቀብዬ ብል ብሰራ ማሰር አቃተኝ።

"ባላገር ነውና!" ብለው ጃንሆይ ራሳቸው ተቀብለውኝ አሠሩልኝ። ሰዓቷም ማሰሪያዋም በወርቅ የተሠራ ውብ ነበረች፣ በኋላ ማጅራት መቺ ወሰዳት። ውቤ በረሃ አጠገብ፣ ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ።

ክርክራችን ላይ እንዲህ አልኩ። "ኢትዮጵያ ሣይንስ ያስፈልጋታል። ሕክምናም ያስፈልጋታል። ሕግም ያስፈልጋታል።" እያልኩ ሁሉንም ሙያ እየጠራሁ እየደገፍኩ ተናገርኩ። ዳኞቹም ሆኑ አድማጮቹ "ዞሮበት ነው ግቡን ሳተ" ሳይሉኝ አይቀሩም። በመጨረሻም ትምህርት ደግሞ ለኢትዮጵያ በጣም ያስፈልጋታል። ቀደም ብዬ የጠቀስኳቸው ሙያዎች ሁሉ እንቁላል ቢሆኑ ትምህርት ዶሮ ናት፣ ትፈለፍላቸዋለች ስል፣ ያኔ አዝነውልኝ የነበሩት በጣም ደስ አላቸው። በደማቁ፣ በደማቁ አጨበጨቡልኝ።" አለና "ሽንቴን ሽንቼ መጥቼ ላጫውትህ" አለኝ።

ነጠላ ጫማ አቀበልኩት።

ደርሶ እንደመጣ "በነገራችን ላይ ጃንሆይን በጣም ነው የምወዳቸው። ያኔ ልጅ ሆኜ መውደድ ብቻ ሳይሆን ከአባት በላይ፣ ከእግዜር በታች ነው የሚሆኑብኝ።" ብሎ ተመቻችቶ እየተቀመጠ "ከሐና በፊት እኔ ምንም ገርል ፍሬንድ አልነበረኝም። ከየት መጥቶ? የዚያን ጊዜ እንዳሁኑ ገርል ፍሬንድ እንደልብህ አታገኝም። ዛሬ ሲኒማ፣ ቴአትር ቤት፣ ቤተ መጻሕፍት ብትሄድ ገርል

@Amharicbookstore



ታገኛለህ። ያኔ ገርል በእኛ ጊዜ ሕልም ነው። ገርሉንም በስታትስቲክስ እናካፍል ብትል አንድ ገርል ለአርባ ጎረምሣ ቢደርስ ነው። እኛ ደግሞ ችስታ ነን፤ የሚረባ ጫማም ልብስም የለንም። ልባችን ቢከጅልም አቅማችንን ስለምናውቅ በጨዋታው ውስጥ የለንበትም። አጋጣሚው ፈቀደና ኮሌጅ እያለሁ ከክፍሌ ልጅ ፍቅር ከጀጀለኝ። *ትዕግስት ትባላለች። የምንማረው ትምህርት አንድ ዓይነት ነው። ጥሩ እንግባባለን። ቀይ፤ አጭር ነች። ለእኔ በወቅቱ በጣም ታምረኛለች። እርሷ ግን የምታየኝ ልክ እንደ እኩያ ወንድሟ ነው። ፍራንክ ካላት ለሲኒማ መግቢያ ትሰጠኝ ነበር። አንዴ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ በደረታችን ሳር ላይ ተጋድመናል። እናወራለን። እጇ ላይ ትንንሽ ቀያይ ፀጉሮች በቅለው ሲያዩዋቸው ያምራሉ። እነርሱን መዳሰስ ፈልጌ ፈራኋት። እንዲህ እንደ ተመኘኋት፣ ውስጤ በፍቅሯ እንደጦፈ ትምህርታችንን ጨረስን። ሁለታችንም ጥሩ ውጤት አምጥተን ተመረቅን። ኮሌጅን በጠስን" ከሣቅ ጋር።

"ከዚያም ለሁለት ዓመታት ያህል ተለያየን። እንደገና አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ለትምህርት ሄደን ተገናኘን። የተገናኘንበት ቦታ እንዴት የአሜሪካንን ባሕል አክብረን መኖር እንዳለብን ሥልጠና በሚሰጠን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነው። ያኔኑ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እያለን በፍቅሯ ልቤ እንዴት እንደጦፈላት ነገርኳት...

"እኔም እንዳንተው አፍቅሬህ ነበር። ሐሳብ ካንተ ሳይሰነዝር ሲቀር ጊዜ እኔም ፍቅሬን ውጬው ቀረ" አለችኝ።

በፍፁም። ሁለታችንም ባይፈቀድልን ነው ተባባልንና ተለያየን። አዲስ አበባ እንደተመለስን ከትግስት ጋር እንደገና ተገናኘን። በወቅቱ አግብታለች። እኔ ትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ስሠራ ባለቤቷ የኔ አለቃ ነው። በጣም ቀናተኛ ነው። በታኮ ጫማ ሁሉ ፈንክቷታል። ይህንን አውቃለሁ። ግን እኔን ከልቡ ይወደኛል። ስንጨዋወትም "ስሚ ትዕግስት፣ ከስብሐት ጋር ሆነሽ አልጋ ውስጥ ባገኝሽ እንኳን ምንም አልጠረጥረውም" ይላል።

በዚህ አባባሉ ተናደድኩ! እንዴ! እኔ ስልብ ነኝ እንዴ? አልኩ። አንድ ቀን ወደ "ቤቱ አድርሺው" ሲል ባለቤትዋ አዘዛት። በቮልስዋገን መኪናዋ ስትሸኘኝ መኪናውን አቁሚ አልኳት። አፍንጫ በር አካባቢ ደርሰናል። አቆመች። "ትግስት፣ ትስጨኛለሽ?" አልኳት።

"እንዴ!! ምን ነካህ?" አለችኝ።

"እንዴ! ምን አባቱን ነክቶት ነው ባልሽ እንዲህ የሚናገረኝ? እኔ ወንድ አይደለሁም እንዴ? ትስጪኛለሽ። አለበለዚያ ከዚህ አካባቢ ንቅንቅ አንልም" አልኳት።

ግር እንዳላት "እሺ፣ አሁን ወደ ቤት እንሂድ" አለችኝ።

"እሺ ብለሻል ዋ!" አልኳት በአጽንኦት።

በፀጥታ እያብሰለሰለች መኪናዋን አስነስታ መንዝ ጀመርን። በሁለታችንም ልብ ግን ይህ ጉዳይ ከዚያች ቃል ፈቅ ብሎ ድርጊት ላይ እንደማይደርስ አውቀነው ነበር...

***

**ያፈቀራት ወጣት ትክክለኛ ስምዋ ተቀይሯል።*

***

፮

# "ብር አምባር ሰበረችልዎ!"

የአዲስ አበባ ሠፈሮች የየራሳቸው ታሪካዊ አመያየም አላቸው። አንዳንዶቹ በታወቁ ሰዎች ሥም ሲሰየሙ፣ ሌሎቹ በአካባቢው በሚከሰቱ ሁኔታዎች ይጠራሉ።

ለአብነት ጥቂቶቹን ብንጠቅስ፣ ደጃዝማች ውቤ ሠፈር፣ ተሰማ አባቀማው ሠፈር፣ አባ ኮራን ሠፈር፣ ራስ ብሩ ሠፈር ከሚጠቀሱት ናቸው። በኅብረተሰብ የዕለት ተዕለት ግጠመኝ ላይ የሚሰየሙ ሠፈሮችም አሉ። እሪ በከንቱ፣ ዶሮ ማነቂያ፣ አፍንጮ በር፣ አራዳ፣ ተረት ሠፈር... ከሚታወቁት መካከል ናቸው።

ተረት ሠፈር ለምን እንደተባለ ካልተጻፈው ታሪካችን እኛው ተመራምረን የደረስንበት እንዲህ ነው" አለና ጋሼ ስብሐት ወፍራም ሳቁን ሳቀና ለስላሳ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ አፍንጫውን አበሰና "መስየ ተረስ የሚባሉ ፈረንሳይ ናቸው በአገራችን የመጀመሪያውን ሲኒማ ቤት በተረት ሠፈር የከፈቱት። ሰይጣን ቤት ተባለ። ተረስ ሠፈርም ከጊዜ በኋላ ተረት ሠፈር ተባለ። ምክንያቱም እኛ ሐበሾቹ የምንሰማው ተረስን ሳይሆን ተረትን ነዋ።



መስየ ተረስ ሌላ መታሰቢያ በተረት ሠፈር አላቸው። ከዕለታት በአንዱ ቀን ነጭ በነጭ ለብሰው ሰይጣን ቤት አጠገብ ይንጎራደዳሉ። አንጎራደዳቸው የትዕቢት ትመስላለች። አንዱ ባለሁለት ሱሪ አበሻ በሸቀ። "በማነው እንዲህ የሚዘንጠው?!" አለና ሳያዩት ጭቃ ከመሬት ላይ ዝቆ ወርውሮ ጀርባቸው ላይ ለጠፋባቸው። መስየ ተረስ ተናደዱና ሠፈራችንን ረገሚት። "ሰው አይብቀልብሽ!" አሏት። እርግማኑ ደረሰ። ከዚያ ወዲያ ሰው በቅሎባትም አያውቅ። በሙሉ ፍሪክ ነው" አለኝና ሣቅን። "የተረት ሠፈር ፍሪኮች ናቸው እንዲህ የሚሉት እንጂ ሠፈራችን አያሌ አኩሪ ዜጎችን አፍርታለች። እንደ ማንም ሌላ ሠፈር።

ተረት ሠፈር መኖር የጀመርኩት ከኩርምስና ከድንግልና ከሸሌዎች ትዝታ ጋር የተያያዘ ነው። ከበርካታ ገጠመኞች ጋር የተቆራኘ ስለሆነ በረጅሙ ላጫውትህ?

እኛ በጃንሆይ ዘመን አዳሪ ትምህርት ቤት የተማርን ልጆች ከሴት ልጅ ውበትና ደስታ ተገልለን ነው ያደግነው። ልጃገረዶቹን ባናያቸውም ጉርምስና ቀስ በቀስ መጣች። ጢም እያበቀልን ድምፅም መጎርነን ጀመረ። በሐሳብ በወሬ በሕልማችን ስናቅፋቸው የነበሩትን ሴቶች በውን ለማቀፍ ብንከጅልም ሕይወት አልፈቀደችልንም። ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ስንገባ ሴት ልጅ በገሃድ ወደ እቅፋችን ልትገባ ሆነ። ውቤ በረሃ ስንሄድ በግል ወይም በቡድን ነበር። እንደ ባሕሪያችን፣ እንደ ፍጥርጥራችን ይህንን የትኩሳት ዕድሜ በቀንጃጅቱ ቅዱስ አካል አስተናገድን።

በጊዜው እኔ ልክ ሃያ አንድ ዓመት ሞልቶኛል። ለክረምት ኮሌጁ ሲዘጋ ሥራ አግኝቼ በሁለት ወር ደሞዝ የቱጃር ስሜት አድሮብኛል። ገንዘቡ ከተማሪነት አንጻር ስታየው ብዙ ነው። በዚያ ዕድሜ እንግዲህ ምንድነው ድንግልና? አልኩና ልገሠስ ወሰንኩ። ሴተኛ አዳሪዎች ቤት ሄድኩ። በዚያን ጊዜ ብዙ የሴተኛ አዳሪ ሠፈሮች ነበሩ። ጣሊያን ሠፈር፣ ሠራተኛ ሠፈር፣ ንፋስ ስልክ፣ ወዘተ...

አሁን ኤንሪኮ የሚባለው ኬክ ቤት አካባቢ መደዳውን ሦስት የሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ነበሩ። አንደኛው ውስጥ አንዲት ቀይ ሴትዮ ተቀምጣ አየኋት። ገባሁ። ሳያት በእድሜ ትበልጠኛለች። ደነገጥኩ። መውጣትም አፈርኩ። በአሁኑ ጊዜ ቢሆን አምስት ብር ሰጥቻት እሄድ ነበር። ያኔ ልምድ የለም፣ ተኛን።

ምንም ዓይነት ስሜት አልነበረም። የተፈጥሮ ግዴታን እንደ መወጣት ቁጠረው። ጨረስኩ ጣጣዬን። ሴትዮዋ ግን እኔ ደስ ያልኳት መሰለኝ። ተመላልሺ እንድጎበኛት ጋበዘችኝ። በሳምንት

@Amharicbookstore

አንድ ቀን እሁድ እሁድ እጎበኛት ጀመር፡፡ አንድ ቀን ግን ችግር ተፈጠረ፡፡

በተለመደው ሰዓት ልጎበኛት ስሄድ እንዲህ አለችኝ "ይኸውልህ፣ እየረዳኝ ያስቀመጠኝ ውሽማ አለኝ፡፡ የቤት ኪራይ ይከፍልልኛል፡፡ አንተ ተመላልሰህ ስትጎበኘኝ አወቀህ፡፡ ድጋሚ ቢያይህ ላይረዳኝ ወስኗል፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ወዳጅነቱን እናቁም" አለችኝ፡፡ እሺ አልኳት፡፡

"ግን" አለችኝ፡፡

"ግን ምን?" አልኳት፡፡

ሌላ ልንገናኝ የምንችልበትን ቦታ ነገረችኝ፡፡ ላልተወሰኑ ሳምንታት እሁድ እሁድ፣ ጓደኛዋ ቤት እየሄድኩ እነሆ በረከት ተባባልን፡፡ ይህንንም ግንኙነታችንን ውሽማዋ ደረሰበትና የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጣት፡፡

ከራሱ ጋር ፈገግ ብሎ "ያኔ በእኔ የትርምስና ዘመን ፋሽን ይመስለኛል፡፡ ሰውን ማመን የለም፡፡ ይህቺ ዝም ብላ ልታጭበረብረኝ የአዞ እንባዋን ታፈስሳለች፣ አልኩና ቻው! ቻው! ከመባባላችን በፊት ተቃቀፍን፡፡ ይህ ዕለትም በእርግጥ የመጨረሻው ሆነ፡፡ እቶ ውሽማም ተመስገን ሳይሉ አይቀሩም፡፡"

እድሜ ነብስ ካወቅኩ በኋላ ድንግልዬን የገሠሠችውን ሴት አስብኳትና አሳዘነችኝ፡፡ እውነቷን ነው፡፡ አማራጭ ስለሌላት እንጂ ትወደኝ ነበር፡፡ መለያየቱ ከብዷት ነው ያነባችው፡፡ ፍቅር ሴተኛ አዳሪዎችን ይይዛቸዋል፡፡ ያስይዛሉም፡፡ ያንን ሁፋ ባለ መልኩ ማስተዋል ከፈለክ ሌቱም አይነጋልኝን እንድታነብ እጋብዝሃለሁ፡፡

ይህች የምነግርህ ገጠመኝ አሁንም ሳስባት የምታስደንቀኝ ነች፡፡ውቤ በረሃ አስገደች አሳምረው ዳንስ ቤት ውስጥ ጨለም ካለው ጥግ ተቀምጫለሁ፡፡ አምቦ ውሃ ነው የምጠጣው፡፡ የሚደንሱትንም፣ የሚዝናኑትንም ባለበት አስተውላለሁ፡፡ ከፊት ለፊቴ ባንኮኒ ደገፍ ብሎ አንድ ሰውዬ ቆሞ ይዝናናል፡፡ ቢራ ነው የሚጠጣው፡፡ ሰውዬው በውቤ በረሃ የታወቀ ተደባዳቢ ነው፡፡ ይህ ሰው እኔ ሚስቴ ብዬ ያስቀመጥኳትን ሴት ቢራ ጋብዞ ያሳስቃል፡፡ በዚህ ጊዜ አንዳች ወንድ ነኝ የሚል ስሜት ውስጤን ይፈታተነኝ ጀመር፡፡ አውቃለሁ ዞቢዳ ሸሌ ነች፡፡ ከማንም ጋር እስከተከፈላት ጊዜ ድረስ ትዝናናለች፡፡ ግን የእኔ ነብስ የወንድነት ፈተናና እልህ ውስጥ አስገባችኝ፡፡ ስለዚህ ሚስቴን ከዚያ ኃይለኛ መዳፍ አላቅቄ ልወስዳት ወሰንኩ፡፡ ተነሣሁ፡፡ ጉዞ ጀመርኩ፡፡ ዞቢዳና ሰውዬው መካከል እስክምደርስ ያለው መንገድ የዘለዓለምን ያህል ራቀብኝ፡፡ በጉዞዬ ላይ



ልዩ ልዩ ዓይነት ትዕይንቶች ይታዩኛል፡፡ በዚያ ማንንም መለተም በለመደ ኃይለኛ ጡንቻው ሲነርተኝ ፀትንትኔ ሲወጣ እየታየኝ ተራመድኩ፡፡ ቡጢው ሲያርፍብኝ የሚታየኝ የቀለማ ቀለም መዓት ከወዲሁ መታየት ጀምሮኛል፡፡ ርምጃዬን አልገታሁም፡፡ ቀጠልኩ፡፡ ሞትም ቢሆን ልጋተረው ወስኛለሁ፡፡ እንደማይደረስ የለምና ደረስኩ፡፡ ዞቢዳን እንደ ጋሻ ከልየት መሐላቸው ገባሁ፡፡

"እ! ሰላማዊ!" አለና አቅፎ ሳመኝ፣ ጋሺ ስብሐት እየሣቀ ያ ያለፈ ትዝታ ትላንት እንደሆነ ቀርቦ እየታየው በኃይል ተነፈሰ፡፡ "ለካስ እኔን በርቀትም ቢሆን በአካኋኔ ስለሚወደኝ ሚስቴን እያጫወተልኝ ኖሯል!"

ዞቢዳና አስቴር ደባሎች ናቸው፡፡ አንድ ክፍል ውስጥ ነው የሚተኙት፡፡ እኔ በዚያን ጊዜ በቂ ገንዘብ አገኛለሁ፡፡ ለወላጆቼ ትንሽ እልካለሁ፡፡ ለራሴም በደንብ ነው የምኖረው፡፡ ለዞቢዳም ድሮ ያልነበራትና የሚያምሯትን ልብሶችና ጫማዎች ገዛሁላት፡፡ በጣም እንግባባለን፡፡ ሸርክ ነን፡፡ በዚያን ጊዜ ከሴተኛ አዳሪ ፍቅር አይዘኝም ሳልል አልቀርም፡፡ ግን የፍቅር ዓይነት ስሜት ሳይጀማምረኝ አልቀረም፡፡ ለምን ብትል የደጃች ውቤን ሠፈር ሳልሳለም አልውልም፡፡ እንደዚያ የሚያስሮጠኝ አሁን ስንጠረጥር፣ ፍቅር ነበረ፡፡ እኔ ወደ ቤቷ እገባና መጽሐፍ ቅዱስ አለ እሱን እያነበብኩ እጠብቃታለሁ፡፡ በምናቤም ሙሴና እግዚአብሔር ሲከራከሩ ቡጊ፣ ቡጊ ሲደንሱም ይታየኛል፡፡ እሷ ዳንስ ቤት ውስጥ አስተናግዳ ትመጣለች፡፡

አስቴር ሞገደኛ ነበረች፡፡ ማንኛውንም ወንድ አብሯት እንዲያድር ከጠየቃት አስቀድማ ታስከፍለዋለች፡፡ ሌላ ወንድ ከጠየቃት ይሔኛውን ጥላ ከሁለተኛው ጋር ጥርግ ትላለች፡፡ "ነገን እግዜር ያውቃል" የምትል አይነት ሸሌ ነች፡፡ ጉልበተኛ የሆነ ሰው ቢገጥማትም አትፈራም፡፡...

አንድ ቀን ማታ ነጭ በነጭ የለበሰ ወጣት አስከትላ መጣች፡፡ ጠይም ነው መልኩ፣ ደስ የሚል ቁመና አለው፡፡ ግባ አለችውና ወደኋላዋ መለስ አለች፡፡ እኔና ዞቢዳ የአስቴርን አልጋ አሳየነውና ይጠብቃት ጀመር፡፡ የአስቴርን ባሕሪ ስለምናውቅ ለዚህ ውብ ወጣት እያዘንለት፣ ጋደም ብለን ለመተቃቀፍ ቸኩለናልና ልብሳችንን አወላለቅን፡፡ የዳንስ ቤቱ ሙዚቃም ተዘግቷል፡፡ ሴቶቹ የቀናትም ቀናት፣ ያልቀናትም ወደየአልጋዋ ሄዳለች፡፡ እኛም ጋደም ካልን በኋላ "በል ወንድም፣ ደህና እደር" አልንና መብራቱን አጠፋነው፡፡

@Amharicbookstore

"እንዴ! አብሩት እንጂ! ምን መሆናችሁ ነው?!" አለ እያለቀሰ፤ ቶሎ አበራሁት። ዘቢዳ ግን በጣም ተናዳለች፤ የወንድና የሴት ባሕሪ የምትለው ነገር አላት፤ "ዚጋ!" ብላ ጮኻበት የስድብ መዓት ልታወርድበት ስትል ተይ ብዬ በግድ አስተኛኋት፤

እሱም "እባካችሁን አታጥፉት! ባይሆን የመብራቱን እከፍላለሁ" እያለ አለቀሰ፤

ሰብለትም እየሳቀ "ይህ ዓይነቱ ሊጋጣሚ ለእኔ በጣም የሚያሳዝነኝ ነው፣ ሲርቅ ጊዜ አሁን ሳቅኩበት እንጂ፤ አሁን ሳስበው፣ ያ ልጅ አካሉ የደረሰ ጎረምሣ ነው እንጂ ነብሲቱ የሕጻን ነች፤ በአስቴር መጥፋት ምድሯን ቁና ያደርጋታል ብለን የፈራነው ጎረምሳ የተገላቢጦሽ እናቱ ገቢያ እንደሄደችበት ሕጻን አልቅሶ፤ እያሳዘነ አሳቀን፤

እዚያ ሠፈር ስትሄድ እያሌ የወንድ ባሕሪ ታያለህ፤ ድርስት መድረስ የሚችሉ ቢሆን እኛን አሳምረው መሣል የሚችሉት ሸሌዎች ይመስሉኛል፤

ብዙ ጊዜ የተለያየ ወንድን ማግኘት የሚችሉት እነርሱ ናቸው፤ ድብቅ ባህሪያችንን ቀድመው የሚረዱት እነርሱ ናቸው ልልህ እችላለሁ፤ እንዷን ላጫውትህ?

'Satyriasis' የሚባል የወሲብ በሽታ አለ፤ ቃሉ የግሪክ ነው፤ ሲሥሉት ከአንገቱ በታች የፍየል፣ አናቱን የሰው አድርገው ነው፤ በሰው ምናብ ፍየል ስሪያ ነዋ ዋና ሥራው፤ በፍፁም መጥገብ አይችልም፤ 'ባዮሎጂው' አካሉ ውስጥ ስለሚሠራ ዘሩን ያፈስሳል፤ አእምሮው ግን በቃኝ ብሎ አይጠግብም፤ እንዲህ ዓይነት ሰው እንዳለ አንዲት ሸሌ አጫወተችኝ፤ "እርመን ነው፤ ገንዘብ አለው፤ ገንዘብ ሲቸግረን እርሱ'ጋ እንሄዳለን፤ ሁሌ ዝግጁ ነው፤ ግን ስለማይጠግብ በጣም ያታክተናል" ብላኛለች።

"ነብስ ካወኩ በኋላ የተዋወኩት ሌላ አበሻ ግን ይህ ችግር ችግሩ አይደለም፤ ደስታው ነው፤ ምክንያቱም ማንም ሴት ትማርከዋለች፣ ግን እንዴ ይበቃዋል እስክምትቀጥለዋ ሴት፤ ለምሳሌ እሱ ራሱ ሲያጫውተኝ ለምሣ ከሥራ መጥቶ ገረዱ እጁን ታስታጥበዋለች፤ በዚያን ጊዜ ሙል ይለዋል፣ አሰኘው፤ እጁን መታጠቡን ያቋርጥና፣ እመቤት ገረድን ይዘዋት ወደ መኝታ ቤት ይገባል...

Satyriasis የወንዶች ነው፤ የሴቶች ደግሞ 'nymphomania' ይባላል፤ በሕይወቴ በዚህ ሕመም የተጠቃች ሴት አላጋጠመችኝም፤ ጣሊያኖች በሠሩት ፊልም ላይ- አንዲት አርቲስት ስትጫወት



አይቻለሁ፤ የሳይኮሎጂ መጽሐፍ ፊልጌ አነበብኩ፤ ወንዱ ረጅም ጊዜ ቆይቶ ቢጨርስም እሷ ሁልጊዜ ዝና ነች፤ ስቃይ ነው፤ ልትቆጣጠረው አትችልም፤ ወንድም ነው፣ አባት ነው፣ አጎት ነው ብሎ መለያየት የለም የሚፈለገው ወንድ መሆኑ ብቻ ነው፤ እግዜሩ በጣም ሸፍጧታል፤ ክሊዮፓትራ በዚህ ደረጃ ላይ ባይሆንም ወንድ ሲበዛ ትወዳለች፤ ሲነሳባት ደህና ደህና አጃቢዎቿን አስከትላ ወደ ወደብ ትሄዳለች፤ እዚያም ከመርከበኞች ጋር እንደልቧ ስትለው ታድራለች፤

ወደሚስማማን የቱርምስና ሠፈር ስንሄድ እዚያ የሚያጋጥሙን አንዳንድ አልሞት ባይ ተጋዳይ የሆኑ ሽማግሌዎች ነበሩ፤ አንዳንዶቹ "ቱርምስና ከንቱ ጉራ ነው፣ ውበትም እንደ ጤዛ ረጋፊ ነው" ይሉናል፤ ሌሎች የቱርምስና ጊዜያቸው ስላለፈባቸው እኛን ተረኞቹን የሚቀኑብን፣ የሚጠምዱን ነበሩ፤ "አር የነፋው ጎረምሣ" ብለው ያንቋሽሹናል፤ እኛ ምን ቸገረን? እነርሱን እኮ እንደ እፉዬ ገላ አጋጣሚው ሲያንቀዋልላቸው ተገናኘን እንጂ ከቅዕበታዊ ግምታዊ እይታችን አያልፉም፤ እኛ ውቤ በረሃ የመጣነው ለሌላ ጉዳይ፤ ሲያሰኘን በጋራ በዳንስ ወለል ላይ ለመውረግረግ፣ ይበልጥ ሲያጋጥም ደግሞ በአልጋ ላይ የግል የቁምነገር ጨዋታ ማድረግ። ዳሩ ምን ያደርጋል? ወደ ውቤ በረሀ የምንጎርፈው ብዙ ነን፤ እየከፈልናቸውም ቢሆን ሴቶቹን መሻማት አለብን፤ ብቻቸውን መጥተው ሽሚያ ውስጥ የሚገቡ አሉ፤ በቡድን መጥተው የሚሻሙም አሉ፤

ፀጋዬ ሲያሰኘው ብቻውን ይመጣል፤ በነገራችን ላይ፣ ፀጋዬ ሌቱም አይነጋልኝ ብዬ በፃፍኩት ልቦለድ ውስጥ ጥላሁን በሚል ስም የምጠራው ነው፤ አሁን በሕይወት የለም። ስለዚህ በስሙ ብንጠራውና ብናስታውሰው አይከፋውም፤

ሲያሰኘውም በቡድን ይመጣል፤ ቢራ ከጠጣ ፀብ ፀብ ይሸተዋል፤ ብቻ ለብቻ ይሁን ቡድን ለቡድን ሲጋጠም እሱ አውራ ነው፤ ከተነሣበት ብቻውን አንድ ቡድን ይገጥማል፤ ያተራምሣቸዋል፤ ይህ እሚሆነው መጠጥ ከቀመሰ ነው፤ ካልጠጣ ግን የሰላም ሰው ነው፤ በግድ ካላስገደዱት አይደባደብም፤

አንድ ማታ ፀጋዬ አልጠጣም፤ ዝም ብሎ አንዲት ጥግ ተቀምጧል፤ አንድ ጉረኛ ጎረምሣ 'ሲጠጡ ነው'ንጂ ካልጠጡኮ ሰውዬው ጨዋ ነኝ ባይ ናቸው" አለ ነገር ፍለጋ፤

ዝም አለ ፀጋዬ፤

"ካልጠጡ ጨዋ ብቻ አይደሉም ፈሪ ጨዋ ናቸው" አለው፤

"እኔን ነው?" ፀጋዬ ጠየቀ፤

@Amharicbookstore

"ቢሆንስ ምን ትሆናለህ?" መለሰ ጎረምሣው።

ፀጋዬ ከዚሱ ቾክ አውጣና ጣውላው ላይ በርሱና በጉልበተኛው መካከል አሠመረ። ከዚያም ቀና ብሎ ቡጢ ጨብጦ ወንድ ከሆንክ ይህንን መስመር ተሻገር አለው።

"አንተው አስመርከው፣ አንተው ተሻገረው" አለ ጎረምሣው።

ፀጋዬ ቡጢ እንደጨበጠ ተሻገረና "በል ይዋጣልን ከፈለክ።"

"እኔን በማላውቀው ቤት አስከብበህ ልታስደበድበኝ!? መስሎሀል!"

"እሺ ወደ ውስጥ እንግባ። አጥር ግቢ ስለሆነ እዚያ ይዋጣልን?"

"ሴቶቹን አስከብበህ ልታስደበድበኝ? ሲያምርህ ይቅር!"

"አሁንስ አበዛኸው! ና ባቡር መንገድ ላይ እጠብቅሃለሁ" ብሎ ፀጋዬ ፈጥኖ ወጣ።

ጉልቤው ጎረምሣ ሮጥ ብሎ ከፀጋዬ ፊት ተንበረከከና እጆቹን እንደፀሎት እደረቱ ላይ እያጣመረ "ማረኝ አጥፍቻለሁ። አንተ አታውቀኝም እንጂ የአክስትህ የወይዘሮ ኤልሳቤጥ ዘመድ ነኝ" አለው።

ተገረመ። የሆነውን ሁሉ ሊያምን አልቻለም። "በሕልሜ ይሆን?" የሚል ሐሳብ ውል ሲልበት በመዳፉ ግንባሩን በኃይል እየመታና በውን መሆኑን እያረጋገጠ "መደባደብ አልፈለክም ማለት ነው?" አለው።

"አልፈለግኩም" በለቅሶ ዜማ መለሰ ጎረምሳው።

"ታዲያ ያ ሁሉ ነገር ፍለጋ ለምን ነበር?"

"ኧረ'ንጃ። እኔ ለራሴ የመጨረሻ ፈሪ ነኝ።"

"ፀጋዬ አብደቱ እንዳይመጣበት ራሱን እየፈራ "በል ጥፋ ከዚህ!" ብሎት ሮጦ ወደ ዳንስ ቤቱ ተመለሰ። ከጤነኛ ሰዎች ለመቀላቀል።

በሚቀጥለው ጀብዱ ፀጋዬ ብቻውን ሳይሆን በቡድን ነበር። የድሬዳዋ፣ የአስመራም ቡድን የውቤ በረሀን ጎረምሶች ያሸቆጠቁጣሉ። እኛ ስንጠረጥር ሁሉቱም ቡድኖች እርስ በራስ ውስጥ ውስጡን በጣም ይፈራራሉ። በልባቸው ፍርሃት እኛ በዞርንበት ዙራ አታውቅም ቢሉም፣ አለመጋጠማቸው የመፈራራት ምልክት እንደሆነ ተገልጾልናል።

የፀጋዬ ቡድን ከአንድ የአዲስ አበባ ቡድን ጋር ተጋጨ። የቤቱን ዕቃ ከምንሰባብረው ውጪ ይዋጣልን ተባባሉ። ባቡር መንገድ ወጥተው በቡጢ፣ በቴስታ፣ ባገኙት አጠና፣ በታጠቀት ጩቤ ተከታከቱ። ቴዎድሮስ ሆዱን ተወጋ። ዕድለኛ ነው፣ ተረፈ። ሆስፒታል ሄደን ጠየቅነው። "በጩቤ ሲወጉህ ምን ተሰማህ?" አልነው።



"በጣም ይቀዘቅዛል፣ ከበረዶ የባሰ ይቀዘቅዛል" አለን።

አሁን ትዝ ሲለኝ ፀጋዬ በራሱ ሥልጣኔ ነበር የሚደባደበው። ላማረው ግን ከዚያም ከፍ ይላል። እንግዲህ ሲኒማ ዓድዋ ለወራት ሲኒማውን ሲያሳይ ይከርምና፣ አንድ ቀን በሲኒማ ፊንታ የቦክስ ሻምፒዮና ውድድር ያቀርባል። አላምረው በገጹ ቀይ፣ በአካሉ ደንዳና የእነዚህ ድንገተኛ ማታዎች ድል አድራጊ ሻምፒዮናችን ነው። አንድ ቀን ማታ አላምረው ሁለት ጓደኞቹን አስከትሎ ወደ ውቤ በረሃ ይመጣል። አብረነው እንቀመጣለን።

በዚህ ጊዜ አንድ የገደል ቅራፊ የሚያክል ሰውዬ መጠጥ መቅጃውን ባንኩኒ ተደግፎ ከሙዚቃው በላይ እየጮኸ የሆነ የሰካር ዝባዝንኪ ያወራል።

"አቦ ጩኸት በዛ" አለን አላምረው።

"ታዲያ ዝም አታሰኘውም?" አለ ዮናስ። አላምረው በጉልቤ አረማመድ እየተጎማለለ እየተንቀባረረ ሄደ። አጠገቡ ቆመና፣"አቦ እዚህ ጩኸት በዛ" አለው።

"ጆሮሽን አትዘጊም?" አለ ግዙፉ ሰው "ወይስ እኔ ልዝጋልሽ?"

"እስቲ!" አለና አላምረው ጉንጩን ለጥፊ አመቻችቶ ሰጠ።

"እንቺ!" አለና ግዙፉ ሰው በጥፊ አጮለው።

አላምረው ጉንጩን እያሻሸ "ታዲያ ይህን እግዚአብሔር ይወደዋል?" አለውና ወደእኛ ተመልሶ መጣ። እና ዮናስን አኮረፈው።

አሁን ደግሞ የማጫውትህ ሠራተኛ ሠፈር የገጠመኝን ነው። ይህንን የሕይወቴ ምዕራፍ የማወጋህ ብራዚላዊ ወዳጄን እያስታወስኩ ነው። ሥሙ ሲሮ ነው። በእኛ ቋንቋ ኪሮስ እንለዋለን። በሙያው የባክቴሪዮሎጂ ሳይንቲስት ነው። ባክቴሪያ፣ ቫይረስ፣ ምናምን እያስታወሰክ፡ ሲሮ ቁመቱ ከእኔም ያጥራል። አመለካከቱ ጥሩ፣ በዲሲፕሊን የሚያምን ሰው ነው። የእርሱ አለቃ የተገላቢጦሽ ዝርክርክ ነበር። ግደለሽና በዋል ፈሰስ የሆነ ሰው ነበር። ይህንን አኳኋኑን ሲሮ ለላኪያቸው የዓለም ጤና ጥበቃ (WHO) ቢሮ ደብዳቤ ፃፈ። "ምንም ሠርቶ የማያሠራ አለቃ ነው የተዘፈዘፈብን። ስለዚህ እርሱን አሠናብታችሁት ሌላ አለቃ መድቡልን" ብሎ ፃፈ። እነርሱም መልስ ጻፉለት። "ከአሁን ሰዓት ጀምሮ አለቃህን አንስተነዋል። በምትኩ አንተ እዚያ ያለውን ቢሮና ሠራተኞች እያሠራህ እንድታስተዳድር ሾመንሃል" የሚል ደብዳቤ ደረሰው።

ከሲሮ ጋር የተዋወቅነው የአሜሪካ የሰላም ጓድ አባሎችን ቋንቋ ስናስተምር ነው። እርሱ ደግሞ የእኛን ሥልጠና ጨርሰው ከእሱ ጋር ስለሚሠሩ፣ ገና ከእኛ ጋር እያሉ ጀምሮ በሙያው ዕውቀት

@Amharicbookstore

እንዲቀስሙለት እየገዛቸው ከእነርሱ እኩል ይደክማል፡፡ በዚህ የሰዓም ጓዶች በጣም ነው የሚወዱት፡፡ እኔም በአሠራሩም፣ በአመራሩም በጣም ወደድኩት፡፡ የሥራ ባሕሪያችን ደግሞ የበለጠ አግባባን፡፡ ከመሥራት በኋላ መዝናናት አለ፡፡ ጋብዞኝ ወይም ጋብዤው ተያይዘን ወደተለያዩ መዝናኛዎች እንሄዳለን፡፡ ሴተኛ አዳሪዎችም ቤት ጎራ እንላለን፡፡ አንድ ጊዜ እኔ የማውቀው ሠፈር አለ አልኩትና ይዤው ሠራተኛ ሠፈር ሄድን፡፡ አካባቢውን ስለወደድነው ብዙ ጊዜ አብረን እየተመላለስን ውሽሞቻችንን ጎበኘናቸው፡፡ ከሙያው አኳያ ያስተማረኝን እየከለከሉልህ እንጨዋወት፡፡

"አልኮል በብዛት ስንጠጣ አንጀታችን ውስጥ ያሉትን ባክቴሪያዎች እንገላቸዋለን፡፡ እነዚህን ባክቴሪያዎች ለመተካት እርጎ መጠጣት አለብን" ብሎኛል፡፡

"እ! ምን እየተባባልን ነበር?" አለኝ የጨዋታችን ውል ጠፍቶት፡፡

አዎን! ሠራተኛ ሠፈር ከሲሮ ጋር ነን Yes! በዚያን ጊዜ ጎረምሳ ደራሲ ነኝ፡፡ ሕይወትን ማየት፣(Adventure) መደሰት የምለው እምነት አለኝ፡፡ ሁሉም ነገር ለድርሰቴ አስፈላጊ ነው እያልኩ የምሄድበት ዕድሜ ነው፡፡ ስለዚህ እግር ጥሎኝ ሠራተኛ ሠፈር ስዞዋወር አንዷ ጠራችኝ፡፡ ከርቀት በእጇ ነው የምትጠራኝ፡፡ ግር ብሎኝ ቆሜ ሳየት ትንሽ ልጅ ላከችብኝ፡፡

"ያቺ ልጅ ትጠራሃለች" አለኝ ልጁ፡፡

"አታውቀኝም፡፡ ምንድነው? ብዬ ሄድኩ፡፡ ጨንቋት ነው የደረስኩላት፡፡ ሐፍረቷን ሁሉ ወዲያ ገፋ ና! ብላ መጥራቷ ከመቸገር የመጣ ነው፡፡ ቤቷ ገባሁና ትንሽ አውርቼ ምንም ሳናደርግ ሶስት ብር ነበረኝ አወጣሁና ሰጠኋት፡፡

"አልቀበልም" አለችኝ፡፡

"ለምን?" አልኳት፡፡

መልስ የለም፡፡ አለመፈለጓን ጭንቅላቷን በመወዝወዝ ገለፀችልኝ፡፡

"እሺ ብንተኛስ?" አልኳት፡፡

"ያኔማ እቀበላለሁ" አለችኝ::

ተኛን፡፡ ሶስት ብሩን ተቀበለችኝ፡፡ አስታውሳለሁ ሳቅፋት በጣም ከስታለች፡፡ ረሃብተኛ ነች አልኩኝ፡፡ በኋላ ሳውቃት ስለሚርባት ሳይሆን በተፈጥሮዋ ለምግብ ግድ የላትም፡፡ ትንሽ ጎረስ ጎረስ አድርጋ ወደ ጫት ነው የምትሄደው፡፡ አዘንኩላት ቀረብኳት፡፡ ከከባችን ሊያቆራኙን ሆነ፡፡ አንድ ቀን እንደተለመደው እነሆ በረከት ልላት ሠራተኛ ሠፈር ሄድኩ፡፡

እንዳየችኝ አዝና ወግ ጀመረች፡፡

@Amharicbookstore



"ይኸውልህ፣ ይህንን የተማረ የተመራመረ ሰው ሙታንቲው ላይ አስደግማ ደጇን ሰይረግጥ አይውልም እያሉ ያሙኛል፡፡ ስለዚህ እኔ ሠፈር ለቅቄ ልሄድ ነው" አለችኝ፡፡

"አንቺን ደስ ያለሽ ቦታ ሄደሽ ተከራይ፡፡ እኔ የቤቱን ኪራይ እከፍላለሁ አልኳት፡፡"

ተረት ሠፈር ተከራየች፡፡

"ይኸውልህ ይህቺ ሴት ወይዘሮ የትምወርቅ ሽፋው ትባላለች፡፡ በኋለኛው የሕይወት ዘመኔ የአራት ልጆቼ እናት ሆነች፡፡ ተረት ሠፈር የገባነው በዚህ አጋጣሚ ነው እልሃለሁ፡፡...

***

# ፯

## የኔታ ስብሐት

"ታሪክን የሠሩትና የመሰከሩለት ሰዎች ሲያልፉ፣ ተከታይ ትውልድ ሲፈራረቅ ታሪክ የነበረችው ቀስ በቀስ አፈ-ታሪክ ትሆናለች፡፡ ዕድሜም ሲሰጣት ተረት ትሆናለች፡፡ ተረትነቷን ዘመን እስኪሽረው ድረስ" አለ ጋሼ ስብሐት አተኩሮ እያየኝ፡፡ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ፀጥ ብዬ እንደምከታተለው ተገንዝቧል። "የምናወጋው የመምህርነት ትዝታዬን ነው? ገብቶኛል፡፡ አንዳንዴ እንዳስፈለገን እንዘባርቃለን፡፡ በጥልቀት ስታብሰለስለው ዝብረቃው ትክክል እንደሆነ ይገባሃል፡፡

ለመምህርነት የሚያበቃኝን ትምህርት ከኮሌጅ ገብይቻለሁ፡፡ የመጀመሪያ ሥራዬን የጀመርኩት አሁን ካዛንቺስ በሚገኘው በአስፋ ወሰን ትምህርት ቤት ነበር፡፡ የማስተምረው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው፡፡ ጋሼ ኃይለ ሚካኤል ምዕዳኖን የማስተምርበት ትምህርት ቤት ርዕስ መምህር ሆኖ አገኘሁት፡፡ አቤት የተደሰትኩት ደስታ! ጠማማ ወይም ብሽቅና መጥፎ የሆነ ርዕስ መምህር ገጥሞኝስ ቢሆን? አቤት የምናደደው ንዴት! ዕድለኛ ስለሆንኩ እማልኩቱም ሁሌም ለእኔ ስለሚያዳሉልኝ ጋሼ ኃይለ ሚካኤል ቀድሞ እዚያ እንዲጠብቀኝ አደረጉ፡፡

ጋሼ ኃይለ ሚካኤል ኮሌጅ አብሮኝ የተማረ ነው፡፡ ቀደም ብሎም መምህር ነበር፡፡ በዕድሜ፣ በዕውቀት ይበልጠኛል፡፡ ሁሉንም ነገር ለማወቅ የሚፈልግ ወጣት መምህርና የሚያቀውን ሁሉ እያስተዋለ ሊሰጥ የሚችል በሳል መምህር ሲገናኙ ደስ ይላል፡፡ ታዲያ ዛሬ ላይ ከአንተ ጋር ተቀምጬ የድሮ ትውስታዬን ስመረምር የሚታየኝ እንዲህ ነው፡፡

ማስተማር ጀመርኩ፡፡ አንድ 'ተርም' እንዳስተማርኩ ጋሼ ኃይለ ሚካኤል ጠራና "ስብሐት፣ እድገት ልሰጥህ ነው" አለኝ።

"እሺ!" አልኩት፡፡ በወቅቱ አስረኛና፤ አስራ አንደኛ ክፍል ነበር የማስተምረው፡፡

እሱም "ወደ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል ልመድብህ ነው ታች ክፍል ሆነው ጥሩ አስተማሪ ከታደሉ ጥሩ መሠረት ይሰጣቸዋል፡፡"

ተስማማሁ፡፡ በተመደብኩበት ማስተማር ጀመርኩ፡፡ በሚቀጥለው ዓመት "ሌላ ዕድገት ልስጥህ" አለኝና ጋሼ ኃይለ ሚካኤል ሦስት፣ አራትና አምስተኛ ክፍልን እንዳስተምር መደበኝ፡፡

ከፍተኛ ክፍል ውስጥ ስትመደብ ለተማሪዎቹ ልትሰጣቸው የምትችለው ዕውቀት ውሱን ነው፡፡ ምክንያቱም እኔም ወጣት ነኝ። የማውቀው ውሱን ነው። በተጨማሪም ታች ክፍል እያሉ በቂ መሠረት አላገኙም፡፡ ዝቅተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ግን ልታካፍላቸው የምትችለው መነሻ ዕውቀት በዛ ያለ ነው።

ያን ጊዜ የትምህርቱ ዓመት በሦስት ተርሞች የተከፈለ ነበር። በሳምንት 31 'ፔሬድ' ነው የማስተምረው፡፡ ይከብዳል፡፡ ያንንም እየጣርክ ደግሞ ድካምህን የሚያበላሹብህ እንደ 'ቲቸር' አንበሴ ዓይነት መምህራን አሉልህ፡፡

ቲቸር አንበሴ እኔ እንግሊዘኛ በማስተምርበት ክፍል ሁሉ ሒሳብ ያስተምራል፡፡ አንድ ቀን የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎችን የቤት ሥራ የሰጠኋቸውን ለማረም ደብተር ሰብስብ አልኩት፣ አንዱን ተማሪ፡፡ "ማንኛችንም የቤት ሥራ አልሠራንም" አሉኝ፡፡

"እንዴት? አልኩ እየተገረምኩ፡፡

"የሒሳብ የቤት ሥራችንን ስላልጨረስን" አሉኝ ተማሪዎቹ።

"ለምን አልጨረሳችሁም?"

"ስለማያልቅ!" አንድ ላይ ጮኹ፡፡

ግራ ተጋባሁ፡፡ ከብዙ ምልልስ በኋላ ገባኝ፡፡ ቲቸር አንበሴ የሚሰጡት የቤት ሥራ ከብዛቱ የተነሳ የማያልቅ ነው፡፡ ሌሎች አስተማሪዎች የሰጡዋቸውን የቤት ሥራ ትተው የቲቸር አንበሴን



ብቻ ከሠሩ፣ ጠንከር ያሉት የማጠናቀቅ ዕድል ይደርሳቸዋል፡፡ ሌሎች ግን እስከቻሉት ለፍተው ዳር ማድረስ ይሳናቸዋል፡፡ 'እንዴት ብሽቅ ነው ይሄ ቲቸር አንበሴ!' አልኩ በልቤ፡፡ 'ከሂሳብ በቀር ሌላ ትምህርት ላይማሩ ነው? ለርዕሰ መምህራችን ልንገረው' አልኩና በልቤ፣ መጀመሪያ ግን ራሱን አንበሴን ማናገሩ እንደሚሻል ወሰንኩ፡፡ ካሁን አሁን ደነፋብኝ እያልኩ ሃሳቡን አስረዳሁት፡፡ የልጆቹን ችግር ገለፅኩለት፡፡ እንዴት መሆን እንዳለበት አማከርኩት፡፡ መልሱም አንጀቴ ጠብ አለች፡፡" አለኝ፣ በእርካታ ስሜት ፈገግ ብሎ፡፡

"በጭራሽ አንተ አሁን የምትለኝን ቀደም ብዬ አላሰብኩትም፡፡ ግን እንዳልከኝ ልጆቹን በጣም አስጨንቃቸው ነበር ለካ? እውነትክን ነው፡፡ እንኳን የነገርከኝ። ይህንን ስህተቴን አስተካክላለሁ" አለኝ፡፡ ከዚህ በኋላ ልጆቹ የሌሎቹን የትምህርት ዓይነቶች የቤት ሥራ ለመሥራት ጊዜ አገኙ፡፡" አለና ከዓመታት በፊት የተከናወነውን ድርጊት አሁን እንደሆነ ሁሉ በርካታና በደስታ አስታውሶ "ቲቸር አንበሴ አሪፍ ሰው ነው፡፡ ከስህተታቸው ሁሌም ለመማር የሚጥሩ እንደ አንበሴ ዓይነት ነብስ ያላቸው ሰዎች ናቸው" አለና ፀጥ ብሎ ያብሰለስል ጀመር፡፡

እኔም በዝምታ ማስተዋሌን ቀጠልኩ፡፡ አንዴ የጨዋታውን ቦይ ካስያዝኩት እርሱ የትዝታውን ምዕራፍ እየገለፀ እንደሚሄድ አውቃለሁ፡፡ ወደ ሌላ ምዕራፍ ሊሄድ ሲል እመልሰዋለሁ፡፡

ሦስተኛ ክፍል እበሩ ሥር አስቸለው ይቀመጣል፡፡ የአስርና የአስራ አንድ ዓመት ልጅ ይሆናል፡፡ ሁሉም ነገር ያስቀዋል፡፡ ሳቁ ደስ ይላል፡፡ እውነቴን ነው፡፡ ይህችን የአስቻለውን ሣቅ በሙዚቃ ኖታ በመዘገብኳት የምታሰኝ ነች፡፡ ይኸ የግዕዝ ፊደላችን ሊጽፈው አልቻለም እንጂ" አለና ሳቀ፡፡

አንድ ቀን የዕለቱን ክፍለ ጊዜ አስተምሬ አብቅቼ ልወጣ በሩጋ ስደርስ ይህ አስቻለው ልክ ልመታው የቃጣሁ ይመስል ዱላውን ለመሸሽ ጎንበስ አለና እጆቹን መከተ፡፡ አንተ ምን ሆንክ? አልኩት፡፡

"ይመቱኛል ብዬ ነው እኽኽኽኽኽኽኽኽ"

"ለምንድነው የምመታህ?"

"ቲቸር' አንበሴ ሲወጡ ሁሌ ይመቱኛል ኽኽኽኽ"

"ለምንድነው ቲቸር አንበሴ የሚመቱህ?"

"ስለሚመቱኝ ነው ኽኽኽኽኽኽ"

"ክፍል ስለደገመ ነው ቲቸር" አለ አንዱ ተማሪ፡፡

"ይኸን ክፍል ስደግም ሦስተኛ ዓመቴ ነው ኽኽኽኽኽ"

@Amharicbookstore

"በል አይዞህ እኔ አልመታህም" ብዬ ወጣሁ። ከዚያ በኋላ አስቻለውን ብዙ ጊዜ አስታውሰዋለሁ። ለአራተኛ ጊዜ ክፍል ደግሞ ይሆን? ከዚህ በኋላ ልከታተለው አልቻልኩም። ምክንያቱም ጋሼ ኃይሉ ሚካኤል ያቀደልኝን ሦስተኛና የመጨረሻውን እድገትም ሳላገኘው ቀረሁ። በሚቀጥለው ዓመት አልተመለስኩም።

ማስተማሩን በጣም ወድጄው ነበር። ተማሪዎቼም አሊቃዬም የማስተማር ችሎታዬን ወደውልኛል። ደመወዜም ለእኔ መተዳደሪያ በቂዬ ነበር። ኧረ እንዲያውም ከበቂ በላይ ነው። ግን ችግር ተፈጠረ። የ24 ዓመት ጎረምሣ ብሆንም፤ ድካም የማይበግረው ትኩስ ኃይልነት ቢጠበቅብኝም አልቻልኩም። ምክንያቱም በወቅቱ ጤናማ ሆኜ ክብደቴ 44 ኪሎ ግራም ነበር። ሳስተምር እውልና ማታ እቤቴ እገባለሁ። ራቴን በልቼ አልጋዬ ላይ እወጣለሁ። የሚመስጠኝን ልቦለድ ጋደም ብዬ ማንበብ እጀምራለሁ። የታሪኩ ጣዕም ሰበት እስከ እኩለ ሌሊት ሊያስኬደኝ ሲገባው እኔ አምስትና ስድስት ገፅ እንዳነበብኩ ድካምና እንቅልፍ ተመካክረውብኝ ይዘውኝ ጭልጥ ይላሉ። ሁልጊዜ ከሦስት ሰዓት በፊት በእንቅልፍ እሸነፋለሁ፤ በዚህም ምክንያት ማስተማርን መሰናበት እንዳለብኝ ወሰንኩ። ከማስተማር ክቡር ሙያ ጋር በፍቅር የተሳሰርነውን ያህል በድካም ተፋታን። ማመልከቻዬን ጻፍኩና ወደ ትምህርት ሚኒስቴር 'ስኮላርሺፕ' ክፍል ተዛወርኩ።

የመጨረሻ ብሽቅና ድብርታም የሆኑ፣ የተከፈተውን የተማሪ አንጎል የሚዘጉ ጥቂት አስተማሪዎች የትም ምንጊዜም አሉ። እነርሱን ሳንረሳ ስለ መምህርነት ሳስብ ሁልጊዜ በልቤ እንዲህ እላለሁ። እኔ እንደማውቀው ከአየርና ከውሃ ቀጥሎ መሠረታዊ የምንጊዜም ፍላጎታችን ምግብ ነው። የምግብን አቅርቦት የምናገኘው ከገበሬ ነው። ገበሬ መኳንንትን፣ ወይዛዝርትን፣ ምሁራንን፣ ነጋዴዎችን፣ ወንበዴዎችን... ይመግባል። እነዚህ ሁሉ ሥራቸውን ሲሠሩ ዝናብ አይነካቸውም። ፀሐይ አይመታቸውም። ምቾት ነው ዕጣቸው። የብልጠትና የጉልበተኞች ሣይሆን የሐቀኞች ፍትሕ ቢኖር ኖሮ ከማንኛውም ኀብረተሰብ ክፍል የገበሬ ገቢ፣ ወይም ደመወዝ ሊበልጥ በተገባ ነበር። ከገበሬው የሆዳችን አምላክ ቀጥሎ የጤናችን አምላክ የሆነው ሐኪም ከፍተኛ ደመወዝ ሊከፈለው በተገባ ነበር። ከእነዚህ ቀጥሎ የአእምሮዎቻችን መብራት፣ የታዳጊው መንፈሳችን ኩትኳች የሆነው መምህር በጣም ወፍራም ደመወዝ በተገባው። ይህ ያለንበት ዓለም ግን የፍትሕ ሳይሆን የብልጠትና የዕድል ዓለም

@Amharicbookstore



ነው። በመሆኑም አስተማሪነትን ስተው ቀለል ወዳሉ ሥራዎች ወፈር ወዳሉ ደመወዝ ተሸጋገርኩ።

በሁኔታው አዝናለሁ እንጂ ሁኔታውን ልለውጠው ስለማልችል ከራስ በላይ ነፋስ ብዬ ከነፋሱ መጠለልን መረጥኩ። ተራ ራስ ወዳድ ሰው ነኝ፣ እንጂ ከታደሉትና መስዋዕት ለመሆን ከሚፈረጁት ጥቂቶቹ ጎን የምሰለፍ አይደለሁም። እግዜር ይቅር ይበለኝ። ይቅር እንደሚለኝ አውቃለሁ። እሱ ነዋ እንዲህ አድርጎ የፈጠረኝ። በነገራችን ላይ፣ የእኔ ዘመን ትውልድ ተማሪዎች እያለን የኔታ የነበረው አስተማሪ፤ እኛ ደርሰን መምህር እንባል ነበር። አሁን ደግሞ 'ቲቸር' ሆኗል አጠራሩ።

"ኸ! ልክ ነህ። እንኳንም ያስታወስከኝ። በሕይወቴ ስለማልረሣው ታላቅ አርቲስት አበራ ላጫውትህ።

የአያ-ድቡልቡሌን ተረት እንደ አዲስ ያስተዋወቀኝ አበራ ነው። በበኋለኛው የሕይወት ዘመኔ ስጽፍ አያ-ድቡልቡሌ ገፀ-ባህሪዬ እንደሆነ እንነብበናል።

ሦስተኛ ክፍል ሳስተምር የገጠመኝ ነው። የፈተና ሰሞን ነው። እኔ የማስተምራቸው እንግሊዘኛ በመሆኑ ለጥናት የሚረዳቸው የምጨምርላቸው ነገር የለም። ስለዚህ እንዲዝናኑ አስቤ ተረት አወራላቸዋለሁ። እነርሱም ለክፍል ጓደኞቻቸውም ለእኔም እንዲያወሩልን እጋብዛለሁ። በዚህ ጊዜ አሁን የማላስታውሰውን ተረት አውርቼላቸው እንደጨረስኩ አበራ ተነሳ። በዕድሜ ከሌሎቹ ይበልጣል። ማውራት ጀመረ። አተራረኩ ሁሉ ትዝ ይለኛል።

ተረቷ አያ ድቡልቡሌ ስለሚባል ጭራቅ ነው የምትተርከው። በዚህ ጊዜ አበራ ተራ በተራ እየጠራች ለፍልሚያ ቤተሰቡን የምትልክ ገፀ ባህሪ አለችው።

ባህሪዋ "አባዬ... ተነሣ! ጋሻ ጦርህን አንሳ!" ብላ ትልካለች። አባዬ እንደደረሱ በአያ ድቡልቡሌ ዋጥ ስልቅጥ ተደረጉ። "ጋሽዬ ተነሳ፣ ጋሻ ጦርህን አንሳ" ብላ ትሸኛለች። ጋሽዬም እንደወጣ ቀረ። በመጨረሻም "እታበባ ተነሺ ጋሻ ጦርሽን አንሺ" ትላለች። ሁሉንም አያ ድብልብሌ ጭጭ ምጭጭ አደረጋቸው።

ከዚያም አበራ በገፁ ላይ ምንም ዓይነት መሸበርም ሆነ፤ መደንቅ ሳይታይበት "ጋሼ አበራ ተነሣ፣ ጋሻ ጦርህን አንሣ" ትለዋለች።

አበራም አስደናቂ የሆነ የወንዳወንድ ባህሪ አሳይቶን ተነሣ። ጋሻውን መኩቶ፤ ጦሩን ወደረ። ይህንን ሁሉ በድርጊት ይገልፀዋል። ወጣ፤ አያ ድቡልቡሌን ገጠመው። አበራ አስገራሚ በሆነ

ቅልጥፍናው አያ ድቡልቡሌን ገደለው፡፡ አቤት እንዴት አድርጎ ተጫውቶት አስደነቀኝ መሰለህ!? 'የትም በኬድ የምንማረው ከምንወዳቸው ሰዎች ነው' ይልሃል ጎተ፡፡ እኔ ላስተምር ገብቼ ከአበራ ተምሬ ወጣሁ፤ ልልህ እችላለሁ፡፡ መማር ከፊለክ ዓይንህን ግለጥ፣ ጆሮህን ክፈት፡፡ ራስህን መቻል ስትጀምር ከቤትህ መውጣት ትጀምራለህ፡፡ መንደር ውስጥ ትገባለህ፡፡ ከተማ፣ ወይ ገጠር ውስጥ ትኖራለህ፡፡ ከአገርህም ትወጣለህ፡፡ ዓለም ውስጥ ትገባለህ፡፡ አሁን ደግሞ ዓለም በሙሉ አገርህ ትሆናለች፡፡

ጎጃም፣ ጎንደር፣ ጋሞና ትግሬ... ይሉሃል እዚያ ያሉ ሰዎች፡፡ እዛኛውጋ ሕንድ ምናምን ይጠሩልሃል የጎሣና የብሔር መዓት፡፡ እንዲህ እንላለን እንጂ ሁሉም ያው ሰው ነው፡፡ ለመሽጋገር የተለያየ ድልድይ ያስፈልግሃል፡፡ ያወቀውን የሚያሳውቅህ፡፡ የተተረጎመውን አንተ ወደምታነብበት ቋንቋ የሚያመጣትም፡፡ ረዥም የቅብብሎሽ ሰንሰለት፡፡

እዚህጋ ደግሞ የሚገርምህ ዓይነት ሰው ይከሰታል፡፡ ማን እንዳለው አላውቅም፡፡ እኔው ልሆን እችላለሁ፡፡ ሰው ሚች አምላክ ነው፡፡ የአምላክን ያህል አቅም አለው፡፡ ሰውን ዝርያውን ስትወስድ ሚች ባይሆን ኖሮ የሙሴ እግዚአብሔር ወይም ዘዩስ በለው፣ የአምላክ የቁጣ መሣሪያ ምንድናት? መብረቅና ነጎድጓድ አይደለችም? ስንት ገድላለች? ምንም ያህል አላጠፋችም መብረቂቱ፡፡ ከፊለክ በሂሮሺማና ናጋሳኪ ላይ የፈነዳውን አቶሚክ ቦንብ ታሪክ አስብ፡፡ የፈጀውን ሕይወት ታያለህ፡፡ ታዲያ እኛ ከአማልዕክቱ እንበልጥም እንዴ? እንዲህ ነው ጉልበታችን አየህ፡፡ ይህንንም ምስጢር ገልፀህ እንድታይ ማነው ያሳየህ? መምህር ነው!!

"ትምህርት ያገኘን ሕዝብ በቀላሉ ይመሩታል፡፡ ሊነዱት በፈለጉ ግን እጅግ አስቸጋሪ ዳገት ይሆንባቸዋል፡፡ የተማረን ማስተዳደር ቀላል ነው፡፡ እንደ ባሪያ መግዛት ግን ከቶም አይቻልም" ይልሃል ሎርድ ብሮዋም፡፡ በፍቅር የሚያስተምርህም መምህር አለ አሀ! እሱ አስተማረንጂ አልጻፈም፡፡ ተከታዮቹ ጥፈውለት መንገዱ የማረከኝ ሰውዬ ኢየሱስ ይባላል፡፡ የመፅናት ጉልበቱ ቢኖርህ በእሱ መንገድ ነው መሄድ፡፡ የእሱና የጴጥሮስ ግንኙነት አሪፍና ደስ የሚያሰኝ ነበር፡፡ እንዲያውም የሁለቱ ግንኙነት ብቻ ነው 'ድራማዊ' ጥበብ ያለው፡፡ አሪፍ መምህርና ደቀ መዝሙር ሲገናኙ እንዲህ ይመስጡሃል፡፡ በፀፀት የሚያለ ቅሰው፤ እዚህ አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የሚባለው፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንተ ሰይጣን



የሚባለው ጴጥሮስ ነው፡፡ እንሂድ ወደ ግሪክ፣ የማደንቃቸውን መምህር ላሳይህ፡፡

ያኸው በምናቤ ሶቅራጥስ ታየኝ፡፡ "እኔ እማውቀው ያለማወቄን ነው" ይልሀል፡፡ እውቀቱ የሚወጣው ካንተ ውስጥ ነው፡፡ እኔ ግን አዋላጅ ማለት ነኝ፡፡ ሶቅራጥስ ተማሪዎችን የሚያስተምራቸው በውይይት ነው፡፡ ለምሳሌ ሶቅራጥስ "አስተማሪ ያስፈልገናል ስትል ምን ማለትህ ነው? አስተማሪ ባይኖርህስ?" ይልሃል፡፡ አንተም "መምህር ሆይ!" ብለህ የሚስማህን መሆን አለበት ያልከውን ትናገራለህ፡፡ ሁሉንም ነገር ካንተ ውስጥ ያወጣል፡፡ እናም ሶቅራጥስን 'ሞዴል' መምህር ነው የምለው፡፡ መካከለኛው ምስራቅም አሪፍ መምህራን በቅለውበታል፡፡

"ማለፊያ፣ ተማሪዎች! እንጠቅስላችኋለን" አለና ቀልዴን በቀልድ መለሰ፡፡ ካቲካላውን ፉት ብሎ በውሃው ተጉመጠመጠና "ሩሚ የሚባል ታላቅ የፋርስ ገጣሚ ነው፡፡ አንድ ቀን የታወቁ መምህር ሩሚ ቤት መጡና 'ግጥሞች ትጽፋለህ ይባላል ሰምቼያለሁ፡' አሉት፡፡

"አዎን አሉኝ" ሲል ሩሚ ይመልሳል፡፡

"አምጣቸው እስኪ?"

ሩሚም አመጣቸው፡፡ ብዙ ደብተሮች ላይ የተጻፉ ናቸው፡፡ መምህርም አገላብጠው ሳያዩዋቸው አጠገቡ ባለ የጉድጓድ ውሃ ውስጥ ጨመሯቸው፡፡ "ና! እንሂድ" ብለው አስከተሉት፡፡

ሩሚም ተከተላቸው፡፡ የሱፊዎቹ ዋነኛ ገጣሚ ሆነ፡፡ ..." አለና "ወደ ሩቅ ምስራቅ እንሻገር!" አለኝ፡፡

በጣም የምወዳት የኩንግ ፉ ትዙ (ኮንፉሽየስ) ታሪክ አለች፡፡ ኩንግ... የመላውን ቻይና ነብስ ቀረጸ ይባልለታል፡፡ አንድ ምሳሌ ልንገርህና ይህንን ርዕስ ቻው! ቻው! እንበለው፡፡

መምህር ኩንግ... ከደቀመዛሙርታቸው ጋር ሲጓዙ ሰንብተው ሩቅ ወደሆነ ወደማያውቁት አገር ደረሱ፡፡ ቦታው ደንና የዱር እንስሳት መናኸሪያ ነው፡፡ ግን እዚያው ውስጥ የምትኖር አሮጊት አለች፡፡ እንዴት እዚህ ዱር ውስጥ ኑሮን ለመዱችው? በምን የተነሣ? መምህርና ደቀመዛሙርቱ ፈለጓት፡፡ በብዙ ድካም አገኙዋት፡፡

"ሙሉ ቤተሰቤ ካገራችን ተሰደን እዚህ መኖር ጀመርን፡፡ አራዊቱ ዘመዶቼን አንድ በአንድ እየበሉ ጨረሱብኝ፡፡ የእኔም ተራ እስኪደርስ እንደዚህ አለሁ" አለች ሴትዮዋ፡፡

"ካገርሽ ባትወጪ ይሻል ነበር?" አሉ መምህር፡፡

"እዚያማ ጨቋኝ ገዢ አለ" አለች ሴትዮዋ፡፡

@Amharicbookstore

"ተማሪዎች፣ ልብ በሉ፡፡ ጨቋኝ ገዢ ባለበት ከመኖር በዱር አራዊት እየተበሉ በነፃነት መኖር ይመረጣል" አለ መምህር ኩንግፉ ትዙ...

አንድ ጊዜ እንደ ነፍሴ የምወዳቸውን መምህሬን የኔታ ገብረ መድህንን ትምህርት ሚኒስቴር መጥተው አገኟቸው፡፡ በወቅቱ እኔ ስኮላርሽፕ ጽሕፈት ቤት ሥራ ጀምሬያለሁ፡፡ አመጣጣቸው ለሥራ ነው፡፡ ትሕትናቸውን አስታውስ፡፡ ግራ ጎብቷቸው መተላለፊያ ላይ ቆመዋል፡፡ ሰላምታ ሰጥቻቸው ጉዳያቸውን አስፈጽሜ ሸኘቼአቸዋለሁ፡፡

እንዲሁ ከነአበራ አርቲስቱ ጋር አንደኛ ደረጃ ያስተማርኩት ተማሪዬ ትምህርቱን ጨርሶ ራሱን ችሎ ኢጋጥሞኝ እየተገባበዝን ስንጫወት ውለናል፡፡

ጋሼ ስብሐት በየካቲት መጽሔት በ1978 ሰለሽቱ ዘ ዳዕሚዳ በሰጠው ቃለ ምልልስ ስለ መምህርነት ሲናገር "የመምህርነትን ሙያ አቤት ስወደው! ለምን መሰለህ? ሽኩቻህ ጥልፊያህ ከማወቅና ካለማወቅ ጋር ነው፡፡ እምትመቀኘው ሌላን ሳይሆን ድንቁርናን ነው፡፡ የሚያስደስትህ ደግሞ የዘራኸው አድጎ ሲያፈራ ማየትህ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን የመምህርነት ሙያ በጣም እወደዋለሁ፤ ክቡር ነው፡፡

***

፳

## "የተወለድኩብሽ ያደኩብሽ ሀገር"

በሀገራችን በየትኛውም አቅጣጫ ብትሄድ በአብዛኛው የምትመለከተው ጎጆ ቤትና ውብ መልክአ ምድር፣ የገበሬውን ሕይወት፣ እንስሳቱንና እርሻውን፣ መስኩን ታያለህ፡፡ በከተሞቹ አካባቢ ስትዘዋወር አንድ አስጋልት መንገድ፣ ጥቂት የድንጋይ ቤቶችና ሱቆች ያጋጥሙሃል፡፡ አንዱ ከአንዱ ሀገር የሚለየው በሕዝቡ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ባህል ታስተውላለህ፡፡ ለጆሮህ አዲስ የሆኑ ቋንቋዎች ትሰማለህ፡፡ ይህ ነው ትልቁ ፀጋህ፡፡ ትልቁ ደስታህ፡፡ ሰው ነህና ከሰዎች ጋር ትሆናለህ፡፡

@Amharicbookstore



ቀደም ብሎ በነበረን እምነት ሕዝቡንም አገሬንም እወዳለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም፡፡ ወጣት ስለሆንኩ ከሰው ጋር መኖርን ነበር ያስቀደምኩት፡፡ርቄ ስሄድ ግን ይህቺን ሀገርና ሕዝብ እንደምወድ ተገለጠልኝ" አለኝና አሳለው፡፡ ሳስሉም እንዳበቃ "ይኸውልህ ሳሎቹም ለኔና ላንተ ውይይት እጅ ይነሳሉ፡፡"

ውጪ ሀገር ሆኜ ናፍቆቴ ተቀሰቀሰ፡፡ አሃ! ለካስ ሀገሬን እወዳታለሁ! ይህኔ የአስቴር አወቀን ዘፈን ታስታውሳለህ፡፡ 'እኔም ሀገር አለኝ የሚታይ በሩቁ' ዘፈኑ ትዝ ይልሃል?

አሜሪካ ሰባት ወር ቆይቼ ስመለስ መጀመሪያ የናፍቆቴ መወጫ ያደረግኩት ምን መሰለህ? ዘር አልኩና መንገድ ዳር ሸናሁ፡፡

እ! ነቀምት ሄጃለሁ፡፡ በወቅቱ የደረጀ ዱሬሳ ሠርግ ይካሄድ ነበር፡፡ ጋባዦችን እማማ የሺመቤት ሀገሬ ነው የምድርህ አሉና ጋበዙን፡፡ መጀመሪያ እዚህ አዲስ አበባ አገባና ደግሞ እናቱ ሊድሩት እዚያ ተጓዝን ማለት ነው፡፡ እዚያ ነው ከኦሮሞ ባህል፣ ወግ፣ አስተሳሰብ ጋር የተዋወቅኩት፡፡

ሐረርጌ የሄድኩት ምናልባት የ36 ወይም 37 ዓመት ጎልማሳ ሆኜ ነበር፡፡ በወቅቱ ለአሜሪካ የሰላም ጓድ የቋንቋና የባሕል ትምህርት ሥልጠና እንሰጥ ነበር፡፡ የእኛ ሀገር አስተሳሰብና ወግ ግር እንዳይላቸው እና ባለማወቅ ሰው እንዳያስቀይሙ ስናሠለጥን አንዱ የሥራ ቦታዬ ድሬዳዋ ነበር፡፡ እዚያ እያለሁ እንዴት ሐረርን ሳላይም ብዬ ወደ ሐረር ሄድኩ፡፡ እዚያም አብዲ፣ ሰላምይሁን፣ ጥበበ ተርፋ ተቀበሉኝ፤ ተዋወቅኩ፡፡ አስራ አምስት ቀን እዚያ ቆየሁ፡፡ ሐረር ምን ዓይነት ትልቅ ሥልጣኔ እንደሆነች አየሁ፡፡ የእውነት ነው ዩምልህ ዓለም የሚያደንቀው የኢትዮጵያውያን መስተንግዶ ነበር የተደረገልኝ፡፡

ይኸውልህ፡፡ እንደ እኔ አይነት ተፈጥሮ ካለህ ስለ ሐረር ማንበብህ አይቀርም፤ ነገር ግን ሄደህ እዚያው ሀገሬው ሰው ጋር ስትኖር ሌላ ሰው ሆነህ ነው የምትመለሰው፡፡ ለምሳሌ ሴትዮዋ ከትልቅ ግቢ ስትወጣ አምስት ሰባት ቤተሰብ አይደለም ያለው?

ማንም ሴት በርዋን አትዘጋም፡፡ "እኳሌት እየሄድኩ ነው፡፡ ቤቴን እያየሽ?" ብላ ውልቅ ነው፡፡ አለቀ፡፡ እንዲህ ተሰባስበው ነው የሚኖሩት፡፡ ምክንያቱም በቁጥር ጥቂት ናቸው፡፡ እንዲህ ካልተሰበሰቡና ካልተፋቀሩ እየተዳቀልን እንውጣቸውና ያልቃሉ፡፡ የአይሁድ ምስጢርም ይኸው እኮ ነው፡፡ ግን የአይሁዶቹ ይጠንክራል፡፡ እየተገፉ

ነውና እውነት አላቸው፡፡ እነዚህ ሐረሬዎች አልተገፉም፡፡ ስታያቸው ደስ ይልሃል፡፡ ጨዋታም አለ፡፡

እንደሱ ሳይሆን! ሁላችንም እንደየአቅማችን ነው፡፡ አየህ፣ ሺህ አሉ፡፡ ማነው ይህ ሠፈር?

የቂርቆስ ሺህ እየዞሩ "ሠፈሩ ደህና ነው ወይ?" ይላሉ፡፡ ሰው ደግሞ ይነግራቸዋል፡፡ "እማማ እገሊት ፍራንክም የላቸው፣" የሚላስ የሚቀመስም አጥተዋል" ይሏቸዋል፡፡ ሺሁ ይሄዱና እንዲህ አይነት ችግር አለ አዋጡ!" ይላሉ፡፡ ያሰባሰቡና ለተቸገረው ይደርሱለታል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሥልጣኔ ነው ያላቸው፡፡ በሕይወት እየኖረ ያለ ሥልጣኔ፡፡

ጎንደርን፣ ጢስ ዓባይን፣ ላሊበላን፣ አክሱምን አይቻቸዋለሁ፡፡ ቆይማ" አለና አብሰለሰለ፡፡ "ቢቃ አንዱን በራሴ ወጪ ሌላውን አንዱን በአሜሪካ ሰላም ጓድ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ስሠራ ገንዘብ ባይኖረኝ አልችልም ነበር፡፡ ይኸውልህ፣ ምንጊዜም ፎቶ ብትል፣ ከለር ፊልም ብትል እነዚህን ታሪካዊ ቦታዎችን በሥዕል ብታይ አላየሃቸውም፡፡ እዚያ ሄደህ ስታያቸው ነው ተአምራቶቹ የሚገለፁልህ::

መጀመሪያ ስታየው ውስጥህ የሚመጣው ጥያቄ ሰውዬው እንዴት መጀመሪያስ ሐሳቡን ፀነሰው? እንዴትስ ይህ ተራራ አንድ ወጥ ድንጋይ እንዳለው አወቀ? ውጥኑ እንዴት እንደሚሰምርለት አብሰለሰለው? የምታነሣው በርካታ ጥያቄ አለ፡፡ ታብሰለስላለህ፣ ታውጠነጥናለህ ትገረማለህ፡፡ ቤተ ክርስቲያን መዝግባ የያዘችው የለም?

እ! እንዲህ ዓይነቶቹን ታሪካችንን ለእኔ ብዙ ጊዜ ታናሽ ወንድሜ ተወልደ ነው የሚያስተምረኝ፡፡ በተለይ የትግሬን ማኅበረሰብ ሕይወትና አስተሳሰብ እሱ ነው፡፡ ምክንያቱስ? ብትል እኔ በልጅነቴ ነው አዲስ አበባ የመጣሁት፡፡ እርሱ ግን ጎርምሶ ነው አዲስ አበባ የመጣው፡፡ ስለዚህ በቂ የሆነ የታሪክ ስንቅ ከትውልድ ሀገሩ ይዞ ስለመጣ አሁን የማጫውትህን እሱ ነው የነገረኝ፡፡ ፈርኦን ያንን ፒራሚድ ሲሠራ ስንትና ስንት መስዋዕትነት ተከፈለበት አይደል?

ላሊበላ ደግሞ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ሲያሰራ ተጽፎ የደረሰን ገድል እንደሚለው ሌሊት ሌሊት መላእክት ናቸው ያነፁት፡፡ ላሊበላም ቀን ሲፀልይ ነው የሚውለው፡፡ ኢየሩሳሌም በቀን ሦስቴ ሄዶ ይመለሳል፡፡ ይህ የነገርኩህ የገድልን ምንጭነት ጠቅሰን ያገኘነው ነው፡፡

ታናሽ ወንድሜ ተወልደ ሲያጫውተኝ ይህንን የላሊበላን ቀረፃ የካሄዱት ሠራተኞች በግዕዝ የሚዘምሩት እሮሮ ነበር፡፡ "አንተ



ድንጋይ ዝም አትበል፣ ተናገር የእግርና የእጅ ደም እየተንገፈቀ ገፈቀ ያወረዛህን::"

ታዲያስ! እንግዲህ ስንት ግርፋትና ስቃይ እንዳለ አስብ፡፡ ስንት መስዋዕትነት እንደተከፈለ ልብበል::

ሦስት ፈረንጆችና እኔ ሆነን ነው መቅደላን ለመጎብኘት የሄድነው፡፡ በአካሄዳችን ዓለም ፐብሊክ ሪሌሽንስ መኪና ያቀርባል፡፡ ፈረንጆች የነዳጅ ወጪ ይችላሉ፡፡ ከዚያም አዲስ አበባ እንደገባን መኪናዋን ጋራጅ በማስገባት ያሳድሷታል፡፡ ይህ እንግዲህ የደረጀን የአመራር ጥበብ ያሳይሃል፡፡

ፈረንጁ የፈረንሣይ ዜጋ ዳንየል ጕስኪ ይባላል፡፡ ጓደኛዬ ነው፡፡ ሚስቱም ጀርመናዊ፣ ጓደኛቸውም አለ፡፡ ከደሴ ወጥተን በኩታበር አድርገን ወደ መቅደላ ስንጓዝ ሀፊ ሜዳ ላይ ደረስን፡፡ ወንዝ መሐሉን ያቋርጠዋል፡፡ እዚያ ተቀምጠን ምሣ እንበላለን፡፡ ዳንየል ጕስኪ ተመራማሪ ነበር፡፡ የአጼ ቴዎድሮስን ታሪክ በቴአትር ሊፅፍ ነው የሚጓዘው፡፡ ጀርመኑ አይታወቅም፣ ሂትለር ልኮት ይሆናል፡፡

እዚያ ሜዳው ላይ ምሣችንን ስንበላ ጕስኪ እረኛውን ጠራ፡፡ መጣ፡፡ ምሣ ጋበዘው፡፡ ከዚያም "ማነው የዚህ አገር ንጉሥ?" አለው::

"እኔ እንጃ!" አለ እረኛው፡፡

እኔ አንድ ሐሳብ መጥታልኝ እረኛውን ጠየቅኩት፡፡ ለመሆኑ ገቢያ ሄደህ ሌባ ነጥቆህ ቢሮጥ ምን ብለህ ነው የምታስቆመው?"

"በኃይለ ሥላሴ አምላክ! ነው የምለው" አለኝ፡፡ ንጉሡ ማን እንደሆነ አያውቅም፡፡ አስማት የሆነችው 'ፎርሙላ' ግን ትሠራለች፡፡

ተነስተን ተራራ መውጣት ጀመርን፡፡ ከሩቅ አንድ ሰውዬ እየሮጠ ይመጣል፡፡ ሜዳውን አቋርጦ ወደ እኛ ገሰገሰ፡፡ የሚነዳው ማን እንደሆነ እንጃ ጕስኪ "አቁም!" አለ፡፡ ደረሰብንና እያለከለከ በትሕትና "በጣም ይቅርታ፣ ልናስተናግዳችሁ አልቻልንም" አለ፡፡ ጋሼ ስብሐት አተኩሮ እያየኝ በኃይለ ቃል "አየኸው፣ ትልቅ ሥልጣኔ ማለት ይህ ነው፡፡ ሰው ሰው ነው፡፡ እንግዳ ከሆነ ያለህን መስጠት አለብህ፡፡

አልተመለሰም፡፡ እንደመሰለኝ ከሆነ ጕስኪ "ቆይ! እኛኮ ምግብ አለን" ብሎ ትንሽ ሳያስተናግደው አልቀረም፡፡ ከዚህ በኋላ የተራራውን ወገብ እየወጣን ስንሄድ ሊመሽ ሲል ተንታ እንደርሳለን፡፡ ከመኪና ወርደን ሰውነታችንን ስናፍታታ ከወዲያ ሁለት ሰውዬዎች መጡ፡፡ አንዱ እጅግ በጣም ረገርም ወጣት ፈረንጅ ነው፡፡ ቅላቱ እንዲታይህ የቀይ ሥርና የካሮት ክልስ አስብ፡፡ አንዱ ደግሞ ሎሌ

@Amharicbookstore

አበሻ ነው፡፡ ፈጠን ብለው መጡና "Hi! how are you? ቻርሊ" አለው ዦርጂን፡፡ ለሰላምታው መልስ አልሰጠውም፡፡ ዦርጂ በፀጥታና በቁጣ አፈጠጠበት፡፡ ሶሜሌው ፍጥጫውን ችሎ "ይህ የጄኔራል ናፒዬር የልጅ ልጅ ነው፡፡ ተዋወቁ፡፡ የአያቱን የድል ሜዳ ሊያይ ነው የመጣው፡፡"

ዦርጂ የባሰ ተናደደ፡፡ "አንተ!" አለ፡፡ ሀበሻውን ረግጦ፡፡ "ምን ልታደርግ መጣህ?!" አለው፡፡ "የናፒዬርን ልጅ እኮ ነው፡፡" ጋሼ ስብሐት እየሳቀ፡፡ "ልጁ እኮ ምንም አላጠፋም፡፡ ግን ዦርጂ እንደ ቴዎድሮስ አብዷል፡፡ ተጋብቶበታል፡፡ ቴዎድሮስ እብድም ጂኒዬስም ነበር፡፡ ዦርጂ በእብደቱ "አያትህ የፈፀመው አስከፊ ወንጀል አነሠና አንተ ደግሞ መጣህ?" ሲለው፡፡ ልጁ የእንግሊዝ ዓይነት መልስ ሰጠው፡፡ "እኔም አንተም እዚህ የመጣነው የእኔ አያት የሠራውን ጀብዱ ለመጎብኘት ነው" አለውና ሄደ፡፡ አንድ ጨዋታ ትዝ አለኝ፡፡ ደብረ ማርቆስ ውስጥ የመጀመሪያው የቆርቆሮ ቤት የኡመር ጠጅ ቤት ነበር፡፡ አንዱ እዚያ ካንዷ ጋር ሲደሰት ማደሩን በግጥም ሲገልጽ እንዲህ ተቀኘ፡፡ አባባሉ ትራም አለበት፡፡

አንድ እግሯን አንስቼ ብላት ዳንግላሣ
የኡመር ጠጅ ቤት ቆርቆሮ ተነሣ፡፡

ወደ ደቡብ ኢትዮጵያም? ሄጃለሁ፡፡ በጣም የተዋበው አዋሣ ነው፡፡ ሐይቁ፡፡ ከሐይቁ ጋር አገሩ ውብ ነው፡፡ ከተማዋም ደስ ትላለች፡፡ መሀረቱን የጣሉት ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ናቸው፡፡

አደገኛ ሰውዬ እኮ ነው ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም፡፡ አዋሳን ስታይ በዘፈቀደ ሳይሆን በዘመናዊ ፕላን ነው የተሠራችው፡፡ በወቅቱ አዋሳን አልፌን ዲላ ተጋብዤ ሄጃለሁ፡፡ ሃያ ምናምን ዓመት ቢሆነኝ ነው ዕድሜዬ፡፡ የታላቅ እህቴ ልጅ ጋብዞ ጠራኝ፡፡ በዕድሜያም ይበልጠኛል፡፡ እዚያ ሄጄ ተስተናገድኩ፡፡ ሚስቱ ትራጌ ናት፡፡ ታውቅበታለች መስተንግዶውን፡፡ ዞር ዞር ብለን እንምጣ አለና ወሰደኝ፡፡ አሁን ስገምት እርግጠኛ ባልሆንም ከቤቱ የግማሽ ሰዓት መንገድ ሄደን ሐውልት አለበት ቦታ ደረስን፡፡ በእኔ ግምት ከአክሱም ሐውልት ትንሽ የሚያጥሩ የወደቁ የድንጋይ ሐውልቶች ናቸው፡፡ ቅርፃቸው እንዳለ የወንድ ልጅ ብልት ይመስላሉ፡፡

"በእውነት! ቁላ አልከኮህ እኮ?!" እየሳቀ "ልክ ነህ ግን፣ እንኳን ነግረውን ስናየውም አናምንም" አለ፡፡

@Amharicbookstore



"የሴትን ልጅ ብልት ጨምሮ እንዲህ ዓይነት ሐውልት ታያጥን ውስጥ አለ፡፡ ፈጣሪዎቻችን ተብለው የአምልኮ ሥርዓት ይፈፀምቢታል ብለኸኝ ነበር፡፡ አዎን ብዬሀለሁ፡፡ አገሩ ግን ሕንድ ነው፡፡

እሬትን መሠረት አድርጎ ክርስትና በዚህ በኩል እስልምና በዚያ በኩል አልሆነም? እንደዚያ ከሂንዱይዝም ቡድሂዝም ይወጣል፡፡ ሕንድ ስትገባ የሌለ አማልክት የሌለ አምልኮ የለም፡፡ ያልከውም የመደሰቻና የመራቢያ አካሎቻችን ሐውልት ተሠርቶላቸው እንደ ፈጣሪ ይመለካሉ፡፡

ደቡብ ኢትዮጵያን ስናነሳ አርባ ምንጭን አይቼዋለሁ ከምንጩም በቦዩና ቅጠል ቀድቼ ጠጥቻለሁ፡፡ ሲጣፍጥ ጣዕሙ የገነት ውሃ ማለት ነው፡፡

ትግራይ ደጋግሜ ሄጃለሁ፡፡ በትግራይ ከጆመርኩ ይበዛል፡፡ እ! በቂ የቴፕ ክር ላይኖርህ ስለሚችል...አጠር አርጌ ላሳይህ አልችልም፣ የያዝነው ርዕስ ሰፊ ነዋ!

ከሃያ ዓመታት በኋላ ትውልድ አገሬትን ሄድኩ፡፡ የዚያኔ የገረመኝ ይኸውልህ ከመኪና ወረድኩ፡፡ በእግሬ ሄድኩ፡፡ ከዚያ ቤታችን ከማዶ ሲታይ እናቴ አገኘችኝ፡፡ እልልታዋን አቀለጠችው፡፡ ሁልጊዜ እኮ ወለላይ ዝም ብላ ነው የማውቃት፡፡ በጣም ገረመኝ፡፡ እልል የሴቶች ቋንቋ ነው፡፡ እኛ ኮ እልል አንልም፡፡ ነሸጥ ካላደረገን በስተቀር"፡፡

እንግዲህ አገር ቤት ለዕለታት ቆየሁ፡፡ ደስ የሚል ጊዜ ከወላጆቼ ጋር አሳለፍኩ፡፡ ቀናት አለፉ፡፡ አዲስ አበባ ተመለስኩ፡፡ እንዲህ እንዲህ ስትል አያሌ ምልልሶች ይኖራሉ፡፡ ከረጂም ዓመታት በኋላ አባቴ ሞቱ፡፡ እንግዲህ በአገሩ ባሕል ሬሣውን አሳድረህ ነው የምትቀብረው፡፡ እንደሞቱ በየከረብታው ላይ "ኡ!ኡ!" እየተባለ ይጮሃል፡፡ ጩኸቱን ይቀባበሉታል፡፡ "እገሌ እገሌ ሞተዋልና ቅበሩን ይላሉ" እየተባለ ይለፈፋል፡፡ ያኔ የሚታወቀው ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤት፣ ወዳጆቻችን ይመጡና ሟቹን ይሸኙታል፡፡

እንዲያም ሆኖ ለቀብር የማይደርስ አለ፡፡ ሁለት ሦስት ቀን አይደለም አስራ አምስት ቀን የሚርቅም አለ፡፡ እርሱን ለመካስ አጎበር የሚባል የቀብር ሥርዓት አለ፡፡ አጎበር ማለት ሬሣ የሌለበት ልክ! እርም ማውጫ ነው፡፡ ያኔ ከአዲስ አበባ ተነስተን ለአቦይ አጎበር ነው የምንደርሰው እንደደረስን አገሬው ግልብጥ ብሎ መጣ፡፡ አየህ? አቦይ ለካ ቀብር ካለ ይሄዳሉ፡፡ ሰው ከታመመ ይጠይቃሉ፡፡

ስለዚህ እሳቸውን ለመሰናበት የመጣው በሺዎች የሚቆጠር ሕዝብ ነው፡፡ ያኔ ነው በጣም የገረመኝ፡፡ ያ ወዴት ይወስድሃል መሰለህ? እዚህ አገር መጥቼ በቀይ ሽብር ዘመን አደጋዎችን እኔ እሡር ሆኜ ሳልፋቸው የአቦይና የወለላይ ውቃቢ መልአክ እየጠበቀኝ መሆን አለበት፡፡ በእኔ ቢሆን ነጎድጓድም ይገባኛል፡፡

ከረጂም ፀጥታ በኋላ "የት ነን?"

ጎሽ ውል አትረሳም፡፡ በትግራይ ታሪክ ውስጥ ከሁሉ ጎልቶ የሚታየው ስሁል ሚካኤል ሳይሆን አይቀርም፡፡ ጎንደር እርስ በርስ ጦርነት እንዳይነሳ ፈርታ ተወጥራለች፡፡ አንዱ ወገን ስሁል ሚካኤልን ድረሱልን ብለው ላኩባቸው፡፡ ስሁል ሚካኤል ከበርካታ ሠራዊታቸው ጋር መጡ፡፡ ጎንደር ገቡ፡፡ ሁኔታዎችን አዩ፡፡ ደብተራዎችን አነጋገሩ፡፡ "እንዴት እናርግ? እኔ መንገስ እፈልጋለሁ" አሉ፡፡ በዲፕሎማቲክ ቋንቋ ሳይሆን አይቀርም የተናገሩት፡፡ "ያለውን ንጉሥ እንዴት ገለል እናድርገው?" አሉ፡፡

"ንጉሥማ ከገደሉ ደም ካፈሰሱ ለሰባት ትውልድ የእርስዎ ዘር ሊነግስ አይችልም" አሉዋቸው፡፡ ቢቃ ይቅርብኝ ብለው ሊተውት ሲሉ፣ ሌላ ተንኮለኛ ደብተራ "ደም ሳያፈሱ በሻሽ አንቀው ማሰናበት ይቻላል" አላቸው፡፡

"እውነቱን ነው!" አሉና ራሳቸው አፄን አንቀው ገደሉት፡፡

"በጨለማ የተሠራውን በብርሃን የሚያይ አለ" የሚሉት ብሂል የሚሠራው ለአምላክ ብቻ አይደለም፡፡ ለሰውም ነው፡፡ ወንጀሉን አንዱ ላንዱ እያለ አዳረሰው፡፡ እሳቸው ሀገር ሰላም ብለው አክሱም ሊነግሡ ሄዱ፡፡ ቀሳውስቱ "ደም ያፈሠሠ..." አሉዋቸው፡፡ "እኔ ደም አላፈሰስኩም" አሉ፡፡ "ደም ማፍሰስ ቃል ናት እንጂ አንቀህ ገለሃል" ብለው ከለከሏቸው፡፡ እዚህ ላይ የዘመኑን አስተሳሰብ ታደንቃለህ፡፡

"እሺ" አሉና ሕጉን ስሁል ሚካኤል አከበሩ፤ እንጂ ማንም እንዳደረገው በጉልበት ሊቀቡ ይችሉ ነበር፡፡ ያኔ ዘመኑም አይፈቅድም ማለት ነው፡፡ ከዚያ "ባልነግስም የፈለኩትን አነግሣለሁ" አሉና ደስ ያላቸውን ያነግሡታል፡፡ ስሙ ነው እንጂ ሥልጣኑ በሳቸው እጅ ነው፡፡

ይኼኔ ነው በሀገራችን ውስጥ የመጀመሪያውን ቀይ ሽብር ያካሄዱት፡፡ ጎጃም ሸፈተ፡፡ አጼው ስሁል ሚካኤልን ላኩ፡፡ አንዳንድ ጦረኛ ደግሞ አለ ተሸንፎ የማያውቅ፡፡ ጎጃም የሸፈተውን ገጥመው አሸነፉት፡፡ ተወልደ ሲነግረኝ አሁን የማጫውትህን ጨካኝ ድርጊት የፈፀሙት እዚያው ጎንደር እያሉ ነው፡፡ ከሌላ የሰማሁት ግን



አፈታሪክ ነው፡፡ አፈኛው እንደፈለገ ይነዳዋል ማለት ነው፡፡ ምንጊዜም የታሪኳ ነብስ አለች፡፡

ጎጃምን ድል አደረጉት አላልኩህም? "አውራውን ያዘው" አሉና ቆዳው እንዲገፈፍ አዘዙ፡፡ በሕይወት እያለ፡፡ ከገደሉት በኋላ ቢገፉት ይችሉ ነበር" አለኝ፡፡ ስልል ባለ፣ ባዘነና በተፀፀተ ልሣን "ተገፈፈ፡፡ በቆዳው ውስጥ ሳር ተጠቀጠቀበት፡፡ ላም ልክ ጥጃዋ ሲሞትባት ወዲያው መታለቧን እንዳታቆም ጥጃው ተገፎ በቆዳው ሳር ተጎስጉሶ እንድትታለብ እንደሚደረገው መሆኑ ነው፡፡

ያንንም አውራ የነበረውን ሰው ፈረስ ላይ አስቀምጠው አጀብ አዘውለት ለአጼ የምስራቹን በግልቢያ ደርሰው እንዲነግሯቸው አዘዙ፡፡ አጼ ልባቸው በስጋት እንዳይንጠለጠል፡፡ ከዚያ ስሁል ሚካኤል ረጋ ብለው ሠራዊታቸውን አስከትለው ተጓዙ፡፡ ከዚያ በኋላ ማነው የሚነሣባቸው?

ይህ ወዴት ይወስደናል መሠለህ? ስሁል ሚካኤል ጭርጭስ ብለው ከባለሟሎቻቸው ጋር ተቀምጠው በአገር ጉዳይ ሲነጋገሩ እንቅልፍ ወሰዳቸው፡፡ ከዚያም ትንሽ ቆይቶ ባነኑና "እናንተ፣ አሁንም ሥልጣኑን እኛው ነን የያዝነው?" አሉ፡፡

"አዎን" ሲሉዋቸው፡፡

"አቤት ጠላቶቻችን እንዴት ያከፋቸው?!" አሉ ስሁል ሚካኤል፡፡

አንድ ከትግራይ ጨምረን ወደ ሌላ ጠቅላይ ግዛት እንሸጋገር፡፡ ማይምሻም ውስጥ የተወለዱ የአያቴ አቦይ ተወልደ መድህን ታናሽ ወንድም አሉ፡፡ የፈረስ ስማቸው ተኽላት በፅሐ ነው፡፡ ተክለ ሃይማኖት ነው ስማቸው፡፡ በፅሐ (ጎረምሳ) ከተፍ የሚል ማለት ነው፡፡ ለአማርኛ አንባቢያን በአንድ ወቅት ስጥፋቸው ተክሌ አባ ድረስ አልኳቸው፡፡

ጎበዝ ገበሬ ናቸው፡፡ ባለፀጋ ሆነው ልጆች ወልደው በሌላ ሰዎች ማሳረስ ሲችሉም እሳቸው ግን ግብርናን ሳይለዩት እንዳረሱ ነው የኖሩት፡፡ እንደመሰለኝ አውቀውታል፡፡ ሰውነት ሲንቀሳቀስ ነው ጤናማ የሚሆነው የሚለው ገብቷቸዋል፡፡

በጣም ቀልደኛም ናቸው፡፡ እሳቸው ጠዋት ተነስተው እስኪመሽ በበቅሎ የሚጓዙበት አገር ዙሪያውን በሙሉ የእሳቸው ግዛት ነው፡፡ እዚያ ውስጥ ሕግ አይጣስም፡፡ ኃይለኛ ጭቃ ሹም ወሳጅ አልባ ልጆችንና ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶችን ማናለብኝ ብሎ ርስት ሲነጥቃቸው ተሟጋች ናቸው፡፡ ሁልጊዜ እንደረቱ ነው፡፡ ቀልድም አግበም እየተናገሩ ነው የሚሟገቱት፡፡ ሉገሬው እየተዝናና ይመዘግበዋል፣ ያወራዋል፡፡

አንዱ ጭቃ ሹም አንዱ ገበሬ በድንገት ቢሞት አሁን ነው የዚህን መሬት መጠቅለል ብሎ ሰፍ ሲል፣ አንድ የተቆረቆሩ የአገር ሽማግሌ አንዱን ኀረምሣ ይጠሩና "ለተክሌ አባ ድረስ ሄደህ አትነግርለትም?!" ብለው ይልኩታል፡፡

ተኸላት በፀሐ. ይደርሳሉ፡፡ ደረሱ ማለት ረቱ ማለት ነው፡፡ ዶን ኪሾቴ የትም ማንም ቢደፈር ቢበደል ይደርሳል አይደል? እኝህ ተክሌ አባ ድረስ አላበዱም እንጂ አንድ ናቸው፡፡ እንግዲህ አባድረስ የደረሱላት ሴት ቆንጆ ትሆናለች፣ ወይም ወጣት ነች፡፡ ውለታ ይኖርባታል፡፡ እነሆ በረከት ይሏታል፡፡ በዚህም ምክንያት በየቦታው ልጆች ወልደዋል፡፡

ይኸውልህ፡፡ አንድ የዳሯት ልጃቸው ከባሏ ተጣልታ ቤታቸው ትመጣለች፡፡ "በማታ ምን ሆንሽ ነው?" ብለው ጠየቋት፡፡ ሌላ ሴት ወሽሞ ማኩረፏን ነገረቻቸው፡፡ እሳቸውም ተገርመው "ታዲያ እኛስ እንዴት አድርገን ወለድናችሁ? ሂጂ ወደ ቤትሽ! ከዚያ በኋላ በሽማግሌ እናያለን አሉዋት፡፡" ፈገግ ብሎ ጋሼ ሰብሐት እያስተዋለን "ተክሌ አባድረስ እንዲህ ገብተው ባይዳኙ ባልየው ጠሙን ያድር ነበር፡፡ የትግራይ ገበሬ ሲፀልይ 'ተመስገን ጌታዬ፣ ኀመኔንና እምሴን አትንሳኝ' ይላል፡፡

ተረት ያወሩልኝ አሁን ትዝ የሚሉኝ አንዷ እትዬ ናቸው፡፡ የሥዩም ተፈራ እናት ናቸው፡፡ እትዬ ነው የምንላቸው፡፡ በስማቸው አንጠራቸውም፡፡ ከሥዩም ጋር ጓደኛማቾች ሆነን ስንማባባ ጊዜ "አንተ ከእትዬ ጋር መተዋወቅ አለብህ" ብሎ ወሰደኝ፡፡ ያጫውቱን ብዙ ታሪክ ነው፡፡ ለልጆቻቸውም ቀደም ብለው አጫውተዋቸው ስለነበር "እትዬ፣ ያንን አጫውቺው" እያሉ ረፈረንስ ይጠቅሱላቸዋል፡፡ እትዬም ደስ እያላቸው ቡናችንን እየጠጣን ያወጉልናል፡፡

አንተ ልጅ ይበዛብናል፡፡ ብዙ እኮ ነው፡፡ አንድ ሁለቱን ለቅምሻ? እናውጋ እሺ፡፡ አገር ቤት ነው፡፡ ከመንደር ይርቃል፡፡ ቤቱ ፈንጠር ብሎ ኀረቤት የለውም፡፡ ወንዙን ተሻግሮ አንድ ትልቅ ዛፍ አለ፡፡ ሰውየው ቤቱ በገባ ቁጥር ዛሬ ማታ ደግሞ አምስት ሆነው ጠበቁኝና..." ብሎ ለሚስቱ ጉራውን ይነፋል፡፡እንዴት እንዳንቆራጠጣቸው ይነግራታል፡፡ ይህም ጉራ ተደጋገመና ሚስት ሰለቸት፡፡ አንድ ቀን የእሱን ልብስ ለብሳ ዛፉጋ ጠበቀችው፡፡ ሲመጣ ቁም አለችው፡፡

ቆመ፡፡

"ተንበርከክ" አለችው፡፡

ተንበረከከ፡፡

ከዚያ ሱሪዋን ዝቅ አድርጋ ቂጧን አፈንድዳ "ሳም" አለችው፡፡

@Amharicbookstore



ሳመ፡፡

ከዚያም "ከዚህ የተነሣህ ሮጠህ ከዓይኔ እስክትጠፋ ብረር" አለችውና ሩጫውን ሲጀምር እሷም በአቋራጭ ቤቷ ገብታ የዘወትር ልብሷን ለብሳ ጠበቀችው፡፡

እሱ ሮጦ አለክልኮ ደረሰ፡፡ ማንም የለም ብሎ ቆም ብሎ ተረጋግቶ እንደገና ጉራዋ መጣች፡፡ ቤት ገብቶ "አምስት ሰዎች አጋጠሙኝ" አላት፡፡

"ድምፃቸውን ስሰማ ወደ ጨለማው ዞር አልኩና" ብሎ መተርተሩን ሲጀምር፣

"አንት ውሸታም!" አለችው፡፡

"እንዴት?" ሲላት

"ስትመጣ እንዲህ እንዲህ አላጋጠመህም?" አለች፡፡

"አዎን፣ አዎን፣ አዎን!" አለ፡፡

"እና ቂጥ አልሳምክም?"

"አዎን፡፡"

"እኔ ነበርኩ!" ስትለው፡፡

"እኔ ደግሞ ይህንን ቂጥ የት ነው እማውቀው እያልኩ እኮ ነው የሳምኩት"

እትዬ እንዲህ ዓይነት ጨዋታዎች ብዙ ያውቁበታል፡፡ አሁን ደግሞ ጭፍግ (ትራጀዲ) ያጫወቱኝን ልንገርህ፡፡

ገደል አፋፍ አጠገብ ነን፡፡ ቆንጆ እርሻ አለ፡፡ ገበሬው ሸመገለ፡፡ ወንድ ልጁ ይጠረዋል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የልጁ ሚስት ባለቤቷን "አሠናብተኝ!" አለችው፡፡ "ምነው? እወድሻለሁ፣ ጠንክሬ እየሠራሁ ነው፣ ምን በደልኩሽ?" ሲላት

"አንተ አይደለህም፡፡ አባትህ ነዘነዙኝ፡፡ አልቻልኩም፡፡ ሁልጊዜም እንደጨቀጨቁኝ ነው" አለችው፡፡

"ጊዜ ስጪኝ፡፡"

"እሺ!" አለች፡፡

ልጅ አባቱ ጋ ሄደና "አባዬ ጥሩ ድረኸኛል፡፡ ለዚያም አመሰግን ሃለሁ፡፡ ቆንጆ ሚስት ነው የዳርከኝ፡፡ ነገር ግን በነገር ነትጉተህ ሚስቴን ልታባርርብኝ ስለሆነ ወይ ዝም ትላለህ፤ አለበለዛም ሌሊት ወስጄ ገደል ነው የምጨምርህ፡፡ ልብ አርግ!" አለው

"ዝም እላለሁ፡፡ ትክክል ነች፡፡ እሷ ምንም ያኀደለችብኝ ነገር የለም፡፡ እንደልብ ነው የምታበላኝ፡፡ በጣም ነው የምታከብረኝ፡፡ በሽታ ሆኖብኝ ነው" ብሎ አባት ተናዘዘ፡፡ "ከእንግዲህ አይለም ደኝም" ዕድል ተሰጠው፡፡

ጠባይ ነውና፣ ሳምንት እንኳ ሳያልፍ ሚስት አሁንም መጣችና "አሰናብተኝ" አለች፡፡

"ነዘነዘሽ?"

"አዎን፡፡"

"በይ ራት እንብላ፡፡ ነገ ጠዋት አሰናብተዋለሁ" አላት፡፡

ራት ከበሉ በኋላ አባቱን አዝሎ ወሰደና ገደል አፋፍ ላይ አወረደው "ከፈለክ ገደል ግባ፣ ከፈለክ የፈለከውን ሁን! አባቴ ስለሆንክ ግን አልወረውርህም" ብሎ ጥሎት መጣ፡፡

ይህ ጎረምሳ ደግሞ ተራውን አረጀ፡፡ ልጁ ሲጠረው አባት ባሕሪው ተለወጠ፡፡ እንደ ሼክስፒርና ግሪኮቹ ትራጀዲ ቴአትሮች ልክ መጣ፡፡ ቀደም ብዬ ያልኩህን አባት ደገመ፡፡ ምዕራፍ ሁለት ልትለው ብትችልም ታሪኳ እንዳለች የቀድሞዋን ሆነች፡፡

በመጨረሻ አባት አላረፈም፡፡ ልጅ አዝሎ ሊጥለው ወሰደው፡፡ አፋፍ ሲደርሱ የታዘለው "እዚህ አውርደኝ፡፡ እኔም አባቴን ከዚህ አላሳለፍኩትም" አለው፡፡

ኢትዮጵያን በንባብ ላሳይህ? በዓለም ታሪክ መድረክ ላይ ሁሌም ኢትዮጵያ አንዱን ገፅ ባህሪ ሆና ታያታለህ፡፡ ይህንን በተመለከተ የፃፍኩትን አላነበብክም!?

የኢትዮጵያን ታሪክ የምትጀምረው 3ሺ ብለህ ነው፡፡ ከመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ የምታገኝት ሳባን ነው፡፡ የሳባ ታሪክ ውብ ነው፡፡ ለጥበብ ፍቅር ብላ ያንን ሁሉ መንገድ መሄዷ ይማርካል፡፡

ሌላው የካሌብ ታሪክ እንዲሁ ያስደስታል፡፡ አንዳንዱን እየጠቃቀስን ላጫውትህ፡፡ አሁን ሱዳን አካባቢ ያለ አገር ድሮ ኑቢያ ይባል ነበር፡፡ ሜሮዌ ከተማቸው ነው፡፡ በወዲህ ደግሞ የአክሱም ሥልጣኔ አለ፡፡ ሁለቱ የለየላቸው ጠላቶች ናቸው፡፡ አፄ ካሌብ ዘመተና ኑቢያን ድምጥማጧን አጠፋው፡፡ ከዘመናት መረሣት በኋላ አርኪዎሎጂስቶች ሄደው ቆፍረው ሜሮዌ የምትባል ከተማ እንደነበረች አሳወቁን፡፡

ካሌብን በራሱ ዓይን እያየን ጨዋታችንን እንቀጥል፡፡ አለዛ አይጥመንም፡፡ ባሕር ማዶ ያሉ ክርስቲያን አሕዛብ ተጨቆኑ፡፡ ያኔ እስልምና አልተሰበከም ገና ነበር፡፡ የቆስጥንጥንያ ንጉሥ ወደ ካሌብ የጦር ስርዳታ አድርጎ ጎረቤቶቹን ክርስቲያኖች እንዲታደጋቸው መልዕክት ላከ፡፡ ካሌብም የድረሱልኝ ድምፁን ሰምቶ ጦሩን ሰበሰበ፡፡ መርከቦችም፣ ሠራዊትም፣ የጦር ዝሆኖችም አስከትሎ ዘመተ፡፡ ሄደው ተዋጉና ድል በድል ተጎናፀፉ፡፡ በዚያን ዘመን ማንም አረብ

@Amharicbookstore



ዝሆን አይቶ አያውቅም፡፡ ውጊያውም The year of the elephant ተባለ፡፡ ነብዩ መሀመድም ይህ ጦርነት በተካሄደ ባመቱ ተወለዱ፡፡

ወላሂ! ካሌብ ከጦር ሲመለስ በመሬት ውስጥ ለውስጥ ነው የመጣው፡፡ ለወታደሮቹም መመሪያ ተሰጣቸው፡፡ ከሚነሱበት አገር አሸዋ አፍሰው እንዲመለሱ፡፡ አንዳንዱ ትንሽ ቆነጠረ፣ አንዳንዱም እሚችለውን ያህል ያዘ፡፡ እዚህች ቅድስት አገር ሲደርስ ያ አሸዋ ወርቅ ሆነ፡፡ ትንሽ የያዘውም ቆጨው፣ ብዙ የያዘውም ቆጨው፡፡ ጨምሮ ሊይዝ ይችል ነበራ! በዚህ ምክንያት የዘገነም አዘነ ያልዘገነም አዘነ ተባለ፡፡

ወደ ምስር እንሻገራለን፡፡ የአሁንዋ ግብፅ ድሮ ስምዋ ምስር ነበረች፡፡ ከግብፅ ነገሥታት አብዛኛውን ጊዜ ፈርኦን ወንድ ነው፡፡ ነገር ግን ሕጋዊ መብቱን የሚያገኘው የእናቱ ልጅ ስለሆነ እንጂ የአባቱ ልጅ ስለሆነ አይደለም፡፡ አልጋው የሚወረሰው ከእናቱ ነው፤ ነገር ግን በወንድ ትልበት ነው የሚረጋገጠው፡፡ በዚያን ጊዜ ሀትሼፕሱት የምትባል ንግሥት ተከሰተች፡፡ ይህች ሴት ከታላላቆቹ ፈርኦኖች አንዷ ሆነች፡፡ ይህች ሀትሼፕሱት ግማሽ ኢትዮጵያዊት ነበረች ይባላል፡፡ በእርግጥ የታወቀ ነገር የለም እንጂ፡፡ እንቀጥላለን፣ እንቀጥላለን እ! የት ነን አሁን?

ከግብጾች ጋር ነን? ይብቃን ስለግብፅ፡ ወደ ጥንት ግሪክ እንሂድ፡፡ አውራ ገጣሚያቸውና የባሕላቸው ዋናው መሠረት የሆነው ሆመር ስለኢትዮጵያ እንዲህ ይለናል "አማልክቱ በየዓመቱ አንድ ጊዜ የሰው ልጅን ከማስተዳደር ጣጣ ለማረፍ ወደ ኢትዮጵያ ሄደው፣ ድንቅ መስተንግዶ ተደርጎላቸው ይመለሳሉ" ኢትዮጵያውያን ደግሞ እንግዳ ተቀባይ፣ የእግዜር እንግዳ ባዮች ነን፡፡ ይህ አባባል የሚሠራው በገጠር ባሕላችን ነው እንጂ፣ የአዲስ አበባውማ ቱሪስት ብላ! ነው የሚልህ፡፡ ሠልጥኗላ!

ወደ ኢየሩሳሌም ስንሄድ እዚያም ኢትዮጵያን እናገኛታለን፡፡ ከ12ቱ ሃዋርያት አንዱ የሆነውን ፊሊጶስን መንፈስ ሂድና ወንጌል ሰበክለት ለኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባ ይለዋል፡፡ ይህ ጃንደረባ ለንግሥቷ እንደ ገንዘብ ሚኒስትሯና የውጪ ጉዳይ ኃላፊ ጭምር ነው፡፡

ይህ ሐዋርያ ሲመጣ ጃንደረባው ሰረገላ ውስጥ ተቀምጦ ትንቢተ ኢሳያስ ውስጥ ስለ ኢየሱስ ያለውን ትንቢት ሲያነብ ሰማው፡፡ "ሰላም! ግባ" ብሎ አስተናገደው፡፡ "የምታነበውን ተረድተኸዋል ወይ?" ሲለው "ማን ነገረኝና እረዳዋለሁ?" አለ "እኔ እንግዳያው

ልግለፅልህ፡፡ አሁን ያነበብከው ትንቢት ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" ብሎ ወንጌልን አስተማረው፡፡ ጃንደረባው ይህንን አድምጦ "እንግዲያው ውሃ እዚህ'ጋ አለ፣ እኔ ብጠመቅ የሚከለክል ነገር አለ እንዴ?" አለው፡፡

"ይፈቀዳል እንጂ" አለውና ሐዋርያው አጠመቀው፡፡

የመጀመሪያው ክርስቲያን ቄሳር ቆስጠንጢኖስ ሆነ፡፡ እናቱ ንግሥት እሌኒ ከልብ ክርስቲያን ናት ከልብ፡፡ ጾም ጸሎቱ ስግደቱ ሳይቀር፡፡ በዚያ ዘመን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ጠፍቷል፡፡ የት እንደገባ አይታወቅም፡፡ ኢሌኒ እየሩሳሌም ሄደች፡፡ እዚያ ሱባኤ ገባች፡፡ "እጣን አጭሺ" ተብሎ በራዕይ ተነገራት፡፡ በበነጋታው ጠዋት ደመራ የሚያክል እጣን ተለኮሰ፡፡ ጢሱ ወደ ሰማይ ወጣና በቀስተ ደመና ቅርፅ በግማሽ ክብ ሠራና ሽቅብ ርቆ ቁልቁል በመመለስ ምድር ላይ አረፈ፡፡ ኢሌኒ ይህንን ስፍራ አስቆፈረች፡፡ እዚያም መስቀሉ ተገኘ፡፡

ለአራት ተቆረጠ፡፡ አንድ አራተኛው ወደ ኢትዮጵያ ተላከ፡፡ ግማደ መስቀል ይባላል ሲያሚው፡፡ በዚያን ጊዜ አፄ ዳዊት ነበሩ፡፡ የት እንደሚያስቀምጡት ጨንቋቸው፡፡ ከልብ አማኝ ስትሆን ያስጨንቃል፡፡ በሕልማቸው "መስቀሌን በመስቀል ላይ አኑረው" አላቸው ጌታ፡፡ ምን ማለት ነው ብለው ቆላ ደጋውን ሲዘዋወሩ ግሼን አምባ ደረሱ፡፡ ሲያዩዋት ቅርፅዋ ልክ መስቀል ይመስላል፡፡ "እዚህ ነው ቦታው!" ብለው ንጉሥ ዳዊት አስቆፈሩና መስቀሉን ቀበሩ፡፡ በዚህም ቦታ ላይ ግሸን ማሪያምን አሠሩ፡፡

"ነብዩ መሐመድ በጣም የሚወዷት የልጃቸው ባል ዓሊ ይባላል፡፡ በእምነቱም ጽኑ፡፡ ነብዩ ለዓሊ ፍቅራቸው ጥልቅ ነው፡፡ በአንድ ወቅት በእስልምና ተፃራሪዎች ይገደላል፡፡ በዚህም አሁን በእምነት ተከታዮች እንደ ሰማዕት ነው የሚታየው፡፡ ዘመናት አለፉ፡፡

ይኸውልህ እንደገና በእስልምና እምነት ደግሞ ኢትዮጵያ ወደ መድረኩ ስትገባ ነቢዩ ከመካ ባለጣኦቶች ጋር ተጋጩና ለቅርብ ተከታዮቻቸው አደገኛ ጊዜ መጣ፡፡ ስለዚህ ነብዩ፣ "ሂዱ ወደ ኢትዮጵያ፣ የመጽሐፍ አገር ነው" አሉዋቸው፡፡ እስራኤልና ኢትዮጵያ ሁለቱ የመጽሐፍ አገር ይባላሉ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ማለት ነው፡፡

"ንጉሡ ይቀበላችኋል፡፡ እዚያ ቆይታችሁ ጊዜው ሲደርስ እንል ክባችኋለን" ብለው እሳቸው ወደ መዲና ሄዱ፡፡ ተከታዮቻቸው ወደ እዚህ መጡ፡፡ አህመድ ነጋሺ ተቀብለው አስተናገዷቸው፡፡ የነቢዩን

@Amharicbookstore



ደብዳቤ አንብቦ እስልምናን እንዲያስተምሩት ጠየቃቸው፡፡ እስልምናን ተቀበለ፡፡ በእስልምና "አጥምቀውት" ማለት ነው፡፡

"ይህ አህመድ ነጋሺ ንጉሥ አይደለም፡፡" የአንድ አካባቢ አዛዥ ነው፡፡ እንደ ካሌብ ዓይነት ንጉሥ ሲኖር አብዛኛውን ቦታ ይገዛል፡፡ ይህኛው ለዘመኑ አጼ አገረ ገዢ ሊሆን ይችላል፡፡ በእነርሱ አህመድ ነጋሺ ነው፡፡ ተቀበላቸው፣ አስተናገዳቸው፡፡ ጊዜው ሲደርስ ነቢዩ መሐመድ በድል አድራጊነት መካ ሲገቡ "ኑ!" ብለው ጠርተዋቸው ወደ አገራቸው ተመለሱ፡፡ አንድ ሰው በሕልሙ ነቢዩ፣ ዓሊ እና አንድ ማንነቱ ሊለየው ያልቻለ ሰው ቆመው ሲወያዩ አየ፡፡ ፍለጋ ጀመረ፡፡ ሐጂ እገሌ፣ ሼህ እገሌ ቢል አላገኘውም፡፡ ይህ በሕልሙ ያየው ሰው በእስልምና ስም እምነት ላይ ታላቅ ሥራ ይሠራል ብሎ ስላመነ ምድረ አረብን አዳረሰ፡፡ አላገኘውም፡፡ ፈላጊው ሰውዬው ተጓዥ ነውና ወደ ኢትዮጵያ መጣ፡፡ በሕልሙ ያየውን ሰው ሐረር አገኘው፡፡ ስሙ አህመድ አልጊራኒ ይባላል፡፡

እኛ መሐመድ ግራኝ የምንለው ነው፡፡ ሕልመኛው ከአህመድ አል ጊራኒ ጋር እየተዘዋወረ የጀግና ወረኛ ገድሉን ጻፈ፡፡ በመጨረሻም ፋቱሕ አል ሐበሻ በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፎ አሳተመ፡፡ አበሻን ነጻ ለማውጣት ማለት ነው፡፡ ይህንን መጽሐፍ ነው የእኛ አገር ታሪክ ፀሐፊው ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ የአህመድ ግራኝ ወረራ በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ፣ በአብዛኛው የተጠቀሙበት፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የጸሎት ማንቂያ አዛን "አላህ አክበር" ያለው ኢትጵያዊ ነው፡፡ እውነት ነው፡፡ ስሙን ቢላል ይሉታል፡፡

እንዴታ! የስነ ግጥም ጉልላታቸው አሌክሳንደር ፑሽኪን አያቱ አሌክሳንደር አኒባል ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ካስታወስክ ሩሲያዊው መምህራችን ሚስተር ሶሎዱሂን ሲናገር "Compared to Pushkin Shakespeare is a crying baby" ብሎን ነበር፡፡ ፑሽኪንን ከሼክስፒር ጋር ብናወዳድር ሼክስፒር የሚያለቅስ ሕፃን ነው፡፡

ይህ አሁን የማጫውትህ ትዝ ያለኝን ነው፡፡ በአንተ ንባብ ደግሞ ወደፊት ተጉዘህ የምታየው ብዙ ይኖራል፡፡ በየትኛውም ዘመን በተከሰተ ታሪክ ብትመረምር ኢትዮጵያዊ ገፀ ባህሪ ታገኛለህ፡፡

ሪቻርድ በርተን የሚባል ተጓዥና ታሪክ ጸሐፊ ሲያጫውተን የዘመኑን የሶማሌ ባሕል ይነግረናል፡፡ ሀብታም የሆነ ሶማሌ ሴት ሲያጭ ልጃገረዷ በተርታ ይቆማሉ፡፡ አጪው ሙሽራ ከጎን ቆሞ

ቂጣቸውን ያያል፡፡ ከሁሉ ወደኋላ የወጣው ቂጥ ይመረጣል፡፡ሆና ነዋ! ደሞስ የሴት ቂጥ ውብ አይደለምንዴ?

ፈረንጆች ከጥንት ግሪካውያን ሮማውያን አንስቶ "ይሄ ተአምረኛ አባይ የሚመነጨው የት ይሆን?" ብለው ለሺዎቹ ዓመታት ሲጠይቁት የኖሩት ጥያቄ ነበር፡፡ በነሱ ዓይን ነው ማየት፡፡

ከካርቱም ከተማ ጥቂር ዓባይን ተከትለው ተነስቶ እስከ ጎንደር ተጉዘዋል፡፡ በእርሱ ገድል አማካኝነትም ኢትዮጵያ እንግሊዘኛው ተናጋሪ ዓለም መድረክ ላይ ታየች፡፡

ሌላ እንግሊዛዊ ታሪክ ጸሐፊ ላጫውትህ፡፡ ቶይንቢ ይባላል፡፡ የሰው ልጆችን ሁሉ ከመጀመሪያችን እስከዛሬ የሚጠቀልል ታሪክ የጻፈ ነው፡፡ A Study of HIstory ይባላል፡፡ በአስራ ሁለት ቅጽ ነው፡፡ ከአንድ አድናቂው ጋር ሆነው ወደ ሁለት ቅጽ አሣጥረው አስነበቡኝና በጣም ወደድኩለት፡፡

ብዙ ታሪክ ጸሐፊዎች ሲጽፉ ወይም ስለ አንድ ጦርነት ብቻ፣ ወይም ረዘም ስላለ ዘመን ይጽፋሉ እንጂ እንደርሱ የሰው ዘርን በሙሉ ጠቅልለው ለመጻፍ አልሞከሩም፡፡ ቶይንቢ በመግቢያው ሲነገርህ ግለሰብ ይሁን፣ ጎሳ፣ አገርም፣ ሥልጣኔም ማኅበርም ብትል 'Challenge and Response' ናቸው የታሪኩን ሂደት የሚወስኑት፡፡

Challenge ማለት ለእናንተ አገር እንዲህ ልንገልጸው እንችላለን" አለኝ:: (በእናንተ አገር ሲለኝ፡ በተራራማው አካባቢ የሚኖረውን የጋሞ ሕዝብ ማለቱ ነው፡) "በዚህች ትንሽ ሀገር ውስጥ ራሳችሁን ቻሉ፡፡ Response እንችላለን ብላችሁ በምትኖሩበት ተራራ እያንዳንዷን ድንጋይ እያጠናችሁ፣ የተፈጥሮ ሀብታችሁን እየተንከባከባችሁ መኖሩን ቻላችሁበት፡፡ ግን በዚያ ተወስናችሁ የራሳችሁን ትልቅ ሥልጣኔ እንዳትገነቡ 'ቻሌንጁ' በዛባችሁ፡፡

ሃዋይ ደሴቶች ስንሄድ ደግሞ ገነት ውስጥ ነው የምንኖረው፡፡ 'ቻሌንጅ' እዚያ የለም፡፡ ሐበሻ ሁሉ በእጃቸው ሁሉ በደጃቸው ነው እንደሚለው፡፡ ለመኖር የሚያስፈልጋቸው ከሚበቃ በላይ አላቸው፡፡ ስለዚህ ተፍጨርጭረው ትልቅ ሥልጣኔ ለመገንባት አልተጋበዙም፡፡

እያልን ግሪክ እንደርሳለን፡፡ ግሪክ ትንሽ ለም መሬት ያላት ዙሪያዋን ማለት እስከሚቻል ድረስ በባህር የተከበበች ድንጋይ የሚበዛባት አገር ናት፡፡ ብዙ ደሴቶች አሏት፡፡ ስለዚህ ለመገናኘት በጀልባ መሆን አለበት፡፡ እያሉም መርከብ መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡ ኤውሮፓን ለመውረር የመጣውን የፋርስ ጦር በመርከቦቻቸው ዝነኛው የሳላሚስ ውጊያ ላይ ድል አድርገው መለሱት፡፡

@Amharicbookstore



የእነሱ 'ቻሌንጅና ሬስፖንስ' ተመጣጣኝ ስለነበረ ያንን ድንቅ ሥልጣኔያቸውን ለመፍጠር ቻሉ፡፡

እ! ቶይንቢ እስከዛሬ ድረስ የሰው ልጅ 26 ሥልጣኔዎችን ፈጥሯል ይላል፡፡ ከዚያም ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ነው፡፡

የኢትዮጵያን ሥልጣኔ 'Fossil' ይለዋል፡፡ ፎሲል ማለት ከሚልዮን ዓመታት በፊት ሲኖር የነበረ ፍጡር አሁን ድንጋይ ሆኖ ይገኛል ቅርፁን እንደያዘ አቢሲኒያ ፎሲል ናት፡፡ 'Always the same!' ድግግሞሽ፡፡ ያኸው ቅዳሴውን ትሰማለህ?" በታከተና በሰለቸው ገጽ አስተዋለኝ፡፡

አውሮፓ Living Civilization ነው፡፡ ሕያው ሥልጣኔ እንደማለት ነው፡፡ ለውጥ! እንዲያውም ለውጥ ነው የሥልጣኔያቸው ሞተር፡፡ በነገራችን ላይ ቶይንቢ እዚህ እኛ አገር ዩኒቨርሲቲ 'Lecture' ሊያደርግ መጥቶ ነበር፡፡ ያም ብቻ አይደለም የአቢሲኒያን 'ፎሲል ሲቪላይዜሽንም' ለማየት ይሆናል፡፡

እዚህ ጋ ልብ በል፡፡ ውዳሴን ብቻ ሳይሆን ወቀሣንም አይተህ መቀበል ይኖርብሃል፡፡ ጊቦን የሚባል ታሪክ ጸሐፊ እኛን ኢትዮጵያውያንን ሲገልጸን እንዲህ ይላል፡፡ "ኢትዮጵያውያን ዓለምን ረስተው እነሱም በዓለም ተረስተው ሺ ዓመት ያህል አንቀላፍተዋል"

እሱ አንድ ሺ ዓመት አለው እንጂ እኛስ ሦስት ሺ ዓመት ነው የተኛነው፡፡ ለምን መሰለህ?

እ? ማለት ጥሩ። ኮፒ ብቻ ስናደርግ፣ የኮፒ መዓት ስንሰበስብ ዘመናቱ አለፉ፡፡ በመጀመሪያ አንድ አዲስ ሐሳብ እዚህ ከመሞከራችን በፊት የት አገር ተደርጎ ያውቃል? ነው የምንለው፡፡ አዲስ ነገር ማድረግ መሞከር እርማችን ነው፡፡ እኛ ሀገር አዲስ ፈጠራ ከመሞከሩ በፊት በመጀመሪያ እየሩሳሌም መሞከር አለበት፡፡ እዚያው ድሮ ድንበራችን ላይ እንደቆምን 1966 ዓ.ም መጣና ደረማመሰው፡፡ ላሰብንበት የሕሊና ነፃነታችንን አግኝተናል፡፡ የዓለማችንን እውነታ ነው አሁን ዓይናችንን ገልጸን የምናየው፡፡

እኔ ዘርዓ ያቆብን አላነበብኩትም፡፡ በደንብ ያነበበው ፈጣን ጭንቅላት ያለው አንድ ጓደኛዬ የነገረኝ ነገር አለ፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ ቢመረምር የዚህ ዓለም ምስጢር ሊገባው አልቻለም፡፡ ዋሻ ውስጥ ገባ እንደ ባህታዊ፡፡ "እስኪገለጽልኝ ከዚህ አልወጣም" አለ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር እልህ ውስጥ ገባ፡፡ በኋላም "ተገለፀልኝ" ብሎ ዘርአ ያዕቆብ ከዋሻ ወጣ፡፡ በእኛም ዘመን ደርሶ ተነበበ፡፡

ይህንን የነገርኩህን ታሪክ ያጫወተኝ ሰውዬ ያንተ ዕድሜ እኩያ ነው፡፡ ትንሽ ሳይበልጥህ አይቀርም፡፡ ቱሪዝም ኮሚሽን ይሠራ ነበር፡፡

በአርቲስቲክ ሕንፃ ውስጥ አንድ አፓርትመንት ተከራይቶ ነው የሚኖረው፡፡ ጥሩ ደመወዝ እንደነበረው አስታውሳለሁ፡፡ እሱ ግን በዘርአ ያዕቆብ ፍልስፍና ተመሰጠና ሥራውን አቆመ፡፡ ኪራይ ቤቶች ያከራየውን አፓርታማ ግማሹን አከራይቶ በዚያ እየተዳደረ በራሱ ላይ የቤቱን በር ዘጋ፡፡ አልተገለፀለትም መሰለኝ በዚያ ፈጣንና አስተዋይ ጭንቅላቱ ምንም ሳይነግረን ሱባኤ ላይ እንዳለ ሞተ፡፡

አዎን፡፡ ሳምነር እኛን ሲያስተምረን የጀዝዊት ዓይነት ፍልስፍና ስለሆነ አብሸቆናል እንጂ ለኢትዮጵያ ያለው ፍቅር ከበሬታና ዕውቀት ትልቅ ነው፡፡ ስለዚህ ሣምነርም ክበሬታ ይገባዋል፡፡

"እ?" ትዝ አለው፡፡ ዓይኖቹ እንደ ከዋክብት አበሩ፡፡ አካሉን በቀላሉ ማጣጠፍ መዘረጋጋት ስለሚችል እንደኳስ ነጥሮ መደቧ ላይ እንደ ጃፓን ባሕል በጉልበቶቹ ተንበርክኮ ተረከዞቹ ላይ ተቀመጠ፡፡ በእጆቹ ጉልበቱን ደገፍ ብሎ ገለጻውን ጀመረ፡፡

"የእምነት መመሪያ የሆኑት መጻሕፍትም ኢትዮጵያን ቅድስት አገር ይሏታል፡፡ ኢየሱስ ለእናቱ "ርስትሽ ናት" ብሎ የሰጣት ምድር ኢትዮጵያ እንደሆነች ይታወቃል፡፡ በተለይም በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዓይን ስትመለከተው እውነትነት አለው፡፡

ከታሪክ ጋር እያያዘህ ስትወስደው ደግሞ አንዳንድ ድንቅ የሆነ ገጠመኝ ታስተውላለህ፡፡ ይኸውም ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ሞተው "አሉ" እየተባለ ሰባት ዓመት አገራችንን ገዝተዋታል፡፡ ሕዝቡ እንዳይሸበር ሲፈለግ እሳቸውን የመሰለ ሰው በርቀት ለሕዝብ እንዲታይ ይደረጋል፡፡ ይህ ሰውዬ ሳይሆን አይቀርም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ተዋናይ፡፡" ከልብ ሣቀና፣ ቀጠለ፡፡ "በርግጥም የምኒልክ መሞት በዘመኑ የነበረውን ሕዝብ ሊያስደነግጠው ይችላል፡፡ ልብ አድርግ፣ ምኒልክ ብልህ የሰላም መሪ ብቻ ሳይሆኑ ድንቅ ጥበብን አድናቂ ንጉሥ ናቸው፡፡ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የመሠረቷት እሳቸው ናቸው፡፡ ትምህርት ቤት፣ ባቡር፣ መኪና፣ ሆቴል ብትል ሕክምና፣ ፖስታም ወደ አገራችን ያስገቡት ካህናቱን እየታገሉ ነበር፡፡ እነሱ አገራችን የጥንት ሆና እንድትኖር ይፈልጋሉ፡፡ ምኒልክ ደግሞ የምዕራባዊው ሥልጣኔ ጥቅም ገብቷቸዋል፡፡ እኝህን 'ጂኒዬስ' የሆኑ መሪ ሕዝቡ ሲጠራቸው 'እምዬ ምኒልክ! እንቅልፌ ምኒልክ' ይላቸዋል፡፡ ታዲያ ሥልጣኔንም፣ ሰላምንም የሰጠህን መሪ ሞት መስማት ለሕዝቡ መራር ኀዘን ነው፡፡ ለዚህም ነው በተከታዮቻቸው ኀዘኑ የተደበቀው፡፡ በኋላም ዘመን ገለጠው፡፡ ቀጥለው የመጡት መሪ ጃንሆይ ናቸው፡፡ የምኒልክን ችቦ ተቀብለው ቀጠሉ፡፡ የበኩላቸውን

@Amharicbookstore



ለማድረግም ጣሩ፡፡ ጃንሆይ ንጉሥ ብቻ ሳይሆኑ 'Statesman' የምትላቸው ናቸው፡፡

አሁን ደግሞ ጃንሆይን ጃማይካዊ ሆነን በራስ ተፈሪያን ዓይን እንያቸው፡፡ እዚያ የሚኖሩት ጃማይካውያን ተገፍተዋል፣ በተወለዱበት፣ በበቀሉበት ምድር ነፃ አይደሉም፡፡ በዚህ ጊዜ አገርህንም ትፀየፋለህ፡፡ በመገፋት ብዛት፡፡ ወደ ምሥራቅ ተመለከቱ፡፡ በዚህች አካባቢ አንዲት ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች ምድር አለች፡፡ ኢትዮጵያ ትባላለች፡፡ ለራስ ተፈሪያኖቹ ይህች አገር የተስፋ ምድር ሆነች፡፡ ባንዲራዋን መለዮ እና ማኅተማቸው አደረጓት፡፡ እነሱን ሆነህ ስታስበው ጌታ በዚህች ምድር እንደገና ተወለደ፣ ማንነቱን ስናጣራ ራስ ተፈሪ የእኛ ጃንሆይ ሆኑ፡፡ 'ሰው አምላክ ሆነ፣ አምላክም ሰው ሆነ' የሚለውን ቃል አስታውስ፡፡

የኛ እምነት ተከታዮች ከሁሉም በላይ ይህችን አገር ይወዷታል፡፡ ቦብ ማርሊንም ዜማውን አስታውስ፡፡ የማርከስ ጋርቬ ቅስቀሳንም ልብ በል፡፡ ስለጋርቬ ትንሽ ገለፃ ያስፈልግሃል? OK! የምነግርህ አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ዓለም ራሷ ለጥቁር ሕዝብ ሲኦል ሆነች፡፡ ጋርቬ ለወገኖቹ ነብይ ሆኖ ነጻዋን አገር አመላከታቸው፡፡ መሪው ጥቁር ነው፡፡ ነጻነት አልባውን አህጉር ወደ ብርሃን እየመራ ነው፡፡ ለእነዚያ ነፃነት ለጠማቸው ሕዝብ ጃንሆይ ሰው መሆናቸው ቀረና ሕያው አምላክ ሆኑ፡፡

ጃንሆይ ይህንን አምላክነት ያጠናከረላቸው አንድ አጋጣሚ መፈጠሩን በርቀትም ቢሆን ሲነገር ሰምተናል፡፡ ሳጫውትህ?

ጃማይካ በድርቅ ተመታ በነበረ ወቅት ጃንሆይ በጉዞ ላይ እያሉ ኤሮፕላናቸው ጃማይካ አረፈች፡፡ ልክ ወርደው መሬቱን ሲረግጡ ጠፍቶ የነበረው ዝናብ ዘነበ፡፡ በዚህ ወቅት የራስታ እምነት ተከታይ ሁሉ የጃንሆይን አምላክነት በግልፅ መሰከረ፡፡" አለና ቆመ፡፡ አካላቱን አፍታቶ ዝግ ባለ ሁኔታ መደቧ ላይ ተቀምጦ እግሮቹን ዘረጋቸው፡፡

ሞቼ ብነሳና ዳግም የመኖር ዕድል ቢሰጠኝ? በዘመኑ ካሌብ ብፈጠር ደስ ይለኛል፡፡ አይሆንም ከተባልኩ የጃንሆይን ዘመን እመርጣለሁ፡፡ እሳቸው በዘመናዊ ትምህርት ሊኮተኩቱን ደክመው ነበር፡፡ እኛ ግን ከጥቂቱ በስተቀር አብዛኛዎቻችን ጨነገፍን፡፡

በታህሳሱ ግርግር አሜሪካን አገር ነበርኩ፡፡ ትዝ ይለኛል ተስፋዬ ገሠሠን ልጎበኘው ሺካጎ ሄጄ ነው የሰማሁት፡፡ የጃንሆይ 'ቲፎዞ' ነኝ ብልም፡ በታህሳሱ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ለዘብተኛ ሆንኩ፡፡ 'የሙድ' ነገር ነው፡፡ ሔጄ አላቆመው ነገር ማንበቤ ምን ዋጋ አለው? ተስፋዬ ግን

ጋዜጣውንም፣ መጽሔቱንም እየሰበሰበ በትልቅ ትኩረት ያነባል። እኔንም እንዳነብ ጋበዘኝ።

«አላነብም» አልኩት።

«እንዴት አታነብም? ይኸ እኮ የአገራችን ጉዳይ ነው» አለና ሎሽከበኝ።

ማንበብ ጀመርኩ። በኋላም በ1966 አብዮት ጃንሆይ ከሥልጣናቸው ሲወርዱ አዲስ አበባ ውስጥ ነበርኩ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ሳነብ ኢትዮጵያን ብዙ ጊዜ ይጠቅሳል፡፡ ከወዳጆቼ ጋር ሳወጋ 41 ጊዜ እንደሚጠራት ነግረውኛል፡፡

አዎን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ጊዜ ኢትዮጵያን ይጠቅሳል ይህ በረከት ግን አሁን በምናውቀው የኢትዮጵያ ካርታ ሰፋት ላይ ለምንገኝ ብቻ አይደለም፡፡ የኩሽ ዘር ባለበት ሁሉ ነው በረከቱ የሚደርሰው፡፡ የኩሽ ዘር ባለበት በምናብ ስትሄድ ዓለምን ሁሉ ይታደጋል ልንል እንችላለን፡፡

ዛሬ ከበኸር ልጄ ከኢየሱ ጋር ተገናኝተን ያጫወትኩት ስለ አቡነ ተክለሃይማኖት፣ ስድስት ክንፍ እንዴት እንዳበቀሉ፡፡ እግራቸው ተቆርጣ ቆይታ ክንፍ አብቅላ የበረረችበት ዕለተ ዓመቱ ባለፈው ወር በሃያ አራት መሆኑን አጫወትኩት እየሣቀ "እንዲህ እንዲህ ዓይነቱን ነው ስነግረው የሰነበትኩት፡፡ ስለ ዝቋላ አቦ አጫወትኩት፡፡ ሌላውን እንግዲህ ፍላጎቱ ካለው ኢንሳይክሎፒዲያና ሌሎች መጻሕፍት ውስጥ ሊያነበው ይችላል፡፡

እ! እንደሱ ነበር ሙሉዋችን፡፡ እትዬን ግን እንኳን አስታወስከኝ፡፡ እሳቸውንም አባ ኪዳነ ማርያምንም እጨምርለታለሁ፡፡ አሁን ጥቂት ቀን ስላለው ታሪካዊ ቦታዎችን ለመጎብኘት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ተጉዟል፡፡ ሲመጣ አጫውተዋለሁ፡፡

አሁን ስለ ኢትዮጵያ ያወጋሁህን ባዕድ ሆኜ ባነበው? ሀብታም ከሆንኩ ኢትዮጵያን መጥቼ እጎበኛት ነበር፡፡ ኢትዮጵያዊ በመሆኔ ምንም አይሰማኝም፡፡ ለምን መሰለህ? ልጅ ሆነህ አባት እናትህና ሠፈርህ ነው ላንተ ዓለም፡፡ ከእርሱ ጋር ጥሩ ኑሮ ኖረህ አድገህ ከሆነ ሌላው ሁሉ ትርፍ ነው፡፡ ግን ደስ ይላል፡፡

@Amharicbookstore



፱

# ሚጢጢዋ ተዓምረኛ ደሴት

ሦስት አገሮች አሉኝ፡፡ እነዚህ አገሮች ውስጥ ለጥቂት ማምንታትና ለወራት ያህል ኖሬያለሁ፡፡ በተለያየ ምክንያት ጎብኝቻቸው ሳልጠግባቸው ተለያየን፡፡

"ወይ አዲሳባ? ወይ አራዳ ሆይ፣

አገርም እንደሰው ይናፍቃል ወይ" የሚለው ግጥም በከማ ተሰማ ድምፅ ከወጋችን በስተጀርባ በሐሳብ እየተሰማን፣ ነው ይህንን የሕይወት ገጠመኜን የማጫውትህ፡፡

ምንጫወተው ስለ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና አሜሪካ ነው፡ ኢያንዳንዳችንን እንደፍጥርጥራችን የሚለያይ እንግሊዝ የምንለው አገር አለ፡፡ እኔ በልቤ ቢያንስ የሁለት አገር ሰው ነኝ፡፡ የተወለድኩባት ኢትዮጵያና አዕምሮዬ ያደገባት እንግሊዝ አገሮቼ ናቸው፡፡

የእኔ ትውልድ በትምህርት ቤት ባለፈበት ዘመን ኢትዮጵያችን እንደ ብዙዎቹ የአፍሪካና የእስያ አገሮች የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የባሕል ግዛት ወይም ኤምፓየር ዳር አገር ነበረች፡፡ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምረን የምንማረው በእንግሊዝኛ ነበር፡፡ ከክፍላን የትምህርት መጻሕፍት ውጪ የምናነባቸው የእንግሊዝ ታሪክና ባሕልን በእጅ አዙር የሚያስተምሩ የእነ ቻርልስ ዲከንስ፣ የነ ዊሊያም ሼክስፒርና ሌሎች የልቦለድ ሥራዎች ነበሩ፡፡ እኔም በልቤ ሐበሻ በአእምሮዬ የዳር አገር እንግሊዛዊ ሆኜ አደግሁ፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ እንግሊዝ ስደርስ ከአውሮፕላን ማረፊያው ወጥቼ በዝነኛው ባለፎቅ የለንደን አቶቡስ ተሳፈርኩ፡፡ ፎቅ ወጥቼ ወንበር ላይ ከአንዱ እንግሊዛዊ አጠገብ ተቀመጥኩ፡፡

እንዷም መንገድ ወይም ሕንጻ እንዳታመልጠኝ ዓይኔ እንደ ጠረጴዛ ኳስ ተመልካች ይወረወራል፡፡ ያነበብኩት ሁሉ ትዝ ይለኛል፡፡ እደነቃለሁ፡፡ በፊት የኖርኩበት ዓይነት ስሜት ይሰማኝ ጀመር፡፡ አጠገቤ የተቀመጠው ሰውዬ ከአምላክ የታዘዘልኝ ይመስል የመንገዱን የሕንጻውን ስያሜ ረጋ ባለ ድምጽ ይገልጽልኝ ጀመር፡

ችኩል አትኩሮቴን እየተከተለ ይነግረኛል፡፡ ዕድለኛ አይደለሁ? ቀጠልን ወደ መሐል ከተማ፡፡

ማነህ? ከየት መጣህ? ወዴት እየሄድክ ነው? እያለ በጥያቄ አላጣደፈኝም፡፡ አይቶኛል፣ የፈለግሁትንም ተረድቷል፡፡ ለንደንን ማስተዋወቁ ለርሱ ግብ ለእኔ ፕሮግራሜ ሆነ፡፡

ከኦቶቡሱ ሲወርድ ትልቅ የተጣጠፈ ወረቀት እየሰጠኝ "ይህ ያስፈልግሃል" ብሎኝ ተሰናበተኝ፡፡ ገለጥ አድርጌ ሳየው ለንደንን ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ካርታ ነው፡፡ ለአዲስ ጎብኚ የሚያስፈልገው ዋነኛ ነገር፡፡ አማልክቱን እያመሰገንን ጉብኝታችንን እንቀጥላለን" አለና አረቄዋን ፉት አለ፡፡ በላይዋ ላይ ውሃ ተጎነጨባት፡፡ ወጉን ቀጠለ፡፡

በነጋታው ሌላ ቅን እንግሊዛዊ የታክሲ ሾፌር አጋጠመኝ፡፡ እ! አማልክቱ ለእኔ ያደላሉ!" አለና እጁንም ዓይኑንም በሠፊው ከፈተ፡፡

"ታክሲዋ ባዶ መሆንዋን አረጋገጥኩ፡፡ ለንደንን ተዘዋውሬ ለማየት የምፈልግ እንግዳ ነኝ፡፡ ስንት ልክፈልህ?" ስለው ለንደን ተወልዶ ባደገ የሠራተኛ መደብ አነጋገር "ጎበዝ" አለኝ "ኮክኒ ነኝ" የለንደን ተወላጅ ነኝ ማለቱ ነው፡፡

"ልክ ላንተ ለወጣቱ በጣም የማስፈልግህ አስጎብኚ አግኝተሃል፡፡ እንኳን ደስ ያለህ፡፡ ለአገልግሎቴ አንድ ፓውንድ ትከፍለኛለህ" አለኝ፡፡

እውነትም ለእኔ ተመርጦልኝ የተላከ 'ጋይድ' ኖሯል፡፡ ተወልዶ ያደገባትን ለንደንን ይወዳታል፤ ያደንቃታልም፡፡ ይኮራባታልም፡፡ ወደ ፓርላማ ሕንጻ ይዞኝ ሔደ፡፡ ስንገባ ባዶ ነው፡፡ ምናልባት ቀኑ የበዓል ዕለት ሳይሆን አይቀርም፡፡ አስጎብኚዬ ገለጻውን ጀመረ፡፡

"ይኸውልህ በዚህ በኩል የሕዝብ ተወካዮች ተቀምጠዋል፡፡ ፊት ለፊታቸው እዚህ'ጋ አመለከተኝ "ንግሥቲቱ የሾሙዋቸው የመኳንንት መደብ ተወካዮች (Lords) ተኮፍሰዋል፡፡ ጋይ ፋውክስን (Guy Fawkes) ቦምቡን እንደጨበጠ በዚህኛው በር ገባና እንዲህ ዘለለ!" ብሎ አስጎብኚዬ ጋይ ፋውክስን ተመስሎ ዘለለና "እናም ቦምቡን እንደዚህ አድርጎ ወረወረ!! ከዚያ በፊትም በኋላም ታይቶ ተሰምቶ የማያውቅ መዓት ወረደ" ብሎ መዳፉን እያራገፈ ከታሪካዊ ድራማው ወደ እኔ ተመለሰ፡፡

እዚያው ሕንፃ ውስጥ በሌላ ታሪካዊ አካባቢ ነን፡፡ ገዳም ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ነገሥታት በየተራ የተኳሉ የተዳኑበት፣ ሲሞቱም የሚቀበሩበት የተከበረ ቦታ ነው፡፡ ከዚያ፣ እስካሁን ማንም ጎብኚ ሳያየው የማያልፈውን ዌስት ሚኒስተር ገዳም (Abbey) ለማየት

@Amharicbookstore



በቴምስ ወንዝ ድልድይ ላይ በእግር እየተሻገርን አስጎብኚዬ ቆመ "ታዲያስ፣ ስለ ቴምስ ምን ታስባለህ?" አለኝ፡፡

"እንደ አሲያየሚ ግዙፍ ሳትሆን ሲያዩዋት ሚጢጢ ወንዝ ነች፣" አልኩት፡፡

ከአፌ ነጥቆኝ "አሜሪካዊው ሲጎበኙትም ይህንኑ ስሜት ነው የገለፀው፡፡ እንደዚህ ስንክሣር የተጻፈላት ቴምስ ወንዝ ይህቺ ነች? እኔ'ኮ የአገሬን ሚሲሲፒን፣ ሚዙሪን፣ ናያጋራን፣ አማዞንን ሳይቀር አይቻለሁ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ግን በሐሳቤ የሚገዝፍብኝ ቴምስ ወንዝ ነበር፡፡ ይህቺ መቶ ባልዲ የማትሞላ ወንዝ!" አለ፡፡

"ጌታዬ" አለው አስጎብኚው ኮክኒ "ይኼ እኮ ተራ ወንዝ እንዳይመስልዎ፡፡ ታሪክ ራሱ በዚህ ድልድይ ሥር እየፈሰሰ ነው'ንጂ" ሲለኝ፣ አባባሉን አጣጥሜ ሳልጨርስ ሌላ ጨዋታ ቀጠለልኝ፡፡

አሁን በሞተር ጀልባዎች ጩኸት ምክንያት የቀረ የቴምስ ወንዝ አስደሳች ባህል ልንገርህ፡፡ ሰዎች ጀልባቸውን እየቀዘፉ በወንዙ ሽቅብና ቁልቁል ሲንሳፈፉ በጨዋ ሥነ ሥርዓት እየተደማመጡ ይወራረፉሉ፡፡ በዚህ በኩል ታላቁ ደራሲ ዶክተር ሳሙኤል ጆንሰን የሚያልፉቸውን ባለጀልባ እንዲህ ብሎ አንጀቱን አራሰው፤ "ሰሙኝ ወይ ጌታዬ የእርስዎ ሚስትኮ ላይ ላዩን የሸርሙጣ አሳዳሪ እመቤት እየመሰሉ፣ ውስጥ ውስጡን የሌባ ተቀባይ ናቸው፡፡"

ለንደን መሐል ትራፋልጋር አደባባይ ደረስን፡፡ እጅግ በጣም ረዥም በሆነ ክብ ዓምድ ላይ የታላቁ ፍሊት አድሚራል ኔልሰን ሐውልት ቆሞ ይታያል፡፡

አደባባዩ'ጋ ስንደርስ ታክሲያችንን ቆም አደረገና አስጎብኚዬ እንዲህ አለኝ፡፡ "ዝነኛው የመርከብ ውጊያ ዴንማርክ በኮፐንሀገን ወደብ አጠገብ እየተካሄደ እያለ፣ የኔልሰን መርከቦች እየሸነፉ ነው፡፡ ከበላይ አካል ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡ መልዕክቱን የሚያስተላልፈው ሰውዬ እዚያ ከሩቅ መርከብዋ ላይ ቆሞ በሁለት በትሮች ጫፍ ላይ የተሰቀሉ ባንዲራዎችን ወደላይ ወደታች ወደግራ ወደቀኝ እያውለበለበ ነው፡፡ እዚህ የኔልሰን መልዕክት ተቀባይ አቅርቦ የሚያሳይ መነፅሩን ባንድ ዓይኑ እያየ መልዕክቱን ጻፈና ለአድሚራሉ አቀበለ፡፡ ወደቡን ለቃችሁ ወደዚህ ተመለሱ ይላል፡፡ አድሚራል ኔልሰን አንድ ዓይና መሆኑን ታውቃለህ?"

ለአንተ እያጫወትኩ ለራሴም ደግሜ ማውራቱን እኔም ወድጄዋለሁ፡፡ አንዳንዴ ደስ የሚልህን ጨዋታ ለሌላ ሰው የምታወራ ይመስልሃል እንጂ ለራስህም ነው የምትደግመው፡፡

ወሬም ይደገማል! "አንዳንዴ እውር የመሆን መብት አለኝ" አለና ፍሊት አድሚራል ኔልሰን ቴሌስኮፑን ተቀብሎ በዕውር ዓይኑ ላይ ደነቀረውና እንዲህ አለ "በእውነት ከዚያ የሚሉኩት መልዕክት አይታየኝም" ውጊያው ቀጠለ፡፡ እናም ትዕዛዙ ሳይሻር ድል ለፍሊት አድሚራል ኔልሰን ሆነች፡፡

ሌላውን ዜጋ ቢሆን በአካል ጉዳተኝነት "ቻዎ!" የሚለው የእንግሊዝ መንግሥት ኔልሰንን ገድልህን ቀጥል ታስፈልገናለህ አለው፡፡

መንገዳችንን ቀጠልንና ወደ አንድ ፐብ (Pub) ገባን፡፡ ቡና ሻይ ቢራ የሚሸጥባት ቤት፡፡ 'Ye Cheshire Cat ይባላል፡፡ ገና እንደገባን "ለጉብኝትህ መደምደሚያ የመደብኩልህ ይሔ ፐብ ነው" አለኝ፡፡ አስጎብኝዬ ሲቀጥል "የልብ ወለድ ደራሲያን ጉልላት አድርገን የምናየው ቻርልስ ዲከንስ ለመዝናናት የሚመጣው እዚህች ቤት ነበር፡፡ ና ወደዚህች ጠረጴዛ የእሱ ቦታ ይህች ነበረች ነው የሚሉት ታሪኩን የሚያውቁት፡፡" ብሎኝ ስለ ቻርልስ ዲከንስና ስለተለያዩ ልቦለዶችና ገጸ ባሕርያቱ ሲነግረኝ ቆይቶ ዝም አለና፣ የገዛ ሐሳቡ እየፈነቀለው "አሰበው ጎበዝ!" አለኝ "አሁን እኮ የተቀመጥከው እንቁ ደራሲያችን ቻርልስ ዲከንስ ራሱ ተቀምጦበት የነበረው ወንበር ላይ ሊሆን ይችላል! ይታይሃል እንዴት ዕድለኛ እንደሆንክ?" አለኝ፡፡

በርግጥም የማደንቀው ደራሲ ወንበር ላይ የተቀመጥኩ ያህል ደስ የሚል ስሜት ተሰማኝ፡፡ የታክሲውን ሾፌር ቅልጥፍናም አደነቅኩ፡፡

ዘወር ዘወር አለና ተመለከተ፡፡ ማንም እንደማያየው አይቶ ቶሎ እጁን ሰድዶ ከቄንጠኛ ካርቶን መሳይ ክብ የሲኒ ወይም የብርጭቆ ማስቀመጫዎች አንዷን አነሳና በፍጥነት ኪሴ ጨመራት፡፡ Ye Cheshire Cat ትላለች፡፡

ብሔራዊ ሙዚዬማቸውን ጎብኝቻለሁ፡ አንተ! 'ብሪትሽ ሙዚዬም' ማለት እኮ ራሱን የቻለ ዓለም ነው፡፡ ፈረንሣዮችም ሊቭር የሚሉት ሙዚዬም እንደዛው አላቸው፣ ውብ ነው ጥሩ ቅርስ ሰብስበዋል? ጥሩ ብቻ አይደለም፣ ሙሉ ነው፡፡ 'ከብሪቲሽ ሙዚዬም' የማስታውሰው አንዱ እንዲህ ነው፡፡ እኔ የእንግሊዝ ቲፎዞ ነኝ፡፡ እዚያ 'ኢጂፕሺያን አንቲኩዊቲዝ' እሚባለው ውስጥ ስገባ ያየሁት አስደነቀኝ፡፡ የግብፅን ደንጋይዎን በሙሉ ነው ያመጡት አልኩኝ፡፡ ቶሎ ቶሎ ብዬ ነው ያየሁት፡፡ ሁለት ሳምንት ነው ለንደን የቆየሁት፡፡ እዚያም እዚያም ሄድኩ፣ ግን የግብፅ ቦታ ነው በሙዚዬሙ ውስጥ ከሁሉ ያስደነቀኝ፡፡

@Amharicbookstore



በዚያን ዘመን በመርከብ እንዴት አመጡት? እያልኩ አብሰለሰልኩ፡፡ እኔ ነኝ እንጂ እነርሱማ ችለውታል፡፡

እንዴት መሰለህ፣ ቴዎድሮስ እኮ ያገራችን ሀብት ነው፡፡ እኔን ሆነህ ስታስብ ስለቴዎድሮስ ስትሰማ፣ የቲአትር ድርሰቶችን ስታነብ ስለምታደግ ሰው አገር ሄደህ እሱን ሳይሆን ሌላ ነገር ነው ማየት የምትፈልገው፡፡ አሜንሆቴፕ አራተኛ የሚባል ፈርኦን ነው ለመጀመሪያ ጊዜ 'አንድ አምላክ ብቻ ነው' ያለው ብሎ፣ ሌላ ሁሉ ጣኦት ነው ያለው፡፡ የእኛ ሙሴ የአሜንሆቴፕ ደቀ መዝሙር ነበር የሚሉ አሉ፡፡ ኢጂፕሽያን ዲፓርትመንትን ሳይ በእርግጥም እንግሊዝ የዓለምን አንድ አራተኛ ቢገዛ ነው ግብፅን ራሷን እዚህ ድረስ ያመጣት ነበር ያሰኘኝ፡፡" አለና ተደንቆ "ይኸውልህ በዚህ አኳኋን ነበር ሚጠጣ ግን ተዓምረኛ ከሆነችው ደሴት ጋር የተዋወቅኩት...

***

፲

# ሀገረ አንክል ሳም

ኒውዮርክ እንደ ደረስኩ በአውሮፕላን ማረፊያው ያየሁት ኪነ ሕንፃ ከመደነቅ ይልቅ ታላቅ ድንጋጤ ውስጥ ጨመረኝ፡፡ ልብ አድርግ፣ የአሜሪካኖቹን ታሪካቸውን፣ ልብወለዳቸውን እያነበብኩ ነው ያደግኩት፡፡ ሲኒማቸውን በብዛት ተከታትያለሁ፡፡ እንደዚያም ቢሆን አስደንጋጭ የባሕሎች ግጭት (Cultural Shock) ውስጥ ከመግባት አላመለጥኩም፡፡ ከአውሮፕላኑ እስከ ሻንጣዬ መውረጃ ያለው ቦታ እንኳን ያለጥርጥር መዐት ሀብት ለግንባታው ፈስሶበታል፡፡ እንግዲህ አስተውል፡፡ አውሮፕላን ማረፊያውን ዞሬ ባይ ምን ያህል ያስደንቀኛል? እኔ ደህቼን ብቻ አይቼ ተሸበርኩ፡፡ ሰዎቹን ሳያቸው ግን ፀጥ ብለው ይጣደፋሉ፡፡ ማንም ሲሳቅ፣ ሲጨዋወት አታይም፡፡ ሁሉም ዝም ብሎ መጣደፍ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሀብት በሚፈስበት ሀገር ፈገግታ እንኳን ሱሚ ነው" አለኝና ለአሜሪካውያኑ በጣም ተከዘላቸው፡፡

በዚያ የወጣትነት ዕድሜ ስትሆን ትወስናለህ፡፡ እኔም ወሰንኩ፡፡ አገሬ እዚህ አሜሪካ ሥልጣኔ ላይ ከምትደርስ እንዳለች ትቅር ስል ተመኘሁ፡፡ ምክንያቱም ምንም ደስታ በማይታይባት የሀብት ክምር ላይ ከምትኖር፣ ያጣሆና የነጣህ ሆነህ ሣቅህን ባትነፈግ ይሻላል፡፡ እንዴት የሰው ልጅ ሳቁን ይነጠቃል? ምን ዓይነት አገር ነው?! ሸይጣን ነው ጉድ የሠራቸው፡፡ 'ማቴሪያል'፣ ገንዘብ፣ 'ቴክኖሎጂ' እያልክ ስታግበሰብስ አንተ በጣም የሚያስፈልግ ይመስልሃል፡፡ ስለዚህ መስዋዕትነቱን ትከፍላለህ፡፡ ባገኘህ፣ በሰበሰ ብክ ቁጥር የደላህ ይመስልሃል፡፡ በመጨረሻ ላይ አንተ አግበስባሹ የለህም! እንደሰት ብለን በጣም እንለፋ ነበር፡፡ እዚያው ስንደርስ መደሰቻችን የለም፡፡ በዚህ በኩል አሜሪካውያን ከስረዋል፡፡

በወቅቱ ለሀገሬ የተመኘሁላት የኢጣሊያን ሥልጣኔ ነው፡፡ አሁን ሀብት ሳይበዛበት አይቀርም እንጂ፣ ጣሊያንን በወጣትነቴ ወቅት እንዳየኋት በቂ ሀብት ነበራት፡፡ ከውጪ ተመልካች ሆነህ ሰውን ስታየው ደስተኛ ነው፡፡ ይሠራል፣ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ይደሰታል፡፡ እና በቃ ለሀገሬ የሚያስፈልጋት ዕድገት እንዲህ ዓይነቱ ነው ብዬ ተመኘሁ፡፡ በቅርቡ ግን አንድ አልቤርቶ ሞራቪያ የሚባል ኢጣሊያዊ ደራሲ የጻፈውን አንብቤ አዘንኩ፡፡

ደራሲው እንዳለውም "አገራችን በጣም ጥሩ ነበረች፡፡ አሁን ግን ዕድገት መጠቀና፣ ሀብትዋም በዛና ሁሉም ነገር ተበላሸ" ብሎ ማዘኑን አንብቤያለሁ፡፡ ኢጣሊያኖችም እንደ አሜሪካኖች በሥልጣኔ ምትሀት ደስታቸውን እያጡ መጡ ማለት ነው፡፡

የሀብት ነገር ካነሳን፣ በሀገር ደረጃ ከወሰድከው ከሁሉ የበለጠች ሀብታም አገር አሜሪካ ነች፡፡ ነገር ግን ሀገሮች ሁሉ ያላቸውን ሀብት ለግለሰብ ዜጎቻቸው እኩል ቢያከፋፍሉ ስዊድን ትበልጣለች፡፡ የሚደንቀው ነገር፣ ራስን መግደል የሚበዛውም በስዊድን ነው፡፡

ጃፓኖች ራሳቸውን የሚገድሉበትን ሁኔታ የሚፈጥር የኖረ ባሕል አላቸው፡፡ 'ሀራኪሪ' ወይም 'ሴፑኩ' ይሉታል፡፡ ይህንን ሥርዓታቸውን በተመለከተ አጫውቼሃለሁ፡፡ ጃፓኖች ከምንም ነገር በላይ ክብራቸውን መጠበቅ ነው የሚያስቀድሙት፡፡ የስዊድኖች ራስን መግደል ግን የሀብት መዘዝ ነው፡፡

ከየሀገሩ የተውጣጣን ለትምህርት ወደ አሜሪካ የተጋበዝን ሰዎች በመጀመሪያ ዋሽንግተን ዲ.ሲ ውስጥ የሁለት ሳምንት

@Amharicbookstore



ሥልጠና ተሰጠን፡፡ ትምህርቱ ስለ አሜሪካን ታሪክ፣ ባሕልና ሕግ ነበር፡፡ ከአሜሪካኖች ጋር በባሕል ግጭት ሳንደናቀፍ ለመኖር እንዲያስችለን ዕውቀት እንድንገበይ የታቀደ ነበር፡፡ ሥልጠናው ሲያበቃ ወደ ተመዘገብንባቸው የትምህርት ተቋማት ተበታተንን፡፡

ካላማዙ ወደምትባል ሚሺጋን ስቴት ውስጥ ወደምትገኝ ትንሽ የዩኒቨርሲቲ ከተማ በረርኩ፡፡ ከአውሮፕላኑ ስወርድ አንድ ጎረምሣ ነጭ አሜሪካዊ መጣና "ሚስተር ኢማዛቤር?" አለኝ፡፡

"Yes?" አልኩት፣ እሰው አገር ሄጄ እግዚአብሔር መሆኔ እየገረመኝ፡፡

"ዩኒቨርሲቲው እስከሚከፈት ገና አስራ አምስት ቀን ይቀረዋል፡፡ ከእኛ ቤተሰብ ጋር ነው የምትሰነብተው፡፡ ሚስቴና አንዲት ሁለተኛ ደረጃ የምትማር ልጄ ነን አብረን ያለነው" አለኝ፡፡

መኪናው ውስጥ ገባንና ከተማው ዳር ወደሚገኘው ቤቱ ወሰደኝ፡፡ ያ ቤተሰብ በጣም የሚያስደስት መስተንግዶ አደረገልኝ፡፡ ልጅቱ መኝታዋን ለቀቀችልኝ፡፡ ትምህርት ሲጀመር ሰውዬው ወሰደኝና ከዲክ ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ ዲክ ወደፊት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፈረንሣይኛ አስተማሪ ለመሆን የሚማር ወጣት ስለሆነ፣ እኔ ደባሉ እንድሆን መርጠኝል፡፡ የመረጠኝ በርቀት፣ ገና ዋሽንግተን ሥልጠና ላይ እያለሁ ነበር፡፡ ደነቀኝ የአሜሪካ አርቆ ማቀድ፡፡

ከዲክ ጋር አንድ መኝታ ቤት ውስጥ ስንኖር ሁለታችንም ከመዋደድና ከመስማማታችን የተነሣ ዩኒቨርሲቲው ለገና በዓል ሲዘጋ ወደ ቤተሰቦቹ ጋብዞኝ ወደ ዲትሮይት ከተማ ተያይዘን ሄድን፡፡ የከተማው ዋና መንገድ ሌሊት በኤሌክትሪክ ያሸበረቁ የልደት ዛፎች በተርታ ቆመው ሲጠቃቀሱበት ማየት የሚያስደስት አዕምሮን የሚያስ ፈነጥዝ ትዕይንት ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ዲትሮይት የአሜሪካ መኪናዎች ፋብሪካዎች ማዕከል ናት፡፡

የዲክ አባት ፎርድ ካምፓኒ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ባለሙያ ነው፡፡ ሁሌም የሚያወራው ስለፈረስ ጉልበት ነበር፡፡ አንድ ዝሆን ከመኪና ጋር ሲመዘን ስንት ጉልበት እንዳለው ይተነትንልሃል፡፡ በሌላ ነገር ውስጥ የለበትም፡፡ ሚስቱ ደግሞ ኪነጥበብ አፍቃሪ ነች፡፡ ግን ማን ያጫውታት? መልክዋ ውብ፣ ድምፅዋ ሙዚቃ ነው፡፡ አባቱ ሁሌም ስለፈረስ ጉልበት ሲያወራ ሰለቸኝና ከቤታቸው ወጥቼ ቀረውን ጊዜ ዋይ.ኤም.ሲ.ኤ በሚባል የወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ክበብ ገብቼ ማረፊያ ተከራይቼ አሳለፍኩ፡፡ እዚያ ረከስ ያለ ምግብም ማረፊያም አለ፡፡

አንድ ቀን ዲክ አስር ሳንቲም የያዘ እጁን ዘረጋልኝ፡፡ ምንድነው እሱ? ብዬ ስጠይቀው፣ ከሁለት ሳምንት በፊት ሰልክ መደወያ ሰጥተኸኝ ነበር" አለኝ፡፡

"ታዲያ በእኔና በአንተ መካከል አስር ሳንቲም ይቆጠራል?"

"አንድ ቀይ ሳንቲምም ቢሆን ይቆጠራል፡፡"

"በጓደኞች መሐልም?"

"አዎን!"

እኛና እነርሱ ገንዘብን የምናይበት ዓይን ምን ያህል የተራራቀ መሆኑ ታየኝ፡፡ ግን ባሰበው፣ ባብሰለሰለው ሊገባኝ አይችልም፡፡ በዚህ ረገድ ሁለት የማይገናኙ ዓለሞች ነን፣ እኛ ኢትዮጵያውያንና አሜሪካውያን፡፡

አሜሪካኖቹ ከእኛ በአንድ ሌላ ነገርም ይለያሉ፡፡ ይኸውም እዚህ ሀገራችን ሰዎች ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው ወይም እጅ ለእጅ ተያይዘው እያወሩ እየተሣሣቁ ነው ዘና ብለው የሚሄዱት፡፡ አሜሪካኖች ግን ከግል ሐሳባቸው ጋር ብቻ እንጂ ከማንም ጋር ሳይነጋገሩ ነው ወደ መሥሪያ ቤታቸውም ሆነ ወደ መዝናኛ ሥፍራ የሚሄዱት፡፡ አንድ ፈገግታ፣ አንድ ጫጫታ የለም፡፡ በፍጥነት መራመድ ብቻ ነው፡፡ አቤት! እኛ ከውጪ ሰናያቸው ማሳዘናቸው! ከዚህ ሁሉ ሀብት አንድም ደስታ ጠብ የሚልላቸውም አይመስልም፡፡

የኒውዮርክ ከተሜዎችማ ከዚህም ይብሰባቸዋል፡፡ 'Candid Camera' ወይም ሐቀኛ ካሜራ የሚል አንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ውስጥ አንዱን ሰውዬ እንደነ ዶን ኪሾት የጥንት ዘመን የብረት ልብስ የራስ ቁር አለበሱትና "ታይምስ ስኩዌር" በሚባል አደባባይ እንዲታይ በእግሩ ላኩት፡፡ ይህ ልዩ የሆነ ሰው በአደባባዩ ሲራመድ አንድም የኒውዮርክ ሰው ቆም ብሎ እንኳን አላየውም፡፡ እነርሱ እንደሆን ሲራመዱ እንዳይጋጩ ያህል ብቻ ነው አንድን ሰው በጨረፍታ የሚያዩት፡፡

እንዲህ ተጨንቀውና ተጠበው ሕይወት ከቋታቸው ጠብ የማታደርግላቸው ብዙ ናቸው፡፡ አንዱ አሜሪካዊ እሑድ ቀን ይሠራል፡፡ ለምን? ዕድሜ ለሙሴ፣ ዕድሜ ልካችንን እንዳንለፋ በሳምንት አንዲት ቀን የምናርፍባት አለችን፡፡ እኛ ግን ለምን ቀንበሩ ወረደልን ብለን እንዳከራለን፡፡ ይህንን አሜሪካዊ ለምን በሰንበት ቀን እንደሚሠራ ጠየቅኩት፡፡

"ሳሎናችን ውስጥ ቴሌቪዥን አለን፣ በእኔና በባለቤቴ መኝታ ቤትም አንድ ቴሌቪዥን አለን፣ አሁን ይህንን ሰንበት ሠርቼ የማገኘውን ገንዘብ ለልጄ መኝታ ቤት ቴሌቪዥን ለመግዛት ነው"

@Amharicbookstore



ብሎ፣ ምን ያህል 'የማቴሪያል' ፍቅር እንዳጠመደው አሳይቶኝ አዝኛለሁ፡፡

ከአንድ ሕዝብ ወጥተህ ወደሌላ ሕዝብ ሄደህ ስትኖር ልዩ ልዩ ባሕርያትና ባሕል ያጋጥምሃል፡፡ ይህ ገጠመኝ አስደንጋጭም፣ አሣዛኝም አስደናቂም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን አሁን የምነግርህን ገጠመኝ ያጫወተኝ ተረፈ አሥራት ነው፡፡ ከሐና ጋር ስንጋባም ሚዜዬ ነበር፡፡ በጣም የምንቀራረብ ጓደኞች ነን፡፡ መልኩ ቆንጆና ረጂም ነው፡፡ ቁመናው ከአበሻው ይልቅ ወደ አሜሪካኖቹ ይቀርባል፡፡ ፈገግ ሲል በተለይ ሴቶች የሚረቱለት ዓይነት ወንድ ነው፡፡ አሁን ምን ሆነ መሰለህ?

አንድ ጥቁር አሜሪካዊ አለ፡፡ የእኛን ፎቅ ያጸዳል፡፡ ሊፍቱንም ከላይ ታች የሚነዳው እሱ ነው፡፡ ይህ ጥቁር ሰውዬ አንድ ቀን ተረፈን አሳፍሮ በሊፍት ሲሄዱ ዘሎ ተጠመጠመበት፡፡ ተረፈ ታግለና አመለጠው፡፡ "ወድጄሃለሁ! ፍቅር ይዞኛል" አለኝ ብሎ ነገረኝ፡፡

ለተረፈ ግን የአሜሪካኖችን ባሕል በቲዎሪ ስለሚያውቀው ምንም አልመሰለውም፡፡ እንጂ እንዳልከው ለፀጉረ ልውጥ አስደንጋጭ ነው፡፡ የምትጠይቀኝ አለ? ወይስ እየመጣልኝ ስለሆነ ልቀጥልህ?" አለኝ ጋሼ ስብሐት፡፡

"ጥሩ፡፡ አሜሪካኖች የገር መጨረሻ ሆነው የምታገኝበት ሁኔታ ያጋጥምሃል፡፡ በነገራችን ላይ የትም ብትሄድ የሕዝብ እርጥም የለውም፡፡ የመንግሥት እንጂ፡፡ እኔ እዚያ በነበርኩ ሰዓት የአሜሪካኖችን ገርነት አስተውያለሁ፡፡ አንዷን ላቀብልህ ነው፡፡

በሌላ ጊዜ ከአንድ ነጭ ዶክተር ሻድለር ከሚባል ሰው ጋር አትላንታ ጆርጂያ ሄድን፡፡ በአትላንታ ወደብ ላይ የምትንሳፈፍ የቀድሞ ጊዜ የሚልዬነሮች መንሸራሸሪያ ጀልባ የነበረች አሁን ግን 'Down the hatch' ስንተረጉመው 'ቁልቁል ወደ መርከቢቱ ከርስ' የምትባል በጣም ቆንጆዬ ምግብ ቤት አለች፡፡ እዚያ ለምሣ ጋበዘኝ፡፡ በታክሲ ወደዚያ ለመሳፈር ቆምን፡፡ ባለ ታክሲዎች ሲመጡ ምልክት ሰናሳያቸው ዝም ብለውን ያልፋሉ፡፡ ምን ነካቸው? ስንል አንዱ ነጭ የታክሲዎን መስተዋት ዝቅ አድርጎ "ታክሲ አሁን አታገኙም፣ አድማ ላይ ነን!" አለን፡፡

ዶክተር ሻድለር አንድ ብልሀት ብልጭ አለችበት፡፡ አማከረኝና ተስማማሁ፡፡ አንድ ጥግ ላይ የቆመ ታክሲ ጋ ሄዶ ነጂውን "ለማንም ሰው እንዳትናገር፡፡ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ያውልህ፡፡ እዚያ ጋ ቆሟል" አለና ወደኔ አሳየው፡፡ "ተራ ግለሰብ መስሎ አገራችንን እየጎበኘ ነው፡፡ ለአገራችን እንግዳ ስትል

@Amharicbookstore

በአድማው ውስጥ መሣተፍህን ጣስና ወደቡጋ 'ዳውን ዘ ሃች' ምግብ ቤት አድርሰን" አለው፡፡

"እሺ፡፡ እልፍ ብላችሁ እዚያ ጋ ጠብቁኝ፤ ሌሎቹ ባለ ታክሲዎች እንዳይናደዱብኝ" አለው፡፡

ባለው ቦታ ጠበቅነው፡፡ መጥቶ አደረሰን፡፡ ማድረስ ብቻም አይደለም፡፡ ዶክተር ሻድለር ሊከፍለው ሲል "ያንተ እንግዳ የእኛም እንግዳ ነው፡፡ ገንዘብ አልቀበልህም፡፡ መልካም ጉብኝት!" አለንና ወደ አድማው ተመለሰ፡፡

'ዳውን ዘ ሃች' ደርሰን ደረጃዎቹን ወርደን ምግብ ቤቱ ውስጥ ገባን፡፡ ዶክተር ሻድለር ምግብ ለምታቀርበው ወጣት ሴት እኔ ጃንሆይ መሆኔን ነገራት፡፡

"My goodness! ታላቅ ክብር ነው" አለች ፊቷ በደስታ እየቀላ፡፡ በጥሩ ሁኔታ አስተናገደችን፡፡ በተመገብነውና በመስተንግዶው ረክተን ልንሄድ ስንል የአፍ ማበሻ ወረቀት 'ናፕኪን' ይዛ ወደኔ ተጠጋችና በአክብሮት "ፈርምልኝ እባክህን" አለችኝ፡፡ በዚያን ጊዜ የነበርን ወጣቶች ሁላችን ልል እችላለሁ የጃንሆይን ፊርማ እናውቃት ነበርና ፈረምኩላት፡፡

"በጣም ታድያለሁ! ቤቴ ስደርስ እንዱን ፎቶ አውጥቼ በሱ ቦታ ይህንን ክቡር ጌጥ አስቀምጠዋለሁ፡፡ ሺ ዓመት ንገሥ" አለችኝ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያችን ሴት ሳስታውሳት፣ አጋጣሚና እድል ከራስታዎች ጋር አስተዋውቋት ይሆን? ብዬ አስባለሁ፡፡ ከእነርሱ ጋር ስትገናኝ ስለጃንሆይና አጋጣሚዋ በኩራት ስትተርክላቸው ይታየኛል፡፡ ራስታዎችም አምላካቸው የሆነው ንጉሥ እንዴት ቀላሉን ሕይወት እንደኖረው ተርከውላቸው አጋጣሚዋን ሲያምኑላት አስብና ፈገግ ብዬ እቀራለሁ፡፡ እራሷስ ራስታ ብትሆን በዚያ የእምነት ነፃነት በታወጀበት ዓለም ማን ምን ይከለክላታል?... ወዘተ

የትም አገር ብትሔድ ጥጋበኛ ጎረምሣ ያጋጥምሃል፡፡ ያ ጎረምሣ ሕዝቡንና አገሩን ስለማይወክል ጎረምሣውን እንጂ አገሩንና ሕዝቡን እንዳትጠላ መጠንቀቅ አለብህ፡፡ በተፈጥሮዬ ዝምተኛና ጭምት ነኝ፡፡ ማንም ላይ አልደርስም፡፡ አንዳንዴ ሁሉም ነገር ከምችለው በላይ ሲሆን አውሬ የምሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ደግነቱ፣ የኔ ቁጣ ባሕሪ ለአደጋ ቢያጋልጠኝም አምላክ በሕይወቴ ውስጥ ተዓምር ሠርቶ እንዳመልጥ ያደርገኛል፡፡ አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ፡፡

ካላማዙ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነኝ፡፡ አንድ ጠዋት ቁርስ ልመገብ ወደ መመገቢያው ክበብ ብቻዬን ስሔድ ጉድ ፈላ፡፡ በጣም ረጃጂም የሆኑ ሦስት ነጭ ጎረምሶች በእኔ አቅጣጫ በኩረደኑ ይመጣሉ፡፡



ይሳሳቃሉ፡፡ ከዚያ በፊት ብዙ ሆነው የሚያጋጥማቸውን ጥቁር ከበው እንደሚደበድቡ ደጋግሜ ሰምቻለሁ፡፡ ዛሬ 'የእኔ ተራ ሆነ' አልኩ በልቤ፡፡ በቃ ቀኔ ደርሳለች፣ ማምለጫም የለኝ፣ እያልኩ ከራሴ ጋር መከርኩ፡፡ ቀኝ ኋላ ዞሬ ፈትለክ ማለት ፈለግኩ፣ አልሸሹም ዞር አሉን እያስታወስኩ" አለና ሣቅን፡፡

"እኔ ራሴ ውስጤ እንዳለ የማላውቀው የጉርምስና እልህ መጣብኝ፡፡ 'ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም' አልኩ ለራሴ፡፡ ወደፊት ተራመድኩ፣ የመጣው ይምጣ ብዬ፡፡ ሦስቱም ወደል ጎረምሶች እየቀረቡኝ መጡ፡፡ ተገናኘን፡፡ ፊት ለፊቴ ቆሙ፡፡ ቆምኩ፡፡ ከሁሉም ረዥሙ "ማነው ስምህ?" አለኝ በሚያስገመግም ድምፁ፡፡

"ስብሐት" አልኩት፡፡

"እኔ ሳባት! ማንም ሰው ቢደርስብህ፤ እንዲህ ትንሽ እንኳን ጫፍህን ቢነካው ለእኛ ንገረን፡፡ አፉን እናበላዋለን!" አለኝ፡፡

"ገረመኝ ዘሎ ቢስመኝ አለች ሴትዮ" አለ ፈገግ ብሎ ጭንቅላቱን እየወዘወዘ፡፡ "እሺ" አልኩት፡፡

ከዚያ በኋላማ ወዳጆች ሆንን፡፡ ሽርኮቼ ሆኑ፡፡ ከዚያማ ምን ይጠየቃል? ኳስ ጨዋታ ሁሉ አስተማሩኝ፡፡ 'አሜሪካን ፉትቦል' የሚባል የጨዋታ ዓይነት አላቸው፡፡ ጨዋታው ላይ እኔ ስለጋ ሲያዩኝ በጣም ተገረሙ፡፡ እኔ ስለኳስ በፍጹም የማውቅ አልመሰላቸውም፡፡ እኛም በአገራችን የእግር ኳስ የምንጫወት መሆኑን ነገርኳቸው፡፡ ተደንቀው ወዳጅነታችን የጠበቀ ሆነ...

ላይብረሪ ሣይንስ ለማጥናት ነው አሜሪካን የሄድኩት፡፡ ይህንን ትምህርት እንድመርጥ ያማከረኝ የኮሌጃችን ዲን ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሳነብ ስለሚያየኝ "ለአንተ የሚስማማህ ትምህርት የቤተ መጽሐፍ ሣይንስ ነው፡፡ ዕውቀት በሙሉ ተጨምቆ የሚገኘው እዚያ ውስጥ ነው" ሲል መከረኝ፡፡ አመንኩት፡፡ ወደ ካላማዙ ሄድኩ፡፡ ሁለት ሣምንት እንደተማርኩ ደበረኝ፡፡ አንደኛ፣ የክፍሌ ልጆች አብዛኛዎቹ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በጡረታ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ፣ ትርፍ ጊዜያቸውን በዚህ መስክ አሳልፈው ሲመረቁ በዚሁ ሙያ ለማገልገል ፍላጎት አላቸው፡፡ ዋናዋ አስተማሪዬ አሮጊት፣ ባለሻኛና ባለ ሙስታሽ ነች፡፡ ይህ ሁሉ ድብርቱን አባባሰው፡፡

የምንማረው ትምህርት ደግሞ ከእኔ ኅብረተሰብ ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የለውም፡፡ ለምሳሌ ልጥቀስልህ፡፡ የመጀመሪያው የአሜሪካ ቤተ መጻሕፍት ስንት ቅጽ ነበረው? የሚል ነበር፡፡ ይህንን ማወቅ ለኔ ምን ፋይዳ አለው? አያስፈልገኝም ስል ወሰንኩ፡፡ ሌሎችም ለራሴ በወቅቱ ያመንኩባቸው ምክንያቶች ታክለውበት ተውኩት፡፡

አገሬ ገብቼ ለሕዝቤ ወደምሠራበት ትምህርት እንዲቀይሩኝ ጠየቅሁ፡፡ የውጭ ተማሪዎች አማካሪ በማመልከቻዬ አምናበት “እናስቀይርሃለን” አለች፡፡ እሷም ለሚመለከታቸው ሰዎች ሪፖርት አደረገች፡፡ “እምቢ” አሉኝ፡፡ እኔም በእንቢታዬ ፀናሁ፡፡ ሰባት ወር ሲኒማና ቴሌቪዥን እያየሁ ኑሮዎቻቸውንም እያስተዋልኩ ቆየሁ፡፡ ከዚያም እንለውጥልህ አሉኝ፡፡ እኔ ግን በዚያን ወቅት ወደ አገሬ መመለሱን ፈልጌዋለሁ፡፡ ተመለስኩ፡፡

እንዲህ ነው፡፡ የምንማረው እኮ በኋላ የተሻለ ሕይወት ለመኖርና ባለንበት ማኅበረሰብ ውስጥ የራሳችንን አስተዋፅኦ ለማድረግ ነው፡፡ እንዲያው ዝም ብለው ትምህርት ጥሩ ነው፣ የተማረ ወድቆ አይወድቅም ስላሉህ ብቻ አይደለም፡፡ የዚያን ጊዜ በእኔ የተማሪነት ዘመን የተማረ የሰው ኃይል ጥቂት ነበር፡፡ ሥራ ደግሞ ከፈለግን እንደልብ ነው፡፡ ለምሳሌ ከዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተመርቄ እንደወጣሁ አራት መሥሪያ ቤቶች ማመልከቻ አስገብቼ አራቱም ቦታ “ና!” ብለውኝ ነበር፡፡ ስለዚህ ውጪ አገር ሄደህ መማር እስካላቻልህ ድረስ፣ ለእንጀራ ብለህ ጊዜና ጉልበትህን ማባከን የለብህም፡፡ አሁንም ሳስበው ዝም ብዬ ለመማርና ወረቀቱ እንዲኖረኝ ፍላጎቴ ስለሌለኝ ውሳኔዬ ትክክል ነበር ብዬ አምናለሁ፡፡

በየዕለቱ ሲኒማ ቤት እውላለሁ፡፡ ሦስት ሲኒማ ቤቶች ነበሩ፡፡ ይህ ከሲኒማ ቤት ዩኒቨርሲቲ የምመላለስበት መንገድ ሁከት የሚበዛበት ነው፡፡ የቢስኪሌት ሰንሰለት (ካቴና)፣ የብረት ቦክስና ጩቤ እየያዙ ከተማይቱን ቀውጢ የሚያደርጉት ጎረምሶች መናኸሪያ ነው፡፡ በዚያ ሳልፍ ሳገድም አንድም ቀን እኔን ይህ ሽብር አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ ጎረምሶቹ ወምበዴ ቢሆኑም ሰው ናቸው፡፡ እኔ ለአገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ እንደሆንኩ ከሩቅ ያስታውቃል፡፡ ሰው ደሞ እንግዳን ያስተናግዳል እንጂ አይተናኮለውም፡፡

ሌላም ማኅበራዊ ሕይወት ነበረኝ፡፡ ዳንስ ቤት እሔዳለሁ፡፡ ባልደንስም ቁጭ ብዬ ማየት ደስ ይለኛል፡፡ ዲትሮይት ውስጥ አንድ ቀን በዳንስ ቤት በኩል አልፋለሁ፡፡ ማታ ነው፡፡ ምናልባት በግምት ሦስት ወይም አራት ሰዓት ቢሆን ነው፡፡ በዚያ ሳልፍ አንዱ የዳንስ ቤቱ አስተዋዋቂ ጮክ ብሎ እንዲህ እያለ ይጋብዛል፡፡ “ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች ባሉበት በጣም ጥሩ ሙዚቃ የምትሰሙበት ዳንስ ቤት ይህ ነው፡፡ ግቡና ተዝናኑ!”

እኔም አባባሉን ስሰማ ልቤ ግባ ግባ አለኝ፡፡ ልገባ ተራመድኩ፡፡ ጋባዡ አቆመኝና “ዕድሜህ አይፈቅድም” አለኝ፡፡

@Amharicbookstore



ስሜቱ ገብቶኛል፡፡ እኔ ጥቁር ስለሆንኩ ገብቼ እንድስተናገድ አልፈለገም፡፡ እኔም፣ “ተሳስተሃል፣ዕድሜዬ ይፈቅዳል ተመልከት ፓስፖርቴን” አልኩት፡፡

የሚለኝ ጠፋው፡፡ “ባትገባ ግን ይሻልሃል” አለኝና በምክር አዘል ስሜት አጉተመተመ፡፡ ችላ ብዬ ገባሁ፡፡ ብዙ ሰው አልነበረም፡፡ ባንኮኒው አጠገብ ሄጄ ቆምኩ፡፡ አሁን ‘ባለጌ ወንበር’ የሚባለው እሱ ላይ ወጣሁና ቁጭ አልኩ፡፡ ባሬስታው ምን መጠጣት ትፈልጋለህ?” አለኝ፡፡

“ኮካኮላ!” አልኩት፡፡

“ክፍያው እኩል ስለሆነ ቢራ ጠጣ” አለና ከፍቶ ሰጠኝ፡፡ እኔ ከተቀመጥኩበት ባንኮኒ ራቅ ብሎ አንዱ ነጭ ሰውዬ ከሴት ጋር ተቀምጦ ያስተውለኛል፡፡ “ሄይ! ከወዴት ነህ?” አለኝ፡፡

ነገር ፍለጋ እንደሆነ ገብቶኛል፡፡ “ከኢትዮጵያ ነኝ” አልኩት፡፡

“የት ነው ኢትዮጵያ?” አለኝ፡፡

ነገርኩት፡፡

“በአገርህ ወተት አላችሁ?” አለኝ፡፡

“አዎን፡፡”

“በቁርቆሮ ውስጥ? እኛ የመፀወትናችሁን ማለትህ ነው?”

“አይ! ላሞቻችን የሚሰጡን ነው” ስለው በጣም ሳቀ፡፡ ሊያናፍጠኝ የነበረ ስሜቱ በርዷል፡፡ ይቅርታ አደረገልኝ ማለት ነው፡፡ ሴትዮዋን ጠጋ በይ አላትና ለሦስት ሆነን ማውራት ጀመርን፡፡

“ከፈለክ ይህቺንም ሴትዮ ልጋብዝህ 20 ዶላር ካለህ” አለኝ፡፡

“አ! ከ200 ዶላር በላይ የምታስወጣ ውድ የሆነች ወይዘሮ ነች” ስለው እሱም እሷም በጣም ሳቁ፡፡ ‘መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች’ እ! በተግባር ከወንናት፡፡ ይህንን ገጠመኜን መልካም ዕድል እለዋለሁ፡፡

አሜሪካኖች የአንዳንዶቹ አኗኗራቸው ከእኛ በጣም የተለየ ነው፡፡ በዚያም ምክንያት ለችግር ሲጋለጡ አንብቤያቸዋለሁ፡፡

ብዙውን ጊዜ አንዳንዶቹ ሆፌ ግቢ ውስጥ ብቻቸውን ይኖራሉ፡፡ ማንም ከጎረቤቱ ጋር አይተዋወቅም፡፡ ቢወልዱ አንድ ወይም ሁለት ነው፡፡ ቢበዛ ሦስት፡፡ አንዱ አሜሪካዊ ቤት ሁለት ልጆች አሉ፡፡ ልጁ ለአቅመ አዳም ይደርስና ከእህቱ ጋር ሲጫወት ታምረዋለች፡፡ እሷም ፈቀደችና እነሆ በረከት ይባባላሉ፡፡ “ያንቺ ከእማዬ በጣም ይጥማል” ይላታል፡፡

ልጅትም “አባዬም እንዲህ ብሎ ነግሮኛል” ብላው እርፍ አለች፡፡

በነገራችን ላይ፣ በጣም የምናምር ነን እኮ? አቢሲኒያ የሚባለው ሐበሻ፣ እህ! ምክንያቱም ቀለማችን ወደ ጥቁር ሆኖ፣ የፊት ቅርፃችን ደግሞ ወደ ነጮች ነው የወሰደው፡፡ "ፐርፌክት ኮምቢኔሽን!" አንዷ ትዝታ እየመጣች ነው፡፤ እዚህ አዲስ አበባ የገጠመኝ፡፡

በወቅቱ ጎረምሣ ነኝ፡፡ ጥቁር ነኝ፡፡ ፈረንጅ ነች ሴትዮዋ፡፡ ምናልባትም ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት ትበልጠኛለች፡፡ መልኳ አስቀያሚ ነው፡፡ አኳኋንዋ እንደ ቆንጆ ሴት ትሽኮረመማለች፡፡ መቼስ ሴት አይደለች? ወጉሳ ማረጉሳ" አለና ፈገግ ብሎ "በጣም አሳዘነችኝና ምን ቸገረኝ አልኩ፡፡ አሁን ቢሆን አልችልም፡፡ እኔ በአሁኑ በሽሚኒት ሰዓት አቅፌያት የማድረው ሴት ቆንጆ መሆን አለባት፡፡ እንድታምቀኝ፡፡

ያኔ ወጣት ስለሆንን ለቁንጅናው እጅግም ግድ የለንም፡፡ እኛ የምንፈልጋት ለሌላ ጉዳይ፡፡ የእናቴ ልጅ አይደለሁም? 'Let me be nice' አልኩና አሳዝናኝ መሣሣም፣ መተሻሸት ጀመርን፡፡ እንደዚህ እንደዚህ ስንል የአካል ጥያቄ ማንሣት ደረሰ፡፡ "ለምን አንድ ቦታ አንሄድም?" አልኳት፡፡ ምን አለች መሰለህ?

"እሱማ ለባሌ ብቻ ነው That is for my husband only!" አለችኝ፡፡

ምን ዝም እላለሁ? "እኔኮ! የፈለግሽኝ መስሎኝ" ሰላት፡፡

"Only this part" አለቺኝ፡፡ (እስከዚህ ድረስ ብቻ ነዋ)

እሷ የፈለገችው በሌላ ወንድ እፈለጋለሁ፣ ወይስ አልፈልግም? ለሚለው የአስቀያሚ ሴት ጥያቄ መልስ ለማግኘት ነው እንጂ በባሏ ላይ መሔድ አልፈለገችም፡፡

አሜሪካንን ስናነሳ ጓደኛዬ ዌንዲ ኪንድረድ ትዝ አለችኝ፡፡ አሜሪካዊት ነች፡፡ እዚህ እኛ ሀገር ሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ሥዕል ለዓመታት አስተምራለች፡፡ አብዮቱ እንደ ፈነዳ ወደ ሀገሯ ሄደች፡፡ ዓመታት ቆይታ ስንናፍቃት ጊዜ ልትጎበኘን አዲስ አበባ ስትመጣ ከጓደኞቻችን መካከል እኔን አገኘችኝ፡፡ ሳስተናግዳት ቡና ቤት ይዞ መሄዱ ለእሷ አያስፈልጋትም፡፡ ለእሷ የናፈቃትን የአበሻ ምግብ የምትበላበት ጠጅ የምትጠጣበት ቦታ ነው ደስ የሚያሰኛት፡፡ ስለዚህ ሰንጋ ተራ ጠጅ ቤት ይዤአት ሔድኩ፡፡ ጠጃችንን አስቀድተን ጨዋታችንን ጀመርን፡፡ ደስ ብሎን እየተዝናናን ሳለ አንዱ አይቶን ደስ አላለውም፡፡ ፖሊስ ነው፡፡ በእሱ ቤት ሲ.አይ.ኤ ላይ ደርሷል፡፡ አብዮቱ እንዳይቀለበስ መከላከል አለበት፡፡

ጠራና ጠየቀኝ፡፡ ላስረዳውሞከርኩ፡፡ ከጥርጣሬው ነብሱ አልነፃችም፡፡ ስለዚህ ፖሊስ ጣቢያ መሄድ ብቻ ነው የሚገላግለን፡፡ ያስቀዳነውን እን ጨርስ እንጨርስ አላስታውስም፡፡ ሒሳባችንን ከፍለን ወደ ፖሊስ ጣቢያው ሔድን፡፡ ፖሊስ ጣቢያ አዛዡ አስተዋይ ነው፡፡ የመጨረሻ ምክሩንም



ለገሰኝ፡፡ "በአረፈችበት ሆቴል መኝታ ቤቷ ከጎበኘሃት ይበቃሃል" አለኝ፡፡ በወቅቱ ከነበረው ጣጣ አኳያ ሳየው ምክሩ ትክክል ነው፡፡

የአስተዋዩን ፖሊስ አዛዥ ምክር ተቀብዬ ልወጣ ስል ያንን ቀሽም አየሁት፡፡ አሁን ደግሞ በትህትና ከመጣንበት ጠጅ ቤት ሊመልሰን ተቅለሰለሰ፡፡ አመሰግናለሁ! ብዬው ወደ አረፈችበት ራስ ሆቴል መኝታዋ ድረስ ሸኘኋት፡፡

አንድ ዘፈን አለች በአሜሪካን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚኖረውን ኅብረተሰብ ሕይወት የምታሳይህ፡፡ እኔ እዚያ በነበርኩ ጊዜ ትዘፈን ነበር፡፡ አለና በጎርናና ወፍራም ድምፅ፤

The Miner's Song

I was born one mornin'
It was drizzlin' rain
Lightening and trouble
Are my middle name
You load sixteen tons. What do you get?
Another day older and deeper in debt.
Saint Peter don't you call me, cause I can't go
I owe my soul to the Company store
I was raised by an old mommaline
The honk-tonk woman made me hop the line
If you see me comin' better step aside
A lot of men didn't, a lot o' men died
One first of iron, the other of steel
If the right one don't get then the left one will.
You load sixteen tons. What do you get?
Another day older and deeper in debt.
Saint Peter don't you call me, 'cause I can't go
I owe my soul to the Company store

*** *** ***

የማዕድን ቆፋሪው እንጉርጉሮ
በአንድ ማለዳ ነበር የተወለድኩት
በጨፍጋጋና ዝናባማ ዕለት
በመብረቅ ብልጭታ ፅቆታ
ያህ ሆኖ የስያሚዬ ሳንቃ
አሥራ ስድስት ቶን ትቆፍራለህ፤ ከዚያስ ምን ጠብ አለልህ?

@Amharicbookstore

ነገ የባሰ ማርጀት፣ የባሰ ዕዳ ዝፍቀት፣
ቅዱስ ጴጥሮስ እባክህን አትጥራኝ፣ ልመጣ አልችልምና
ለኩባንያው ማምጃ ቤት ነብሴን ዱቤ አስያዝለሁና፣
    በባልቴቷ አዋላጂ ወደዚህ ዓለም መጣሁ
    በሚያንባርቅ ድምፅዋ አነቃችኝ፣ እንደ ነብሳት አዘልላ
ሲያስታውሉኝ፣ በተሻለ ደረጃ ላይ እገኛለሁ
አብዛኛውን አልነበርኩም፣ አ! አያሊያቹም አልፈዋል።
    አንደኛው ሙሜዬ የብረት፣ ሌላኛው የብረት ብረት
    የመጀመሪያውን ብትሸውድ፣ በቀጣዩ ትነረት፣
አሥራ ስድስት ቶን ትቆፍራለህ፣ ከዚያስ ምን ጠብ አለልህ?
ነገን የበለጠ ማርጀት፣ የባሰ ዕዳ ውስጥ መግባት
ቅዱስ ጴጥሮስ እባክህን አትጥራኝ፣ ልመጣ አልችልምና
ለኩባንያው ማምጃ ቤት ነብሴን ሸጫታለሁና

***   ***   ***

በአሜሪካ አንድ ሀብታም ነበር። አሜሪካዊ ነው ሃዋርድ ዩስ ሮበርድ *Hughes Haward Robard ይባላል። ከማንም ሰው ጀርም እንዳይተላለፍበት በመስታወት ቢሮ ውስጥ በበርካታ ቴሌፎን ተከበ ነው ሥራውን የሚያከናውነው። የግድ ሰው ሊያናግረው ወደ ቢሮው የሚገባ ከሆነ እንግዳው ላይ ፀረ-ጀርም ተረጭቶበት በአካል እንዲያገኘው ይደረጋል። ይህንን ያህል ከሞት ቢቆራረጥም ሞት እንደሆን አትቀር ብሎ ጋሼ ስብሐት በትካዜ ፊገግ አለና ብቅ ብለው በአጭር ጊዜ አሜሪካንን አይተዋት ሲመለሱ የአንክል ሳም ሀገር አሜሪካ ይህንን ትመስላለች። እኛ ከየናት ዓመታት ተቆጥረዋል። በማምት አርባ ዓመት ሆኗታል። አሁንስ የኮምፒዩተሩን፣ የኢንተርኔቱን ማይንስ ጨምረን ዘሁ ርቀት ስናስተውላት ደግሞ አሜሪካ ምን ትመስል ይሆን? … ማይንስ ፊክሽን እየሆነች ሄዳለች።

***

*HUGHES HOWARD ROBARD (1905-1976) በአሜሪካን ኢንዱስትሪና በፊልም ግብብ ባለፀጋ ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። እንዲህ ይጠንቀቅላት የነበረች ሀይወት 71 ዓመት ኖሮ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። The world book Encyclopedia ቅጽ 11 ገጽ 372

***



# ፲፩

## ማሪያን - ላ ቤል ፍራንስ

ሁሌም የሚቆጨኝ በግብፅ ሰማይ ላይ ለበርካታ ጊዜ ሳንዣብብ አንድ ጊዜም ዕድል ገጥሞኝ አገሪቱን አለመጎብኘቴ ነው። ወላሂ! ከእየሩሳሌም በበለጠ ሁኔታ! ታጓጓኛለች።

ተፈሪ መኮንን ስንማር እንግዲህ የጀዝዊት ቤት ነው ብለናል። እነሱ ፈረንሣይኛ ያስተምሩን ነበር። ከዚያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ስንመጣ ጀዚዊቶቹ ናቸው አብረውን የሄዱት። እዚያም ፈረንሣይኛ አስተማሩን። ከዚያ በኋላ ፈረንሣይ እስኮላርሺፕ ሰጠች። ለዩኔስኮ ነው የሰጠችው። ሌሎችም አገሮች እንዲህ ዓይነቱን ዕድል ለዩኔስኮ ይሰጣሉ። ዩኔስኮ ደግሞ ያስፈልገዋል ለሚለው አገር የነፃ ትምህርት ዕድል ይሰጣል። ለእኛ አገር ሲሰጥ እኔ ደረሰኝ። እኔ ከትንሽ በላይ ፈረንሣይኛ ስለምችል፣ በተጨማሪም ፈረንሣይ አገር ከመሔዴ በፊት ሁልጊዜ ስለማነብ፣ ስለፈረንሣዮች የተሻለ ዕውቀት ኖረኝ በዚህም ዕድሉ ገጥሞኝ ወደ ፈረንሣይ ሄድኩ። አየር ማረፊያው ወርጄ ስገባ እንዲህ ሆነ። ለንደን ስገባም እንደእዚያው ነው የሆንብኝ። በቃ ይኸው ነው እንዴ ፓሪስ? አልኩ። መንገዶች፣ ፎቆች፣ ከተማ ነው በቃ። እንዴት ልበልህ? ፓሪስ እኮ በዘፈን፣ በተረት፣ በስንት የፖለቲካ ፍትፍት፣ በስንት የሥነ ጽሑፍ ምንጭነት የምናነባት ናት። አሁን ዝነኛውን ገዘ ባህሪ ሼርሎክ ሆምዝ በአካል ብናገኘው እናምናለን? እንዲያውም! እንደዚያ ሆነችብኝ። ማመን አይቻልም። በቆይታ ለመድኩት። ትንሽ ቆየሁና ያችን መጽሐፍት፣ ሲኒማዎች ያስቀመጧትን ፓሪስ ቻው አልኳት። የዐይ ወራት ነበር። በእንግሊዝኛ ስፕሪንግ ይሉታል። ውብ ጊዜ ነው። ሙቀትም በቂ አለ፣ ሴቶቹም እንደ አበባዎቹ ውብ ይሆናሉ። በዚያን ሰዓት በፓሪስ አውራ ጎዳና መንሸራሸር ነው። በተለይ ሻንዘሊዜ በሚባለው አውራ ጎዳና። በቃ ለከስ ዘፋኞቹም፣ ፋሽኑም፣ ሽቶውም ዓለም ቢወዳቸውም፣ ይሄ እየረገጥነው የምንሄድ ባቡር መንገድ ጥበብ ሲሆን ማን ወይ ማሪያን ላ ቤል ፍራንስ ጎብኚ በመሆኔ ሲአል እዚያው ውስጥ ስለሌለ ደስ አለኝ። በገዛ አገርህ እኮ ሲኦልም አብሮህ ይኖራል።

@Amharicbooks.store

ነገ የባሰ ማርጀት፣ የባሰ ዕዳ ዝፍቀት፣
ቅዱስ ጴጥሮስ እባክህን አትጥራኝ፣ ልመጣ አልችልምና
ለኩባንያው ግምጃ ቤት ነብሴን ዱቤ አስይዣለሁና፣
    በባልቴቷ አዋላጂ ወደዚህ ዓለም መጣሁ
    በሚያንባርቅ ድምፅዋ እኑቀችኝ፣ እንደ ነብሳት አዘልላ
ሲያስታውሉኝ፣ በተሻለ ደረጃ ላይ እገኛለሁ
አብዛኛውን አልነበርኩም፣ አ! ኢየሴዎቹም አልፈዋል፡፡
    አንደኛው ጡጫዬ የብረት፣ ሌላኛው የብረት ብረት
    የመጀመሪያውን ብትሸውድ፣ በቀጣዩ ትነረት፣
አሥራ ስድስት ቶን ትቆፍራለህ፣ ከዚያስ ምን ጠብ አለልህ?
ነገን የበለጠ ማርጀት፣ የባሰ ዕዳ ውስጥ መግባት
ቅዱስ ጴጥሮስ እባክህን አትጥራኝ፣ ልመጣ አልችልምና
ለኩባንያው ግምጃ ቤት ነብሴን ሸጫታለሁና

***    ***    ***

በአሜሪካ አንድ ሀብታም ነበር፡፡ አሜሪካዊ ነው ሃዋርድ ዩስ ሮበርድ *'Hughes Haward Robard' ይባላል፡፡ ከማንም ሰው ጆሮም እንዳይተላለፍበት በመስታወት ቢሮ ውስጥ በበርካታ ቴሌፎን ተከበ ነው ሥራውን የሚያከናውነው፡፡ የግድ ሰው ሊያናግረው ወደ ቢሮው የሚገባ ከሆነ እንግዳው ላይ ፀረ-ጀርም ተረጭቶበት በአካል እንዲያገኘው ይደረጋል፡፡ ይህንን ያህል ከሞት ቢቀራረጥም ሞት እንደሆን አትቀር˝ ብሎ ጋሼ ስብሐት በትካዜ ፈገግ አለና ˝ብቅ ብለው ለአጭር ጊዜ አሜሪካንን አይተዋት ሲመለሱ የአንክል ሳም ሀገር አሜሪካ ይህንን ትመስላለች፡፡ እኛ ከየናት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በግምት አርባ ዓመት ሆኖታል፡፡ አሁንስ የኮምፒዩተሩን፣ የኢንተርኔቱን ማይንስ ጨምረን ከዚህ ርቀት ስናስተውላት ደግሞ አሜሪካ ምን ትመስል ይሆን? ... ማይንስ ፊክሽን እየሆነች ሄዳለች፡፡

***

*HUGHES HOWARD ROBARD (1905-1976) በአሜሪካን ኢንዱስትሪና በፊልም ግዛብ ባለፀጋ ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ እንዲሁ ይጠነቀቅላት የነበረች ህይወት 71 ዓመት ኖሮ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ The world book Encyclopedia ቅጽ 11 ገጽ 372

***

@Amharicbookstore



## ፲፩

# ማሪያን - ላ ቤል ፍራንስ

ሁሌም የሚቆጨኝ በግብፅ ሰማይ ላይ ለበርካታ ጊዜ ሳንገርብብ አንድ ጊዜም ዕድል ገጥሞኝ አገሪቱን አለመጎብኘቴ ነው፡፡ ወላሂ! ከእየሩሳሌም በበለጠ ሁኔታ! ታጓጓኛለች፡፡

ተፈሪ መኮንን ስንማር እንግዲህ የጀዝዊት ቤት ነው ብለናል፡፡ እነሱ ፈረንሣይኛ ያስተምሩን ነበር፡፡ ከዚያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ስንመጣ ጀዚዊቶቹ ናቸው አብረውን የሄዱት፡፡ እዚያም ፈረንሣይኛ አስተማሩን፡፡ ከዚያ በኋላ ፈረንሣይ እስኮላርሺፕ ሰጠች፡፡ ለዮኔስኮ ነው የሰጠችው፡፡ ሌሎችም አገሮች እንዲህ ዓይነቱን ዕድል ለዩኔስኮ ይሰጣሉ፡፡ ዩኔስኮ ደግሞ ያስፈልገዋል ለሚለው አገር የነፃ ትምህርት ዕድል ይሰጣል፡፡ ለእኛ አገር ሲሰጥ እኔ ደረሰኝ፡፡ እኔ ከትንሽ በላይ ፈረንሣይኛ ስለምችል፣ በተጨማሪም ፈረንሣይ አገር ከመሔዴ በፊት ሁልጊዜ ስለማነብ፣ ስለፈረንሣዮች የተሻለ ዕውቀት ኖረኝ በዚህም ዕድሉ ገጥሞኝ ወደ ፈረንሣይ ሄድኩ፡፡ አየር ማረፊያው ወርጄ ስገባ እንዲህ ሆነ፡፡ ለንደን ስገባም እንደእዚያው ነው የሆነብኝ፡፡ ቢቀ ይኸው ነው እንዴ ፓሪስ? አልኩ፡፡ መንገዶች፣ ፎቆች፣ ከተማ ነው ቢቃ፡፡ እንዴት ልበልህ? ፓሪስ እኮ በዘፈን፣ በተረት በስንት የፖለቲካ ፍትፍት፣ በስንት የሥነ ጽሑፍ ምንጭነት የምናነባት ናት፡፡ አሁን ዝነኛውን ገሀ ባህሪ ሼርሎክ ሆምዝ በአካል ብናገኘው እናምናለን? እንዲያውም! እንደዚያ ሆነችብኝ፡፡ ማመን አይቻልም፡፡ በቆይታ ለመድኩት፡፡ ትንሽ ቆየሁና ያችን መጻሕፍት፣ ሲኒማዎች ያስቀመጧትን ፓሪስ ቻው አልኳት፡፡ የፀደይ ወራት ነበር፡፡ በእንግሊዝኛ 'ስፕሪንግ' ይሉታል፡፡ ውብ ጊዜ ነው፡፡ ሙቀትም በቂ አለ፣ ሴቶቹም እንደ አበባዎቹ ውብ ይሆናሉ፡፡ በዚያን ሰዓት በፓሪስ አውራ ጎዳና መንሸራሸር ነው፡፡ በተለይ ሻንዘሊዜ በሚባለው አውራ ጎዳና፡፡ ቢቃ ለካስ ዘፋኞቹም፣ ፋሽኑም፣ ሸቶውም ዓለም ቢውደቸው ውም፣ ይሄ እየረገጥነው የምንሄድ ባቡር ነመንገድ ጥበብ ሲሆን ግን ወይ ማሪያን ላ ቤል ፍራንስ፣ ጎበኘ በመሆኔ ሲኦል እዚያው ውስጥ ስለሌለ ደስ አለኝ፡፡ በገዛ አገርህ እኮ ሲኦልም አብሮህ ይኖራል፡፡

አብራኝ አለች፡፡ እዚያ ግን ወይ ጉድ! እንኳን ሻንዜሊዜ በእግሬ ሄድኩ እላለሁ፡፡ ውብ ነው፡፡ በግንባታው፣ በአስተናነፁዋ፡፡ በንባብ የምታውቃቸውን ሁሉ እንድታስባቸው ያደርግሃል፡፡ እነ ማርሴል ፕሩስትን፣ ማዳም ሰዋንን ሁሉ አሰቤያቸዋለሁ፡፡ አልቤር ካሙንም፣ ኤሚል ዞላንም አትርሣ፡፡ በጣም የሚያምን አማኝ እየሩሳሌም ደርሶ ተመልሶ ቢያጫውትህ የሚሰማህን ስሜት አስበው፡፡ የእኔንም እንደእዚያ እንዳጫወትኩህ ውሰደው፡፡

እግዚርዬው ኃያል ደራሲ ነው፡፡ ስቀህ ሲአልን በረሳህበት ቤታ ትራጀዲውን ይልክሁና ልብህ በኀዘን በትር እንዲመታ ያደርግሃል፡፡ እዚያው ፓሪስ በነበርኩ ጊዜ ነው፡፡ ጆን ኤፍ ኬኔዲ የተገደለው፡፡ በቴሌቪዥን በየጎዳናው ሕዝቡ ሲያነባ አየሁና ለካ ፈረንሳይ ሰው ነው አልኩ፡፡

ፓሪስ ሌላ ፍራንስ ናት፡፡ ፍራንስን ለሁለት እንክፈል፡፡ ወደ እንግሊዝና ጀርመን በሚዋሰነው አካባቢ ብርዳምና ቀዝቃዛ ነው፡፡ ደቡብ ደግሞ ሞቃታማ ነው፡፡ የደቡቡ ዋና ከተማ ማርሰይ ነች፡፡ ማርሰይ የአውሮፓ ወንጀለኞችና አመፀኞች ማዕከል ነች፡፡

እስያ ውስጥ የሚመረተው ዕፅ ኦፕየም ወደ ምእራቡ ዓለም ማሸጋገሪያም ሆና ታገለግላለች፡፡ ከማርሰይ ነው እንኒውዮርክ ይህንን ዕፅ የሚያገኙት፡፡ ከማርሰይ በመኪና ምናልባት 30 ደቂቃ፣ ወይም ሃያ ደቂቃ ሳይወስድ አይቀርም ኤክስ ለመድረስ? ሚጢጢ ከተማ ናት፡፡

ማርሰይ በጣም የሚያምር እንደ ቅስት ክብ የሆነ መንሸራሸሪያ ጎዳና አለ፡፡ ባሕርና ምድር መሐል የተሠራ፡፡ ፕሮመናድ ዴዛንግሌ ይሉታል፡፡ የእንግሊዞቹ መንሸራሸሪያ እንደ ማለት ነው፡፡ እንግሊዝ ነዋ፣ የዚያን ጊዜ ሀብታም፡፡ አሁን አሜሪካ እንደሆነው፡፡ የእንግሊዝ ሀብታም ሲመጣ የበኩር ልጁን ይዞ ነው፡፡ ዓለምን እንዲያውቅ አብሮት ይንሸራሸራል፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ ለአንድ ዓመት አውሮፓን ያዳርሣል ሀብታም ፕሮመናድ ዴዛንግሌ ላይ ስትንሸራሸር ከማዶ ጋራ አለ፡፡ ጋራው ላይ ቆንጆ ቤተ ክርስቲያን አለች፡፡ እርሱ ነው የማርሰይ ምልክት፡፡ ለፓሪስ አይፍል ታወር እንዳለው ማለት ነው፡፡ ከሐና ጋር እዚያ ሄደናል፡፡ በዚህ በልኩህ በማርሰይ ጎዳና ላይ ስንንሸራሸር ከፊት ለፊታችን አንድ ሽማግሌ ቀስ እያሉ ዳገቱን ይወጣሉ፡፡ ገና ሩቅ ናቸው፡፡ እንዲሁ በርምጃ እየዘገሙ ዞር አሉና አዩን፡፡ እዚህ ላይ አንድ የሚያስገርም፣ ፈረንሣይ ኢንተርናሽናል ነው የሚያሰኝህ ባህሪ አላቸው፡፡ በእነርሱ ቤት ፈረንሣይኛን እስካወቅክ ድረስ ሙሉ ለሙሉ ሰው ነህ ይሉሃል፡፡

@Amharicbookstore



እ! ዞር አሉና ሽማግሌው ልብ ብለው አዩን፡፡ ፈረንሣይ ስለሆኑ አይደለም ሰው ስለሆኑ ነው፡፡ ሽማግሌ ሆነህ ፍቅረኞች ተያይዘው ስታይ ደስ ይልሃል፡፡ Alors, les amoureux, ca marche? አሉን፡፡ "ታዲያስ ፍቅረኛሞች፣ ልክ እየሄደ ነው?"

"ልክ እየሄደ ነው! አልናቸው፡፡ ቀጠሉ መንገዳቸውን፡፡ አለቀ፡፡ ተመልሰው ከየት መጣችሁ? ዝባዝንኪ አላስፈለገም፡፡

እኔ ከፈረንሣይ የምወድለት ነገር፣ በተለይ አሜሪካ ደርሼ ትንሽ አይቼ ከመጣሁ በኋላ፣ ፈረንሣይ ልትቀርበው ካልፈለክ ብቸኝነትህን ይፈቅድልሃል፡፡ በር ካንኳኳህ ይከፍትልሃል፡፡ አንዴ ደግሞ ደስ የሚለኝ ምን አየሁ መሰለህ?" እየሳቀ "ኤክሳንፕሮቫንስ ሆኜ ነው፡፡ በከተማዋ የትራፊክ መብራት አለ፡፡ አንድ ሽማግሌ ሽበት ብቻ የሆኑ፣ ፀጉራቸው አጭር የሆነ፣ መኪና እየነዱ መጡ፡፡ ቀይ መብራት አቁሟቸው ዞር ዞር ብለው አዩ ትራፊኩ የለም፡፡ ጥሰውት ጭልጥ!

ይህ የምነግርህ የድሮ ምዕራፍ ነው፡፡ ፈረንሣዮች እስካል ተነቃባቸው ድረስ መንግሥታቸውን ይሸፍጣሉ፡፡ መንግሥትን ግብር ሸውደህ ብታልፍ ጠላት ቢሰማብህ እንኳ አያጋልጥህም፡፡ (የከረረ ጥል ካልሆነ) ትክክል ነው የሚልህ፡፡ እንግሊዞች ግን የፖሊስ ወገን ናቸው፡፡ የፈረንሣይ ፖሊስ ሽጉጥ ይታጠቃል፡፡ የእንግሊዝ ፖሊስ አጭር ዱላ ብቻ ነው የሚይዘው፡፡ በእንግሊዞች የመንግሥት ግብር ሳትከፍል ዞር ማለት ማንም እንደማይነቃብህ እርግጠኛ ከሆንክ ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ ማኅበረሰቡ መንግሥትን የሸፈጠ፣ ግብሩን በአግባቡ ያልከፈለ እያለ ሲያማህ ይኖራል፡፡ ይህም ሸፋጩን በጣም ነው የሚቆጨው" አለኝና ፈገግ አለ፡፡

እዚህቸጋ ነዋ በርናርድ ሾን የምናነሣው፡፡ ሾ አይሪሽ ነው፡፡ አይሪሾች በእንግሊዝ ተገዝተዋል፡፡ ሾ ደግሞ ብቻውን እንግሊዝን ለመማረክ ዘምቶ የተሳካለት ጥበበኛ ነበር፡፡ አንዱ ቴአትሩ ዘ ሚሊየኔር የምትል ነች፡፡ ባለፀጋው ሰውዬ ተዋናይ ልጁን ሚሊዮን ብር ሰጥቷት ለሰዎች እንድታድለው ያዛታል፡፡ ነገሩ ፈተና ነው፡፡ ልጅት ታወጣ ታወርድና አንድ አርቲስት አለ፣ ከሜዲያን፣ ትቀጥረዋለች፡፡ እሱ ደግሞ ፓውንዶቹን በመቶ፣ በሺ፣ በሺ አርጎ ከምሮ በትሪ አድርጐ አደባባይ ይወጣል፡፡ በትሪው ላይ የተፃፈበት ካርድ "take one please" ይላል፡፡ አንድም ሰው ግን ንክች አላደረጋትም፡፡ አይቶት ወደ ጉዳዩ ቱር ይላል፡፡ አየህልኝ ሕግንና እንግሊዛውያንን?

ፍራንስ አይደል ያለነው? የመርሰይ ነጋዴዎች ለየት ያለ ባሕሪ የምታይባቸው ናቸው፡፡ አንዱ ሱቅ ዘው ብለህ ስትገባ ነጋዴው

ፍራንስ አይደል ያልነው? የመርሰይ ነጋዴዎች ለየት ያለ ባሕሪ የምታይባቸው ናቸው፡፡ አንዱ ሱቅ ዘው ብለህ ስትገባ ነጋዴው ከወዳጁ ጋር ቆሞ ያወጋል፡፡ አንተ የራስክን ጉዳይ እያሰብክ "እንትን ስጠኝ?" ትለዋለህ፡፡ ነጋዴው ፀጥ ብሎህ ጨዋታውን ይቀጥላል፡፡ "አንተ ምነው እንትን ስጡኝ ብዬዎታለሁ እኮ!" ስትለው፣ ዞር ብሎ ያይህና፣ "ምነው ወንድም? ጨዋታ ላይ እኮ ነን!" ይልሃል፡፡

ፊሎዞፊና ሶስዮሎጂ ላጠና ነው ፈረንሣይ የሄድኩት፡፡ ይኸውልህ፣ ወጣት ነኝ፡፡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ማታ አመሻለሁ፡፡ በተለይ ከአዲስ አበባ ማስታወሻ ይዤ የሄድኩትን ረዥም ልቦለድ እየጻፍኩት ነበር፡፡ ክፍል ደግሞ በጠዋት ነው የሚጀመረው፡፡ በተለይ በጣም እወዳቸው የነበሩ ሁለት ትምህርቶችን እንኳን ማለዳ ተነስቼ መከታተል አልቻልኩም፡፡ በእኔ እምነት ግዴታ ማወቅ ከፈለግኩ በክፍል ብቻ አይደለም ትምህርት፡፡ አነባለሁ፡፡ ስለዚህ ዕውቀቱን በአቋራጭም ቢሆን መገብየቴ ስለማይቀር ጊዜዬን ለመጻፍና ለማንበብ አውል ጀመር፡፡ በዚህ ላይ ልብ አድርግ፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ስላገኘሁ አገሬ ብመለስ ለእንጀራ የሚሆን በቂ የምስክር ወረቀት ስለነበረኝ አልተጨነኩም፡፡ የፊሎዞፊ መምህራችን የዶክተር ማምነር ረዳት ሆኜ እንዳገለግል ነበር ወደ ፈረንሳይ የተላኩት፡፡

ፕሮፌሰር ሆነዋል? አዎን የፕሮፌሰር ረዳት መሆን ነበር ግቤ፡፡ እንዳያውም ከበቂ በላይ በንባብ የፍልስፍናውንም ሆነ የሶስዮሎጂውን ዕውቀት በደንብ ገብይቻለሁ፡፡

ሰባተኛው መልአክ በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ባሕሪያት መካከል አየለ ነብሮን ታስታውሰዋለህ፡፡ አየለ ነብሮን ስሙንም መልኩንም ለዋውጬ ነው ገጸባህሪዬ አድርጌ የቀረጽኩት፡፡ ገጠመኞቹንም የመጽሐፉን ታሪክም እንዳለ ነው የጻፍኩት፡፡ ይህ አየለ አበደ፡፡ ወደ አገሩ ይዞት የሚመልሰው ሰው አስፈለገ፡፡ እኔ ትምህርቴን አቋርጫለሁ፡፡ የምጽፋቸውንም ሆነ የማነባቸውን በበቂ ሁኔታ ገብይቻለሁ፡፡ ስለዚህ አየለን ይዤው ለመመለስ ፈቃደኛ ሆንኩና ወደ አገራችን ይዤው መጣሁ፡፡ ደግሞ! አንድ ዓመት ከአስር ወር በኤክሳንፕሮቫንስ በምማርበት ዩኒቨርሲቲ ተቀምጫለሁ፡፡ ይህ የሆነው እንግዲህ የፈረንሣይን አስተዳደር እያታለልኩ ነው፡፡ ቢቀረኝ ሁለት ወር ነው፡፡ ከዚያ በላይ ማምታታት አልችልም፡፡ ስለዚህ ሁለት ወር የመቆያ ጊዜዬን ብቻ ነው ለጓደኛዬ መስዋዕት ያደረግኩት፡፡

አዎን አየለ ነብሮ በሕይወት አለ፡፡ አሁንም በአገራችን ውስጥ ይኖራል፡፡ ጤንነቱ ተመልሶለት ሰላማዊ ሕይወቱን እየመራ ነው፡፡

@Amharicbookstore



"ቆይ እስኪ?" አለና ጥቂት አብሰልስሎ "አዎን ያራሲ ኤሚል ዞላ ካረፈ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ ነው "ወደ ፈረንሣይ የተጓዝኩት ይኸውልህ፣ ኤሚል ዞላ ሲጽፍ ደፋር ነበር፡፡ ሲኖርም ደፋር ነበር፡፡ ምናልባትም ከሩቅ ስታየው ሥነ ሥርዓት የሚባል ነገር የማያውቅ ልትለው ትችላለህ የውስጡን አናውቅም፡፡ ወደ ፈረንሣይ ሥነ ጽሑፍ ስንሄድ የመጣው Naturalism ይባላል፡፡ እንዳየነው ተፈጥሮን እንዳለች መጻፍ ማለት ነው፡፡ በሥነፅሑፍ ሌላ ዘመን መጣ ማለት ነው፡፡ ዞላ ብዙ ነው የጻፈው፡፡ ለመኖር ጊዜ እንዴት እንዳገኘ እኔ እንጃ፡፡ እኔ ጥቂቱን አነበብኩ፡፡ አንዷ ያነበብኩለትና የመሰጠችኝ ናና የምትባል መጽሐፍ ነች፡፡

አዎን እኔ ዞላን እማውቀው፣ ያደግኩትም፣ እከተለዋለሁ ያልኩትም አገሬ ሆኜ ነው፡፡ ይኸውልህ ናና ሸሌ ነች፡፡ እርሱም አልፎ ብዙ ከቆየ በኋላ ያገኘሁት መጽሐፍ ውስጥ በዚያን ዘመን እውቅ የነበሩ ሰዎች ሥዕሎች ያሉበት መጽሐፍ ላይ ከተመዘገቡት መካከል አንዷ ናና ነች፡፡ ዞላ አላሉም ታላቅነቱን ለመጥቀስ ናና ነው ያሉት፡፡ ያንን ያህል ነው የዞላ የመጻፍ ችሎታ፡፡ ይህን ያህል ይደነቃል፡፡

አይደለም፡፡ ብትፈልግ ሴት ልጅ ወንድን ስትወድ የሚያሳይ ሥራቸውን ያስነበቡኝ ብዙ ደራሲዎች አሉ፡፡ የዞላ ከሌሎቹ ደራሲዎች ልዩ የሚያደርገውና እኔንም የመሰጠኝ ሕይወትን እንዳየኋት ነው የምጽፋት ማለቱ ነው፡፡ ሁልጊዜም የምትጠቀስ ናት አባባሉ፡፡ እንዲህ ይልሃል "ተፈጥሮን ከነብጉሯ፣ ከነማዲያቷ ነው የምናሰፍራት፡፡ እኛ አልፈጠርናትም፣ አናሻሽላትም" ከዚያ በላይ ያለውን ግን እኔ የለሁበትም፡፡ ምክንያቱም እኔ ተዋጊ አይደለሁም፡፡

እ! ዞላን ወደ ሕይወቱ ስንመጣ እንደ እኔ ዓይነት ፈሪ ተፈጥሮ ያለው፣ ወይም ለልጆቹ ብሎ የሚፈራ፣ ወይም ለራሱ ብሎ የሚፈራ ሰው አይደለም፡፡

ዞላ ለተበደሉ እንዴት እንደሚሟገትላቸው አንድ ጭብጥ አነስቼ ላሳይህ የፈረንሣይ ነገር ሸራቢዎች ካፕቴን ድረይፉስ የሚባል ሰውዬ ላይ አነጣጠሩ፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ የፈረንሣይ ወታደራዊ ምስጢር ለጀርመን ተሽጧል፡፡ ማን እንደሸጠው አይታወቅም፡፡ ከፈረንሣይ የጦር መኮንኖች መካከል ማነው ይሁዲ? እንፈልጋለን፡፡ አየህ? አገኙ ካፒቴኑን! ዶልተው ሸርበው የውሸት መረጃ ጨምረው ሲፈርዱበት አቤቱታውን ለመስማት ዕድልም ሳይሰጡት ይሁዲ በመሆኑ ብቻ ተከሰሰ፡፡ እና በወታደራዊ አካዳሚ ግቢ ማዕረጉን ተገፈፈ፡፡ በሳንጃ ወድር ተዋርዶ ተባረረ፡፡ ከዚያም ዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበት ዴቭልስ አይላንድ ተጋዘ፡፡

አዎን ታውቀዋለህ ጋፒዮን ካነበብክ፡፡ አንብበኸዋል? ይህንን ፍርድ ዞላ ይሰማል፡፡ በዚያን ወቅት ዞላ ሚሊየን አገር ነበር፡፡ አባቱ ሚሊየን ነው፡፡ ቆይ፣ ካፒቴን ድሬይፉስ ያላትን ሳጫውትህ፡፡ እንደዚያ አዋርደው ሲያባርሩት ምን አለ መሰለህ?

"I am innocent! Longlive France! 'እኔ ከደሙ ንፁህ ነኝ ፍራንስ ለዘለአለም ትኑር'' እያለ ነው ወደ ዴቨልስ አይላንድ የተጋዘው፡፡

ከዚያማ ዞላ ጥልያን ቆይቶ ሲመጣ የካፒቴን ድሬይፉስ ጉዳይ ተደምድሟል፡፡ አንድ ዘመዱ ይህንን ፍርደ ገምድልነት አጫወተው፡፡ ዞላ ተናደደና ፃፈ፡፡ 'I. accuse' ወይም "እፋረዳለሁ'' በሚል ርዕስ ፃፈ፡፡

ግልፅ ደብዳቤ ለፍራንስ ፕሬዚዳንት ይላል፡፡ መጀመሪያ የምከሰው የጦር ሠራዊቱን አዛዦች ነው፡፡ ገና ለገና ይሁዲ ተብሎ ፍርድ ሲሰጥበት ለአቤቱታ እንኳን ጊዜ ሳይኖረው መጋዙ ፈረንሣይን የሚያሳፍር ነው፡፡ ያውም'ኮ ፍራንስ ናት ለዓለም 'እኩልነት፣ ነፃነት፣ ወንድማማችነት!' ብላ ወርቃማውን ሕግ ያስተማረች! እያለ በአጽንኦት ፍርድ መዛባቱን ጻፈ፡፡ ቢጋዜጣ ላይ ወጣ፡፡ በወቅቱ ፍራንስ ልትተረከክ ደረሰች፡፡ ከፍተኛ ነውጥ ተነሣ፡፡ ካፒቴን ድሬይፉስን ወንጀለኞች ሰውት፡፡ ምንጊዜም ሐቅ ደግሞ የራሷን ሰው ትሾማለች፡፡

ይኸውልህ ሪደርስ ዳይጀስት እና ሆሊውድን ስታይ ወንፊት ቢጤ ማጣሪያ ማድረግ እንዳለብህ አትርሳ፡፡ ማን አባቱን መርምሮ ይደርስበታል ብለው ደስ እንዳላቸው ፊልም ሲሠሩም እውነቱን ሳይሆን ለመሸጥ የሚመቸውን ነው፡፡ አንተ እውነቱን አወከው አላወከው እነሱ ደንታም የላቸው፡፡ 'እከሰሳለሁ' በታተመ በነጋታው ሚት ዞላን በጉልበት ይዘው መርዝ ግተውት ሞቶ ተገኘ ይላል ያየሁት ፊልም፡፡ ያንጊዜ እኔው መሳሳቴ አንሶ፣ በአንድ ወቅት እግረመንገድ ዓምድ ላይ በመጻፍ ይህንኑ ውሸት አሰራጭቼዋለሁ፡፡ በቅርቡ La ve'rite en marche (ሃቅ በሂደት ላይ) በሚል ርዕስ ስለዚህ ስለድሬይፉስ ዞላ ራሱ የፃፈውን ሳነብ ኤሚል ዞላ የሞተው የእግዜር ሞት መሆኑን ተረዳሁ ...

የካፒቴን ድሬይፉስ ጉዳይ እንደገና ታየ፡፡ የፈረንሣይን ወታደራዊ ምስጢር አሳልፎ ለጀርመኖች የሸጠው ሰው ራሱን አጋለጠ፡፡ ድሬይፉስ ማዕረጉም ክብሩም ተመለሰለት፡፡ I am innocent! Longlive France!

@Amharicbookstore



"ፈረንሣይን ማሪያን ላ ቤል ፍራንስ ይሏታል ዜጎቿ ሲጠሯት፡፡ ውቢቱ ፈረንሣይ ማለት ነው፡፡ የማሪያምንና የሐናን ስም አጣምረው ሲጠሯት ነው፡፡ ሐና የማሪያም እናት ነች፡፡

ፈረንሣዮች በየአሥር ዓመቱ የምትወክላቸውን ኮከብ ቆንጂት ይመርጣሉ፡፡ ስሟም ማሪያን ይሆናል፡፡ እኔ ፍራንስ በነበርኩ ጊዜ ማሪያን ብሪገርት ባርዶ የምትባል የፊልም አርቲስት ነበረች፡፡ ለፈረንሳዮች እንደ አሜሪካዊቷ አርቲስት ማሪሊን ሞንሮ ነች፡፡ የኔይቱን ማሪያን-ላ ቤል ፍራንስን ይህንን ያህል ካሳየንህ ሄደህ እንድትጎበኛት መልካም ፈቃዳችን ነው...

፲፪

## የዕድሜ ልክ እውነት

"እንደ የሩሳሌም እንዳክሱም ጽዮን
ተሳልሜው ልምጣ ዓይንና ጥርሷን
እንደሷም አልወዳት ወላጅ እናቴን"

አዝማሪው

ሐና ይልማ ፍቅረኛዬ የሆነችው በድንገት ነው፡፡ ልጅቱ የእኔ የቅርብ ጓደኛዬ የሆነው የሰለሞን ጴሬሣ የአክስቱ ልጅ ነች፡፡ ከእኔም ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅነው በገነት ሆቴሉ ፓርቲ ላይ ነበር፡፡ ዳንስ እየተገባበዝን ብዙ ደነስን፡፡ በጣም ተደሰቼ የልቤን አጫወትኳት፡፡ ከልብ አደነቅኳት "አቤት! እንዴት ደስ የምትል ቆንጆ 'Girl' ነች፤'' እያልኩ፡፡ እሷ በኋላ እንደነገረችኝ እዚያው በተጫወትነው ፓርቲ ላይ የእርሷ 'boy friend' ነበር፡፡ ትንሽ ተኮራርፈዋል፡፡ እሱ እሷን ለማስቀናት ከአንዲት ልጅ ጋር ብቻ ደጋግሞ ይደንሣል፡፡ እሷ ደግሞ በበኩልዋ ከእኔ ጋር ዳንሱን አጦፈችው፡፡ እኔም ሳላምራት አልቀረሁም፡፡ እንዴ! ለእኛ ለወንዶች ሴቶች እንደ ሚያምሩን እኮ! እኛም እናምራቸዋለን፡፡ ያ 'እንደቀልድ የጀመርነው ጓደኝነት በእኔና በእሷ መካከል ፍቅር ሆነ፡፡ ፍቅረኞቹም እየተራራቁ ሄዱ፡፡ እሱ እንደዚያ ባያደርግ የሚወዳትንና የምትወደውን ልጅ

ሄዱ፡፡ እሱ እንደዚያ ባያደርግ የሚወዳትንና የምትወደውን ልጅ አያጣም ነበር፡፡ በኋላ ከእኔ ጋር ተግባብተን ስንጫዋወት በጣም ትወደው እንደነበር ነግራኛለች፡፡

እኔና ሐና ሁለት እንቅፋቶች ነበሩብን፡፡ አንዱ የመደብና ከቤተሰብ የምታገኘው ነው፡፡ ሌላው እንቅፋት የሐና ታላቅዋ ታላቅ የሆነችው እህቷ ነች፡፡ ፀዳለ ትባላለች፡፡ እኔን በማል የወንድሞቿም ጓደኛ ስለሆንኩ ትወደኛለች፡፡ ነገር ግን ከእኔ በፊት የነበረውን የሐናን ፍቅረኛ ታውቀዋለች፡፡ ፀዳለና ልጁ በጣም ሸርኮች ናቸው፡፡ የእርሱ የአፈቃቀር ብልሃት እኔጋ ቦታ የለውም፡፡ ለምን ሐናን ከማቅረብና ከማሳመን ይልቅ ፀዳለንና አባቷን ነው በጣም የሚቀርበው፡፡ ይህ ብልሃቱም በአጠቃላይ ኢላማውን አስቶታል፡፡ ትንሽ ያለመግባባት በመካከላቸው ሲፈጠር "ምን ሆንሽ ነው? እኔስ ምን አጠፋሁ?" ብሎ ችግሩን ከመፍታት ይልቅ ቅድም ባልኩህ የማስቀናት መላ ነው የመጣባት፡፡

ፀዳለ እርሱን ነው የመረጠችው፡፡ ምክንያቱም ከአባቷ ጋር ያለውን ቅርበት አስተውላ ወደፊት የት እንደሚደርስ ይታያታል፡፡ እኔ፣ እሷ 'ኢንቴሌክችዋል' ነው የምትለኝ ዓይነት ወጣት ነኝ፡፡ እህቷን እስካላገባሁባት ድረስ ትወደኛለች፡፡ ታከብረኛለች፡፡ እህቷ አካባቢ ሳንገብብ ግን የመከላከያ ዘዴዎች ነበሯት፡፡

"ምን አደረገች መሰለህ፣ አሜሪካ ሰባት ወር ቆይቼ ስመለስ፣ ከእንግዲህ ውጪ አገር ሄጄ የመማር ዕድሌ አብቅቷል፡፡ ከዚያ በኋላ ዕድሉ የሚሰጠው ላልደረሳቸው ወጣቶች ነው፡፡ በእኔ በኩል ይህን ደምድሜ ተቀምጫለሁ፡፡ ፀዳለ ግን ጠራችኝና "ፈረንሣይ አገር የትምህርት ዕድል መጥቷል፡፡ ለምን 'ስኮላርሺፕ' ጽሕፈት ቤት መጥተህ አታመለክትም?" አለችኝ፡፡ ዕድሌን ያቃጠልኩ መሆኑን ነገርኳት፡፡ በወቅቱ ፀዳለ የስኮላርሺፕ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ነች፡፡

"ግዴለህም፤ በቂ የፈረንሣይኛ ችሎታ ያላቸው ወጣቶች ተጠርተው አላመለከቱም፡፡ አንተ ብትሞክር አታጣውም" አለችኝ፡፡

ተስማማሁ፡፡

ዋናው አላማዋ እኔን ከሐና መለያየት ነው፡፡ እርሷ አንድ ሰው፣ እኔና ሐና ሁለት ሆነን በመጨረሻው ልንቀድማት እንደ ምንችል አልገባትም፡፡ በእያንዳንዷ ጉዳይ እኔና ሐና እንመካከራለን፡፡ ስለእኔ ፀዳለ የምትላትን ሁሉ ትነግረኛለች፡፡ እኔ ፍቅረኛዋ ልሆን እንደ ማይገባ ደጋግማ ወትውታታለች፡፡ ስለዚህ ፀዳለ ስለ ስኮላርሺፕ ~~ዩልችኝን ለሐና ነገርኳት፡፡~~



"እሺ በላትና ሂድ፡፡ እኔ ደግሞ ከአባቴ ጋር እመካከርና ወደ እንግሊዝ አገር እሄዳለሁ፡፡ ከዚያም አውሮፓ እንገናኛለን" አለችኝ፡፡

ተስማማሁ፡፡

ሐና በእቶ ይልማ ሕይወት ውስጥ ያላትን ቦታ አውቃለሁ፡፡ ሐና ካለቻቸው ይስማማሉ፡፡ ልቧን ያማት ስለነበር በሕክምና ሰበብ ወደውጪ አገር የመሄድ ዕድል ነበራት፡፡ ይህንን ሁሉ ስለማውቅ ምንም ሳላመነታ ስኮላርሺፕ ጽሕፈት ቤት አመለከትኩ፡፡ የውጪው ትምህርት ዕድል ተፈቀደልኝ፡፡ የእሷ ሐሳብ ደግሞ ቢዝነስ ተምራ፣ ስትመለስ ቤተሰቧ 'ካፒታል' መድቦላት ራሷን መቻል ነበር፡፡

"አንድ ቀን ውጥናችን በፍጥነት አይሰምርም፣ ጊዜ ይወስዳል" አለቺኝ፡፡

"ለምን?" አልኳት፡፡

"አባቴ ራሱ ሐሳቡን ያመነጨው እስኪመስለው እንዲያብሰለስ ለው ጥቂት ጊዜ መጠበቅ አለብን፡፡"

አየህልኝ! አባትና ልጅ እንዴት እንደሚተዋወቁ?! ትክክል ነበረች፡፡ የአባቷ ባሕርይ ነበር፡፡ ሁሌም ሐሳብ ከርሳቸው የመነጨ መሆን ነበረበት፡፡ ቀስ በቀስ ውጥኑ ተግባራዊ ሆነ፡፡

ሞኝህን ፈልግ! ውጥናችን እንደሚሰምር የማረጋግጥበትን ፍንጭ ሳልይዝ ከሐና መለየት 'ወይ ፍንክች፣ ያባ ቢላዋ ልጅ!' አልኩ፡፡ የትምህርት ዕድሉን ለሰጠኝ ድርጅት፣ በደረሰብኝ ችግር ምክንያት ፈረንሣይ በጊዜ መድረስ ስላልቻልኩ ዕድሉን ለአንድ ዓመት፣ ካልተቻለም ለስድስት ወራት እንዲያራዝሙልኝ ጠየቅኩት፡፡ እሷም በዚህ መሃል በወራት ቀድማኝ ወደ ለንደን ሄደች፡፡ እኔም ጊዜዬን ጠብቄ ወደ ፈረንሣይ ተጉዤ ኤክስ ከተማ ከደረስኩ በኋላ የፍቅርም የሰላምታም ደብዳቤ መጻጻፍ ጀመርን፡፡

የትምህርት ቤት የእረፍት ጊዜያችን በአንድ ወቅት ነበር፡፡ እኔ መጀመሪያ ወደ እንግሊዝ በባቡርና ቀጥሎም በመርከብ ተጓዝኩና ፍቅረኛዬን ጎበኘኋት፡፡ ለንደን ውስጥ በጣም ቆንጆ የመፈቃቀሪያ፣ የመጫወቻና የመደሰቻ ጊዜ አሣለፍን፡፡

በአጠቃላይ ከሐና ጋር ያሳለፍናቸው ጊዜያት ሁሉ ቆንጆዎች ነበሩ፡፡ እኔና እርስዋ የተኳረፍንበት ጊዜ የለም ልልህ እችላለሁ፡፡ እንዳልምል ብቻ አንድ ሁለት ጊዜ ያህል ተኳርፈናል፡፡ 'ትልቻ ለትልቻም ይጋጫል' ይላሉ የተባረኩት አበው፡፡ ለፍቅር ደግሞ ይህች ዓይነቷ ኩርፊያ እንደማጣፈጫ ቀመም ነች፡፡ እነዚህን ዕለታት ብንደምራቸው ከሶስት ሳምንት አይበልጡም፡፡ አንዷን ላጫውትህ፡፡

እዚህ አዲሳባ ውስጥ ሆነን ፈንዴ ተኳረፍን፡፡ አምባሳደር ሲኒማ ቤት አካባቢ 'ቡቲክ' ነበራት፡፡ እዚያ መሄድ አቆምኩ፡፡ ውስጤ ግን እንደ እንዳች ይሸበር ነበር፡፡ እሷም እንደ እኔው ተሰቃይታ ኖሮ፣

ደወለችልኝ፡፡ መደብሯ ሄጄ እንድጎበኛት ጠራችኝ፡፡ ሄድኩ፡፡ ሳያት ሳቁ መጣ፡፡ ነገር ግን አልሣቅኩም፡፡ በጣም ስለማፈቅራት ሳቄን አመቅኩት፡፡ በእንግሊዝኛ እንዲህ አለችኝ "ወይ አግባኝ ወይ ከዚህች ከተማ ድራሽህ ይጥፋ!"

"እርቀ-ሰላም አውርደን የልባችንን መጨዋወት ጀመርን፡፡ ሁለታችንም እውነተኛውን ስቃያችንን ልክ ለሌላ ሰው እንደሚያወራ አወጋን፡፡ አቤት! ከዚህ በኋላ የሣቅነው ሣቅ!" አለና አፉን በጣቶቹ እየተመተመ ፍዝዝ ብሎ ጥቂት ፀጥ አለና ጨዋታውን ቀጠለ፡፡

"ጥያቄህን እንዳትረሣ፡፡ ወደዚያ እመለስልሃለሁ፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጋር የተያያዘች ትዝታ ስለሷ እንዳጫውትህ የልሳኔን በር እያንኳኳች ነው፡፡

ይኸውልህ፣ አንድ ቀን እኔና ሐና ከምንዝናናበት ውለን ወደ ቤቷ እሸኛታለሁ፡፡ ደርሰን መኝታ ቤቷ ገባን፡፡ ስናወጋ ቆይተን ወደ ቤቴ ልሄድ ስል በርሳዋን ከፍታ ደስ የምትል ትንሽ ሽቱጥ አውጥታ ሰጠችኝ፡፡ አጠቃቀሙን ጠየቅኳት፡፡ መጠበቂያዋን ነካችና "እንዲህ ስታደርጋት፣ ቀዩ ምልክት ላይ ሲሆን ይተኩሳል፡፡ ነጬ ላይ ስታደርገው ይጠብቃል፡፡ አዎን እንዲያ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ብቻ ወሣ ስትል ሞክረው" አለችና ተወችልኝ፡፡ ተነሣሁ፡፡ በወቅቱ እኔ ካዝንችስ ነው ሰፈሬ፡፡ ሸኝታኝ ተመለሰች፡፡

ሽጉጤን መሞከር አለብኝ አልኩ፡፡ በየት በኩል ልሞክር? ከሞከርኩ አልቀረ ልክ 'የሩሲያውያን ሩሌት' እንደሚባለው ጆሮ ግንዴ ላይ አድርጌ መሞከር አማረኝ፡፡ ወንድ አይደለሁም እንዴ? ማድረግም አለብኝ፡፡ ምን እንደነካኝ አላውቅም፣ ከራሴ ጋር መሟገት ገጥሜ ጆሮ ግንዴ ላይ እንደ ደገንኩት ቃታ ሳብኩ፡፡ ጥይቷ ተተኮሰች፡፡ አምላክ በሕይወቴ ላይ ተዓምር ሠራ፡፡ ውቃቤ መልአክ ቃታዋን ልስብ ስል ቀድሞኝ እጄን ወደታች ዘረጋው፡፡

ሌላ የሚገርመኝ ደሞ፣ ከዚያ ሁሉ ድንጋጤ በኋላ በርግጌ ወደ ቤቴ ልፈረጥጥ ነበር፡፡ ጭንቅላቴ በዝግታ ነው መራመድ፣ በዝ ግታ፡፡ ከተኩስ ድምፅ በኋላ የሚታይ ፍጥነት ያስጠይቃል፡፡ የሚል ዓይነት ትዕዛዝ ሰጥቶኝ ቀስ ብዬ ገባሁ፡፡ ይህን ያዘዘህ ጭንቅላትህ ነው ወይስ መልአኩ ነው? ብትለኝ፣ እኔንጃ፡፡

የሩሲያ ሩሌት መራር ጨዋታ ነው፡፡ ድርጊቱ ሲፈፀም አንድ ጥይት ብቻ ሽጉጥ ውስጥ ይገባና አሽከርክረው ለተፋላሚው ይሰጡታል፡፡ ቃታዋን ለስንተኛ ጊዜ ሲስቧት እንደምትተኩስ ከእዝጌር በቀር ማንም ሊያውቅ አይችልም፡፡ እንግዲህ ተፋላሚው ጆሮ ግንዱ ላይ ደግኖ ቃታ ይስባል፡፡ ከከሸፈ እንደገና መኖር ይጀምራል፡፡ ሽጉጡን

@Amharicbookstore



ለተፋላሚው ያቀብለዋል፡፡ ይህኛው ተራውን ደግኖ ይስባል ቃታዋን፡፡ ይከሽፋል፡፡ አልያም በጥይቷ ጆሮ ግንዱ ተበድሶ ይህችን ዓለም ኩራ እንዳለ ይሰናበታታል፡፡ ተፋላሚዎቹ ከሁለት አንዳቸው መሞታቸው አይቀርም፡፡ ይህንን ሩሲያን ሩሌት ይሉታል፡፡

አሌክሳንደር ፑሽኪን እና ሚካኤል ሌርሞንቶቭ የመሳሰሉት ደራሲያን የሞቱት በፍልሚያ ነው፡፡ የእነርሱ ፍልሚያ ግን እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ሽጉጥ ይዘው ከጠላታቸው የተወሰነ እርምጃ ርቀው በአልቢትሩ ምልክት መሠረት ወደ ተፋላሚው ዞረው መተኮስ ነው፡፡ ተፋላሚዎቹ አንዱ ሌላውን መትተው ሊወድቁ ይችላሉ፡፡ ወይም አንዱ ያልፍና ሌላው ይተርፋል፡፡ ተራ በተራም የሚተኩሱበት ደንብ አላቸው፡፡ ፍልሚያው በስምምነት መሆኑ ነው፡፡

ሐናን እያበሰልኩ ነው እንግዲህ፡፡ እሷ እያበሰለችኝ እንደሆነም አላውቅም፣ እየሆ? በኋላ ነው የገባኝ፡፡ እሆ?! መበሳሰል ነው ፍቅር፡፡ ተቀጣጥረን የምንገናኝበት ቦታ ኮሌጅ ነው፡፡ ከኮሌጅ ወደቤቷ ማድረስ ጀምሬያለሁ፡፡ አንድ ቀን ልሸኛት ከአሥራ አንድ ተኩል እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት መሃል ባለው ጊዜ ደረስኩ፡፡ እዚያ ቀጠሮ ቦታችን ላይ ከአንድ ሰው ጋር ቆማለች፡፡ ስሙን ሁሉ አስታውሰዋለሁ፡፡

"ስብሐት" አለችና ለእኔም የወዘተን ስም ነገረችኝ፡፡ ተጨባበጥን፡፡ ከዚያች ቅጽበት በኋላ እኔን እስከ መፈጠሬም ረሳኝ፡፡

"እ? የት ነው የምታውቂው?" አላት፡፡ እኔ የለሁም፡፡ በአጠቃላይ እሱ ሰው ከሚላቸው አልመደብም፡፡ ምክንያቱም ሰው የፈጠረልኝ ማዕረግ የለኝም፡፡ እሱ በዚያን ወቅት ረዳት ሚኒስትር ነበር፡፡

ያዝ፣ ይህ በጣም 'ኢንተረስቲንግ' ነው፡፡ ብዙ ትርጉሞች ይኖሩታል፡፡ እዚያው እያለሁ መኖሬን ሰርዞ "ተማሪ ነው? ወይስ ሥራ አለው?" ይላታል፣ አጠገቡ ቆሜ፡ ትነግረዋለች ሐና፣ ስለ እኔ ብዙ ጥያቄዎች መለሰች፡፡ በጣም ነበር የተናደድኩት፡፡ ግን በሐና ፊት ጨዋነቴን መርሳት አልፈለግኩም፡፡ ስለዚህ የአቦይ ልጅ መሆኔን ተውኩና የእናቴ ልጅ ሆንኩ፡፡ ዝም፣ ጭጭ ምጭጭ ሆነ ተግባሬ፡፡ ምክንያቱም አቶ ወዘተ ቢባልግም እኔ ገና እያበሰልኳት ስለሆነ፡፡

አቶ ወዘተ በጥያቄና መልስ ብዙ ጊዜ ወሰደ፡፡ እኔም ለራሴ "ምን ያህል ሐና ፍቅር ብታስይዘኝ ነው ይህንን ያህል የታገስኩት?" እያልኩ እያሰላሰልኩ ቆየሁ፡፡ ከዚያም ተለያዩ፡፡ ስሸኛት "ማን አባቱ ነው ይህ ደንከዬ?" ሳልላት አልቋርም፡፡

እሷም "እ! ተወው፡፡ እሱክ እኔም አንተም ምኑም አይደለንም፡፡ እሱ የአንድ ኃያል ሚኒስትር አቃማሪ ነው፡፡ በማቃጠር ነው

ለምክትል ሚኒስትርነት ማዕረግ የደረሰው፡፡ ምንም አይደለም፡፡ "Forget it" ለእኔም ብለህ ቢሆን" አለችኝ፡፡

'All right' አልኩና ደ ጊዜ አለፈ፡፡ ይህን የደረሰብኝን ለሰለሞን ነገርኩት፡፡ ይገርማል የአበሻ ነገር፤ እያልን አወራንበት፡፡ ኤንሪኮ የሚባል ኬክ ቤት አለ አይደል? እዚያ ገብቼ ተቀምጬለሁ፡፡ እንደ ምትሀት ሰለሞንና አቶ 'ወዙተ' ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ ከአሥራ አንድ ዓመት በኋላ ነው'ኮ፡፡ እኔም አበሻ አይደለሁም? ሄድኩና ሰላም አልኩት ሰለሞንን፡፡

"ከአቶ እገሌ ጋር አትተዋወቁም እንዴ?" አለኝ ሰለሞን፡፡

"አይ!" አልኩ፡፡

ያደማህን ቁስል ግን አትረሣም፡፡ እሱ ደግሞ እንደሸረሪት ድር በሰው ላይ ያደራል እንጂ ምን ያህል እንዳደማህ ልብ አይልም፡፡ ቢልም ደንታ አይሰጠውም፡፡ ምን እንዳለህም አያስታውስም፡፡ እሱ ግን መረሣቱን አልፈለገም፡፡

"እ! እ!" ጭንቅላቴን ወዘወዝኩ፡፡

"እንዴ፤ ሶፍያ አላስተዋወቀችንም እንዴ?" አለ ወዙተ

"ኧረ! እኔ ነኝ ሐና መሆንዋን የማውቀው እሱ እኮ ረስቶሃል፡፡ ምን ነው ሰው ንቆ መሬመድ? እኛ ነን ቁስላችንን ይዘን እስከዚህ የደረስነው!

"ሰው ከንቱ! አላስታውስም" አልኩት፡፡

ሰለሞን አለመተዋወቃችንን አምኖኝ "እገሌ ነው እኮ" አለኝ፡፡ ተጨባበጥን፡፡

"እንዴ?" አለ አቶ ወዙተ ትልቅ ነው፤ እንዴት ይረሳል?

"ምናልባት ሐና ትሆን እንዴ ያስተዋወቀችን?" አለኝ፡፡

"ኧረ እኔ'ጃ! ትዝም አይለኝ" አልኩት፡፡

ግር እንዳለው፤ ባለመታወቁ እየቆጨው ተሰነባበትን፡፡ በጨዋ ደንብ፡፡ እንደሄደ "እውነት አላወቅከውም እንዴ?" አለኝ ሰለሞን፡፡

"ገና ብዙ እረሳዋለሁ!፡፡ ለራሴ ብቻ አውቀዋለሁ፡፡ ለእርሱና ለአካባቢው ግን አላውቀውም፡፡ ሆነ ብዬ፤ አውቄ፤ ነው፡፡"

ይገባኛል ማንም ሰው በምድር ላይ ከሚጠላው ነገር አንዱ አላውቅህም መባል ነው፡፡ አንድ ሰውዬ ምንአሉኝ መሰለህ "ስሜን ያስጠራ እንጂ የመጨረሻ ወንበዴም ልጅ ይኑረኝ፡፡" ብለውኛል፡፡ አየህልኝ፤ የዘለዓለማዊ ሕይወት ጥማትህን የምትወጣው ስምህን ቢቻል በጥሩ ባይቻል በመጥፎ በምድር ላይ በመተው ነው፡፡ እማላውቀው የሆንኩበት ምንም አለመሆኑን ላሳየው ነው፡፡ ብዬ ያለፈውን ታሪክ ለሰለሞን አስታወስኩት፡፡

እሱም እየሣቀ "አንተ ደብተራ!" አለኝ፡፡

@Amharicbookstore



"ደሞ ብትፈልግ ገና ሌላ ቀን ሳገኘውም እረሳዋለሁ፡፡"

•

ወጎች እየጣፈጡ ሐሳቦች ሐሳቦችን እየወለዱ ሲሄዱ ጋሺ የወጉ መነሻ ይጠፋዋል፡፡ ስለዚህ የጋሼ አድማጭ በጣም ጥሩ አትኩሮት ያለው መሆን አለበት፡፡ በአትኩሮቱ ውሉን ካስያዘው በጨዋታ ምናብ እንደገና አብረው ይመጥቃሉ፡፡ እኔም ጭብጡን አስያዝኩት፡፡

"እ? ከዚያም የእኔ እንግዳ ሆና ሐና ወደ ፈረንሣይ መጣች፡፡ በማርሰይ ወደብ ቆይታ አደረግን፡፡ ወደ ኢጣሊያ ተሻገርን፡፡ ሮማን፤ ፍሎረንስና ጄኖቫን ተዘዋወርን ጎበኘናቸው፡፡ ከበርካታ ገጠመኞቼ መካከል የጄኖቫ ብቅ አለች፡፡ እሱን ላጫውትህ?

በእግር እየተዘዋወርን አንድ አጭር ኢጣሊያዊ ሰውዬ አይቶን፤ መኪናውን አቁሞ መጣና ሠላምታ ሰጠን፡፡ አጸፋውን መለስንለት፡፡ ከሚስቱ ጋር ራት ሊጋብዘን እንደሚፈልግ ነገረን፡፡ ተገኝቶ ነው? በደስታ ተቀበልኩት፡፡ የት እንደምንገናኝ ተቀጣጠርንና ተለያየን፡፡ ሰውዬው ከሄደ በኋላ ሐና ፍርሃትዋን ነገረችኝ፡፡ በዚያን ጊዜ በአውሮፓ ውስጥ በርካታ ጥቁር ሴቶች አልነበሩም፡፡ ስለዚህ ነጭ ወንዶች ጥቁር ሴት ካጋጠማቸው አስገድደው ይገናኟታል የሚባል ወሬ በሰፊው ይወራ ነበር፡፡

ጥቁር ወንዶችን ነጭ ሴቶች በጣም ይቋምጡብን እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ ይህንን ስጋትዋን ነግራኝ ቀጠሮውን ብንሰርዘው ይሻላል አለችኝ፡፡ እኔም ከአቅማችን በላይ ቢሆን እንኳን አላፊ አግዳሚው ያግዘልናል፡፡ በዚህ ላይ "እኔም እኮ ወንድ ነኝ!" አልኳትና አቅራራሁ፡፡ "ለዚያውም ለጥልያን?! በአባቶቻችን እንተዋወቃለን!" አለና ሳቁን ለቀቀውና ወደ ጨዋታችን ተመለሰ፡፡

በሐሳቤ ተስማማች፡፡ እኔ ግን እውነተኛ ሰው እንደቀጠረን እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ተግባባን፡፡ እተባለው ቦታ፤ በተቀጠርንበት ሰዓት ሄድን፡፡ ሰውዬው ባለቤቱን ይዞ መጣ፡፡ ሚስቱ ረጅም ነች፡፡ እሱ ደረቷ ላይ ቢደርስ ነው፡፡ "በሁለቱ ታጅበን ከሚዲትራኒያን ባህር ዳርቻ ወደሚገኝ መዝናኛ ወሰዱን፡፡ በዚያ መዝናኛ ፒሣ ብቻ ነው የሚሠራው፡፡ ፒሣውን የሚያበስለው ባለ ሆቴሉ ነው፡፡ ረጅም ነጭ ቆቡን አጥልቆ፤ ሊጡን በመጥበሻዋ ላይ ይጠፈጥፍና ወደላይ ያሽቀነጥረዋል፡፡ ከዚያ እንደ መደነስ፤ አንድ ሁለቴ እንደመሽከርከር ብሎ ጠረጴዛውን እንደ ታንቡር ኳ! ኳ! እንዳደረገ የፒሣዋ ሊጥ ከላይ ትመጣለች፡፡ በመጥበሻው ይቀልባታል፡፡ ጋባዦቻችን ባልና ሚስት ነሽጥ ሲያረጋቸው በኦፔራ ስልት ነው የሚያወሩት" አለና እርሱም በኦፔራ ስልት ድምፁን ቃኝቶ አንጎራጎረ፡፡

እኔና ሐና ደስ ብሎን እየሣቅን፣ እየበላን፣ እየጠጣን፣ እየተጫዋወትን ከአስተናጋጆቻችን ጋር አስደሳች ጊዜ አሳለፍን፡፡ ኢጣሊያ ሙሉ በሙሉ ፍቅር አስያዘችኝ ልልህ እችላለሁ፡፡ አሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ሄጄ በሥልጣኔያቸው መረበሼን አጫውቼሃለሁ፡፡ አሜሪካ መንገድ ላይ የሚስቅ ሰው ፍፁም አታይም፡፡ ሁሉም ወደሥራው ሌትም ቀንም ይጣደፋል፡፡ ሣቅ በአሜሪካ በየቤቱ ውስጥ ታግቷል፡፡ ኢጣሊያ ግን ልክ እንደ አገራችን እዚህ ጋ የቆመው ሰውዬ እዚያ ማዶ ካለው ጋር ሲያወራና ሲሣሣቅ ታያለህ፡፡ የት ጋ ነው ያለነው? ውሉን አስያዘኝ?"

እሺ! በወቅቱ አባቷ እኔ ሐናን እንዳገባት አልፈለጉም፡፡ ለምን? ማለት ጥሩ፡፡ ዘሬ ትግሬ በመሆኑ፡፡ አባባላቸውን ሁሉ አስታውሳለሁ፡፡ "የትግሬ ወንድ ስለሆነ አይመችሽም፡፡ አሁን ሊያግባባሽ ነፃ ሰው ይመስላል እንጂ ካገባሽ በኋላ ቤቱ ቀልፎብሽ ነው ሥራ እንኳን የሚሄደው" አሉዋት፡፡

"ሰብሐት አንተ እንደገመትከው አይደለም፡፡ አንተ የእኔን ያህል ጸርሱን አታውቀውም" በማለት ከግባባቻቸው በኋላ፣ እንደ ምንም በግድ ተቀበሉኝ፡፡ "ከወደደች ምን ላድርግ?" ብለው እንድንጋባ መልካም ፈቃዳቸው ሆነ፡፡

የወላጅ እናቷ? አቀባበል በጣም ድንቅ ነው፡፡" እሷ ከወደደችው አለቀ፡፡ መርጣዋለች፡፡ ልክ እኔም አንተን እንደ መረጥኩህ ነው" ያሉት ወይዘሮ ኤልሳቤጥ፡፡

በወቅቱ እኔ ተመርቄያለሁ፡፡ ሥራም አለኝ፡፡ ለአባቴ አንዲት ባለመደገፊያ ወንበር ገዝቼላቸው ወደ ጎድዋ መሄዴን አጫውቼሃለሁ፡፡ የምሥራችም አለኝ፡፡ ትንሽ ከቆየሁ በኋላ "አቦይ እንንሸራሸር?" አልኩዋቸው፡፡ እሺ አሉኝና ነፋስ መቀበል ጀመርን፡፡ በሽርሽራችን ላይ "አቦይ ይኸውልዎ ሚስት ላገባ ነው፡፡ የማገባት ልጅ ዘርዋ እሮሞ ነው፡፡ ፎቶዋም ይኸውልዎ" አልኩና ሰጠኋቸው፡፡

ፎቶዋን ተቀብለውኝ አይተውት "ውይ! እንዴት ታምራለች! ቆንጆ ልጅ ነች፡፡" አሉና ፎቶዋን ሳሙት፡፡ "እንኳንም ትግሬ ያልሆነች፡፡ ዶክተር ተወልደ ብርሃን እንደነገረኝ እኛን ከሌላው ዘር ጋር መጋባታችን ያበዛናል፤ እኛ የሌለንን ተሰጥኦ ልጆቻችን ከሌላው ዘር ያገኛሉ እንጂ የሚፈጥረው ችግር የለም፡፡ እግዚአብሔር ጋብቻችሁን ይባርከው" አሉኝ፡፡ አለና እየሣቀ "የገዛ ልጃቸውን ዶክተር ተወልደ ብርሃን ብለው ሲጠሩት አያስቅም?"

ከወላጆቿ ጋር እስከ ወደ ኋላ ድረስ አልተገናኙም፡፡ ዜናውን ስትሰማ ግን ተደስታለች፡፡

@Amharicbookstore



"እሁሁሁ!" ሣቀ፡፡ "ይኸውልህ፣ መተቃቀፍ ስትል ልብስ እንደተለበሰም መተቃቀፍ አለ" ዓይኑን ቡዝዝ አድርጎ አየኝ፡፡ ሩቅ እንደሚያይ ሰሚቴን ገመተ፡፡ በመካከላችን ፀጥታ እንደሰፈነ ሰኮንዶች አለፉ፡፡

"ሩቅ ነው፡፡ ትዝ እንደሚለኝ እማስታውሰው እኔ በወቅቱ አልደፍርም፡፡ 'Almost' እሷ ነች የምትስበኝ፡፡ ጊዜ ወሰደ፣ ተጋብተን እንደልቤ እስከምሆን ድረስ፡፡ እሷ 'You are welcome' ካለችኝ በኋላ 'I made myself welcome' ማለት ነው፡፡ ግን ቦታውና ሁኔታዎቹ አሁን ትዝ አይሉኝም፡፡ ተያይዘን ብንዝናናም ገንዘብ የሚያስከፍል ቦታ አንሄድም፡፡ ከደረጄ ጋር ነው የምንንሸራሸረው፡፡ እሱ አሜሪካዊት 'girlfrend' አለችው፡፡ አብረን በመኪና ከአዲስ አበባ ከተማ እንወጣለን፡፡ በረጺ በኩል ገጠር ውስጥ ሜዳ መርጠን እንዝናናለን፡፡ ማንም የለም፡፡ ነፃ ነን፡፡ እዛ 'enjoy' እናደርጋለን፡፡"

እስከመተቃቀፍ የሚያደርስ አልነበረም፡፡ እዚያ ለመድረስ ዓመታት ፈጅቷል፡፡ መሣሣም መጫዋወት ግን ነበር፡፡ አስፋወሰን ትምህርት ቤት ሳስተምር እዚያው አካባቢ ነበር የመኖሪያ ቤት የተከራየሁት፡፡ ቅዳሜና እሁድ ልትጎበኘኝ ትመጣ ነበር፡፡ እዚያ ነው፣ መተቃቀፍ የጀመርነው፡፡

ሐና ወጣት በነበረች ጊዜ ውብ ነበረች፡፡ ብዙም አድናቂዎች ነበሯት፡፡ አሁን ሳስበው ለእኔ የተረፈት ያህል የራቀብኝ ትዝታ አለኝ፡፡ ሐና ድብን ያለ እንቅልፍ ይዟት ሄዶ እሷን ማየት እንዴት ደስ ይላል መሰለህ! በጣም! በጣም! ተውባ የምትታየኝ እዚያ ጋ ነው፡፡ አቤት ስታምር! እዚህ ውበት ጋ ተኝቶ የሚያንኮራፋም ይኖራል...

እንደነገርኩህ የሠርግ ሥነ ሥርዓት እንደማንፈልግ ለአባቷ ሐና ነግራቸው ከተስማሙ በኋላ ሐሳባቸውን ቀየሩ፡፡ ወደ ጃንሆይ ወስጄሽ ላግባ ነው ፍቀዱልኝ ትያቸውና ይፈቅዳሉ፡፡ በቤተክርስቲያን ሥርዓት በተክሊል ትጋባላችሁ፡፡ አለዚያ ጃንሆይን እንደ መናቅ ይቆጠርብኛል፡፡ ከዚያም ከቤተ ክርስቲያን መልስ የቁርስ ሥነ ሥርዓት በኢትዮጵያ ሆቴል ይዘጋጅላች ኋል፡፡ የፕሮግራሙ ፍፃሜ ይሆናል፡፡ ተስማማን፡፡ ሐና አባቷን ረጅም ሥርዓተ ተክሊሊ እንዳይሆን አሳሰበቻቸው፡፡ ለአንድ ሰዓት ብቻ በፊጀ ሥነ ሥርዓት እንደምንፈጸም ተስማሙ፡፡ ይህን ለቀሳውስቱ እንደሚነግሩዋቸው ቃል ገቡላት፡፡ አሁን እንደምጠረጥረው ልጃቸውን እሺ ይበሏት እንጂ ለቀሳውስቱ የነገሯቸው አይመስለኝም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ደንብ መሠረት ሥርዓተ ጋብቻችንን ፈፀምን፡፡

እሊጋ ወራሽ እንግዳችን ነበሩ። ጃንሆይን ልንተዋወቅ ሄደን እጅ ስንነሳቸው ጎርነንና ዝግ ባለ ድምፅ "የማን ልጅ ነው?" አሏት ጃንሆይ።

"ጃንሆይ አባቱን አያውቋቸውም" አለቻቸው ሐና።

ጃንሆይ በጋብቻችን መደሰታቸውን ገልጸውላት ሰባት ሺ ብር ሸልመዋት መጣች። የሜትላ ሽርሽራችን መቀሌ፣ ዓድዋ፣ አስመራና ምፅዋን ተዘዋውረን ጎበኘን። ይህን በሽበሽ የሜትላ ሽርሽር የጋበዘንና አብሮን የተጓዘው የሁላችንም ታላቅ ወንድም አያይ ገብረ ክርስቶስ ነበር። አይ መስተንግዶ!

አዲሱ ገነት ቤት አካባቢ ኪዳኔ በየነ ሕንፃ አጠገብ ለአዲስ ተጋቢዎች የምትመች ትንሽዬ አፓርትማ ተከራይተን ኑሮ ጀመርን። ቤተሰቦቻችን ይጎበኙናልም፣ እንጎበኛቸዋለንም። አባቷ አንድ ቀን ማታ እቤት መጡ። እንደገቡም ሐናን ጠየቋት። "እኔ እከ እናንተ አካባቢ ያለች መስሎኝ ነበር" አልኳቸው። በኋላ እንደታወቀኝ የእርሷ እቤት ውስጥ አለመኖር አስደንግጠዋቸዋል። "ወይኔ ልጄን አሳጣኋት" የሚል ስሜት ይንፀባረቅባቸዋል። እኔም ደህና ከሆነች የእርሷ በመከከላችን ያለመገኘት እንደማያጎድለን አወጋኋቸው። በሩን ቆልፈባት እንደማልሔድ ተገነዘቡ። እፎይ አሉ። ከዚህ ዕለት ጀምሮ እንደ አብራካቸው ክፋይ ያዩኝ ጀመር።

እኔና አቶ ይልማ በጣም ከመቀራረባችን የተነሣ ወጣት ሆነው የጻፏትን አነስተኛ ድርሰታቸውን አሳይተውኛል። ለእኔም መጀመሪያው ገፅ ላይ ማስታወሻ እንደፃፉልኝ ትዝ ይለኛል። በማምት ሳስታውሳት እንደ አደራ ተቀባዮቸው ነው ያዩኝ።

አንድ መጽሐፍም ተውሰውኝ ነበር። The Fall of the British Empire' የምትል መጽሐፍ ነች። ከሰው መጽሐፍ ሲዋሱ አይቼ አላውቅም። እንግሊዝ ለእሳቸው ሁለተኛ አገራቸው ነች። እዚያ ነው የተማሩት። ስለዚህ የመጽሐፉ ደራሲ የእንግሊዝን አወዳደቅ እንዴት ያየት ይሆን? ብለው ነው የተዋሱኝ።

በጣም ሽርክ ከሆንን በኋላ የነገሩኝን ላካፍልህ። አቶ ይልማ፣ ጃንሆይ ልከዋቸው ከወቅቱ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ዲ.ሮዝቬልት ጋር ለመነጋገር ዋሽንግተን ዲሲ ሄዱ። የተጓዙበት ምክንያትም በወቅቱ እንግሊዝ ከደቡብ አፍሪካ ከኬፕታውን እስከ ግብፅ ዋና ከተማ ካይሮ ድረስ የባቡር መስመር ለመዘርጋት አስባለች። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለቅቃ ብትወጣም እንግሊዝ በእግሯ ተተክታ የመዘማየቱ ነገር ጃንሆይን አሳስቧቸዋል። የባቡር መስመር መዘርጋት በኢኮኖሚ ረገድ ጥሩ እሴት ሊኖረው ይችላል፤ ነገር ግን



መስመሩን የሚዘረጋው እንግሊዝ ነውና የሚያመጣው መዘዝ ምን እንደሆነ አይታወቅም።

ዋሽንግተን በታሰበው ዕለት ቢገቡም ፕሬዚዳንት ሮዝቬልትን በቀላሉ ማግኘት ግን የማይታሰብ ሆነ። ከስንትና ስንት አገር ደጅ ለመጥናት በርካታ ጠቅላይ ሚኒስትሮችና ዲፕሎማቶች ናቸው ኋይት ሀውስ የሚመጡት። ስለዚህም የአንዲት ትንሽ አገር መልዕክተኛ እንደመሆናቸው ምንም ዓይነት ዕድል አልነበራቸውም። አንዲት መንገድ ብቻ ፕሬዚዳንቱ ቢሮ ልታደርሳቸው እንደምትችል ገመቱ። ስለዚህ የሚስስ ሩዝቬልትን ጓደኛ ተዋወቁዋት። ይህንን ገጠመኞቸውን ሲያወሩልኝ እየፈሩ ነበር።" አለና ጋሼ ስብሐት እየሣቀ "ሴትዮዋ በዕድሜ ትበልጣቸዋለች። መዝናናቱ፣ መደነሱ፣ ማውጋቱ ተጀመረ። ቀስ ብለው ወደ ፍቅ ወጡ። ለምን ወደ ፍቅ እንደወጡ አልነገሩኝም። ፍቁ የሰማዩን ገፅ በሙሉ ያሳያል። ተፈጥሮን እያደነቁ አወጉ። በሚቀጥለው ቀን አቶ ይልማ በሴትዮዋ አማካኝነት ከፕሬዚዳንቱ ባለቤት ጋር ተዋውቀው የመጡበትን ምክንያት አዋዩዋቸው። በነጋታው ፕሬዚዳንቱ'ጋ ለመቅረብ ፕሮግራም ተያዘላቸው። በቀጠሮው ቀን ከፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ዲ. ሮዝቬልት ጋር ተገናኝተው በተላኩበት ጉዳይ ላይ ተወያዩ፤ ፕሬዚዳንቱም ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ትዕዛዝ አስተላለፉ። የእንግሊዝ አላማ ተደናቀፈ። እንግሊዞች በዚህም ተበሳጭተው ከአገራችን ሲወጡ የሚችሉትን እየነቃቀሉ፣ ያልሆነላቸውን እያፈራረሱ ሄዱ።

በሆነሩቱ የለውጥ ንፋስ መንፈስ ሲጀምር እሳቸውን አራተኛ ክፍለ ጦር ሊወስዱዋቸው ምሽት ላይ ወታደሮች ሲመጡ አብረን ነበርን። አንድ ሰው ለመውሰድ አንድ ማክ ሙሉ ወታደር ነበር የመጣው። ወታደሮቹ በግቢው ዙሪያ መሽገው ነበር። ሠራተኞቸው እኔና እሳቸው ወዳለንበት ክፍል ገብቶ ወታደሮች እንደሚፈልጓቸው ነገራቸው። ራሳቸውን ሲያዩ የቤት ልብስ ነው የለበሱት። "ቆይ መጣሁ በላቸው" አሉና ወደመኝታ ቤት ገብተው ልብሳቸውን ቀየሩና መጡ። ገጽታቸውን ስመለከት አንድም የመሸበርም ሆነ የመፍራት ስሜት አልነበረባቸውም። የግቢውን ዙሪያ ከበው በነበሩት ወታደሮች ታጅበው ከቤት ወጣን። እሳቸው አቶ ይልማ መሆናቸውን ነግረው መኪና ውስጥ ገቡ። ተያይዘው ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ሄዱ። ብዙም ሳይቆዩ ታመሙ። ሆስፒታል ገብተው እንዲታከሙ ተፈቅዶላቸው በሕክምና ሲረዱ ቆዩ። ምን ያህል ጊዜ በሆስፒታል እንደቆዩ አላስታውስም። ብቻ እዚያው ሆስፒታል ውስጥ ማረፋቸውን አውቃለሁ።

@Amharebookstore

ከሐና ወንድ ልጅ ከነቀጭሉ ወልደናል፡፡ ስሙም ኢየሱ ስብሐት ይባላል::

በእኔ የደረሰብኝን ልጨምርልህ፡፡ እኔን ከገንዘብና ከሕግ በስተቀር የሚገዛኝ ነገር የለም፡፡ ከዚያም በላይ ፍቅር ነው የሚረታኝ፡፡ ሐና ግን ለእኔ ከዚያም በላይ ነበረች፡፡ እንዴት ልንገርህ እናቴ ማለት ነበረች፡፡ በሕይወትህ አንዳንዴ ሙሉ ሰው የምትለው ሰው ይከሰታል፡፡ ለእኔ ሐና ሙሉ ሰው ነበረች፡፡ በውበትም ዓይኔ ከምንሠራበት በር ማዶ ነው እኔና ሐና አፓርተማ ተከራይተን የምንኖረው፡፡ ግማሽ እብድ ግማሽ ጂኒየስ የሆነው የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ሳምሶን ፈረስ እኛ ቤት መጣ፡፡ ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ እኔ ምንም ሳይታየኝ በጣም እንደራበው ሐና ታይቷታል፡፡ አየህ፣ እንዲህ ናቸው ሴቶች፡፡ አቀራርባለት ተመገበ፡፡ ሌላ ቀን ሲሮ የሚባል የብራዚል ሰው የሆነ ወዳጃችን እንዳለ አጫውቼሃለሁ፡፡ የዚያን ጊዜ ኢየሱን ነፍሰ ጡር ናት፡፡ ስለዚህ ሲሮ ጋ ለመሄድ እሷን ማስፈቀድ ያስፈልገኛል፡፡ ፈቅዳልኝ ሲሮ ቤት ሄድኩ፡፡ ሲሮን አግኝቼው የሚጠጣ ይዘን አንድ ሁለት ብለን ጨዋታ ጀመርን፡፡ በዚህ መካከል ስልኩ ጮኸ፡፡ ተነሣ፡፡ ስልኩ የፈለገው እኔን ነው፡፡ ሐሎ ስል ሐና ነች፡፡ አስታውስ ነግሬያት ነው የሔድኩት፡፡ በስልኩ ውስጥ ግን እያለቀሰች ነው፡፡ "ብቻዬን ትተኸኝ?" ነው ምክንያቷ፡፡ ላምን አልቻልኩም፡፡ እግዜር ረድቶኝ ቀደም ብሎ ስለ ነፍሰጡር ሴቶች ባሕሪይ መለዋወጥ አንብቤ ባልቆይ ኖሮ አበደች ብዬ እደነግጥ ነበር፡፡ ሐና በፍፁም አልቅሳ አታውቅም፣ ወዳጅ ዘመድ ካልሞተ በቀር ያውም እንጃ፡፡ ትዝ የሚለኝ አጋጣሚ የለም፡፡ ስልኩን ቁጭ አድርጌ ወዳጄን ይቅርታ ጠይቄ ወደቤቴ ሔድኩ እልሃለሁ፡፡ ልጨምርልህ?"

ይህን የምነግርህ አንብቤውም ኖሬውም የማውቀውን ነው፡፡ ሴቶች ከእኛ ከወንዶቹ ይበልጥ ስሜታዊ ናቸው፡፡ በአስተዳደግ ይሁን በተፈጥሮ አይታወቅም፣ አሁን ባለንበት ስሜታቸው ከእኛ ከወንዶቹ ይለያል፡፡ ሴቷ! ነፍሰ ጡር ሳትሆን ሰውነትዋ ከልጅነት ጀምሮ እንደ እኔና አንተ ብቻውን ነበር፡፡ አንድ ቀን ሳፍቅር ብላ ብትተቃቀፍ ሁለት ሰውነት ይኖርባታል፡፡ ስለዚህ ሕሊናዋ ሳይዘርበት አይቀርም፡፡ ደግሞም እውነት አላት፡፡ ሰውን የሚያክል ፍጥረት በአካሏ ውስጥ እየፈጠረች አይደል? ሚሊዮን ወንድ ጂኒየስ ቢሰበሰብ እኮ እንደ እሷ አንድ ሰው አይፈጥርም፡፡ አንተ ግን ይህንን ጊዜ እኔ ትንሽዋን ልጄን እንደማቀብጣት ማቅበጥ ነው፡፡ ይህ አድራጎትህ ምን

@Amharicbookstore



ያስከትላል መሰለህ? አካላቸው መረበሹን ትቶ ዘና እንዲል ይሆናል፡፡ ውስጧ ያለውም ፍጥረት እንደ ልቡ " ይዋኛል፡፡ ውጪውን ከረበሽከው፣ ውስጡ ሊበጠበጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ አንተ ጠንቃቃ ሁን:: ይህንን የምነግርህ አስበህበት እንድትቆይ ነው፡፡ በቅርቡ ከፀሐይ ጋር እንጋባለን? ብለኸኝ የለም? እንድታውቀው ስንቅ እያቀበልኩህ ነው፡፡ እንቀጥል...

የጥበብ ውጤቶችም ሆነ ባሕላዊ ቁሳቁስ መሰብሰብ የሚማርካት ሐናን ነው፡፡ እንዴ አሌክስ (እስክንድር ቦጎሲያን) ልዩ ልዩ ሥዕል እየሳለ ለጓደኞቹ ይሰጠን ነበር፡፡

እሱ የሳለልን ሥዕል እቤታችን ነበር፡፡ ሐና አሜሪካን እንደገባች እኔ ጋ ቢሆን ይጎሳቆላል ብዬ ለአንድ ነውረኛ ለሆነ፣ በወቅቱ እንዲህ ያደርጋል ብዬ ላልገመትኩት ተዋናይ በአደራ እንዲያስቀምጥልን ሰጠሁት፡፡ ዓመታት አለፉ፡፡ አንድ ቀን ጥበበ ተርፋ አንድ የታዋቂ አስመጪና ላኪ የሆኑ ሰው ቤት ይህንን ሥዕል አይቶ ከየት እንዳገኙ ጠየቃቸው፡፡ አሁን ማንነቱን ካልገለፅኩልህ ተዋናይ በሰባት መቶ ብር እንደገዙት ነገሩት፡፡ በወቅቱ ተናደድኩ፡፡ ሳገኘው የሠራው ሥራ ፀያፍ እንደሆነ ልነግረው ወሰንኩ፡፡ ሳንገናኝ ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ ሰውየውን ግን እንቀዋለሁ፡፡

ተከዝ ብሎ አየኝ፡፡ «እእ! መለያየት በሁለታችንም ነፍስ ውስጥ የለችም፡፡ ችግር ግን የማንወደውን ምዕራፍ አመጣችው፡፡ እሷ የልብ ሕመምተኛ ነች ብዬሃለሁ፡፡ በዚህም ምክንያት በጃንሆይ ጊዜ ለሕክምና ወደ ለንደን ሄዳ ታክማለች፡፡ ፍቃድ የሰጧት የአገር ውስጥ ዶክተሮች ናቸው:: ለድጋሚው ጉዞ አልሰመረም:: ምክንያቱም ደርግ ወደ ሥልጣን የመጣበት ጊዜ ነበር:: ደርጎች እርስ በራሳቸው በጣም ይፈራራሉ፡፡ ምን እንደሚሠሩም ገና በደምብ አያውቁትም፡፡ ማን ደፍሮ ወደ ለንደን ለሕክምና እንድትሄድ ይፍቀድላት? ፈቃጅ ስታጣ ጊዜ "እዚህ ተቀምጬ ሞትን ከምጠብቅ ለምን አልኮበልልም?" ብላ በኦፕሬሽን ደረጀ አማካይነት አገር ጥላ ጠፋች፡፡

ደረጀ ደሬሣ የአክስቷ ልጅ እንደሆነ እናስታውሳለን፡፡ እሱ ከሚቼልኮትስ ኩባንያ ጋር ተነጋገረ፡፡ ኩባንያው ሴስና የምትባል ትንሽ አውሮፕላን አለችው፡፡ ምናልባት ከአሥር እስከ አሥራ አንድ ሰዎች ትጭናለች፡፡ ያችን አውሮፕላን ለጥ ባለው ቢሾፍቱ መንገድ ላይ አሣረፋት፡፡ እነ ሐና በመኪናቸው ደረሱ፡፡ ቀጠሮው ሠመረ፡፡ ሴስና አቆበቆበች፣ በሠላም ተነሣች፣ ፍቅረኛዬንና የማደንቀውን ጓደኛዬን ይዛቸው በረረች፣ እልሃለሁ፡፡

እነደርጉ የዚያን ጊዜ ገና እጅ እጅ አላሉንም፡፡ አዲስ ወቅት ነው፡፡ ተስፋ የምናደርግበት፡፡ አንድ ጊዜ የሚቻልኮትስ ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ኦቴል ቤት ራት ተጋብዘን የደርጎች ጉዳይ ተነስቶ ስንጨዋወት ተጣላን፡፡

ወደ ፀብ ከመሄዴ በፊት መጀመሪያ ሚስተር ኦቴልን ላሳይህ፡፡ በባሕሪው ጠጪ ነው፡፡ ከጧት እስከ እኩለ ሌሊት የሚጠጣ ሰው ነበር፡፡ ነገር ግን ሕሊናው በምንም አይነት ሚዛኑን አይስትም፡፡ ሥራውንም በደንብ ያከብራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከሰላሣ እስከ አርባ የምንሆን 'የቢዝነስ' መሰሎቹን እንዲሁም የሚግባባንንና ወዳጆቹን በቤቱ ራት አዘጋጅቶ ይጋብዘናል፡፡ በነገራችን ላይ የራት ግብዣን ሳነሣ ገብረ ክርስቶስ ደስታ ትዝ አለኝ፡፡ እሱም እቤቱ በወር በወር በርሱ ዝንባሌ ዙሪያ ያለነውን ሰዎች ራት የመጋበዝ ባሕል ነበረው፡፡ ወደ ሚስተር ኦቴል እንመለስ?

የደርጎቹ ስም ተነሳና እንዲህ አለ "እነዚህ አሁን የለውጥ እውነተኛ አርበኞች ይመስላሉ እንጂ ጉበ ሲለምዱ ይነቅዛሉ፤" ይህን ጊዜ እኔ በጣም ተናደድኩ፡፡ "ሚስተር ኦቴል!" አልኩት፡፡ በገዛ ቤቱ፡፡ እኔ ያውም ራሴን ጨዋና ጭምት ነኝ ብዬ የማምን ሰው ነኝ፡፡ የዚህ ዕለት ግን አላስቻለኝም፡፡ "ቢነቅዙም እንኳ ብዙ አስፈላጊ ለውጥ ከመጡ በኋላ ነው" ብዬ መጮሔን አስታውሳለሁ፡፡

አዎ! ደረጀና ሐና በዚህ አባባሌ ግድ የላቸውም፡፡ ዓላማቸው እኔ ሳላውቅ እርሷን ይዞ ከአገር መውጣት ነው፡፡ ሚስተር ኦቴልን ባልናገረውም ኖሮ፣ ተደብቀው መኮብለላቸው የታመነበት ጉዳይ ነው!

እኔ ከአገሬ የመውጣት ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ እኔ ከዚህች አገር አልወጣም፡፡ እንዴት ይህንን ብሩሕ ተስፋ ሳልቋደስ፣ የበኩሌንም ሳላዋጣ አገሬን ጥዬ እኮበልላለሁ? በጣም የሚያስደስት ተስፋ ነበር የተቀጣጠለው፡፡ ፀጋዬ ገብረመድህን 'ሀሁ በስድስት ወር' የሚል ርዕስ የሰጠውን ቴአትር ስታነብ ግልፅ ይሆንልሃል፡፡ ሁላችንም እንደእዚያ አይነት ተስፋ ነበር በልባችን የሰነቅነው፡፡ ግን በቆይታ ስናየው አልሆነም፡፡ 'ላም አለኝ በሰማይ...' እንዲሉ ሆነ፡፡" አለና ተከዘ፡፡

እህ! ይሄም አጋጣሚ ባይኖር ትተውኝ ነበር የሚሄዱት፡፡ በሚገባ ያውቁኛል፡፡ እኔ ከዚህች አገር መውጣት አልፈልግም፡፡ በእርግጥ ወቅቱ አብዮት የሚካሔድበት ጊዜ ባይሆንና ቀድሞ የነበረው የጃንሆይ መንግሥት ቢቆይ ኖሮ ተነጋግረን እንሰነባበት ነበር፤"



ለሥራ ጉዳይ ለአስራ አምስት ቀን ከአዲስ አበባ ወጥቼ ነበር፡፡ ስመለስ ከአራት ቀን በፊት መሄዳቸውን ሰማሁ፡፡ እሌኒ መኩሪያ ነበረች ይህንን የነገረችኝ፡፡

ደረጀ እኔንና ሐናን ጠንቅቆ ያውቀናል፡፡ ስለዚህ ሐናን እንዲህ ያላት ይመስለኛል፡፡ ይህ የምነግርህ እርግጠኛ ነኝ ብዬ የማምነውን ነው፡፡ አጠፋፋቸው ተጠንቶ አልቋል፡፡ ሐናም የመጨረሻ ውሳኔዋን ልትነግረኝ ፈልጋ ለደረጀ አማከረች፡፡ እሱም እንዳትነግረኝ ከለከላት፡፡ ሲያሳምናትም "ስብሐት አብሮን መኮብለል አይፈልግም፡፡ ስለዚህ እኛ ከጠፋን በኋላ ደርጎች ይመረምሩታል፡፡ የዚያን ጊዜ ስለ አጠፋፋችን ምንም የሚነግራቸው አይኖርም፡፡ ይኸንንም ደርጎች ስለማያምኑት አማክረህ ነው የሸኘሃቸው፤ ብለው አሣሩን ነው የሚያሳዩት፡፡ ምንም ሳንነግረው ከሄድን ግን ደህንነቱን ለመጠበቅ የተሻለ መንገድ ነው" ሳይላት አልቀረም፡፡

አዎን! ሐና ለንደን መድረሷን ከሰማሁ በኋላ ሁለት የደርግ አባሎች ቢሮዬ መጡ፡፡ አንዳንድ ጥያቄዎች ይጠይቁኝ ጀመር፡፡ ከአጠያየቃቸው የተረዳሁት የመደብ የበላይነትና የበታችነት አለበት፡፡ በእነርሱ አስተሳሰብ ሐና የኔን መደብ ንቃ ከድታኝ ነው የኮበለለችው፡፡ እኔ ግን በፍጹም ከድታኝ እንዳልሄደች ነገርኳቸው፡፡ መታመሟንና ፈቃጅ ማጣትዋን ላስረዳቸው ሞከርኩ፡፡ በተጨማሪ በጃንሆይ ዘመነ-መንግሥት ሐና አንድ ሕቡዕ ድርጅት ውስጥ እንድንገባ ትገፋፋኝ ነበር፡፡ እኔ ግን የጃንሆይን ነጭ-ለባሽ መበጣጠስ የሚችል ጠንካራ ድርጅት በአገራችን ውስጥ ስለሌለ ይህንን ሐሳብዋን መተው እንዳለባት አስረድቼ ከለከልኳት፤ እንጂ የሐና ነፍስ አብዮተኛ እንደሆነ ላስረዳቸው ጣርኩ፡፡ አላመኑኝም፡፡ ዕድለኛ ስለሆንኩ የቢሮው በር ተንኳኳ፡፡ ሰው ገባ፡፡ በዚህ ጊዜ ደርጎቹ ተሰናብተውኝ ወጡ፡፡ ከዚያ በኋላ ለእኔ በጣም ጥሩ ሰዎች ሆኑልኝ፡፡

በዚያን ወቅት ቀበሌ አዲስ ነገር ነው፡፡ የዚያው ሠፈር ቀበሌዎች ቢሮ የሚያደርጉት ቤት አጡ፡፡ ይህንን ሊያማክሩኝ ወደ እኛ ቢሮ መጡ፡፡ 'ለጊዜውም ቢሆን የምንሠራበት ትርፍ ክፍል ካላችሁ?' ብለው እንድናውሳቸው ተማፀኑን፡፡ እኛም ከአሜሪካን የሰላም ጓድ አባል ሆነው የሚመጡ ወጣቶችን የምናሠለጥንባቸው ሰርቪስ ክፍሎች አሉን፡፡ በዓመት ውስጥ ለአራት ወራት ብቻ ነው የምንጠቀም ባቸው፡፡ እነዚያን የሰርቪስ ክፍሎች እንዲጠቀሙባቸው ፈቀድኩ፡፡ ይህንን ቀበሌዎቹ ለደርጎቹ ሲመጡ ነገሯቸው፡፡ ደርጎቹም ይህንን ሲሰሙ ልክ እንደ ሀቀኛ ዜጋ ድርጊት ቆጠሩት፡፡ ቀበሌዎቹ ቢሮ ባይጠይቁኝ፣ እኔም ፈጥኜ ባልተባበራቸው ኖሮ ምን ይውጠኝ ነበር?

አንድ ቀን ደርጎቹ መኖሪያ ቤቴ መጡና ከቤቴ እንድወጣ አዘዙኝ፡፡ እሷ በሌለችበትም ቤት ውስጥ መኖሩንም አልፈለግኩትም፡፡ ስለዚህ ሻንጣዬን አንጠልጥዬ ወጣሁ፡፡ እሌኒ መኩሪያ ጋ ሐና የመሠነባበቻ ደብዳቤና አሥር ሺ ብር ትታልኝ ሄዳለች፡፡ ያንን ተቀብዬ ቀሪውን ሕይወቴን ጀመርኩ፡፡

ደብዳቤዎቹ አሁን የሉም ከዓመታት በኋላ እኔ የጻፍኩላትን ደብዳቤዎች ሰብሰባ ሰጠችኝና ተለያየን፡፡ በዚያን ጊዜ አብዮቱ በአገራችን ፈንድቷል፡፡ ደብዳቤዎቹ ለእኔ ጥሩ ትዝታ ቢኖራቸውም እየቆየ በውስጤ የሚተራመሰውን ሲቀይ መቻል አቃተኝ፡፡ ስለዚህ ለዜና እናት አንድ ቀን እንኪ፣ እሣት ለኩሺበት፡፡ ብዬ ሰጠኋት፡፡ አብረን ያተነሣናቸውን ፎቶዎች ደግሞ ሐና አውሮፓ ከገባች በኋላ ሰብስቤ ላኩላት፡፡ እኔ አገሬ ውስጥ ነው ያለሁት፡፡ እሷ ብዙ የሀገሯ ልጅ በሌለበት ዓለም ውስጥ ነው ያለችው፡፡ ስለዚህ አንዳንዴ ትካዜዋን መክፈያ እንዲሆናት፣ ለልጆችንም ዘመዶቹን እንድታስተዋውቀው አስቤ ላኩላት፡፡

ሐና አሁን አሜሪካ ነች:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መልዕክተኛ ነች፡፡ በአንድ ወቅት ደቡብ አፍሪካ ሄዳ ነበር፡፡ ኔልሰን ማንዴላ ትከሻዋን አቅፈው ፈገግ ብለው የተነሱት ፎቶግራፍ ወላጅ እናቷ ቤት በቅርቡ አይቼዋለሁ፡፡ በአውሮፓ ውስጥ የኮሶቮ ችግሮች ሲከሰቱ ተልካ ሔዳለች፡፡ ጥይት በአናቷ ላይ እየጮኸ ተልእኮዋን ከግብ ለማድረስ ትጥር እንደነበር በቅርቡ እዚህ አዲስ አበባ መጥታ አጫውታኝ አጫውታኛለች፡፡ "የሚተኩሱት ሊገድሉን ይሁን ሊያስፈራሩን እንጃ" አለች፡፡

ሊያሱ?! እሱማ በባዮኬሚስትሪ የዶክትሬት ዲግሪውን ተቀብሏል፡፡ የሚስማማውንም ሥራ አግኝቷል፡፡ በግምት ከኒውዮርክ በባቡር ሰላሣ ደቂቃ በሚያስኬድ ከተማ ውስጥ ይኖራል፡፡" በፀጥታ ጢሙን ሲልግ ቆየና " The Iron Lady የሚለውን ሐረግ ስትሰማ ማንን ታስታውሳለህ?

አዎን ማርጋሬት ታቸርን ታስባለህ:: እኔ ግን ሐና ይልማን ነው የማስታውሰው፡፡ ጠንካራ፣ በራሷ የምትተማመንና በሥርዓት የታነፀች፣ ሰው አፍቃሪ፣ በባሕሪዋ ቀጥተኛ ሴት ነበረች፡፡ ያ ቆራጥነት ባይታከልበት ኖሮ እዚህች አገር ብትቀር ኖሮ ያኼኔ አፈር ልትሆንም ትችል ነበር፡፡ ስለዚህ ሐና የማፈቅራት ብቻ ሳትሆን የማደንቃትም ሴት ነች" አለኝ፡፡ አዛውንቱ የገሃዱ ዓለም መምህሬ፣ የዕድሜ ልክ እውነቱን አጉልቶ አሣየኝ፡፡

***



*ኃይለ መለኮት መዋዕል ጋር ወደ ሰሜን ሸዋ ደብረሲና በ1981 ዓ.ም ሄደው ነበር። ደብረሲና ቀበሌ ሰላሌ ውስጥ ልዩ ስሟ ጓዜል በምትባል ቦታ መስክ ላይ ተቀምጠው ስለሌት ስለ ሐና ሲያወሩለት ከቆየ በኋላ "ቀደም ብለው ነግረውህ ቢሆን ኖሮ አብረሃቸው ትሄድ ነበር ወይ?" ብሎ ጠይቆት ነበር። "አልሄድም ነበር ትልቅ የወይራ ዛፍ ካለበት ቦታ ተንቅሎ እንደገና ቢተከል አይበቅልም። እኔ ሥራዬም ግንደም ያለውና የሚኖረው እዚሁ ነው" ብሎ ከምሩ እንደሚጠላው ገልጾልኛል።*

## ፲፫

# ያለፈውን ታሪክ ፍለጋ

ሐምሌ 12 ቀን 1992 ዓ.ም በር ጠረጴዛዬ ላይ የእሌኒ መኩሪያን መልዕክት አገኘሁ፡፡ ደወልኩላት፡፡ ከሰላምታ መለዋወጥ በኋላ ሐና ይልማን በመስመር ላይ አገኘኋት፡ አዲስ አበባ መጥታለ

ቀደም ብዬ ስለ ማስታወሻ ለእሌኒ አጫውቼአታለሁ:: ይህን ሥራዬን በተመለከተ ለሐና ነግራታለች፡፡ ስንነጋገር የሰነበተ ወዳጅነት እንዳለን ነው የተሰማኝ፡፡ ከአወራሯ እንደተረዳሁት ቅን ነች፡፡ ነገ በአምስት ሰዓት ሒልተን ሆቴል ተቀጣጥረናል፡፡

ቀጠሮው ተሰውጦ በሌላ ሰዓት ሼራተን አዲስ ሰመርፊልድ ሬስቶራንት እንድንገናኝ እሌኒ ቀጠረችኝ፡፡ በዕለቱ ከፊያው ገለል ብሎ የዳመና ግላጭ ፀሐይ ወጥታለች፡፡ ወደ ውስጥ ዘለቅሁ፡፡ የሆቴሉ ፀጥታ አስከባሪዎችና አስተናጋጆች መድፍ ቀረሽ ሰላምታ እየሰጡኝ እኔም አፀፋውን እየመለስኩ በተባለው ቦታ ደረስኩ፡፡

ሸራተን እንደደረስኩ በሆቴሉ አስተናጋጅ መሪነት የታሰበው ቦታ ደረስኩ:: ጠምዘዝ እንዳልኩ እነ ሐናን ከፊት ለፊት አየኋቸው፡፡ በሬስቶራንቱ ከአንዱ ጥግ የሐና ቤተሰብ ታድመው የከምሣ በኋላ ቡናቸውን ሲጠጡ ነው የደረስኩት፡፡ መጀመሪያ ዓይኔ ያረፈው እሌኒ ላይ ነው፡፡ እኔ ከምመጣበት አኳያ ሐና ጀርባዋን ሰጥታኝ ነው የተቀመጠችው፡፡ አጠገባቸው ስደርስ ተነስታ ተቀበለችኝ፡፡

ሐና ይልማ ገፅታዋ የቀይ ዳማ ነው፡፡ በቁመት አጠር ብላ በስፖርት የተገራ የሚመስል ሸንቃጣ አካል አላት፡፡ ለቁመናዋ

የሚስማማ ቀለል ያለ አለባበስ ለብሳለች፡፡ ቄንጠኛ መነፅር አድርጋለች፡፡ በዕድሜዋ ከጋሼ ስብሐት በሰምንት ዓመት እንደምታንሰው ባውቅም አሁን በአካል ያገኘኋት ወይዘሮ በዕድሜዋ አርባዎቹ ውስጥ ያለች ነው የምትመስለው፡፡ ከዕድሜዋ 16 ዓመታቶቹ የት ገቡ? 'ሰው ማንን ይመስላል? ቢሉ ኑሮውን' አልኩ በልቤ፡፡ በአነጋገሯ ከአማርኛው ይልቅ እንግሊዝኛው ነው የሚቀናት፡፡ ይህች ወይዘሮ ነች የጋሼ ስብሐት የዕድሜ ልክ እውነት፡፡

ራሷን አስተዋውቃኝ ቤተሰቦቿን አከለች፡፡ ከቤተሰቡ ተነጥለን ብቻችንን እንድናወጋ ቦታ ቀየርን፡፡ ጥድፊያው ተጀመረ፡፡ ስትራመድ ሐያዎቹ ዕድሜ ክልል እንደሚገኙ ወጣቶች ቀልጣፋ ነች፡፡ የምጠጣውን እንዳዝ ጋበዘችኝ፡፡ ቡና አዘዝኩ፡፡ ለጨዋታው ቸኩያለሁ፡፡ ሐና ግን በመጋበዙ ፀናች፡፡ "ብፈ የተዘጋጀ ገበታ ስላለተነሳ የምርጫህን አንስተህ ወደ ጨዋታው ብንመለስ?" አለችኝ፡፡

እርሷን ደስ እንዲላት ወደተሰናዳው ምግብ ሔድኩ፡፡...

"በቅርቡ ከኒውዮርክ ወደ ደቡብ አፍሪካ መሥሪያ ቤቴ አዛውሮኛል፡፡ አሁን ያለሁት በጥድፊያ ላይ ስለሆነ ጊዜ የለኝም እንጂ፣ ሥራህን ባነበውና ባግዝህ ምርጫዬ ነበር፡፡ የሚቻል ከሆነ ቤተሰባችንን የሚመለከቱትን ምዕራፎች ብትሰጠኝ ለሰለሞን አልክለትና አስተያየት እንዲሰጥበት እፈልጋለሁ" አለችኝ፡፡

እኔ እንደምገምተው ሰለሞን ደሬሳ ካነበበ የቤተሰቡን ብቻ ሳይሆን የጓደኛውን ሙሉ ታሪክ ነው ማንበብ የሚፈልገው፡፡ ስለዚህ "ሙሉ መጽሐፉን የምልክለትን ብልህት እፈጥራለሁ" ብዬት በእርሷ ዓይን ስብሐትን እንድታሳየኝ ጠየቅኳት፡፡

ረጅም ፀጥታ፣ ከውብና የመደነቅ ፈገግታ ጋር "ይኸውልህ፣ ስብሐት ብዙ ሰው ነው፡፡ ሲያስኘው ማንንም ከራሱ ነጥሎ የሚወደውን ማሳየት ይችላል፡፡ እኔ ግን እርሱን ከራሴ ነጥዬ ላሳይህ አልችልም፡፡ እሱ ምንጊዜም ከእኔ ጋር ነው፡፡ በወደደው መንገድ ተጓዘ፡፡ እንደ ሌሎቹ የሙያ ባልደረቦቹ ሁሉ ጧፍ ሆነ፡፡

"ልጆችን ኢየሱን አዲስ አበባ ሲመጣ ተገናኝታችሁ ተጨዋወቱ፡፡ አስተምሬ እዚህ ያደረስኩት አባትየው እንደሚፈልገው ነው የተቀረፀው፡፡ ቋንቋው እንግሊዝኛ ከመሆኑ በቀር ነብሱ እንዳለች ያበሻ ነች፡፡ 'ፖዘቲቭ' ነሽ ላልከኝ፣ እንዴት የስብሐት ሚስት ተኩኖ 'ኔጌቲቭ' መሆን ይቻላል?"

አብረን ሣቅን፡፡ በአገራችን፣ ባለፈው ታሪካችን፣ በአሁኑ የሕዝባችን ጥንካሬ ላይ አውግተን ስንደመድም ወይዘሮ እሌኒ መጥታ እንደሚበቃን ነገረችን፡፡

@Amharicbookstore



እኔም "ሐና፣ የመጀመሪያውን በመጨረሻ በመናገሬ ይቅርታ፣ ዛሬ ጠዋት ከጋሼ ስብሐት ጋር ቡና አብረን ጠጥተናል፡፡" ብዬ መልዕክቱን ነገርኳት፡፡ "እንኳን ደህና መጣሽ፡፡" ከቀጠርሺኝ በፈለገሽው ቦታና ጊዜ ለመገኘት ይመቸኛል በልልኝ ብሎኛል" አልኳት፡፡

"እኔ እኮ እነእሌኒን ፊልሙ እያልኳቸው ነበር፡፡ ነገ ቀጠርልኝ፡፡ በአሥር ሰዓት ግዮን ሆቴል" አለችኝ፡፡

"የሰዓት አቆጣጠሩ በእኛ ወይስ በምዕራቡ አቆጣጠር ነው?" አልኳት፡፡

"በእኛ ነው?"

እሌኒ በጨዋታችን መሐል ገብታ "4 ሰዓት ማለቷ ነው" ብላ አግባባችን፡፡ ሐና እንደምትኖርበት ዓለም ደንብ መሠረት 'በክሬዲት ካርድ' የሆቴሉን ሒሳብ ከፈለች፡፡ ወደ ቤተዘመዶቿ ስንቀላቀል የ83 ዓመት አዛውንት የሆኑትን እናቷን ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ወርቅነህን በድጋሚ እያስተዋወቀችኝ፣ "ያለውን ታሪካችንን መስማት የምትፈልግ ከሆነ እሷ በሰፊው ታጫውትሃለች" አለች፡፡ ልጎበኛቸው ብዘልቅ እናቷ ተቀብለው እንዲያስተናግዱኝ ነገረቻቸው፡፡ በተግባባን ስሜት ደርባባዋ ወይዘሮ ጭንቅላታቸውን ወዘወዙ፡፡

ወይዘሮ ኤልሣቤጥ የታዋቂው ዲፕሎማት የሐኪም ወርቅነህ ልጅ እንደሆኑ ሰምቻለሁ፡፡ ጋሼ ስብሐት ስለሐኪም ወርቅነህ ሲያጫውተኝ የሚያሳድጉት ለማዳ ነብር ነበራቸው፡፡ ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ከነብራቸው ጋር ሲጫወቱ እጃቸውን መላስ ጀመረ፡፡ ሐኪሙም መዳፋቸውን ሰጥተውት ከራሳቸው ጋር በሐሳብ ያወጋሉ፡፡ እጃቸውን አድምቶት ደማቸውን እየላሰ ነው፡፡ ነቅነቅ ብለው ቢቆጡ ዘሎ የሚያንቃቸው እንደሆነ ተገንዝበዋል፡፡ እጃቸውን ሳይሰበስቡ ከቤተኛው አንዱን ጠርተው ሽጉጥ እንዲያመጣላቸው አዘዙ፡፡ ነብሩ አሁንም ደማቸውን እየላሰ ነው፡፡ ሽጉጣቸውን በሌላኛው እጃቸው ተቀብለው አናቱ ላይ በመደገን ቃታ ሳቡ፡፡ ነብሩ ተዘረረ፡፡ ሐኪሙም እጃቸውን ማስታመም ጀመሩ፡፡

ሐኪም ወርቅነህ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ከልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ጋር በጄኔራል ናፒየር ጦር ታግተው ወደ እንግሊዝ በመጓዝ ተምረዋል፡፡ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዶክተር ለመሆን የበቁ መሆናቸውን አስታወስኩ፡፡ በርግጥም እኝህ ወይዘሮ ያለፈውን ጊዜ በመፈለግ እንደሚመሩኝ ተማመንኩ፡፡

'አለቤ ሾው' ላይ ስብሐትን እንዳዩትና በአመላለሱ መርካታቸውን አውግተን ለወዳጅነታችን መሠረት ጥለን ተሰነባበትን፡፡ ይሳካ አይሳካ አላውቅም፡፡ ሐና ለረጅም ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ሠርታለች፡፡ ባልሳሳት ለሩብ ክፍለ ዘመን ያህል (25

ዓመታት) ይህንን ልምዷን እንድትፅፈውና እንድታስነብበን አማክሬያት፤ እንደምትሞክር ቃል ገብታልኛለች። እንዲህ ዓይነቱ ትልቅ ዓለም አቀፍ ተቋም ገብተው ዓለማችንን ማገልገል ለሚፈልጉም ወጣቶች ማለፊያ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።

በ1993 ዓ.ም በመስከረም ወር በሰባተኛው ቀን አራት ሰዓት ገደማ "ሲደለር!" ሲል ጋሼ ጠራኝ። በዚህ ቅፅል ስም የሚጠራኝ እሱ ብቻ ነው። ጠዋት ቡና ጠርተነው አልመጣም። የበኩር ልጁ ዶክተር ኢያሱ ከአሜሪካ መጥቶ፣ ታናናሽ ወንድሞቹ በእግር በፈረስ ፈልገው ከልጁ ጋር አገናኝተውት፣ አቶ ዮሴፍ ቤት አምሽተው፣ እዚያው ማደሩን ሰምቻለሁ።

"የስ ሰር" ብዬ ወጣሁ።

ከኋላው ሁለት ወጣቶች ቆመዋል። ኢያሱን እንዳየሁት ነው ያወቅኩት። አወጣጡ እንደ ሰንበሌጥ ሙሽራ ያማረ መለሎ፣ ፀይም፣ ክብ ጢም ያጤመ ወጣት ነው። የመልኩን ገፅ ከአባቱ ቤተሰብ ሲከርጅ፣ አረዛዘሙ በእናቱ ዘሮች ነው። ኢያሱን ልብ ብዬ ሳስተውለው ዶክተር ተወልደ ብርሃንን በልጅነታቸው የማየት ስሜት ተሰማኝ።

"ይህ መርከበኛው ጓደኛዬ ነው" አለ ጋሼ ሰብሐት በእንግሊዘኛ ልጁን ሲያስተዋውቀን።

ስሞችንን ተለዋውጠናል። ከዘር ማንዘሩ ቋንቋ ለመግባባት እንኳን እንዲችልም አይችልም። ለሰላምታ ያህል ጥቂት የአማርኛ ቃላትን ይሞክራል። በእንግሊዘኛ ሐሳባችንን መለዋወጥ ጀመርን።

በቀጥታ ወደምፈልገው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጨዋታው እንዲያነጣጥር አደረግኩ። የእናቱን ደህንነት ከጠየቅኩት በኋላ "ለመጽሐፌ የሚሆኑ ፎቶዎች እንደምትልክልኝ ነግራኝ ነበር። አመጣህልኝ?" አልኩት።

እናቱ ይህንን ጉዳይ እንዳነሳችበት አስታውሶ፤ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ቤት አያቱ ወይዘሮ ኤልሣቤጥ ታመው፣ ወደ ደቡብ አፍሪካ ወስዶ ለማሳከም ድንገት እንደመጣ ነገረኝ።

አባቱ ቤት ገብተን ወጋችንን ቀጠልን። ስለ መጽሐፉ ጠየቀኝ። ባለፈው ታህሳስ ወር መጥቶ በነበረ ጊዜ አባቱ ስለእኔም ሆነ ስለሥራው እንዳወጋው አውቃለሁ። አሁንም አጠር አድርጌ ገልጬለት የአባቱን የሕይወት ታሪክ ለማንበብ አማርኛ ቋንቋን መማር እንዳለበት ስነግረው፤ ተሣሣቅን። መማሩ ግን የግድ እንደሆነ አወጋኝ። ከደቡብ አፍሪካ ጉዞ በኋላ ወደ ኒውዮርክ እንደ ተመለሰ ፎቶዎቹን እንደሚልክልኝ ገልጾልኝ የኢሜይል አድራሻውን ሰጠኝ።

@Amharicbookstore



ኢያሱ ረጋ ያለ ነው። ከመናገር ማድመጥን ያዘወትራል። ከሰው ጋር ሲጨባበጥ በትህትናና በሁለት እጁ ነው። ይህ ወጣት ዶክተር በለንደንና በአሜሪካ ውስጥ አድጓል ብሎ ለመገመት ተቸገርኩ።

ጋሼ ሰብሐት ከዓመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ልጁን ነብስ አውቆ ሲያገኘው ለእናቱ "ልጄን እንደፈለኩት ነው ያሳደግሽልኝና አመሰግንሻለሁ በልልኝ" ብሎ በራሱ በኢያሱ መላኩን ያወጋልኝን አስታወስኩ።

እናቱ ወይዘሮ ሐና "የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪ ከመሆኑ በቀር ነብሱ እንዳለች የሐበሻ ነች" ያለችው ትዝ አለኝ።

እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ለአባቱ ዛሬም ሦስት መጽሐፍ ይዞለት መጥቷል። አገላብጬ አየኋቸው።

"ጊዜ ስላልነበረኝ ከአሜሪካ መጻሕፍት ይገርልህ ልመጣ አልቻልኩም። እነዚህን ከሴት አያቴ ቤት መጻሕፍት ነው ያመጣሁልህ። እምትወዳቸውን አስቀርና ምርጫህ ያልሆነውን ሲመችህ መልስላት" አለ ኢያሱ አባቱን።

ብፌ ውስጥ በአንድ ወገን መጽሐፍ መደርደሪያ አድርገውታል። ጋሼ ሰብሐት ተነስቶ ብፌውን ከፈተና The Sign and the Seal መጽሐፍን አንስቶ አሳየው። "ገዝተህ አንብበው" አለዉ ተቀብሎ አስቀመጠው። "ለምን አልሰጠውም?" ስል አብሰለሰልኩ። መጽሐፉን ከልብ እንደወደደው አውቃለሁ። ልጁም በሚኖርበት ዓለም በቀላሉ ያገኘዋል ብሎ እንዳሰበ ገመትኩ።

ይህንን መጽሐፍ መገዛት እንዳለበት ወሰንኩ። እንደመታደል በዚያን ሰሞን ከጓደኞችን ከሙሴ ኃይሉ ጋር ተቀጣጥረን ስናወጋ "በሚቀጥለው ወር የጋሼን 64ኛ ዓመት በዓሉን ስለምናከብር ቤታችን ብቅ ብለህ ቡና አብረን እንጠጣ" አልኩት።

"እኔም ያቅሚቱን ያህል አንድ ነገር ባደርግ ደስ ይለኛል፤ አንተ ደግሞ የቅርብ ሰው ስለሆንክ ፍላጎቱን አጥናና ደስ የሚለውን ነገር አይተህ ንገረኝ" አለኝ።

የመስለል ያህል ጋሼን ለአንድ ወር ተከታተልኩት። ልደቱን የምናስብበት ሚያዝያ 27 ቀን ተቃረበ። አሁንም ከግራሀም ሀንኮክ መጽሐፍ ጋር ነው። ቡና ላይ "ጋሼ አንድ ወዳጃችን ልደትህን ምክንያት በማድረግ አንድ ነገር ማድረግ አስቦ The Sign and the Seal እንዲገዛልህ ነግሬዋለሁ" ስለው

"ይህ ሰው ፀደቀ በለኝ" አለ።

መጽሐፉ ተበረከተለት። ጋሼ ጭምረቅ ብቻ አይደለም፣ እፎይታ ጋዜጣ ላይ ይህንኑ መጽሐፍ ምንጭ አድርጎ የጻፋቸውን አምስት

ምዕራፍ ያለውን ጽሑፍ ሰብስቦ ለሙሴ እንዲያነበው ሰጠው፡፡ ጋ
ስብሐት የፃፈውን ጽሑፍ ሲሰበስብ ሳይ ይህ የመጀመሪያዬ ነው፡፡
ይህንን እያብሰለሰልኩ ወደ ኢያሱ ተመለስኩ፡፡ "እድለኛ ነህ
ምክንያቱም ሴት አያትህ እንግሊዘኛውን አቀላጥፈው ስለሚናገ
ሐሳብ ለመለዋወጥ አትቸገርም" አልኩት፡፡

"ባይገርምህ ችሎታዋም የተራው እንግሊዘኛ ተናጋሪ ቋንቋ ሳይሆ
የአሪስቶክራሲው ነው" አለንና ተነሳ፡፡

ቤት ያፈራውን እንድንቃመስ አባትና ልጁን ጋበዝኩ፡፡ ኢያሱ
ከአያቱ ጋር ቀጠሮ እንዳለው ነግሮን ተሰነባበትን፡፡

ሐሙስ ጥቅምት 2 ቀን 1993 ዓ.ም ዶክተር ተወልደ ብርሃ
አማራጭ የኖቤል ሽልማት ተሸላሚ በመሆኑ ለጋዜጣ ሥራ
ላነጋግረው ወደ ቢሮው የዘለቅኩበት ዕለት ነው፡፡ ከአንድ ሰዓት በላ
በጄኔቲክ ኢንጂነሪንግና በማኅበረሰብ የባለቤትነት መብት ዙሪ
ያደረጉትን አስተዋፅኦና እንቅስቃሴ ገልጸልኝ ስንሰነባበት "ዘነበ
አንድ አሳዛኝ ነገር ደርሷል፤ ወይዘሮ ኤልሣቤጥ አርፈው ዛሬ የቀብ
ሥነ ሥርዓታቸው ይፈፀማልና ለቅሶ እንዲደርስ ለስብሐት ንገረው
አለኝ፡፡

ደነገጥኩ፡፡ ይህ መጽሐፍ ታትሞ ከእጁ እንደወጣ "ያለፈውን
ታሪክ ፍለጋ" በሚል ርዕስ ለምጽፈው መጽሐፍ እኝህ ወይዘሮ
እንደሚረዱን እርግጠኛ ነበር፡፡ ወዳጅነቴም መልካም በሆነ መልክ
ተጀምሮ ነበር፡፡ ሲጋሼም በወይዘሮ ኤልሳቤጥ ላይ ወግ አንስቼበት
ለወጣት ደራሲ በጣም ለስፈላጊ ሰው ናቸው፡፡ ወዳጅነትህን
ቀፅልበት፡፡ እንዲያውም የመጀመሪያውን ጉብኝት አብሬህ
እሔዳለሁ፡፡" ብሎኝ ነበር፡፡

ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ተምረዋል፣ ከ80 ዓመት በላይ ኖረዋል፡፡
ተንብበዋል፡፡ በሳቸው የዕድሜ ደረጃ የራሳቸው ቤተ መጻሕፍት ያለው
ሰው ሳውቅ እኝህ ወይዘሮ የመጀመሪያዬ ናቸው፡፡ ዜና ረፍታቸው
በጣም አሳዘነኝ፡፡ አሁን በወይዘሮ ኤልሣቤጥ ዜና ዕረፍት ሐዘኔን
ቀሰቀሰው እንጂ ስንቱን አይደል ኢትዮጵያ ጭጭ ምጭጭ እንዳለ
የምትሸኘው? እንደቆዘምኩ እያሌዎቹን እያብሰለሰልኩ ወደ ቢሮዬ
አዘገምኩ፡፡

አርብ ጠዋት ከጋሼ ስብሐት ጋር ቁርስ አብረን ተቋደስን፡፡
ቡናችንን ጠጥተን ወደ ሥራ ለመሄድ ስንነሣ "ጋሼ መጥፎ ዜና
ልነግርህ ነው ወይዘሮ ኤልሣቤጥ አርፈው ትናንት የቀብር ሥነ
ሥርዓታቸው ተፈጽሟል፡፡ ባለቤትህም ሆነች ልጅህ አዲስ አበባ
መጥተዋል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ስለዚህ ለቅሶ መድረስ አለብህ"
አልኩት፡፡



ከረጂም ፀጥታ በኋላ "እሺ" አለኝ፡፡ ቅዳሜ ጠዋት ቡና እየጠጣን
ለቅሶ መድረሱን ጠየቅኩት፡፡

"አልሄድኩም፡፡"

"ለምን?" ብዬ በጥያቄ ላፋጥጠው አልፈለግሁም፡፡ ወይዘሮ
ኢልሣቤጥን እንደሚወዳቸው፣ እሳቸውም ለእርሱ ያላቸውን ጥልቅ
ፍቅር አጫውቶኛል፡፡ ይህንን እያብሰለሰልኩ "አንድ ቀን ዓምድህ
ላይ ተወዳጅዋን ወይዘሮ ታስነብበናለህ?" አልኩት፡፡

"አልጽፋቸውም" አለኝ በእርጋታ፡፡

"ለምን?"

"ከወይዘሮ ኤልሣቤጥ ጋር ብዙ ውብና ቆንጆ ትዝትዎች አሉኝ፡፡
እነዚህ ትዝታዎቼ አብረውኝ እንዲኖሩ ፈልጌ ነው ለቅሶ መድረሱን
የተውኩት፡፡ ሐዘንተኞች መሐል ሆኜ ስለ ሕመማቸውና የቀብር ሥነ
ሥርዓታቸው የሚያወሣውን ምዕራፍ መስማት አልፈልግም፡፡ እኔ
እስካለሁ ጊዜ ድረስ ወይዘሮ ኤልሣቤጥ እኔ ውስጥ ሕያው ናቸው፡፡
ወደ አንባቢዎቼ ስንመጣ፣ የማካፍላቸው ዕውቀትም ጨዋታም
የመኖሩን ያክል የማላጋራቸውም ይኖረኛል፡፡ እሳቸው የብቻዬ
ናቸው" አለኝ፡፡

ከዚህ በኋላ ከጋሼ ጋር በዚህ ርዕስ ብዙ መሄድ አንችልም፡፡
በእንዲህ ዓይነት ስሜት ብቻውን መሆን ነው የሚፈልገው፡፡ ከሰው
ጋር ቢሆንም ዝምታውን ፈቅጄለት ወደ ሥራ አዘገምኩ፡፡

አባባሉ ሆደ̄ን በላዋ፡፡ እንባዬ በዓይኔ ግጥም አለ፡፡ እያዘገምኩ
አብሰለስላለሁ፡፡ 'አካካዩ' ለሚለው ምዕራፍ ብላታ ዴሬሣ አመንቴን
መቼ እንዳረፉ ጠይቄው ሲመልስልኝ "እኔ እንጃ እኔ ውስጥ ያሉት
ብላታ ሕያው ናቸው" ብሎኛል፡፡

ጨለማው ያዝ ሲያደርግ ነው ቤት የገባሁት፡፡ ጋሼም ረፈድ
አድርጎ 2፡45 ገደማ መጣና አጠገቤ ተቀመጠ "የዕለቱ ውሎህ
እንዴት ነበር?" አልኩት የጨዋታ በር ለመቅደድ ያህል፡፡

"ለቅሶ ቤት ውዬ መምጣቴ ነው" አለኝ ጋሼ፡፡

'ጎሽ ለልጁ ስትል ተወጋች' አልኩ በልቤ፡፡ ልጁና ባለቤቱ
መምጣታቸውን ሰምቻለሁ፡፡ ለእነርሱ ሲል ከሚጠላው እውነታ ጋር
መጋፈጡን ተገነዘብኩ፡፡ ሊሰማው የማይፈልገውን የመጨረሻውን ምዕ
ራፍ ሰማ "ልጅህንና ባለቤትህን አገኘሃቸው?"

"አዎን!"

ከዚህ በኋላ ጥያቄ መጠየቅ የለበትም፡፡ በእንዲህ አይነት ወቅት
ስሜቱን ከመንካትና ከማስቆጣት በቀር ቅንም የሚረባ ነገር
እንደማያወጋ ከልምድ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከጥቂት ፀጥታ በኋላ "ራት
በልተሃል?" አልኩት፡፡

@Amharicbookstore

"አዎን፡፡ አሁን የሚያስፈልገኝ ለጥ ብዬ እንቅልፌን መለጠጥ ብቻ ነው" አለና በርሳውን አንግና ወደ መኖሪያ ቤቱ አዘገመ፡፡

***

## ፲፬

## ባለመትረየሱ

ደረጀና ሐና ሁልጊዜ አብረው ናቸው፡ ልብአርግ፡፡ እና እኛን የሚጠብቁን እነሱ ናቸው፡፡ መኖሪያ ቤታችን ከከተማ ዳር ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ዘነበ ወርቅ አካባቢ ነበር የምንኖረው፡፡ እንግዲህ ዘመኑን ስንመዝነው ጃንሆይ አርጅተዋል፡፡ መውደቃቸው አይቀርም፡፡ እና ምንም ነገር አላስተካከሉም፡፡ እናውቃለን ደግሞ ሽኩቻ እንደሚኖር፡፡ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ራሳችንን መጠበቂያ ያሻናል የሚል ሐሳብ መጣ፡፡

@Amharicbookstore

ገበሬውም ሆነ በከተማው በተለያዩ መልኩ መጥቶ የተከማቸው ሥራ አጥ ለወረራ ወደ አዲስ አበባ ይገባል፡፡ በወቅቱ በደምም መስከር አለ፡፡ ስለዚህ ራስን መጠበቂያ ያስፈልገናል አሉኝ፡፡ እና መትረየስ ይገዛ ተባለ፡፡ መትረየስ ከድሬዳዋ ነው ልናመጣ የምንችለው፡፡ ኮንትሮባንድ ከእዚያ ነው የሚገኘው፡፡ እኔ ተመረጥኩኝ፡፡ ከድሬዳዋ መትረየስ ገዝቼ እንዳመጣ ሽኙኝ፡፡ ባቡር ጣቢያ ድረስ ተሸኘሁ፡፡ በባቡር ተሳፍሬ ድሬዳዋ ገባሁ፡፡

ሆቴል ያዝሁ፡፡ ከተማዋ ውስጥ ተዘዋወርኩ፡፡ አወጣሁ አወረድኩና በጆብሉ ነጋዴ በኩል ሰው ለመተዋወቅ ወሰንኩኝ፡፡ ጠራሁ አንድ ትንሽ ልጅ፡፡

«አይ ሲጋራ ሳይሆን ሌላ የሚገዛ ነገር እፈልጋለሁ ሰው አገናኘኝ» አልኩት፡፡ ሐሳቡ ገብቷታል፡፡ ሰተት አድርጎ ወሰደኝ፡፡

የወሰደኝ ሰውዬ ጋር ተዋወቅን፡፡ ስንጫዋወት ሁለታችንም የዓድዋ ልጆች ሆንን፡፡ «ቡና ልጋብዝህ» አለኝ፡፡ እሺ አልኩና ስንገባበዝ የመጣሁበትን ጉዳይ ነገርኩት፡፡ በአጭር ሰዓት ተግባብተን ግልጽ ሆንኩለት፡፡ አንዳንድ ቀን ወዲያውኑ ከከበህ ይገጥማል፡፡ መትረየስ መፈለጌን በግልጽ አዋየሁት፡፡

«እሺ» አለኝ፡፡ በጣም ስለተግባባን «የምሸጥበት 900 ብር ነበር፡፡ አንተን ግን ስለወደድኩህ በገዛሁበት 700 ብር እሰጥሃለሁ» አለኝ፡፡

«እሺ» ብዬ በደስታ ተስማማሁ፡፡



ከዚያ ስናወራ የበለጠ አወቅኩት፡፡ ለጫወታ ያህል «እንዴት ነው ኑሮ በድሬዳዋ አንተስ እንዴት ትኖራለህ?» አልኩት፡፡

«ይኸውልህ የጭነት መኪና አለኝ፡፡ በእሱ ለጦር ሠራዊት ቀለበኛ የሚያስፈልግ መድኃኒት ጭኜ እየነዳሁ ሰተት ብዬ እሰበክብት እገባለሁ፡፡ የማንኛውም ሠራዊት ቢሆን ይፈልገኛል፡፡ ሽጩለት እመለሳለሁ፡፡ አንድ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሠራዊት ሽጩ ልመለስ ስል ተኩስ ተከፈተ፡፡ ገባሁ ወደ ቁልቁለት ተደበቅኩ፡፡ ተኩሱ ቀጠለ፡፡ አልሸናነፍ እያሉ፡፡ ሦስት ቀን እዚያ ቆየሁ፡፡ አይ አልኩና በሬዲዮ ድረሱልኝ ብዬ ለሸሪኮቼ ተናገርኩ፡፡ ደረሱልኝ፡፡ በሾፌር ነው የምሄደው፡፡ ከማዶ ተተኮሰ፡፡ ሾፌሩ በጥይት ተመትቶ ሞተ፡፡ ዞር አደረግኩና መንዳቴን ቀጠልኩ» አለኝ፡፡

«የሚቀጥለው ጥይት አንተን ቢመታህስ?» ስለው

«ግልግል ነዋ» አለኝ፡፡

እውነቱን ነው፡፡ መዘነጡም አይደለም፡፡ ሥራው ሁልጊዜም የሚጫወተው ከአደጋ ጋር ነው፡፡ «ግልግል ነዋ» ሲል የምሩን ነበር፡፡

ወደ እኔ ስንመለስ መትረየሱን የምረከብበትን ቦታ ነገረኝ፡፡ «አዲስ አበባ ተመልሰህ ትሄዳለህ፡፡ መርካቶ እንዲህ እንዲህ ቦታ ትሄድና ሐጂ እገሌን በመደብራቸው ውስጥ ታገኛለህ፡፡ አሁን ስሙን ረሳሁት እገሌ ነው የላከኝ ትላቸዋለህ፡፡ መትረየስህን እዚያ ትረከባለህ» አለኝ፡፡

በጣም ገርሞኝ «እንዴት ሆኖ?» አልኩ በመደነቅ «እስኪ ከዚህ እስከዚያ እንዴት እንደምታደርሱት ንገረኝ» አልኩት፡፡

ግልፅ ነው «ይኸውልህ ምድር ባቡር ውስጥ ያሉ ፖሊሶቹ ሁሉ የእኛ ደመወዝተኞች ናቸው፡፡ በመተላለፊያ ኬላዎቹ ላይ የሚገኙ ፖሊሶች ሁሉ በጫነው ዕቃ ላይ ያደረግነውን ምልክት ያውቁታል፡፡ እሱን መፈተሽ የለባቸውም፡፡ ያ ምልክት ከሌለበት ግን ይፈትሻል፡፡ የእኛ በእንዲህ መልኩ ሳይፈተሽ ሰተት ብሎ አዲስ አበባ ይገባል» አለኝ፡፡

ልቦለድ የሚነብ ነው የመሰለኝ፡፡ ተሰነባበትን፡፡ አዲስ አበባ ደርሼ በተሰጠኝ ምልክት መሠረት መርካቶ መጣሁ፡፡ ሐጂን አገኘኋቸው፡፡ የወዳጃቸውን መልዕክት መያዜን ስናገር ተቀብለው አስተናገዱኝ፡፡ ክፍያውንም አጠናቅቄ መትረየሴን ተረክቤ ለላኩኝ ቤተሰቦቼ አስረከብኩኝ፡፡

***

# ፲፫

## ነጂና ተነጂ

ሰለሞን ዴሬሣ አሜሪካ ሲሄድ ከወንድሞቹ ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ በእርሱ ምትክ እንዲያዩኝ አደራ አላቸው፡፡ በርግጥም ልክ እንደ ሰለሞን አቀረቡኝ፡፡ እንደ ወንድማማች እንተያይ ጀመር፡፡

በዚህ ወቅት ነው ደረጀ ዴሬሣ በእኔ ሕይወት ውስጥ የነገው፡፡ ቁመናውን ላሳይህ፡፡ መልኩ በጣም የሰጠ፣ ጭንቅላታም፣ ፀጉሩ ትንሽ ሸሸት ያለ፡፡ ፈገግታው በጣም የሚያምር፡፡ ጥርሶቹ ከዝኼር የበለጠ አዋቂ በጥበብና በጥንቃቄ የቀረጻቸው ነው የሚመስሉት፡፡ ረጅምም ቀጣም ነው፡፡ እኔ ደግሞ እንደ እዚያ ቆንጆ አድርጎ ፈጥሮት ቀጣም አርጎ አከሰረው፣ እያልኩ እግዜሩን እታዘበው ነበር፡፡ በእኔ ቤት ሴት ልጅ ነች ቀጣም ስትሆን የምትወደድ፡፡ ብዙ ዓመታት ካለፉ በኋላ የአሜሪካኖችን ሪደርስ ዳይጀስት መጽሔት ሳነብ ሴቶች የሚወዱትን የወንዶችን ቁመና ዘረዘሩልኝ፡፡

እየሣቀ ቀጠለ፡፡ "የፊልም ተዋናዩ በርትላንካስተርን የሚያክሉ የፔ እጅግ መልከ መልካም ግዙፎችን አራተኛና አምስተኛ ደረጃ ላይ ነው ያስፈሩዋቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሚወደደው ግንባረ በራ ነው፡፡ ይህ ደረጀ ሲፈጠር ተሰጥቶታል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ቀጣም ወፃድ ሲል በእራሴ ላይ ሣቅኩ፡፡ ያ የደረጀ ቂጥ ለካ ትልቅ እሴት ኖሯል! ደረጀም ሴት በጣም በጣም ስለሚወድ ተገናኝተዋል፡፡

ደረጀ ማለት ትንሹ ይልማ ልትለው ትችላለህ፡፡ እሳቸው በፖለቲካ፣ ደረጀ ደግሞ በቢዝነስ ዓለም ለእኔ የተሣካላቸው ነበሩ፡፡ በአስተሳሰባቸውም ሁለቱ የሚመሳሰሉበት ባሕሪ አላቸው፡፡ ተቃራኒያቸው ሳይገምታቸው እነርሱ አስቀድመው በመንቃት አንድ ርምጃ የመቅደም ልዩ ኃይል አላቸው፡፡ የቼዝ ጨዋታ ምስጢሩ የተቃራኒህን ርምጃ አጢነህ በሐሳብ አንድ ርምጃ ቀድመኸው መሔድ ነው፡፡ እነርሱም ሁሌም እንደቼዝ ተጫዋች በንቃት አካባቢያቸውን እያስተዋሉ ነው የሚኀዙትና ተወዳዳሪያቸውን የሚቀድሙት፡፡

ደረጀ ተቃራኒዎቹንም ሆነ ወዳጆቹን አቅርቦ የሚያጫዋውታቸው ጊዜ ነበረው፡፡ በተወሰነ ጊዜ አንድ ቀን ቤቱ ፓርቲ አዘጋጅቶ

@Amharicbookstore



ይጠራቸዋል፡፡ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ይደንሳል፡፡ እንደ፡ አስታውሳለሁ የባሕል ዘፈን ተጫዋቹን ባህሩ ቃኜን ቤቱ ጋብዞት ሌሊቱን ሙሉ ሲያጫውተን አድሯል፡፡ ባህሩ ጥሩ ድምፅ፣ የግጥም ምንጭ የሆነ ሕሊና ተፈጥሮ ቸራዋለች፡፡ ስማችንን ብቻ ነግረነው በግጥሙ እየተቀኘልን ሲያስደስተን አምሽቷል፡፡

ደረጀ በተፈጥሮው ለገንዘብ ግድ የለውም፡፡ ገንዘብን የሚፈልገው የልቡን ለማድረስ ነው፡፡ ገንዘብን አያመልክም፡፡ አይቼዋለሁ ዝም ብሎ ሲበትን፡፡ ገንዘብ የሚወድ ሰው እንደሱ አያደርግም፡፡ ለደረጀ ገንዘብ መረማመጃው ነው፡፡

ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጥሬ እየሠራሁ ነበር፡፡ ከበዓሉ ግርማ ጋር መነን መጽሔትን እናዘጋጅለን፡፡ ታድያ ደረጀ መጣና "ቢዝነስ እናቋቁም" አይለኝ መሰለህ?

"አውቃለሁ፤ አንተ ለገንዘብ ግድ እንደሌለህ፡፡ ባለቤትህ ግን ሙሉ ጤና የላትም፡፡ የሐናን ደህንነት ጠብቀህ ለመኖር ሀብት ያስፈልግሃል፡፡ ስለዚህ ከእኔ ጋር አንድ ኩባንያ መስርተን አብረን እንሥራ፡፡ ቢዝነሱን ለእኔ ተወው፡፡ አንተ የራስህን የፈጠራ ሥራ እየሠራህ እኔን ባለህ ተሰጥኦ ታግዘኛለህ"አለኝ፡፡

"ተስማማሁ፡፡" አለና በሐሳብ ተውጦ ጢሙን ሲያፍተለትል ቆይቶ "ትክክል ነው፡፡ የልብ ሕመምተኛ ሚስት አግብተህ ሀብት ሳይኖርህ እንዴት መኖር ይቻላል? በዚህ መስመር ደረጀ ዴሬሣ እንደፈለገ እየነዳኝ ነው የኖርኩት፡፡ እኔን በሕይወቴ ማንም ነድቶኝ አያውቅም፡፡ ደረጀ ግን እንደፈለገ ነድቶኛል፡፡ ይህንንም ስልህ አንዳንድ ነጂ አለ፣ የራሱን ጥቅም ብቻ ለማስከበር የሚጋልብህ፡፡ ደረጀ ለእኔና ለሐና ደህንነት ሲል ነው የሚነዳኝ፡፡

ዓለም የሕዝብ ግንኙነት ብለን ሥራ ጀመርን፡፡ በወቅቱ ለሥራ ማስኬጃ ገንዘብ የለንም፡፡ እንዲያም ሆኖ ምንም ለማግኘት መጨነቅ የለብንም፡፡ የደረጀ ጭንቅላት አለና! ደረጀ ሲያስተውል አቶ አቢን ተመለከተ፡፡ አቶ አቢ ግማሽ ግሪክ ሲሆኑ ብሔራዊ ሎተሪን በአገራችን የጀመሩ ሰው ናቸው፡፡ አሁን የሎተሪ አርማ የሆነችው እንሥራ አዝላ የምትታየውም ሰጎን የእሣቸው ፈጠራ ነች፡፡ በጣም 'brilliant' ሰው ሲሆኑ፣ በተጨማሪ የይልማ ዴሬሣ ጭፍራ ናቸው፡፡ ድርጅታቸው ብሔራዊ ሎተሪ የገንዘብ ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ነው፡፡

ደረጀ በተፈጥሮው ለሚወደው ሰው ግልጽ ነው፡፡ ከሌላው አህዛብ ጋር ግን በብልሀት ነው የሚኀዘው፡፡ ደረጀ ዴሬሣና አቶ ይልማ ዴሬሣ በአባቶቻቸው ስመ ሞክሼነት እንጂ የአንድ አባት ልጆች አይደሉም፡፡ አቶ ይልማ ለደረጀ አጎቱ ናቸው፡፡ የእናቱ የእማማ የሺመቤት ባል የአባታቸው ሞክሼ ናቸው፡፡ ደረጀም እኔ ደረጀ

ደሬማ ነኝ ሲል የሚሰሙ ሁሉ የይልማ ወንድም ነው የሚሉት፡፡ እሱም ተሳስታችኋል አይላቸውም፡፡

አቶ ኢብን ተጠጋቸው፡፡ እንዴ አስታውሳለሁ እኔንና ሌሎችንም በዚህ ሙያ ላይ የተሠማራነውን ሰበሰበንና አቶ ኢብ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉን ጋበዛቸው፡፡ እሳቸውም በደስታ ይነግሩን ጀመር፡፡ የብሔራዊ ሎተሪንም መጽሔት እንድናዘጋጀው ሰጡን፡፡ እኛ ምንም የጨመርነው ነገር የለም፡፡ ቃላት ነው ያስተካከልነው፡፡ ደረጀ በምስጢር እሳቸውን የድርጅታችን ሲሶ ሸሪክ አደረጋቸው፡፡ እሳቸው በቂ ገንዘብ ሰጥተውን ከዜሮ ተነሣን፡፡

በዚያን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ሥራ ስትጀምር 15ሺ ብር ባንክ ማስያዝ አለብህ፡፡ ያንን ደረጀ በደንብ አሳምኗቸው ገንዘቡን ተቀበላቸው፡፡ ሥራውን ከጀመርን በኋላ በማንኛውም ጊዜ አውጥተን እንደምንመልስላቸው ቃል ገባንላቸው፡፡

በዚህ መሐል ጃንሆይ ሹም ሽር አደረጉና አቶ ይልማ ደሬማን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር አደረጓቸው፡፡ ይኼኔ ደረጀ ለአቶ ኢብ እንደቀድሞው አያስፈልጋቸውም፡፡ ስለዚህ አንድ ቀን አቶ ኢብ እንዲህ አሉን፡፡ "እናንተ ሥራችሁን ቀጥሉ፡፡ እኔ ዕድሜዬ እየገፋ ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘቤን መልሳችሁልኝ እንለያይ"

ደረጀ አስማተኛው ያን ዕለት ያላቸው ትዝ ይለኛል፡፡ አባባሉን ስሰማ ለካ ደረጀን አላውቀውም ነው ያልኩት፡፡ እንዲህ አላቸው፣ "በጭራሽ! አቶ ኢብ ያስፈልጉናል፡፡ እንዴትስ ይለዩናል እዚህ ካደረሱን በኋላ?" እምቢ ሊሉ እንዳይችሉ አርጎ ለመናቸው፡፡ ስምንት ፐርሰንት ሽርካችን ሆነው እንዲቆዩና በፍፁም አለመለየታችንን ወዳጆቻችንም ሆነ ጠላቶቻችን እንዲያውቁ መሆን እንዳለበት ነገራቸውና ተስማሙ፡፡

አያስፈልጉንም፡፡ የደረጀ እልህ ነው፡፡ አቶ ይልማ ከገንዘብ ሚኒስቴር ሲነሱ ጊዜ አቶ ኢብ እኛን እንደ አላስፈላጊ ሸክም ሊያራግፉን ነውኮ! የደረጀ ስሜት ግን እኛ በትንሽ ክርም ቢሆን እንቆጣጠራቸዋለን ነው፡፡ አየኸው?

አሁን ሳስታውስ እዳችንን ከፍለን ጨርሰን ምንም እዳ ሳይኖርብን እርምጃችን አድጓል፡፡ ድርጅታችንም በሁለት እግሩ ቆሟል፡፡" ጋሼ የጨዋታችን ውል ጠፍቶት ጥቂት ግር አለውና "እ? ከደረጀ ጋር ነን? ፖሊቲከኛ፣ ነጋዴ፣ ሸሌ እርስ በርስ እንደሚቀናና ሁሉ፣ የቢዝነስ ሰውም እንደዚያው ነው፡፡ ደረጀ ግን እርሱ በፍፁም የቢዝነስ ሰው ያልሆነ ያህል ሌሎችን ሲያደንቅ እሰማዋለሁ፡፡ እንዴ ምን አለኝ መሰለህ? "ተመልከት ይህንን ገብረየስ ቤኛን፡፡ እርሱን የሚያክል የቢዝነስ ሰው የትም ብትሄድ አታገኝም፡፡ እየው

@Amharicbookstore



ይቀጥላል፡፡ ማንም ምንም የማያቆመው ሰው ሆኖ ታገኘዋለህ" አለኝ፡፡ ይሄ በጃንሆይ ጊዜ ነበር፡፡ ቀጠለ፡፡ ደርጉም መጣ፡፡ ገብረየስን ምንም አላቆመውም፡፡ በአሁኑም ዘመን እንደቀጠለ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አማልጋሜትድ የሚባል የድርጅት ስም ሰምተህ ታውቃለህ? በቅሎ ቤት አካባቢ መሰለኝ፣ ቢሮው፡፡ የሱ ድርጅት ባለቤት ነው፡፡ ገብረየስ ቤኛ፡፡

የእኔና የደረጀ ተፈጥሮ ተቃራኒ ነው፡፡ ለምሳሌ እኔ አንድን መንገድ ደጋግሜ ካላየሁት ይጠፋኛል፡፡ አንድ ማታ ከደረጀ ጋር ፓርቲ ተጠርተን እንሄዳለን፡፡ የምንሄድበት መንገድ ጉራንጉር ነው፡፡ መጠማዘዝ ይበዛበታል፡፡ በዚህ መንገድ ስንሄድ እንዴት አባቱን ከዚህ ውስጥ ሊወጣ ይሆን? አሰብኩና "አንተ፣ እንዴት አድርገህ ልትመለስ ነው?" አልኩት፡፡ እንዲህ አለኝ፡፡ "የእኔ አንጎል የሚሠራው እንደ ቴፕሪከርደር ነው፡፡ አሁን ወደፊት እየሄድን ያለፍነውን መንገድ ጭንቅላቴ rewind እያረገው እንዳለሁ፡፡ እንዳመጣጣችን ሳልደናገር እንመለሳለን" አለኝ፡፡ አምኜዋለሁ፡፡ ከእንደ እኔ ዓይነት ሰው ጋር ምን ያህል እንደሚራራቅ ነው የሚያሣየው፡፡

ከሐና ጋር ደግሞ አንድ ዓይነት ተሰጥኦ አላቸው፡፡ በሌላ ቀን ከደረጀ ጋር ፓርቲ ተጠርተን ሄድን፡፡ ከተጠራንበት ቤት ስንደርስ ቤቱ በሰዎች ተሞልቷል፡፡ ደረጀ ወደሌላ አቅጣጫ እየተመለከተ በሹክሹክታ "እገሌንና እገሊትን እያቸው፣ ተኳርፈዋል" አለኝ፡፡ የተባሉት ሰዎች በጣም ተራርቀው ነው የተቀመጡት፡፡ በኋላ፣ ጊዜ እያለፈ ስከታተላቸው በርግጥም ተኳርፈዋል፡፡ በዚያ ውክቢያ መካከል፣ በዚያ ርቀት ሰው አይተህ ሁኔታቸውን መረዳት የሚደንቅ ነው፡፡

ልክ እንደ ደረጀ ሐናም ቀድማ ታያለች፡፡ በፍቅረኝነት ዘመናችን ለንደን ውስጥ መጀመሪያ ምቹ ሆቴል ነበር ያረፍኩት፡፡ እዚያ ዋጋው ለተማሪ በጣም ውድ ነው፡፡ የሐና አባት ባለፀጋ ቢሆኑም በተማሪ ደረጃ እንድትተዳደር የሚያበቃ ተቆራጭ ብቻ ነው የሚያደርጉላት፤ በእምነታቸው ሕይወቱንም እንድትለምድ ጭምር ነው፡፡ የገንዘብ ችግሬን ለሆቴሉ አስተዳደር ነግሬ ቀለል ባለ ዋጋ ሆቴል የምከራይበትን እንዲጠቁሙኝ ጠየቅኋቸው፡፡ የዚሁ ሆቴል ቅርንጫፍ የሆነ አንድ አካባቢ እንዳለ ጠቆሙኝ፡፡ እኔ ቀድሜ ሄጄ መኝታ ቤት ተከራይቼ ጠበቅኳት፡፡ የተቋበለኝ የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ መልኩ ልክ የታወቀው የልቦለድ የወንጀል መርማሪ ሼርሎክ ሆምዝን (Sherlock Holmes) ነው የሚመስለው፡፡ ተግባብተን ሼርሎክ ሆምዝ

እንደሚመስል ነገርኩት፡፡ ብዙ ሰው እንደ እኔ እንደሚለው አጫወተኝ፡፡

"ባይገርምህ ስሜም ዋትሰን ነው፡፤" አለኝ፡፡

"አ! ዋትሰን፡፡ ዶክተር ዋትሰን የሼርሎክ ሆምዝ የቅርብ ጓደኛና ረዳት መሆኑን ታውቃለህ?"

"ይኸውልህ፣ ለዚህ ሰውዬ የልጃገረድ ጓደኛ አለችኝ" አልኩት፡፡

"አይ እንግዲህ እዚህ ሴት ይዞ መምጣት ክልክል ነው፡፡ ግን እኔ ሳላይህ ይዘህ መግባት ትችላለህ፡፡ እኔም እያየሁህ አላይህም" አለኝ፡፡ ተሳሳቅን፡፡

ሐና መጣችና ገና ከሩቅ እንዳየችው በእንግሊዝኛ "የንን ሰው አልወደውም" አለቺኝ፡፡

"ምን ማለትሽ ነው?" አልኳት፡፡

"አንተን የሚያይበት አስተያየት ደስ አላለኝም" አለችኝ፡፡

"ዝም ብለሽ ነው" ብዬአት ባለውለታችን መሆኑን እያጫወትኳት ገባን፡፡ ተመላልሳ እዚያ ሆቴል ትመጣለች፡፡ ሰውዬው አይቶ እንዳላየ ያሳልፈናል፡፡ ጥሩ ጊዜ አሳለፍን፡፡ ከሥራ አስኪያጁም ጋር ይበልጥ ተቀራረብን፡፡ የኔ ወጣት ነኝ፡፡ ሁሉን ነገር የማውቅ ከፍተኛ ጉጉት አለኝ፡፡ ታዲያ ሚስተር ዋትሰን "እንዲያው ፈገግታህ በጣም ደስ ይለኛል" አለኝ፡፡ ገባኝ፡፡ የሐና ዕይታ ተገለፀልኝ፡፡ የፍቅር ጨዋታን ከተቃራኒ ፆታ ጋር ሳይሆን ከተመሳሳዩ ጋር መደሰት የሚፈልግ ሰው ነው፡፡ በጨዋ ቋንቋ ልተባበረው እንደማልችል ነገርኩትና በሁኔታው እየዘነኩ ተለያየን፡፡

ደረጀ ትምህርቱ ከሁለተኛ ደረጃ የዘለለ አይመስለኝም፡፡ ግን በዚያን ወቅት እዚህ ደረጃም ድረስ መማሩ ሥራ ያስገኛል፡፡ የእርሱ ግን ከዚያም በላይ በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡

ልነግርህ ነው፡፡ ሚቼልኮትስ ኩባንያ ውስጥ ሥራ ተቀጥሮ ገባ፡፡ ትዝ ይለኛል ቢሮው በመተላለፊያ ኮሪደር ላይ ነበረች፡፡ በወቅቱ የዚህ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ኦቱል ይባላል፡፡ ደረጀም በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍጥነት ማደጉን አስታውሳለሁ እዚህ ድረስ ብርቱ ሰው ነው ደረጀ ማለት፡፡ 'ኮምፕሌክስ' የሌለበት፣ በራሱ የሚተማመን ሰው ነበር::

አንድ ጊዜ ሰለሞን ደሬሣ "አንተ ተጠንቀቅ፡፡ ደረጀ 'ለቢዝነስ' ማንንም ከመሸጥ ወደኋላ አይልም" አለኝ፡፡

ያን ጊዜ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን፣ የሚቼልኮትስን የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት ሥራ የምንሠራው እኛ ነን፡፡ ቀጥሎ ቢስ ኩባንያ ላይ አነጣጠርን፡፡ በዚያ ኩባንያ ውስጥ አስፈላጊያችን የሆነ



ሥራ አለ፡፡ የዚያ ሥራ ኃላፊ እኔና ደረጀን ጠራን፡፡ ሚስተር ጆንሰን ይባላል፡፡ ሄድን፡፡ ቢሮው ገባን፡፡ ደረጄ ከፊት ለፊቱ ሆኖ እንዲደራደር እኔ በሩ አጠገብ ተቀመጥኩ፡፡ "በሩን ዝጋው" አለኝ ጆንሰን፡፡ ንቀት ያለበት ትዕዛዝ ነው፡፡ ዝም አልኩት፡፡

"አሁንም በእንግሊዘኛ በሩን ዝጋው እያልኩህ ነው!" አለኝ፡፡

"እኔን ነው የምትለው?" አልኩት፡፡

"አዎን!" አለ፡፡

ደረጀም ጣልቃ ገባና "ሚስተር ጆንሰን፣ አቶ ስብሐት የእኔ ሠራተኛዬ አይደለም፡፡ ሽሪኬ ነው" አለው፡፡ እኔም ጨመርኩበት "በሩን መዝጋት ከፈለግክ ራስህ ተነስተህ መዝጋት ትችላለህ" አልኩት፡፡ በቁጣ ወደኔ ዞሮ 'ዝጋ ብዬሃለሁ' ሲል

"ሚስተር ጆንሰን፣ ነገርኩህኮ..." ብሎ ደረጀ ሲጀምር፣ ከአፉ ነጥቄው "ደረጀ ጆንሰንን ተወው፡፡ ኬንያ ምን ሲሠራ እንደከረመ ሰምቻለሁ፡፡ እዚያ 'ቡዋና' ነው የሚሉት" ብዬ ወደ ጆንሰን ዞሬ "ቡዋና ጆንሰን አሁንም ኬንያ ያሉ መስሏቸው ነው ተዋቸው ደረጀ፡፡ ቡዋና ጆንሰን፣ ሌላስ የምናደርግሎት አለ?" አልኩት፡፡

ዝም አለ፡፡ ደረጀ ሲደመድምልኝ፡፡ "ቡዋና ጆንሰን፣ አንተ ክብራችንን ስለደፈርክ የያቅርታ ደብዳቤ ለድርጅታችን እስካልጻፍክ ጊዜ ድረስ ያንተን ቢዝነስ አንፈልግም" አለው፡፡

ደህና ሁን እንኳ ሳንለው ተነስተን ወጣን፡፡ ምን የመሰለውን ቢዝነስ ተውነው፡፡ ቡዋና ጆንሰን በብልግናው ተፀፅቶ ደብዳቤ ጻፈልን፡፡ ደረጀም እየሳቀ መልሱን ጻፍ አለኝ፡፡

ውድ ሚስተር ጆንሰን፣ ክብራችንን ለመንካት ትንሽ ብትባልግም ይቅር ብለንሃል:: ሥራችንን ለመቀጠል ዝግጁ ነን... ብለን አጭር መልስ ፅፈንለት ሥራ ጀመርን፡፡

የደረጀን መጨረሻ ያጫወተኝ ታናሽ ወንድሙ ዮናስ ነው፡፡ ከሐና ጋር ደረጀ ለንደን መግባቱን አጫውቼሃለሁ፤ ከዚያም ወደ አሜሪካ ተሻገረ፡፡ የአጥንት ካንሰር በሽተኛ ሆነ፡፡ በቅልጥሙ ውስጥ ያለው መቅኒ ነው ሕመም የሆነበት፡፡ ከዘመዶቹ ተመሣሣይ መቅኒ ሲፈለግ የሰለሞን እንደሚስማማው ታወቀ፡፡ ሰለሞንም መቅኒውን ለመስጠት ፈቀደ፡፡ የሰለሞን መቅኒ በቆይታም እንደሚተካ በሳይንስ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ደረጀ አልተረፈም፡፡ መሞቱን ተቀበላት፡፡ በእር ጋታ፣ በፀጥታ፣ ሳይርበተበትና ሳይሸበር ሞትን ተሳፍሮ ሄደ፡፡ ምናል ባት ይኸ ደረጀ እኔን ብቻ ሳይሆን የማትቀረውን ሞትንም ነድቷት ይሆንንደ?!

***

@Amharicbookstore

# ፲፯

## "አካካዩ"

ለእኔ በሕይወቴ በጣም የሚያስገርሙኝና የማደንቃቸው ሰው ጥራ ብባል ብላታ ዱሬሣ አመንቴን ነው፡፡ በጣም የማደንቅላቸው ሦስትና አራት ልዩ ልዩ ተሰጥኦዎች ነበሩዋቸው፡፡ እንደበተ ርቱዕ ተራኪ፣ የታሪክ ሊቅ፣ ለአገራቸውና ለወገናቸው ታማኝና ድንቅ የባሕል መድሐኒት አዋቂ ነበሩ፡፡

ከእኔ ጋር ስንተዋወቅ እሳቸው ከሰማኒያ እስከ ዘጠና ዓመት ይሆናቸዋል፡፡ እኔ በጊዜው ሊጋ ወጣት ነኝ፡፡ ትዝ እንደሚለኝ ከሰለሞን ጋር ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተዋወቅን፡፡ ከዚያም ወንድሞቼ ጓደኞቼ ሆኑ፡፡ በመቀጠል ከሐና ጋር ተዋወኩ፡፡ እናም ስሄድ ስሄድ አያታቸው'ጋ ደረስኩ፡፡ ሁሉም ልጆች አያታቸውን 'አካካዩ' እያሉ ነው የሚጠሩዋቸው፡፡ በኦሮምኛ አያቴ ማለት ነው፡፡ እሣቸው ደግሞ ሁሉንም ልጆቻቸውን በጣም የሚወዱ ቢሆንም ሐና ላይ ፍቅራቸው ያይላል፡፡ ቅፅል ስም ሁሉ አውጥተውላት ነበር፡፡ 'ገርቢቲ' ነው የሚሏት፡፡ ባሪቾ እንደ ማለት ነው፡፡ እሷም በጣም ትወዳቸዋለች፡፡ ሁሉም ልጆቻቸው ያደንቋቸዋል፡፡ ከአፋቸው ላይ አካኩዩ አይጠፋም፡፡ ቀልድ ሁሉ ያውቁበታል፡፡ አንድን ልንገርህ፡፡ አንዱ የልጃቸው እኩያ የሚሆን ይመጣና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ "አውቀውኛል?" ይላቸዋል፡፡

"አዎን" አሉት፡፡

"እርግጥ አውቀውኛል?" አላቸው ደገመና፡፡

"አዎን!" አሉ አሁንም፡፡

"ማነኝ?" አላቸው፡፡

"ችኮ መንቻኮ ነህ?! አይደለህም?!" አሉት አለና ጋሼ ስብሐት አሁንም ከልብ ስቆ ወደ ወጋችን ተመለስን፡፡ "ብላታ ዱሬሣ ሌላ የሚያስደንቀኝ ባሕሪያቸው ጥሩ የሬዲዮ ፕሮግራም ተከታታይ ነበሩ፡፡ በዚያን ዕድሜ (እስበው) የወጣቱ ጋዜጠኛ የአማምነው ገብረወልድ አድናቂ ነበሩ፡፡ ልክ እንደ 'ቲፎዞ ማምለክ' 'Hero Worship' ምንም የማያረጅ ጭንቅላት ነበር ያላቸው፡፡ በወቅቱ መኖሪያ

@Amharicbookstore



ቤታቸው ቢሾፍቱ ነበር፡፡ አዲስ አበባ ሲመጡም የአማምነውን ፕሮግራም ይከታተላሉ፡፡

በባሕሪያቸው ፍርሐትና መርበትበት የሚባል ነገር በአጠገባቸው ዝር አይልም፡፡ በአመኑበት ሥርተው ጡረታ ወጡ፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ አገልግለዋል፡፡ መሥሪያ ቤቱ የትኛው እንደሆነ አሁን አላስታውስም፡፡ አስፈላጊ ከሆነ 'ቼክ' እናደርጋለን፡፡

በወቅቱ በቂ ደመወዝ ያገኛሉ፡፡ አስፈላጊ ከሆነም በእጅ አዙር የሚገኝበት ሁኔታ ነበር፡፡ ለምሳሌ በመንግሥት ገንዘብ ለሌላ ሥራ ተፈርሞ መኪናም ሶፉም ለሹሙ መግዛት በዘመኑ የተለመደ ነው፡፡ እሳቸው ግን ይህንን አላደረጉም፡፡ አንድ ቀን በእግራቸው ሲሄዱ ጃንሆይ አገኙዋቸው፡፡ መኪናቸውን አቁመው "እንዴት ነው ብላታ?" አሉዋቸው፡፡

"እየሔድን ነው!" አሉ ብላታ፡፡

"መኪናዎስ?" አሉ ጃንሆይ፡፡

"የለኝም፡፡"

በነጋታው ጥቁር መርቼዲስ ቤንዝ ከቤተ መንግሥት ተላከ ላቸው፡፡ መርቼዲሷን እኔም ደርሼባታለሁ፡፡ በእርሷ ነበር ከአዲስ አበባ ቢሾፍቱ የሚመላለሱት፡፡

እኔ ፀጋ የምለው ባሕሪ የተሰጣቸው ሰው ናቸው፡፡ እኔ በማንበብ ሊዮ ቶልስቶይ ብቻ ይህንን የርሳቸውን ተግባር መፈፀሙን አስታውሳለሁ፡፡ እሱ ደራሲም 'ካውንትም' ነው፡፡ ካውንት በማዕረግ 'ራስ' ይሆናል፡፡ እኚህ መኳንንት በአገራቸው ብዙ መሬት አላቸው፡፡ ለልጆቻቸው የሚበቃቸውን ያህል አከፋፍለው አወረሷቸው፡፡ የተቀረውን ለጭሰኞቻቸው ያላችሁበት የገዛ መሬታችሁ ነው ሲሉ አሳረፉላቸው፡፡

አዎን! ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ ነው እንዲህ ያደረጉት፡፡ አይደለም እንዴ? ብሎ አብሰለሰለ፡፡ "ቆይ እስኪ" አለና ጋሼ እንደማስታወስ ዓይኑን ጨፈን አድርጎ ካውጠነጠነ በኋላ "አዎን ከዚያ በኋላ ነው ያደረጉት" አለኝና በኢጣሊያን ወረራ ወቅት ብላታ የት እንደነበሩ ያወጋኝ ጀመር፡፡

ወደ ሱዳን ተሰደዋል በካርቱም ከተማ ነበር የሚኖሩት፡፡ ያኔ ለምን አላልኳቸውም እንጂ አሁን ሳስበው ልክ እንደሆኑ ነው የሚገባኝ፡፡ ምን አደረጉ መሰለህ? በካርቱም ጠጅ ቤት ከፈቱ፡፡ ምክንያቱም ከአገራቸው ልጆች ጋር ለመገናኘት እንዲችሉ ነው፡፡ አበሾች ከየትም ቢመጡ ጠጅ ቤት አለ ካሏቸው መምጣታቸው አይቀርም፡፡ በዚያም ከአገራቸው ልጆች ጋር በመጨዋወት ስለ

አገራቸው ብዙ ወሬ ይሰማሉ፡፡ ልክ ዛሬ ሳስበው በዚርቱም የአገራችን የስለላ ማእከል የነበሩ ይመስለኛል። በሕይወታቸው እያሉ ነቅቼ ብጠብቃቸው ኖሮ ይነግሩኝ ነበር። እንደ ጥይት ጋዜጠኛ ናቸው መረጃን ሰብስበው ሲመረምሩ፡፡ የስደቱም ጊዜ አብቅቶ ወደአገራቸው በሰላም ተመለሱ፡፡

በነገራችን ላይ፣ ደረጀ "አክከዩን ብትጠይቃቸውና ብትወዳጃቸው ብዙ ታሪክ ሊነግሩህ ይችላሉ" ብሎኝ፣ የሚያጫውቱኝን ወግ መመዝገቢያ ቴፕሪከርደር ሰጥቶኝ በበርካታ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያወጉኝን ወግ ቀርጫቸው ነበር፡፡ በኋላ ከሱና ጋር ስንለያይ ቤት ውስጥ ጥዬው ልውጣ አልያም የት እንደደረሰ አላውቅም፣ ጠፋ፡፡ ይሁን እንጂ በቂ እዚህ ውስጥ ቀርቷል፡፡ እሱን እዚህም እዚያም እያልን ላጫውትህ" አለኝ ጭንቅላቱን እየነካ፡፡

ፀጥ ብዬ አስተውለዋለሁ፡፡

ሥራዬ ብዬ በማምንት አንድ ቀን ቢሾፍቱ እሔዳለሁ፡፡ የሚያስፈልግና እኔ ብቻ ላውቀው የሚገባኝ ነገር ሲያወጉኝ "ቴፑዋን አጥፋ!" ይሉኛል፡፡ አጠፋና አደምጣቸዋለሁ፡፡ እንጫወት እንጫወትና ቴፑዋን አቁመኸታል እንዴ? በል ቀስቅሳት" ይሉኛል፡፡

በሀገራችን ውስጥ ቢሮክራሲው እንዴት እየተገማመደ እየተራዘመ እንደሔደ ሲያጫውቱኝ "ይኼ መሬቱ አሉኝ፣ በልጅ ኢያሱ ዘመን ነው የገዛሁት፡፡ ቀደም ብሎ ልገዛው ስፈልግ ለሌላ ጉዳይ ታስቧል ተብልኩ፡፡ ልጅ ኢያሱ ሲያልፉ መግዛት አይቻልም? ስላቸው ይቻላል እንጂ አሉኝ፡፡ አራት ፊርማና ሦስት ቀን ጉዳዩን ለማስፈፀም ፈጀብኝ፡፡ በኋላ ለንግድ ባንክ ልሸጠው አሰብኩና ጉዳዩን ለማስፈፀም ስድስት ወር ፈጀ፡፡ የ52 ባለ ሥልጣኖች ፊርማ አስፈለገው፡፡ ያውም በዜድኩበት ድሮ የማውቃቸው ወጣቶች በታ በታ ይዘው ስላሉ ረዱኝ እንጂ መንፈቅም አይበቃውም ነበር" ብለውኛል፡፡

በአስተሳሰብ ዴሞክራት ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ አንዳንዴ ራሳቸውን ፊውዳል አርገህ የምታይበት ሁኔታም ይፈጠርብህና ትደነቃለህ፡፡ ለምሳሌ ልጆቻቸውን ይልማን ለንደን ልከው ነው ያስተማሯቸው፡፡ አቶ ይልማ የለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ ምሩቅ ናቸው፡፡ ሴት ልጆቻቸውን ወይዘሮ የሺመቤትን ግን አላስተማሯቸውም፡፡ የነደረጀ እናት እማማ የሺመቤት አባታቸውን በዚህ ተግባራቸው በጣም ነበር የተቀየሟቸው፡፡ ማካካሻ እንዲሆናቸው ርስት ሰጥተዋቸዋል፡፡" አለና በመገረም ፈገግ አለ፡፡

"እማማ የሺመቤት ያጫወቱኝ ትዝ አለኝ፡፡ እማማ የሺመቤት በእምነት ብረት ናቸው፡፡ ያቀዱትን ለመሥራት፣ የፈለጉትን ነገር

@Ambabookstore



ለማግኘት የሚያግዳቸውም ያለ አይመስለኝም፡፡ አንዴ ከአዲስ አበባ ወደ ጊምቢ ይጓዛሉ፡፡ ብቻቸውን፡፡ ጠመንጃ ታጥቀዋል፡፡ አካባቢው አገራቸው ቢሆንም፣ ወቅቱ ደግሞ የሚያስፈራ" ነው፡፡ የጥልያን ጊዜ ነው ሕግ የለም፡፡ አንዱ ሰውዬ በአጋሰስ እህል ቢጤ ጭኖ ይሄዳል፤ ከፊታቸው የጥይት ድምፅ ተሰማ፡፡ አጋሰሱን የሚነትተው ሰውዬ ወደቀ፡፡ አንዱ ከቁጥቋጦው ውስጥ ወጣና አጋሰሱን ነዳው፡፡ ሬሳውን እዚያው ተወው፡፡ እልፍ ሲሉ እንዲሁ ተተኩሰ፡፡ ባለ አጋሰሱ ወደቀ፡፡ ገዳይ ብቅ አለና ሬሳውን ትቶት አጋሰሱን ነተተው፡፡ ነቀምቴ እስከሚደርሱ 29 ሰዎች መሞታቸውን ቆጠሩ" አለና ጣቱን አፋጩ በመደነቅ፡፡

የታሪካችን መነሻ የሆነን ፖሊስ ነው፡፡ እማማ የሺመቤት ፖሊስ አይኑር አይባልም ብለው ነው ይህንን ታሪክ ያጫወቱኝ፡፡ ጥሩ ፖሊስ ቢኖረን ጥሩ ነው፡፡ ከጠፋም ጉቦኛው ፖሊስ ንብረትህን እንጂ ለአንድ ስልቻ እህል ነብስህን አያዘርፍህም፡፡

ብላታ በጠባብነት ወይም በትምክህት ሳይሆን የዘር ማንዘራቸውን አመዛዝዝ ታሪክ እንደ ታሪክ አዋቂነታቸው አጫውተውኛል፡፡ ልንገርህ፡፡ በከሬ የጆቴ ታናሽ ወንድም ነው፡፡ ወሊጋ የጆቴ ወርቅ ሲባል ሰምተህ አታውቅም?

የጆቴ ታናሽ የበከሬ የልጅ ልጅ ናቸው፡፡ ከቤተሰብ ወደ ኦሮሞው ማኅበረሰብ እንግባ፡፡ አቤ ምኒልክ አገር እያቀኑ ናቸው፡፡ ለሚቀናው አገር ባላባት በመጀመሪያ ሰው ይልኩበታል፡፡ ኅበና ነው መልዕክተኛቸው፡፡ ሁለት ዓይነት መልዕክት አላቸው ምኒልክ፣ አንድ "ከእኛ ጋር አትዋጋ፡፡ ብንዋጋ አትችለንም፡፡ በሰላም የገባህልን እንደሆነ የዓመት ግብር ከፍለህ ከዚያም እንደ አባቶችህ አገርህን አረጋልሃለሁ፡፡ እንቢ ካልክና ከተዋጋኸን ግን ገዥ እልክብሀና ትገዛታለህ፡፡ ሕዝብህም ጪሰኛ ይሆናል" ይሉታል፡ ምርጫው የባላባቱ ነው፡፡

ሞረዳ በመገበሩ ተስማምቶ ገባላቸው፡፡ ገብረ እግዚአብሔር ብለው ክርስትና አነሱት፡፡ ገብረ እግዚአብሔር አዲስ አበባ መጣ፡፡ በደስታ ተቀበሉት፡፡ ከዚያም አቤውን በቆይታ እንዲያናግሩት ጠየቀ፡፡ እነ ራስ እገሌ ወጡ ሁለቱ ብቻቸውን ቀሩ፡፡ ገብረ እግዚአብሔር ቀበቶውን ፈታ። ውስጡ ጥይት አይደለም ያለው፣ ወርቅ ነው፡፡ ምኒልክ ፊት ጠረጴዛ ላይ ተከመረ፡፡ ገብረ እግዚአብሔርም "የወሊጋ አገረ ገዥ እኔ ከሆንኩ በዓመት በዓመት፣ ይህንን የሚያህል ወርቅ አስገባለሁ፡፡ አይሆንም ብለው ከቅርብ ሰዎችዎ ከሾሙብን የዚህን ሩብ አያገኙም" አላቸው፡፡ አቤውም እዚያው ገዥ ሆኖ እንዲረጋ

ፈቀዱለት ይባላል" አለና ጋሼ ጨዋታው ወደሌላ ርዕስ ተቀየረ። ከልምድ እንደማውቀው የፈለገውን ርዕስ አውግቶ አዙሮ ከዋናው ርዕስ ጋር እንደሚያቆራኘው ስለማውቅ ፀጥ ብዬ እከታተለው ጀመር።

"እኔ ወጣት ብሆን ሀሰን እንጃሞን ነው የታሪካዊ ልቦለድ ዋና ገፀ ባህሪ የማደርገው። ጀግና ነው ሀሰን እንጃሞ። ጉራጌ ነው። ብላታ እንዳጫወቱኝ፣ ሸፈተ። ምኒልክ ራስ ጎበናን ላኩበት። ጎበና በዘመኑ ማንም አይችለውም። ሀሰን ግን ገጥሞ አሸነፈው። ይህ ተደገመ። ይሔኔ ራሳቸው ምኒልክ ዘመቱበት። ሕይወት እንደ አልበርት ካሙ 'አብሰርድ' አይደለችምን? ሀሰን እንጃሞ በጦር ሜዳ ሳይሆን በወባ በሽታ ታሞ ሞተ። ሀሰን እንጃሞ ብቻ ነው ጎበናን የተቋቋመ። በማሪያም ይህቺን ወግ አስታውሰኝ፣ ሀሰን እንጃሞን እግረ መንገድ ዓምድ ላይ እፅፈዋለሁ። ራስ ጎበናን ልጨምርልህ?

ራስ ጎበና ታላቅ የጦር መሪ ስለሆኑ በርካታ አጋሮች አሏቸው። ለምኒልክ "ሌላ የጦር አበጋዝ ይሹሙ እንጂ። ራስ ጎበና'ኮ አርጅተዋል" እያሉ ደጋግመውላቸው። አንድ ቀን ምኒልክ መስክ ላይ እያሉ ጎበና መጡ። ፈረሳቸው እንደ ማዶ ነው። ቃልዋን ሁሉ ይዤያታለሁ። በኦሮምኛ 'ሰረጁ' ይሉታል። እርካብ ሳይረግጥ ዘሎ ፈረስ ላይ ጉብ ብሎ ፈትለክ አለ። ምኒልክም ይህንን ሲያዩ "እውነትም ጎበና አረጀ" ብለው ሣቁ።

የበሰልኩት ብላታ ዴሬሳ ታሪክ እያጫወቱኝ ነው። ላንተም ካጫወቱኝም ካነበብኩትም አካፈልኩህ። በብላታ ደሬሳ ላይ የጀመርነውን ለመቋጨት የባሕል መድኃኒት አዋቂነታቸውን ልጨምርልህ

ታናሽ ወንድማቸውን ለትምህርት እንግሊዝ አገር ላኩት። እዚያ ሄዶ ሲማር የሳንባ በሽታ ያዘው። በዚያን ዘመን የሳንባ በሽታ ገዳይ ነው። ቲቢ ይሉታል። ሞቃት አገር ቢመጣ ግን በሽተኛው ዕድሜው ትንሽ ይረዝማል። እንግሊዞቹ በሽተኛውን ወደ አገሩ ላኩት። አገሩ እንደገባም "እንዴት ነው?" ሲሉ ብላታ ጠየቁት።

"አገርህ ገብተህ ሙት ብለው ነው የላኩኝ" ሲል ነገራቸው።

ይህንን የሚያጫውቱኝ እራሳቸው ናቸው። "እነርሱ ይሞታሉ እንጂ አንተ አትሞትም" አሉና ባህላዊ መድሐኒት ቀምመው አደረጉለት ዳነ። በሚቀጥለው ዓመት ትምህርት ቤት ሲከፈት ወደ እንግሊዝ አገር ተመልሶ ትምህርቱን ቀጠለ። ብላታም ይህንን ያህል የዘመኑን በሽታ የሚቆጣጠር እውቀት ነበራቸው" አለና ጥቂት አብሰልስሎ "በአገር ባሕል መድኃኒታቸው እኔንም አድነውኛል። የሚጥል በሽታ ነበረብኝ። የእኔ እንደ ደራሲ ዶስቶየቭስኪ እያነሣ የሚያፈርጥ ዓይነት አይደለም። እኔ ላይ የደረሰብኝን ወንድሞቼ እንደነገሩኝ፤

@Amharicbookstore



ሌሊት እነሳና በኃይል! በኃይል! እጮሀለሁ። ተነስቼ እሮጣለሁ። ይዘውኝ በግድ ያስተኙኛል።

ጡንቻዬ ደግሞ የዚያን ጊዜ ጠንካራ ነው። ጠዋት ስነሣ በጣም ድካም ያደርገኛል። አንዳንዴም ትንፋሼን እነክሳለሁ። አንዳንዴ ሟት ስነቃ ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሰኮንዶች ማን እንደሆንኩ የት እንደሆንኩ አላውቅም። በዚህ በሽታ ምክንያትም ልጅ ላለመውለድ ወስኜ ነበር። በምወልደው ልጅ ላይ ይተላለፋል የሚል ፍርሐት ነበረኝ።

ባለቤቴ ምን አማራጭ አላት? የሚቸልኩትስ ቼርማን እንደ አባቷ ነበር። ኤውሮፓ ውስጥ ከሚገኙት አራት ዋነኛ የንዲህ ዓይነት በሽታዎች እስፔሻሊስቶች አንዱ ከሆነው ሀኪም ጋር ሚስተር ዳክ ቀጠሮ ያዘልን።

"በሽታህ በዘር አይተላለፍም" አለኝ ሐኪሙም "ነገርግን ማንኛውም ልጅ ሲወለድ 'ኤፕሌፕቲክ' ለመሆን ሦስት ከመቶ ዕድል አለው። ስለዚህ ምናልባት ያንተ ልጅ ኤፕሊፕቲክ ቢሆን፣ ለተሪው፣ ሦስት ከመቶው ደርሶት ነው እንጂ ካንተ ወርሶት አይደለም አለኝ። ኪኒኖች አዘዘልኝ በቀን አንድ ጊዜ የሚዋጡ።

ለብላታ ያመኛል ሳልላቸው ላማክራቸው ወሰንኩ። አነሳሁና ጠየቅኋቸው። ይህ በሽታ በእኛ አገር የባሪያ በሽታ ይባላል። ይህንን ጥያቄ ለመመለስ እንደ ማርኮ ፖሎ ጉዞ ከአንድ ሰዓት በላይ በባሪያ በሽታ ትንታኔ ይዘውኝ ተጓዙ። በመጨረሻ መልሣቸው እኔ ሠርቼበት አላውቅም ሆነ። "እንደኔው ያገራችን መድኃኒት የሚያውቅ ጓደኛዬ እገሌ እንደነገረኝ..." ብለው አንድ መድኃኒት ጠሩ። ተጠቀምኩበት። ብዙም ሳልቆይ ከበሽታዬ ዳንኩ። ኪኒኑን መዋጥ አቆምኩ። ከሐና ጋርም የመጀመሪያ ልጃችንን ያለምንም ስጋት ለመውለድ ተስማማን። "መድኃኒቱን ታስሬበታለሁ።

...

"ጎሊስ ተወው ብሎኝ።"

...

"ይላሉ።"

...

"መድኃኒቴ ከሕመም ፈውሶኛል። ደስታንም ይፈጥርልኛል።"

...

"አንዳንዱ በሰው ሕይወት ውስጥ ጥልቅ ብሎ ይፈተፍታል።"

...

"ደግሞ እኮ ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው' ሲል ትሰማዋለህ።"

"ግን የእኔም በባሕሪዬ አደባባይ መሆን የጎዳኝ መሰለኝ።"

...

"እንደዚያ ነው የሚደረግ፣ ሰው ምን ይለኛል እያልክ?"

...

"አልነግርህም!"

...

"ዘነበ አምንኃለሁ። አንተም ሌላ የምታምነው ወዳጅ አለ። ስለዚህ ትንግረውና ሳይታወቅህ መድኃኒቴን ታረክሱብኛላችሁ።"

፲፯

@Amharicbookstore

## ፍቅሩን በእንባው አየሁ

ሌላው መምህሬ ብዬ ልጠራልህ የምችለው ሰው ሥዩም ስብሐት ይባላል። ስጠራው ጋሼ ሥዩም ነው የምለው። ተፈጥሮው ከማድነቅ ያበልጥ መውደድን ነው የሚቀሰቅስብህ። በጣም የምወደው ሰው ነበር። ጎንደሬ ነው። በባሕሪውም የጎንደሮች ኩራት አለበት። የተማረው እንግሊዝ አገር ነው። ጸሐፊ ተውኔቱን በርናርድ ሾን ያመልከዋል። ከሩቅ ከተማ ዩኒቨርሲቲ ሾን ፍለጋ ለንደን ድረስ ሄዶ ተዋውቆታል።

እኔና ጋሼ ሥዩምን ያስተዋወቀን የየካቲት መጽሔት አዘጋጅ ማዕረጉ በዛብህ ነበር። "ስለ ታከለ ወልደ ሃዋርያት ጥሩ ዕውቀት አለውና አነጋግረው" ብሎ ላከኝ። ሄድኩ። የነገረኝን ጻፍኩ። ጋሼ ሥዩም ጽሑፉን በጣም ወደደው። ሲያጫውተኝ "ከዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተማሪዎች መጥተው አነጋግረውኝ ጽፈዋል። ሥራቸውን ሳየው የነገርኳቸውን አዮሌውን ስተውታል። አንተ ግን ያልኩህን ነው የጻፍከው፣" ሲል ሥራዬን አመሰገነልኝ።

እ! በቃ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጓደኛሞች ሆንን። ጋሼ ሥዩምን አሁን ሳስበው በመውደድ ነው። ሲስቅ ፈገግታው ደስ ይላል። ትንፏሹም ስርጉድ ትላለች። የጎንደሬነት ኩራቱ እንዳለች ሆና፣



በባሕሪው ትሁት ነው። መኖሪያ ቤቱ አራት ኪሎ ፎቅ ላይ ነበር። በሣምንት አንድ ቀን ልጎበኘው ሔዳለሁ። በጊዜ ብዛት ቤተኛ ሆንኩ። የባለቤቱ ወንድም የሆነ ኮሌጅ አብሮኝ የተማረ ጓደኛዬን አገኘሁትና ወዳጅነታችን ቀጠለ። በመጻሕፍት ላይ ከጓደኛዬ ጋር ለረጂም ሰዓታት እናወራለን። ከጋሼም ጋር እንደዚሁ።

ጋሼ ሥዩም በገንዘብ እጥረት እየተቸገረ አንዳንዴ ኩራቱ እንዴት እንደሚፈታተነው ይገርመኛል። አንዷን ላውራልህ። መኪና ነበረችው፣ የፈረንሣይ ስሪት የሆነች ሲትሮይን። ዋጋዋ ውድ!

በአንድ ወቅት የወር ገቢ አልነበረውም። ወጪው ግን ይበዛል። ይህንን አይቼ፣ እኔና ጋሼ ሥዩምን የሚያደባብቀን የምንከለልበት አጥር ስለሌለ "ጋሼ ሥዩም፣ ለምን ይህችን መኪና ሸጠህ ችግርህን አትከላከልም? አሁን ባለህበት ሁኔታ መኪና አያስፈልግህም'ኮ" አልኩት።

"በጭራሽ!" አለ።

"እንዴት? ኩራትህ በለጠብህ" አልኩት።

"አዎን። ክብሬ አይፈቅድልኝም" አለኝ።

ሲያጫውተኝ በተለይ ደስ የሚለኝ ስለ ደጃች ታከለ ነው። ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሃዋርያት ከጃንሆይ ጋር ብዙ ጊዜ ተፋጭተዋል። የምር ጠላቶች ናቸው። ጋሼ ደግሞ የደጃዝማች ታከለ 'ቲፎዞ' ነበር። የጃንሆይን ስም ሲጠራ፣ 'ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ' ነው ምንጊዜም የሚላቸው። 'ጃንሆይ እንዳይል!' አይወዳቸውም። ግን መናቅ የለም። ክብራቸውን አይነካም። እሱ እራሱ ኩሩ በመሆኑ፣ የሰውን ልጅ የክብር ልክ ያውቃላ። አክብሮ መከበር ይገባዋላ! ስለዚህ ሊወቅሳቸው ሲፈልግ እንኳን አክብሮዋቸው "ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጭቦኛ ናቸው!" ይላል።

ጃንሆይም 'ኢንቴሌክቹዋል' ናቸው። ያውቃሉ ጋሼ ሥዩም እንደሚጠላቸው። የደጃዝማች ታከለ 'ቲፎዞ' ነው፤ ሲያስፈልግ ሰላዮም ይመድቡበታል እንጂ ሥራ ግን አላስፈቱትም። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት ሥራ አስኪያጅ አድርገው ለአምስት ዓመታት አሠርተውታል።ሌላ እስካሁን የሚገርመኝን ላጫውትህ።

ጋሼ ሥዩም አንድ መጽሐፍ አነበበ። ጂላስ የቲቶ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረ ሰው ነው። The Third class ሲል አንድ መጽሐፍ ጻፈ። በዚህ ቲቶ ተቆጥቶ ከሥራው አስወገደው። ለስም ሲባልም ታስረሃል አለው። የቁም እስረኛም ቢሆን ክብሩ ግን አልተነካም። ጋሼ ሥዩም መጽሐፏን ከአንድ ሰው ተውሶ አነበበ። በጣም ወደዳት። ስለዚህ ባለንብረቱን እንዲሸጥለት ለመነው። ባለቤቱ ግን ለመሸጥ ፈቃደኛ አልሆነም። "እሺ ትንሽ ጊዜ ስጠኝ" አለና በደረት

ኪስ በሚያዙ ማስታወሻ ደብተሮቹ ላይ ገለበጠው፡፡ በጣም በደቃቅ የእጅ ጽሕፈት ነው የጻፋቸው ፊደላቱን፡፡ እኔም ይህንን አይቼ "ጋሼ ሥዩም፣ አሁን ይታይሃል እንጂ ስታረጅ እንዴት እነዚህን ቀጫጭን ፊደላት ማንበብ ትችላለህ?" ስለው፡

"እችላለሁ ግዴለህም" አለኝ፡፡

እንዲህም ዓይነት ባሕሪ አለው፡፡ ሰውን ስንወድ ምክንያት እንፈልጋለን፡፡ ጋሼ ሥዩም ግን ምንም የሚያደርግልኝ ነገር የለም፡፡ ፍቅሩን ውስጤ አስርጿል፡፡ ለምጽፋቸው ሥራዎቼም ታሪኮችን አዋጥቶልኛል፡፡ ጋሼ ሥዩምን ሳስብ አልቤር ካሙ 'አብሰርድ' የሚለው ጭብጥ ነው በሕሊናዬ ውስጥ የሚከሰተው፡፡ እንዴት መሰለህ?

Absurd ማለት፣ እኔ ሁሉም ነገር እንዲገባኝ፣ እንዲገለጽልኝ የምፈልግ ፍጡር ነኝ፡፡ ተፈጥሮ እኔም ሆንኩ ማንም ሊገባው የማይችል የተዘጋ፣ የተቆለፈ እንቆቅልሽ ምስጢር ምናምን ምናምንቴ ነው፣ ምኑም ለማንም የማይገባ፡፡

ጋሼ ሥዩም ሁልጊዜ ማታ ማታ ነጭ ሽንኩርት ተከትፎ በቡና ስኒ ተሞልቶ ያድርለታል፡፡ጠዋት በእኛ ጠዋት አይደለም፣ በእናንተ በመርከበኞቹ ጠዋት ይነቃል፡፡ አዎን ከጠዋቱ 12 ሰዓት? ይነቃል፡፡

እ! ነጭ ሽንኩርቱን በማንኪያ ዋጥ ዋጥ ያደርጋል፡፡ ከዚያ በቀዝቃዛ ውሃ አካላቱን ይታጠብና ቁጭ ብሎ ያነባል፡፡ ወይ ይጽፋል፡፡ ይህ የሁልጊዜ ፕሮግራሙ ነው፡፡ ማርያምን! ምንጊዜም ፕሮግራሙ ነው፡፡ ከዚያ እስኪመሽ ጨዋታ ነው፡፡ ከሰው ጋር መሆን በጣም ደስ የሚለው ሰው ነው፡፡ የታመመን መጠየቅ፣ የሞተን መቅበር ልማዱ ነው፡፡ አንዴ ሰው ሞቶና በላንድሮቨር ደሴ ሊሄድ ተሳፈረ፡፡ በጉዞ ላይ መኪናው ተገልብጦ ጋሼ ሥዩም በእሳት እየተቃጠለ፣ እየተቃጠለ ሞተ..." አለና ጋሼ ስብሐት እንባው አቀረረ፤ ድምጹ ሰለለ፤ በጸጥታ እያብሰለሰልኩ የገሐዱን ዓለም መምህሩን ምን ያህል ይወደው እንደነበር ፍቅሩን በእንባው አየሁ፡፡

@Amharicbooksstore

***

ስለ አቶ ሥዩም ስብሐት የበለጠ የማወቅ ጉጉት አደረብኝ፡፡ በከንቲባው ብሔራዊ ቴአትር ሥራ አስኪያጅ ቢሮ ደወልኩ፡፡ የቴአትር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ አስፋው አርጋውን መስመር ላይ አግኝቼው ሰላምታ ተለዋወጥን ቢሮው ብቅ ብዬ ላነጋግረው እንደምፈልግና ፈቃደኛም እንደሆነ ጠየቅኩት፡፡ ፈቀደልኝ፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ አወጋሁት፡፡ ሲያደምጠኝ ቆየና "እንተባበርሃለን" ብሎ ፀሐፊውን በደወል ጠራት፡፡ ቀናነቱን ወደድኩት፡፡ ፀሐፊው ገባች፡፡ እስኪ 'dead file' ውስጥ አቶ ሥዩም ስብሐት የሚል ማኅደር አምጪልኝ አላት፡፡ አመጣችው፡፡

ቢታይ ምንም አይነት ፎቶግራፍ በማኅደሩ ውስጥ የለም፡፡ አቶ አስፋው "በዚያን ዘመን የሚዘጋጁ የግል ማኅደሮች ፎቶግራፍ አይቀመጥባቸውም ማለት ነው ለማንኛውም



አንድ ሰው ብትጠቀምበት በደንብ ሊያግዝህ ይችላል፡፡ ይህ ሰው የቴአትር ቤታችን ታሪክ ኢንሳይክሎፒዲያችን ነው፡፡ ስሙ ጌታቸው ደባልቄ ይባላል፡፡ ወደ ክበብ አካባቢ ብትዘልቅ ታገኘዋለህ፡፡ በተፈጥሮው ቀናና ወጣቶችን ማገዝ ስለሚወድ ይተባበርሃል" ብሎኝ ተሰነባበትን፡፡

አርቲስት ጌታቸው ደባልቄን አግኝቼ አወጋሁት፡፡ በወቅቱ የሚያጠናው ቴአትር ስለነበር በጥድፊያ ላይ ነበር፡፡ ሌላ ቀጠሮ ተለዋውጠን ተሰነባበትን፡፡

በሌላ ሰንበት ቀን ብሔራዊ ቴአትር ካፊቴሪያ ብቅ ስል ጋሼ ጌታቸው ቁጭ ብሎ የቴአትር ድርሰት እያነበበ አገኘሁት፡፡ እንዳየኝ ቆይ አንድ ያገኘሁልህ 'ማቴሪያል' አለ፡፡ ለጋሼ ሥዩም አርባኛው ቀን መታሰቢያ የታተመለት ጽሁፍ አግኝቼልሃለሁ፡፡ የአቶ ሥዩም ስብሐትን አጭር የሕይወት ታሪክ ያነብልኝ ጀመር፡፡

አቶ ሥዩም ስብሐት ኅዳር 6 ቀን 1917 ዓም ከመምህር ስብሐት ገብረ ሕይወትና ከወይዘሮ የሺምነሽ መንገሻ በጎንደር ጠቅላይ ግዛት ቢጋይንት አውራጃ በቤተልሔም ከተማ ተወለደ፡፡

ቤተሰቡ መምህር ቀጥረውለት የፊደል ዘርን ዘልቆ ወንጌልና ዳዊትን ደግሟል፡፡ በደሴ፣ በጎንደር ከተሞች ተዘዋውሮ ዜማና የግዕዝ ቋንቋ ተምሯል፡፡ ደሴ በተማረበት ለአንድ ዓመት አስተምሮ ወደ አዲስ አበባ ተጓዘ፡፡ 1935 ዓ.ም ቀን እየሠራ ማታ ማታ ዘመናዊ ትምህርቱን በመድኃኔዓለም ትምህርት ቤት ጀመረ፡፡ ውጤታማም በመሆኑ በሀገሪቱ በዚያን ዘመን ብቸኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረው ኮተቤ የመማር ዕድል ገጠመው፡፡

የውጪ ትምህርት ዕድል አግኝቶ መጀመሪያ በስዊዝ በሳን ጋል በርዝንበርግ ኮሌጅ የአንድ ዓመት ኮርሱን ወስዶ በ1941 ዓ.ም ወደ እንግሊዝ ሀገር ተዛወረ፡፡ በለንደን ኢተን ኤንድ ዋሊስ ቱቶሪያል ኮሌጅ የሚያስፈልጉትን ኮርሶች ወስዶ በሳይንስ ትምህርቱን አጠናቋል፡፡

በእንግሊዝ ሀገር በተማሪነት ዘመኑ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በተሻለና በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲጓዝ የበኩሉን ጥሯል፡፡ ላየን ካብ ወይም የአንበሳ ደቦል በሚለው መጽሄት ላይ አመራማሪ ጽሑፎችን ንባብ አብቅቷል፡፡ በ1942 ዓም በቼስተር በተደረገው የተማሪዎች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ 'ሀገራችን እንድትለማና የሕዝቧ ኑሮ እንዲያድግ ከተፈለገ መሬት ሁሉ የሕዝብ ሀብት መሆን አለበት' የሚል በወቅቱ እንደ እንግዳ ይታይ የነበረውን ሐሳብ ሰንዝሯል፡፡

በዚህ ወቅት የታወቁት የኢትዮጵያ ወዳጅ ማዳም ሲልቪያ ፓንክረስት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ በእንግሊዝ ሀገር በሚያደርጉት ቅስቀሳ ላይ ሥዩም ስብሐት የኤርትራው አባቱን ፈለግ በመከተል ሲልቪያ ፓንክረስት በሚያዘጋጁአቸው ስብሰባዎች ላይ እየተገኘ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል መሆንዋን መስክሯል፡፡ የኤርትራ ሕዝብም ፍላጐት ኢትዮጵያ ወይም ሞት በሚል መፈክር እየገለጸ መሆኑን ከታሪክ አገናዝቦ ለማስረዳት ከደከሙ ወጣት ምሁራን መካከል አንዱ ነበር፡፡

ሥዩም ስብሐት በ1946 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡ በወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር በመንፈሳዊ ኮሌጅና በትምህርት ቤቶች አዳራሽ እየተገኘ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር አድርጓል፡፡ በዚህ ወቅት በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ የሥልጣኔ ትርጉም በሚል ርዕስ ተከታታይ ጽሑፎች አቅርቧል፡፡

አቶ ሥዩም በተለያዩ ኃላፊነቶች በመንግሥት ሥራ ላይ ተሰማርቷል፡፡ በኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ፣ በእርሻ ሚኒስቴር፣ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ቤት የመጀመሪያው የቴአትርና የኪነጥበባት ዳይሬክተር ሆኖ

አገልግሏል። 'ላቨር' የተባለው የሞልዬርን ዝነኛ ኮሜዲ ለሀገራችን ባሕል እንዲስማማ አድርጎ በመተርጐም ለመድረክ ሰይቶ አብቅቶታል።

በ1953 ዓ.ም የመንግሥት ምክር ቤት አባል ለመሆን በሰፊው ቢንቀሳቀስም አልቀናውም። ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት በሚያደርጉት የፖለቲካ ትግል ግንባር ቀደም አጋራቸው ሥዩም ስብሐት ነበር። በሐምሌ ወር 1953 ደጃዝማች ታከለ ወደ ጎሬ ሲጋዙ እሱም በእሥራት ወደ ጊሚራ ተወሰደ። ቀጥሎ ወደ ጂማ ሲዛወሩ ሥዩም ወደ አሰላ እንዲሸጋገር ሆነ። በአሰላ አንድ ዓመት ከሰባት ወር በግዞት ቆይቶ በታኅሣሥ በሦስተኛ ዓመቱ በ1956 ዓ.ም ተፈታ።

ለሦስት ዓመታት ያህል በትርጉምና በንግድ ጉዳይ ፈፃሚነት ሠርቷል። በ1959 ዓ.ም በስውር ተሰደደ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ከሚቃወሙ ተራማጅ ኃይሎች ጋር ግንባር ለመግጠም በፈረንሣይ፣ በኢጣሊያና ግብፅ ተዘዋውሯል። በመጨረሻም ወደ ሱዳን ተመለሰ። የኃይለ ሥላሴ ተፅእኖ ስለደረሰበት ሱዳንን ጥሎ ለመውጣት ተገደደ። በ1964 ዓ.ም ወደ ፓሪስ ተጉዞ ለአንድ ዓመት ቆየ። በ1965 ዓ.ም ወደ ጋና በመጓዝ በሌጎስ ዩኒቨርሲቲ በአፍሪካ ጥናት ኢንስቲትዩት በምርምርና ጥናት በተባባሪነት ሠርቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በ1966 ዓ.ም ሲቀጣጠል የሰባት ዓመታት ከሁለት ወር ከ11 ቀናት የስደት ኑሮው አብቅቶ ወደ እናት ሀገሩ ተመለሰ። በአዲስ አበባም ከውድ ባለቤቱና ከአንዲት ሴት ልጁ ጋር ተቀላቅሎ አብሮ የመኖር ዕድል ገጠመው።

የትርጉም ሥራውን ቀጠለ። በዚህ እንቅስቃሴው ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ አንድ ጠቃሚ የሥነ ልሳን መጽሐፍ ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ተርጉሞ አበርክቷል። በዚህ ወቅት ነው ከደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ጋር የተዋወቀውና ስለ ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት ታሪክና ሕይወት በሰፊው ቃለ ምልልስ ያደረጉት። እኚህ ሠራዬ የሚላቸው በመጥር አርበኛ ሕይወትና ሥራ ላይ ምስክርነቱ በወቅቱ ታከለ ታገለ በሚል ርዕስ በየካቲት መጽሔት በ1973 ዓ.ም በኅዳር በታኅሣሥና በጥር ወራት ላይ ለሕትመት በቅቷል።

አቶ ሥዩም ልሳነ ብዙ ነበር። ግዕዝ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ እንግሊዘኛ ጣሊያንኛ ፈረንሣይኛ፣ ዓረብኛ በጥልቀት ያውቃል። የሀገራቸውን ባሕል፣ ወግ፣ ሥርዓት በጥልቀት ከሚያውቁት ከፍተኛ ምሑራን መካከልም አንዱ ነበር።

በ1949 ዓ.ም ለሕትመት በበቃው የዊሊያም ሼክስፒር ዩልዮስ ቄሳር ቴአትር ላይ ተርጓሚው በቀለ ተገኝ ለዚህ ምሑር አክብሮቱን ሲገልጽ "አቶ ሥዩም ስብሐት የእጅ ጽሑፉን ደጋግሞ በማንበብ በትርጉሙ ላይ ምስጢሩን የሳተ አማርኛ ወይም የሚያስነውር ግድፈት እንዳይኖር በማረም አግዞኛል። ጽሑፉን ከማሳተሜ አስቀድሜ ግብረ ታሪኩን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቴአትር እንዲታይ ሳመለክት ካደረገልኝ ዕርዳታ በኋ ብቻ ሳይሆን ይህንን የመሰለ ሥነ ጥበብን የሚያነቃቃ ጥንታዊ ልማድንና ዘመናዊ ሥልጣኔን አቀራርቦ የሀገር ቋንቋን ደረጃ ከፍ ከፍ የሚያደርግ ድካም ሁሉ ፍሬ አያገኝ እንዲዳብር በመርዳት ስላየሁበት ታጋይ መንፈስ እሱን መሳይ የሀገርና የወገን አገልጋይ ሁሉ በበጎ ምግባሩ እንዲበረታታ ስል መልካም አርአያውን በሕትመት ለመግለጽ ዕድል ስላገጠመኝ እጥብቄ እደሰታለሁ።" ሲል ተርጓሚው ምሁሩን ይበል ይለዋል። ይሁን እንጂ ይህን ያህል የተደከመበት ቴአትር በልዩ ልዩ ምክንያቶች በወቅቱ ለመድረክ ቀርቦ አለመታየቱን ይገልጻል።

ከልጅነት ጀምሮ ለዓመታት ያልተለየውን የሥነ ጽሑፍ ዝንባሌ መሠረት በማድረግ አንድ ሀበይ ልቦለድ ለመጻፍ አጽመ ታሪኩን ነደፈ። በዚህ መሐል የታላቅ እህቱን ባለቤት ዜና እረፍት ሰምቶ ኀዘኑን ለመግለጽ ወደ ደሴ ሲገሠግስ በመንገድ ላይ ባጋጠ

@Amharicbookstore



መው የመኪና አደጋ ሩቅ አሳቢው ምሑር ቅርብ አዳሪ ሆነ። ዕለቱም ጥር 2 ቀን 1975 ዓ.ም ነበር።

ሰውዬው ስዩም የራስ ዳሸንን ያህል ገዝፎ ታየኝ። ይህንን መምህሩን ማጣቱ ነው ጋሼ ስብሐትን ያስነባው። እኔም በሰንባዎቹ ዘለላ ውስጥ በጥበብ ምትሐት ፍቅሩን ገዝፎ አየሁት።

***

፲፰

# ዜና መልሕቁ ናት

ቻርሊ ቻፕሊን The Great dictator በተባለ ፊልሙ ላይ በርካታ የናዚ ጀርመን ከፍተኛ መኮንኖችን በአንዴ ማረካቸው። ጋዜጠኞች በጣም ተገርመው «እንዴት ይህንን ያህል ጄኔራል ባንዴ ማረክህ?» ሲሉት «ከበብኳቸው!» አላቸው።

እኔም በአኗኗር እነሆ አዲስ አበባን እየከበብኳት ነው። ቻርሊን እየኮመኮመ እኔ ደግሞ እየኖርኩ በልጅነት የኖርኩባቸውን ብንቀጥር ይበቃል። ከተረት ሰፈር እንጀምር ከላዛሪስት ሚሲዮን ትምህርት ቤት ጀርባ፣ ቂርቆስ፣ መካኒሳ፣ ላፍቶ፣ ኮተቤ ከወዲህ ጠርዝ ላይ መገናኛን አጠቃቅሼ ወደ ሲኤምሲ፣ ሰንቀላል ፋብሪካ (ሚኪሊላንድ መንደር) ቡልጋሪያ ማዞሪያ፣ እንደገና ቂርቆስ ኢያልን ወዘተ ኖረናል።

ላዛሪስት ተከራይተን የመማንበት ቤት 160 ብር እንከፍላለን። ድሮ ተረት ሰፈር ስንኖር 12 ብር ከ50 ሣንቲም ነበር ኪራዩ። እዚህ ፀጥታው፣ ቤቱም ሰፋ ብሎ ሦስት ክፍል መሆኑን አስብ ጥሩ ነው። አሁን እኔ መርከብ ነኝ። ዜና ደግሞ መልህቅ ናት። አሁን የእኔ ጊዜ አልፏል። የወጣቷን ሐሳብ ሰምተን መከተል ተግባራችን ነው።

በኋላ ዜና እንደነገረችኝ እዚህ አዲሱ ሰፈር ከትንሽዋ ልጁ ኩኩሻ ጋር ከዋልንበት በመመለስ ላይ ነን። የአባቷን ተፈጥሮ አታውቀውም አይደል? "ቆይ አባዬ" ብላኝ መንገድ ላይ ጥላኝ ተሹለክልካ በእቋራጭ ወደ ቤት ሔደች። እኔም በገዛ መዲናዬ አዲሱ ቤቴ ጠፋብኝ። ስንከራተት አምሽቼ ምንም ችግር ሳያገኘኝ ጠዋት ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል አካባቢ ቤተሰቤ አገኙኝ።

ቀደም ብሎም ሳያመኝ አይቀርም። የሳንባ በሽታ እንዳለብኝ ቀጨኔ አካባቢ የሚገኝ የእናት ክሊኒክ ሐኪም ነገረኝ። እዚያው ሕክምና ጀመርኩ። ከዚያ ከአቅማቸው በላይ ቢሆን ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተዛወርኩ።

በሆስፒታሉም ለሶስታት አከሙኝ ፈውስ የለም። ስለቸኘና መውጣት እንደምፈልግ ለሐኪሞቹ ነገርኳቸው።

ሐኪሞቹም በሁለት ምክንያት ብቻ እንደምወጣ ነገሩኝ፡፡ አንድም ድኜ፣ ሁለትም ሞቼ ነው። ከዚህ ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል መውጣት የምችለው፡፡ ያ ካልሆነ ከዚያ አካባቢ ንቅንቅ አልልም፡፡ እኔ ደግሞ እስከምድን አካባቢው አስጠላኝ፡፡ እስከምሞትም መጠበቅ አልቻልኩም፡፡ እነርሱ ደግሞ በዶክተር ያምናሉ አይደል? ተወልደ ሲመጣ ይህ ታናሽ ወንድሜ ነው፡፡ በሙያው እንደናንተው ዶክተር ነው፡፡ እቤቱ ወስዶ ሕክምናውን ቢሰጠኝ ደስ ይለኛል፡፡" አልኳቸው፡፡

ዶክተሮቹም «እሳቸው እሺ ካሉ እንስማማለን» አሉኝ፡፡ ተወልደም እስከምድን እሱ ቤት እንደምኖር ቃል አስገባኝ፡፡ ዕድሜ ለወንድሜ! ሳልሞትም ሳልድንም ከሆስፒታል የወጣሁት በዚህ አጋጣሚ ነው።

በጊዜው ተወልደ ዘነበ ወርቅ አካባቢ ነበር የሚኖረው። እዚያ ቤቱ ወስዶኝ ይንከባከበኝ ጀመር። መድኃኒቱን በአግባቡ እወስዳለሁ ጤናዬ እየተሻሻለልኝ መጣ። በዚህ ጊዜ ለምለም ተወልደ የሚያስፈልጉኝን መጻሕፍት ታመጣልኝ ጀመር። እነሮማንም ይመጣሉ ይጎበኙኛል። አንተም፣ ሰለሞን ደሬሳም ተመላልሶ የሚጠይቀኝ እዚያ ነው። ወይዘሮ ሱም፣ ተወልደም አገር ውስጥ ካሉ ማምሻቸው የእኔ መኝታ ቤት ነበር።

ጤናዬም ተመልሶ ሙሉ ለሙሉ መዳኔን ሲያይ አንድ ቀን ተወልደ «ስማ ስብሐት እኔ ከዚያ ሆስፒታል ሳወጣህ እዚህ እቤትህ መጥተህ ሙት ብዬ ነበር። እኔም ሆንኩ ዶክተሮቹ መሞትህን ነበር ያመንነው። አንተ ግን የሆነ ነገር አለህ። ድነሃል። ባትድን ኖሮ አልነግርህም ነበር» አለኝ። ተወልደ ልጆቹ ተወልዷ እያሉ ነው የሚጠሩት እልሃለሁ።

የሐና እናት ቪላ ቤት ለመኖሪያ ሰጥተውን ነበር፡፡ ይህንን ቤት በአሁኑ ጊዜ የማስመለሱ ሐሳብ የለኝም፡፡ ባለፈው ዓመት አሞኝ ተወልደ ቤት ሳለሁም አንድ የሐና አብሮ አደግ ጓደኛ ሊጠይቀኝ መጥቶ ቤቱን ለማስመለስ በመሯሯጥ ላይ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ አንድ ማመልከቻም ይዞ ነበር፡፡ ቤቱን የማልፈልገውና የወይዘሮ ሐና ይልማ ንብረት መሆኑን እንድፈርምለት የሚጠይቅ ነው፡፡ ፈረምኩለት፡፡ በአሁኑ ጊዜ ቤቱን ያረከቡት አይረከቡት ግን አላውቅም፡፡

ዓለም ፐብሊክ ሪሌሽን ቢሮን ለማቋቋም እኔ፣ ሐናና ደረጀ ሆነን ከባንክ ገንዘብ ተበድረን ባለሦስት ፎቅ ሕንፃ ሠራን። አሁን ሕንፃው

@Amharicbookstore



በደብረዘይት መንገድ ከጠመንጃ ያዥ ባንክ ፊት ለፊት ይገኛል። እኔ ለማስመለስ ሙከራ ያደረግኩበት ጊዜ የለም። በአንድ ወቅት ዜና መመለስ አለበት ብላ በማሰቧ ለሷ ስል አብረን ትንሽ ተንቀሳቀስን። ከእርሷ እረፍት በኋላ አልተከታተልኩትም። አሁን ማነው ያለበት? የአሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ሆኗል። ነው የምትለኝ? ባለቤቶቹ ናቸው የወረሱት ተዋቸው ይሥሩበት።»

ከ12 ዓመት በፊት፣ ይህንን መጽሐፍ ለማጠናቀቅ በምጣደፍበት ወቅት ጋሼ ስብሐት አዘውትሮ እሁድ ዕለት ሊጎበኘን ይመጣል። ምንጊዜም ከማለዳው ሦስት ሰዓት መድረሻው ነው። ከአቅሙ በላይ ካልሆነ አይቀርም። በ1992 ዓ.ም በታኅሣሥ ወር መጀመሪያ ባለችው ሰንበት ማለዳ መጥቶ ወግ ጀመርን።

«ዜና ከአንድ ጓደኛዋ ጋር አብራው ለመኖር ሄደች። እኔ ብቻዬን ሆንኩ። ኩኩን አክስቷ ማርታ ልታሳድጋት ወስዳታለች። የቤት ኪራዩ ደግሞ ተቆለለ። የቀድሞውን ትቼ እዚህ አንተ አካባቢ አንድ ክፍል ቤት ባገኝ ብቻዬን ስለሆንኩ ብከራይ ይበቃኛል።

«እዚህ እናንተ ግቢ ውስጥ 150 ብር የሚከራይ ቤት አለ? አሪፍ ነው። እከራየዋለሁ። ምንም አይደል። ከቤቴ ፊት ለፊት ሽንት ቤት መኖሩ... የእኔ አፍንጫ እኮ አያሸትም። ነገሬሃበሁ አዲስ አበባ ለእኔ ነው የተሠራ ችው። የሚታ ፀሐይ ቤቱ ውስጥ ይገባል። ይግባ እንደውም ፀሐይ ላይ አንድ ጥናት ማድረግ አለብኝ እያልኩ ሳብሰለስል 100 ዓመት ሞላው። አሁን ተገጣጠምን እኔና ፀሐይ። በል ቤቱ እንዳይያዝ አሁኑኑ ተከራይልኝ።»

በቅድሚያ የአንድ ወር ሂሳብ ከፈልን። አንዲት ፋምሊ አልጋ፣ አንድ ሦስት ሰው የሚያስቀምጥ ሶፋ፣ አንድ ሳጥን፣ የሻማ ማስቀመጫ እና የቡና ጠረጴዛ ይዞ መጥቶ ኑሮን ጋሼ ስብሐት ለአብ ጎረቤቴ ሆኖ መኖር ጀመረ።

በዚህ በቀሳቀስ ፍላጎት በሚኖርበት ዓለም ውስጥ ተሻምቶ መኖሩን ንቆ እንዲህ ዓይነት ቀላል ኑሮ ጀመረ። በንባብ ዓለም ይህንን ዓይነት ሕይወት ሊመርጥ የሚችል ሰው ቢጋራ አንድ ሰው እናውቃለን። ያም ሰው ማህትማ ጋንዲሂ ነው። በገሃዱ አለም ኑሮዬ ጋሼ ስብሐትን አወቅኩ። ቀለብ ተጋግዘን ሽምተን ቀርስ ምሳና ራት አብረን እንመገባለን።

እንበሳ የሚያክል ውሻ የዘብ ሥራውን በግቢያችን ውስጥ ያከናዳል። ይህ ውሻ ጋሼን እንዲለምደው ቅባት የነካካው አጥንትም ያለበት ፍትፍት በድስት አድርገን ሰጠነው። ጋሼ በር ላይ ድስቱን ይዞ ጠበቀው። ውሻው ተጠራ ከተፍ አለ።

«በሉ ድፉለት» አለች ፀሐይ።

«የምን መድፋት እንድንወዳጅ አትፈልጉም ማለት ነው?» አለና ጋሼ ስብሐት ለውሻው ድስቱን ዝቅ ሲያደርግለት፣ ውሻው በፍጥነት መመገብ ጀመረ::

«እንዴ ጋሼ ስብሐት ድስቴን አስለከፉብኝ» አለች ፀሐይ::

«ዝጊ! እኔም፣ አንቺም፣ ውሻውም የእግዜር ፍጥረት ነን::»

«ይገባኛል ድስቴ ግን ተለከፈ::»

«ጠበል ታስረጪዋለሽ!»

«ጆርሙስ?»

የጎንዮሽ እያየት «ውሃ አፍልተን እናጥበዋለን» አለ:: በእንዲህ መልኩ የቂርቆስ ሰፈርተኛ ሆነ::

ለዓመታት አብረን ኖርን ዜና መጥታ ትጠይቀዋለች:: ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ጠራኝና «ነግሬህ ነበር እኔ መርከብ ነኝ፡ ዜና ደግሞ መልህቁ ነች:: አሁን ወደ መካኒሳ አካባቢ ቤት ተከራይታ ጓደኛዋን አስፋው ሀብቴን አግብታው ልትኖር ነው:: እኔ አብሬያት እንድኖር ፈልጋለችና መቅዘፌ ነው» አለኝ::

እናም ከዐጁ ጋር ቀዘፈ::

***

@Amharicbookstore

፲፱

## ድብቋ ፍቅረኛ

ጋሼ ስብሐት ከእኔ ጋር ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ አንድ ግቢ ውስጥ አብረን ኖረናል:: እሱ ቤት ለመድረስ ማንኛውም ሰው በእኔ ደጅ ነው የሚያልፈው:: ስለሆነም በወታደራዊ ቋንቋ አላፊ አግዳሚውን ለመቆጣጠር ገዢ መሬት ላይ ነበርኩ:: አንዲት ወጣት አዘውትራ ትመጣ ነበር:: ስሟን ነግራኝ ተዋውቃኛለች:: በማስታወሻው ሥራዬ እንብባው ወዳው ስለነበር አመስግናኛለች:: ሁለት ሦስቴ ተገናኝተናል:: የሥጋ ዘመዱ ትመስለኝ ነበር:: አማርኛ ስትናገር ትግሪኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋዋ እንደሆነ ከአነጋገሯ ተረድቻለሁ:: ዕድሜዋ 25 ዓመት ቢሆናት ነው:: መኪናዋን ራቅ



አድርጋ አቁማ ወደ ግቢው ትዘልቃለች:: አዘውትራ መጠጥና ሽሚዝ እና ሌሎች ስጦታ ይዛለት ትመጣለች:: አንድ ቀን እኔ ከኋላዋ መኖሬን ሳታውቅ በር ላይ እንደቆመ ከንፈሩን ስትስመው አየሁ:: እንደመሰናበት ነው ወይስ ፍቅር? አልኩና ዜናን ጠየቅኳት «ተጣብሰው ነው» አለቺኝ:: ከብዙ ጊዜ በኋላ ነው ይህ የሆነው:: ስንበትበት ብሎ ምን አልባትም አንድ ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ ይህንን ግንኙነትን ጠየቅኩት::

"እህ ይኸውልህ ረስቻታለሁ... አይ እኔ እንግዲህ አሁን እየረሳኋት ነው:: ግን እንደማስታውሰው ከሆነ (ረጅም ፀጥታ አብሰለሰለ) ትዝ እያለኝ ነው:: ይኸውልህ አዎን አብረን ወጥተናል:: እሷ እንግዲህ ለገኒ 'ሬድሳል' ነበረች:: እዚህ መጥታ በመኪናዋ አሳፍራኝ ትወስደኛለች፡ ቤቷ ስንደርስ ብዙ አፓርትመንቶች አሉ:: የእሷና የቤተሰቦቿ ናቸው:: አንዱ አፓርትመንት ውስጥ የራሷ መኝታ ቤት አላት:: በነፃ የፈለገችውን ሰው የምታሳድርበት:: ስትወርድ ደግሞ ቡና ቤትና ቁርስ ቤት አለ:: ያ ሁሉ ስትመጣ እጅ መንሳት ሳይሆን የመውደድ ዓይነት ነው:: እንደ ገኒ ዓይነት ናት:: መሳሳም ቢኖርም አልተቃቀፍንም:: አብረን ስናድር ስንጫዋወት ስናወራ እኔም እሷም ደስ ብሎን ነው የምናድረው::

በጣም ሳቀ:: «ፍቅር ፍቅር የሚታይህ እናት ብዙ ዓመት ያልሞላው ልጅዋን ስታጠባ ስታይ ነው:: ፍቅር ወለል ብሎ የሚታይህ:: በጉልምስና በዚህ በዚህ ብለን ከተነተንነው እኔና አንተ ወንድ ነን እነሱ ሴት ናቸው:: በቃ መፈላለግ ነው:: ይኼ ነው:: ደግሞ እግዜሩ ዘር ሲዘራ ወጣ:: እኛ የለንበትም:: ድንገት ስታድግ ታገኘዋለህ:: ወንድ ነኝ ሴት ይፈሊጋል እንጂ እኔ የለሁበትም:: የምታፈቅረኝን እስካገኝ እፈልጋለሁ:: ዕድለኛ ስለሆንኩ ደግሞ ባስፈለገኝ ጊዜ አግኝቻለሁ:: ከእዚህች ከወይዘሪት እገሊት ጋርም አፓርትመንቱ ውስጥ ስንሳሳም ትዝ ይለኛል:: የእኔን ሥዕል ወስዳለች:: ማን የሳለውን? እንኳንም ወሰደችው ይገባታል::

***

ኸ

# እነሆ ባህር ማዶ መሻገሩ ቁርጥ ሆነ

ትዕግስት ወልደየስ (ቲጂ) በዩኤስ አሜሪካ የእኔን ሥራ ማንበብ የምትወድ ነች። አብሮ አደግ ጓደኛዋ ወይዘሮ *ገነት ታደሰ ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት ለመንዝ ማሰቧን ለጓደኛዋ ትፈፋት ታወጋታለች። ትፈፋትም «ስብሐት ገብረእግዚአብሔር የሚባል ደራሲ አለ። አዲስ አበባ እንደገባሽ አግኝተሽው ደህንነቱን ጠይቀሽ ደውይልኝ» ትላታለች።

ቲጂ ብቻ ሳትሆን ስገምት ለእኔና ለገኒ ማገኙነት የጃርሶም እጅ ሳይኖርበት አይቀርም። ጃርሶ ሞት ባይኖር ከፋቤል በሆነ ቦታ አንብቦኝ መሆን አለበት እሷ ወደ እዚህ ስትመጣ ይልካታል። ሽርኩ ናት። በጣም በጣም ገንዘብም እየላከችለት ከኢንግላንድ እሷ ወዳለችበት ስዊዝ ታስመጣዋለች። ስለሚናፍቃት ስለምትናፍቀው። ወደእዚህ ስትመጣ እንደልማድዋ «ስብሐትን ሳታገኚው እንዳትመጪ በቃ አለበለዚያ እንጣላለን» ብሏት ይሆናል። አበሻ ከአንጀቱ ሲያስጠነቅቅ እንዲህ ነው የሚለው።

«ከመምጣቴ በፊት አውቅ ነበር። እኔና አንተ እንደምንፋቀር» አለችኝ ገነት። አመንኳት። ሌሎች ነገሮች ደግሞ አስቀድማ ታውቃለች። እንዲህ ዓይነት ፀጋ አላት። ብዙ ሰው ናት። አደራውን ተቀብላ ወደ አዲስ አበባ የመጣችው ገነት ከእኔ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዱ አበበ ቤት ተገናኝተን ተጨዋወትን። ከከባችን ገጠመ።

«እኔም ሆንኩኝ ባለቤቴ ስዊዝ ብንጋብዝህ እንግዳችን መሆን ትፈቅዳለህ?» አለች ገነት።

«ደስታው ይገለኛል» መለስኩ።

ወደ ስዊዝ እየሄድኩ ነው፤ ለእረፍት ልውሰድህ ነው የምትለኝ እንግዲህ። ቅዱስ አለ፤ የልጄ የዜና ልጅ ገና ስምንት ወሩ ነው። ቢያንስ

@Amharicbookstore



እስከሚቀጥለው ዓመት ለቅዱስ እኔ አስፈልገዋለሁ የሕይወት መሠረት ላይ ስለሆንን። የዛሬ ዓመት ግን ደስ እያለኝ እሄዳለሁ አልኳት።

ከባሏ ጋር በኋላ ተዋወቅን። እንዴት ያለ ግሩም ሰው ነው። የእውነት ሰው ነው የምለው ሰው ነው። ታሪኩን ገነት አስቀድማ ነግራኛለች። እንዴት ያለ ድንቅ ሰው እንደሆነ። እዚህ አዲስ አበባ *ሊዮ ተልስቶይ ይመጣል። ለሥራ ማለት ነው። ከዚያም ወደ ደብረ ብርሃን ይዘልቃል። በድርቁ በችግሩ ዘመን መሆን አለበት። ሕፃናትን ሲረዳ ቆይቶ በኀዘን ብዛት ለሁለት ቀን እህል መብላት አልቻለም።

በኋላ ሊዮን አግኝቼው ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደመጣ ጠይቄው ነበር። «እንደምታውቀው ስዊዝ ሁሉም ነገር በፕሮግራም ነው፤ ሦስት አገሮችን ሄጄ መሥራት ምርጫ ነበረኝ። ሁሉም አልተሳካልኝም። ወደ ኢትዮጵያ ተላኩ። በኋላ ሳስበው ምርጫዬ ቢቃና ኖሮ ገነትን አላገባም፤ እነዚህን የምንወዳቸውን ሦስት ልጆቼን አልወልድም ነበር። ስለዚህ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ከእነዚህ በረከቶቼ አኳያ አግባብ ነው» ብሎኛል።

እዚህ ተገናኘን አይደል? ገነትን ስናቆላምጣት ገኒ ነው የምንላት። ገኒ ብቻ ናት እስከ ዛሬ ድረስ የፈለገችውን እንዳደርግ የምታዘኝ። እኔ የባላገር ልጅ ነኝ። የባላገር ልጅ ዓመት በአል ሲደርስ ነው አካላቱን ወንዝ ወርዶ የሚታጠበው። እኔም አሁን ብዙ የሚያልብ ሥራ ስለሌለብኝ አልታጠብም። ከእሷ ጋር ከገጠምኩ በኋላ በየቀኑ አካላቴን ታጥበኛለች። ደስ እያለኝ ነው የምታጠብላት፤ በአለባበሴም ታዘንጠኛለች። እንደዚህ እንግዲህ የሰው ሰው ሆነህ ስታየው እንዴት ደስ ይላል መሰለህ? ድሮ ሰው ሲያጎርሰኝ አልወድም፤ አሁን እሷ ነች የምታጎርሰኝ። አስገዳጅ ባህል ውስጥ ካልሆንኩኝ እኔ ከሰው እጅ አልጎርስም። እሷ ስታጎርሰኝ ለመድኩትና እንዲያውም በገዛ እጄ ቆርሶ መብላቱን ተውኩት።

እዚህ ጓደኝነት ውስጥ እንግዲህ አብሮ አደጎቼ አሉ። አንዷ ቱቱ ነች። ቱቱ ከጓደኝነት የበለጠ ሳቅ የምታስቀኝ ነች። የቀልድ ንግሥት ልልህ እችላለሁ ሌላዋ ራሔል ናት። ሦስቱ እና እኔ መደሰት አብረን መዝናናት ጀመርን። ሰፈሯ ደግሞ ቀጨኔ ሦስት ራስታዎች አሉ። የእሷ ጀለሶች ናቸው። ትደውልና «ይድኔ!» ይድኔቃቸው ማለት ነው «ቾሬ አለወይ? ልልከው ፈልጌ?» ስትለው «እኔ አለሁ አይደለም እንዴ?» ይላትና በመኪና ሄዶ ምን ብሎ የፈለገችውን ያመጣላታል። እሷ ቀጭ ብላ መዘነጥ ብቻ ነው።

እኔና እሷ የምንመሳሰለው ሁለታችንም ከሰው ጋር እንግባባለን። የግድ ካልሆነ በፍቅር መግባባት ነው ሸጣችን። እሷ ወዲያውኑ ነው የምትግባባው። የእኔ ባህሪ ቀስ ብሎ ነው። ለምሳሌ ወደ ደቡብ ለሽርሽር ሄደን

ነበር እስከ አዋሳ። አንዱ ራስታ እየነዳ ነው። አብሮን ይገፈማቸው አለ። ከዚህ እስከ እዚህ ድረስ ስንሄድ የሚያጋጥሙን የሚገርሙ ነገሮች ናቸው።

አንድ ሰውዬ አገኘነው። በጣም ደስ አለው መስፍኔ ነው የምትለው። ከባሏ ጋር፣ ባሏ ሳይሆን በፊት ብዙ ፕሮፌሽናል ግንኙነት አላቸው። መስፍኔ 'ጂኒየስ' ነው። ውሃን ለአልግሎት ማብቃት ሲችል 80 ሚሊዮን ብሮች እንደዚህ የሚፈጀውን እሱ በስምንት ሚሊዮን መሥራት የሚችል ነው።

መስፍኔን ስናገኘው እየተጨዋወትን በእርሱ ወጪ ሆነ የምንሄደው እንግዲህ ስንቀጥል ደግሞ ገኒ ሰው ታምናለች። አምና ሰጥታ ትናደዳለች። ወኪልነት። የባንክ ደብተሯ ሁሉ ሳይቀር ሰው ሲሸፍጣት ሲሸፍጣት አይቶ መስፍኔ ሊጠብቃት ሊከላከላት ወሰነ። እንደ ችግር ሊገጥማት ሲል 'ፋክስ' አደረገላት። «ቶሎ ውክልናውን አዛውሪ» አላት። አዛወረች። ሰው ያድናል። እሷ ደግሞ ሄዳ ሰው ነው የምታድነው።

አንድ ምግብ ቤት ገባን ቁጭ አልን። ሰው ሁሉ እ እ እ እ አለኝ። (እከብሮችና አድናቆታቸውን ገለጹልኝ ለማለት ነው እ እ አለኝ የሚለን) ሁለቱ አስተናጋጆች ቆመዋል ከማዶ አንዱ እንዲህ ደፋ ብሏል ጭንቅላቱ።

«ምንድነው? የእኔ ወንድም ና እስኪ ማነው ስምህ ምንድነው? አንገት መስበር ቀና ቀና በል እንጂ አብረን እንደሰት» ስትላቸው። ስማቸውን ሰው ስጠቀላቸው ሰው ስለሆኑ በቃ ተለወጡ። እንደዚህ አይነት ተአምር የምትሠራ ነች ገኒ። አብሬያት እየሄድኩ ነበረ መደሰት መገረም ብቻ። እኔ ላይ የምታደርገውን ተአምር አይተሃል እንግዲህ። ስዊዝ ውስጥ የቤት እመቤት ናት። ይሁን እንጂ ቤት ውስጥ ምን አልባት ሦስት አሽከር የሚያሻውን ሥራ ትሠራለች። የዚያኑ ያህል ብዙ 'ኢነርጂ' አላት።

እንደ ከባልዋ ጋር የሚለያዩም አይደለም። እንዳቸው ካልሞቱ እሷ ቅዱስ ሰው ናት አላልኩህም። እሷ ደግሞ እሱ ነው ቅዱስ ሰው ትላለች። ባልዋ ሊዮ ይባላል ፈረንጅ ጀርመን ስዊዝ ነው ዜግነቱ። ቀደም ብሎ እንደነገርኩህ አገራችን ውስጥ ነው 'የተጣበሱት።' እሷ እንግዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሁ ሲተያዩ ደስ አላት። ልጋብዝሽ ሲላት እሺ ብላ በባቡር እየሄደች ጫት እየቃመች ነው የምትሔደው። እዚያ ስትደርስ ምርቃናዬን እንዳያውቅብኝ ብላ ተጉመጥምጣ ስትወርድ እሱ ትልቅ 'ተግዚና' ወጥሮ ጠበቃት።

ሦስት ልጆች አሏቸው ሁለት ሴቶች አንድ ወንድ፣ አንድ ወንድና ሴት ልጃቸው አብረዋቸው ስዊዝ ሲኖሩ ሌላዋ ሴት ልጅዋ አሜሪካን አገር እየኖረች በችሎታዋም የቴኒስ ሻምፒዮን ናት። የተቀሩት አንድ ላይ ነው

@Amharicbookstore



የሚኖሩት። እዚህ ደግሞ አገሯ መኖሪያ ቤት ሰላላት ትመላለሳለች። እኔ በዚህ ነው የሸማኔ መመርመሪያ ያልኳት።

ቤተሰብ ግን እንቆጣጠርሽ አላት። ለምን አመሸሽ? ለምን ከእነእገሌ ጋር ሄድሽ? ምናምን ምናምን ጭቅጭቅ መጣ። አባቷ ሲገልጽዋት ራስታ ጓደኞቿን «እራሳቸው ላይ የፈረስ ጭራ የሚጎነጉኑ አሁን እነሱ ምን ሊያደርጉላት ነው?» አሉ እንግዲህ ጓደኛዋን ይመርጡላታል በ43 ዓመቷ።

ይሄ ይሄ ስላስጨነቃት በቃ እንሂድ ብለን ስደት ሄድን። እየሳቅን ስደታችን እስከ አዋሳ ሆነ። በጣም ቆንጆ ጊዜ ላንጋኖ አሳለፍን። የሆቴሉ ባለቤት መጣና እጅ እንደመንሳት አለና «እርሶን እዚህ መቀበል ትልቅ ክብር ነው» አለኝ። «እሺ thank you ደግሞ በጣም ቆንጆ ነው ቤቱ ምኑ ሁለመናው አያየዙ ደስ ይላል» ስለው «ደግማቸሁ ኑ » አለኝ።

«እሺ በቃ ተወኝ በጣም ደስ እንዲለኝ ዝም ብለን 'ሪላክስ' እናድርግ ከሆነ በቃ አታመስግነኝ። አብረን እንጫወት» ስለው፡

«ደስ ይለኛል» አለ።

ከእዚያ ምንም ሳንከፍል አደርን፤ ሰውዬው ሰዩም ነው ስሙ። አዲስ የሚጀምር ባለሆቴል ነው።

ብዙ ቦታ እንደዚህ ገኒ ስትሄድ በጣም 'ፖዘቲቭ' ስለሆነች የትም ቦታ ታዛለች የፍቅር ማዘዝ፡ እናም የገንዘብ።

ወንዶች ሽማኔ ሆነው ለሴቶች ይመቻሉ ወይ ነው ያልከኝ? ይህንን የራሴን ነው ልነግርህ የምችለው። ገኒ ለእኔ በጣም ነው የምትመቸኝ፡ እኔም እመቻታለሁ። ለምሳሌ ቆመን ስንደንስ እንዲህ ስታቅፈን በቃ እንደታቀፍኩ ነው አለቀ። እኔ ደግሞ ያኔ የት እንዳለሁም አላውቅም። አንቺን እንዳቀፍኩ ብቻ ነው የማውቀው። ዳንስ ቤቶች ሄደናል። አንዱ ጋ «ለደራሲ ስብሐት እኔ እዘፍናለሁ።» ስለ አንዱ አቀነቀኝ።

ባቴ ላይ የምታየው ቀለበቶች የገኒ ናቸው። ከጓደኞቿ ጋር እያለን ስንስቅ ስንስቅ አስታውሳለሁ መርቅነናል። ቢያንስ ከሦስታችን አንዳችን አይመረቅንም እኮ። ማለት አትቅምም ነበር። ስንጫወት ወይም ጨብሰ አልያም ዳንስ ላይ እያለን «እንደ በቃ እንጋባ እንጂ» ተባባልን እኔና ገኒ።

«እንጋባ። እናንተም ሚዜዎቼ ናችሁ አለቻቸው። ሚዜ ሆኑና አለበሷት። በቃ ይህንን ቀለበት አደረገችልኝ። ይህንንም ጆሮዬ ላይ ያደረግኩትን ሎቲ እሷ ነች ያደረገችልኝ። ይህንን መስቀሉን ስፈልግ አንቺን ሳስታውስ እንዲህ እንድይዘው አልኳትና ሰጠቺኝ አንገቴ ላይ አጠለቅሁት።» አለ መስቀሉን በመዳፉ እየጨበጠ።

የአገር ውስጥ ስደታችን ቀጥሎ አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ሆቴል ቤት መኝታ 150 ብር ተከራይተን አብረን ኖርን። ጓደኞቿም እየጎበኙን ሳቃችን ቀጠለች።

የሃይማኖት መጻሕፍትን እኔ ከእሷ እኩል የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም። ምን አልባት ኤልያስ አወቀ የእሷን ያህል የእኛ አገር ታሪክ ያውቃል። የእሷ ግን ይበልጥ ይመስለኛል። ሰው ትወዳለች። ሰው ሁሉ የእሷ ነው። ርህራሄዋን ሳሳይህ አንድ ደምለው የሚባል ወጣት አለ። ደምለው ብጉንጅ ያዘው፤ ብጉንጅ ደግሞ ይመዘምዛል። እያሠሠው እንዳይቆይ ጎንት ሳታደርግ በባዶ እጅዋ ቶሎ ብላ አፈረጠችለት በኋላ በሳሙናና በውሃ ታጠበች። ምንም አትፈራም። እ ምን ትላለች? «አዲስ ነገር እኮ መጀመሪያ ብቻ ነው የሚያቅተው እንጂ ከዚያ በኋላ እንችለዋለን። የማንችለው ነገር የለም» ነው የምትለው። ደግሞ ይሄ ደምለው ሄዶ እንዲመረመር የሕክምና ስፔሻሊስት ጋ ላከችው። ደውላ የአክስቷ ልጅ አለች ሐኪም ጠየቀቻት። አማርኛ ላከችው። ቀናት ደግሞ። ቢቆይ ኖሮ ሐኪሙ ጋ ሳይደርስ ቢቀር ይህ ደምለው ሟች ሊሆን ይችል ነበር። ደግሞ የሆነ ነገር ይነግራታል። ምን ማድረግ እንዳለባት።

አሁን አውሮፓ ሄዳለች። አሁን ለገኒ ደብዳቤ እየጻፍኩላት ነው። ቀደም ብሎ አንዱን ስንዱ አበበ ልካዋለች። አንዱ አልተላከም። ከፈለግክ ታነበዋለህ። ትጫወታለህ እኮ ከምትወደው ጋር አንደ. ስንጫወት ለገኒ የነገርኳት ነው። አሁን አንቺ እንደ ሎተሪ ነው የደረሽኝ። በዚህ ዕድሜ አብቅተናል። እኔ እንደውም ለራሴ የልጆቼ እናት የትምወርቅ ከሞተች በኋላ ከሴት ጋር መሆን አያምረኝም። አልተቃቀፍኩም። ለእሷ ሐቀኛ ሆኜ ምናምን አይደለም። ስላላሰኘኝ ነው። ቢያሰኘኝ እንኳን ለደደበም የትምወርቅ ሞቷ እያለችም አልምርም ነበር። ... እውነት ነው አስደሰትሽኝ ማለት እኮ ነው።

አሁን ገኒ አውሮፓ ነች። እንዳልኩህ ስትናፍቀኝ ይህንን መስቀል (አንገቱ ላይ ያጠለቀውን) በመዳፌ እጨብጠዋለሁ። በቅርብ አንድ የሥነ ልቦና ችግር ደረሰባት። «ቶሎ ና» አለችኝ። ተጉዤ ከአጠገቧም ሆኜ ሳረጋጋት እነሆ ለመሔድ ወሰኛለሁ። በወጣትነቴ የማውቃትን አውሮፓ እነሆ በአዛውንትነቴም ይህ ዕድል ደርሶኝ ገኒንና ቤተሰቧን መጎብኘቴ ቁርጥ ሆነ ሁሉንም ወጪዬን የምትችለኝ ገኒ ነች።

***

@Amharicbookstore



*የወይዘሮ ገነት እና የባለቤቷ፣ የጓደኞቿ ስሞች ተቀይረዋል። ልጆቿ ጋሼ ስብሐት ታሞ በነበረበት ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበሩ ሊጠይቁት ሃሌሉያ ክሊኒክ መጥተው ነበር። በወቅቱ ጋሼ ስብሐት ጥልቅ እንቅልፍ ላይ ስለነበር መቀስቀሱን ጠልተው መልዕክት ትተውለት ሄዱ። እንደነቃ መልዕክቱ ሲደርሰው በጣም ተቆጨ። ከዚህ በኋላ ሲመጡ ቤተኛ እንዲሁ እንዲቀሰቅሱት ለአስተማማኞቹ ተናገረ፤ ይሁን እንጂ ልጆቹም ምልክታቸው በድጋሚ ላልመጡም። እሱም እንደናፈቃቸው ለዘለዓለሙ አሸለበ።*

***

## ፳፩

## ስዊዝ

በአሁኑ የአዛውንትነት ዕድሜዬ ወደ ውጪ አገር መሄድ አስቤም አላውቅም። ሰው የእግዜር መልዕክተኛ ነው። ሌላ ሰው አስቦት ይህንን ሲያሳየኝ የሚደንቅ ነው። በእግዜር ካላመንኩ ልክ አላመንኩም ወይም የፎረሸኩ ነው የሚሆነው።

ከሠራት በፊት ከአገሬ ስወጣ አየር ማረፊያውን ዝግ እያልኩ በመራመድ ሳቋርጥ ሁለት ነገሮችን አስብ ነበር። አንደኛው ቅዱስን ነበር። ቀደም ብዬ እንዳልኩት ቅዱስ የልጅ ልጅ ነው። በጣም ተላምደናል። አሁን ርቄ ስሔድ ምን ይሆን ይሆን? ስል አስቤዋለሁ። ግን እመለሳለሁ እኮ እለዋለሁ እራሴን። ቢበዛ ሣምንት ትዝ ብለው ነው። ከዚያማ ካቀፈው ሰው ጋር ኑሮአቸውን ይቀጥላሉ።

ወደምሄድበት ሃሳቤ ሄደ። የምታስተናግደኝ ወይዘሮ ገነት ታደሰ ባለቤቷን ሊዮ ተልስቶይን አስብኩ። ሁለት ልጆች አሏቸው። ገነት እንዳጫወተችኝ ከሆነ ሰተት ብዬ ገብቼ ቤተኛ መሆን ነው። ግን ደግሞ ከእነሱ መካከል አንዱን ብደብረውስ? መቼም እንግዳ ለሦስት ቀን ነው ክብር የሚሆነው። ከዚያስ እያልኩ ከራሴ ጋር እየተጨዋወትኩ አገሬን ትቼ ሄድኩ።

በረራው ቀጠለ። የምናልፈው በካይሮ በኩል ነው። ሁሌም ባለፍኳት ቁጥር የምጓጓላትን ከተማ ከሰማይ ላይም ቢሆን ቅልቅል አያታለሁ እያልኩ አስብ ነበር። ይሁን እንጂ እንዳለመታደል ከተማዋ ላይ ሳናርፍባት በጨለማ

በአየር ላይ አለፍኳት፡፡ ይህቺ ካይሮ እስከ መቼ ይሆን ሰንቀልልጬ እያለችኝ የምኖረው?

ቀደም ብሎ ከአገሬ ከወጣሁ ግፋ ቢል 40 ዓመታት አልፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ እስካሁን ምንም ግር ያለኝ ነገር የለም፡፡ ባረፍኩበት ቦታ ሁሉ አማልክቱ የሚያግዙኝን ሰው ይልኩልኛል፡፡ ይጠይቁኛል የምፈልገውን እነግራቸዋለሁ፡፡ የሚገርመው የያዝኩትን ቁሳቁስ ሁሉ በመሸከም ጋሪ ላይ በመጫን አግዘውኛል፡፡ አንዱማ ፈረንጅ ተጠጋኝና በአማርኛ «ወዴት ነው የሚሄዱት?» አለኝ፡፡ ተመልከቱ አማልክቱ የት ድረስ ጥላ ከለላዬ እንደሆኑኝ፡ ለእነሱ ኃላፊነቱን ሰጥቼ ጉዞዬን ቀጠልኩ ችግር የለም፣ መደናበር የለም፣ ሰተት ብዬ አውሮፓ ገባሁ፡፡ ይህንን ያህል የሚቀናው ብዙ ሰው እኮ አይኖርም፡፡ እኔን ወይ ከነቤ ነው አለበለዚያም ዕድሜዬ አግዞኝ ያጋጠሙኝ ሰዎች ሁሉ እያገዙኝ አለምኩበት ደረስኩ፡፡ ይህንን መራራት በራሴ ሳየው ደስ አለኝ፡፡ ከዚህ ከአገራችን ስነሳ ቀለል ያለ አለባበስ ለብሼ ነው አውሮፓ የገባሁት፡፡ ያ አለባበሴ ደግሞ ለእዚያኛው የአየር ሁኔታ የሚስማማ ነበር፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሰምርልኝ፣ በደረስኩበት ሰው በፍቅር ሲቀበለኝ፤ አየሩም እንዲስማማኝ ሲሆን ጊዜ በሆዴ የእግዜር እጅ አለበት አልኩ፡፡ የአውሮፓ ፀሐይ እንዳለች አለች በዚህ መልኩ ድንቅ የአየር ሁኔታ፤ ድንቅ መስተንግዶ ጠበቀኝ፡፡

እንግዳ በሆንኩበት ቤተሰብ መደባበር የለም፡፡ ድብርት ከየት መጥቶ? ሁላችንም በጣም ተግባባን፡ ልጆቹም በጣም ሸርካቼ ሆኑ፡፡ ባለቤቷ ሊዮ የማነባቸውን አሪፍ አሪፍ መጻሕፍት አሰናዳልኝ፡፡ የምጎበኛቸውን ሙዚየሞች እርሱ ነው የሚያቅድልኝ፡፡ የበረዶ ሸርተቴም ተጫውቻለሁ፡፡ ለክስ እኔን ለመቀበል ነው ፀሐይዋ የዘገየችው፡፡ ትንሽ ቆይቶ የበረዶው ጊዜ መጣ፡፡ የዚያኔ እኔም በኩሽኒታ በሚነዳ የበረዶ ሸርተቴ ተጫወትኩ፡፡ እቤት ውስጥም አካል ለማጠንከር የሚነዳ ብስክሌት አለ፡፡ ቢጋልቡትም ብስክሌቱ አይንቀሳቀስም፡፡ ስዚያው ደገሸራፀ፤ እሱንም ነዳሁ፡፡

ከዚህ ልምምድ በኋላ የበረዶ ሸርተቴ እንድጫወት ያዘጋጅልኛል፡፡ ከላይ መንሸራተት ነው፡፡ እሷ ``እንዳታንሸራትተው ይጎዳል`` ብላ ትወተውተዋለች፡፡ በሌላ ጎኑ ስትጠብቀኝ ነው፡፡ እኔ ደግሞ እችላለሁ እላለሁ፡፡ ያንሸራትተኛል፡፡ እየጠበቀኝ፡፡ ባልዋ ትልቅ መልአክ ነበር፡፡

ከሊዮ ጋር በከተማው ውስጥ ስንሸራሸር የእያንዳንዱን ቦታ ስያሜ ታሪክ ይነግረኛል፡፡ የእነሱ ነፃ አውጪ አርበኛ ዊሊያም ቴል ይባላል፡፡ እያንዳንዱን ፍልሚያ ተጋድሎ ያጫውተኛል፡፡ በአጠቃላይ ሊዮ 'ፐርፌክት ጋይድ' ነው፡፡

@Amharicbookstore



አዎን አንድ ቀን ጠፍቻለሁ፡፡ ትንባሆ ልገዛ ነው ከቤት የወጣሁት፡፡ ስሄድ ባመኝ ቀይ እዚያ ጋ ስደርስ እመለሳለሁ ስል ስሄድ ደከመኝ አረፍ ብዬ ልብ ብዬ፣ ሳስተውል ለካንስ ጠፍቻለሁ፡፡ አላፊ አግዳሚውን ስልክ ጠየቅኩ፡፡ የሚገርመው የእነ ገነትንም ስልክ አላውቀውም፡፡ ፖሊስ ጣቢያ ጠየቅኩ፡፡ አሳዬኝና ለፖሊሶቹ ችግሬን ነገርኳቸው፡፡ ስልክ ማውጫ ላይ ተፈለገ፡፡ በብዙ ድካም አድራሻው ተገኘና ተደወለ፡፡ ስልኩን ያነሳችው የገነት ሴት ልጅ ነች፡፡

«አዎን ጠፍተብናል በታክሲ ብትልኩት ገንዘቡን እንከፍልለታለን» አለች፡፡ ታክሲ አስቆሙና በታውን ነግረውት ሸኙኝ፡፡ ሾፌሩም በሰላም አደረሰኝ፡፡ የዚያን ዕለት አጠፋፌ ግን ግማሽ መጥፋት ግማሽ ጉብኝት ነበር፡፡

በአገሪቱ በየትኛውም አቅጣጫ ቢዞር ተራሮች አሉ፡፡ ጠዋትና ማታ ብርሃን ሲቀባበሉ ተራሮቹን ማየት ማራኪ ነው፡፡ ትናንት ያየሁት መሆኑን ሳላምን ዛሬም አየዋለሁ፡፡ አልፕስ ተራራ እዚያ ነው ያለው፡፡ በዓለም ረጃጅም ከሚባሉት ተራራዎች አንዱ ነው፡፡ እዚያ ተራራ ላይ የተሠራ ሆቴል አለ፡፡ ልጎበኘው ሄድኩ፡፡ ድሮ ጀምስ ቦንድ ፊልም ሠርቶበታል፡፡ ድንቅ ነው፡፡ ሆቴሉ ውስጥ ቁጭ ብዬ እየተሽከረከረ ዙሪያውን ጎበኘሁ፡፡

የየዕለቱ 'ፕሮግራሜ? እንደልቤ እተኛለሁ፡፡ እንደነቃሁ እነሳና እጽፋለሁ፣ ወይ አነባለሁ፣ እጎበኛለሁ፡፡ ይኸውልህ አውሮፓን እንደዚህ ዘንጥኩባት፡፡

ሸይጣን በካፒታሊዝም ዓለም ውስጥ ገነትን እንሥራት ብሎ እንደሸወዳቸው ከዓመታት በፊት ጽፌያለሁ፡፡ በእርግጥም ከጉብኝቴ እንዳስተዋልኩት ገነትን ምድር ላይ ሠርተዋታል፡፡ የሚገርመው እየኖሩባትም ነው፡፡ አሁን ሄጄ ሳየው እንዲህ አስተዋልኩኝ፡፡ ስዊዞች ሴቷ ካረገዘች ጀምሮ እስክትወልድ አቅም ባይኖራት ቤተሰቡን መንግሥት ያግዛል፡ ማዋለዱን፡፡ ከወለደች በኋላ ወጪውን ምናምኑን ሁሉ ይመዘግባሉ፡፡

ልጁ ወይም ልጅቱ ይወለዳሉ፣ ያድጋሉ፣ ይማሩና ሥራ ይዘው ራሳቸውን እስኪችሉ ይጠብቃል፡፡ ከዚያም ወጣቶቹ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሸምተው ከተቋቋሙ በኋላ በገቢያቸው መጠን እዳቸውን መክፈል ይጀምራሉ፡፡ ይህንን ሁሉ ለማድረግ ስዊዝ እውነቱን እኮ ነው የዓለም ሰዓት የሆነው፡፡ ሁሉም ነገር በሰዓት ነው፡፡ በዚህ ተዋጥቶላቸዋል፡፡

ግንኙነቱ እንደልብ አይደለም (ዘመድ ዘመዱን መጠየቅ) እነሱ በጌታ ልደት ወይም የተሻለ ሕይወት የሚኖሩ ከሆነ በዊልያም ቴል የስዊዝ ነፃ አውጪ የልደት ቀን ነው የሚገናኙት፡፡ ከዚያ ለየብቻቸው ነው ኑሮን

የሚኖሩት:: ሸወዳዋ የምትወጣው እዚህ.ጋ ነው:: ለየብቻ እየተሆነ ከኑሮ ጋር ግብ ግብ ይያያዛል:: በዓመት ውስጥ ከላይ በጠቀስኳቸው ሁለት ቀናት በስተቀር የቀሩት ለብቻ ነው የሚኖሩት:: ይኸው ሰይጣን ግብሩን ማስከፈል ጀመረ:: በመኖር መንገድ እየሄዱ እየሄዱ ባል ወይም ሚስት ከሁለት አንዱ ይሞታሉ:: ያልሞተው ብቻውን ይቀራል:: በአንድ አፍታ ያረጅና ጭርጭስ ይላል:: እንዴ? እንዴት ብቻውን ይሆናል ብሎ የሚደርስለት የለም::

እኛ አገር 'ውሃ የሚያጣጣው አጥቶ ሞተ' ይባላል:: እዚያኛው ዓለም ላይ እንዲህ አይነቱ ችግር ይደርሳል:: ከዚህ ጋር ደግሞ የ70 ዓመት የ74 ዓመት ሚስቱን ትቶ ከሌላ ጋር ፍቅር ይይዘዋል:: ወዲያ "ቻው! ቤቢ!" ብሏት የሚሄድም አለ:: ዕድሜው ሲረዝም የፍቅር 'አድቬንቸር' የሚጥመው አለ::

ቆነጃጅት ብትል ፈረንጅ አገር በጣም ቆንጆ ይፈጠራል:: ተዋናይም ስለሚሆኑ ድፍን ፈረንጅ ቆንጆ ይመስለናል:: ግን እኮ ሁሉም ቦታ ቆንጆም ፉንጋም አለ:: ለምሣሌ አዲስ አበባ ውስጥ 20 ውብ ልጆች መንገድ ላይ ብናይ እዚያ ሁለት ወይም አንድ ብታይ ነው:: ይህ እንግዲህ በእኛ የዓይን ሚዛን ነው:: ይኼኑ እነርሱ ወደ እኛ ሲመጡ የእኛ ቅርፅ ብዙም ላይማርካቸው ይችላል:: ለእኔ ከፈረንጅ ውበት ዓይናቸውና ፀጉራቸው ይስበኛል::

ልዩ ልዩ ውብ ቀለማት አላቸው:: ሕዝብ ከባዕድ ጋር ያለው፣ ቅርርቡ እጅግም አይስታውቅም:: ግን ቀደም ብዬ በአውሮጋም በአሜሪካም ያላጋጠመኝ በመንገድ ስትተላለፍ "ሩትስር" ይሉሃል ሰላም እንደማለት ነው:: እኔ ባላየውም ይለኛል ሆሬ ምላሹን እሰጣለሁ::

እዚያ አገር መሬህ ክልክል ነው:: አንድ የሲሪላንካ ሰው ዘመድ ሞቶበት ድንገት ነገሩት:: ለካስ ሲሪላንካውያን ባህላቸው እንደ እኛ አገር ነው:: "እገሌ ሞተ" ሲሉት ሰውዬው ጩኸቱን አቀለጠው:: በአገሩ ደግሞ መሬህ በሕግ የታገደ ነው:: ወሰዱና አሠሩት ተገቢውንም ፍርድ ሰጡት:: ወዮ ልጄ! ወዮ ወንድሜ! የለም:: በስዊዝ ሐዘንን ዋጥ ማድረግ ነው::

አበሻ የትም ቢሆን ያው ነው:: ስደት ላይ ሲሆን፣ የራሱ ብሶት ስለሚበዛበት እየባሰ ይሄዳል:: ናፍቆቱ ምኑ ምኑ ግማሽ መንገድ አበላሽቷቸዋል:: በዚያ መሐል ደግሞ የሚደንቁ ምንም ይህ ነገር የማይነካካቸው አሪፍ የእኛንም ሰዎችንም አግኝቻለሁ:: ቁጥራቸው ያንሳል ግን ግድ ነው::

ክፍሌ ተካ፣ ኃይሉ ሱዛን የሚባሉ ሰዎች ጄኔቫ ውስጥ አዳራሽ ተከራይተው ራት ግብዣ ተደረገልኝ:: በጣም አሪፍ ግብዣ ነበር:: ከእኔ መጻሕፍት የተወሰኑት ያንተን ማስታወሻ አስተዋወቁ:: እዚህ ግብዣ ላይ

@Amaricbookstore



በተፈሪ መኮንን የትምህርት ቤት ጓደኞቼ የነበረውን አገኘሁት፤ ደስ ብሎን ተጫወትን:: ንግግር ሁሉ አደረግሁ:: ሐሳቡን አላስታውሰውም:: አንዱ ነሸጠውና 20 ፍራንክ ሸለመኝ:: እኔም አመሰግናለሁ ይኸው በወከላችሁት አማካኝነት ሽልማታችሁ ደርሶኛል:: አልኩና አጫውቻቸው ከመድረክ ላይ ወረድኩ::

ኢትዮጵያውያን ልጆች የአገራችንን ቋንቋ አማርኛ የሚማሩበትን ባሕል ማዕከል ተጋብዤ ነበርሁ:: ልጆቹም አጫውተን ብለውኝ ስለ እያ ድብልብሉ አወራሁላቸው:: እናቶቻቸው በማዕከሉ ተጋብዘው ስለነበር ተረቱ ግቡን መትቶ ነበር::

ገነት ቤት ድምፃዊ መሐሙድ አህመድ መጣ:: ቀደም ብሎም በአካል እንተዋወቃለን:: ሲያገኘኝ ደስ አለውና ይዘፍንልኝ ጀመር:: ትዝ ይለኛል ከዘፈኖቹ በጣም አረፈን ተጫወተልን፣ 'ፍቅሬ ለመሆንሽ' ድንቅ ነበር::

ቤንት ሉዊን አስታውስ:: አንድ ቀን ቀሳውስቱ መጡና "ቅዱስ ሆይ ይምጡና ቤተ መቅደሱ ውስጥ የተፈጠረውን ተአምር ተመልከቱ" ተባሉ:: እሳቸውም "እዚህ በዙሪያዬ ያለውን ተአምር ዓይኔ አልጨረሰኩም" አሉ:: እኔም ስዊዝ ውስጥ ያለውን ተአምር ተመልክቼ ሳልጨርስ እኮ ነው ወደ አገሬ የመጣሁት::

ለምን ፈረንሣይ፣ እንግሊዝ እሄዳለሁ? እዚያው ስዊዝ ውስጥ ዓመት ብጨምር የተአምሩን ብዛት የምጠግበውም አይመስለኝ:: የልጅ ልጄ ቅዱስና ሌሎች ጥቂት ሰዎች ካልናፈቁኝ በስተቀር የሚሰለቸኝ አይመስለኝም::

ካገኘሁትና ተረት ስፈር፣ ቁርቁስ፣ መኪና፣ ላፍቶ... እያልኩ አዲስ አበባ ውስጥ ኖሬያለሁ:: ሁሉም የሚከራይ ቤት ነው:: ተስማምቶኝ ነው ሁሉም ሰፈር የኖርኩት:: ቤተሰቤም እንደ እኔው እንደተስማማው እገምታለሁ:: አሁን ግን አውሮፓ እያለሁ ቤት እንዲኖረኝ ወሰንኩ:: ቢቻል ከእቶ ስብሐት ቤት አጠገብ ቢባል ምን አለበት? ደስ ይላል:: ይህንን ውሳኔ እንድወስን ያደረገኝ የሲዮና የገነት ሁኔታ ነው:: ወደፊት አዲስ አበባ መጥተው መኖር ይፈልጋሉ:: ስለዚህ ለመቀበያ የሚሆን ቤት እኔ በአዲስ አበባ ኖሮኝ ለምን አልቀበላቸውም:: ስለዚህ እዚያው አውሮፓ ሆኜ ከወዳጆቼ ጋር በስልክ መገናኘት ጀመርኩ::

የአበሻን ቢሮክራሲ ስለማውቀው እኮ ነው እዚያው አውሮፓ ሆኜ ከወዳጆቼ ጋር በስልክ መገናኘት የጀመርኩት:: በጣም ማገዝ የሚፈልግ ባለሥልጣን ሳይቀር ቢሮክራሲው አስሮት የሚገኝበት አገር እኮ ነው

አገራችን:: መጀመሪያ የደወልኩለት ድሮ ለማውቀው አሁን የማስታወቂያ ሚኒስትር ለሆነው አቶ በረከት ስምኦን ነው:: እኔ በረከትን የማውቀው እንደ ባለሥልጣን አይደለም እንደምወደው እንደሚወደኝ ነው:: ደወልኩለት አሁን ለመጻፍ ተነስቶብኛል:: ስዊዝ ቀንጆ አረፍት አሳለፍኩ:: ስለዚህ እባክህን የኪራይ ቤት እማገኝበትን ሁኔታ ፍጠርልኝ:: ብዬ ለፀሐፊው ነገርኳት:: እነግረዋለሁ ብላኛለች:: እንደምትነግረው ተስፋ አለኝ::

ከመጣሁ በኋላ ሆቴል አረፍኩ:: ገና ነኝ:: ሃጂ አላናገርኩትም:: እዚህ አዲስ አበባ ከደረስኩ በኋላ ለአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አርከበ ዕቁባይ ደውዬለታለሁ:: ቀጠሮ እንዲሰጠኝ ጠይቄአለሁ፥ እሱን አላገኘሁትም:: መቼም እንደምናውቀው እኔም በቅርብ ነው የመጣሁት:: እሱም ሥራም ስብሰባም ስለሚበዛበት ይደውልልኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: አሁን የርሱን የስልክ ጥሪ እየጠበቅኩ እናንተንም እያነጋገርኩ ነው:: ምክትል ከንቲባው ሀላዌ ዮሴፍም ሊያግዘኝ ወስኗል::

ተስፋ ብቻ አይደለም ነገን አናውቅም:: ያ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚያ በማናውቀው ነገር ውስጥ እርግጠኛ ነኝ በልቤ ውስጥ:: እንዴት አጣለሁ? ይገኛል እኮ ቤት::

ቀደም ብዬ ማስታወሻ ላይ ለእንጀራዬ ከዚህ በኋላ አጫጭር ጽሑፎች ከጻፍኩ በቂዬ ነው ብዬ ነበር:: ይህ ጉብኝት ያንን ውሳኔ እንድሽር አደረገኝ:: ረጅም ልቦለድ መጻፍ ጀመርኩ:: መጣብኝ መጻፍ እኮ እንደዛር ክርር አይልም፥ እንጂ ድንገት ይነሳል:: ተነሳብኝ አራት ምዕራፎች እዚያው እያለሁ ጽፌያለሁ:: በጣም አጫጭር ምዕራፎች ናቸው:: እርግጠኛ ነኝ ቤት እንደማገኝ፥ ባላገኝም መጽሐፌን ጽፌ እንደምጨርስ እርግጠኛ ነኝ:: የወዳጆቼ (አስጎብኚዎቼን) በማሰብ እጨርሰዋለሁ:: ዕድሜውን ይስጠን::

ከአዲስ አበባ ከመውጣቴ በፊት አንዷን ሴትዮ ስዊዝ ኤምባሲ አናዳኝ ነበር:: እንደመሰለኝ ለሥራው አዲስ ነች:: ማንነትን ከማጣራት መወሰን የሚቀላት አይነት ሴት ነች:: ቀደም ብዬ ከአገሬ ወጥቼ መመለሴን ማረጋገጫ ጠየቀችኝ፥ በቃል ነገርኳት:: ዶክሜንት አምጣ አለቺኝ:: ይኼኔ ተናደድኩ:: አዲስ መሆኗን ባውቅ ኖሮ እምራት ነበር:: ስላላወቅኩ ተናገርኳት:: ይሄውልሽ እንኳን «እዚያ ሚጢጢ አገር ሃጂ ልቀር ለንደንም ብሄድ አልቀርም:: እኔ አገሬን ነው የምወደው:: እዚህ ነኝ» አልኳት:: ተናድጄ ነበር:: ግን ልክ ነበርኩ:: አገሬ ከተመለስኩ በኋላ አምባሳደሩን አንድ ጓደኛዬ አግኝቶት ቅሬታዬን ነግሮታል::

@Amharicbookstore



ልክ እንደ ገነትና ሲዮ የአዲስ አበባውን ጓደኛዬን ቤከር (አቡበከር ናስር) ማመስገን እወዳለሁ:: እርሱ ባይኖር እዚህ ያለውን ቪዛ የማግኘት ጣጣ በእኔ በቀላሉ ታካችነት አልወጣውም ነበር:: እርግጥ አምላክ ልኮልኝ ጉዳዬ ሁሉ በመፈጸሙ መልክ በማስያዝ ስላገዘኝ የጓደኝነት ተግባሩን ተወጥቷል:: ድሮስ የተረት ሰፈር ልጅ እንዲህ እኮ ነው:: ለጓደኞቼ ቺርስ!

*መደምደሚያችን ላይ አንድ ጆክ ያስፈልጋል:: የፈረንጆቹ ጆክ ማብራሪያ ይበዛበታል፥ ልተወው ከአበሻ አንድ ልስጣችሁ::*

አንድ ሰውዬ ለአቡዬ ጣዲቁ ተሳሉ:: ልጅ እንዲሰጣቸው፥ አቡዬ ስለቱን ሰሙና በዓመቱ ወንድ ልጅ ወለዱ፥ ስሙንም ሰጡኝ አቡዬ አሉት:: በዓመቱ ሴት ልጅ ወለዱ ደገሙኝ አቡዬ አሏት:: በዓመቱ አሁንም (ወንድ ይሁን ሴት አስወለዱ) ሰለሱኝ አቡዬ አሉ:: በዓመቱ አሁንም አስወለዱ አባት ተበሳጭና «አበዙት አቡዬ» አሉት::

***

*ይህ ጽሑፍ ቅዳሜ ጥር 8 ቀን 1996 ዓ.ም አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ፊሽ በሚል የብዕር ስም ወጥቷል:: ጽሑፉን የጻፍኩት እኔ ነኝ:: በዚያን ወቅት አዲስ አድማስ ላይ እነሆ አማኑኤል፥ መልሕቅ፥ አሌክስ በሚል የብዕር ስሞች እጽፍ ነበር::*

***

## ፷፱

## ከወጣቷ ጋር መፈጣጠም

ቃልኪዳን ታደሰ ሚስቴ ሆነች:: የዘመኑ ልጅ ነች:: ስንተዋወቅ 23 ዓመቷ ነው:: ሲኤምሲ አካባቢ መንግሥት ቤት ሰጠኝ:: ገነት ታደሰ መጀመሪያ ከአውሮፓ እንደመጣን አስገኘችልኝ:: አሁን ከቃልኪዳን ጋር ስንኖር ቤቱን መግዛትም ቀልፋን መሸጥም እንደምንችል አጫወተችኝ:: ብንጨሽጠው ግን በምናገኘው ገንዘብ የመጻሕፍት እና የቪዲዮና ሲዲ መደብር ከፍተን መሥራት እንደምንችል ነገረችኝ:: እሺ ሽጪው አልኳት:: ቀልፋን በ80ሺ ብር ሸጠችው:: ልብ ማለት ያለብህ አሳድጋት የነበረች አንዲት ልጅ ነበረች:: ይህቺ ልጅ በወር በወር ለቤቱ ኪራይ እስጣት የነበረውን ገንዘብ አትከፍልም ነበር:: የአንድ ዓመት ያህል ውዝፍ እዳ አለብን:: ስለዚህ ወደ ሰባት ሺ ብር ገደማ ነበረብን:: ለቪዲዮ መግሪያ የሰጠኋት ገንዘብ ነበር:: አልተጠቀመችበትም:: በአጠቃላይ ስንሸዋወድ

ኖረናል። ስለዚህ እዳችንን ከፍለን ቃል ኪዳን ባለበችው ሥራ ገንዘብ ማግኘት አለባት። ተስማማሁ የቤቱ ቀልፍ ተሸጠ።

አሁን ከቃል ኪዳን ጋር አንስ ያለ ቤት በስድስት መቶ ብር ተከራይተን እዚያው ሲኤምሲ አካባቢ (በቱዲዮ) ነው በፍቅር እየኖርን ነው። የተዋወቅነው እንዲህ ነው ትኩሳትን አነብብኩትና ይህንን ሰው በአካል ማግኘት እፈልጋለሁ ብዬ ነው የመጣሁት አልኳት።

«ስምሽ ማነው?»

«ቃልኪዳን እባላለሁ።»

«ቃልኪዳን ምቶም ነሽ እንዴ? አልኳት። የሥቶም ተፈራ ልጅ ስምዋ ቃል ኪዳን ነው።

አሸናፊ መጽሐፍ መደብር ውስጥ ነበርን። አለመሆንዋን ነገረችኝ። አይ እንግዲያው ቆንጆ ልጅ ነሽ አልኩና ሳምኳት። እኔ አላወቅኩም አዝማሚያዋን። ከዚያ በኋላ ነው የምትነግረኝ። መቼ እንገናኝ ተባባልን። ተቀጣጠርን። መገናኘት ጀመርን። ቀጠልን ቀጠልን ቀጠልን ተዋደድን ወጣት ናት ትቻኩላለች። እኔ ደግሞ ቀስ ነው እሷን ሆና ካልቸኮለችማ...

ደግሞ እኮ ሰውን እንመዝነዋለን። ስለዚህ እግዜር ልኮልኛል አልኩ። ከጓት ጋርም ተስማምቶኝ ነበር። ከእሷ ተለያየን። ይህቺ መጣች። እንዷንም ገነት ተወችኝ ነው ያልኩት።

በእንዲህ ዓይነት የዕድሜ ልዩነት ኖሮ ማጋባት ሊከብድ የሚችለው ከብደቱ የሚኖረው ፈትዳ ሳይሆን ተገዳ ሲሆን ነው። እኛ ግን ተግባብተን ደስ ብሎን እንደምታየው እየኖርን ነው። እነ ተወልደ ብርሃን ምን ቢሰሙ ብቻ? ወስጄ አስተዋውቄዋለሁ።

ሳነብም አንዳንዴም በቴሌቭዥን ሳይ አንዳንድ እንደ ቃልኪዳን ዓይነት ልጆች የዕድሜአቸውን እኩያ የሆነ ጎረምሳ አይመርጡም። በፐርሰንት ሲያስቀምጡዋቸው ሦስት በመቶ ገደማ ይሆናሉ። ጎረምሳው ስሜት አይሰጣቸውም! ሽማግሌ ነው የሚፈልጉት። አንቺ እንደዚህ ዓይነት ትሆኚ ብያት ነበር።

«አዎን እንደእሱ ነው!» አለቺኝ።

«በእዚያ ላይ ደግሞ ታውቂያለሽ ልጅም አይደለሽም። ብዙ 'ኤክስፒሪያንስ' ሳይኖርሽ አይቀርም። ስለዚህ You are free ፍቅር ሌላ ወሲብ ሌላ አልኳት።»

@Amharicbookstore



«ይገባኛል። እኔ ስለምወድህ ልነግርህም እችላለሁ። በማንኛውም ጊዜ ፍላጎቱ ኖሮኝ ከሄድኩ ልነግርህ ሁሉ እችላለሁ። ምንም ማለት አይደለም» ተባባልን። ይኸውልህ በእንዲህ መልኩ እየቀጠልን ነው።

***

*ከዓመታት በፊት ከዕለታቱ በአንዱ ቀን ጋሼ ስብሐት እኔ ቤት መጥቶ ስንጫወት ዋልን። ጀንበር እንደጠለቀ ልሸኘው አብረን ማዝገም ጀመርን። ጉዞአችን በፀጥታ የሚከወን ነው። ልክ አራተኛ ክፍለ ጦር ጋ ስንደርስ «አንተ ብቻዬን ጥሎኝ ትሄድ!» አለና ቆመ። ጨነቀኝ። የምመልስለትም አልነበረኝም። ወይዘሮ ገነት ታደሰ ሕይወት ጥሩ አድርጋ አስጀምራው እሱም ወድዶት ነበር። ድንገት ተሰናብታው ባሕር ተሻግራ ሄደች። ይህ ውስጡን በእያሌው አውኮታል። ሲኤምሲ አካባቢ መንግሥት ቆንጆ ቪላ አከራይቶት ነበር። እየረዳት አብራው የምትኖር ልጅ አለች። ታናሽ ወንድሙ ዶክተር ተወልደ ብርሃን ይህንን ቤት አይቶት «አሁን ቆንጆ ሆነልህ። በሕይወትህ መጨረሻ ለአኗኗርህ የሚስማማ ቤት አገኘህ» ብሎ እንደነገረለት አውቃለሁ። ይሁን እንጂ ይህ ቤት ከዚያች ፍቅረኛው ውጪ ኦና ሆኖቢታል። አውቃለሁ በርካታ የስብሐት ወዳጆች አለን። ሁላችንም ከጋሼ ጋር በልተን ጠጥተን ተጫውተን ጀምበር ስትጠልቅ መኝታው ድረስ እንሸኘዋለን። እንደ አስፈላጊነቱ አልጋውን ገልጸን እናስተኛዋለን። የሔዋን ዘር ግን አብሮ መብላት መጠጣት ብቻ ሳይሆን አብራው ትተኛለች። በዕድሜ ብዛት የቀዘቀዘ አካላችንን ያሞቁታል።*

*በእንዲህ ዓይነቱ ጭንቅ ወቅት ነው አለሁልህ ብላ የባሕል ትብትቡን በጣጥሳ በሕይወቱ ውስጥ ቃል ኪዳን ታደሰ የተከሰተችው። ወሩን ባላስታውሰውም ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ቃል ኪዳን ከጋሼ ስብሐት ጋር አብራው መኖር ጀመሩ። አቅም በፈቀደ መጠን ምቾቱን በአግባቡ ትጠብቅለታለች። ቀን ሠጣ ሲል የሚለብሳቸው ልብሶች ምርጥ ናቸው። ከእውርጊ ሲመለስ ባመጣቸው ላይ ራሷም ገዝታ ጨምራለታለች።*

*የሌሊት ልብሶቹ ውብ ለስላሳና ምቹ ናቸው። በአገር ባሕል የተሸመኑና በፋብሪካ የተፈበረኩ ሁለት ሶስት ጋዋኖች ነበሩት። ከእልጋ የሚወርድባቸው ነጠላ ጫማዎቹ ምቹና ባለፈር ነበሩ። መኝታውን ንጹህና እንዲደላው አዘጋጅታለታለች።*

*የሚመገበውን ቁርስ፣ ምሳ፣ ራቱን ራሷ ታዘጋጅለታለች። ቋሚም ሆነ ተመላላሽ ሠራተኞች እንደነበሩት አስታውሳለሁ። በሚጽፍበት ጊዜ ምቹ ሶፋ ላይ ተቀምጦ ጭኑ ላይ አንዱን ትራስ አኑሮ ይጠበባል። ይኼኔ «ቆይ አበይ ቀና በል» ትልና ቃል ኪዳን ከጀርባው አልያም ከጎኑ መከዳ ታኖርለታለች። የሚወዳቸው ሰዎቹን ከቤት ሳይወጣ በቅርብ እንዲያገኝ ታደርጋለች።*

*ሲኤምሲ፣ ሰንቀላል ፋብሪካ አካባቢ በሚዚሊላንድ መንደር በኋላ፣ ቁርቆስ ክፍለ ከተማ ቡልጋሪያ፣ ማዞሪያ አካባቢ የኖሩባቸው ቤቶች ሁሉ ኮንዶሚኒየም በመሆናቸው መታጠቢያ ቤቶቹ አጠገቡ ናቸው።*

*«እኔ የባላገር ልጅ ነኝ የባላገር ልጅ ለዓመት በዓል ነው አካላቱን የሚታጠበው። የሚያልብ ሥራም ስለማልሠራ እንደ ከተማ ልጅ ቶሎ ቶሎ መታጠብ አያሻኝም» ይበል እንጂ ጋሼ ስብሐት የሔዋን ልጅ ያስፈልግሃል ካለችው ካቀበጠችው አሁንም አሁንም ይታጠባል። ልብሱን በአግባቡ ቀይሮ ከውብ ሱፍ ልብሶቹ*

እንዱን ለብሶ ቁንጠኛ ኮፍያውን አናቱ ላይ አድርጎ አደባባይ ብቅ ይላል፡፡ ናዝሬትን ጨምሮ በአዲስ አበባ ዙሪያ በ100 ኪሎ ሜትር ርቀት ወጣ እያለ ተዝናንተው ተናፍሰዋል፡፡

በምቾት መንፈላሰስ በፍቅር ከንፎ ሥራውን ጠብ እርግፍ አድርጎ አልተወም፡፡ እንደወረደ የጻፋቸው መጻሕፍቱ የመታተም ዕድል የደረሳቸው በዚህ ወቅት ነበር፡፡ ሌቱም አይነጋልኝ፣ ትኩሳት፣ ሰባተኛው መልአክን ጨምሮ በዚያው ወቅት ይጽፍላት የነበሩት የፍቅር ሻማዎች የተባሉ ሥራዎቹ ለጥራዝ በቅተዋል፡፡

ይህንን የፍስሐ ሕይወቱን አንድ ቀን ውድ እህቴ መስከረም ጎሳዬ አጫውተኝ አለችኝ፡፡ በደስታ አጫወትኳት «ይህቺ ልጅ አንድ የኢትዮጵያን እሴት እየጠበቀች መሆንዋ ገብቷት ይሆን?» አለችኝመስከረም በአድናቆት፡፡

«ገብቷትም የአበሻን ታቡ በማጥባ እየኖረች ነው» አልኳት የመስከረም አስተዋይነት እየገረመኝ የወዳጄ አሰፋ ጎሳዬ እህት ሆና እንዲህ ባታስብ ነበር የሚገርመኝ፡፡

በጊዜ ከቃል ኪዳን ጋር በጣም ሸርካች ነን፡፡ በሰላሙ ወቅት አንድ ቀን ቃለ ምልልስ አደርግላታለሁ እያልኩ እያሰብኩ ሳይሞላልኝ መደምደሚያው ላይ በመድረሳቸው ሃዘንተኛ ነኝ፡፡

ቢሾምቢ የአንድ ቀን ውሎአችንን በደንብ አስታውሰዋለሁ፡፡ በዕለቱ ጋሼ ቤት አልነበረም፡፡ እኔና እሷ ብቻ ወይን እየተጎነጨን ብዙ አወጋን፡፡ ስለ እርሱም ሆነ ስለቤተሰቦቹ ወንድምና እህቶቹን ከልብ እንደምታደንቃቸው ያጫወተችኝ የዚያን ዕለት ነበር፡፡

ቀደም ብዬ እንዳልኩት ቤትን በአግባቡ ለተፈወሰባት መድኃኒት ነች፡፡ ቃል ኪዳን ያንን ብቸኝነት ገፋለት "አለሁልህ" ስትለው ጋሼም ወዲያው ተነቃቅቶ መኖር ጀመረ፡፡ ጥላው የሄደችውንም ፍቅረኛውን ድጋሚ መጥታ ካቆምንበት እንጀምር ስትለው «አሁንማ ሌላ ወጣት አፍቅሬያለሁ፡፡ አንቺንም አብረን ባሳለፍነው ደስታ ሁሉ ከልብ አመሰግንሻለሁ» ብሎ እንደሸኛት አስታውሳለሁ፡፡

አምላክ ቃል ኪዳንን በሕይወቱ ውስጥ እንድትኖር የፈጠረበትን ቀን ግን ባሰላው ቀደም ብሎ ቃል ኪዳን እንድትፈጠር ሆኖ በአብዮቱ ወቅት ሕይወቱ ላይ ተከስታ ቢሆን ኖሮ ጋሼ ስብሐት ሌላ ሰው ሌላ ደራሲ ሌላ ጥበበኛ በሆነ ነበር ስል እቆዝማለሁ፡፡ በዘመኑ ግን ቃል ኪዳን አልተወለደችም፡፡

ምናልባትም በወጣት መንፈስ ተወስኖ የተሰሩ ጥቃቅን ስህተቶች ናቸው ብዬ የማነሳቸው አንድ ሁለት ሀሶች አሉ፡፡ አንደኛው አዝናኝ የቪሲዲ ፊልም ሲሰሩ ሳያማክሩኝ ቀረጻውን አካሂደው ለገበያ ማቅረባቸው ነው፡፡ በዚህም መሪር ትችት በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ተጽፎበት እሱም የምር አዝኖ ተመልክቻለሁ፡፡ በእኔ እምነት ይህን ቀረጻ ሲያከናውኑ አማክረውኝ ቢሆን ኖሮ እርባና ያለው ሃሳብ ማቀባት ይቻል ነበር፡፡

ሌላው የቤቱን ቁልፍ ሲሸጡ ምንም መረጃ አልነበረኝም እንጂ ከቤታ ቤታ መንከራተት ሳያስፈልግ አንድ ስቱዲዮ ላይ ተጨማሪውን ገንዘብ አግኝቶ መኖር የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር እንችል ነበር፡፡ ይህ የመመካከር ባሕል ባለመፈጠሩ የፈራሁትን ያህል ባይሆንም ከተማ ውስጥ ተዘዋውሮ መኖር ግድ ሆኖባቸው አስተውያለሁ፡፡ ያም ሆኖ ቃልኪዳን ገንዘቡን ለኑሮዋቸው ማዋሏዋን መመስከር



እችላለሁ፡፡ በሰላም ወቅት ከዕለታቱ በአንዱ ቀን «በጣም አዝናለሁ ዘነበ እኔ መሰላችሁ ገብቼ ድሮ የምታደርጉትን ውይይት የደናቀፍኩት ይመስለኛል» ብላኛለች፡፡ እኔ ደግሞ የእሱዋ በመሰላችን መከሰት የእሱን ህይወት ለማርዘም ትልቅ ፋይዳ እንዳለው አወጋሁዋት፡፡ ይህን ስል ደግሞ ከአንጀቴ ነው፡፡ በርግጥም የእሱዋ በእሱ ህይወት ውስጥ መንጎት ግዙፍ ፋይዳ ነበረው፡፡

ሁለታችንም ተገናኝተን የሆድ የሆዳችንን የወጋንበትን ቀን ባርከን ማምሻዬን ወደ ቤቴ ሄድኩ፡፡ በሚቀጥለው ቀጠሮ ከጋሼ ስብሐት ጋር ተገናኝተን «አንተ ጠፋህ...» ብዬ ወሬ ስጀምር «እንኳንም ያልኖርኩ የተጨዋወታችሁትን ሁሉ አጫውታኝ አብረን ወደድነው» ብሎኛል፡፡

ሕይወት ለሁሉም ነገር መደምደሚያ አላት፡፡ በ1998 ጀምሮ የነበረው የወጣቷና የአዛውንቱ ትዳር 2003 ዓም በክረምቱ ወቅት ተደመደመ፡፡ ችግሮቹን ስመረምራቸው አያሌዎች ናቸው፡፡ አንደኛው ዛዚ የተሰኘው መጽሐፉ በፈረንሣይ ኢምባሲ ስፖንሰር አድራጊነት በስንዱ አበበ ለሕትመት እንደበቃ ስንዱ ወደ ፈረንሣይ አገር ሄደች፡፡ መጽሐፉ በአንባቢያን በፍጥነት ተቀባይነት በማግኘቱ ከገበያ ሊጠፋ ሲል ቃል ኪዳን ሁለተኛው ሕትመቱ እንዲወጣ አደረገች፡፡ ይህ ጉዳይ በሁለቱ ሴቶች መካከል መጣጣምን አሳጣ፡፡ ሌሎች ችግሮችም ተፈጠሩና የአዛውንቱና የወጣቷ ፍቅር ልክ ባበበ በሰባት ዓመቱ ከሰመ፡፡

ቀደም ብዬ እንዳልኩት ጋሼ ስብሐት ከመጨረሻ ልጁ ጋር ለመኖር ወደ እኔ ሰፈር መጣ፡፡ ከቃል ኪዳን ጋር መለያየቱ አንዳች ዓይነት የቅስም መሰበር እንደፈጠረበት ተሰማኝ፡፡ ጋብቻቸውን በግሉ እሚያየው መሥሪያ ቤት ሂዶ ፊርማው እንዲቀደድ ማድረጉን ሲነግረኝ ነው ሀብትሽ ከሀብቴ ተብሎ በሕግ መጋባታቸውን ያወቅኩት፡፡

በግሌ ቃል ኪዳን ታደሰ ከጋሼ ስብሐት ጋር ያሳለፉት ጊዜ ውብና ማፋጭ ነበር፡፡ እሱን በከፍተኛ ደረጃ አነቃቅታው መኖርን ከልብ እንዲወደው አድርጋለች፡፡ በመጨረሻው ላይ የተፈጠሩት ችግሮችም የሕይወት ሕግ ነውና እቀበለዋለሁ፡፡ ቃልኪዳንም የባሕልን ትብታብ በጣጥሳ ራሷን ሆና እምነቷን በመኖሯም ለቃልኪዳን ታደሰ ያለኝ አክብሮት ከፍ ያለ ነው፡፡

***

## ሸ፫

## አለቆች

*ሻምበል ነበር፡፡ የፖሊስ ሻምበል፣ እሱ ነበር የኩራዝ አሳታሚ አስተዳዳሪያችን፡፡ አብዮታዊ ነው፡፡ ማርክስን ተረጎምን፡፡ እና ጭማሪ በሺዎች የሚቆጠር ብር ነበር የሚደርሰን ለሌሎቹ ከፍለው እኛን ዘለሉን፡፡

@Amharicbookstore

አምስት ሳንቲም አልደረሰኝም። ሌሎቹ ጥሩ ገንዘብ ደረሳቸው የኢሠፓ አባል ስለሆኑ።

አንድ ቀን ቢሮው ሄድኩ። ቢሮው በጣም ሰፊ ነው። የመሰብሰቢያ ጭምር ስለሆነ ነው። ዝርዝሩን እረሳዋለሁ። የሆነ ነገር ጠየቅኩት። ምንድነው ያለው ነበር? «ለእናንተ ፀረ - አብዮታውያን ምናምን ነገር ምንም የምናደርገው ነገር የለም። ከደመወዝህ ውጪ ምንም የምናደርግልህ ነገር የለም» አለ። ዝርዝሩን እረሳለሁ።

«እሺ ተወው» አልኩ።

ዘመን ተለዋወጠ የነጓድ እገሌ ዘመን ተሻረ። እነ መለስና ጓደኞቹ መጡ። እኔ በወቅቱ አቃቤ ሕግ የነበረው የታናሼ ታናሽ ወንድሜ ዮሴፍ ታስሮ ልጠይቀው ሄድኩ። የት ነበር የታሠሩት? አምን እስር ቤት ልጠይቀው ሄድኩኝ፣ ዮሴፍን አግኝቼው ስመለስ «ጋሼ ስብሐት» አለኝ የሆነ ሰው። ዞር ስል ሻምበሉ አለቃችን ነው።

«እንዲያው ምናምን በጣም ይቅርታ ከዚህ በፊት ተሳስቼ ይሆናል ምናምን...» አለ።

እንዴት መሰለህ። እንደ እርሱ ዓይነት ሰው ደግሞ ሁልጊዜ የሚታወቀው ነው። ወይም ይከረኩምሃል፣ ወይም ይንበረከካል። በሕይወቱ የሚያውቀው ሁለቱን ብቻ ነው።

«ይቅርታ አድርጉልኝ ምናምን ምናምን» አለ። እንግዲህ አሁን እኛ የምንከስ የምንመሰክር ነን ለእሱ ነበስ። ፈርቶ ነው።

«አይዞህ ኧረ ባክህ ምንም አይደለም ተነስ ኧረ ባክህ ደህና ሁን እንጂ አንተ የምን መጨነቅ ነው» ብዬው ሻምበልን አፅናንቼ ተሰናበትኩት። በልቡ ነበር የተንበረከከው።

***

ሌላኛው *አለቃችንን እዚህ ጋ ማንሳት አለብኝ። ስለዚህ ሰው አጠያየቅህ ከፒራሚዱ ጫፍ ላይ ቆርጠህ እንደማየት ነው። ይረዝምብሃል ወይንስ ሙሉውን ላውራልህ?

እንግዲህ አየህ? ችሎታህ ይታይና ቤተ ክህነትም ይሁን፣ ቤተ ጦርም ይሁን የትም ይሁን እድገት ታገኛለህ። በእንግሊዘኛ አንድ ስለት ያ ያደክበት ቦታ እዚያ ማደግ አልነበረብህም፣ እዚህ ከታች ነበር የመጨረሻ እድገትህ። You are promoted to the level of incompetence. ይልሀል ቢቃ፣ ከአቅም በላይ ሆነበት። እስካሁን መጥተህ መጥተህ ትሄዳለህ ሊደርስ ሲል እንደሚደናቀፍ ዓይነት ነው።



ጥይት ኤዲተር ነበር። በጣም ደግ ሰው እንደዚህ እንደዚህ የሚገርምህ ሰው ነበር። እንዲያውም ብትፈልግ "አንድ ቀን ና አለኝና የሠራተኛ ቤት ትልቅ ቤት ሲሠራ አለ አይደለም? «ይህ የእኔ ቤት ነው። ይህንን ለአንተ ልሰጥህ እችላለሁ። አንተና ሚስትህ ከልጆች ጋር እዚህ ውስጥ መኖር ትችላላችሁ። እኔና ሚስቴም እዚሁ አካባቢ አብረን እንኖራለን» አለኝ። ይህንን ያህል ደግ ነው። እኔ ምን አልኩት «ሁለት ቤት አንድ ላይ ማኖር አይሠራም እንጂ ሐሳብህ አሪፍ ነበር» አልኩት። ደግሞ እውነቴን ነው። እንደዚህ ነው እንግዲህ።

ያን ጊዜ የምንሠራው ቱሪዝም ኮሚሽን ነበር። እሱ ነው እንግዲህ የሕትመትና የእንደዚህና የእንደዚያ ክፍል ኃላፊ ነው። እሱን ከፈለግክ ታገኘዋለህ። እኔ የእንግሊዘኛው ዝግጅት ክፍል ባልደረባ ነኝ። የአረብኛ አለ የሌሎችም ቋንቋዎች አለቃ ነው።

በቃ የዚያን ጊዜ የሆነ ነገር ዞሮበታል። ሁሉም ላይ ይጽፋል። ስህተቶችን ሆነ ብሎ ይፈልጋል። ይጽፍልንና በመዝገብ ቤት በኩል እንዲያልፍ ሁሉ ያደርጋል። ሌላው ቀርቶ ፀሐፊውንም አልማራትም። ፀሐፊው እኮ ስልኩን የምታነሳለት። የምትሸሽገው እኮ ናት። እሷም ላይ የሴክሬተሪዎች ተግባር ብሎ ጻፈባት። ሦስት ነው አራት ገጽ። ጥፋቶቿን ጻፈ። በፀሐፊነት «እኔን እንዲህ ይሉኛል?» እያለች አነባች። ከእንግዲህ እሷ ስልክ አንስታ ጓድ እገሌ አትልለትም። አሳዮችኝ እያለቀሰች። ሁላችንንም ጻፈብንና እኛን አፋቀረን። ጭንቅላቱ እኮ ይህንን ነገር አይስትም። 'ሌቨል ኦፍ ኢንኮፒታንስ' ሆነ እልሃለሁ።

***

*የሁለቱም አለቆቹ ስሞች ተገድፈዋል።

***

*ኃይለመለኮት መዋዕል*

*ጋሼ የነገረውንና አብሮ ያጋጠመውን እንዲህ ያስታውሰዋል፣ «ኮራዝ አሳታሚ ድርጅት ካፒታልን ያስተረጉም ነበር። ለትርጉም ሥራው ከተመረጡ ሰዎች አንዱ ጋሼ ስብሐት ነበር። መጽሐፉ ሲተረጎም ገጽ ተከፋፍሎ ነው። ጋሼ ስብሐት ጠቡሉን ወስዶ ተረጎመ። በመጨረሻም ላይ የአርትኦት ሥራም ሠርቷል። ለዚያ ለሠራው ሥራ ክፍያ ነበረው። ክፍያውንም ቢሆንን ያህል በገጽ ይከፈላችኋል ተብለው ተነጋግረው ነው ሥራውን የጀመሩት። በታሰበው መልክ ተጠናቅቆ አለቀ። ከእርሱ ጋር የሠሩት ሰዎች ተከፈላቸው። ሁሉም የኢሠፓ አባላት ነበሩ። እሱ ነገ ይሰጡኛል ዛሬ ይሰጡኛል እያለ ጠበቀ። ዝም አሉት። እሱ ደግሞ ተፈጥሮ ሆኖ ንዝንዝ አይደለም ገፍቶም አልሄደም። በዝምታው ብዙ ቆየ። አንድ ቀን ለእኔና ለአረፋዓይኔ ሐጎስ ነገረን። እኛም በጽሑፍ እንዲጠይቅ መከርነው። በዚጋው ጻፈና አስገባ። ዝም አሉ። ለሁለተኛ ጊዜ ይህንኑ ማመልከቻውን እንዲጽፍ አደረግን። ይሄኔ ይከፈለው ተብሎ ተነገረለት።*

አሁን የገንዘቡን መጠን እረሳዋለሁ 2500 ብር ገደማ ነበር። ቼኩን እንደተቀበለ ደወለልኝ። እኔና እሱ ሆነን አራዳ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሄደን ቀጭ ብለን ፕሮግራም አወጣን። ሰዳ የሚከፈላቸው፣ ውሊታ የሚከፈላቸው፣ ለቤት የሚሰጠው፣ ለቸሲታ የሚመፀውተውን፣ (የዱሮውን ባላውቅም) ባሕሉ ባይኖረውም ገንዘብ ባንክ በመጠኑ ማስቀመጥ የሚገባውን ሁሉ ሰቅዳችን ውስጥ አስገባን።

ቼካችንን ይዘን ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋንድሂ (GANDHI) ቅርንጫፍ ሄድን። የባንኩ ሠራተኛ ወጣት ቼኩን ተቀበለውና እሱን እሱን አፍጥጦ እያየ ቼኩን ሳያይ ፈረመለት። ቀጣዩም እንደሥራ ባልደረባው በመደነቅ ፈገግ ፈረመለት። ሦስተኛው ሰው ጋ ስንደርስ ቼኩን ያዘው። ለባልደረቦቹ እንዴት ብላችሁ ነው ይህንን ቼክ ያሳለፋችሁት? አላቸው «ምነው ምን ጎደለው?» ብለው ሲያዩ ለካንስ የመሥሪያ ቤቱ ማህተም አልተደረገበትም። በዚህ ምክንያት ባንኩ ገንዘቡን እንደማይከፍለው ተነገረን። ያንን ቼክ ይዘን ወደ መሥሪያ ቤቱ ሄድን። ሂሳብ ክፍል ገብተን «ይህንን ቼክ ሰጣችሁኝ። ባንኩን ገንዘቡን እንዲሰሙኝ በምጠይቅበት ወቅት ቼኩ አይሠራም አሉኝ። የማናጀሩ ፊርማ ቢኖረውም ማህተም አልተደረገበትም። ለምንድነው ያላደረጋችሁት?» አላቸው።

«ይቆይ ተባሉ።»

«ይቆይ ከተባለ የማይከፈልበት ቼክ ለምን ሰጣችሁኝ?»

ፀጥ አለ። ቼኩን ሳለላቸውና ወጣ። በጣም በጣም አዘነ። ከእኔ ጋር 1976 ዓም ጀምሮ ነው የምንተዋወቀው እንደዚያን ቀን ሲከፋው አላየሁም። እንዴት ያታልሉኛል? እንዴት ሐቄን ይከለክሉኛል? በሚል ስሜት የምር አዝኖ ያየሁት የዚያን ዕለት ነው። እዚያው ከበብ አላቸው ገባን፣ ምሳችንን በላን፣ ሻይ ጠጣንና አፅናናሁት። ቢቃ እኮ አለኝና ያንን ዕለት እንዲሁ በኀዘን አሳለፍን። ያ ገንዘብ ሳይከፈለው እንዲሁ ቀልጦ ቀረ።

ጋሼ ስብሐት ሲጽፍ ጽሑፉን በመጀመሪያ አንጎሉ ውስጥ ጨርሶ ነው። ጽሑፉ ልቅም ያለ! መስመር አልባ ወረቀት ላይ ሲጽፍ አይንጋደድም ቀጥ እንዳለ ከዳር ይደርሳል። ጽሑፉ ታይፕ ከተመታ በኋላ የፊደላት እንጂ የሐሳብ እርማት የለበትም። በሥራው ብርቱ ነበር። ያ ገንዘቡ ሳይከፈለው መቅረት ቅር ስላሰኘው የሥራ ሳይ ትጋቱ ተቀነሰ። ማርፈድ፣ በል ሲልም መቅረት ባሕሪው ሆነ። በዚህም ምክንያት ከሥራ አገዱት። በወቅቱ አንድ ሻምበል ለውጤ ነበሩ ዋናው ሥራ አስኪያጅ። ለአረፋዓይኔ ሐዝስ ነገረው። አረፋዓይኔ ደግሞ ለእኔ ነገረኝና ተመካከርን። አማላጅ ሆነን ቀብር አስይዘን ሄድን። ለውጤው በሥነ ሥርዓቱ አነጋገረን። ሥራውን እንደ ድሮው በጥንቃቄ አይሠራም ብሎ ነገረን። እኛም እንዲታረም እንነግረዋለን አልነው። በዚህ ተስማማንና ተሰነባበትን።

እንደገና ምንአልባት ዓመት ገደማ ቆይቶ መሰለኝ አሁንም ከሥራ አገዱት። ነገረን። አሁንም እኔና አረፋዓይኔ ተያይዘን ሄድን። «ደግሞ ምን አጥር ጣላችሁ?»አለን። አዋየነው። «መቼም እናንተን የሚያከል እንግዳ መጥቶብኝ?...» ብሎ እግዱን አነሳለት ወረቀቱም ከግል ማህደሩ እንዲወጣ ሆነ።

ሥርዓቱ ተለወጠ። ይህ ሥራ አስኪያጅ ታሰረ። ምን ያህል ጊዜ እንደታሰረ ለላውቅም። እኔና ጋሼ ስብሐት ቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ ጋስቴ ቤት ገብተን ሻይ ጠጥተን ጋስቴም በልተን ለመንሸራሸር ወደ ጊዮርጊስ እቅጣጫ ወጣን። ከማዘጋጃ



ቤት ግርጌ ሜዳው ላይ ደርሰን ስናሽቅብ ይኼኔ ያ የቀድሞው አሲቃው ሻምበል መጣና ሰላም አለን። በሚገባ በሥነ ሥርዓት ጋሼ ስብሐት ሰላም አለው።

«እንዲሁ ሰው ለሰው ሆኖ የማይገኝ የለም እና ችንዝ አስቀይሜህ ሲሆን ይችላል ባለፈው ጊዜ... »አለና እንደ ይቅርታ መጠየቅ አለ።

ጋሼ ስብሐትም «እኔ እንደዚያ ዓይነት ሃሳብ የለብኝም። ትዝም አይለኝ። አንተም ትዝ እንዳይልህ። ልብህ ውስጥ እንዳትስቀምጥ። አሁን እኔና አንተ ይህንን አዲስ ሕይወት መቀበል ነው ያለብን። ሌላ ጊዜም ስንገናኝ እንዲሁ ሰላም ተባብለን ነው መተላለፍ ያለብን። አሁን ድንገት መንገድ ላይ ተገናኘን እንጂ ሻይ ቡና መባባል ነበረብን» አለው ለውየው ደስ ብሎት ተሰነባበቱ። ለውጤው ጊዜው በመለወጡ ምክንያት ይበቀለኝ ይሆን የሚል ሲጋት ነበረበት። ስብሐትን አያውቀውማ!

***

## ፳፬

# የክብር ሕግጋት

'Code of honour' የሚባል ነገር አለ፡፡ የክብር ሕግጋት እንደማለት ነው፡፡ ፀሐይንም እንተንም ስለምውዳችሁ ነው የምነግርህ፡፡ ስንኳረፍ እኔ ነኝ ቀድሜ ይቅር በይኝ የምላት፡፡ መኳረፍ መጋጨቱ ያለ ነው፡፡ የእነርሱ ደግሞ የሴቶቹ ሌላ ነው። ፍቅረኛዬን እወዳታለሁ አይደል? የቂል ልማድ አለ፡፡ አኩርፌያለሁ፡፡ ይህ የነፍስ ኬሚስትሪ ነው፡፡ ቀድሜ ላኩርፍ እንጂ፣ እሷ ከመጣች በኋላ መፈታት ነው ያለብኝ፡፡ ይህ ከልጆችንም ጋር የሚከናወን ኮድ ነው፡፡ ከባለቤቴም ጋር ኮድ ይኖራል፡፡ በፍፁም እሷ ቀድማ ይቅርታ አትጠይቀኝም፡፡ ያጠፋችው እሷ ብትሆንም እንኳን፡፡ የእኔ ነቻ፣ አልፈዋለሁ፡፡ ዘንግታ ያጠፋችውን ቀድሜ ይቅርታ ስጠይቃት ክብሯን እየጠበቅሁ ነው፡፡ 'Between her and me' በእርሷና በእኔ መካከል የሚቀር ቢሆንም የእርሷ ክብር ነው የሚበልጥብኝ፡፡ አለዚያ እልህ ነው፡፡ ወንድ ለወንድ ስንሆን አንበላለጥም፡፡ እኩል ለእኩል ነን፡፡

Shit! እኩል ለእኩል ነን:: give and take ነው መሆን ያለበት:: ከማን በልጠህ ነው ከሚሰጥህ በላይ የምትሰጥ:: ከማን አንሰህ ነው የሚሰጡህን ያህል የማትሰጥ? በእጅህ ያለው ገንዘብ ይሁን ስሜት ይሁን ፍቅር ይሁን እኔም አለኝ የምሰጠው፣ እናም የምቀበለው::

አዎን! እኛም ቆነጃጂቱን ታጥቀን እናስተናግዳቸው እየተባባልን ነው፡፡ ውቢቱ ከእኛስ በምን ታንሳለች፣ ብትበልጠን እንጂ!? አውሮፓውያን 'gesture' የሚሉት ባሕል አላቸው፡፡ ሴት ክብርት ናት፡፡ በቴአትር አቀራረብ ላጫውትህ፡፡ የንግሥት ኤልዛቤትን ሥዕል አይተሃል?

እኛ እጇን ስንስመው በርከክ ብለን ነው፡፡ እሷም ዘና ብላ እጇን ትለቅልናለች፡፡ ይህንን ያህል ነው የምናከብራት፡፡ አየህ፣ ይህች አክብሮት፣ ይህች ሥልጣኔ ደላትና ፋሽን ሆነች፡፡ እኛ ትሕትናችን እስከቻለ ፍቅረኞቻችንን እዚህ ድረስ ማክበር አለብን፡፡

እሷን ነው የምንቀድማት:: አንድ ቀን ደግሞ ፀሐይ ያለቺኝን ልንገርህ እንግዲህ በሳቅ ሰዓት ነው እንግዲህ እኔ ቢሮ ነበርኩ:: እሷ ሻይ ልትጠጣ ስታልፍ ነበር:: ጎራ አለችና «አሁን እኮ ከዘነበ ጋር ተኳርፈናል» አለቺና ሳቀች:: «እና አሁን ሲያልፍ ዝም እያልኩት እኮ ነው» ብላ ስትስቅ አስታውሳለሁ:: በእውነት ይኼ ጤነኛ ኩርፊያ ነው:: ይህን ስልህ እንኳን ሰው፣ ጉልቻ እንኳን ይጋጫል:: እኛ ግን እንዲህ ነን:: አንዳንዱ ቂም መሰሉ እየተፍለቀለቀ ካለ ስናገረው ይወጣል፣ ከሌለም ግድ የለውም:: ግን ከልብ ያስቀየመቺኝ ካለ ግን የኩርፊያው ጊዜ ሳይረዝም ምነው እንዲህ አደረግሽኝ? ለማለት መቻል አለብህ::

ልጨምርልህ አንተና ፀሐይ ልትጋቡ መወሰናችሁን ነግረሽኛል:: ከወዲሁ ላስጠንቅቅህ:: ከእሷ ጋር መፋቀር እንዳለ ሁሉ መጣላትም አለ:: የዚያን ጊዜ እኔ ሁሌም የማግዘው ለእሷ ነው:: ይህንን የምነግርህ ከወዲሁ አስበህበት እንድትጠብቀኝ ነው:: ምንጊዜም እሷን ነው የማግዘው ይህ ነው ለእኔ የክብር ሕግጋት::

እ ይኸውልህ:: ቆንጆ መጣችልኝ አባባሏ:: ለራት እንዴት እንልበስ እንደሚሉ እንግሊዞች የእኛን 'ሌዲ' እንዴት 'ትሪት' እናድርጋት? ነው:: ደግሜ ደጋግሜ ልንገርህ ከፍቅረኛችን ጋር ፀብ ሲፈጠር ቻል እናደርጋለን:: በቆይታ እኛ ነን ቀድመን ይቅርታ የምንጠይቃት:: እሷም ብትሆን የበደለችን ከእኛ በምን ታንሳለች ብትበልጥ እንጂ፣ ይቅርታ ለመጠየቅ እኛ ነን ምንጊዜም የምንቀድመው:: 'ራይት!'

@Amharicbookstore



አሁን የማወራልህ ኢሮጳውያን ለመኖር መሥራት የሌለባቸው፣ ሌላው እየሠራ እነሱ የሚዘንጡ የሚኖሩ መኳንንቶችን ሕይወት ላሳይህ:: የእነሱ ሥልጣኔ እንግዲህ መሰረቷ ፍራንስ ናት:: ሴት ክብርት ናት::

የንግሥት ኤልሳቤጥ ጊዜ ነው:: እሷ እንዲህ ነች ሚስታችን ነች ጓደኛችን ናት:: እንግዲህ ሥልጣኔዋ በላትና 'ፋሽን' አደረጓት:: አንድ ክልክል የሆነ 'ሴሪሞኒ' ይኖራል:: አንተ የለህም:: እዚያ ፀሐይ አለች አንተ ብትኖር ይቅር የምትለውን ነውር ነገር ፍቅረኛህ ላይ ተደረገ:: ትሰማለህ:: ይኼኔ እናትክን ምናምን አይደለም የምትለው:: "እባክትን ጌታዬ.." ትልና ጓንትህን ታወልቅና በጓንቲዋ በጥፊ ትመታውና ጓንቱን ትጥልለታለህ:: ጓንቷን ካነሳት ከእዚህ ወጥተን ይዋጣላችኋል:: መጣሪያ ተሰጥቷችሁ፣ ተቀጣጥራችሁ ትፋለማላችሁ:: በዘመኑ መጋደል በሕግ ክልክል ነው:: ይሁን እንጂ ክብር ነዋ:: በድብቅ ተቀጣጥረው ይፋለማሉ:: ከሕግም በላይ ክብር ያፋልማል:: ጓንቲዋን ካላነሳ ክብሩም አልተነካም ፍልሚያው ይቀራል:: ይቅርታ ጠይቋል ማለት ነው::

የእነ ቶልስቶይ ዘመን አለ፡፡ አንተን የሚያክሉ ጎረምሶች ተሰባስበው ከምሳ ሰዓት ጀምሮ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፡፡ ምንም አይነት ሥራ የለባቸውም፡፡ አራተኛ ወይም አምስተኛ ፎቅ ላይ ነው የሚዝናኑት፡፡ እናት አገር ከጠራቻቸው ብቻ ይዋጋሉ፡፡ መብታቸውም ክብራቸውም የሚፈቅደው እንዲህ እንዲኖሩ ነው፡፡ ከእራት በኋላ ይዋጣልን ይባባላሉ፡፡ አራተኛ ፎቅ ላይ ናቸው አስታውስ:: የተከፈተ መስኮት ጠርዝ ላይ ቆመው ጀርባቸውን ለጭለማው ሰጥተው አንድ አንድ ጠርሙስ ቮድካ ጅው ገና አፋቸው እንደተጠጋው፣ ቮድካው እስኪያልቅ ዶቅ-ዶቅ-ዶቅ አድርገው ይጠጣሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ይከነበላሉ፤ አለበለዚያም ወደፊት ይከስከሳሉ፡፡ አንድ ጠርሙስ ቮድካውን ጨርሶ ወደኋላም ገደል ሳይገባ ወደፊትም ሳይከነበል የቀረው፣ በደህና የወረደው አሸናፊ ይሆናል፡፡ አቶ ክብር ወይም ስምና ዝና እዚህ ድረስ ያደርሣል፡፡

ሩስኪዎች ደግሞ የነዶስቴዬብስኪ አገር አይደሉም? ይህቺን ቤቶች ሲፋጩ ይለውጧታል:: ተፋላሚዎቹ ወጥተን ጀርባ ለጀርባ እንቆማለን:: ተፋላሚዎቹ ሁለታችንም ጥይት የተለጎመበት ሽጉጥ ይዘናል:: ዳኛ አለ:: ይቆጥርልንና በተፈቀደልን ርቀት ከደረስን በኋላ ዞረን እንተኩሳለን:: ብቆስል የሚያነሱኝ አማኞች አሉ:: ሐኪምም አለኝ:: እዚያ ፍልሚያው የሚከሄደው በጠዋት ነው:: ደግሞ እንቁላርም ያውቃሉ:: ይሁን እንጂ በሕግ የተከለከለ ነው:: ባሕላችን ስለሆነ እያወቅን ነው የምንፋለመው:: አየኸው? ቀደም ብሎ እንዳጫወትኩህ አሌክሳንደር ፑሽኪን ያለፈው እንዲህ ነው:: ሌላው ደራሲያቸው ሚካኤል ሌርሞንቶቭ የሞተው እንዲሁ በፍልሚያ ነው:: የሆድ ጣጣ ሲቀር ጊዜ ክብር art ሆነች:: ከድ እፍ ሆነር

ጋሼ ባለበት ከጓደኞቹ ጋር ከበነው እንጨዋወታለን፡፡ አንድ ጓደኛዬ ድመት በጣም እንደሚፈራ ሲናገር ጋሼ ከአፉ ነጠቀውና «የሁላችንም ነፍስ የአይጥ ስለሆነ ነው» ሲል ሰምቼዋለሁ፡፡

ፍቅርንና ተሰጥኦን እያወዳደርን እናወጋለን፡፡ አንደኛው ጓደኛችን የአያሌ ደራሲያንን ስም ጠራና «ጂኒዬስ የሆኑት ከሴቶች ጋር ፍቅር እያሉ ጊዜና ጉልበታቸውን ባለማባከናቸው ነው» አለ፡፡

ጋሼም የጓደኞችንን ሐሳብ ተረድቶ ከወንድ ጋር ምንም ዓይነት ጥምረት ሳይኖራቸው የተሣካላቸው የሴት ደራሲያንን ስም ጠራና «እነዚህ ቆነጃጂት የድርሰት ሥራቸው የተሣካላቸው ከምንም ዓይነት ወንድ ጋር ባለመተቃቀፋቸው ሊሆን ይችላል፡፡ እነ እገሊትን ብትወስድ ደግሞ ደስ ካላቸው ወንድ ጋር እንደልባቸው እየተቃቀፉ ነው ጂኒዬስ የሆኑት፡፡ እኔ ግን እንደ ነፍስህ ከምትወዳትና ከጂኒዬስነት ምረጥ ብትለኝ፣ አትጠራጠር ጂኒዬስነትን ቻው! ብዬ አትየምወዳትን ልጅ እቅፍ ነው የማደርጋት፡፡»

ሞቼ እንደገና የመወለድ ዕድል ቢኖረኝ ሴት ሆኜ መፈጠር እመርጣለሁ፡፡ ለምን? ማለት ጥሩ፡፡ እንዴት መሠለህ፣ ልብ አትለው ይሆናል እንጂ የሴትነት ዓለም ውብ ነው፡፡ መጀመሪያ መመልከት ያለብን በሴቶችና በወንዶች መካከል የተፈጠረውን ልዩነት የሚጠላ፣ ወይም የሚሰርዝ የለም፡፡ ሁለቱም አንዱ ለሌላው፣ ሌላው ለአንዱ ይፈላለጋሉ፡፡ ከልዩነታችን ለሴቶች እንሰጣቸዋለን፡፡ እኛም የሌለንን ከእነርሱ እንወስዳለን፡፡ የእዚያኑ ያህል አለ የሴት ልጅ ተፈጥሮ የሚማርከው፡፡ የወንድ ዓለም 'fascinate' የሚያደርጋቸው ሴቶችም አሉ፡፡ አብዛኞቻችን የምንኖረው በራሳችን ዓለም ነው፡፡ እኔ ግን የሴቶችን ዓለም ለመኖር በርካታ ጊዜያት በተመስጦ አብሰልስዬዋለሁ፡፡ በሴቶች ላይ የተዓፋትን እንብቤአለሁ፡፡ ከሐና ጋር ሳንደባበቅ አፍረጥርጠን እውግተንበታል፡፡ እናም ይማርከኛል፡፡

***

@Amharicbookstore



፳፫

## አልአሚን

የታላቅ ወንድሜ የአያይ ገብረ ክርስቶስ ልጅ ብርሃን ወይኖ ነበር፡፡ ብርሃን 'ብሪሊየንት' ነው፡፡ በተጨማሪ ጨዋታም ያውቃል፡፡ ልክ እንደ አባቱ ነው፡፡ ሳቅ በደንብ ያውቃል፡፡ አስር ደቂቃ አብረኸው ከሆንክ ቢያንስ አምስት ደቂቃውን ሳትስቅ አትቀርም፡፡ ከእኔ ጋር በጣም እንግባባለን፡፡ መጣ እንግዲህ መመየን አስፏል፡፡ አዋየኝ፡፡ አወጣሁ አወረድኩና «እንግዲህ ብርሃን ስማ» አልኩት፡፡ «አያይ ገብረ ክርስቶስ እናንተን ለማሳደግ ብዙ ያየው መከራ አለ፡፡» ብዬ በዝርዝር ነገርኩት፡፡

መከራዎቹ ብዙ ናቸው እሱ አይመረርም እንጂ፡፡ «እና አንተ አወይናለሁ ብለህ ምናምን ምናምን ብለህ ብትሄድና ብትሞት አደጋ ነው ብዙ ተስፋ አድርጎብሃል እና አስበውና ወስን፡፡ የአሁኑ ውሳኔህ ግን ቅብጠት ነው ተወው» አልኩት፡፡ ሁለት ሣምንት ቆይቶ ግን ወየነ፡፡

ሌላም አሉ፡፡ ሁልጊዜም የሚያስቁን ሰውዬ ናቸው፡፡ ምን ያህል ነው ለማሳቅ የሚችሉት ሳውጋህ፡፡ አንደ፡ ወደ ጎንደር ይበራል፡፡ አውሮፕላን ውስጥ አለ አይደለም ከበረራ በፊት ለሚጓዙ ማሳሰቢያ ይነገራል አይደል፡፡

የጉይለቱ ረዳት ወይም ጉዳዩ የሚያገባው ሰው ተጓዦች ቀበቶአችሁን አጥብቁ እንደዚህ እንደዚህ ይባላል፡፡ ደንብ ነው፡፡ አለቃም «አይ ሲያቀብጠኝ አውሮፕላን ውስጥ ገብቼ ወራጅ!» አሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው ናቸው፡፡ እኛ ስንጠራቸው አለቃ ነው የምንላቸው፡፡ መጡና «እነዚህ ሰዎች አበዱ?» አሉኝ፡፡ ደርጎቹን ማለታቸው ነው፡፡ «ምን ይበጃል?» አልኳቸው፡፡

«እ እንዲህ አይቀልድብንም እኔ አወይናለሁ ስልሳ ብር አበድረኝ፡፡ በሕይወት ከተገናኘን ብድርህን እከፍላለሁ» አሉኝ፡፡ የጠየቁኝን ያህል ብር አበደርኳቸው፡፡ ሄዱ፡፡ አልተመለሱም፡፡ እንደወጡ ቀሩ፡፡ እንደ ፈራሁት ሳይሆን ብርሃን ግን ተመለሰ፡፡

ጋሼ ባለበት ከጓደኞቼ ጋር ከበነው እንጨዋወታለን፡፡ አንድ ጓደኛዬ ድመት በጣም እንደሚፈራ ሲናገር ጋሼ ከአፉ ነጠቀውና «የሁላችንም ነፍስ የአይጥ ስለሆነ ነው» ሲል ሰምቼዋለሁ፡፡

ፍቅርንና ተሰጥኦን እያወዳደርን እናወጋለን፡፡ አንደኛው ጓደኛችን የአያሌ ደራሲያንን ስም ጠራና «ጂኒዬስ የሆኑት ከሴቶች ጋር ፍቅር እያሉ ጊዜና ጉልበታቸውን ባለማባከናቸው ነው» አለ፡፡

ጋሼም የጓደኛችንን ሐሳብ ተረድቶ ከወንድ ጋር ምንም ዓይነት ጥምረት ሳይኖራቸው የተሣካላቸው የሴት ደራሲያንን ስም ጠራና «እነዚህ ቆንጆጂት የድርሰት ሥራቸው የተሣካላቸው ከምንም ዓይነት ወንድ ጋር ባለመተቃቀፋቸው ሊሆን ይችላል፡፡ እነ እገሊትን ብትወስድ ደግሞ ደስ ካላቸው ወንድ ጋር እንደልባቸው እየተቃቀፉ ነው ጂኒዬስ የሆኑት፡፡ እኔ ግን እንደ ነፍስህ ከምትወዳትና ከጂኒዬስነት ምረጥ ብትለኝ፣ አትጠራጠር ጂኒዬስነትን ቻው! ብዬአት የምወዳትን ልጅ እቅፍ ነው የማደርጋት፡፡»

ሞቼ እንደገና የመወለድ ዕድል ቢኖረኝ ሴት ሆኜ መፈጠር እመርጣለሁ፡፡ ለምን? ማለት ጥሩ፡፡ እንዴት መሠለህ፣ ልብ አትለው ይሆናል እንጂ የሴትነት ዓለም ውብ ነው፡፡ መጀመሪያ መመልከት ያለብን በሴቶችና በወንዶች መካከል የተፈጠረውን ልዩነት የሚጠላ፣ ወይም የሚሰርዝ የለም፡፡ ሁሉቱም አንዱ ለሌላው፣ ሌላው ለአንዱ ያፈላሊጋሉ፡፡ ከልዩነታችን ለሴቶች እንሰጣቸዋለን፡፡ እኛም የሌለንን ከእነርሱ እንወስዳለን፡፡ የእዚያኑ ያህል አለ የሴት ልጅ ተፈጥሮ የሚማርከው፡፡ የወንድ ዓለም 'fascinate' የሚያደርጋቸው ሴቶችም አሉ፡፡ አብዛኛዎቻችን የምንኖረው በራሳችን ዓለም ነው፡፡ እኔ ግን የሴቶችን ዓለም ለመኖር በርካታ ጊዜያት በተመስጦ አብሰልስ ዬዋለሁ፡፡ በሴቶች ላይ የተፃፉትን እንብቤአለሁ፡፡ ከሐና ጋር ሳንደባበቅ አፍረጥርጠን አውግተንበታል፡፡ እናም ይማርከኛል፡፡

***



፳፫

## አልአሚን

የታላቅ ወንድሜ የአያይ ገብረ ክርስቶስ ልጅ ብርሃን ወይኖ ነበር፡፡ ብርሃን 'ብሬሊየንት' ነው፡፡ በተጨማሪ ጨዋታም ያውቃል፡፡ ልክ እንደ አባቱ ነው፡፡ ሳቅ በደንብ ያውቃል፡፡ አስር ደቂቃ አብረኸው ከሆንክ ቢያንስ አምስት ደቂቃውን ሳትስቅ አትቀርም፡፡ ከእኔ ጋር በጣም እንግባባለን፡፡ መጣ እንግዲህ መወየን አስቧል፡፡ አዋየኝ፡፡ አወጣሁ አወረድኩና «እንግዲህ ብርሃን ስማ» አልኩት፡፡ «አያይ ገብረ ክርስቶስ እናንተን ለማሳደግ ብዙ ያየው መከራ አለ፡፡» ብዬ በዝርዝር ነገርኩት፡፡

መከራዎቹ ብዙ ናቸው እሱ አይመረርም እንጂ፡፡ «እና አንተ እወይናለሁ ብለህ ምናምን ምናምን ብለህ ብትሄድና ብትሞት አደጋ ነው ብዙ ተስፋ አድርጎብሃል እና አስበውና ወስን፡፡ የአሁኑ ውሳኔህ ግን ቅብ ጠት ነው ተወው» አልኩት፡፡ ሁለት ሣምንት ቆይቶ ግን ወየነ፡፡

ሌላም አሉ፡፡ ሁልጊዜም የሚያስቁን ሰውዬ ናቸው፡፡ ምን ያህል ነው ለማሳቅ የሚችሉት ላጫጋህ፡፡ አንደ ወደ ጎንደር ይበራል፡፡ አውሮፕላን ውስጥ አለ አይደለም ከበረራ በፊት ለሚጓዙ ማሳሰቢያ ይነገራል አይደል፡፡

የጉደይለቱ ረዳት ወይም ጉዳዩ የሚያገባው ሰው ተጓዦች ቀበቶአችሁን አጥብቁ እንደዚህ እንደዚህ ይባላል፡፡ ደንብ ነው፡፡ አለቃም «አይ ሲያቀብ ጠኝ አውሮፕላን ውስጥ ገብቼ ወራጅ!» አሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው ናቸው፡፡ እኛ ስንጠራቸው አለቃ ነው የምንላቸው፡፡ መጡና «እነዚህ ሰዎች አበዱ?» አሉኝ፡፡ ደርጎቹን ማለታቸው ነው፡፡ «ምን ይበጃል?» አልኳቸው፡፡

«እ እንዲህ አይቀልድብንም እኔ እወይናለሁ ስልሳ ብር አበድረኝ፡፡ በሕይወት ከተገናኘን ብድርህን እከፍላለሁ» አሉኝ፡፡ የጠየቁኝን ያህል ብር አበደርኳቸው፡፡ ሄዱ፡፡ አልተመለሱም፡፡ እንደወጡ ቀሩ፡፡ እንደ ፈራሁት ሳይሆን ብርሃን ግን ተመለሰ፡፡

@Amharicbookstore

በኋላ እንደሰማሁት የአክሱሙን ባንክ ወይኒዎች ሲዘርፉ አሲቃ ነበሩ መሪው:: እንዲህ ዓይነት አደገኛ ጨዋታ እየተጫወቱ መትረፍ አይታሰብም:: እኛ አሲቃ እንላቸዋለን እንጂ የጦር ሜዳ ስማቸው አልአሚን ነበር:: «ታማኙ» ማለት ነው በአረብኛ::

***

# ፳፮

## ሻህራዛድ

ጋሼ ስብሐት ለስንዱ አበበ የጻፈው የፍቅር ደብዳቤ እንዳለ ሰማሁ:: ከስንዱ ጋር ጥሩ መቀራረብ ስለነበረኝ እንዳገኘኋት ስለዚህ መጽሐፍ አወጋኋት::

ስንዱ አበበ በአንድ ወቅት የጋሼ ስብሐት ቃል አቀባዩ፣ በኋላማ የስብእዊ መብት ተከራካሪው ነበረች:: ቀጭ ብለን ስናወጋ ሰድሜዬን ጠየቀችኝ:: ከመጽሐፉ ጋር ምን አዛመደው? በሚል ስሜት አብሰለሰልኩና አራት አስርት ዓመታት ውስጥ መግባቴን ነገርኳት::

ጥሩ ነው:: "ቶሎ ቶሎ ጻፍ፣ ብዙ ሰዎች ዕድሜያቸው ሃምሳ ዓመት ከሞላቸው በኋላ ከመሥራት ይልቅ ትዝታቸውን ማውጋት ይቀላቸዋል:: ከዛጠመኚ አንፃር አንተም ወደትዝታህ ልትመለስ አሥር ዓመት ነው የቀረህና ፍጠን::" ስትለኝ አብረን ሣቅን::

"ለሥራው መነሻ የሚሆነህ ምን ላዋጣ?" አለችኝ፡፡

እጇ ላይ ያለውን ደብዳቤ እንደምፈልግ ነገርኳት፡፡ ተስማማን፡፡ ተቀጣጠርን፡፡ በቀጠሮው ዕለት ስናወጋ "የፍቅር ደብዳቤ መሆኑን አላውቅም ነበር፡፡ በኋላ ጋሼ ስብሐትን ስጠይቃቸው አለማወቅሽ ነዋ እርፍናው?" አሉኝ አለችኝ፡፡

ጋሼ ስብሐትን በዕለተ ሰንበት እሷ ቤት እንድንገናኝ ቀጥሬው መጣ፡፡ እንደምርጫችን እየተጎነጨን ይህንን ደብዳቤ ስንዱ ታነብልን ጀመር፡፡

ጋሼ በጣም ተደንቆ አዘውትሮ እንደሚያደርገው "ፐ! አንድ ሁለት መስመር ወደኋላ ተመለሺና አንብቢልን፡፡ ኡ እዚህ ጋ!



ጉዬቴክ አገላለፅ!" እያለ ያደንቃል፡፡ ይህን የፍቅር ደብዳቤ የፃፈው እርሱ እንደሆነ ነገርነው፡፡

"ተው እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡ እኔ ከሆንኩ ጉዬት ነኝ ማለት ነው፡፡ ጉዬት መሆኔን ባውቅ ጥቂት ሳልከራባችሁ አልቀርም" አለን፡፡

ደብዳቤዎቹ በየጊዜው የተፃፉ ናቸው፡፡ በመካከላቸው ጉስተኛም አልገባ፡፡ ብቻውን በሆነ ቁጥር ይፅፍላታል፡፡ የዕለቱ ዕለት ወይም፣ በሌላ ቀን ተቀብላው አንብባ ታጠራቅመዋለች፡፡ ስለዚህ እነዚህ ስብስብ የበርካታ ክዕለታት አንድ ቀን ጥርቅሞች ናቸው፡፡

በትንሽ የማስታወሻ ደብተር በየጊዜው የተፃፉትን ደብዳቤዎች ተቀብያት አየኋቸው፡፡ ባለፉት ሰባት ዓመታት አሳምሬ የማውቀው የእጅ ጽሑፍ አፈጠጠብኝ፡፡ ፊገማ አልኩ፡፡ እርሱ እንደፃፈላት አረጋገጥኩ፡፡

የጋሼ የእጅ ጽሕፈት ጠዋትና ማታ ይለያያል፡፡ ጠዋት ከሆነ በማለዳ ሕሊና ስለሚፃፍ ጥርት ያለ ሲሆን፣ ሐሳቡ በደንብ ተገልጾ ይነበባል፡፡ ጀንበር ካዘቀዘቀች የሚፃፈው ግን ትልህና በትላልቅ ፊደል የሰፈረ ውስን ሐሳቡን የያዘ ሆኖ የዕለቱን ናፍቆት የሚገልፅ ነው፡፡ ዛሬ ይህ ደብዳቤ ታሪክ ሆኗዋል፡፡ የተፃፈላትም የፍቅር ደብዳቤ መሆኑን አላውቅም ስትል፣ ፀሐፊውም መፃፉን ረስቶታል፡፡ ጋሼ ይህን ደብዳቤ ብጠቀምበትም፣ ብተወውም መብቴ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ የስንዱን ፍቃደኝነት ስጠይቅ እንደፈለኩ እንድጠቀምበት ሰጠችኝ፡፡ እናንተጋ በማድረስ ረገድ ይህ በሁለቱም አቅጣጫ ዕውቅናን የተነፈገውን ደብዳቤ በሚወዳት ገፀ ባህሪ በሻህራዛድ ሥም ላስነብባችሁ፡፡

ብዙዎቻችን ወንዶች ለምናፈቅራቸው እንስቶች በልባችን የምንፅፍላቸውን ደብዳቤ ጋሼ ስብሐት በብዕሩ አስፍሮልናልና እነሆ!

መጋቢት 20/1980 ዓ.ም

"…On n'aime plus Personne des qu'on aime…"

M- Proust

"ፍቅር ከያዘን ሰዓት አንስቶ ማንንም አንወድም"

ማርሴል ፕሩስት

ባገኘሁዋት ቁጥር እሷ ነብሷን ለሳቅ ትለኩስልኛለች፡፡ ነብዩ የወደፊቱን የሚመጣውን እንዲያሳትፍ፡

እሷ ያለፈውን የወደኋላውን (ልጅነቴን) የምታሳትፈኝ፣

ያውም ያን ሁሉ የልጅነት ሳቋ ተንኮል አክላበት!!

ሻ ፀሐይ!

@Amharicbookstore

አንቺ ስትመጪ ሊቀበልሽ ከውስጤ ይወጣል፣ አበባው፣ ከከቡ፣ ጨረቃው ፈገግታው፣ ያለኝ ቆንጆ ነገር ሁሉ ተዘግቶ ከቆየበት ይወጣል አንቺ ስትመጪ ዙሪያውን ሲያስስ የነበረው ፊትሽ እኔ ጋ ሲደርስ፡ በፈገግታሽ ብልጭ ይላል፡
ያኔ እኔ ውስጤ ብርሃን ፈገግታ እሆናለሁ፡፡ ባየሁሽ ቁጥር!
ለሻራዛድ
"ሁልጊዜ ሻህራዛድ በኔ ይሁንብሽ! እውነቴን ነው
ይህ የናፍቆት መዘባረቅ ነው፡፡
ደብዳቤ፣ ደብዳቤ፣ ደብዳቤ
Proustን ሳነብ ቆይቼ አንቺ ስትመጪ መጽሐፉን ስዘጋና ወዳንቺ ስዞር እኩል ይሆናል (አንድ በይ) ከመቼው ከሱ ወዳንቺ ማለት!
ወይ አቶ Proust! አላስጠጣ አላስጥፍ አሉንኮ!
እና ለካ ይኸውልሽ ሻህራዛድ ሆይ (አንቺ ነሽ ሻህራዛድ)
ሀልም ዓለም አልቤርጎ ማደር በጀመሩ በ8ኛው ንጋት (ወዬው! ስምንተኛው ሺ ሲነጋ ወይም ሲጨልም ይሆንንንዴ? ምናልባት ከቶ? (ከዚህ በፊት ተብሏል፡፡ ግን እንደ ውሻ ጩኸት ወይም እንደ ዕብድ አባባል እንዲህ ሐሳብን ዝም ማሰኘት ላይቻል ነው)

ደብዳቤ ለሻ ነብሴ
ብትፈልጊ የመጣውን በመቀበል የተቀበለውን መልሶ በመወርወር ኢየሱስ ነብሴ ካንቺ እኩል ሊሆን ይችላል ቢፈልግ!
!!! ወይኔ፡ ሁለታችሁን አንድ ላይ ባየሁዋችሁ!! ሰለሞን ይሆንንንዴ?
አንዳንዴ ሁሉ ወለል ብሎ ይታየኛል ከገዛ ራሴ ጭምር!!
እና ተወው ዝም በለው የፈለገውን ይሁን ወደፈለገው ይውሰድህ... ይለኝና ራሴ፣
እንቃና! የዚያችን የፀሐይ ነገር ሳላይ?!
እላለሁ፡፡ ነብሴ ትሆንንንዴ? ቅዱስ ሚካኤልን!!!
ለሻ ነብሴ አፈርድሚ ጠጅ ቤት ውስጥ ያዝማሪ ዘፈን እየሰማሁ፡ አቤት ደስ ማለቱ! ከድንገተኛ ፈገግታሽ እኩል! ሲመጣልኝ ላንቺ!
እንግዲህ መጣብኝ፡፡ ያ ሁሉ ሳቅና ያ ሁሉ ማዘን ያ ሁሉ ግዴለሽነት ያ ሁሉ ሻህራዛድ
አንዲትም ቃል የለች አንቺን የምታክል አንቺን የምትወክል፡፡ አጀብ! ማለቱ ይበቃል!! አንድ ቀን ካንቺ ጋር ሆኖ ማለፉ ይበቃል!! አትጠገቢምንጂ!

@Amharicbookstore



ሻ ነብሴ፣ ሰዎችና ተረቶች አንድ እየሆኑብኝ፡፡ እንግዲህ አንቺ ሰው ነሽ እያልን ነው፡፡ ውስጡ ግን ሻህራዛድና አንቺ ልዩነት ይኑራችሁ? እንጃ!!
መሆኑን ከናት እኩል እናት መሆን ያልተፈረደበት አባት ቀረበት!
ይኸ ዝም ብሎ መዘባረቅ ይመስላል፡፡ ነውም!!! ደሞም እውነት ነው፡፡
ስቀጥል ሻ ነብሴ፡ ስላንቺ እንዲያ የሚመስለኝ ለካ እኔ ብቻ አይደለሁም፡፡ ሊያውም ደግሞ አይቸዋለሁ አውቀዋለሁ ሰለሞን ዛሬ ማታ ስሸኘው ስላንቺ ነገርኩት፡፡ ለካ ሁለታችንም ነን ያንቺ ተከታዮች፡ ጠባቂዎች፡ አፍቃሪዎች! ወይስ አንቺ ነሽ የተላክሽልን? እና እንደምትሰበር ዕንቁላል የምንጠብቅሽ፡፡ ያውም ከኛ የጠነከረ ብረት መሆንሽን እያወቅን ነው!
ቅዱስ ሚካኤልን! ነብሴ ሻህራዛድ! ከዚህም በኋላ ገና ልጅ ነሽ፡፡
ደብዳቤ ለሻ ነብሴ፣ ከዝምታ ከፀጥታ እንኳ ትሻይኛለሽ! ሻ ነብሴ

10፡9፡80

አሁን የምፅፍልሽ በ4:30 ሰዓት በማምት በአፈርድሚ ከሺ. ሰማንያ ሙጥቼ፡፡ እና ከሺሰማንያ እስከ አራት ኪሎ በእግር ስመጣ ካንቺ ጋር እየተጫወትኩ ስለ ሥዩም በቲቪ. አይቼው!
ይኸውልሽ ይሁኔ በኃይል ያውቀኛል፡፡ ጎረቤት ወስዶ (በግድ ያህል) አሳየኝ፡፡ ያየሁት ሰለሞን አርቲስቱን እሸቴ ዘ ጃንሜዳን አራፍ አርቲስት አቅራቢውን፡፡ የእሸቴን ፊትም ሆነ ምንም አላየሁም፡፡ ሥዩምን አቀረበልን፡፡ እሱን አይቼ መንገድ ላይ ሁሉ ካንቺ ጋር ነው የምወያየው፡፡ ሰፈሬም ደርሼ ይኸው ላንቺ ነው እምጽፈው፡፡ ምን ዓይነቷ ብትሆኚ ነው? ሻ ፀሐይ፡ ለዛሬ ጽፌልሽ ጨርሼ ባፈርድሚ ጠጅ ቤት በመሸ ሰዓት አሁን " It was fascination I know king cole አንቺን ለኔ ዘፈነልኝ፡፡ ታድዬ!!!
ይኸውልሽ ሻህራዛድዬ! ውስጤ ያ ሁሉ ተዓምር አጋጠመኝ ዛሬ ዕሁድ፡፡

ግን ዓይኔን ጨፍኜ ከራሴ ጋር ተጨፋፍኜ ያ ሁሉ የዛሬ ተዓምር ሁሉ ቀርቶብኝ ካንቺ ጋር ሩብ ሰዓት እንዴት በበለጠብኝ!
ሻ ነብሴ፡ አሁን ስፅፍልሽ (ከብዙ ቀልድና ሳቅ ጋር ጠይም ፊትሽ ላይ ዓይኖቹ ብቅ ይላሉ ሁሉን ያስረሳሉ፡ በተለይ እኔን ሁሌ ሚጠብቀኝ እኔነቴን ያስረሱኛል ዓይኖችሽ፡፡ ያኔ ነፃ እወጣና (ከውስጤ) በባዶ ዓይን አይሻለሁ፡፡

ገና ዘወር ብዬ አንቺን ከማየቴ እውስጤ ባዶ የነበረው ሁሉ ሞልቷል፡፡ ያኔ ከሌላ ሰው ካንቺ ጋር መሆን እችላለሁ፡፡ እና፣ ዘወር ብዬ በሙሉ ዓይኔ ሳይሽ፣ ልቤን ባዶ አድርጌ ግቢበት እያልኩ ሳይሽ፣ ሳይሽ፣ ሳይሽ፣ ሳይሽ ዝምበል ብዬ ተዝናንቼ ሳይሽ፣ ሳይሽ የማታልቂ ድንቅ ምሥጢር ነሽ

ባላውቅሽ ምንቸገረኝ? አጠገብሽ መሆን፣ እብደት ልጅነትሽን መጋራት

እነሆ ሻህራዛድ ነብሴ የመጀመሪያ ተዓምር፡፡

ሻ ነብሴን ሸኝቼ ስመለስ፡፡

አይ ሻ ነብሴ ይህንን ብጥፍልሽም ባልጥፍልሽም ልዩነት የለውም፡፡ እስከዛሬ የጣፍኩልሽን ግን እንኳን ጣፍኩልሽ፡፡

ሻ ነብሴ፣ ድንገት ከሩቅ ሳይሽ ነብሴ በርራ ወጥታ ትቀበልሻለች፡፡ ሐሳቦቼ ሺ አሽከር ሆነው ልቤን ይጠርጉልሻል፡፡ ያዘጋጁልሻል እንድትገቢበት፡፡

ገባሽበት፡፡

እና ርብሽ ብጥብጥ አረግሽው በሳቅ በደስታ በግደለሽነትሽ፡፡ እኔ የለሁበትም! አንቺ አጠገብ ስሆን ፍርሃት አያውቀኝም፡፡ እኔም አላውቀውም፡፡ ቅዱስ ሚካኤልን! ተንጠራርቼ ገዝፌ እየቆምኩ "ሂድ ከዚህ" ስለው ፈትለክ ይላል ፍርሁቱ!! ይኸኔ ወዳንቺ ዘወር እልና "ስማኝ፣ ሻህራዛድ ሳቅ ጥላዋ ሆይ!" ገ ሳቅ ለባሺቱ አውልያ፡፡

አንቺኮ በኑሮ ጎዳና ስትጓዝ ማንም ቢያጋጥምሽ የጉዞ መሥመራችሁ አንድ ሆኖ ቆይቶ አንድ ቀን ሁለት ከሆነ፣ ያንቺ መንገድ ይኸ አንድ፣ ያ ሌላው መንገድ ያ ሁለት፡፡ ቻው ቻው በይው፡ አብረን ስንጓዝ ግን ደስ እያለኝ ነበር በይው፡ ሲቻልሽ በአፍሽ በድምፅሽ ሳይቻል በልብሽ በውስጥሽ፡፡

"እና ምን ይጠበስ?" አላቸው ሽይጣንነታቸው

"ሲርበን እናስብበታለን" አሉትና በገዛ ምላሳቸው ሳቁ፡፡

በጣም ይቅርታንጂ ሻህራዛድ ነብሴ፡ አንዳንዴኮ እንደዚያች መግቢያ መሄጃ የሌላት ጫጬት ወፍ መስለሽ ትታይኛለሽ፡፡ እና ልቤ ይጨመቃል፣ ይጨነቃል፣ ይጨበጣል፣ ይጨፈለቃል ወዘተ፡፡ ወዘተም ይጨነቃል፣ ይጨፈለቃል፣ ይጨማለቃል፡፡

እሱ ብቻም አይደለ፣ ሻ ነብሴ፡ ሁሌ ድምፅሽ፡ ይበልጥ የሳቅ ድምፅሽ ጆሮዬን እንኳን ጆሮ ሆኜ ተፈጠርኩ! ያሰኙታል፡፡ ነብሴን! አሁን እንግዲህ የቅዱስ ሚካኤልን ትቼ ሻህራዛድ ነብሴንም ስም ጠርቼ መማል ልጀምር ነው፡፡ ዳሩ ማናባቱ ነው እኔን የሚያስምል? ያውም ያንቺ የሳቅ ጥላዋ ጓደኛ ሆኜ!!!

ሻህራዛድ ነብሴን!!!

@Amharicbookstore



ቢራቢሮ ሱፌትንና ፀሐይን ተራ በተራ ስታገኛቸው፣ ስምንተኛውን እንትን መጠራጠር ደርሶ ስለነበረ ጠረጠሩዋትና ቢራቢሮን መተማመኛሽስ? አሉዋት፡፡ እነሆ ዘበኞቹ እንዳያውቁባት በነፋስ በመርገፍ የምትውለበለብ ቅጠል መስላ ገብታ የነበረች ቢራቢሮ ክንፎችዋን ዘረጋች፡፡ የሻ ፈገግታ የሆነ ሥዕል! እና ከዚያ ወዲያ ሻህራዛድ ነብሴን የሚያገኛት የሚያደርስባት ሳቅ ጨዋታ! ሐዘን ለቅሶ የለም፡፡ እንደ ፀሐይ ልሙቃት እንጂ፡፡ እንደ ጨረቃ ልያት እንጂ፡፡ ከዚያም ይበልጥ አዲስና እውነት፡፡ እንደ ሻ እንደ ራሷ ላያት ልሞክር እንጂ፡፡ እና መግቢያው የት ነው? ዘፈንና ፀሐይ የተቀላቀሉበት ሳቋ ነው? ወይስ አንቺ ሄደሽብኝ ለራሴ ማፅናኛ እየጻፍኩ ነበር?

ሻ ነብሴ፣ ዞሮ ዞሮ ራሴ ውስጥ ተዘባርቆ እንደ ሻይ ስኳር ተማስዬ የነበር ረጋ ለማለት ስፈልግ ወይ ፈገግታሽ ወይ ሳቅሽ ወይ የሆነ ሌላሽ ሁሉም ያንቺ ተረኛ መስኮት ናቸው ከኛ ከኔ ጋር የምትተያይባቸው፡፡

Soul Sister Shahrazad
For thee we have
Full respect
Full trust
Full affection
With thee we live
The full hour
For us thou art us thou complete.
Thou art:
The complete child
The Complete Grownup.

ሻ ነብሴ ከሁሉ ደስ ከሚሉኝ አንዱ፡ አንቺ ዓለሙን፣ አዳሙን፣ አዲሳባውን ስታዩ እኔ አንቺን አያለሁ፡፡ የሳቅ ተንኮል ከየት ይመነጭ ይሆን?... ይኸንኪ ቃላት ነው፡፡ ከንቱ ነው፡፡ ምንም አይገልፅም፡፡ እንኳን አንቺን አንድ ተረት ግለፅ ስንለው አባይ በሬ ወይም ተራጋጭ አህያ ወይም ሃምሳ የበየነ ታክሲ እየሆነብን

ሻ ነብሴ፣ ሻ ስንቂ፣ ሻ ቤቱ፣ ሻ መልኬ፣ ሻ ቆንጆ ስዓቴ፣ ሻ ሙላቴ፣

ካንቺ ጋር ከሆንኩ በኋላ የኑሮን ከንቱነት እችለዋለሁ፡፡

ሻ ነብሴ፡ አንቺኮ የዓይኔ የዟት ጤዛ፣ የጣይ ጥልቀት ቀለማት፣ የሌሊት ከዋክብቱ የጆሮዬ ድምጽ፡፡ እሱማ ቋንቋ የለውም፡፡ ጆሮዬ ሁሌ ሁሌ ሁሌ ያንቺን ድምፅ በሰማ!

የሁለመናዬ ደም ሻህራዛድዬ ነሽ። ቃል የለም፣ ዝም ዝም ብሎ መደነቅ ነው አንቺን እያዩ በሌለሽበትም አንቺን እያሰቡ።

ሻ ነብሴ፦ እንዳላመልክሽ ሰው ነሽ ይባላል። እንዳልተውሽ አንቺን ያላመለኩ ማንን ወይስ ምንን አመልካለሁ? ባታመልክስ ቢቀርስ እንዳትይኝ ደሞ 'አምልክ አምልክ' ይለኛል። 'ተምበርክክ ሸቅብ ተመልከት' ይለኛል። አጠገቤ ያለሽው አንቺ ከሆንሽ። አለበለዚያ ደሞ ሳጣሽ እስካገኝሽ ማቆያ ስንቅ አለኝ። አውሰጤ መልኮችሽና ድምጾችሽ እና የምትናገሪያቸው ቃጭል ...

ሻ ናፍቆቴ፣ ሻ ጉድለቴ፣ ሻ ሙላቴ! ሙላትሽ ለሌለሽበት ሰዓት ጉድለት ሲሆኚ ይታይሽ። ግን አንቺ ወይ እኔ ወይ ሁለታችን ከኃይላችን የተነሳ በትዝታ ስትመጪልኝ በቂ ትሞይኛለሽ። አሁን ይህን ደብተር ስዘጋ ሙሉ ነኝ። ሻህራዛድ ነብሴን!!!

ሻ ነብሴ፦ አንቺን መውደድ ያህል ቀላል ነገር፣ አንቺን ማወቅ ያህል ከባድ ነገር! እንዲያውም አንቺን መውደድ ያለ ነው። አንቺን ማወቅ ግን የለም። አንቺን ማወቅ ክልክል ስለሆነ ወደ ማመሳሰል እንሂድ። አንቺና ኢየሱስ ነብሴ። ኧረ አንቺ ከየት መጣሽ? ልቤ ውስጥ የሁሉንና የሁላሁሉን ቦታ የሞላሽ የኔ ወልይ ነሽ።

ሻ ነብሴ፦ በኔ ይሁንብሽ፣ ከሞት በስተቀር እዚህኛውም ይሁን እዚያኛው ዓለም እኔ ያንቺው ማንንም ምንንም አልፈራም (ይመስለኛል) አንቺን ግን እፈራሻለሁ። ደሞ አንቺን ቀን ፍራት አያስፈልግም። እፎይ! እንኳን እምፈራትን አገኘሁ!!

ሻ ነብሴ፦ ሻ ልቤ፣ ሻ ውስጤ፣ ሻ ውበቴ፣ እና ሻ ብርሃኔ፣ ያን እሽቱን አንድ ቀን የጮህኩበትን ስለነገርሽኝ ዛሬ ደሞ ካንቺ ጋር ላመሽ መጥቼ ከሱ ጋር አመሸሁ። ስንሊያይ እጅ ለእጅ ተሳስምን። ዕድሜ ላንቺ!

ሻ ነብሴ፦ ዛሬ ማታ ግሮሰሪ ረኻም ምሽት ካንቺ ጋር አመሻለሁ ስል ብቅ ብለሽ ሄድሽብኝ። ለካ ተራዬ ኖሯል። ለሌላው ሰው ብርሃን ሆኜ አመሽሁልሽ እልሻለሁ። ነብሴ ያውም እሸቴ ጋር ስንጫወት አመሻሽንና እጄን ስሞ ተለያየን። አንቺ ለኔ የምታበሪልኝን ያህል እኔ ደሞ ለሌሎቹ ብርሃን ሆኜ አላመሸሁም መሰለሽ? ያም ሁሉ ሆኖ ግን ካንቺ ጋር ሩብ ሰዓቴ ይበልጥብኝ ነበር። ሻህራዛድ ነብሴን!!!

አሁን ወደ አራት ሰዓት ላይ ነው። ያን ሁሉ ጊዜ አንቺን ወክዬሽ ለሌላው ሰው ማረፊያው ስሆን ነበር እልሻለሁ። ቻው ፍቅርዬ!

@Amharicbookstore



ሻ ነብሴ፣ አንቺንኳ ማወቅ ማስረዳት አይኖርብሽም፣ ብቅ ማለት ብቻ! ብቅ ብለሽ መሄድሽ ይበቃል። እኔን ደፋር ፃድቅ አድርጎኝ አመሸ።

ሻ ነብሴ፣ አሁን ብው ብዬ ስክሬ ነው ምፅፍልሽ (ደብዳቤ!) አንቺ ፀሐይ እኔ ሱፍ ከሱፍ ሱፍ ተፊት። አንቺ ኮከብ እኔ - ዓይን። አንቺ ውሃ እኔ ጥም። አንቺ እንቅልፍ እኔ ህልም??

ሻ ነብሴ እንኳን ማለቂያ መጀመሪያ የለሽም። ለኔ ዘላለሜ ነሽ። እና ማን ትሆኚ?

ታድዬ! (ባንቺ አባባል) ታድዬ በኑሮ ጉዞ አንቺን ማግኘቴ። ግን እኔ ያንቺ ወንድም አልፈራም እንጂ (እንበል) ብፈራ ኖሮ የሚያስፈራኝን ልንገርሽ?

ሻ ነብሴ ሳታጋጥመኝ ይህን ኑሮ አልፌው ቢሆንስ?

ውዷ ሻህራዛድ፦ ዛሬ ሳላይሽ ዋልኩ። ቀኑ ግማሹ ባዶ ሊሆንብኝ መስሎኝ ነበር ግማሹን ትውስታሽ ይሞላዋል።

ቀኑ ጎደሎ ሊሆንብኝ ነበር ስልክ ደወልሽልኝና (ያውም ሁለቴ) በድንቅ ድምፅሽ ሞላሽው እየሳቅሽ።

ድምፅሽን መስማት እንደሚያቅተኝ እንዴት አወቅሽ ግን!

እንዴት ደግ ነሽ! ጎዶሎውን ቀን ስትሞይው ይህ ሌላው የሻ ነብሴ ተአምር ነው። ያንቺው የራስሽ። የሁሌሽ።

ሻ ነብሴ፣ ዛሬ እስክትመጪ ስጠብቅ ይህን ከመጀመሪያ አነበብኩት። በዚያ ዓይን ብታነቢው ቆንጆ የፍቅር ተረት ነው። በራሱ አባባል የተባለ።

ሻ ነብሴ ምናልባት (ካስቻለኝ) የመጨረሻው ደብዳቤ አንቺ እና 'ወይዘሮ' በብዙ አይነት ትመሳሰሉብኛላችሁ። ከልማድ ውጭ እነብሴ ውስጥ እሆናለሁ እናንተን ሳገኛችሁ።

ዋ! ለወይዘሮ ደብዳቤ መጻፍ አለመቻሌ!

------------------ // --------------

ሻ ነብሴ፦ አንቺ ሁሌ ያቺው አንቺ፣ ለኔ ሁሌ ሌላ ምስጢር ትሆኚልኛለሽ። አንቺ ባለሽበት ደሞም አንቺ በነበርሽበት ለኔ ያ ቦታና ጊዜ ደስና የደስ ደስ አለው ሁልጊዜ!!

ሻህራዛድዬ ስንት ቦታ አየሁሽ!! እና ሁሌ አንቺው ነሽ!! እና እቴዋ፣ እና እኔዋ (!) ነብሴ፦ አንዳንዴ ሻ ነብሴ፦ እዝጌር ራሱ ተወራርዶኝ አንቺን ላከሽ (በስሜቴ ውስጥ) ብል እንካ ሳቅ ድፍረት ለሌላው ማዘን በሌላው መሳቅ በላ!! በላ! የኛ 'ነብስ' አለኝ።

"እስቲ አንድ ቀን አንድ ሰዓት አንድ ደቂቃ ከሻራዛድ እኩል ሁን። አለያም አምልካት እኛ ላንተ የላክናት ናት። ያውም እግረ

መንገድዋን አጋጥመሃት እንጂ (ታድለህ!) እሷማ ገና የትና የት የምትሄድ ሰንትና ሰንት የሚጠብቃት..."

ሻ ነብሴ፦ ለካ አንድ ዕድሜ ሲደርሱ ለራስ መፍራት ከተራገፈ በሁዋላ ለሚወዱት መፍራት፤ ያውም ከኛ ይበልጥ ጠንካራ ሆኖ፡፡ ሻህራዛድ ሆኖ!!

በሌለሽበት

እቴዋ፦ ካንቺ የተማርኩት አለ፣ ካንቺ ጋር መሆን ይበልጥብኛል እንጂ በስጋ በሌለሽበትም ካንቺ ደግነትና ጤነኛነት ሙሉነትና ፀሐይነት ቁጤማነት ሰጥተሽኝ ወስጄ ልቤ ውስጥ ቆልፌበት የነበረውን አወጣውና ከሱ ጋር እቆያለሁ፡፡ ያቆየኛል፡፡ ለምለም ሣር እስኪደርስ ጭዱ በሬውን እንደሚያቆየው፡፡ ወይም ፀሐይዋን ሲሞቁ ቆይተው እሷ በሙቀትዋ ያጠራቀመችውን ባትሪ፡፡ ትውስታ ትዝታ ወደ ቅድም ገልመጥ መልከት ብዬ ከዚች ከምጥፍበት ደቂቃ እስክሪፕቶውን እንደጋባቢ ፈረስ ቶሽ ብዬ ባቆመውና ቆም ቢል እና ገልመጥ ብል ምን አያለሁ? ያንቺን ብርቅርቅ ለምለም ድንቅ ሥጋና ብርሃንን አንድ ላይ የያዝሽ...

እቴዋ ሻ ነብሴ፦ በሌለሽበት ነብስ ለነብስ ሆነን ስለሚታየኝ፣ ያኔ ታላቅ ነሽ በኔ ቤት፡፡ በኔ ልብ

ዩህን ደስ በሚል ልንገርሽ በታሪክ ምሳሌ

Qeiz Roleigh – Knight of the…

አሁን አብረሽኝ በነበርሽ በሳቅሽ በሳቅኩ በሳቅን፡፡ የሳቃችን ባለድምፅሽ መብረቅ ጣራውን ቀዶ ሃይ ሰማዩን በሰነጠቀው፡፡ ለኔ ያኛ ያህል ሀብቴ ነሽ፣ ለኔ ያን ያህል ፀጋዬ ነሽ፤ ለኔ ያን ያህል በረከቴ ነሽ፤ ለኔ ያን ያህል ድንቅ እጣዬ ነሽ፡፡ አንቺ ግን ላንቺ አንቺ ነሽ፡፡

አንቺ ላንቺ ለውስጥሽ አንቺ ማን እንደሆንሽ እንጃ... ይኸኔ ስሜትም አይሰጥሽ፡፡ ላንቺ ለውስጥሽ ድብቅ ስውር የሆነችዋ የውጭዋ አንቺ፣ እሷ ናት የኔ ሻህራዛድ፡፡ ስለሷ ነው ሁሌ የምጥፍልሽ ስለሷ ነው የማታውቂ፡፡ (ሁለታችሁ አንድ ናችሁ)

እሷ ለራሷ ተአምር ነገር፤ የጠፋሁ መንገደኛ ባጋጣሚ አጋጥሚያት ቢጨልም ብርሃን ሆናኝ ቁጥር የሌለው ፀጋ ሰጥታኝ እኔ ዕድል አገኘሁና ነው እንጂ ያቺ የኔ ተዓምር፣ የለገሰ ተአምር፣ የአሰፋ ጉያ ተአምር እስቲ ለስንቱ ናት? እንዲህ ብለሽ አክብሪያት አድንቂያት፡፡ በብዙዎቻችን መሀል ነው ምትኖረው፡፡ ምትውለው ለብዙዎቻችንም ደስ ትለናለች፡፡ ቀኑ እሷም ባትኖር ይጎድልብናል



ለያንዳንዳችን በየበኩላችን፡፡ እሷ ደሞ እሱን ታውቃለች (በምናንደምታውቀው እንጃ)

ለኔ ለሌሎቹም እንደየሚገባቸው ዳር የለሽ ትሆንብናለች፡፡ እኔ ታድዬ ነቃ ብዬ በማያይ ዓይን ባየሁዋት ቁጥር የምትታይ ናት፡፡ ሽ ዓይን በኖረኝ ለሷ! ዓይኔ እሷን ሳያይ ጨልሞ ቢሆን እና አውቄው በነበር፡ ካለመፈጠር ካለመኖር ካለመሳቅ እኩል ጠቀመኝ፡፡

ደግነቱ (ያጋጣሚያዋ) ደግነቷ (የሷ) ደግነቴ (የኔ) ተናገረች ሰማኋት፡፡ የደረሰችኝ ሎተሪ ናት፡፡ ድምጿን ነው፡፡ አይ የሷ ድምፅ! እዚህ ውጭ ሆነች አቤት! አቤት ድምጿ! አቤት ድምጿ! አቤት! አቤት! አቤት!

ድምጿ ለጆሮዬ አቤት ሲጣፍጥ! አቤት ልብ ሲያጠፋ! 'አላሁ አክባር!' ቢል በድምፃዊ ድምፅ እና አማኝ ቢሰማው ከዚያ ያርቃል ልቤ እስኪጠፋ ድምጿ የሷ፡፡ ስትናገር ስትስቅ ስትጣራ ስትተነኩል፡፡ ያ ተንኮል የኔ ገነት!

እሷ ለራሷ ወሰን የላት፣ ቃላት በአቅማቸው ከድንጋይ ውርወራ አይርቁ፡፡ ወሰን የለሽ ናት አላህሽ ናት ለኔ ሁሌ! ሁሌ! ሁሌ!

(አሁን እሷን ተሰናብቼ ወደ አቶ አጋፋሪ ወዘተ)

ሰውየውና ኩረዳይቱ

ስድሳ ዓመቱ ነው፡፡ ኧረ ለራሱ መስታወት ካየ ዘበን የለውም፡፡ ሴት ጭን መሃል የነበረው ገነት ምን እንደሆነ ሊያስታውሰው'ንኳ ይርቅበታል፡፡

እና እሷ ድንገት ከተፍ አለች፡፡ የውብ ኩረዳ ሥጋ ለብሳ የሳቅ ብርቅርቅ ጃንጥላ ዘርግታ ብቅ!

ሰውየው ሳይታወቀው በሷ ስልጣን (እሷስ ስልጣኗን መች አውቃው?) የውጭ ዝገቱን የውስጥ ጥቀርሻውን አራገፈ፡፡ ነብሱን ጠራረገ ወለወለ፡፡ ለገዛ ዓይኑ ቀንጆ ሆኖ ታየ፡፡ በአባ ኩኩሉ ዜማ ንጋቱን ለገዛ ራሱ አበሰረ "ሻህራድ ፀሐይ ከነጋችልኝ እኔ ውብ ምድር ብሆን ነው" ብሎ አሰበ፡፡ አለ ሙሉ ስሙን ጠርቶ ስብሐት ለአብ ዝንኛ ፊርማውንም አስፈረ፡፡

24፡7፡80

ሻህራዛድ ነብሴ መርከቤ ክንፌ፡ ዛሬ ደሞ ሌላ ተዓምር ደረሰ፡፡ ትከሻ፤ አንገትሽና ጉንጭሽ መሀል ቁጭ ብሎ ነበር የኔ እጅ (ታድሎ!) ከካዛንችስ ወደፒያሳ በሊዎንቺኖ ስንሄድ ሦስቱም እጄን መሀላቸው አደረጉት፡፡ እና ድንቅ ሰው ሆንኩ! ገነትን አቅፌ ሄድኩ፡፡

ሲመስለኝ ሻ ፀሐይ ለምለም፣ ሺ ዓመት ቆይቼ ሳይሆን አይቀርም፡፡ እኔንጃ! ከደቤ ቤት ወደ ጊዮርጊስ ስንሄድ ግን አይ አንቺ ከቃላት ውጪ እና እልቤ ውስጥ ወይ እንቺ!!

ሻህራዛድ ነብሴ፣ ዛሬ ማታ ከሺናሺ ዓመት ናፍቆት (በኋላ በአንቺና በአላህ ቤት አንድ ቀን ይበላል) ልፅፍልሽ ልሞክር፡፡

ሺናሺ ዓመትን ለመድኩት፡፡ በየቀኑ አንቺን ማግኘት በስልክ ድምፅም ለኔ አንቺን ማግኘት ያህል ነው፡፡ ዛሬ ግን ከሩቅ ሳይሽ ልዩ የራስሽ አረማመድም የለ በስልክ ስሰማው ከሌላው ውበትሽ ተለይቶ ብቻውን ስሰማው ከውበቱ ብዛት ሌሎቹ ውበቶችሽ ሳያስፈልጉት ብቻውን በስልክ ድምፅሽ ብቻውንኮ አንቺን ያቀብለኛል!

ያም ሁሉ የለ፡፡ እብደትሽን ፈገግታሽን አልመሰልነትሽን፣ ያን ሁሉ አጥቼዋልኩ፣ አመሸሁ፣ አድር ይሆናል!!

ማነሽ አንቺ፣ ሴት የለችም ካልኩ በኋላ ሴት ሆነሽ የመጣሽ?

ከዚያም ሌላ፣ ማነሽ አንቺ እዝጌር የለም እያልኩ በባዶ ሰላም መኖር ስጀምር ስጋ ለባሽ እንደኔው ለሁሉ የኑሮ አደጋ የተጋለጥሽ ሆነሽ የመጣሽ ማነሽ?

ሻ ነብሴ፣ ዛሬ አብሬሽ ግማሽ ዋልኩ፡፡ ሽግሽግ ግሮሰሪ ሆኜ ሳነብ ማን ከተፍ ይላል? የነብሴ ወንድም፡፡ ምን ዓይነቱ ሰውዬ!

ለነብሴዋ፣

ወይ አንቺ ልጅ! እየናፈቅሽኝ አስቸገርሽኝኮ፡፡ ናፍቆትሽ ግን ካንቺ ጋር ከማስታውስሽ ጋር ስለሆነ፣ አቤት ደስ ሲል አንቺን መናፈቁ!!

ፀኝ እንግዲህ ያየሁት ሀገር ሲናፍቀኝ ነው፡፡ ከከብ ዓይኖችሽ፣ ብርሃን ፈገግታሽ (Vino) የቁጠማ ለምለም ጠይምነትሽ፣ "ተንከባለኛ ልጅና ጤነኛ አዋቂ" መሆንሽ፣ እና ውሎታ የማይቆጥር ደግነትሽ...

ሻህራዛድ ኮከቤ መርከቤ፣ ያላየሁት አገር ሲናፍቀኝ ብታይ ደሞ የሚያንገበግብ ናፍቆት ነው፣ ስዩም ተፈራ ሦስት ቀን ርቦት ደምበኛ ቁርጥ ቢያይ... የማይከፋው ናፍቆት ነው፣ መከፋትን አልፈዋለሁ መሰለኝ(?)

ናፍቆት ከመልክሽ ከድምፅሽ ከውቃ ሆኜ ከማይሽ ሻ አልፌ አንቺን ሻህራዛድ አንዴ ባየሁሽ! አንዴ ብቻ! አንዳንዴ ብቻ!... እንደማይቻል የታወቀ ነው፡፡ እየታወቀም ናፍቆቴ ነው፡፡

ኮከቤ መርከቤ (የነገ ናፍቆቴ)

አብደላ (ትላንት አሱና ባሴ ጋር "ቢያድግልኝ ሆቴል") ለወር እዚያ ሄጄ እንድፅፍ ሲጋብዙኝ ቀድሞ የታየኝ በዚያ ተፈላጊ ሁኔታ ስፅፍ አልነበረም፡፡

@Amharicbookstore



ድንገት ሆድ አንጀቴን የሸመቀቀኝ እዚያ ብሔድ አንቺን ማጣቴ እፊቴ ድቅን ሲልብኝ ጊዜ ነበር፡፡ ይኸ ነሽ እንግዲህ አንቺ ለኔ፡፡ ተገድጄ ካልሆነ በገዛ ራሴ ፈቃድ ከሆነ፣ አንቺ ርቀሽኝ ከሚሆን እንኳን ፈፅሞ ኢየሱስን ማግኘት ይቅርብኝ፡፡ ግና ዞሮ ዞሮ መቅረትሽ ላይቀር ሻህራዛድ ነብሴ ሻ የውስጤ...

----------//---------

ይህን ስፅፍልሽ ከሰለሞን ቆንጆ ጋር ስላንቺ ብዙ ዓመት ተወያየን (ከነሩይ ቤት እስከ እኔ ሰፈር) እና አሁን ይኸውልሽ (እርግጠኛ አይደለሁም) አንቺ ከሸምሽኝ በሁዋላ ሳይሆን አይቀርም እንጃልሽ! በሄድኩበት ሰዎች እጄን ይስሙኛል፡፡ እና ድሮ አልፎ አልፎ ሲደርስብኝ ይቀፈኝ ነበር፡፡ አሁን ግን ካንቺ ጋር መዋሉ ካንቺ ስልጣን መቀበሉ ይሁን እንጃ አይከብደኝም፡፡

ይህንንም የጣፍኩልሽ አንዱ (አፈርድሚ ስገባ) እጄን ወስዶ ሳመ እጄን መሳሙን ተቀበልኩ፡፡

ይኸኔ ሦስተኛ ሚዜ ሆነሽ የት ነሽ? እኔ አሁን (አፈርድሜ) ናፍቆትሽ መጣብኝ፡፡ ሳቂታ እንባም ዓይንሽን እያበራ የመብረቅ ያህል ድንገት ነው ሁሌ ፈገግታሽ ብልጭ! የሚለው ከጠይሙ ሰማይ ፊትሽ

ኤድያ! ተይው ሻ ነብሴ፣ ሁሉንም ለምን አልተውውም? ቃላት መተርተርና ማሰለፍ ነው እንጂ እውነቱ ቃል በሌለሽበት አልሽኝ ውስጤ፡፡

ወየው! ምን ይሻለኛል?

------------//---------

ኮከቤ ነብሴ፣ ኑሮ ገቢያ ቢሆን ካንቺ ጋር ስለሰነበትኩ አሁን ዜን የምታረገው ነገር ይታየኝ ጀመር፡፡ በተለይ ድንገት ብድግ ብላችሁ ስ ወስኑ እና "ቢቀርስ!?!" የሚል አይነት ጉልበት አላችሁ፣ እና የምወዳቸው (እና የሚያውቋችሁ) ጓደኞቼ ደሞ እኔ ምወዳችሁን ዓይነት ይወዷችሁዋል ሁለታችሁንም!!

አንቺን ይመስል ቴምር እየኝኩች "ይጣፍጣል- ይመራል"... ማንስ መጣ ማንስ ሄደ ምንስ ተገኘ ምንስ ቀረ ምንስ ምን ሆነ ማንስ ምን አደረገ ምንም ልዩነት ላያመጣ፡፡ ከሻ ነጻ ፈገግታና እሷነቷ በስተቀር!

ይህ እንግዲህ የኔ ወንጌል ነው፡፡ ሲቀጥል፣ በግድ ለኔና ለልጆቼ መሥራት ከሚኖርብኝ ሰዓት ውጪ አንቺ!

አብረሽኝ ስትሆኚ ኑሮ ድንቁ፡፡ ኑሮ በምንም በማንም የማይለወጥ የማትለወጪ

ስትለይኝ ትዝታሽ ድንቅዬ ትውስታሽ በምንም የማልለውጣት

ኑሮ ገቢያ ቢሆን

ደግነቱ አንድ ገቢያ የለም! ያገኘሁሽ ሁሉ ለሁሌ ልቤ ውስጥ ነው፡፡ የሰጠሽኝም ሁሌ ልቤ ውስጥ!

ነብሴ መልኬ ውዴ መውደድ እብደቴ ናፍቆቴ ነሽ፡፡ አቤት! ዛሬ አላገኘሽ መስሎኝ ናፍቆቴ እየባሰብኝ ... ከተፍ አልሽ በዕብደት ላይ ዕብደት ጭነሽ፡፡ አቤት ያኔ ማማርሽ!!

ማመንታቴም ነሽ

1. ላንቺ ስል
2. ለኔ ስል

I disturb the universe to try to reach you. Let me now retire from my body

ተደበላለቁ ቀንና ሌሊቱ እጅና እጅ ተጠፋፋ፡፡

These days my life is running as if I was the teacher in the Alexandria DARCY (By) Quartet

ሻ ነብሴ፣ ይኸውልሽ ባሴ የሚሉት ጓደኛችን ነበረ ሁላችንን ያያል በየጠባያችን የሁላችን ይሆናል፡፡ እሱ ያያል እሱ አይታይም ሁሌ ባ ንል እሱ ፊት እኛን መሆን ደስ ይለናል ባንቺ በኩል እንኳ በኛ ግን The Invisible Man

------------------ // ------------------

1983ዓ.ም

ዛሬ ደሞ ሌላ ዛሬ! እቴዋ ዓይኔ ነሽ አቤት ዓይንሽ! አቤት ደስ ሲል! ባንቺ ዓይን መታየት ፀሐይ እንደ መሞቅ! ስታይኝ ስትሞቂኝ!

ማነሽ ከነወይን ፍሬ መልክሽ ማነሽ አብሬሽ ስሆን ፀሐይ ውስጥ ደስታ ውስጥ ፍቅር ውስጥ የምታስገቢኝ ማነሽ?

ነብሴ ነሽ፣ ፍቅሬ ነሽ:: እኔ ግን አውቀዋለሁ እቴዋዬ አንቺም ከ ታውቂያለሽ የኔ ወይን ፍሬ መሳይ ጠይም ብርሃን ነሽ፡፡ ውስጥሽንማ ስታውቂው አንቺ ላንቺ አንቺ ነሽ፡፡ ውጭሽን አታውቂውማ!

አቤት ውጭሽ ከውጭ ሆኜ ሳየው ማማሩ! ካንቺ እኩል የሚያምር ተፈጥሮ አያውቅም ለኔ ለስብሐት ለአብ፡፡

ካንቺ እኩል ቆንጆ ነገር አለንዴ? ለኔ የለም፡፡ እየበዛሽ እየሰፋሽ ትሄጂልኛለሽ፡፡ ወይ አንቺ!!!

ዛሬ እሁድ

እቴዋ ሻህራዛድ (ድሮ ቀረች ሻ ነብሴ ልጅ ነበረች ለኔ አሁን ሴት ሆነች) ስለዚህ ዜናን ባንድ በኩልዋ ልሰጥሽ ጠብቂልኝ፡፡ ይህን ልፃፍና እንብበውና የመሰለስሽን አንብቢላት (ንገሪያት) በተለይ



እሱን መጠበቅ ወዘተ እርሺው፡፡ ሻ ሆነሽ ከዜና ጋር ሁኚልኝ፡፡ እርግጠኛ ነኝ እኔ ካንቺ ያገኘሁትን እኩል ታገኛለች ካንቺ፡፡ እንደሰዎች ስንሆን እንደሴቶች ስትሆኑማ! አባት አይምረጥ እንጂ ለልጁ መመኘት ይችላል፡፡ እኔ እሷ ካንቺ ብዙ ብዙ እንደምታገኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡

ሻህራዛድ ግን ይህን ያነበብሽውን ዘወር አርገሽ እንደ መጋረጃ ሻህራዛድ ሁኝላት ያኔ ስንቅ ሆንሻት፡፡ "ያኔ ስንቅ ሆንሻት" "ያኔ ስንቅ ሆንሻት" "አጋፋሪ እንደሻው ስንቄ የሚሉት የዕድሜ ሙሉ ስንቅ ይዞ የሚመራቸው፡፡

አደራዬን ከጫንኩብሽ በኋላ ወይን ውበቱ የፊትሽ ከአበደ ተስፋዬ ጋር "ወይኒቱ" የምልሽ (አንዷ ነብሴ ከብዙዎቹ አማር ተስፋዬ "ወይኒቱ" ባለ ቁጥር መልክሽ ወይን ለነብሴ ደሞ የመሳቅና ሰው የመሆን ወይን የምታጠጪኝ፡፡ ያውም ሆን ብለሽ አይደለም፡፡ ካደረግሽው በሁዋላ ግን ይታይሻል፡፡

ዛሬውኑ

ዛሬውኑ Chap II

ያው እየሆንም እየተለወጥንም ነው ምንሄደው ጉዞውን:: ያው ያቺ ልጅ ጓደኛዬ እየሆንሽ እያለሽ ደሞ አንዷት ሴትዮ ሆነሻል:: ነሽ፡፡ ደሞ ቂጥ አላቸው ሴትዮዋ! አንቺ ግን ያኔ ቂጥ አልነበረሽም እኔ ሳይሽ ወይኒቱ ነብሴ፡፡

ዛሬውኑ Chap III

ታምቆ ቆየ መሰለኝ፡፡ አባት ነኝና ልጄን አስቀደምኩ እንጂ ከተረፈሽ እኔ ደሞ ማወቅ እምፈልግ ለማወቅ መጠየቅ አንቺን መጠየቅ እፈራለሁ:: አሁን ስትበቅል ስታብብ የማያትን ሴትዮ ራሷንኳ ራሷን ልታውቀው ትችላለች... ግን አንቺ ነች፡፡ ታድ ለሽ! ታድዬ!

ዛሬውኑ Chap IV

ሳስብበት ጊዜ፦ እኔን ላንቺ እንደ መጽሐፍ ቁጠሪኝ፡፡ በፈለ ግሽበት ሰዓት የፈለግሺውን ገጽ ማንበብ ሙሉ መብት የሰጠሁሽ፡፡ በጊዜ ጎዳና ስንጓዝ እንኳን መንገዳችን ተገናኘ ሲለያይም አይከፋንም መንገደኞች ነና! ፈገግታሽ ዓይንሽ ሁለመናሽ አንቺ እኔ ውስጥ ያለሽው፡፡

እቴዋ ፍቅሬዋ በኑሮ ጉዳና ስንጓዝ ሁሌ ፍቅር እንደያዘኝ መውደድ ባሁኑ ቦታና ሰዓት አንቺ ነሽ ፍቅሬ፡፡ ደሞ ትናንት ልብሶችሽ፣ ቦርሳዎችሽ፣ ጫማዎችሽ፣ በሰልሽብኝና ይህን ይህን ማየት ጀመርኩ፡፡ አንቺ ላይ፡፡

@Amharicbookstore

ወይኒቱ! ስላንቺ ምን ይባላል? እንኳን አየሁሽ እንኳን ሰማሁሽ እንኳን አብሬሽ ሆንኩ፡፡ ካንቺ ጋር መሆን መባረክ!! ወላሂ! በፈገግታሽ እሞላለሁ በብልጭታው ትርክክ ያደርገዋል ውስጤን፡፡ ፈገግታሽ ብልጭ ሲል ብልጭ ሲልልኝ ፈገግታሽ ከጠይም ጧት የሚበለጭ ፀሐይ ያንቺ ፈገግታ ዓይኔ ላይ ሲነጋ ፈገግታሽ አንቺን ቀድሞ እንደ ቃፊር ሲበራልኝ

ወየው! እኔ የለሁበትም! ከፈገግታው በስተኋላ ሻ ራሷ ትሆንና!

"ወየው አባዬ በጺሙ ይጠጣል" ኩኩዬ ያለችው። አንቺ ወይን እሷ እንኮይ! ስወድሽ!!!

እቴ ወይኔ ልዋል
በፈገግታሽ ብርሃን
በፈገግታሽ ብርሃን
ላስብሽ ተስፋ ነሽ
ላገኘሽ ስጦታ
ዓይኖችሽ ዓይኖችሽ
ሲቀባበሉ ብርሃኑን ከጥርሶችሽ ይነጋል
ልቤ ውስጥ ውበትሽ

አንችኮ ትታያለሽንጂ አትነገሪም፡፡ ልቤን ውስጤን ታሚኛለሽ ከዚያ ጋሯ ደሞ እንዲህ እያመምሽኝ ሁሌ ብኖር ደስታዬ

አቤት ደስ ሲል አንቺን መጉምገት!!

ያምስገን፤ አንቺ እንኳን ያልቀረሽብኝ! አቤት እንዴት ይጨልም ብኝ ነበር! የኔ ጠይም ብርሃን! የኔ እብደት የኔ ደስታ

Mood ይለዋወጥ እንጂ፤ ጠግቤሽ አላውቅም ሰልችተሽኝ አታውቂም፡፡ አትጠገብ አትሰለች ነሽ ለኔ፡፡ ታድዬ!

እና የሚመላለስብኝ ሃሳብ፤ እትያልታየና ብርሃኑ እኔና አንቺ "ብፁአን ናቸው የኑሮአቸውን ትንቢት ሳያውቁት የሚጥፉ!" ወላሂ!

ከተራ (ደመራ) ነገ ጥምቀት፡፡ ልቤ ውስጥ አንቺ፡፡ አንጀቴ ውስጥ አንቺ፡፡ ዝቅ ብሎ አንቺ ወላሂ አልሞተም፡፡ ሌላ ቀን ማታ ስጥፍልሽ፦ ብቻዬን ነኝ፡፡ መቶ በመቶ፡፡ እጠራሻለሁ ትመጫለሽ እወድሻለሁ ትፈቅጂያለሽ፡፡ ትታቀፈልኛለሽ! የምኞቴ ነሽ፡፡ የልቤ ነሽ፡፡ እቴዋ ፍቅሬዋ እኔ ለኔ ለራሴ ነፃነት አወጀኩና በውስጤ ውስጥሽን አገኘኋት- በምኞት፡፡ ያዝኳት- በምኞት አቀፍኳት- በምኞት... በምኞት ከዚያማ አቶ ሼክን ቢሆን አልፈራትም እንትንሽን፡፡

በሚቀጥለው ኑሮማ እንገናኝ Who Cares? I love you! For me the unreachable እወድሽ! እንኳን መገናኘት መንጠራራት እማክ ላከሉበት አገር ተፈጥረን፤ እኔናንቺ ግን ልብ ለልብ አንድ ነን፡፡ እኔ

@Amharicbookstore



ልሙትልሽ! (እብደቴ ነብሴ ገና ዛሬ ለሰው ሞትኩ ላንቺ ሞትኩ (???) አቤት ስታምሪኝ! አቤት ስጎመዥስ! "

አሁን ለኔ ከመጉምገት እኩል የለም፡፡ ልጎምዥሽ ብቻ!!! እባክሽን ልጉምጅሽ፡፡ ይፈቀድልኝ፡፡

እቴዋ ወይኔዋ ፍቅሬዋ የመጨረሻዬዋ እናም ደስታ ፍስሐዬዋ ባንቺ የሰከረች ነብሴን ላንቺ በዚች ደብተርሽ እጥፍልሽ፡፡

ወይኔዋ ለፈለግሽው ሰው ገልጠሽ ማሳየት የጣፍኩልሽን ሁሉ ማስነበብ ሙሉ መብትሽ፡፡ ለዚሁም

ፊርማችን ባለዝነኛው፡፡

ዛሬ

እቴዋ፦ ሳናስበው ይህ ክቡር ብራና የኔ Diary እየሆነ ነው፡፡ የምጥፈው ለኔም ላንቺም ይኸውልሽ(ኝ)

ኢዩ ሽክን በዚያች ቀውጢ ሰዓት እኔን ቢያገኝ ኖሮ (ሃያ ዓመት የምበልጠው) አይሰቀላትም ነበር፡፡ ለየትኛው? ለየትኛው መንግስተ ሰማያት ይልቅ ሂድ ከመግደላይቱ የናትህ ሞክሼ ጋር!!

አሁን ሳውቅ ጠይቂኝ ቢያሰኝሽ እንጂ አልፃፍ ፍቀጂልኝ ይላል ወንድምሽ አፍቃሪሽ፡፡ ምናልባት ፈገግታሽን ፍለጋ!

ዛሬም ዛሬ

የልቤ ወይኒቱ የምኞቴ ወይኒቱ የተስፋዬ ወይኒቱ ከንግዲህ እንደበፊቱ ልጥፍልሽ አፈልጋለሁ፡፡ ግና በፊደል በወረቀት ሳይሆን በድምጼ በጆሮሽ ይሁንልኝ፡፡ ፍቀጅልኝ፡፡ ምክንያቱም ከንግዲህ ዓይኔን የሚያጠምደው ልቤን የሚያጠፋው ፈገግታሽ ነው፡፡ ብልጭ ሲል፡፡ ከንፈርሽ ነው፡፡ ክፍት ሲል፡፡ ዳሌሽ ነው ወዝወዝ ሲል፡፡ ነብስሽ ነው ያን ሁሉ ዘልቆ ብልጭታው የሚደርሰኝ፡፡

ትንሽ ትሁን ትልቅ አላውቃትም አንቺዋ እኔን እንደምትሞላኝ ግን አሳምሬ አውቃለሁ፡፡ ወላሂ! የትላንት የነገ ሌላ ነው፡፡ የዛሬ ግን ልቤ ውስጥ አንጀቴ ውስጥ ሐሳቤ ውስጥ እኔ ውስጥ ያለሽው አንቺ ነሽ፡፡ ወላሂ!!

የካቲት ፱(?)

አንቺ በኔ ዓይን አንቺ ነሽ፡፡ ምን ትመስያለሽ? (ምንድነሽማ አይነገርም ቃላት የሉትም)፡፡ ቁጤማ ትመስያለሽ ወይን(ም) አበባ ትመስያለሽ፡፡ ድምፅሽና ፈገግታሽ አብረው እልቤ ውስጥ ጥልቅ ሲሉ ደሞ ቀስተ ደመና ትመስያለሽ፡፡ ነብሴ ውስጥ ሆነን ስናይሽ፡፡

Dr Faust ሆኜ Mephistopheles መጥቶ ቢፈታተነኝ ነብሴን እሸጥለት፡፡ ወላሂ!

ሌላ ተከታይ ቀን ካንቺ እኩል ቆንጆ ሰው አበባ ከተማ ጤዛ የለም ለኔ ዓይን፡፡ ደሞ ሥጋ እየሆንሽ ነው፡፡ ጡትና ወገብ ቂጥ

እየሆንሽ ነው፡፡ የለንም እኔም የለሁ አንቺም የለሽ አንቺ ግን አለሽልኝ ከነእንትንሽ፡፡ ከዓይንሽ ተነስቶ ከንፈርሽን ፈልቅቆ ሳቅሽን የሰማ ይሰማ፡፡ ሳቅሽ ጆሮዬ ውስጥ የገነት ድምፅ፡፡ ስወድሽ! አሁንማ ሥጋ እያለበሰኩሽ ነው፡፡ ወየውልሽ! በምኞቴ ሳቅፍሽ! ፍቅሬዋ
ፍቅሬዋ፡-

------------//----------

ይድረስ ለእቴዋ ነፍሴ
የተላከ ከኔ ከራሴ
ዛሬ ከሰዓት ለኔ ከገነት ተስፈንጥራ የመጣች ናት፡፡ አንቺ ገነት ስንገባ የሚጆነለግሉን፣ ውብ ውቢቶች ተጠቅልለው ነሽ)
ግማሽ ቀን ሙሉ
ስቃይ ሰዓትን እንደሚያስረዝም
ደስታ ሰዓትን ዛሬ አረዘመልኝ፡፡
ድንቅ ውሎ
ይላል ትንሽ ትሁት አገልጋይሽ ስብሐት
P.S ማማርሽ ከነሰውዬሽ (በነገራችን ላይ አሪፍ ሰውዬ ነው)
በዚች ደቂቃ ብቻዬን እነ አሌክስ ቤት ሊመሻሽ ሲል)
እንግዲህ መጣሽ፣ ልቤ ውስጥ ገባሽ፣ ዓይኔ ውጭውን ሲያይ፣ ፍጥረት ሁሉ ውበት ካንቺ ተውሶ ለብሷል፣ ብቸኛ ሰማይና ባሕር ዛፍ፥ እዚያ ነፋስ፥ ሰማይና መሬት መሀል በረኸሙ በቀስታ ያወዛውዛል፥ ጠላቂ ፀሐይና ረኸሩም ጥላ መሀል ይጫወታል፡፡
እሱ አንቺን ይመስላል ውበቱን ካንቺ ተውሷል አለዚያ አይታ የኝም ነበር፡፡ (አንቺማ ምን ትመስያለሽ!! አንቺን፡፡ ከዚያ ውጭ ውበት የለም ለኔ በንዲህ ዓይነት ሰዓት፡፡ ያንቺ ሰዓት፡፡ እውስጧ ብዙ ብዙ ብዙ ሰዓት፡፡ ከቁጥር ውጭ!
ነብስሽ ነብሴ ላይ ጥላዋን ትጥልብኛለች
የዓይንሽ የኮከብ ብርሃን ጥላዋን
የፈገግታሽ የጨረቃ ብርሃን ጥላዋን
የትንፋሾችሽ የለምለም ቄጤማ ጥላዋን
የድምፅሽ የገደል ማሚት ናፍቆት ትውስታዋን
የዕብደትሽ ዝላይ ዘላይ ጥላዋ ሥር
ማረፍ ለኔ ሲኦል ውስጥ ድንገት ያጋጠመችኝ ገነት ዛፍ ሥር ማረፍ፡፡
ደሞኮ እነ አቶአን ትቀሰቅሺብኛለሽ፣ ብዙ ጊዜ! ለምሳሌ አሁን አሁን መሽቶ አብዛኛው ሰው ቤቱ ገብቶ እኔም ልተኛ ልዘጋጅ ሲጋደም ከተፍ ትይልኛለሽ ፈገግታሽን ለብሰሽ ለብሼሽ እጋደማ



ለሁ፡፡ ሲጋዬን ለእንቅልፍ አስረክባለሁ፡፡ ስተኛ ለብሼሻለሁ፡፡ ልብ ሱና እንቅልፉ አንድ ይሆኑና በህልሜ አየሁሽ (ሁለቴ ብቻ!!)
ህልምና ሎተሪ እፈለጉበት ይወድቃሉንጂ ሲጠሩን እንሰማ ስንጠራቸው አይሰሙን፡፡
የኔን ህልም አባርሬ ታዛዥ ህልም በገዛሁ! ሁሌ በህልም ሰዓት አንቺን ብቻ አይሽ ነበር፡፡ ያኔ፣ እኔ እያወቅኩ ሳይሆን ሳላውቅ አለሙ ሁሉ አንቺን ይለብስልኝ ነበር!!
ሻ ፀሐይ ሻ ነብሴ ሻ ውዴ መውደዴ ጠይም ቄጤማ እየውልሽ፣ ስለማንበብ ይሁን ስለመጻፍ ግድ ስለሌለሽ በየት አቋራጭ ቀደምሽኝ?
እብደት የኖህ መርከብ፡፡ ዕብደት የኮሎምበስ መርከብ፡፡ ዕብደት ሻህራዛድ ፀሐይ ነብሴ ያንቺ ፈገግታ ከዓይን ይሁን ከከንፈር ከየት ይጀምር እንጃ የዓይንም የከንፈርም ፈገግታ እኩል ብልጭ ሲልብን ያኔ ነብሳችንን
ሻ. ነፃ እብደቴ እብደትና ሳቅ ስፅፍ ስፅፍ ስፅፍ ኖሬ አንድ ቀን አንቺ መጣሽ እንደ አራዊት አለመድሽኝ እብደትና ሳቅን ኖርኩት!! አሁን ላንቺ ምን ይዋልልኛል? እንዲህ ስልሽ ስትስቂ ይታየኛል ግን እውነቴን ነውኮ!
"እስቲ የሳቅ ዳውላዬን አስቀድሙልኝ ጭንቱ እንደሁ አይቀር ልኝ፡፡ ገጣባ አህያ በወፈፌው ጠበቃ አፈቀላጤነት(T!) "ተአምረ አቶ አ" (TT!!)
ዛሬ ሥላሴ
ሻህራዛድ ነብሴ
ለካ እውነትም ነብሴ ነሽ፡፡ ለራሴ ልነግረው የምፈልገውን ላንቺ ባልነግረው ያመልጠኛል፡፡ ለዚህ ነው ለካ ምጥፍልሽ (አንዳንዴ) (ይህን የምጥፍልሽ ባህሩንና መሰንቆውን እየሰማሁ ነው አፈርድሜ ሆኜ!!) እና ስለ ወሎ ማውቀውን እነግርሽ ያልኩት ብዙ ነበር ግን ጭራሽ አያስፈልግሽ! አንቺ ለራስሽ ባቋራጭ ደርሰሽበታል፡፡ ወይ አንቺ ራስሽ ነሽ!
ኤድያ! ላንቺ ምን ይነገራል!? ተጠግቼሽ እንደማታ እሳት ነብሴን ማሞቅ እንጂ!! እቤት ስታሞቂኝ ስታበሪኝ! ይህን ስንቴ ደጋግሜ ጥፌልሽ ይሆን? ግን ከዚያ የባሰ ስንትና ስንቴ አንቺ ዘንድ ያንኑ መልኬን ለብሼ እቀርብ ይሆን?
አንቺ ግን ባገኘሁሽ ቁጥር ሌላ ነሽ የዝጌር ቀኖች የሚመሳሰሉትን ያህል (ፀሐይ በመውጣቷ በመግባቷ) እና የሚለያዩትን ያህል እና ምን ያህል ይለያያሉ፣ ሻ ነብሴ! እንደዚያ ነሽ

@Amharicbookstore

ሃሳብ ቢራቢሮ እና ዶክተር ኤሊ ድንጋይ ልብሱ "ትዕግስት ትዕግስት ናት" አሉ ዶክተር ኤሊ። "እንደኛ ናት ቀስታ ናት ጥታ ናት"

ሸካራ እንገታቸውን ጠምዘዝ፣ ስዕል መሳይ አይናቸውን ከብለል እና ከንፈ ዓይናቸውን ሸውረር!

"እና ከተቃራኒያችን ጋር ካልሆነ መኖር ያለ አልመሰለም እስካሁን" ዘወር ሸውረር ብለው ደራሲውን መልከት "በራስህ ልታየው ትችላለህ።

"ነብሴ ሰማይ ነብሴ የንጋት ኮከብ" ብለህ በሌለችበት ምታስባት ማናት? ልትደርስባት የማትችል ሃምሳ ወደ ሃያ ርቀቱ አይደረሴ ናት። ፀሐይ ነብሴ ዘንድ ከነሲጋህ መድረስ የለም። ቢኖርማ ኖሮ ተራ ኮድ ብዮኖ ባለፈ።

ሌላው ነብሴ ደሞ ምን ይላል መሰለሽ አንቺ የኔ የንጋት ኮከብ፣ የኔ ፀሐይ የኔ ሰማይ "ሁሌም ተዓምር አለ። ተዓምረ ሻህራዛድ ሊኖር ይችላል። ማን ያውቃል እስካሁን አደሰችኝ። እደሳው በቃ ያለ ማነው?

ጥር3፥1987

ሻህራዛድ ነብሴ፦

እንዲያው አልፎ አልፎ እንደዛር እየተነሳብኝ እንደሚያደርገኝ፣ ዛሬም ናፍቆትሽ ብልጭ አለብኝና(ፈገግታሽን ለብሷል የታወቀ ነው) እያነካከስኩ ተንደርድሬ ቸርቺል ቁልቁለቱን ከወያላ ጋር ተንከባልዬ ጥቁር አንበሳን ዳኀቱን ካንቺ ጋር ሽቀብ ወጥቼ ይህን ዉሉ ጀብዱ ሰርቼ ብመጣ አይሻለሁ ብዬ እንደአክሱም ጽዮን አስለምሽ ብዬ የለሽም አንቺ ሆዬ!

በሚቀጥለው ትክሽኛለሽ

ያንቺ ስብሐት ለአብ ከነፈርማው

መጋቢት 22/80 ጧት

ለሻህ ነብሴ፡-

ከትንናት ማታ ጀምሮ-ሌሊት ጭምር- ይኸው እስከ አሁን፣ ያንቺ ነገር ቅር ቅር እያለኝ እያባባኝ ከረመ!

ደስ ያላለኝ፣ ቅር ያለሽ፣ የከፋሽ እየመሰለኝ እያስቸገረኝ

እኔን ይክፋኝ! (ሻህራዛድ ነብሴን!!)

ትንሹ ነገር የሚጉዳሽ እየመሰለኝ- እንደ ቢራቢሮ ክንፍ።

ባንቺ የመጣ እውር የሆንኩ እየመሰለኝ - ሳላውቅ የማስከፋሽ።

አሁን ጧት ልደውልልሽ በጣም ፈለግኩ - ድምፅሽን ልሰማ።

ኢቃተኝ- ፈራሁ። እንዲህ ሆኘም አላውቅ።

@Amharicbookstore



ይህን የምጥፍልሽን እሰጥሽ ይሆን?

ፈርቼ ሳላስቀረው አልቀርም።

ደህና ነሽ ወይ?

ሳቅሽ ነሽ ወይ?

ሻህራዛድ-ሻህራዛድ-ሻህራዛድ-ሻህራዛድ አትጠገብ።

ሻህራዛድ- ሻህራዛድ- ሻህራዛድ አትሰለች።

ሻህራዛድ -ሻህራዛድ -ሻህራዛድ አንቺን የሚመስል ሰው አለ?

ሻህራዛድ -ሻህራዛድ-ሻህራዛድ ሙሉ ዓለም ከነፀሐይዋ።

እንጃልሽ በቃ! የራስሽ ጉዳይ!!!

የምወድሽ ወንድምሽ

ስብሐት ለአብ

ለእመቤት ሻህራዛድ
አዲስ ገበያ፣
ኢትዮጵያ፣
አፍሪካ፣
ዓለም፣
እንጃ!!!

## ፳፯

## አጫጭር መልዕክቶቹ

ጋሼ ስብሐት ለአብ አጫጭር ደብዳቤዎችን ለበርካታ ጊዜያት ከወዳጆቹ ጋር መለዋወጥን ይወዳል። እነዚያ ወዳጆቹ ርቀው፣ ባህር ተሻግረው፣ አልያም በቅርብ ርቀት ተለይተውት ወይም አጠገቡ ተቀምጠው ይሆናል። በዚህ አጫጭር መልዕክቶቹ ውስጥ ፍቅር፣ አድናቆት፣ ሰላምታ፣ ናፍቆትና የወደፊቱን ትንቢያ ያስተላልፍባቸዋል። በጣም ጥቂቶቹ እኔ እጅ ገብተዋል። ለቅምሻ እንዲህ አሰናድቻቸዋለሁ። በነገራችን ላይ የአማርኛ ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ላይጠቀም ይችላል። እኔም ይህንኑ የእርሱን አጻጻፍ ስልት ንክች ሳላደርግ ነው እንዳለ ያቀረብኩላችሁ።

***

ይድረስ ለመለስ ዜናዊ

የተላክ ከስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

ጉዳዩ፡- የግል ደብዳቤ እየላኩልህ ነው::

አንተጋ ሳይደርስ የሚያነቡት እንደሚኖሩ እገምታለሁ:: ማንም ቢያነበው ደስ ይለኛል:: እንደሚደርስህ እርግጠኛ ነኝ:: እስከ ዛሬ የአገሬን ታሪክ ሳውቅ አንተ ነህ የእኔ መሪ:: ከሁሉ እኔ የምመርጥህ:: ምክንያቱስ እኔ እስከ 10 ዓመቱ ባላገር ተወልጄ ስላደግኩ የገበሬውን ችግርና ሲቀይ አውቀዋለሁ:: አንተ ግን ሆን ብለህ በፖሊሲም በተግባርም ለገበሬው የቆምክ ስለሆንክ የእኔ መሪ አንደኛ አንተ ነህ::

ይቅናህ! ምናምን ሳልል አልቀርም:: እንዲህ ባኖኩለት እልሀለሁ:: ሰዎች እኮ አሉ ሲያገኙት የሚችሉ በእነሱ ነው የሰደድኩለት::

***

ይድረስ ለማህሌ ሥላሴ ብርሃኑ ማርያም

ይድረስ - ለአጋዝ ማህለ ሥላሴ B.M

የተላከ - ከአጋዝ / Honourary/ ስብሐት ቀን - ዛሬ

ከዘነበ ወላ ጋር በሚርቃና ስለ «ፍኖተ ሕይወት»

ጸና ስለተጎነጉ አንተ ስናወራ

መልዕክት - እንኳን አደረሰህ

ተስፋ - ዘነበ አንድ ቀን ይገናኝናል

እስከዚያው -ኢንሻላህ!

ኢጋዝ ሳህሌ እስከ ጉራጌ መሠረቱ

እስከነ Jesuit disciplinኑ

P.S. Immanuel Kant!

Peace & Love



Cheers!

(Confusion to the enemy of the Crown!)

ስብሐት ለአብ

***

**ለቅድስት ክፍለ ዮሐንስ**
**እህዱ**

እኔና ሚጢጢ በቅድመ ልደት የታቀደልንን ሙሉ መገናኘት፣ በቦታ ልክ መታንና

በጊዜ ወይ ሁለታችን ወይ አንዳችን ተሳስተናል

(እኛ'ንኳን ልንሳሳት አንችልም)

ስለዚህ ፍቅርን እንደ ፅጌረዳ ተክሎ ማሳበብ ሳይሆን፣ እንጂ ፒንግ ፖንግ ኳስ መቀባበል በፈገግታ፣ በሰላምታ፣ መሳሳም፣ በመንገድ`ስናቋርጥ እጅ ለእጅ መነካካት፣ መላቀቅ፣ ፒንግ ፖንግ

ፒንግ ፖንግ ያንቺና የኔ ዓይነቶቹ ፈጣኖች የሚጨዋወቱት ኑሮ

(ኑሮኮ ጨዋታም ነው ኪዳዬ)

ፒንግ ፖንግ

ከማታ ወደ ቧት መንጠር

ኢዮ ደግሞ ነጋ

ኢዮ! ፀሐይዋ ያው ፀሐይ ናት::

ታድያ ለምን ተመልሶ ነጋ? ኢዮ!

ብሽቅ ድግግሞሽ አለች ልዕልት ሚጢጢ

ከዚህ ቀጥሎ ልዕልት ሚጢጥ ቡድሃ ራሱ ሸበት ለብሶ የመጨረሻ ልጁ ሆና ተወለደች ፒንግ ፖንግ ኳስ ሆና

እይ ያን ጊዜ YMCA (የወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኀበር) ሄዳችሁ ባያችኋት

ፒንግ ፖንግ ኳስ ሲነጥር ሲነጣጥር ጥር ር

አይተናል የሷ አነጣጠር ግን!!

ብሎ መሰከረ ስለወደዳት

እውነቱን ነው

ለሱ ከሁሉ በላይ ናት ፒንግ ፖንግ ፀሐይን ምሥራቅን ምእራብ ሲጫወቷት

**ማክሰኞ ማታ ተረት ሰፈር**

ማጠቃለያ፣

ዛሬም ስትናፍቂኝ ዋልሽ፡፡

``ማታ እደውልላታለሁ`` እያልኩ ድምፅሽን ለመስማት ስጓጓ ዋልኩ፡፡ ሰዓቱ ሲደርስ መደወሉን ፈራሁት፡፡ ተውኩት፡፡ ፈገግታሽ አይዘህ ካላለኝ እፈራለሁ፡፡

ወደ ውድ ናፍቆትሽ ተመልሼ ብዙ ብዙ ብዙ ውበቶችሽን እያስታወስኩ ማምሸቴ ነው እንግዲህ፡፡ ታድዬ

ደሞ ይኸ አነሰና፣ ነገ በፀሐይ ብርሃን አበባ ውበትሽን ላየው ነው!! እና እኔ አልፎ አልፎ በገነት ሰዓቶች እየኖርኩ ነው እኔና አንቺ መቀራረብ ከጀመርን ወዲህ፡፡ ቅዱስ ሚካኤልን

ያንቺው ስብሐት ለአብ

በዓይኔ ሥጋ ከኔ ጋር በሌለሽበት ሰዓት ልቤ ውስጥ የሚመላለሱት አንቺዎች ቢሮ፡ በሩ በልስልስ ተንኳኩቶ (ባንዳፍታ አውቀዋለሁ)

በቀስታ ተከፍቶ፣ አንቺ ፈገግታሽን አስቀድመሽ

ብቅ ስትይልኝና ልቤ ብዙ ዓይነት ታምቡሮች ሲመታ

ነብሴ የቢራቢሮ ክንፍ ባንዳፍታ ስታበቅል

የኔ ዓለም ምድራዊት ንፀሀት ገነት ስትሆን

ምሳ እየበላን ቀና ብዬ እያየሁሽ እየተደሰትኩብሽ እጣዬን ስባርክ

ሲጃራው ተለኩሶ፣ ጪሱ መልክሽን ሲለውጠው፣ ሌላ ስትሆኚ ሌላ ብዙ፣ ብዙ ሌላ

ደረጃውን ስንወርድ ይሁን ስንወጣ የአረማመድሽ ድምፅ

በሌለ ወንዝ ላይ የተዘረጋው ድልድይ ልሙጥ ድንጋይ ላይ፣ ሚጢ ሚጢጢ ታኮዎችሽ የሲኒማ ድምፅ ኳ! ቋ! ኳ! ቋ! ባቡር መንገድ ስንሻገር፣ መኪና እንዳይደጠኝ እጄን ይዘሽ ስታሻግሪኝ በዚያች ደቂቃ ልቤና ነብሴ መዳፍሽ የጨበጠው መዳፌ ውስጥ ናቸው፡፡

ማክሰኞ ማታ

አንዳንድዬ አንቺን ከመውደዴ የተነሳ፣ ብቻዬን ከሐሳቤ ጋር ልሆን ስችል እኔና ሐሳቤ ስላንቺ እናስባለን ማለት አንቺን ሆነን እናየዋለን ያንቺን የነገ ኑሮ፡፡

ዛሬ እንዲህ አሰብነው፣ አየነው፡፡ ባጭሩ በሚጢጢው አንቺ በዚህ ሀገር በዚህ ጊዜ እህል ጦሃሽ ውጭ ነው ሂጂ ከዚያ የመጣው ይምጣ፡፡ በቂ ጭንቅላት፣ ውበት፣ ጠባይ፣ የሰው መውደድ አለሽ፡፡

የትም ብትሄጂ ቆንጆ ሰዎች ያጋጥሙሻል፡፡

ቆንጆ ሰው ነሻ፡፡

``ቢቃ``! አንቺ እንደምትይው፡፡

***

ለገነት ታደሰ

@Amharicbookstore



ገንዬ የኔ እናት እመቤት

ወደናንተ መምጫዬን ላፋጥን ልወጣ ስል የዜና አብሮ አደግ ሐጂ ኢብራሂም ስልክ ደውሎ «Mayday የሠራተኞች ቀን በዓል ስለሆነ መሥሪያ ቤት ሁሉ ዝግ ነው»

እኔ ምን ገዶኝ? ከገንዬ ትዝታዎችና ትዝታዎች ጋር እውላለሁ ጫቴን እየቃምኩ ትውስታዎቼ፣ ፈጠራዎቼ፣ ወደ ምርቃና ተራራ ስደርስ ካንቺ ጋር የኖርኳቸው የፈገግታሽን ብርሃን ለብሼ የሳቅሽን ሙቀት እየሞቅኩ ቅዕበቶቻችን ተከታትለው እንደ ዶቃ የዘለዓለማት ሀብል ሲሠሩ እቴዊ የኔ የፍቅር ቄጠማ እንዲሁም የዘምባባ ማር እንዲሁም የኔ ገንዬ ጧት በተነሳሁ ቀጥር እንቅልፌም አድሶኛል፡፡ አንቺም በፍቅርሽ ሥልጣን ወጣትነቴን አልብሰሽኛል አቤት ብታይኝ ሲያምርብኝ! የብቻሽ ስብሐት ለአብ

ገንዬ የኔ እናት የኔ ጠባቂ ገንዬ የነብሴ ሌላ ግማሽ የኔ ናፍቆት የኔ ትዝታ በሰላም ብቻዬን ሆኜ አንቺን ማስታወስ አቤት የሚሰጠኝ ደስታ ስምሽን እንደ ውዳሴ ማርያም ለራሴ እደጋግመዋለሁ እደጋግመዋለሁ ይባርከኛል፡፡ እስቲ አሁንም ደስስስስ ይበለኝ በምናብ ወደ ገንዬ ቤት ከተፍ ስል «ታጥቃ ተነስታ» ፈጣሪ አበርክቶ የሰጣትን Energy አጥጋቢ አመርቂ ሥራ ትሠራበታለች፡፡ ይህን ይመስላል የኛ ናፍቆት ወደ እናንተ ሲበር፡፡

***

ማክሰኞ ማታ

ፎቶዎችን መታወቂያዎችን ወዘተዎችን ላፋጥን ላጣድፍ ሄጄ ዋልኩና ስመለስ ደውለሽልኝ አጣሽኝ አሉኝ፡፡

የኔ ፀሎት፣ የኔ እናት፣ የኔ እቴዊ፣ የኔ ገንዬ በዚች ሰዓት ከኔ ጋር ነሽ እንዲሁም በሌሎች ሰዓቶች ገንዬ ገንዬ እያልኩ ተይልኝ ያልኩሽን መስቀል ደረቴ ላይ ተንጠልጥሎ እይዘውና አገኝሻለሁ ያን ያህል ነው ስወድሽ የኔ እናት «...» ስትይኝ እሰማለሁ አሁን «...» ብላኝ ታውቃለች እንዴ? ብዬ ራሴን ስጠይቅ- ያንች ፀሐይ ፈገግታ ጥልቅ ወደ ውስጤ ፈገግታው ይቆይልሽና አንገቢጋቢ ጥያቄ ፈጥነሽ መልሺልኝ እንደ ትዝታ በፖስታ - እውነት «...» ብለሽኝ ታውቂያለሽ ወይ?

ZORBA THE GREEK by Nikol Kazant zakis

የገንዬ ነብስ የወንድ ሥጋ ለበሰ፡፡

***

**ለፀሐይ በላቸው**

Princess ሆይ - ወይ ቤሎሙ

በቂ « የቅርብ ርቀት» በመሃላችን ስላለ

ለኔ ሁሌ አዲስ ነሽ

ለዘነበና ላንቺ ግን -እርስ በርሳችሁ

የልማድ ሕግ ነው እንደ ነብስ ዝገት ዝገት ለዝገት ትጎለታላችሁ

አሁን ከኛ ጋር የዋለው ዘነበ ከሦስት ዓመት ልጅ እስከ Chemistry genius —እስከ የዜና ፍቅረኛ አስፋው አስር ሰዎች መሀል እንታይሽ የዩኒቨርሲቲ Professor

መለኪያ ለሌለው ሰዓት ያንቺ ዘነበ

ሙሉ ትኩረታችንን ስቦ እኛ በፀጥታ...

Princess በልማድ እንዳትዝጊብኝ

እኔን አስታውሺና በወጣትነት ዘመናችሁ የምትወጂውን ያሀል ዛሬም እንደምትወጂው አሳይው - በዓይን በማቀፍ

ስም ዝና ከሥልጣን እኩል (?) ያስከራልና-

በሚንቀባረርበት ሰዓት

«አይደለም ጋሞ

ምርጥ Abyssinian ቅድስት ሀገራውያን ቢሰለፉ በአይን ጥቅሻ ብንበረከክናቸው ያውም መንበርከኪያ ትራስ አስተካክለን -

ዞሮ ዞሮ እምቧ ላንቺ፣ ለቤቲ፣ ለፀጋ፣ እና አራት ኪሎ ለተከሰተችልኝ እቴነሽ

***

ለቤቲ ቆንጆ ቀይ እንኮይ ፀሐይ ትንገርሽ ለፀጋ ጀግና አደገኛ ለPrincess ነብሴ ለሌሎ ትናፍቆኛላችሁ ከዘነበ ጋር መጥቼ እንጫወታለን ይላል አቦይ ራሱ በእጅ ጽሕፈቱ በፊርማው «ከጠላት በፊት አሳዛኝ አስኮናኝ ፊርማ ነበረችኝ:: ዕድሜ ለጠቅል ኃይሌ ወድቃ የተነሳችው ባንዲራ እስካሁን እንድትውለበለብ ለሳልሳዊ ምኒልክ አስረክበናል::

Love to the Princess!

***



**ለአብይ ለገሰ**

አብይ ሆይ

ሁላችን በፈጣሪ እጅ ብንሆንም ለምንወደው ሰው ስንፀልይ ይሰማናል ትዝ ባልከኝ ቁጥር ከልቤ እንደ ፀለይኩልህ ነው::

ከኩኩሻ ጋር መጥተን እስክናጫውትህ ድረስ በጤና ሰዓት ካጫወትከን ብልጭታዎች አንዳንዶቹን እያስታወስኩ፣ አንዳንድ ጊዜ እገረማለሁ፣ አንዳንድ ጊዜ እስቃለሁ:: እስክንመጣ ድረስ «ሰምና ወርቁ ተሰማ እሸቴ» የተባለ የሚጥምህ መጽሐፍ እንልክልሃለን መልዕክተኛ ካልታዘዘልን እኛው ራሳችን የቅኔዎቹን ክብደት ተሸክመንልህ ከተፍ!

ኢንሻ አላህ ኢንሽ አብይ ወንድምህ ስብሐት ለአብ በአረብኛ አብደላ!

***

**ወንድም አብይ ሆይ**

ለትንሽ በማምለጥህ ዳዊት እደግምልሃለሁ በፀሎት ብቻ እንዳይሆን በማሰብ እስኪርበኝ ድረስ እያምልሃለሁ - ወላሂ

See you soon

ወንድም ስብሐት ለአብ

***

**ለተስፋ ልደት ገብረ ሚካኤል**

**እሴት ያለው ሕይወት ኑር**

ተዘጋጀህም አልተዘጋጀህም ጉዳዩ አንድ ቀን ያበቃል:: ከእንግዲህ የምትወጣ ፀሐይ አትኖርም:: ደቂቃዎችም፣ ሰዓቶችም፣ ቀኖችም የሉም::

እነዚያ የሰበሰብካቸው ነገሮች ሁሉ የወደድካቸውም ይሁኑ የረሳሀቸው ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋሉ:: ሀብትህ፣ ዝናህ፣ እና ዓለማዊ ኃያልነትህ መንምኖ እዚህ ግባ የማይባል ይሆናል:: ምን ምን የግልህ እንደነበረ ወይም ምን ምን እዳ ሊከፈልህ ይገባ እንደበረ ልዩነት አያመጣም:: ቂምህ፣ አትንኩኝ ባይነትህ፣ ኩምታዎችህ እና ቅናትህ ጨርሰው ይጠፋሉ:: እንደዚሁም ተስፋዎችህ፣ ዕኑ ፍላጎቶችህ፣ ዕቅዶችህ፣ የሥራ ዝርዝሮችህ ጊዜ ያለፈባቸው ይሆናሉ:: በፊት በጣም አንገብጋቢ ይመስሉህ የነበሩት ድሎችና ሽንፈቶችም በንነው ይጠፋሉ:: ከየት መጣህ?፣ ደስተኛ፣ ወይስ መከረኛ ኑሮ አሳለፍክ፣ በመጨረሻው ልዩነት አይኖረውም:: መልከ ቀና ነበርክ ወይስ ጥበበኛ ልዩነት አያመጣም:: ፆታህና የቆዳህ ቀለም ሳይቀር እዚህ ግባ የማይባል ኢምንት ጉዳይ ሆኖ ይቀራል:: እንግዲያው (ታዲያ)

@Amharicbookstore

ልዩነት የሚያመጣው ምንድን ነው? የኖርካቸው ቀናት፣ የእሴታቸው ልክ እንደምን ሊመዘን ይችላል? ለወደፊት ዋጋ የሚኖረው ስኬታማ ውጤትህ ሳይሆን በሰዎች ልቡና የሚጠራቀምልህ እሴትህ ነው:: ልዩነት የሚያመጣው ምን ምን እንደገዛህ አይደለም ለሰዎች ምን ምን እንዳበረከትክ ነው እንጂ::

በመጨረሻ ልዩነት የሚያመጣው ችሎታህ ሳይሆን ጠባይህ ነው::

ስንቶች መሰናበትህን እንዳወቁ ሳይሆን፣ አንተን ያለማግኘት የሁልጊዜ እጦት እንደሚሆንባቸው

ትውስታዎችህ አይደሉም፣ የሚወዱህ ሰዎች ውስጥ የሚቀረው

ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያስታውሱህ አይደለም፣ እነማንን ለምን እንደምትታወሳቸው እንጂ:

እሴት ያለው ሕይወት መኖር ባጋጣሚ አይመጣም:: ሁኔታዎች የሚወስኑት ጉዳይ ሳይሆን፣ አንተ ራስህ መርጠህ የምትፈጽመው ነው::

ፀሐፊው ስሙን አልጻፈም:: ህሊናችንን ለመሆን እየሞከረ ይመስላል::

***

ለተስፋዬ ገብረአብ

**ወሬ ጦር ይፈታል**

የኢያሱ ጥሩምባም የኢያሪኮን ግምብ አፈረሰው

ተስፋዬ ገብረአብ (የልብ ጓደኛዬ)

እውነትና ውሸት በኬሚስትሪ ቀምሞ ተከሰባችኋል እኛ ሁለታችን ሕዝብ በመሆናችን ለሕዝቡ የተላከውን missile መከላከያ ጋሻ ለናንተ ለመጠቆም የሰላም ምኞትና የአገር ፍቅር ያስገድደናል። በትንሹ የኛ እይታ መዋጮ ይሆናል በሚል ተሰሩ

በውጊያው ገለልተኛ (የተስፋዬ አድናቂ)

ለውጤቱ ግን ተስፋዬን እንቃወማለን

ለሱ ጽፈንለት የምትልኩለት የተሸፈነ ግልጽ ደብዳቤ እነሆ

***


@Amharicbookstore

# ክፍል ሁለት

# "ይናገራል ፎቶ!..."

"በልጅነቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ፎቶ ተነስቼ ሲያሳዩኝ ይህን ነው የምመስለው!..." ብዬ ገረመኝ ፎቶውን ግን አምኜዋለሁ። ሌሎችን አንስቶ አይቼዋለሁዋ! ከዛ ሲያዩኝ ይህን ነው የምመስለው..."

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር











“በሥራው ዓለም ምስለኔ ከሆኑት መታወቂያዎቼ ጥቂቶቹ”


@Amharicbookstore



ወላጆቼ አቶ ገብረእግዚአብሔር ገብረዮሐንስና ወዘሮ መአዛ ተወልደመድህን



ከግራ ወደቀኝ ጋሼ ስብሐትና አብሮ አደጉ ኤፍሬም ሐጐስ



በሕይወቴ ከመጠጥ ጣፍጦኝ የጠጣሁት ሻምፓኝ ብቻ ነው የቀመስኩት ከሃና ጋር
የተጋባንበት ቀን ነበር።" ስብሐት ለአብ




For your Sibi with lots of smiles.
ሐምሌ 1967 ዓ.ም
(ከፎቶው ጀርባ ያገኘሁት መልእክት)





“ልጆቼን እንዳሳደግኋቸው ስላሳደግሽልኝ አመሰግናለሁ!”
ስብሐት ለአብ

@Amharicbookstore






ቃልኪዳን ስብሐት ለአብ



ቅዱስ፡ ስብሐት ለአብ እና ቃልኪዳን
74ተኛ የልደት በዓሉን ሲያከብሩ፤


@Amharicbo re




"ዓይንና ጆሮ መሆን ደስ ይለኛል!"
ስብሐትለአብ




ደረጀ ደሬሳና እናቱ ወይዘሮ የሺእመቤት ደሬሳ




ከግራ ወደቀኝ ሰለሞን ደሬሳ፣ ስብሐት ገብረእግዚአብሔርና ጌታቸው ደባልቄ




"እዚህ ደርሰናል... አልሃምዱሊላሂ"




"... ለእኔ አስፋው ሙሉ ቤተ
መጻሕፍት ማለት ነው" ስብሐትለአብ



[illegible]






"እምዬ ምኒልክ እና ሙሰጥ [illegible] ናቸው!"
ስብሐትለአብ




ከፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ጋር በቼዝ ሲፋለሙ


@Amharicbookstore




ከግራ ወደቀኝ ሰደፌ ሀማ፣ ጋሼ ስብሐት፣ ዘና እና እኔ፡




ከልጆቼ ጋር ዶ/ር ኢያሱና ዜና ስብሐት




ከአዲሱ ትውልድ ጋር ፤




በ1993 ዓ.ም የመጀመሪያ ማስታወሻ ሕትመት
በኢምፔሪያል ሆቴል ሲመረቅ፤



በሩሲያ ባህል ማዕከል ሰባኛ የልደት በአሉ ሲከበር፤




አባትና ልጅ ቴሌቪዥን እያዩ ሲዝናኑ፤


@Amharicbookstore



ዶክተር ተወልደብርሃን፡ ስብሐት ለአብ፤ዮሴፍ ገብረእግዚአብሔሮች፤



ኃይለመለኮት መዋዕልና ጋሼ ስብሐት ለአብ፤



ለቼጉቬራ ያለውን ፍቅር ሲገልጽ፤




ከልጁ ዜና ጋር ሲጨዋወቱ፤

@Amharicbookstore



የመልካም ሥራ የምስክር ወረቀት በአሜሪካን የሕይወት ታሪክ የምርምር ተቋም ተልኮልን ከወዳጃችን አንባሳደር ሙሴ ኃይሉ እጅ በአክብሮት ሰንቀበል:: /ሰኔ 1993 ኢምፔሪያል ሆቴል/




ማስታወሻ ሲመረቅ እኔ፤ጋሼ ስብሐት፤ሰንዱ አበበና ጋሼ መስፍን ሀብተማርያም፤


@Amharicbookstore



ያነጋገረው ፎቶ፤



ግንቦት 1986 ዓ.ም በዛሬዩቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ ቃለ ምልልስ ስናደርግ::
( ፎቶ በእሱባለው ዘገዬ)




አቶ ሥዩም ስብሐት




ብላታ ደሬሳ አመንቴ



እትዬ በሰሙ ኃይሌ



በስዊዝ ዕረፍት ላይ ሆኜ፤



@Amharicbookstore





Mon Capitan

ከአቶ ግኒ ጋር በቋንጣ ጫት ዱሉ  እያረግን ነው ምንጽፍልህ
ለPrincess በናፍቆት በረጉ የሚደርስ ሰላምታችንን አቅርብልን
... ግኒ ግንባርህ ላይ ትስምሃለች
ለቤቲና ለሀጋ ሰላምታ ሳሙልን!

***

ስለላክልኝ ማስታወሻ በጣም አመሰግናለሁ።
እንወድሃለን።
ግኒ
በካርዱ ጀርባ ላይ የተላክልኝ መልዕክ




የቀድሞው ማስታወሻ መጽሐፍ ላይ ከጀርባ የነበረው ምስል ፡

@Amharicbookstore

# ክፍል ሦስት

# ማዕደ ጥበባት

... ሰው እያለ አለገባችን
ቅንነቱን ማየት ሲያመን
ከኛ አብሮ በሕይወት ቆሞ፤ መልካሙን ስሞን
መጥፎት ሲያንቀን
"ሰው ካልሞተ ወይ ካልሄደ አይነሳም" እንላለን
እንዲህ እያልን፤
ስንቱን ጠቢብ እየሸኘን፤
አበባውን ቀጥፈን ጥለን፤ አበባ (እ)ናስተቃምጣለን

ነቢይ መኮንን
ጥቁር ነጭ ግራጫ



የቀድሞው ማስታወሻ መጽሐፍ ላይ ከጀርባ የነበረው ምስል ፤

@Amharicbookstore

# ክፍል ሦስት

# ማዕደ ጥበባት

... ሰው እያለ አጠገባችን
ቅንነቱን ማየት ሲያመን
ከኛ አብሮ በሕይወት ቆሞ፤ መልካሙን ስም
መጥራት ሲያንቀን
"ሰው ካልሞተ ወይ ካልሄደ አይነሳም" እንላለን
እንዲህ እያልን፣
ስንቱን ጠቢብ እየሸኘን፤
አበባውን ቀጥፈን ጥለን፤ አበባ (እ)ናስቀምጣለን

ነቢይ መኮንን
ጥቁር ነጭ ግራጫ

## ፳፫

# መጻሕፍት ለሁሉም

ተረት ሰፈር በአዲስ አበባ እንብርት ላይ ትገኛለች፡፡ ከአራዳ ዝቅ፣ ከቸርችል ጎዳና ፈቀቅ ብላ ነው የተመሰረተችው፡፡ ታላቁን ቤተ መንግስት በራስጌዋ ቴዎድሮስ አደባባይን በግርጌዋ፣ ሰይጣን ቤትንና ሊሴ ገብረ ማርያምን (የፈረንሣይ ትምህርት ቤት) ከላይና ከታች ጎንዋ አኑራለች፡፡

ተረት ሠፈር በስታቲስቲክስ ቋንቋ ስትገለፅ ወረዳ 2 ቀበሌ 16 ትባላለች፡፡ በዚህ ቀበሌ በቤት ቁጥር 336 ውስጥ ጋሼ ስብሐት ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ ኖሯል፡፡

ቤቷ አንድ ክፍል ነች፡፡ ይህችው ክፍል ሳሎን መኝታ ቤትና ማዕድ ቤት ሆና ታገለግላለች፡፡ ክፍልዋ አንድ ጎንዋ በመጋረጃ ተከልሏል፡፡ በዚያች ውስጥ የወጥ ቤት ቁሳቁስ ተደራጅቶባታል፡፡ ከማዕድ ቤቷ ውጪ ፋሚሊ አልጋው በወጉ ተነጥፎ በአንድ ጎን ይታያል፡፡ በስተግርጌ በአነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ትልቅ ቴፕሪከርደር ተቀምጧል፡፡ የቢትልስን ሙዚቃ ያንቆረቁረዋል፡፡ ክሮቹም ተደርድረው የመደመጥ ወረፋቸውን ይጠብቃሉ፡፡ ከእርሱ አጠገብ አንድ የስፖንጅ ፍራሽ ለደከመው ሰው ማረፊያ እንዲሆን ተነጥፏል፡፡ ከአጠገቡ የሳጠራ ጠረጴዛ ጥቂት መጻሕፍት ተደርድረውበት ይስተዋላል፡፡ እኔ የተቀመጥኩበት የቀርከሀ ሰፌ ወንበር ከወደ በሩ አለ፡፡ ከአልጋው ፊት ለፊት ሁለት ብርኩማዎችና አንድ ሣጥን ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይስተዋላሉ፡፡

እኔና ዜና እየተጨዋወትን ነው፡፡ ምሣም ስለጋበዘችኝ ማዕድ ቤቷ ውስጥ ጉድ ጉድ ትላለች፡፡ በቅርብ እናቷ በአንጀት መታጠፍ ሕመም አርፋለች፡፡ ስለዚህ ቤቷን ማስተዳደርና ታናሽ እህቷን መንከባከብ የዜና ድርሻ ነው፡፡

ጋሼ ስብሐት መጣ፡፡ እንዳየኝ "አ ሴይለር!" አለኝ፡፡ ተነስቼ ተቀበልኩት፤ ተሣሣምን፡፡ በእጁ ሁለት ያልፈነዱ እንቡጥ ፅጌረዳዎች ይዟል፡፡ አንደኛዋ ቀይ፣ ሌላዋ ሮዝ ናቸው፡፡ ለልጁ ሰጣት፡፡ ፈገግ ብላ ተቀበለችው መጽሐፍቶቹ አጠገብ ባለው ብርጭቆ በውሃ ውስጥ ተከለቻቸው፡፡

@Amharicbookstore



ምሣ ቀርቦ እያወጋን ተመገብን፡፡ ጋሼ ሞቅ የሚያደርገውን ያዘ፡ እኔም ፍራሹ ላይ ወርጄ ተቀመጥኩ፡፡ ወግ ጀመርን፡፡

"እነዚህም መጻሕፍት የዜና ናቸው" አለኝና ጨዋታውን ቀጠለ፡፡

በወጣትነቴ ዘመን መጻሕፍት የመሰብሰብ የመግዛት ባህሉን አዳብሬው ነበር፡፡ አስታውሳለሁ በርካታ መጻሕፍትን በቤቴ በጥሩ መደርደሪያ ላይ አከማችቼ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት የአጋጠመኝ ሰው መጻሕፍትን መሰብሰብ ማይሆን ካነበብኩ በኋላ ለማኅበረሰቡ እንዲዳረስ መበተን እንደሚኖርብኝ አሳሰበኝ፡፡ በጉዳዩም አመንኩበትና ተግባራዊ አደረኩት፡፡ ሰውዬው ዶክተር ስተርሊንግ ሁዊለር ይባላል፡፡ አሜሪካዊ ነው፡፡ የሥነ ልቦና ምሁር ነው፡፡ እዚህ የመጣው ወደ አገራችን የመጡት የሰላም ጓዶች የሥነልቦና ችግር ቢደርስባቸው ወይም እንዳይደርስባቸው ለመርዳት ነው፡፡

በዚያን ወቅት እኔም ከሰላም ጓዶች ጋር እሰራ ስለነበር በሥራ ፀባዬ አመቺነት ተግባባን፡፡ በጣም ተቀራረብን፡፡ ከሐናም ጋር አስተዋወቅኩት፡፡ እርሱም ባለቤቱን አስተዋወቀኝ፡፡ ቤተሰብ ሆንን፡፡ የእኔና የሐናን ፍቅር እንደ ፍቅረኞች ተምሣሌት ይወስዱት ነበር፡፡ የእኛ ዕድሜ እነርሱ ደረጃ ላይ ሲደርስ እንደነርሱ በጥልቅ ፍቅር የተሣሠርን ባልና ሚስት የመሆን ምኞቱ እንደነበረን አስታውሳለሁ፡፡

በዚያን ጊዜ ስተርሊንግ 52 ዓመት ሲሆነው፣ ባለቤቱ ከርሱ ትንሽ ብታንስ ነው፡፡ ስተሪሊንግን በጣም ስለምንወደው የምንጠራው በመጀመሪያ ስሙ ነበር፡፡ በባህላቸው እንጥራው ብንል ዶክተር ሁዊለር ብለን ልንጠራው ይገባን ነበር፡፡ እሱም በዚህ አጠራራችን ይደሰትበት ነበር፡፡ ባለቤቱንም ዶት ነበር የምንላት፡፡

አንድ ቀን ስተርሊንግ መጽሐፍ አዋሰኝ፡፡ የመጽሐፉ ጭብጥ የሲ.አይ.ኤን ጉድ የሚዘከዝክ ነው፡፡ ደራሲው በዚህ ግዙፍ የስለላ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊ የነበረ ሰው ነው፡፡ መጽሐፉን አሁን ሳስበው አሜሪካ ውስጥ ባይሆን የትም የማይጻፍ፣ የትም የማይታተም ነው፡፡ እኔ አንብቤ በስተርሊንግ ግብግቦ ተደሰትኩ፡፡ ይህንን አሪፍ መጽሐፍ ጓደኛዬም ማንበብ አለበት ብዬ አዋስኩት፡፡ እሱ አንብቦ እስከሚመልስልኝ አንድ ሣምንት ፈጀ፡፡ ጓደኛዬ እንደ እኔ አንብቦ ተደስቶና ተደንቆ ከመለሰልኝ በኋላ ወደ ስተርሊንግ ሄጄ፣ "የአዋስከኝን መጽሐፍ ለአንድ ሣምንት ያህል አዘገየሁብህ፡፡ ምክንያቱም እኔ አንብቤ በጣም ስለተደሰትኩ ጓደኛዬ ከደስታዬ እንዲጋራ ብዬ አውሼው ነበር፡፡ ከአንተ ፍቃድ ሣላገኝ በሠራሁት ጥፋት ይቅርታ እጠይቅሀለሁ" አልኩት፡፡ የእርሱ መልስ እኔን አነቃኝ፡፡ መጽሐፍትን አሰባስቦ በመደርደሪያ ላይ ከምሮ በአንድ ክፍል መቆለፍ ልክ እንዳልሆነ ተረዳሁ፡፡

"እንኳንም ያዋስከው፡፡ መጻሕፍት እኮ ብታተሙ በኋላ ማንበብ የሚችል የሰው ዘር እንዲያነባቸው ነው የተፃፉት፡፡ ማዋስህም ከመጽሐፉ ደራሲ አላማ አኳያ ትክክል ነው፡፡" አለኝ፡፡

አየሁ፣ አባባሉ እኔን ለወጠኝ፡፡ ተገለፀልኝ፡፡ ሳይ እኔ መንት መጻሕፍት እየገዛሁ አንብቤያቸው መደርደሪያዬን አጨናንቀዋል፡፡ ሥራ ፈትተው ነው የተቀመጡት፡፡ እኔ በፍቅራቸው ተጠምጄ እስረኛዬ አድርጌያቸዋለሁ፡፡ ከዚህን ዕለት ጀምሮ ነፃ መውጣትና ንባብ ለጠማው ሁሉ በየደረሱበት ጥሙን እንዲያረኩ ወሰንኩ፡፡ ቤቴ ሰብስቤ ያስቀመጥኳቸውን መጻሕፍት እያወጣሁ ለሚያነቡ እንዲዳረስ መስጠት ጀመርኩ፡፡ ለጠየቀኝም አንብቦ ለሌላ እንዲያስተላልፍ እሰጣለሁ፡፡ ከዓመት ወይም ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሜ አነበዋለሁ የምለውን ካልሆነ እቤቴ አላስቀምጠውም፡፡

ከዓመታት በፊት በአደራ ደበበ እሸቱ ቤት አስቀምጫቸዋለሁ፡፡ አንድ መጽሐፍ እንዴት እንደወጣ አላውቅም፣ መርካቶ አሮጌ መጻሕፍት ተራ አግኝቼዋለሁ፡፡ እንደጠረጠርኩት መቼም ደቤ አንድ ብሽቅ ሠራተኛ ቀጥሮ፣ ሰርቆት የወጣ ይመስለኛል፡፡ ታዲያ ይህ የማላውቀው ወዳጄ ባለውለታዬ ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ለራሱ ገንዘብ ለማግኘት አስቦ ሳያውቀው የእኔን አላማ እያራመደ፣ እያስፋፋልኝ ነው፡፡ ሳያውቀው የእኔ ሠራተኛ ሆነ፡፡ የተቀሩት መጻሕፍት ግን አሉንም አሉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ከፈለግን ደበበ እሸቱ ቤት ሄደን አምጥተን ማንበብ እንችላለን፡፡

ደግሞ እኮ እንደ ሰው በዚህ ቀን በዚህ ሰዓት እንገናኛለን አንልም እንጂ ከመጻሕፍት ጋር ቀጠሮ አለን፡፡ ከረጅም ዓመት መለያየት በኋላ የተገናኘኋቸው በርካታ መጻሕፍት አሉ፡፡

አሮጌ መጻሕፍት ነጋዴ ጓደኞች አሉኝ፡፡ ከጓደኞቼ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመጻሕፍቱ ጋርም ቀጠሮ አለኝ፡፡ አሁን ተውኩት እንጂ ወዳጆቼ ቤት ስሄድም የምወዳቸውን መጻሕፍት አገኛቸው ነበር፡፡

ድንቅ ድርጊት ነው:: ጋንድሂን በእምነቱ የምናምነውና የምንከተለው ነው:: ሚስተር ሻህ እንደነገርከኝ የጋንዲሂ ጋሻ ጃግሬ ነበሩ:: መጻሕፍት ሲሰጡህ እንደ ጋንድሂ መጻሕፍት ለሁሉም የሚለውን እምነት አራማጅ ነው ብለውሃል:: እኔም የዚህ ሃሳብ ደጋፊ ነኝ::

እንዲህ ነው መሆን ያለበት፡፡ እንደዚያ ካላደረግን እንደኛ ድሀ በሆነ አገር ውስጥ ላለ ዜጋ ገዝቶ የማንበብ አቅሙ አይኖረውም፡፡ ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ዜጋ ሆዱ ቢሞላም መንፈሱ ጎድሎ ይኖራል፡፡ ፍላጎቱ ላላቸው ወጣቶች እንዲህ ተቀባብለን የመንፈስ ረሃባቸውን በትንሹም ቢሆን ብናስታግስ ጥሩ ይመስለኛል፡፡ እኔ በዚህ አካሄዴ

@Amharicbookstore



**ደስተኛ ነኝ፡፡ በሕይወቱ በጣም የምወዳቸውን አስር መጻሕፍት ርዕስ ልጻፍልህ? በደስታ::**

1. መጽሐፍ ቅዱስ
2. ሼክስፒር (ጠቅላላ ሥራዎቹ)
3. Illiad & Odyssey - Homer
4. (Athens ቴአትሮች) Sophocles Aristophannes
5. Moby Dick – Herman Melville
6. Crime & Punishment- Dostoyevsky
7. The Devils (The Possessed)
8. The Brothers Karamazv
9. War & Peace/ Tolstoy.
10 Anna Karenina /Tolstoy
11. Fathers & Sons/ Turgenev
12. Oblomov -Goncharov
13. Hell, Purgatory, Dante Alighieri
14. Cyrano de Bergerac - Edmond Rostand
15. Sherlock Holmes- Sir Arthur Conan Doyle
16. Alice in Wonderland- Lewis Carroll
17. Through the Looking Glass - Lewis Carrol
18. Yaroslav Hasek – The Good Solider Schweik **እናም ሌሎች ወዘተ... እንበለው**

## ፳፱

## ጥበበ ሰይጣን ቤት

ሲኒማ ታላቅ ጥበብ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ዕውቀት ልትገበይበት ትችላለህ፡፡ ያወቀበት ይጠቀብበታል:: ድሮ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ 'Citizen Cang' የሚባል ፊልም አይቻለሁ፡፡ ይህ ፊልም በወቅቱ ቅርስ ሆኖ ነበር፡፡ የትም ይታያል፡፡ ከገበያው ከወጣም በኋላ የእኛ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ክበብ አስመጥቶት ነው

ያየሁት፡፡ ይህንን ፊልም አርሰን ዌልስ ከሠራ በኋላ ሌሎች ፊልሞችም ሠርቷል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ 'ሲትዝን ኬን' መሆን አልቻሉም፡፡ ስለዚህ "ምነው ሌሎቹ ሥራዎችህ እንደ 'ሲትዝን ኬን' አልተዋጡልህም?" ብለው ጋዜጠኞች ጠየቁት፡፡

እርሱም ሲመልስ "የፊልም ሥራን ከቁንጮው ስለጀመርኩ ወደታች እንጂ ወደላይ የሚያስኬድ መንገድ አልነበረኝም" አላቸው፡፡ ይኸው አርቲስት ድንቅ ተራኪ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት በሬዲዮ ባዕዳን የሌላ ዓለም ነዋሪዎች ኒውዮርክን ሲወሩ ይተርካል፡፡

በዚህ ጊዜ ብዙ የኒውዮርክ ሕዝብ ቤቱን ዘግቶ ራሱን ለመከላከል ሽሽት ጀመረ፡፡ ይህንን ያህል ኃይል ያለው ተራኪም ነበር፡፡ ይህ ስጦታ ከሂትለር እኩል ነው፡፡ ቦታው ይለያያል እንጂ፡፡

አንድ አርቲስት ነበር የአክሽን ፊልም የሚሠራ፡፡ ስሙ ኢሮል ፍሊን ነው፡፡ በጣም መልከ መልካም ነው፡፡ ሁልጊዜ በሻሾላ፣ (ማለት በሹል ሰይፍ) የሚፋለሙትን ዓይነት የፊልም ትወና ይጫወታል፡፡ በሽጉጥ ብትል፣ በቦክስ ብትመጣ ማንም አይችለውም፡፡ ሁልጊዜ ያሸንፋል፡፡

እጅግ የተዋጣለት ነው፡፡ ሁለመናው ስልህ!! አለእዚያኮ የዓለምን ፊልም አፍቃሪ ሊማርክ አይችልም ነበር፡፡ ሰውየው መጠጣትና ከሕዝብ ጋር መሆንን ይወዳል፡፡ ፊልም ላይ ያዩት ጎረምሶች ይተናኮሉታል፡፡ "አሁን እኮ አዘጋጁ አሁን ምታ፣ ምናምን እያሉት ነው እንጂ አቅም የለውፊታ" ይላሉ የሚቀኑበት ናቸው፡፡ አንዱ ይጠጋውና "እስኪ ወንድ ከሆንክ ይዋጣልን" ይለዋል፡፡ "በደስታ!" ይልና ያገላብጠዋል፡፡ ምክንያቱም መደባደብ በጣም ነው የሚወደው፤ ወደ ሕዝብ መዝናኛም ሲመጣ የሚደባደበው እንደሚያጋጥመው ተስፋ እያደረገ ነው፡፡

እ! ደግሞ የእርሱ አዘጋጅ ነበር፡፡ ጆን ፎርድ ይባላል፡፡ በጣም ቆንጆና ጎበዝ አዘጋጅ ነበር፡፡ ከኢሮል ፍሊን ጋር ሽርክ ናቸው፡፡

አንድ ጊዜ ሁለቱ በጣም ጨዋ በሆኑ ሰዎች መሀል ተጋብዘው ሄዱ፡፡ ማንም የሚተናኮል የሚደባደባቸው እዚያ ግብዣ መሀል የለም፡፡ ተዋናይና አዘጋጅ ትንሽ ጠጡና "ውጣ ብለን ትንሽ አንልም?" ተባባሉ፡፡ አለ ጋሼ ፈገግ ብሎ እጆቹን ለቦክስ ፍልሚያ ጨብጦ፡፡

"ደስ ይለኛል" ተባባሉና ወጥተው ተደባድበው፣ ተደባድበው፣ አፍንጫቸው ደምቶ ልብሳቸው ተቀዶ ደስ ብሎዋቸው ተመለሱ፡፡ እየሳቀ "ይህ የእውነት ታሪክ እኮ ነው፡፡ ለዚህ እኮ ነው የአክሽን እንቅስቃሴያቸውን በደንብ የሚሠሩት፡፡

@Amharicbookstore



የካኔቴራን ገበያ ዘጋ ያልኩህ ክላርክ ጌብል ይባላል፡፡ ጎን ዊዝ ዘ ዊንድ የሚባለውን መጽሐፍ ታውቀዋለህ? ነቢይ መኮንን እስር ቤት ሆኖ ነገም ሌላ ቀን ነው ብሎ የተረጎመው መጽሐፍ፡፡ በፊልም የተጫወተው ይኸው አርቲስት ነው፡፡ እሱ ፊልም ሲታይ 94 ሰዓት የሚወስድ ሆኖ ተሠርቶ ወደ አራት ሰዓት ይሁን 4፡30 አጥሮ ነው ለሲኒማ ቤቶች የተሰራጨው፡፡ ምን ያህል እንደ ተለፋበት አስብ፡፡ እኔ ይህንን ፊልም ካየሁ በኋላ መጽሐፉን ፈልጌ ማንበብ አላስፈኝም፡፡

ክላርክ ጌብል ሌላ ፊልም ሲሠራ በሙቀቱ ወቅት ስለነበር ሸሚዙን ሲያወልቅ ካናቴራ አልለበሰም፡፡ ይህንን ያየ የአሜሪካን ጎረምሣ ሁሉ "ለካስ ክላርክ ጌብል ካናቴራ አይለብስም" ብለው ተከተሉት፡፡ የካናቴራ ነጋዴዎች ለአንድ ወቅት ገበያቸው በጣም ወረደ፡፡

ግሪኮቹ 'አማልክት የሚወዱት ወጣት ሆኖ ይሞታል' የሚሏት ዓይነት ነበረች ማሪሊን ሞንሮ፡፡ የመጨረሻ ውብ ነች፡፡ የእንስት ውበት ተምሳሌት ሆነች፡፡ ቻይና ፔኪንግ ብትሄድ እንኳን ፎቶዋ በትልቁ ተሰቅሎ እስካሁን ይታያል፡፡ 'ጎደስ' ይሏታል፡፡ የትም አገር አገሯ ነው፡፡

በጣም ነው በሕዝብ የምትወደደው፡፡ እሷ ግን በቂ የተወደደችና የተደነቀች አይመስላትም፡፡ ፕሬዚዳንት ኬኔዲ ለልደቱ "መጥተሽ ዘምሪልኝ" ብሎ ጋብዞዋታል፡፡ ያም ቢሆን የመወደድ ፍላጐቷን አላረካውም፡፡ አፈፃፀሟ አይታወቅም፡፡ የማናውቀው ልማድ ይኖራታል፡፡ የእንቅልፍ መድኃኒት ለሞት የሚያበቃትን ያህል ዋጠችና ተሰናበች፡፡ የሀገራችን ሰዎች 'ሞቴን አሳምርልኝ' ያሉት ወደው አልነበረም፡፡ ሽበት፣ጠባሳ፣መጨራመት ምናምን ሳይኖር እንዳማረባት ተለየችን፡፡

ማሪሊን ሞንሮ ተጫውታ በጣም የወደድኩላት ፊልም 'ዘ ሪቨር ኦቭ ኖ ሪተርን' የሚል ነው፡፡ ጎረምሶችን ፈተና ላይ የሚጥላቸው ነው፡፡ ሌላ ፊልሟ 'ሳም ላይክ ኢት ሆት' የሚባለው ነው፡፡ አስቂኝ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ አንደኛ ኮሜዲያን ከሚባል ከጃክ ሌመን ጋር ድንቅ አድርገው ነው የተጫወቱት፡፡

ሌላው በጣም የሚያስደንቀኝ የሆሊውድ አክተር ዳኒ ኬይ ይባላል፡፡ ከቻርሊ ቻፕሊን ወዲህ ትልቁ የሣቅ ንጉስ ነበር፡፡ ዘማሪና ዳንሰኛ ነበር፡፡

ዳኒ ኬይ ኒውዮርክ ናይት ክለቧ ውስጥ ዳንስ እየተጫወተ ሲዘፍን ነበር የሆሊውድ ቃፊሮች ያገኙት፡፡ ሆሊውድ ገብቶ ድንቅ አርቲስት

ወጣው፡፡ በዚህ ላይ ለዩኔስኮ በዓመት አንድ ወር ነፃ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የፈለጉትን አገር ልጆችን ሕፃናትን ያጫውታል፡፡ በጣም፣ በጣም ልጆችን በማጫወት የተዋጣለት ነበር፡፡ ሌላ ችሎታው የቻይና ምግብ ማብሰል ባለሙያ ነበር፡፡ ምናልባት ቻይና ውስጥ የሚወዳደረው ይኖራል፡፡ እራሱ የሚነዳው አውሮፕላን ነበረው፡፡ እይ እንግዲህ ስንት ዓይነት ሰው እንደሆነ! ትክክል፡፡ እንዳልከው ጥበብን ጨምሮ 'ሁሉ በእጁ፣ ሁሉም በደጁ' የሚባልለት ነው፡፡ ለዳኒ ኬይ ይገባዋል፡፡

ዘፋኝ ስንል እንደ ኤልቪስ ፕሬስሊ እስካሁን የተወደደ ዘፋኝ ያለ አይመስለኝም፡፡ አሁን ምን አልባት ማይክል ጃክሰን ሊሆን ይችላል፡፡ 'ኤልቪስ ሴቶችን ደስ የሚያሰኛቸው ሲደንስ የዳሌ ውዝዋዜው የማንቋለጥ ያህል ነው፡፡ ጋዜጠኞቹ 'ፔልቪስ' ነው የሚሉት፤ ፔልቪስ ማለት በእንግሊዘኛ ይህ ነው'' ዳሌዎቹን በሁለት እጆቹ ይዞ እያሳየኝ፡፡

ሲዘፍንም ከልቡ አርቲስት ነው፡፡ በዚያን ዘመን ድምፁ ዳንሱና ዘፈኑ ይበልጥብናል እንጂ፤ የተውኔትም ባለሙያው ነበር፡፡ ኤልቪስ ፊቱ የሴት ዓይነት ውበትና ቅርፅ ያለው ሆኖ ሌላው አካሉ ወንዳ ወንድ ነበር፡፡

ዕድገቱ አንድ ቦታ ላይ ሲደርስ ጨረሰ፡፡ ገንዘብም እንደልብ ሆነ፡፡ ቤቱን 'ግሬስ ላንድ' አለው፡፡ የፀጋ ዓለም፣ ወይም ምድረ ገነት እንደማለት ነው፡፡ መደነሱን መዝፈኑን ተወ፡፡ ያ ሁሉ ጉልበቱ ወደ እህል መብላት ዞረ፡፡

በዚያን ወቅት ሀምበርገር የሚባል የሥጋ ሳንድዊች ነው ዘር ማንዘሮቹ የሚያውቁት፡፡ ኤልቪስ ከተቆረጠ ቺዝ ጋር ጠብሶ በላው፡፡ በጣም ጣፈጠው፡፡ ቺዝ በርገር የኤልቪስ ግኝት ሆነ፡፡ ቺዝ በርገሩን ሲበላ፣ ሲበላ ማቆም አልቻለም፡፡ በጣም ወፈረ፡፡ እነዚህ መገናኛ ብዙኃን የሚባሉት መቼስ የሰውን ሐፍረት መሸፋፈን አያውቁም፡፡ እንዲያውም ማንጓጠጥ ነው የሚወዱት፡፡ የኤልቪስን ውፍረት ለአፍቃሪዎቹ በተከታታይ አርድተው አስለቀሷቸው፡፡ እንደዚያው እንደወፈረ ተሰናበተ፡፡

"ኤልቪስ ሰው መራቅና መጥላት ጀምሮ ነበር የሚባለው ሐሰት ነው፡፡ አንተ ጋዜጠኞችን አንብበህ ነዋ! በእኔ ንባብ ግሬስ ላንድ በርካታ ሰዎች እየሄዱ ይጎበኙት ነበር፡፡ ከቺዝበርገሮቹ ጋር በፍስሀና በሰላም መኖሩን አውቃለሁ፡፡

@Amharicbookstore



በእኔ የሲኒማ ዓለም ውስጥ ከቻርሊ ቻፕሊን ቀጥሎ ኢንግማር በርግማን የሚባል ስዊድናዊ ደራሲ እና አዘጋጅ ነው ገዝፎ የሚታየኝ፡፡ ያውም ለእኔ በማውቀው ቋንቋ አልነበረም የቀረበልኝ፡፡ ድርጊቱ እየተካሄደ ከሥር ይጻፍልሃል፡፡ 'Sub title?'

እ! ከውጪ ወደ ፈረንሣይ የሚገቡ ፊልሞች በሙሉ ተተርጉመው ነበር የሚታዩት፡፡ ኢንግማር በርግማን ግን ፈረንሣይ ውስጥ አይተረጎምም፡፡ በስዊድንኛ ነው የሚታየው፡፡ እንደ ተባባልነው ከፊልሙ ሥር 'ሰብ ታይትል' ይጽፉበታል፡፡

የሲኒማው ጥበብ ልክ እንደ አገሩ ጭፍግግ አድርጎ የሚይዝ ነው፡፡ አንዷን ላጫውትህ፡፡ 'ሰባተኛው ማህተም' ትባላለች፡፡ ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ነፃ ለማውጣት ዘምተው ሲመለሱ በደህና አድርሳ የመለሰቻቸውን የቡርዥ ማርያም ለመሳለም የተሳሉትን ሰዎች አንዱ አርበኛ ሊያደርሳቸው ነው፡፡ እየተጓዙ እያሉ ሞት ሰው ተመስሎ ይመጣል፡፡ ለአርበኛው ሞት መሆኑን ነግሮት እንሂድ ይለዋል፡፡

''እኔ አልፈራህም፡፡ ስዋጋ የኖርኩት ስለማልፈራህ ነው፡፡ ግን እነዚህን ሰዎች ቡርዥ ማርያም እስካደርስ ጊዜ ስጠኝ'' አለ አርበኛው፡፡

''ሰዎች ልወስዳቸው ስመጣ ምክንያት ይደረድራሉ'' አለ ሞት ቅሬታውን እንደሰማ፡፡

አርበኛው ''ቼዝ ጨዋታ ግጠመኝ፡፡ እስካላሸነፍከኝ ድረስ ጉዞዬን እንድቀጥል ፍቀድልኝ፡፡

''እሺ ይዋጣልን!'' ይላል ሞት፡፡

የተመልካች ጭንቀት እዚህ ጋ ይጀምራል፡፡ መቼ? ማን ያሸንፋል? ነው እንግዲህ ጥበቡ፡፡ ሞት እንደሚያሸንፍ የታወቀ ነው፡፡ ግን መቼ? አሰቡበት ይደርሳሉ ወይስ መንገድ ይቀራሉ? ነው ጭንቀቱ፡፡ ልባችን እንደተንጠለጠለ አሰቡበት ይደርሳሉ፡፡

አርበኛው ''ውሰደኝ!'' ይለዋል ሞትን፡፡ ከማዶ ከጋራው ወድያ ጨረቃ ወይም እንደፀሐይ ሆኖ በዚያ ግርዶሽ የሚሞቱት ሰዎች እየደነሱ ይሄዳሉ፡፡ ሟቹንም አርበኛ እዚህ ውስጥ እየደነሰ ሲሄድ እያየነው ፊልሙ ይደመደማል፡፡...

የሆሊውድ አርቲስቶች በትንሽ ደመወዝ ለብዝበዛ ይጋለጣሉ፡፡ ይህንን ያየው ቻርሊ ቻፕሊን ብጤዎቹን ሦስት አርቲስቶች ሰብስቦና የራሳቸው የፊልም ማምረቻ ኩባንያ መሠረቱ፡፡ 'ዩናይትድ አርቲስትስ' ይባላል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ሆሊውድን የመሰረቱት ይሁዲዎች አይደሉም። ሆሊውድን የመሠረቱት ሁኔታዎች ናቸው። ግን ሆሊውድ በደንብ ለዓለም የፊልም ውጤት ማበርከት ሲጀምር ዋናው ሰውዬ ይሁዲ ሆኖ ተገኘ። ሥርጭቱን የቻለበት፣ አርቲስቶቹን ማስተዳደር ያወቀበት ሰው ነበር።

ሚስተር መየር ይባላል። መየር አክተሮቹን እንደ ልጆቹ ነው የሚያያቸው። ደግሞም ከልቡ ነው። ሚኪ ሩኒ የሚባል የአሜሪካ ጀግና ሆኖ የተጫወተ አርቲስት ነበር። ሲባልግ መየር አየውና "አንተ እኮ የአሜሪካ ጀግና ነህ። እንዴት ብለህ እንዲህ አገርህንና ሕዝብህን ታዋርዳለህ?" ብሎ አለቀሰ። ማልቀስም ይወዳል።

ይኸውልህ፣ እኛ አገር እኮ አንድ ነገር ይጀመራል! እናም ጉራ ይነፋል። ዘራፍ ይባላል። ገና ሳይገደል ግዳይ ይጣላል።" እየሣቀ "እና ቆንጆ ጀምረው ነበር። ጉማ፣ ሂሩት አባቷ ማነው?፣ ሻፍት ኢን አፍሪቃን አየን። ወጥም ተሳትፎም ነው። አሁን ያልካቸውን ፊልሞች አየን። ነገር ግን ውሃ አድራ ሚሚች። ከዚያ በኋላ ለብዙ ዓመታት የፊልም ሥራችን አልታየም። በቅርብ ጊዜ አንድ ፊልም መሥራታቸውን ሰምቻለሁ። አስቴር ይባላል ርዕሱ?

እንግዲህ አስቴርን ከሥሩ ጥበቡ አልሞተም ማለት ነው አለ። ቀደም ሲል በቴሌቪዥን ውብሸት ወርቃለማሁ 'ውለታህ ጥፊ' በሚል ርዕስ ራሱ ፅፎ፣ አዘጋጅቶ የተጫወተውን ፊልም አይቼው ነበር። ውብሸት በዚህ ፊልሙና አተዋወኑ አስደነቀኝ። በቆይታ የተሻለ እንጀራ ፍለጋ ወደ ማስታወቂያ ሥራ ሄደ ቢባል አዘንኩ። ያገሬ ድህነት ዕድል ስለማይሰጥህ ከምትወደው ሙያ ያሸሽሃል።

ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት መድረክ ላይ በጌታ ልደት ጊዜ እኔ እንደ ማርያም ሆኜ ተጫውቻለሁ። ሙት! እንዲህ ቀላል ሰው መሰልኩህ? ዮሴፍ ደግሞ ተስፋዬ ነበር። ሐምሌትን ፀጋዬ ገብረመድህን ተርጉሞ ሲያዘጋጅ እኔና ተስፋዬ ጓደኛሞች መሆናችንን ያውቃል። ስለዚህ አብረን እንድንጫወት ፈለገ። ጠየቀን፣ ተስማማን። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ታየ። ፀጋዬም ጥሩ ገቢ አግኝቶበታል።

ለኪስ ብሎ ጥቂት እንኳን ጉርሻ አልሰጠኝም። የተስፋዬን አላውቅም፤ ለእኔ ምንም አልሰጠኝም። ፀጋዬ ድኖ ከአሜሪካ ይምጣ እንጂ መክሰሱ አይቀርለትም" አለና ሣቀ።

@Amharicbookstore



የቪዲዮ ፊልሞችን አዎን፣ ዕድል ሲያጋጥመን እናያለን። በቅርብ ካየሁት 'ታይታኒክ' አስደነቀኝ። ከኩኩሻ ጋር ረጅም ሰዓት የፈጀ ውይይት በፊልሙ ላይ አካሄድን" እየሳቀ "በጣም አሪፍ አርገው ነው አርቲስቶቹም የተጫወቱት፤ አዘጋጆቹም በጣም እንደደከሙበት ያስታውቃል። ልብ አርግ፣ የእኔን ዕድሜ ተመልከት። ከኩኩሻ ጋር ሁለታችንም እኩል እንድንደሰት አደረጉን። ይህ ፊልም ከልቡ ፊልም ነው። ሰሞኑን 'Time' መጽሔት ይዤ አይተኸኛል። ታይታኒክ ላይ የተጫወተው ሊዮናርዶ ዲካፕሪዮን አስመልክተው በሰፊው ፅፈዋል፤ በቆንጆ ቆንጆ ፎቶግራፍ አስደግፈው። ለኩኩሻ እንድታየው ወሰድኩላትና "እኔጋ ትንሽ ይሰንብት" አለችኝ። "እሺ" አልኳት። ልክ ነች። የዘመንዋ አርቲስት ነዋ!"

አሜሪካ በነበርኩ ጊዜ አንዱ በጣም ደስ እያለኝ የምዝናናበት ማስታወቂያ ማየት ነበር። አንዷን ልንገርህ። ጀሪ ሉዊስ የተባለ የታወቀ ይሁዲ ኮሜዲያን ነበር። እንደ አሮጊት ሆኖ ቁጭ ብሎ ቴሌቪዥን ያያል። አሜሪካ ስታረጅ አጫዋችህ ቴሌቪዥን ነው። ማስታወቂያው መጣ። "ፀጉርዎ ዘማነቱን እንደጠበቀ እንዲቆይ ይፈልጋሉ?" ይላል አስተዋዋቂው። "ይህንን ቅባት ይጠቀሙዋ?!" ያሳይሃል ቅባቱን። ዞማ ፀጉር ያላቸው ወንዶችም ሴቶችም ይታዩሃል። "አሁኑኑ ይግዙት! Buy now!" ይላል!!

አቶ ኮሜዲያን ቱር ብሎ ከፎቅ ወርዶ ገዝቶት ይመጣል። በኋላ እቀባዋለሁ ይልና ያስቀምጣል። ቴሌቪዥኑ ላይ ያፈጣል። ሌላ የሚያማልል ማስታወቂያ ደግሞ ይቀጥላል። እንዲህ እያለ ብዙ የማያስፈልጉትን እቃዎች በቲቪ ትዕዛዝ ገዝቶ ይደረድራል።

የሮልስ ሮይስ ማስታወቂያ እንዲህ ይላል፤ 'At 60 miles per hour. the only sound you hear is the ticking of the clock! አየህ? እንዴት የሚጥም ቃና እንደሚኖረው? በአማርኛ እንበላት። "ሺ ጊዜ ፈጥነህ ብትነዳ የምትሰማው ድምፅ ቢኖር የሰዓቱ ቲክታ ብቻ ነው።" ይህ ግን ባለፍክ ባገደምክ ስለሚደጋገም 'clich'e' ይሆንብሃል።

ክሊሼ? አርቲስቱ አንድ አሪፍ 'ኦሪጅናል' ሥዕል ይስላል። ከዚያም ይህንን እያባዙ ይሸጡታል። በብዛት ምክንያት ተራ ሥዕል ይሆናል። በእኛ አባባል 'ያልፈሳንበት ዳገት የለም' አለች አህያ ሲሉ ስትሰማ መጀመሪያ ያስደንቅሃል። በኋላ አላፊ አግዳሚው ሲደጋግማት ግን 'ክሊሼ' ትሆናለች።

@Amharicbookstore

አንዱ ባለሀብት 'ሮልስ ሮይስ' ገዝቶ ተበላሸበትና ለኩባንያው ደወለ፡፡ ያለበትን ቦታ በጠቆማቸው መሠረት በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሄሊኮፕተር 'ሮልስ ሮይስ' ጭና መጣች፡፡ አዲሷ ወረደች፡፡ አሮጌዋ ተጫነች፡፡ ሰውየው ወደ ኩባንያው ደወለና ያደረጉለትን ውለታ ጠቅሶ አመሰገናቸው::

"ተሳስተሃል" አሉት፡፡

"እንዴት?" አለ ሰውዬው፡፡ በኩባንያው ወገን ያለው ሰው ሲመልስ "ሮልስ ሮይስ አይበላሽም" አለው፡፡

ባጠቃላይ ጥሩ ከሠራህ ማስታወቂያ አያስፈልግህም፡፡ አንድ ጫማ ሰሪ አለ ለንደን ውስጥ፡፡ እነ ፕሪንስ ፊሊፕ ደምበኞቹ ናቸው፡፡ እነኒሪ ኩፐር ከአሜሪካ ለንደን ድረስ ሄደው ጫማ በልካቸው ያሠራሉ፡፡ ሩቅ አትሂድ፡፡ የአንተ አባት አቶ ወላ ወጋ ሸማ ለመሥራት ማስታወቂያ ይለፍፋሉ? በቃ፡፡ ለጥሩ ሥራ ማስታወቂያ አያስፈልገውም፡፡ ለሸማችህ ማስታወሻ ቢያሻህም መርጫህ ሳይሆን ማሳየቱ በቂ ነው፡፡

ተረት ሰፈር አንድ ሻይ ቤት አለች፡፡ ባለቤቷ ባልቻ ይባላል፡ ኩሽና ውስጥ ሻይ የሚያፈላ ትንሽ ልጅ አለ፡፡ በኩሽናውና ሻይ ቤቱ መሀል ባለች በር ላይ አንድ ማስታወቂያ ተለጥፋለች፡፡ ከሠራተኛ በስተቀር መግባት ክልክል ነው፡፡ ኮሚቴው ይላል፡፡ ኮሚቴው እኮ ባልቻ ነው፡፡

ይኸውልህ! ሺ ጊዜ ሎሚኸህ ድርጅትህን ከማስተዋወቅ ጥቂት እንደ ቶታል በማድረግ ድንቅ "ማስታወቂያ መሥራት ይቻላል" አለኝ ጋሼ ተደንቆ፡፡ "አካፑልኮ የኩኩሻም ተወዳጅ ፊልም ነው፡፡ አክስቷ ቤት ቅዳሜ ልጎበኛት ስሄድ ፊልሙ መታየት ሲጀምር "ተርጉምልኝ" ትለኛለች፡፡ እሺ ብዬ ግማሹን እንዳየን "በቃህ ሂድ ይመሽብሃል" ትለኛለች፡፡ የእኔ ጠባቂ!

"ዘነበ አስታውስ!" አለ ጋሼ ስብሐት "ሲኒማ ታላቅ ጥበብ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ዕውቀት ልትገበይበት ትችላለህ፤ ያወቀበት ብዙ ይጠበብበታል ከምወዳቸው የተወሰኑትን ልጣፍልህ? ማስታወሻ አቀበልኩት::

1. Gone with the wind (actor Clark Gable)
2. Ben Hur (actor: Charlton Heston)
3. Every film of Chrlie ChPLIN
4. Les Enfants du Paradis (French)
5. Silence (director: Ingmat Bergman)
6. Toto al'Inferno (actor; Toto!)



7. The Three Musketeers (actor; Gene Kelly)
8. Some Like It Hot (director: Billy Wilder)
9. Irma La Douce (actress: Shirley Maclane)
10. Mondo Cane ( **ውሻ ዓለም የሚል የጥሊያን** documentary)
11. The Magnificent Seven ( Yul Brynner; actor)
12. Knock on Wood (Danny Kay; actor)
13. The Court Jester (Danny Kaye: actor)
14. Hans Christian Andersen (Danny Kaye: actor) **ወዘተ**"
15. Our Man Flint
16. Shane
17. High Noon **ወዘተ**

***

## ፴

## <u>ባርነትና ነፃነት</u>

ከቱሪስት ሆቴል ወደ አምባሳደር ቴአትር በታክሲ እየተጓዝን ነበር፡፡ ፀጥታ በሁለታችንም መካከል ነግሣለች፡፡ የየራሳችንን ሐሳብ እናብሰለስላለን፡፡ የጋሼ ስብሐትን እንጃ እንጃ እኔ የዚያን ዕለት እንድናወጋ የፈለኩት በካርል ማርክስ ፍልስፍናና ሕይወት ላይ ነበር፡፡

አምባሳደር ቴአትር ደረስን፡፡ መንገዱን ተሻግረን በሐራምቤ ሆቴል ጥጉን ወደ መስቀል አደባባይ ማዝገም ጀመርን፡፡ ጋሼ ስብሐት አዘውትሮ እንደሚያደርገው ፀሐይዋን ለመከላከል ሹራቡን ከፌስታል ውስጥ አወጣና እናቱ ላይ አደረገ፡፡ ፌስታሉን ተቀበልኩት፡፡ አረማመዱን በርሱ ፍጥነት ልክ መጥኜ እያዘገምኩ ወግ ጀመርን፡፡

ባህሪው ለረጅም ጊዜ አብሮ ከመዋልና ከማደር ገብቶኛል፡፡ ረጅም መንገድን የሚረሳው በጨዋታ ነው፡፡ 'ይህንንም በፍልስፍና፣ በሃይማኖት፣ ወይም በድርሰት..."አንድ ነገር ሊያወጋኝ እያሰበ ነው፡፡ ወጉን ከመጀመሩ በፊት እኔ በዕለቱ ወደፈለኩት የጨዋታ ቦይ

መራሁት፡፡ ሐሳቤን ከአፌ ነጥቆኝ “የማርክስ ፍልስፍና ወንጌል ነው” አለኝ አተኩሮ እያየኝ፡፡ ሐሳቤን ያለመጨረሴን ተረድቶ ቀጥል በሚል ስሜት ጠቀሰኝ፡፡

ስታዲዮምን በቀኝ፣ መስቀል አደባባይን በግራ ትተን በደብረዘይት መንገድ አቀናን፡፡ በመሿለኪያ አቋርጠን ወደ ቂርቆስ የሚወስደውን መንገድ ይዘናል፡፡

“ማርክስ እንኳንም ደራሲ ያልሆነ!” አለ ጋሼ ስብሐት ተቆጥቶ እየተስተዋለኝ፡፡ “በሌሎች ደራሲያን ተጽፈው ስንትና ስንት ድንቅ ጽሑፍ ነው ያነበብነው፡፡ የማርክስ ሥራ ከእነዚያ ምርጥ ሥራዎች አንዱ ቢሆን ነው እንበል፡፡ እናስ ምን አዋጣ? ያው እንደነ እገሌ ደራሲ አልነው፡፡ አጨበጨብንለት፡፡ ለእኔ ግን ፍልስፍናው ይበልጥብኛል፡፡ አይደለም አንድ ቤተሰብ አንድ አውራጃም ይራብ፡፡ ፍልስፍናው ሲገባህ የእሱን መራብ ትቀበላለህ፡፡ የሰው ልጆች በአግባቡ ተጠቀሙበት አልተጠቀሙበትም፣ ያ ሌላ ጥያቄ ነው፡፡ ማርክስ ግን መከራውንም፣ ችግሩንም ችሎ ያለውን ተክሶ” አለኝና ቆም አለ፡፡ ሲጀምር ይቆጣ የነበረው ጋሼ ስብሐት ከዐረፍተ ነገር ወደ ዐረፍተ ነገር ሲሸጋገር ቁጣው እየበረደ ካርል ማርክስ ውስጡ እየገዘፈ ሄደ፡፡

“መጀመሪያ በዓለም ላይ የሚባለውን ልንገርህ? ይህ ያለንበት ክፍለ ዘመን የሶስት ሰዎች መዋርጃ ነው፡፡ ሶስቱም ይሁዲ ናቸው፡፡ ካርል ማርክስ፣ ሲግሞንድ ፍሮይድ፣ አልበርት አይንስታይን ናቸው፡፡ እንግዲህ ‘የምድር ጨው ናችሁ’ የሚለውን አባባል አስታውስ፡፡” አለና ጢሙን እያፍተለተለ አስተውሎኝ ወጉን ቀጠለ፡፡ “ስለ ካርል ማርክስ ወጣት ሆነን ስንሰማ በጀርመንኛ ነው የጻፈው አሉን፡፡ ረጃጅም ዐረፍተ ነገር እንደሚያበዛም ሰማን፡፡ ቀጥሎም ወደ እንግሊዘኛ ተተረጎመ፡፡ ሲነበብ ማርክስ አይገባም ነው የሚሉን፡፡ በቃ፡፡ እኔ አላነበውም አልኩ፡፡ ግን ለእኛ በሚገባን ቋንቋ ከሌለ ከየት ወስደን እናነበዋለን? የምስክር ምስክር ይበቃናል፡፡ ሰውዬው የሚደነቅ ሰው ነው፡፡ ደግሞ ሥራውን ስትገምት የእርሱ ትንቢት ነው ዓለምን እንዲህ በካፒታሊዝምና በኮሚኒዝም የገመሳት፡፡ ከራሴ ጋር ስንጨዋወት ይህ ሥራ የሚነበብ ነበር፡፡ እኔ ግን እዚያ ውስጥ መግባት አልችልም ብዬ ለዳግመኛ ተውኩት፡፡ የደርጎቹ ጊዜ መጣ፡፡ አንድ ቀን የእነ መንጌ ‘ጥላን’ ካርል ማርክስ'ጋ ወሰደን፡፡ አንዱ በአማርኛ ‘ካፒታልን ተረጎምኩ’ ብሎ ለጓድ ሊቀመንበር ገፀ በረከት አቀረበላቸው፡፡ ለወቅቱ አብዮተኞች ይህ ትልቅ እሴት ያለው ስጦታ ነበር፡፡ እኛ ከያለንበት ለማረምና ለማስተካከል ተጠራን፡፡ ሥራውን ሣየው በእውነቱ ተርጓሚው ባይሞክረው ይሻል ነበር፡፡ እኛን

@Amharicbookstore



ተርጉመው ብለው ቢያዙን ይሻለን ነበር፡፡ ይህንን ስልህ የእኔ አስተያየት ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ነው፡፡ ‘ኤዲቲንትን’ ሰባት ሰዎች ሆነን ጀመርነው፡፡ ሁለቱ ብልጥ የፓርቲ አባላት ስለነበሩ ምክንያት ፈጥረው ተሰናበቱና አምስታችን ቀረን፡፡

አምን ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ነው የሰበሰቡን፡፡ እኔ ቱሪዝም ኮሚሽን ነበር የምሠራው፡፡ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ አላማከሩኝም፡፡ አልጠየቁኝም፡፡ ብቻ “ና!” ተባልኩ፤ መሄድ ነበረብኝ፡፡ የዚያን ጊዜ ባርነት ውስጥ እንዳለሁ ገባኝ፡፡ ነፃ ዜጋህንማ ትችላለህ ወይ? ፈቃደኛ ነህ ወይ? ሌላም ችግር ካለብህ በምን ዓይነት ሁኔታ አግዘንህ ትሣተፋለህ? ይሉህ ነበራ! እነ መንጌ ግን ደብዳቤ ብቻ ጣፉልን፡፡ በቃ ባርነት ነው አልን፡፡

በቀጥታ ከቤተ መንግስት ነው ደብዳቤ የደረሰን ፡፡ ከእነ መንጌ ቢሮ እልፍ ብሎ ነው የምንሰራበት፡፡ እና ብሽቅ ሥራ ነው አተረጓጎሙ፡፡ መተርጎም ሁለቱን ቋንቋና ባህል ጠንቅቀህ ስታወቅ ነው፡፡ የኛ ተርጓሚ ግን አማርኛውንም እንግሊዘኛውንም አይችልም፡፡ ለምሣሌ and so the ball rolls የሚለውን እንግሊዘኛ ‘እንዲህ ሁኔታዎች ይቀጥላሉ’ የሚለውን ሃሳብ ተርጓሚያችን ‘ኳስዋ እንደዚያው ትንከባለላለች’ ብሎ ተረጎመልን፡፡ በዚህ ዓይነት ግድፈቱ ብዙ አለፉን፡፡ እኔም ማበላሸቱን ሲያበዛብን፣ በቃ ይህንን ገፅ በአዲስ እተረጉመዋለሁ ብዬ እያያዝዋለሁ፡፡ ደግነቱ በወቅቱ ጉልበቱም አለ፣ ጫትም እቅም ነበር፡፡ ስንል ስንል የካርል ማርክስን ሥራ ወደ አማርኛው ማምጣት ቻልን፡፡ በዚህ ጊዜ እንኳንም ያስገደዱኝ አልኩ፡፡

የካርል ማርክስን ሥራ ለማንበብ ቻልኩ! በስመአብ...” ብሎ በመደነቅ ስሜት በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ከሰኮንዶች በኋላ “ማርክስ ያኔ ገንዘብ የለው፣ ምንም የለው፣ ሰውዬው ችስታ ነው፡፡ በእጁ እየጻፈ ነው ማስታወሻ የሚይዘው፡፡ ሥራውን እያጠናሁ ስሄድ፣ ይህንን ያህል ተአምረኛ ጭንቅላትም አለ?! ነው ያሰኘኝ፡፡ እንደዚህ ለተጨቆኑት የቆመ ይህ ሰው ነብይ ነው አልኩ፡፡ እንኳንም ባርነቱን ለገሱኝ አሰኘኝ፡፡

የሥራ ግንኙነታችን ጥሩ ነበር፡፡ አለቆችን ነብስ የሆነ ሰውዬ፣ አንድ እጁ ሰላላ ነው፡፡ የመንጌ አስተርጓሚ ነው፡፡ ግርማ ባሻህ ይባላል፡፡ እንደዚት ዓይነት ሰው መሰለህ! እዚህ ገሀነም ውስጥ የተሰማራ መልአክ፡፡ ለግርማ ጓዶቹ ነገሩትና “ለልፋታችሁ 20 ሺ ብር ተመድቦዋል” ብሎን ነበር፡፡ በባህሪው ግልፅ ሰው ነው፡፡ በኋላ ካዱት፡፡ ስንጋ ሊጣልልን መታሰቡ ተወራ፡፡ እሱም ቀረ፡፡ ግርማ ግን

የሚወዳት ቦታ አለች፣ ጫትም ጠጅም ያለባት፡፡ በሳምንት አንድ ቀን ቡድኑ ተያይዘን ሄደን በእርሱ ግብዣ እንዝናናለን፡፡

እሱስ የኢሠፓ አባልና የጓድ መንግስቱ አስተርጓሚ ቢሆንም ማንንም አይፈራም፡፡ ምንም አይፈራም፡፡ ከሰው ጋር ይደባለቃል፡፡ እንቁልልጭ ያሉን ሽልማት ሁሉ ቀርቶብን ሥራው ተጠናቀቀ፤ ዕድሜ ለማርማ በሻህ፡፡ ልፋታችን ዋጋ ተሰጥቶት እኔ ካለሁበት መሥሪያ ቤት ወደ ኩራዝ አሣታሚ ድርጅት ተዛወርኩ፡፡ በደሞዜ ላይ 200 ብር እድገት ተሰጠኝ፡፡ ይህም የእንግሊዝኛን አባባል ያስታውሰኛል፡፡ ባርነቴ የእግዜር ግራ እጅ ነበር፡፡ ብንፈልግ ደሞ አብዮታውያኑም በግራ እጅ ቡጢ ነበር መፈክሮቻቸውን የሚነዙብን 'እናሸንፋለን! ሳይንሳዊ ሐቅ ነው አንጠራጠርም! ወደፊት!' ይሉናል፡፡

እኛ ደሞ ውስጥ ውስጡን፣ 'ያልጠረጠረ ተመነጠረ' እንላለን፡፡ ይኸውልህ፣ እንደ ማንኛውም ወንጌል ነው የማርክስ ወንጌል፡፡ ለድሆች ደህንነት የቆመ ነው፡፡ ከኢየሱስ ወንጌል የሚለየው በአንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ገነትን እዚሁ መሬት ላይ እንዘረጋለን ይላል ማርክስ፡፡ ሠራተኛው መደብ ያሸንፋል ነው ትንቢቱ፡፡ አብዮታዊ ፓርቲ ለጭቁኑ አገልግሎት ነው የሚዋቀረው፡፡

ፍልስፍናው በተግባር ሊተረጎም ካልቻለ የማይቻል ቢሆን እኮ ነው፣ እንጂ ማርክስ ሐሳቡ በጣም ልክ ነበር፡፡ ሐሳቡን እንይ፡፡ 'ለሁሉም እንደ ችሎታው፣ ለሁሉም እንደሚያስፈልገው' ነው የሚለን፡፡ ኅብረተሰብ እንደ አንድ ሰው ሆነ ማለት ነው፡፡ ሀብቱ በሙሉ የጋራ ነው፡፡ ለማንም አናደላም፡፡ ድል ስናደርግ መደብ አይኖርም፣ ወገን አይኖርም፡፡ እንደዚያ ነው ትንቢቱ፡፡ ለእኔ ሕልም ነው፡፡ ግን ሰው ያለሕልም አይኖርም፡፡

እኔ ቀርቶ እኛ ሆኗል፤ በማለት ማርክሲስት ነን የሚሉ ፓርቲ ዎች አዲስ ገዢ መደብ ሆኑ፡፡ ምንም አልተለወጠም፡፡ እነሱም የሚፈልጉትን ያገኛሉ፣ ሕዝቡም ለጥቂቱ ነገር ይሰለፋል፡፡ 'ይበልጥ ሲለወጥ ይበልጥ ያው ነው' ይሉናል ፈረንሳይ፡፡

የአሜሪካ ሠራተኞች ግን ማርክሲዝምን በሥራ ላይ አዋሉት፡፡ ተደራጁ፣ ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው እንዲከበር በሥራ ማቆም አድማ ጠየቁ፣ የሥራ ሰዓታቸው በቀን 8 ሰዓት ብቻ እንዲሆን ታገሉና አሸነፉ፡፡ ዝቅተኛው የቀን ሠራተኛ ደመወዙ በቀን ቢያንስ 10 ዶላር እንዲሆን፣ ሠራተኛው በጥፋት ካልሆነ ከሥራው ቢሰናበት ካሣ እንዲያገኝ የተደረገው በአሜሪካን አገር ነው፡፡ 'በእስታንዳ ማርክሲዝምን በደንብ ተጠቀሙበት' ብሎ ማቀና ተቀድቶ ፊቱ የተቀመጠ ሲኒ ቡና አንስቶ ፉት እያለ በሃሳብ ጭልጥ አለ፡፡በዚህ ጊዜ ስኔ ቤት ደርሰን ምሣችንን በልተን ዘና ስያልን ነበር፡፡

@Amharicbookstore



"እንዳልከው ካፒታል ሦስት ቅፅ ነው፡፡ ሁሉቱን ቅፅ ሠርተን ጨረስን፡፡ በዚያን ወቅት 1ሺ500 ብር ጉደማ መሰለኝ አብረውኝ ለነበሩት ሰዎች የሰጧቸው፡፡ ለእኔ ብቻ አልከፈሉኝም፡፡" ለምን? እኔ የፓርቲው አባል አልነበርኩማ!

ካፒታልን በማስተካከል ስኖር ከሰዎቹ ጋር ተግባብተን ነበር፡፡ ስለዚህ የፓርቲያቸው አባል እንድሆን ጠየቁኝ፡፡ እኔ ደግሞ የፓርቲው አባል ብሆን ጥሩ ነበር፡፡ እኔ ግን 'ኤቴይስት' አይደለሁም፣ በእግዚአብሔር አምናለሁ፡፡ ፓርቲው ደግሞ እግዚአብሔር የለም ይላል፡፡ ስለዚህ እኔ ለመንግሥት በመሥራት ማገልገል እንጂ በሃይማኖቴ ምክንያት የፓርቲው አባል ልሆን የተፈቀደልኝ አይደለሁም አልኳቸው፣ ተውኝ፡፡

የማሌ ጥናት ተብሎ በየመሥሪያ ቤቱ የውይይት ክበብ ስብሰባ ይካሄድ ነበር፡፡ በወቅቱ አንተ እንድትሳተፍ ተጠይቀህ አታውቅም? ይካሄድ ነበር፡፡ በወቅቱ... ነው ያልከኝ? ምንድነው ማሌ? የማርክሲስት ሌኒንስት ፍልስፍና ውይይት?

በፍጹም፡፡ እነሱም አያስገድዱኝም፡፡ እኔም አልቀላቀላቸውም" ለረጂም ጊዜ በእጁ መዳፍ አገጩን አንተርሶ ሲተክዝ ቆየና "ሰውዬው ካርል ማርክስ አሪፍ ፈላስፋ ነበር፡፡ ሰዎቹ ግን ሳይገባቸው ፈተፈቱት፡፡ ፍትፈታውንም ውይይት ክበብ አሉት፡፡

"የቤተክህነት ሰዎች መጥተው ቤተ ክርስቲያንን አገልግል ቢሉኝ?" እየሣቀ "የእኔን ተፈጥሮ ልብ በል፡፡ አንድ 'Formula' ተከትሎ ያችኑ መደጋገም ደስ አይለኝም፡፡ በክርስትና፣ በእስልምና፣ በፖለቲካ ፓርቲም እያልክ ብታጠናቸው አማኞቻቸውን ደንግገው የሚይዙበት ሕግጋት አላቸው፡፡ ያ ደግሞ 'ሼል' ሆኖ እንደ ዕንቁላል ቅርፊት ሌላን የምታይበትን ዓይን ይጋርድሃል፡፡ ስለዚህ በምንም ዓይነት የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት ድርጅት ተከታይ መሆን አልፈልግም" አለኝና እጆቹን በትሕትና እያሻሸ በምናብ የፈጠራቸውን አበው ዞር ብሎ እያየ "አባቶቼ ልክ ናችሁ፡፡ አያት ቅድመ አያቶቼ እስከ ምንጅላት ቅንጅላቴ ድረስ አስራ አራት ዘሮቼ ቀሳውስት ነበሩ፡፡ ቤተክህነትን ማገልገል ከአማኞቿ የሚጠበቅ ነው፡፡ እናንተም ከልባችሁ ቤተክህነቷን እያገለገላችኋት ነው፡፡ ግን እኔም እንደናንተ እንዳላገለግል 'ኤቴይስት' ነኝ እላቸዋለሁ፡፡

***

## ፴፩

# አይኔን አበራልኝ

ፍሮይድ ወደራሱ ውስጥ! ውስጥ! ገብቶ የመረመረ ተጓምረኛ ‘ሱፐር ጂኒየስ’ የሆነ የሥነ ልቦና ሊቅ ነበር፡፡ በሌላ አባባል ለእኔ የውስጣችንን ገልብጠ የሚያሳይ ማለት ነው፡፡ በአእምሮአችን ውስጥ! ውስጥ! ውስጥ ሔዶ የሳቅም፣ የፍቅርም፣ የተአምራትም የመሆን ሁኔታዎች ያሳይሃል፡፡ በር መዝጋትም ታይበታለህ፡፡ ሙሉ መሆን ድሮ ቀረ” አለና ሳቀ፡፡

እንዲያውም ዓይኔን ያበራልኝ ሲግሞንድ ፍሮይድ ነው፡፡ ልክ ብላታ ዴሬሳ በሕይወት ውስጥ ይህንን የአገራችንን አኗኗር ባሕሉን ታሪኩን እንዳሣዩኝ፣ ፍሮይድም የውጪውን ዓለም ውስጣዊ ማንነትን አሳይቶኛል፡፡ እንዲያውም ከእርሱ እኩል የሰውን ነብስ ኅልጉሎ ያሳየኝ ያለ አይመስለኝም፤ ኢየሱስ ካልሆነ...

ይኼውልህ ሲግሞንድ ፍሮይድ የቪየና የኦስትሪያ ዋና ከተማ ልጅ ነው፡፡ እዚያ ነው ያደገው፡፡ ወላጆቹ ይሁዲዎች ናቸው፡፡ ሀብታሞች ናቸው፡፡ በሕይወቱ ምንም ዓይነት ችግር ሲያልፍም አልነካካውም፡፡ ስለ እራሱ ብዙ ጊዜ የሚያጫውተን እራሱ ነበር፡፡ ልጅ ሆኖ ይጋጠመውን ሲያጫውተን፣ “በልጅነቴ አንድ ጊዜ ለእናቴ እንዴት ነው እግዚአብሔር ከጭቃ ሰውን ሠራ የሚባለው? ይህ ልክ አይመስለኝም” አልኳት፡፡

በዚህን ጊዜ እናቴ “እንደዚያ ነው የመሰለህ? በል እጄን ተመልከት!” አለችኝ፡፡ ከዚያም መዳፍዋን አፋትጋ እድፍ እየተንከባለለ ወጣ፡፡ “አየኸ?” አለችና በርግጥም የሰው ልጅ ከጭቃ መሠራቱን አሣመነችኝ፡፡ ይህች ናት እንግዲህ ለሲግሞንድ ፍሮይድ በልጅ ሕሊና የምርምርና የግኝት ውጤት የሆነችው፡፡

ልብ አድርግ፣ ፍሮይድ ይሁዲ ነው፡፡ መኅርመስ በጀመረበት ዘመን የሚያየው እውነት አለ፡፡ በወቅቱ አይሁድን መናቅ፣ ማንቋሸሽ ነው! ክርስቶስን የሰቀሉ እየተባሉ የመዋረድ ዕዳ አለባቸው፡፡ ‘አንቲ-ሴማቲዝም’ የሚሉት ጣጣ፡፡ ለምሣሌ ፍሮይድ በደረሰበት ጊዜ አዛውንት አይሁድ መንገድ ሲሄድ የክርስቲያን ዘር የሆኑ ሕፃናት ድንጋይ አንስተው “አንተ ሽሜ ጉጉ! እጅ

@Amharicbookstore



አትነሣም?” ሲሉ ያስፈራሩታል፡፡ አዛውንትም ለጥ ብሎ ለሕፃናቱ እጅ ነስቶ ያልፋል፡፡ ይኼንን ያህል ነው አይሁድነት የተገፋው፡፡ በዚህ ወቅት ፍሮይድ በይሁዲነቱ አነስተኛነት ወይም ጎደሎነት አይሰማውም፡፡ የወላጆቹ መልካም አስተዳደግ ስላለው ጥሩ የሥነ ልቦናና የግብረገብ ስንቅ አለው፡፡ በዚህ ላይ አይሁድና ሌላው ሕዝብ ያላቸውን ልዩነት አሣምሮ ያውቃል፡፡

አስራ አምስት፣ አስራ ስድስት ዓመት እንደሆነው አባቱ ቀልድ ነገረው፡፡ ቀልዱ በተነገረው ጊዜ አልሳቀም፡፡ ተቆጥቶ ሄደ፡፡ እያደገ፣ እየበሰለ ሲሄድ በጣም ከሚወዳቸው ሐቅን በጥልቀት ከያዙ ውብ ቀልዶች መካከል አንዷ ሆነችለት፡፡

ቀልዷን ላጫውትህ፡፡ ‘ኦሪየንት ኤክስፕሬስ’ የተባለ የታወቀ የባቡር መስመር አለ፡፡ በዚያን ጊዜ እርሱ ነው ትልቁ የሕዝብ መጓጓዣ መስመር፡፡ በወቅቱ በኦሪየንት ኤክስፕሬስ ተጉዣለሁ፣ ማለት ራሱ የሚያኮራ ነበር፡፡ በኦሪየንት ኤክስፕሬስ ከፖርቱጋል ተጀምርና በስፔን አርገህ፣ በኢጣሊያ፣ በፈረንሣይ፣ በሌሎቹ የአውሮፓ አገሮች አቋራርጠህ ሩሲያ ትገባና ሳይቤሪያ ድረስ ትጓዛለህ፡፡ ያዝክ?

ይኼውልህ ባቡሩ ተነስቷል፡፡ በዚህ ጉዞው ባቡሩ በየጣቢያው ይቆማል፡፡ ተቆጣጣሪዎቹ ይገባሉ፡፡ ተሳፋሪዎቹን ትኬታቸውን እንዲያሳዩ ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ መሐል አንድ ሰው ጋ ደረሰ ተቆጣጣሪው፡፡ ተሣፋሪው ይሁዲ ነው፡፡

“ትኬት ይዘዋል?”

“አልያዝኩም” ይላል ይሁዲው፡፡

“እንግዲያው ይክፈሉ፡፡”

“ገንዘብ አልያዝኩም፡፡”

“እ? ገንዘብ አልያዝኩም!? አንት ቆሻሻ ይሁዲ!” ብሎ በቦክስና በጥፊ ያጣድፈውና ትቶት ይሄዳል፡፡

እሚቀጥለው ጣቢያ ወራጅ ይወርዳል፡፡ ተሳፋሪም ይጫናል፡፡ እዚያም ሌላ ተቆጣጣሪ ይመጣል፡፡ ሌሎቹን ሁሉ ጠይቆ ይሁዲውን ይጠይቀዋል፡፡

“አልያዝኩም” ይላል ይሁዲ፡፡

“ይክፈሉ፡፡”

“ገንዘብ የለኝም፡፡”

“ኧረ!” በጥፊና በቦክስ አገላብጦት “ንፍጣም ይሁዲ! ሁለተኛ እንዳይለምድህ” ብሎት ትቶት ይሔዳል፡፡ እንዲህ እየተደበደበ፣ እየቻለ ብዙ ጣቢያዎች አለፉ፡፡ ረጂም ርቀትም ሄዱ፡፡ አጠገቡ ተቀምጦ ሁሉንም ድርጊት ሲያይ የነበረ ሰው ዘሩ አይሁድ ያልሆነ

ገርሞት "አንተ ሰው፣ ይህን ተደጋጋሚ ድብደባ እስከ የት ልትችለው ነው?" ሲል ጠየቀው።
"ሰውነቴ እስከቻለ ድረስ" ሲል መለሰ ይሁዲው።
አየህ፣ ይህችን ፍሮይድ በኋላ አድጎ በስሎ ሲያብሰለስል፣ ሲያውጠነጥናት፣ ለካ የቀልዱ ይሁዲ እስራኤል ራሷ ናት። እነፋርስ ይመጣሉ ይደበድቧታል።እነ ሮማ። አሁንም እነ ሎርድ እንግሊዝ። እንደ ባቡር ጣቢያዎቹ ቲኬት ቆራጮች እየተከታተሉ የዓለም ገዢ ነን ባዮች ሲመጡም ያንን ሁሉ ወገራ ችላ ነው እዚህ የደረሰችው።

ሲግሞንድ ፍሮይድ በዕድሜ ማወቅ ሲጀምር ሕልሞች በጣም ስሜት ይሰጡታል። እና ምን ያደርጋል? ሊተኛ ሲል ደብተሩን፣ እርሳሱን እራስጌው አጠገብ ያስቀምጣል። መብራት ያጠፋና 'ሕልም አያለሁ፣ ሕልም አያለሁ!' እያለ ለራሱ ይነግራል 'ህልሜን አስታውሰዋለሁ፣ አስታውሰዋለሁ' እያለ ይተኛል። እንደነቃ የሚያስታውሰውን በሙሉ ይጽፈዋል። እንዲህ እያደረገ ለብዙ ጊዜያት ፃፈ። በኋላ የወንድሞቹን፣ የአባቱን፣ የእናቱን ምን ህልም አየህ? እያለ መመርመር ጀመረ። ከሌሎች ጋር እያስተያየ የመረመረውን The Interpretation of Dreams የተባለው መጽሐፉን፣ ከዓለም ተገልሎ ብዙ ጊዜያት ከጣረበት በኋላ፣ ለአንባቢያኑ ገፀ በረከት ሰጠ።

አውሮፓውያን ከፍሮይድ በፊት ስለሕልም የነበራቸው ዕውቀት ልክ እንደኛ አገር ነበር። ከእርሱ በፊት ሕልም መልዕክት ነው። ሊገባህም ላይገባህም ይችላል። እኛ'ጋ ርቦህ ብታይ ትጠግባለህ፣ ቀይ ሴት ሰናይ እምዬ ማርያም ነች፣ እያልን እንደምንፈታው ነበር የእነርሱም ባሕል። ይኼ የሚያሳይህ በእኛ እምነት ሕልም ከውጪ ነው። በፍሮይድ ምርምር ግን ሕልም ከውስጥ ነው። ከእኛ ነው የሚወጣው። የማየው ሕልም እንቅልፍ ውስጥ ነው። እንግዲህ ማነው እንቅልፍ? ማለት እንጀምራለና።

እንቅልፍ መቼስ የደከመ ገላችንን የሚያድስልን ፀጋ ነው። ተኝተን ስንነሣ በጤና ተሞልተን፣ ታድሰን ነው የምንነሣው። ለመታደስ መተኛት አለብህ። ሰውነትህም መጠበቅ አለበት። ምክንያቱም በተፈጥሮ ወንድም፣ እህት፣ አጎት ወላጆች የምትላቸው ነቅተህ አብረህ የምትኖራቸው የኅብረተሰብ አካል ያደርጉሃል እንጂ፣ በእንቅልፍ ውስጥ ብቸኛ ነህ። ብቻህን ስለሆንክ ዓለም ደግሞ አደገኛ ነው። ስለዚህ ዓይንህን ብትጨፍንም፣ ጆሮህ ክፍት ነው። አንድ ነገር ኳ! ቢል ትነቃለህ።

@Amharicbookstore



ምንም ላትተኛ ነው። አይደል? አንተ ግን መተኛት ያስፈልግሃል። እዚህ'ጋ ሕልም ይመጣል። ሕልም ከውስጥ ነው ብለናል። ሁለት ሥራ ነው ያለው። አንዱ እንቅልፍን እንድትተኛ ማረጋገጥ ነው ዋናው። ስለዚህ በጆሮህ የመጣው ድምፅ እያባነነህ ችግር እንዳያመጣ መፍትሔ ውስጥህ ይፈጠራል። ለምሣሌ ሰሞኑን ስለቴዎድሮስ አውርተናል። ታዲያ ተኝተህ አንድ ድምፅ ከውጪ ዷ! ሲል አንተ የምትሰማው ድምፅ ሲባስቶፖል መድፉ ሲተኮስ ነው። ጦርነቱንም እያየኸው ነው። ሰውነትህም እንቅልፉን ይቀጥላል። ይኸ አንደኛው የሕልም ተግባር ነው።
ሁለተኛውን እንይ። ይኼውልህ፣ ሕዝብ 'ጂኒየስ' ነው። የአበሻ 'ጂኒየስ' አንዷ ፍሬ ምን ትላለች? 'ድሀ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ ንጣት ይገለው ነበር' አትልም?
እሷ ነች የፍሮይድ ሕግ። ሕልማችን Wish fulfillment (የምኞትህን ማግኘት) ነው ሁለተኛው ሥራው። ምክንያቱም ምኞት አለ። እኔ ደግሞ የምመኘውን ሁልጊዜ አላገኘውም። በውን ባላገኘውም ሌላው ቢቀር በሕልሜ አገኘዋለሁ ማለት ነው። እዚህ ላይ ነው ትኩረት የምናደርገው። የምንነጋገርበትን ጭብጥ ለማስቀመጥ አሁን ነው 'ኢድ፣ ኢጎ፣ ሱፐር-ኢጎ' የምንመጣው።
ፍሮይድ ምንድነው ያደረገው? ፍተሻ ነው። የሰው ልጅ ሔዶ የማያውቅበት ቦታ የሄዱ አይደሉም 'ኤክስፕሎረርስ' የሚባሉት? እነ ኮሎምበስ፣ ማርኮ ፖሎ ባሕር ለባሕር እና የብስ ለየብስ አሰሱ። ኒል አርምስትሮንግ ወደ ጨረቃ ወጣ። ፍሮይድ ወደ አእምሮው ውስጥ ነው የጠለቀው። ከእርሱ በፊት ደፍሮ የገባ የለም። ውስጥ፣ ውስጥ ጠልቆ፣ ያለውን መርምሮ፣ ራሱን የተቀበለ ነው። እዚህች ላይ ትንሽ ትንታኔ 'ባክግራውንድ' ያስፈልግሃል።

መጀመሪያ ፍሮይድ ያጠናው ሕክምና ነው። በጣም ጎበዝ ተማሪ ነበር። ለዲግሪው ኢል የሚባል ዓሣ ነው ያጠናው። ኢልን ፍሮይድ ከማጥናቱ በፊት ብልቱ የቱ'ጋ እንዳለ አይታወቅም። ሳይንሱ ኢልን መርምሮ ባይደርስበትም እነርሱ ግን እየተራቡ ነው። ይኼንንም ፈትሾ ያገኘው ሲግሞንድ ፍሮይድ ነው። 'Brilliant' አይደለም? እዚያው በተማረበት ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነ።
ወጣት ሳለ የመጀመሪያው ዲግሪውን እንደተቀበለ ፓሪስ ውስጥ አንድ የሙያ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ትልቅ የእብዶች ሐኪም ቤት አለ። ከዚህ በፊት ያበደ ሰው ሁሉ ይደበደባል፣ ውጣ! ተናገር፣ ልቀቅ! ስቃይ ነው። የፓሪሱ ሰውዬ ግን ዕብዶችን በሆስፒታል ሰብስቦ መረመራቸው። መደብደባቸውን አስቀረ። የተሻለ ጤንነት

ያላቸውን ለብቻቸው አስቀመጡ፡፡ የባሰባቸውን ሳይመቱ ታስረው እንዲረዱ አደረገ፡፡ ፍሮይድ ወደ ፓሪስ ሄዶ ከዓመት በላይ በመቀመጥ ከዚህ ሰውዬ ብዙ ተማረ፡፡ የሰውዬውን ስም አውቀው ነበር፡፡ ዘነጋሁት፡፡ ይኼውልህ እዚህ ላይ ነው ዕድሜ አተላ የምትለው" ብሎ ቅር አለውና "አ! ሻርኮ (Charcot) ነው" አለና ፈገግ ብሎ ትንታኔውን ቀጠለ፡፡

ፍሮይድ ሲመለስ ተለውጦ መጣ፡፡ የፍሮይድ ፕሮፌሰር ደግሞ በዚህ በአእምሮ ሕመም ላይ የማጥናት ፍላጎቱ አላቸው፡፡ 'ኢንተርን ሺፕ' ይባላል፣ ጨርሷል ዲግሪውንም አግኝቷል፡፡ ሲለማመድ ፕሮፌሰሩ አብረውት እየዞሩ፣ እየጠየቀ ዕብዶችን ያጠናል፡፡ ከጥንት ጀምሮ ታዲያ ዕብድና ጤነኛን ሁለቱን እያነፃፀረ ሲመረምር ብዙ ልዩነት የላቸውም፡፡ ልዩነቱ በጣም ትንሽ ነው፡፡

ፍሮይድ ወደ ውስጥ እየገባ፣ ሕልሞቹን እየጻፈ፣ እየመረመረ ቀጠለ፡፡ አንድ ቦታ ላይ ደርሶም እንዲህ ይመስለናል፡፡ ወደ አእምሮ ውስጥ ስንገባ ነብሳችን እንደ ስጋችን እያደገ ነው የሚሔደው፣ አይደል? ስንወለድ ምንድን ነን? መደሰት ብቻ ነው የምናውቀው፣ አይደል? መቆሸሻችንን እንኳን አናውቅም፡፡ አሁን ምንጊዜም መደሰትን የሚፈልገውን 'ኢድን' ሆንክ ማለት ነው፡፡ እና ሙቀት ሲበዛብህ፣ ሽንት ሲመጣብህ፣ በፍፁም ህመም (ፔይን) አትወድም፣ መደሰት (ፕሌዠር) ብቻ! ጭንቀትህን አትፈልግም፡ ይዘሃል?

ኢድ እውነታን፣ ምናብን (ኢማጂኔሽን) ልቦለድን አይለይም፡፡ ያው ነው፡፡ በህልሙ የበላውም፣ በውኑ የበላውም ለኢድ እኩል ነው፡፡ ልብ አርግ፣ ኢድ አይደለም ህልም የሚያየው፣ ሰውዬው ነው፡፡ አሁን ሰውዬውን በኢድ፣ በኢጎና በሱፐር ኢጎ ለሦስት ከፋፍለን ነው የምናወጋው፡፡

ኢድ ሆነን አንቀርም፡፡ 'ኢጎ' ደግሞ እንሆናለን፡፡ ኢጎ ደግሞ እውነታ (ሪያሊቲ) ጋር ነው የሚተዋወቀው፡፡ ኢድ ሁኜ እሳቱ ደስ ብሎኝ ስጨብጠው፣ ሲፈጀኝ ኢጎ ተነሣ፡፡ ሁለተኛ አልጨብጣትም፡፡ ኢድና ኢጎ በደንብ ይግባባሉ፡፡ ሁለቱም ግብረ ገብ (ሞራሊቲ) አያውቁም፣ ትክክልና ስህተት የሚባል ነገር የለም እነሱ ጋ፡፡ ቋንቋ፣ ከሰው ጋር መግባባት፣ ሥራ፣ ኑሮ የኢጎ ኃላፊነት ነው፡፡ ኢጎ ሁልጊዜ ኢድን ማገልገል ነው ሥራው፡፡ ኢጎ እያደገ ይሄዳል፡፡ አሁን ኢጎና ኢድ ብቻቸውን ቢሆኑ ባንተ ዕድሜ ደርሰዋል እንበል፡፡ ታናሽ እህትህ አለች፤ አሥራ ሦስት አመቷ ነው፡፡ ደርሳለች፡፡ ኢድ ሲያያት ምንም አይመስለው፡፡ ሴት መሆኗን ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ ኢጎም እህትህ ናት እኮ አይልህም፡፡ መጀመሪያ እሷ እሺ ትላለች ወይ? እሺ ካለችስ ሳይታወቅ ምስጢር ሆኖ ይቀራል?



የሚታወቅ ከሆነ አያስፈልግም፡፡ የማይነቃብህ ከሆነ ለምን አታደርገውም? ግን ብታረግዝ ብንስ? እንዳታረግዝስ ምን ጥንቃቄ እንወስዳለን? ይልሃል ኢጎ፡፡ ትክክሉንና የተሳሳተውን እንዲህ ይመረምረዋል፡፡

ሱፐር ኢጎ ይመጣል፡፡ እስካሁን ከግለሰብ ጋር ነን፡፡ እኔና እኔ እውነታን እንደፈለግን እንሸውዳታለን፡፡ ሱፐር ኢጎ ነው ኅብረተሰብን የሚወክልልኝ፡፡ ምክንያቱም የማኅበረሰባችን አባል ነኝ፡፡ ከነርሱ ጋር ካልተግባባሁ መኖር አልችልም፡፡ ሱፐር ኢጎ ወደ ሞራሊቲ (ግብረገብ) ይወስደናል፡፡ በምሣሌ እናስደግፍና እንመርምር፡፡

ይኸውልህ፣ አንተ ገና የሦስት ዓመት ልጅ ሆነህ'ንደ! "ልጆቹ ንፍጣም እንዳይሉህ፣ በል በደንብ አፍንጫህን ጥረግ" ስትባል ቶሎ አፍንጫህን ትጠርጋለህ፡፡ ይህቺን እንድታከናውን ያስደረገችህ የሕሊናህ ሱፐር ኢጎ ናት፡፡ በግብረገብ የመጣ፣ ከማኅበረሰብ ጋር የምታደርገው ሁሉ የሱፐር ኢጎ ኃላፊነት ነው፡፡

ስንተኛ የሚጠብቀን? ይኼ ራስህ እንብበህ የምታጠናው ነገር ነው፡፡ እስካሁን እኔ አንብቤ የደረስኩበት ነገር የለም፡፡ ራሳችን ግን ልንተነትናቸው እንችላለን፡፡ ኢድ እንዳስተዋልነው የደስታው ክፍል ነው፡፡ ጊዜ፣ ሁኔታ አያስገድዱትም፡፡ ኢጎ ከእውነታ ጋር የምናደርገውን ግንኙነት ያስተካክልልናል ተመችቶን እንድንኖር፡፡ ያሰኘህን ማድረግ፣ ደስ ያለህን መፈፀም መብትህ ነው፡፡ ሱፐር ኢጎ ሲመጣ ግን የማኅበረሰብን ሕግና ደንብ ይዞብህ ይመጣል፡፡

ተራራ መውጣት አስተማሪዎችም አሉ፡፡ መተዳደሪያቸው እሱ ሥራ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል አንተን አውሮፓ የሚገኘውን አልፕስ ተራራን አስወጣሃለሁ እያለ ቃል የሚገባልህና የሚያለማምድህ ሰውዬ አንድ ቀን ትንሽ ኩረብታ ሲወጣ አዳልጦት ወድቆ ሲሞት ታያለህ፡፡

ምንድነው የገደለው? ይህ የተራራ መውጣት ፕሮፌሰር ማኅበረሰብ የከለከለውን አንድ ነውር ነገር አድርጓል፡፡ አየህ፣ ኢድ አምጣ አለው፣ ኢጎ እናስተካክላለን ይለዋል፡፡ ሱፐር ኢጎ በዚያን ጊዜ ምንም መደመጥ አልቻለም፡፡ ጊዜውን ጠብቆ ራሱን በማሰናበት ይፈርድና ይሰዋል፡፡

ምሳሌዎችንን ተጨባጭ እናድርገው፡፡ ደራሲው ኧርነስት ሄሚንግዌይ የታወቀ አዳኝ ነው፡፡ እርሱ በሕይወት በነበረ ዘመን አምስት ስድስት ሆነው አፍሪካ ውስጥ ትላልቅ የዱር እንስሳትን ለማደን ይጓዙ ነበር፡፡ የተሣካለት ዓሣ አጥማጅም ነበር:: በራሱ ላይ

@Amharicbookstore

ተኩሶ ነው የሞተው፡፡ ዕድሜው ከ60 እስከ 61 ሆኖታል፡፡ እንግዲህ አስበው፡፡ ያለውን የሕይወት ልምድ፣ እውቀት፣ ብስለት ጋር አያይዘህ አብሰልስል፡፡ የጦር መሣሪያን የሚያውቀው ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው፡፡ ያንን ሁሉ አገር እስከ ከትላልቅ የዱር እንስሳት ጋር የተፋለመ ሰው እንዴት ጠመንጃ ባርቆበት ሞተ? ይህንን በሱፐር ኢጎም እየተነተንን ልንሄድ እንችላለን፡፡ በልምድ ደግሞ ስናየው ሄሚንግዌይ በቃኝ ብሎስ እንደሆን? ሱፐር ኢጎ ብቻ አይደለም ራሳችንን እንድንገል የሚያደርገን፣ በራሳችንም በቃኝ ማለት እንችላለን፡፡ በነገራችን ላይ፣ ሄሚንግዌይ አባቱ የሕክምና ዶክተር ነበሩ፡፡ እንደ እርሱው በ61 ዓመታቸው ነው ራሳቸውን ያሰናበቱት፡፡ ፐፍፍ..." በረጅሙ ተነፈሰ፡፡

ፍሮይድ ሲፈጠር 'ጂኒዬስ' መሆኑን አትርሣ፡፡ ይህ ጂኒዬስነት ለማንኛችንም የሚደርሰን ዕጣ ነው፡፡ ከጂኒዬስ ተፈጥሮ ጋር ባሕል፣ ቤተሰብ፣ ዕውቀቱን የሚያቀብልህ ማኅበረሰብ ሲዳመር ፍሮይድን ትሆናለህ፡፡

እ! የኔ አቦይም ሆኑ ወለላይ ጤነኛ ናቸው፡፡ በሥነ ልቦና በኩል ችግር የለብኝም፡፡ ነገር ግን ድህነቱ በጣም ይበዛል፡፡ ፍሮይድ ሲነግረን ወንድ ልጅ እናቱን ነው የሚወደው፡፡ ሴት ልጅ ደግሞ አባቷን ነው፡፡ ለወደፊቱ ሕይወታቸው ሁሉቱም ከወላጆቻቸው ጋር የሚኖራቸው የመዋደድ ግንኙነት ያስፈልጋቸዋል፡፡ እንደ ቴአትር ልምምድ አርገህ አስበው፡፡ የተዛባውን ስላከመ እኮ ነው ፍሮይድ ዝነኛ የሆነው፡፡ እንቀጥል፡፡

እያብሰለሰልኩ ነው፡፡ ፍሮይድን ዓለም ነው ዶክተር የሚለው እንጂ፣ እርሱ ሁሉንም እየፈተሸ ነው የሥነ ልቦና ሊቅ የሆነው፡፡ ታማሚውን እየነገረን ምርምሩን ይቀጥላል፡፡ በሽተኛውን ያመጣና ያጋድመዋል፡፡ 'አናቶሚን' ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ያመቻቸዋል፡፡ የበሽተኛውንም ታሪክ ይፅፈዋል፡፡ በሽታ ምረጥ፡፡

"ብቻህን የማውራት ችግር አለብህ?" አውራ፡፡ እኔ ይህንን ወሬህን እጽፍልሃለሁ፡፡ እየህ ይህ ችግር የሚከሰተው ከልጅነት ጀምሮ ነበር፡፡ ስለዚህ እስኪ ወደ ልጅነትህ ተመለስ፡፡ ምን ትዝ ይልሃል? ካሰኘህ ተናገር፤ አለበለዛም ዝም ብለህ ተዝናና ይልሃል፡፡ የንስሀ አባት ማለት ነው፡፡ የንስሀ አባትህን "አባ ከአልጋ ላይ ወድቄአለሁ፣ ትላለህ፡" "እግዚአብሔር ይፍታህ" ይሉሃል፡፡ ነብስህ ታምናለች፡፡ ይኼንን በማድረግህ ሕሊናህ ንፁህ ይሆናል፡፡ ይህ ከቀረ በኋላ ነው እነ ፍሮይድ የመጡት፡፡ ምን እያልን ነበር?

እ!የት ደረስን መሰለህ፡፡ ቂስ ቀረ፣ ሥነ ልቦና አዋቂ ሕመምተኛውን ያናዝዘው ጀመረ፡፡ አሜሪካን አገር የሥነ ልቦና አዋቂ



(ሳይኪያትሪስት) አስፈላጊ ሆነ 'ሳይኪያትሪስት' እዚያ ሀብታም ነው፡፡ በሰዓት የሚያስከፍለው ብዙ ገንዘብ ነው፡፡ ምናልባት የቀዶ ጥገና ባለሙያ ሊስተካከለው ይችል ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አሜሪካን አገር ሥጋ ይጠግባል፡፡ ነብስ ግን በሁለት በሽታ ትሰቃያለች፡፡ እዚህ የእኔ አባት ያንተን አባት ያሸንፋል አይደል የሚባለው፤ እዚያ ግን ልጆች የኔ ሳይኪያትሪስት ያንተን ሳይኪያትሪስት ያከማል የሚሉበት ደረጃ ላይ ተደረሰ፡፡

አዎን፡፡ በተደጋጋሚ እያናዘዘ ያከመዋል፡፡ ከዚያ ወዲያም እንዲህ ያደርጋል የምልህ የለኝም፡፡ ምክንያቱም ፍሮይድ እንዲህ አድርጎ አክሞኛል ያለ ሰው በአካልም ሆነ በጽሑፍ አልገጠመኝም፡፡ ግን በዚህ ረገድ ጥልቅ በሆነ መልኩ መመርመሩን ልመሰክርልህ እችላለሁ፡፡

በእነርሱ ባህል ያመንከበትን ትጽፋለህ፡፡ ኑዛዜህንም ያከብሩልሃል፡፡ ይህ ማንም የማይነካው እኔ ከሞትኩ ከ50 ዓመት በኋላ የሚከፈት ብለህ ታሽጋለህ፡፡ ይህ ደግሞ ለአገሌ ቤተ መጻሕፍት የሚሰጥ፣ ከአሥር ዓመት በኋላ የሚጠቀሙበት ብለህ ትሰጣለህ፡፡ እናም ያልከው እውነት ሳይሆን አይቀርም፡፡ የዘመኑ አስተሳሰብ ስላልደረሰባቸው ታትመው እኛ ጋ ያልደረሱ ምርምሮች ይኖሩት ይሆናል፡፡

በሕይወት ያለው ሲግሞንድ ፍሮይድ እና ኮናን ዶይል የፈጠረው ዓለም እንደ ሕያው ገፀ ባሕሪ የሚያየው ሼርሎክ ሆምዝ የተጫጨሙቱትን እንዴት አረፍ ፊልም ለቅምሻ ላጫውትህ፡፡ ታሪኩ ሲጀምር ሼርሎክ ሆምዝ ትንሽ አብዶ ነው፡፡ ዶክተር ዋትሰን የሚባል ደባልና የልብ ጓደኛው አለ፡፡ ዶክተር ፍሮይድ እንዲመረምረው ወደ ቪየና ይዞት ይመጣል፡፡ ወደ ቪየና እንሂድ ሳይለው፣ የሀሰት ወንጀል ፈጥሮ ምልክቶች እየተወ፣ ሼርሎክ ሆምዝ እየመረመረ ምልክቶቹን እየተከተለ ተያየዘው ተጓዙ፡፡ ቪየና ደረሱ፡፡

ፍሮይድና ሼርሎክ ሆምዝ ይለያዩ እንጂ እኩል ድንቅ ሰዎች ናቸው፡፡ በዝናም በጣም ይተዋወቃሉ፣ በጣም ይደናነቃሉ፡፡ ዋትሰን ነው ያገናኛቸው፡፡ እንደተያዩ ይጨባበጣሉ፡፡ "ምን ያህል ድንቅ መርማሪ መሆንህን ስለማውቅ ይኼንን ቤቱን እይና እንዴት እንዳስተዋልክ ንገረኝ" ይላል ፍሮይድ፡፡

ሼርሎክ ሆምዝ ያስተውልና "በአንድ ወቅት የተከበሩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ብዙ የምስክር ወረቀት ሸልመውህ ነበር፡፡ ነገር ግን በአንድ ወቅት እነዚህን የምስክር ወረቀቶች አንስተሃቸዋል፡፡

@Amharicbookstore

ምክንያቱም እነዚያን የኅብረተሰብ ክፍሎች ማስታወስ አያስፈልገኝም ብለህ ራቅካቸው፡፡"

"እንዴት ልትደርስበት ቻልክ?"

"ቀላል ነው፡፡ ይኸው የግርግዳውን ቀለም እንመልከት፡፡ እዚህ፣ እዚህ አካባቢ የምስክር ወረቀቶች ተሰቅለው ነበር" ይላል ሼርሎክ ሆምዝ፡፡

ዋትሰን በዚህ ደስ ይለዋል፡፡ ጓደኛው ጤናማ ሆነለት፡፡ አንድ ቀን ፍሮይድን ለማዝናናት "ዶክተር፣ ቴኒስ አንጫወትም?" ይለዋል፡፡

"እሺ እንጫወት" ይልና ፍሮይድ ይዞቸው ይወጣል፡፡ በነገራችን ላይ ፍሮይድ Moses and Monotheism በምትለው መለስተኛ መጽሐፉ ውስጥ ሙሴ አንድ ሳይሆን ሁለት እንደሆነ እንደሚያምን ጽፏል፡፡ ይኼንንም ሲገልፅ በጣም እንደሚያዝን፣ ነገር ግን በአይሁድነቱ እውነቱን መናገር እንደሚኖርበት ይመሰክራል፡፡ አያሌ ይሁዳዎችንም ባስቀየም የመሰለኝ ይኼ ነው ብሎ ይተነትናል፡፡ ፍሮይድ በዚህ ወቅት አሜሪካ ውስጥ ፋሽን ነው፡፡ ወደ ስፖርቱ እንመለስ፡፡

በዚህ ጊዜ አንድ ጄኔራል ይመጣል፡፡ እላይኛው ክንፉ ላይ መስታወሽ ያለው፡፡ "ዶክተር ፍሮይድ፣ ባለፈው ምሽት ከእናትህ ጋር ተኝተህ ነበር?" ሲለው፡

ዶክተር ዋትሰን በጥፊ ጄኔራሉን ይመታዋል፡፡ እስከ ሞት እንፋለም ማለቱ ነው፡፡ "ዶክተር ዋትሰን" ይላል ፍሮይድ "የራሴን ፍልሚያ ራሴው ልፋለም ፍቀድልኝ?"

"የፍልሚያ ሕግ ታውቃለህ? ሕጋቸው እንዲህ ነው፡፡ ነገር የፈለገው ሳይሆን፣ የተፈለገው ነው መሣሪያ የሚመርጠው፡፡ ስለዚህ ክብሩ የተነካው ፍሮይድ እኔ ልምረጥ አለና "ራኬት!" አለ፡፡

"ራኬት?" ነገር ተፋጣጪው ተገርሞ፡፡

"አዎን ራኬት!" አለ ፍሮይድ፡፡ እዚህ ላይ ነው ሲኒማውን የሠሩት ሰዎች የሳቁት፡፡ ሲጫወቱ ጄኔራሉ ሳቅ ያለ ችሎታ አለው፡፡ ፍሮይድም በቂ ችሎታ አለው፡፡ በዚያም ላይ በእእምሮውም መጫወቱን አትርሳ፡፡ በዚያም በማስተዋል ችሎታው ልቆ ሲጫወንድ ፍሮይድ አሸነፈ፡፡

በፍሮይድ ትንታኔ፣ ራስን ከማኖር (ከመመገብ) ቀጥሎ ራስን ማባዛት (ወሲብ) ነው የሰው መሠረታዊ ፍላጎት፡፡ ለሰው 'የኢነርጂ' የሀይል ምንጩ ወይም ሞተሩ ወሲብ ነው፡፡ ስንወለድ ወንድ ነው ሴት? ነው የመጀመሪያው ጥያቄ፡፡

@Amharcbookstore



ስታድግ ወይም በምንኩስና ወይም ሴት በማጣት ምክንያት የወሲብ 'ኢነርጂን' ካልሠራህበት፣ ያን ሁሉ ኃይል ምን ታረገዋለህ? ወደ ሌላ ጉዳይ ታዛውረዋለህ፡፡ ወይም አርቲስት ትሆናለህ፣ ወይም ሳይንቲስት፣ ወይም ወንጀለኛ፣ ወይም እንጃ፡፡

ፍሮይድ 'ጆኮችን' ቀልዶችን አጥንቷቸዋል፡፡ ወሲብ 'ኢነርጂው' ወደ ጆክ እንኳ ይጎርፋል፡፡ አንዲት ትንሽ የመሀል ኤውሮፓ አገር ውስጥ ንጉሡ ሲሞቱ አገሪቱ አንድ ዓመት ሙሉ ኀዘን ላይ ትሆናለች፡፡ አልጋወራሹ የሚነግሰው አንዱ የሀዘን ዓመት ካለፈ በኋላ ነው፡፡

አልጋ ወራሹ ሥራ ከምፈታ ለምን አገሬን ተዘዋውሬ አልጎበኝምና ሕዝቤን ለማወቅ አልሞክርም? ብሎ ተነሳ፡፡ ሲዞር ሲዞር አገሪቱ ወሰን የመጨረሻዋ መንደር ደረሰ፡፡ ሕዝቡ ሊቀበለው ግልብጥ ብሎ ወጣ፡፡ እና፣ እዚያ ሕዝቡ መሀል፣ አንድ እኩያው የሚሆን ጎረምሳ መልኩን አየ! "ሰአሊ ለነ ቅድስት! ዘርም ሊዘራ ወጣ አለ ሰውየው! የእኛ ሽሜ አልለገመም!" ብሎ አሰበ አልጋወራሹ፡፡

ጠጋ አለና ያንን ጎረምሳ "ምናልባት እናትህ ቤተ መንግሥት ውስጥ ሠራተኛ ነበሩ ይሆን?" ሲል ጠየቀው፡፡

"ኧረ እኳ! ከዚህ ከትውልድ መንደሬ ወጥታም አታውቅ፡፡ አባቴ ግን ከወጣትነቱ ጀምሮ የቤተ መንግሥት አታክልተኛ ነው፡፡"

"ጃንሆይ ጉድ ተሠሩ!" አለ አልጋ ወራሹ በልቡ፡፡ ፈጣን አእምሮ የታደለው አልጋ ወራሽ እንዲህ አለ በልቡ "ወይ አባዬ! ቀን አትክልት ሌሊት ንግስት! ጃንሆይ እንኳን ይህን ሳያውቁ ወደ አባቶቻቸው እቅፍ ሄዱ!"

Jack the Ripper ለንደን ከተማ ውስጥ ነው የሚኖረው፡፡ በዚያን ዘመን በየመንገዱ የኤሌክትሪክ አምፖል አይበራም፡፡ አልፎ አልፎ በጋዝ የሚሠራ ፋኖስ ይንጠለጠላል፡፡ መናፈሻዎቹ ይጨልማሉ፡፡ እዚያ ውስጥ ነው ሴተኛ አዳሪዎች የሚመጡትን ወንዶች በአካላቸው አስደስተው የዕለት ጉርሳቸውን የሚያገኙት፡፡ አንድ ጊዜ አንድዋ ሴተኛ አዳሪ ታርዳ በአግዳሚ ወንበር ላይ ተዘርራ ተገኘች፡፡ በጣም ባለሙያ ነው ሴትየዋን የበለታት፡፡ ይህንን በበነጋታው የታወቀው የስኮትላንድ ያርድ ፖሊስ ይደርስበታል፡፡ ሳምንታት ቆይቶ እንደገና ሌላ መናፈሻ ውስጥ ሌላ ሴተኛ አዳሪ ታረደች፡፡ ልክ እንደዛችው ሴት ነው አበላለቷ፡፡ ሲባል 11 ሴተኛ አዳሪዎች በተከታታይ ታርደው፣ በባለሙያ ተበልተው ተገኙ፡፡

ይህንን ሰው ማን እንደሆነ አላወቁትም፡፡ ጃክ አሉት፡ ስያሜውን የሰጠው አንድ ጋዜጠኛ ነው፡፡ ጊዜ ይወስዳል እንጂ የስኮትላንድ ያርድ ፖሊስ ይደርስበታል ይባላል፡፡ ሰው ጉራና ስም ይወዳል

አይደል? "እኔንን ጃክ ቀዳጁ" የሚል መልዕክት ለፖሊስ ደረሰው፡፡ ከደረሱት መልዕክት አንዷ ብቻ ነች እውነትነት ያላት፡፡ ለምን፣ በትናንትናው ሌሊት የታረደችውን ሴትዮ ጆሮ ፖስታ ውስጥ አሽጎ ጃክ ልኮላቸዋል፡፡

ፖሊስ ከብዙ ክትትል በኋላ ጃክን ያዘው፡፡ ጃክ የቤተ መንግሥቱ ልዑል ሆነ ይባላል፣ አየኸው?

በዚያን ጊዜ ለባኪንግሃም ፓላስ "ያዙት እንጂ" ብለው ፖሊሶች አመለከቱ፡፡ ከዚያ በኋላ ቤተመንግሥቱ ውስጥ 'ጃክ ዘ ሪፐር' እንደ ታሰረ ነው ይባላል፡፡

የሰው ልጆችን አስተዳደግ ልብ በል፡፡ የትም፤ ከተቃራኒዎቻችን ጋር ነው፡፡ ሰውን ትተህ እንስሳቱም፣ ተክሎችም እንኳን ወንድና ሴት እየሆኑ ነው የሚያድጉት፡፡ የጃክ ግን የወንድና ሴት ሕይወት ጥምረት ተበላሸበት፡፡ ተዘበራረቀበት፡፡ ሂደ ከማሃቀፍ በማልባሌ በማረድ ይረካል ማለት ነው፡፡ ይህ ነው የወሲብ ኃይል፡፡ ጤናማ በሆነ መንገድ መውጫ ካጣ በመጥፎ መልኩ መውጣቱ አይቀርም፡፡ ጃክ አንድም ወንድ አላረደ፡፡ በብዙዎቻችን ስታየው ወሲብን በሰላማዊ መንገድ ስንደሰት፡፡ አንዳንዴም እንደ 'ጃክ ዘ ሪፐር' ወሲብን መውጫው ወንጀል ሆኖ ታየዋለህ ይልሃል የፍሮይድ ሕግ፡፡

ፍሮይድ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲካሄድ ቪየና ውስጥ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ደግሞ ቪየና በናዚዎች ተይዛ ነበር፡፡ ይሁዲ በመሆኑ በዚያንስ መሰቃየት፣ ከከፋም መሞት ነበረበት፡፡ እንዴት ምንም አይነት አደጋ ሳይደርስበት እንግሊዝ አገር እንዲገባ ሆነ? ይህ የሚደንቅ ነው፡፡

በጣም የምትጠላውን ሰው እየጠላኸውም እንድታደንቀው የሚያደርግ አጋጣሚ የሚፈጠረው በእንዲህ ዓይነቱ ወቅት ነው፡፡ በቤኒቶ ሙሶሊኒ አማላጅነት ሂትለር ፍሮይድ ቪየናን ለቆ እንዲወጣ ፈቀደለት፡፡

እንዴ?! ሙሶሊኒ ወደ አመራር ሲመጣ ዴሞክራት እንደነበር አትርሳ፡፡ ከመነሻው ሙሶሊኒ ጋዜጠኛ ስለነበር ፍሮይድን ሳያነበው አይቀርም፡፡ የአማላጅ ደጅ ጥናት ያልከበደው ለዚህ ነው" አለና ጭንቅላቱን እየወዘወዘ "አየህ ፍሮይድ የእኔን ብቻ ሳይሆን የፋሽስቶችንም ዓይን የመክፈት ኃይል አለው!" ብሎኝ ፈገግ ብሎ "የፍሮይድ የልጅ ልጁ 'ዳንሴሪ' ነች፡፡ አያቷን ታነበው እንደሆን ተጠይቃ "አንብቤው አላውቅም፣ ወደፊትም አላነበውም" ብላለች፡፡

***

@Amharicbookstore



፴፪

## ጋዜጦች ላይ መዝራት

በአንድ ዓይነት ሙያ ውስጥ በሕይወትህ እንዴት ገብተህበት እንደምትሣተፍ አታውቀውም፡፡ ዜና ዘገቤ አላውቅም፡፡ ጋዜጣ ላይ በመጻፍ ሃሳቤን እንድዘራ በበዓሉ ግርማ ታጨሁ፡፡

በኋላ ነው 'እ! ለካስ ጀምሬዋለሁ' የምትለው፡፡ እኔ በአንድ ወቅት በትምህርት ሚኒስቴር በስኮላርሺፕ ክፍል እየሰራሁ እያለ አንዱን ቀን በአሉ ግርማ "እዚህ ዝም ብለህ ከቢሮክራሲ ሥራ ጋር ጊዜህን አታባክን፡፡ አሁን በስኮላርሺፕ ለምትሠራው ሥራ አገሩ በርካታ ሰዎች አሉዋት፡፡ ለአንተ ተፈጥሮ የእኛ ሙያ ነው የሚስማማህ" አለኝ፡፡

"እሺ እውነትክን ነው" አልኩና መልቀቂያ እንዲሰጠኝ ላለሁበት ትምህርት ሚኒስቴር ማመልከቻዬን ጻፍኩ፡፡ እዚህ ላይ አንድ 'Interesting' ነገር ልጨምርልህ፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ማመልከቻዬን አይቶት "ለምን ትሔዳለህ፣? እኛ እንፈልግሃለን፣ እድገትም አስበንልሀል" አለኝ፡፡ ከዚህ ሰውዬ ጋር ጥሩ የሥራ ጊዜ አሣልፌያለሁ፡፡ በባህሪው እዚህ'ጋ ብቻ አበሽኑቱን አየሁበት፡፡ በውሳኔዬ እንደፀናሁ ሲያይ ጊዜ፣ በፃፌልኝ የመሸኛ ደብዳቤ ላይ 'ያሰብንለት እድገት የሌለ መሆኑን እናስታውቃለን' ይላል፡፡

አየህልኝ? ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሄጄ እድገት ታስቦልኛል ጨምሩልኝ ብዬ እንዳልጠተውት መሆኑ ነው፡፡ በሄደበት ይቆርቁረው፣ የታባቱን! ዓይነት ነገር ናት የክቡር ሚኒስትሩ ደብዳቤ፡፡

እኔ ግን እየታዘብኩት ከበአሉ ግርማ ጋር ሥራ ጀመርኩ፡፡ ከበአሉ ጋር መሥራት ማራኪ ነው፡፡ የመጀመሪያ ሥራዬ እንዲሆን አፈወርቅ ተክሌን አነጋግርና ጻፍ አለኝ፡፡ እኔ እንዲህ ዓይነት ዝነኛ ሰው አነጋግሬ አላውቅም፡፡ "ስለምፈራ ተውኝ፣ አንተው እንደ ለመድከው ሂድ አናግረው አልኩት፡፡ "እኔም አብሬህ እሄዳለሁ" አለኝ፡፡ ተስማማሁ፣ ሄድን፡፡ አፈወርቅን ሳየው እንደገመትኩት

የማያስፈራ አይደለም፡፡ ወደ ቤቱ የሚወስደውን መንገድ አልፋ ጎዳና ብሎ ሰይሞታል፡፡ በጣም ቆንጆ ቤት ነው፡፡ የጎንደርን ቤተ መንግሥት ያስታውስሃል፡፡ ውስጡ ስትገባ አትክልቱ፣ ምኑ! በቃ እንደ ስዕሎቹ መኖሪያ ቤቱም ውብ ነው፡፡ ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ቁጭ እንዳልን አፈወርቅ "እገሌ" አለና የቤት ሠራተኛውን ጠራው፡፡ ሲመጣ "እባክህን ሻይ አምጣልን" አለው፡፡ "ሻይ አምጣልን ቶሎ! አይደለም ያለው፡፡ በጣም ደስ አለኝ አስተዛዘኑ፤ የጨዋ ሰው ነው፡፡ ከእኔ ጋር ስናወራ እኔም ፍሬን ለቀቅኩ፤ ከአፈወርቅ ተክሌ ጋር የማወራ መሆኑን እስከምዘነጋ፡፡ ማስታወሻ ወሰድኩ፡፡ ቆንጆ አድርጌ ጻፍኩት፡፡ ለካስ በአሉ እኔና ታላቁ ሰዓሊ ስንነጋገር ፎቶ እያነሣን ኖሯል፡፡ ፎቶዎቹ ከጽሑፉ እኩል ቆንጆዎች ነበሩ፡፡ አፈወርቅም ጽሑፉን ወድዶት ከመጽሔቱ መቶ ኮፒ ገዝቶ ለወዳጆቹ ወደ ተለያዩ አገሮች ላከው፡፡

'ኮምፕሌክስ' ነበረብኝ ማለት ነው፡፡ ይህን 'ትልቅ ሰው፣ ስም ያለው፣ የተከበረ ሰው ማነጋገር ብዙ ጊዜ የሚወስድብኝ ይመስለኛል፡፡ ቁጭ ብሎ መነጋገር እንኳን የምችል አይመስለኝም ነበር፡፡ ሐና ነች ከሰው መቀላቀል ያላመደችኝ፡፡ ከእሷ በፊት እንደ ባህታዊና መነኩሴ ዓይነት ባህርይ ነበረብኝ፡፡

መጽሔቱ ላይ ምናልባት ሁለት ዓመት ሠርቼ ይሆናል፡፡ የሠራሁትም መነን መጽሔት ላይ ነበር፡፡ እንዳልኩህ ዜና የሚባል ነገር ሠርቼ አላውቅም፡፡ አዲስ ሪፖርተር ላይ ስፅፍ ዓለም ፐብሊክ ሪሌሽንስ ውስጥ እየሠራሁ ነው ጽሑፎችን ያወጣሁት፡፡

በአሉ ምንም 'ኮምፕሌክስ' የሌለበት ሰው ነበር፡፡ አሪፍም አለቃ ነው፡፡ አብረን በርካታ ሰዎችን እንዳነጋገርን አስታውሳለሁ፡፡ አቶ ሀዲስ ዓለማየሁን ከእርሱ ጋር ነበር ያነጋገርኳቸው፡፡ ልክ ቢሮዋቸውን ከፍተን ስንገባ "በአራት መቶ ገጽ ያወራሁላችሁ አልበቃ ብሎ ነው አሁን በተጨማሪ ልታስለፈልፉኝ የመጣችሁት?" ብለው ተቀብለው አነጋገሩን፡፡

አሁን በአሉ ቢሮ ያጋጠመኝን ልንገርህ፡፡ አንድ ቀን ሥራ አርፍጄ እገባለሁ፡፡ ሥራዬን እስከሰራሁ በአሉ ግድ የለውም፡፡ በአሉን ላናግረው ፈልጌ እሱ ቢሮ ስገባ አሜሪካውያን ፈረንጆች ተቀምጠዋል፡፡ ጥግ ላይ መንግስቱ ለማ ይታየኛል፡፡ ሁሉንም ተራ በተራ እየጨበጥኩ መንግሥቱ አጠገብ ደረስኩ፡፡ ስጨብጠው "እኛም ይድረሰን እንዴ?" አለኝ፤ አለና ምስሉ አሁን እንደታየው ሁሉ ሣቀ፡፡

@Amharicbookstore



የበአሉን ሌላ ገጽታ ላሣይህ፡፡ ረሻድ የሚባል ወጣት ጋዜጠኛ ደርሶበት ነው የጫወተኝ፡፡ በአሉ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ እያለ ሪፖርተሮቹን ሰብስቦ ያነጋግራል፡፡ ረሻድ ባልቃ እየገባ ያቋርጠዋል፡፡ በአሉ ይጀምራል፡፡ ረሻድ አሁንም አላረፈም ባልቃ ይገባል፡፡ በአሉ ቁጣውን ውጦ ስብሰባውን እንደምንም ከዳር ያደርሰዋል፡፡ ሪፖርተሮቹ መውጣት ሲጀምሩ በአሉ ረሻድን "ቆይ!" አለው፡፡ ቆየ፡፡ በአሉ ቢሮውን ቆለፈ፣ ኮቱን አወለቀና ረሻድን በቦክስ አናፈጠው፡፡ ረሻድ እየተከላከለ በክሱን ጠጣት፡፡ "ውጣ!" አለው ሲበቃው በአሉ፡፡ ረሻድ ወጣ፡፡ ቆይቶ ቆይቶ ለእኔ ሲያጫውተኝ "እንኳንም የመታኝ" አለ፡፡

"ለምን" አልኩት፡፡

"ሌላ ተራ ቀሽም አለቃ ቢሆን ኖሮ የግል ማህደሩን አምጡልኝ ብሎ በብዕሩ ይወጋኝ ነበር፡፡የሕመም ደግሞ ዕድሜ ልኬን ተከትሎ ሲያደማኝ በኖረ፡፡በአሉ ግን ጎሸመኝና ሥራችንን ቀጠልን" አለኝ፡፡

አየህልኝ? በአሉ እንዲህ ዓይነት ሰው ነበር! ሌላ ገጠመኙን ላጫውትህ፡፡ አንድ ቀን ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቁ ሥላሴ በአሉ ቢሮ መጡ፡፡ ሁለት ግድንግድ አሽከሮች አስከትለዋል፡፡ በትናንትናው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ውስጥ እሳቸውን የሚያስቆጣ ጽሑፍ ወጥቶ ኖሯል፡፡ በሩ ተዘጋ፡፡ በአሉ ቆመና እንዲቀመጡ ጋበዛቸው፡፡

"አንተ ነህ ይህንን የጻፍከ?" አሉት፡፡

"እኔ እንኳን አይደለሁም፡፡ ግን አዘጋጅ እንደመሆኔ በእኔ ኃላፊነት ነው የሚወጣው፡፡"

"ውሸትም ስህተትም ሞልቶበታል፡፡ የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው፡፡"

"መልስ ሊሰጡበት ይችላሉ፡፡"

"መልስ ብሰጥህ ጽፈህ ታወጣዋለህ?"

"አዎን፡፡"

በረጂሙ አነጋገሩትና ሄዱ፡፡ ጽፎ አወጣው፡፡ በበነጋታው ተመልሰው መጡ፡፡ ማንንም ሳያስከትሉ፡፡ "ላመስግንህ ነው የመጣሁት፡፡ ቃሉን የሚጠብቅ ሰው ብዙም አይደለም" አሉት፡፡

ቡና እየጠጡ በረዥሙ አወጉ፡፡ ልክ ልጆች ሆነን እሳት ዳር ተቀምጠን ማታ ማታ እንደሚተረክልን ተረት ነበር፡፡ አያ ነበር፣ ፍየልንና ቀበሮን "መጥቼ ከምበላችሁ፣ መጥታችሁ ብምራችሁ ይሻላችኋል" ብሎ ይልካባቸዋል፡፡ ፍየል ,ምሕረት አገኛለሁ ብላ ስትመጣ፣ ቀጨም አደረጋት፡፡ ቀበሮ ግን "ሞኝህን ፈልግ" ብላ ጠፋች፡፡ ደርግም የቀድሞ ባለሥልጣኖችን "መጥቼ ከምይዛችሁ መጥታችሁ እጃችሁን ብትሰጡ ይሻላችኋል" አላቸው፡፡ ብዙዎቹ

እየመጡ እጃቸውን ሰጡ፡፡ ደጃዝማች ፀሐዩ እንቈ ሥላሴ ግን "ሞኝህን ፈልግ" ብለው ሽፈቱና ሲዋጉ መራቤቴ ላይ ሞቱ፡፡ ሊሸፍቱ ሲሉ በአሉን ቢሮ መጥተው ተሰናብተውት ነበር፡፡

ጊዜው እረዘመ፡፡ ከ30 ዓመት በላይ ሳይሆነው ቀረ? ብቻ ውስጣችን የቀረውን ፈላልገን እናውጋ፡፡ በዚያን ጊዜ ጎህ የምትባል የኢሕአፓ መጽሔት ነበረች፡፡ ደርጎች ዘጓት፡፡ የጎህ ሰዎችም አሁን እምነታችንን በየት በኩል መተንፈስ እንችላለን? ብለው አሰቡና ቁምነገርን ሊጠቀሙባት ፈለጉ፡፡ ደርጎች ደግሞ ይህንን ቀድመው ስለጠረጠሩ እኛን የቁምነገር አባሎችን ሊያስጠነቅቁን ፈለጉ፡፡ ታምራት ፈረደ የደርግ አባልም፣ ጥሩ ሰውም ነው፡፡ በበዓሉ ግርማ አማካይነት ቀደም ብለን ተዋውቀን ስለነበር እንግባባለን፡፡ ለወደፊትም ደራሲ ለመሆን ፍላጎቱ ስላለው አንድ ሙከራውን አስነብቦኝ ጥሩ ጥረት የሚያሣይ ሥራ እንዳለው ተገንዝቤ ነበር፡፡ አስተያየቴንም መስጠቴን አስታውሳለሁ፡፡ አሁን ደግሞ ቁምነገር አገናኝቶን ጠርቶ ያስጠነቅቀናል፡፡ "በእናንተ በኩል ሰርጎገቦች ገብተው እንዳያወናብዱአችሁ ለማድረግ ነው የጠራናችሁ" አለን፡፡

ሁለት፣ ሁለት እየሆንን ነው የምንጠራው፡፡ እኔና ሀሰን ተጠርተን ሔድን፡፡ ሀሰን በጊዜው ቀንደኛ የኢ.ህ.አ.ፓ አባል ነበር፡፡ ዕድሜው አስራ ዘጠኝ ዓመት ነው፡፡ በቃ የለየለት ማርክሰሲት ነው፡፡ ሁሉም ነገር በርሱ አተረጓጎም የመደብ ነው፡፡ ይህንን አክራሪ ማርክሲስትነቱን ሲያፀዛው ጊዜ፣ "ምን ማለትህ ነው ሀሰን? አሁን ሽንት ቤት አንድ ሰው ተቀምጠ ፈሱ ቢያመልጠው ያም የመደብ ነው?" ስለው፡፡

"ነውና!" አለኝ፡፡

ጋሼ እየሣቀ "እንደዚያ ዓይነት ወጣት ነው ሀሰን፡፡ እነመንጌን ፋሽስት ነው የሚላቸው፡፡ በወቅቱ ኢህአፓዎች ይገድሉዋቸው ነበር፡፡ ሀሰንና እኔን ታምራት ገለፃ ሲያደርግልን "እኛ እናሸንፋለን ነው የምንለው፡፡ እነሱ እናቸንፋለን ይላሉ፡፡ እኛ ወዛደር ስንል፣ እነሱ ላብአደር ነው የሚሉት" ብሎ ስለ ልዩነታቸው አስረዳን፡፡

"ይህ የቃላት - አለመግባባት ደም ያፋስሳል እንዴ?" ብዬ ስጠይቀው በር ተንኳኳ፡፡ ግቡ ለማለት ጊዜ ሳይኖረን ተከፈተና መንግሥቱ ኃይለማርያም ከተፍ አለ፡፡ ተነስተን ጨበጥነው፡፡ እኔ አሁን ሳስታውሰው መንጌን ስጨብጠው ደስ አይልም እጄን የሚያልበው ሰው ብዙ ጨብጫለሁ፤ እጅህን ጠርገኸው ትረሣዋለህ፡፡ እጁን አያልበውም፡፡ ግን ደስ አይልም፡፡ የሆነ ነገር አለ፡፡ ይህ



ስሜት የእኔ ብቻ ይሆናል፡፡ መንጌ በመምጣቱ ከሀሰን ጋር ታምራትን ተሰናብተን ወጥተን ታክሲ ውስጥ እንደገባን፡፡

"ታሪካዊ ዕድል እኮ ነው አንተ!" አለኝ ሀሰን፡፡

"ምኑ" አልኩት፡፡

"ጓድ ሊቀመንበርን ጨበጥን እኮ!" አለኝ፡፡

"የዚያን ጊዜ ብልጭ አለብኝ፡፡ በቃ ይኼንን ልጅ መንጌ ጠርቶ ገዳይ ጓድ ቢያደርገው እሺ ይላል ማለት ነው፡፡ ማንም ይሁን ክንፍ ያለው ወይም ቀንድ ያለው ግድ የለውም፡፡ ዋናው ነገር መሪው ከጨበጠው ለእርሱ ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ ምክንያቱም ኢህአፓ ሩቅ ነዋ!" አለና ተከዘ፡፡

ደበበ እሸቱ በጣም ጥሩ አለቃ ነው፡፡ ቢሮዋችን ረዥም ሰፊ ክፍል ነበር፡፡ ከአምስት እስከ ስድስት የምንሆን ቋሚ ሠራተኞች አለን፡፡ እየተጨዋወትን ነው የምንሠራው፡፡ ደቤ ሲመጣ ኖር እንኳን እንለውም፡፡ ሰላም ብሎን ሥራውን ይጀምራል፡፡ ደስ ያለህን እስበህ እንዲህ ቢሠራስ ስትለው "ቀጥል!" ነው የሚልህ፡፡ እኔ እንደእርሱ ዓይነት አለቃ አጋጥሞኝ አያውቅም" አለና አስተዋለኝ፡፡

አንድ ቀን ቁራጭ ወረቀት ከሳንሱር ጽሕፈት ቤት ተላከልኝ፡፡ በዚያን ጊዜ የምፅፈው በአጋፋሪ እንደሻው ላይ ነበር፡፡ የደረሰኝ ማስጠንቀቂያ 'የወዛደሩን ልዕልና የሚያሣይ ካልሆነ ቀልድ ክልክል ነው' ይላል፡፡

ለካ ሞትና አጋፋሪ እንደሻው ውስጥ ቀልድ ነበር፡፡ ወዛደር አይደሉም እሳቸው፡፡ እኔም በባህሪዬ ልክ እንዳባቴ ቶሎ እቆጣለሁ፡፡ እግዜርም አትታሰር ሲለኝ ለደቤ ለቅቄ መውጣት እንደምፈልግ ነገርኩት፡፡ "ሂድ!" አለኝ፡፡ ወጣሁ፡፡ በወሩ ቁምነገር መጽሔት ተዘጋች፡፡

ደበበ እሸቱ አሁንም በሕይወት አለ፡፡ ፍጹም ምፅዋ ታየ ተባለ፡፡ ሀሰን ተረሸነ፡፡ ሠዓሊያችን ሰላም ይሁን ነው ስሙ፡፡ እንዳልከው የመጽሔታችን ሠዓሊ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ የሠራተኛውን ሰልፍ የሚያሣይ ሥዕል ሣለ፡፡ በዚህ አሰሩት፡፡ የወዛደር ሰልፍ ሥዕሉን ከሩቅ ሲያዩት ሽቅብ ቁልቁል የወጣ ምስል ይታያል፡፡ "ይህን ናቅፋ ተራራን መሣልህ ነው!" አሉት፡፡ አይደለም፡፡ ስምዋ ጠፋኝ አንድ ተራራ ነበረች፡፡

አዎ! አሲምባን ነው የሣልከው አሉት" አለና እየሣቀ "በዚህ ምክንያት ሰላም ይሁን ተገደለ፡፡ ሩቅ ስለሆነ የሚያሳዝነው አጋጣሚ ያስቃል፤ እንጂ በወቅቱ አንጀታችን ነበር ያረረው፡፡ ምንም ጉልበት የለንም፡፡ እንደ እሱ ለመሞት ካልሆነ በስተቀር ምን ልናደርግ እንችላለን? በዚህ መልኩ የቁምነገር መጽሔት አባሎች ተበታተንን፡፡

ይኸውልህ፡፡ በዚያው ዛሬ ድሮ በሆነው ወቅት ሙሉቀን መለሰ የተባለውን ዘፋኝ ሳነጋግርልህ ሄድኩ፡፡ ቃለ ምልልሳችንን አደረግን፡፡ በዚያን ወቅት ሙሉ ቀን "እናንተ ጋዜጠኞች የልባችንን ስንነግራችሁ፣ እናንተ ግን ሌላ ነገር አትማችሁ ታወጣላችሁ፡፡ አሁንም ልንገርህ፡፡ ዓለማየሁ እሸቴን የመሰለ ሙዚቀኛ ሙያውን ትቶ በሹፍርና ላይ ተሰማርቷል፡፡ እኔን ሆነ ሌሎቹንም የታወቁትን ድምፃውያን ብትወስድ ድምፃውያን ነን፡፡ ዓለማየሁ ግን ጥበቧን የተካናት ሙዚቀኛ ነው፡፡ ከማቀንቀን ውጪ የሙዚቃ መሣሪያም ይጫወታል፡፡ ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ሙዚቀኛ ከሙያው ኮብልሎ ሾፌር መሆን ነበረበት? ይህ ለእኔ አሣዛኝ አጋጣሚ ነውና ዓለማየሁን ወደሙያው እንድንመልስ ይህንን መልዕክቴን አድርስልኝ" አለኝ፡፡

ጻፍኩኝ፡፡ በኤዲተር ወይም፣ በሕትመት ላይ ይህ ሙሉቀን የላከኝ መልዕክት ሳይታተም ቀረ፡፡ በዚህ አዝኜ የመጽሔቱን አዘጋጅ ሄደን ሁኔታውን እንድናስረዳውና ይቅርታ እንድንጠይቀው አማከርኩት፡፡ "ተወው!" አለኝ በእጁ ወደዚያ እያመናጨቀው፡፡ ተናደድኩ፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያ ላይ ግን ቃለ ምልልስ እንድናደርግ ሙሉቀንን ለማግባባት ብዙ ተጥሯል፡፡ አሁን መጠይቁ ተጣክቶ ከታተመ በኋላ ይቅርታ አድርግልን ማለት ይበዛበታል? በዚህ አዝኜ እዚያ መጽሔት ላይ መጻፍ አቆምኩ፡፡ ያውም በነፃ ነበር የምፅፍለት፡፡ መጽሔቷ ፀደይ ነበረች፡፡

አሪፍ ሲያጋጥምህ፣ እርፍናው እንዲቀጥልና አንባቢም የተሻለ ጽሑፍ እያነበበ እንዲደሰት አንተም ማዋጣት አለብህ፡፡ እኔ በዚህ ስሜት ተነሣስቼ መጻፍ ጀመርኩ፡፡ ኢትዮጵያን ሔራልድ ላይ የዚያን ጊዜ አረፋይኔ ሐጎስ አሪፍ የቀልድ አምድ ስለነበረው አንብቤው ተደሰትኩ፡፡ እርፍናው እንዲቀጥል እኔም ማዋጣት ጀመርኩ፡፡ በዚያን ጊዜ እኔ የምሠራው ኩራዝ አሣታሚ ድርጅት ነበር፡፡ Humour in the Highlands (የደጋ አካባቢዎች አስቂን ወግ) በሚል ርዕስ በተከታታይ እጽፍ ነበር፡፡ በወቅቱ እኔ የገቢ ችግር የለብኝም፡፡ አንድ ስድስት ወር እንደሠራሁ አንድ ቀን የፕሬስ መምሪያ ኃላፊ የነበረው ሙሉጌታ ሉሌ ብርሃንና ሰላም ሕንጻ 'ሊፍት' ውስጥ አገኘኝ፡፡ "እ! ሚኒስትሩ ጠርተውኝ ይከፈለዋል ወይ ይህ ሰው?" ብለው ጠየቁኝ፡፡ "አይከፈለውም" ስላቸው "ለምን አይከፈለውም እንዲህ ጥሩ እየጻፈ? "ከእንግዲህ እየተከፈለው ይሥራ" ብለውኛል አለኝ፡፡ ሚኒስትሩ ግርማ ይልማ ይባላሉ፡፡



በጣም የምወደው የአርጀንቲና ደራሲ አለ፡፡ ቦራኼስ ይባላል፡፡ ዓይነ ስውር ነው፡፡ ለአርጀንቲና ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ዲሬክተር ይፈለጋል ሲባል፣ እናቱም ጓደኞቹም "አንተ ለዚህ ሥራ ብቁ ነህ፣ አመልከት"አሉት፡፡

ቀጣሪው ኮሚቴ ቃለ መጠይቅ ሲያደርግለት "ለዚህ ሥራ ብቁ የሚያረግህ ምንድነው?" አሉት፡፡

"ያን ጊዜ ሆን ብዬ አልነበረም'ንጂ አሁን ስገነዘበው ግን ለዚህ ሥራ ሃያ አምስት ዓመት ሙሉ ስዘጋጅ ኖሬአለሁ" አላቸው፡፡ ሥራውን አገኘ፡፡ ፈጣሪ 'እግረ መንገድ' ዓምድን ሲሰጠኝ እንደ ቦራኼስ ነው፡፡ ለካ እስካሁን ሳነብ የኖርኩት በአንድ በኩል ለዚህ ነበር አልኩኝ፡፡ በነገራችን ላይ ቦራኼስ በኋላ በሥነ ጽሑፍ የኖቤል ሽልማት አሸናፊ ሆኗል፡፡

አየህ ሰው ለአገሬ ብሎ ደፋ ቀና ቢል፤ እኔ በበኩሌ አላምነውም። ለራሴ ብሎ ጀምሮ በቀይታ ለአገር የሚተርፍ ከሆነ አምነዋለሁ፡፡ 'ለእኔ ቀርቶ ለእኛ' እያሉ የሚነዙትን መፈክር አላምነውም፡፡ ውሸት ነው፡፡ ግለሰብን ለሕብረተሰብ የምታሣይ አባባል ትዝ አለቺኝ ላጫውትህ፡፡

ፍራንክሊን ዴላኖ ሮዝቬልት የሚባል የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረ ሰው ለፕሬዚዳንትነት እጩነቱን ለአሜሪካውያን ሲያስተዋውቅ 'በእያንዳንዱ አሜሪካውያን ጠረጴዛ ላይ የበሰለች ዶሮ፣ በየጋራዡ አንድ መኪና' በሚል መፈክር ለምርጫ ቀርቦ ተወዳደረና ተሳካለት፡፡ እጩነትህን በውስጠ ታዋቂ አኑረህ እኛነትን እንዲህ አግዝፈህ ማሣየት ይቻላል፡፡

ተሰጥኦ አንዳንዴ በሽታ ነው፡፡ አንተንም እንኳን የማይህ እንደ መጽሐፍ፣ ወይም እንደ ተረት ሆነ፡፡ ይኸውልህ ስንት ዓመት ኖሬያለሁ" እናቱን ዳብሶ ዞማ ሸበቶ ፀጉሩን በእጆቹ አስተኛ፡፡ በሃሳብ የፈጠረውን መጻሕፍት ዓይነት በእጁ እየገለጸ "እዚህ ውስጥ እኮ ቤተ መጻሕፍት አለ፡፡" ጭንቅላቱን በጠቋሚ ጣቱ ጠቆመ፡፡ "ንባብ በቃኝ የሚባልበት ቀን አይመጣም፡፡ እንጂ እኔ በቂ አንብቤያለሁ፡፡ የፈለግከውን ጠይቀኝ፣ የማውቀውን ሁሉ አካፍልሃለሁ፡፡ ጠይቅ!፡፡

ከሳምንት እስከ ሳምንት ለመጻፍ? የምፈልገውን ካደረጉልኝና ምቾቱን ካሟሉልኝ እችላለሁ፡፡

እኔ ሳነብ አንዴ አንብቤ ከገባኝ ጥሩ ነው፡፡ ካልገባኝ ቀሽም ነው ብዬ አልፈዋለሁ፡፡ ወይም ይኼ እንደገና ሕነበብ አለበት ብዬ ደግሜ አነበዋለሁ፤ እስኪገባኝ፡፡ ለምን አስር ጊዜ አይሆንም? አነበው ነበር፡፡ እንኳንም ደጋግሜ አነበብኩት የምለው የሙኖሩን ያህል ዝም ብዬ

የማልፈውም አለ፡፡ እኔን የሚያነበኝ አንባቢ ደግሞ ከተግባባን ያንብብ፣ ካልተግባባን ይተው፡፡ ጽሳት እኮ አይደለም፡፡ ጋዜጣ ላይ የምታየው ጽሑፍ ነው፡፡ አንባቢ ደስ የሚለውን ማንበብ፣ የማይለውን ግን ማለፍ አለበት፡፡ የእኛም አላማ አንባቢን ማጫወት ማዝናናት ነው፡፡ እኛም የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን፡፡ በሳምንት አንድ ቀን እረፍት ያወጀልን፣ የመጨረሻው ጻድቅ የምንለው ሰው ነው፡፡ አለበለዚያ አንድ ቀን ሳናርፍ፣ ሳንስቅ ዕድሜያችንን ሁሉ እንሠራ ነበር፡፡ ስለዚህ የሙሴን ግብዣ እየተቀበልን፣ እየተከተልን እናርፍና በእግረ መንገድ ተዝናኑ ነው የምንለው፡፡

ፀሐይ በላቸው የእግረ መንገድ ዓምዴ ለረጂም ጊዜ ስትተይቢልኝ ቆይተሻል፡፡ በሥራው አጋጣሚ የሚፈጥረውን ስሕተት አሳይተሽኝ ትክክል መሆንሽን ተረድቻለሁ፡፡ በዚህ ተግባርሽ ዓምዴ ላይ ሾሜሻለሁ:: በቃ! ከዛሬ ጀምሮ አንቺ የእኔ አርታኢ ነሽ፡፡ ስሕተት ብለሽ ያጋጠመሽን ቃል፣ አረፍተ ነገር እርግጠኛ ስትሆኚ የመሰረዝ ሙሉ መብት ሰጥቼሻለሁ፡፡ Sailor ጽሑፎቼ ከተተየቡ በኋላ አሬጅናሉን ማየት እንደሚፈልግ ነግሮኛል፡፡ ስለዚህ አስነብቢው፡፡ ለራስ መውሰድ የሚፈልገው ኮፒ ካለም ብትሰጪው መልካም ፈቃዴ ነው፡፡

ውጭ አገር እያለሁ ጋዜጣ አላነብም ነበር፡፡ እዚያኛው ዓለም አገሌ አገሌትን አወጣት፣ አቶ እገሌ እና እገሌ ቤት እራት ሣይጠሩ ሄዱ፣ ወዘተ ነው፡፡ ወደ እዚህኛው ዓለም ስትመጣ 500 ሰዎች በወንዝ ሙላት ተወሰዱ፡፡ 60 ሰዎች በጠርነት ተደመሰሱ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ ስትል ይዘገንናል፡፡ ሁልጊዜ አሣዛኝ ወሬ ነው የምትሰማው፡፡ ጋዜጣ ላይ መልካም ወሬ ቦታ የለውም፡፡ ስለዚህ እኔ ሄጄ ያንን ሰቆቃ የዘነበበትን ሕዝብ ላላድነው ለምን አነባለሁ? በኋላ ፈረንሣይ ሄጄ ከሰው ለመቀላቀል Le Monde የሚሉትን ጋዜጣ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ አረፍ ጋዜጣ ነው፡፡ መረጃ ሲሰጥህ፣ የቆየን ታሪክ ሁሉ ያክልልሃል፡፡ አብዛኞቹ ጋዜጦችና መጽሔቶች መነሻውን ታሪክ ሊጨምሩልህ አይጥሩም፡፡ የአሁኑን ነው የሚጽፉልህ፡፡ ለምንድ ግን ይህ የቆየ ታሪክ እንደሚያስፈልግህ አይዘነጋም፡፡ ለእኔም ይህ ጋዜጣ ዓይኔን ከፈተልኝ ልልህ እችላለሁ፡፡

ከእንግሊዞችስ? ድሮ The Observer ጋዜጣቸው ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ከእርሱም ጋር ከተለያየን ዓመታት ተቆጠረ፡፡ Newsweek መጽሔት ጥሩ ነው

አዎን! አሜሪካንና እንግሊዝን እኮ የሚለያያቸው ጥቃቅን ነገር ነው፡፡ አንድ ሕዝብ ናቸው ልንላቸው እንችላለን፡፡ አሜሪካኖች

@Amharicbookstore



ሲቀልዱ እንግሊዝ 53ኛዋ 'ስቴት' ነች ነበር የሚሉት፡፡ ከፈለግክ most intersting National Geographic የሚባል መጽሔት አለ፡፡ እሱን እንደ ልብ አታገኘውም እንጂ ዕውቀት እርሱ ውስጥ ተከማችቷል ልል እችላለሁ፡፡ ሰፊ ጥናት አድርገው በቆንጆ ፎቶግራፍ አስደግፈው ነው የሚያትሙት፡፡ የማይመረምሩት የዕውቀት ዘርፍ የለም፡፡ በመጥፋት ላይ ያሉ ሕዝቦችን ሁሉ ናሽናል ጂኦግራፊ መርምሮ ያስነብባል:: በዚህ ጥረታቸው ለመጽሔቱ አዘጋጆች ታላቅ አክብሮት አለኝ:: እንስሳትን፣ ባህልን፣ እያደጉ ያሉትን ሕዝቦች፡፡ Reader's Digest ደግሞ መጠነኛ ዕውቀት ላላቸው ሰዎች የምትዘጋጅ መጽሔት ነች፡፡ መዝናኛም ሆነ መረጃ ታቀብልሃለች፡፡ በሌላ በኩል ካየሃት Reader's Digest የምትሠራው ለአሜሪካ መንግሥት ድጋፍ ነው፡፡ ትንሽ ስለኮሚኒዝም ለሚያውቅ ሰው የመጽሔቷ ሥራ ሊያስቀው ይችላል፡፡ ኮሚኒዝምን ስትዘግብ ጭራቅ አድርጋ ነው፡፡

አንድ ነገር ትዝ አለኝ ለ ሞንድ ላይ ያነበብኩት ነው፡፡ ምን ልንገርህ እያልኩ ሳብሰለስል ራሷ ብቅ አለች፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ የዩጎዝላቪያ ፕሬዚዳንት የነበረው ማርሻል ቲቶ ደስ ይለኛል፤ እንደ ጃንሆይ፡፡ ሁለቱም የትግል ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ በኮሚኒዝሙ ዓለም ከእስታሊን መመሪያ የማይቀበል መሪ ቲቶ ብቻ ነበር፡፡ እንደ እኔው የሚያደንቀው ፈረንሳዊ ጋዜጠኛ ሄዶ አነጋገረው፡፡ ያኔ እኔ ተማሪ ነበርኩ፡፡ ቲቶ በጠርነቱ ጊዜ አንድ የቀለበት ጣቱ ተቆርጧል፡፡ አሁን ግን አስር ጣቱ ሙሉ ነው፡፡ ጋዜጠኛው ይህንኑ የጣት ጉዳይ አንስቶ ጠየቀው፡፡ ቲቶ ሳቀ፡፡ አሣሣቁ ራሱ የሚያስቅ ነበር፡፡ ምንጊዜም የዚህች ጣት ነገር ከተነሣ ያንን ወፍራም ሣቁን ይለቀዋል እልሀለሁ::

እንዲህ ሆነልህ፡ እ.ኤ.አ 1973 ሁለት ጥይቶች ጋዜጠኞች Washington Post ጋዜጣ ላይ የአሜሪካንን ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን (Richard Nixon) በውተር ጌቱ ቅሌት አጋልጠው ጻፉ:: ጋዜጠኞቹ ፕሬዚዳንቱ ለዳግም ምርጫው ውጤታማ ለመሆን ከተቃዋሚ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ቢሮ ሰነዶችን አሰርቆ መውሰዱን ደርሰውበታል::

ኒክሰን ካደ፣ በተጨማሪ አስፈራራ:: ጋዜጠኞቹ ፍንክች አላሉም:: ሥልጣኑን እየወደደውም ቢሆን ስላልቻለ ለመልቀቅ ሁለት ዓመት ከመንፈቅ እየቀረው የግዱን ኋይት ሀውስን ተሰናበተ:: ይህ ወንጀል የወተርጌቱ ቅሌት ይባላል:: በእነዚያ ድንቅ ጋዜጠኞች ኒክሰን ተጋልጦ በትረ ሥልጣኑን ባይለቅ ኖሮ፣ ምንአልባትም ከታላላቅ የአሜሪካን መሪዎች መካከል አንዱ በሆነ ነበር::

ክስ ተመስርቶበት ነበር:: በወቅቱ ለአጭር ጊዜ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበረው ጄራልድ ፎርድ 'Gerald Ford' "አሜሪካን ፕሬዚዳንቷን

አትከሰም'' በማለት ኒክሰንን ነጻ አወጣው:: ከዚህ አወዳደቁ ይህ ሰው ተነስቶ በኋላ የሕይወት ታሪኩን በመጻፍ አስነበበ:: በዚህ ዕናቱ ኒክሰን ሊደነቅ ይገባዋል::. የኒክሰንን ጥንካሬና ሽንፈት በጋዜጠኞቹ ድንቅ ችሎታ እንድናይ ሆነ::

በአንድ ወቅት ሪደርስ ዳይጀስት ውስጥ ለንደን ውስጥ ብቻ 2ሺ600ሴት ጠንቋዮች መኖራቸውን አንብቤያለሁ፡፡ አሜሪካ ውስጥ ደግሞ The Salem witch hunt ኤንሳይክሎፒዲያ ውስጥ አንብብ፡፡ እነዚህ 'ዊች' የሚሏቸው ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ አሮጊቶች ናቸው፡፡ በሌሊት መጥረጊያን እንደ ፈረስ እየጋለቡ ነው በአየር የሚሄዱት፡፡ ከእኛ አገር ቡዳ ጋር የርቀት መመሳሰል አለው፡፡ ሳሌም ከተማ ውስጥ ዊች ናቸው እየተባሉ ብዙ ብቸኛ አሮጊቶች በጥርጣሬና በጥላቻ እየታፈሱ ተቃጠሉ እንደ ኢንኩዊዚሽን::

***

ጋሼ ሰብሐት ከአምስት አሰርት ዓመታት በላይ አንብቧል፡፡ ይህንን የንባብ ልምዱን በእግረመንገድ አምዱ ላይ በተለያዩ አቅጣጫዎች በጻፋቸው ጭብጦች አካፍሎናል፡፡ እግረ መንገድ ዓምድ ሐምሌ 25 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ፣ እስከ ጥር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ድረስ ለሀትመት በቅቷል፡፡

በዚህ ዓመት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባካሄደው ዓመታዊ ግምገማ አንዳንድ ዓምዶች ለውጥ ተደረገባቸው:: እግረ መንገድም እስከወዲያኛው እንዲታጠፍ ተደረገ፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ስለነበርኩ ይህን ዜና ስሰማ አስደንግጦኛል:: በሕይወቴ አብረን በልተናል ጠጥተናል ከምላቸው ሰዎች ጋር በድንገት ተለያይተናል:: በዚህ ወቅት እደነግጣለሁ፡፡ አብረን አስበናል ብዬ ከማምነው ሰው ጋር መለያየ ጊዜያችንም ሳይታሰብ ደረሰ:: ይህ አሳዛኝ ዜና እኔን ብቻ ሳይሆን ተሰብሳቢውን ሁሉ አስደንግጧል፡፡ ከዚቱ ጋዜጠኛ ደረሰ ተክለወልድ "ለምን እግረ መንገድ ታጠፈ?" ሲል ሰብሳቢዎችን ጠየቀው::

"ሰውየው ዝዝ ደራሲ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በዲስፕሊን ጉድለት ዓምዱ እንዲታጠፍ ሆኗል፡፡" ሲል መድረኩን በመምራት ላይ ያለው አቶ ከፍያለው አዘዘ ገለፀና ውይይቱ በሌላ ርዕስ ጉዳይ ላይ አተኮረ፡፡ በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋሽ ሰብሐትን ዲስፕሊን ሊያስተምረው ሲወስን የ62 ዓመት አዛውንት ነበር::

በሐሳቤ ጋሼ ሰብሐት መጣ፡፡ በአንድ ወቅት በእግረመንገድ ላይ ስናወጋ "አንድ ማጂሊያን መጥቶ ከዕድሜዬ ላይ 20 ዓመት ቀንሶልኝ ከዛሬ ጀምሮ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነህ ቢለኝ መጀመሪያ የምወስደው እርምጃ ምን መሰለህ?" አለኝ

"እርምት ክፍል (Proof readers) ሠራተኞችን በሙሉ ሰብስቤ ትምህርት ቤት አስገባቸዋለሁ፡፡ ለምን መሰለህ? የማመሩልኝ መስሏቸው ያላልኩትን እያሉ ያበላሹኛል" አለኝ ተክዞ፡፡

@Amharicbookstore



ከዚህች ትንሽ ብስጭትም ተነሳንስ፡፡ አንድም ቀን እርምት ክፍል ሄዶ "ለምን እንዲህ ታደርጉብኛላችሁ?" ሲል ግን አልሰማሁትም፡፡ በሳምንቱ የጋዜጣ ግምገማ ላይ እርስ በርስ በግልጽ ድክመታችንን አንዱ ለሌላው ስናሳይ እግረመንገድን የሚገመግመው ጎልማሣ ግን ሁሌም ለሥራው አክብሮቱን ይቸረው እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ ጋሼ ሰብሐት የዓምዱን መታጠፍ አልሰማም፡፡ እኔም አልነገርኩትም፡፡ በሚቀጥለው እሁድ ጓደኞችን ሰይፈ ሠማ ቤት ምሣ ተጋብዘን አብረን እንውላለን፡፡ እንዴት ልነግረው እንደምችል ሳብሰለስል ያዋየኋቸው ጓደኞቼም አለመንገሩን መርጠው በዝምታቹ እንድፀና መከሩኝ፡፡ ከእኔ ይልቅ ደምሴ ፅጌ ውብ በሆነ መልኩ እንደነገረው ፀሐይ አሜወተችኝ፡፡ ተደሰትኩ፡፡ ደምሴ፡ ጋሼ ሰብሐት፣ ዛሬ መጥፎም ጥሩም ዜናዎች እነግርሃለሁ፡፡ ከጥሩው ዜና ልጀምርልህ፡፡ ትኩሣት ዛሬ ገቢዮ ላይ ውሏል፡፡ ይህ ድንቅ ዜናዬ ሲሆን፣ አሳዛኙ ደግሞ እግረመንገድ ታጥፎአል አለው፡፡

በዚህ ውብ አቀራረቡ ደምሴን ሳገኘው አመሰገንኩት፡፡ በዚያ ሰሞን ቅዳሜ ቀን ተረት በፈር ሔድኩ፡፡ ዜና ሰብሐት ምሣ ጋበዘችኝ፡፡ ከጋሼ ጋር ከተመገብን በኋላ መጨዋወት ጀመርን፡፡ የዚያን ዕለት ጋሼ ለለውጥ ያህል ጠጅ ነበር የሚጠጣው፡፡ አጠጣጡ እንደተለመደው በውሃ እየበረዘ ነው፡፡

"ጠጅም በውሃ መበረዝ አለበት?" ለእኔ አዎን፡፡ ጣዕሙን ስለማልወደው በውሃ አሸንፍዋለሁ፡፡" አለኝ፡፡

በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ስንጨዋወት ቆይተን ስፈራ ስተር አቆይቼው እግረ መንገድን አነሣሁ፡፡

"ልክ ነህ፣ አለመናገርህ፡፡ ከመንገር ይልቅ አለመንገሩ ጥሩ ነው ብለህ አስበህ ይሆናል፡፡" አለኝና አንዴ ጠጁን ተጎንጭቶ "እግረ መንገድ ይታጠፋል ብዬ ከገመትኩት በላይ ቆይቷል፡፡ አሠራራቸውን እንደማውቀው ቶሎ ቶሎ ነው ዓምድ የሚቀያይሩት፡፡ ሊያጥፉት ሲዘጋጁ ቢታ ፈልግ ዓምድህን ልናጥፋው ነው፣ ብሎ የነገረኝ የለም፡፡ ለእኔ ግን ምንም ልዩነት አያመጣም፡፡ አሁን የእንባዚዬ ዓይነት ይለወጣል፣ ቁጥሩም ያንሣል እንጂ The Sun የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ላይ ሥራ ጀምር ብለውኛል፡፡ ደሞዙ እንደሆነ ከአዲስ ዘመን እኩል ነው፡፡ The Sun ላይ የሚሠሩት ጋዜጠኞች በቅርቡ ምዕራፍ የሚል የአማርኛ ጋዜጣ ስለሚጀምሩ አንድ ዓምድ ይዤ ሥራ እጀምራለሁ፡፡" ብሎ አበሰረኝ፡፡ እንጀራ ቅቤ ጠጣ፡፡

በቀደም ዕለት እፎይታ ቢሮ ሄጄ ተስፋዬ ገብረአብን አገኘሁትና "አሁን ጤናማ ሆኛለሁ፣ በዚህ ጊዜ በጣም ያስፈለገኝ ሥራ ነው ብዬ ሳልጨርስ "እዚህ ጀምራ! አለኝ፡፡

ትልቅ የምስራች ነበር፡፡ ተደሰትኩ፡፡ በአሁኑ ሰዓት ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ወቅት ጋሼ በእፎይታ ጋዜጣና መጽሔት ላይ ይጽፋል፡፡ ቢጋዜጣው ላይ በረከተ ብዕር የሚል ዓምድ ያዘጋጃል፡፡

## ፴፫

## ድርሰተ ስብሐት

አጋፋሪ እንደሻው የእውነት ታሪክ ናቸው ከ! ታሪኩን የነገሩኝ እማሆዩ ጣዲቄ ነው የምንላቸው የተረት ሠፈር ሴት ናቸው፡፡ ቡና ስንጠራቸው የራሳቸውን ስኒ ይዘው ነው የሚመጡት፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ሴት በቂ ሲኒ የላትም፡፡ ሰፈሩ ድሃ ነው፡፡ ስለዚህ እማሆዩ የእራሳቸውን ሲኒ ይዘው ይመጣሉ፡፡ የዜና እናት በደጉ ሰዓት ለሰው አዛኝ ናት፡፡

ከእማሆዩ ጋር ከቀብር ተመልሰው ይወጋሉ፡፡ የትምወርቅ "እንዲያው እንደዚያ ሞትን ሲሸሹ አልሞትም ሲሉ ይሙቱ?!" ብላ በጣም አዝና ተናገረች፡፡

አብሬያቸው ቁጭ ብያለሁ፡፡ መድኃኒቱን ወሳሰጂ ነቃ ብያለሁ፡፡ ጸኸኑ እማሆዩ "ታዲያ ምንድነው? እንኳን እሳቸው ደጃች ሳህለ ጆርጊስ ሞተዋል!" አሉ፡፡

ያን ጊዜ ብልጭ ብሎ ታየኝ፡፡ ሞትን የሚሸሹት ሳህለ ጆርጊስ ናቸው፡፡ "እንዴት እማሆዩ?" አልኳቸው፡፡ በኋላ አጋፋሪ እንደሻው ጆልኳቸውን አብረውን የኖሩትን ገፀ ባህሪ ታሪክ ነገሩኝ፡፡ እንደነገሩኝ ጻፍኩት፡፡ ልዩነቱ በነገሩኝ ላይ የጨመርኩት አጋፋሪ እንደሻው የትም ቢሄዱ የሳምንት ስንቅ ተጭኖ የሚከተላቸው ስንቂ የሚባል በቅሎ ነበራቸው፡፡ የምትል ዐረፍተ ነገር ጨምሬበታለሁ፡፡

ደጃዝማች ዳኛቸው አሉልህ፡፡ ሕይወትና ሞት የገባቸው፡፡ አጋፋሪ እንደሻውን "ምነው በተቻለኝና ሞትህን በሞትኩልህ!" ይሏቸዋል፡፡ ደጃዝማች ዳኛቸው የእራሳቸውን እንጂ፣ የሌላን ሰው መሞት አልተፈቀደላቸውም፡፡ ማን የማንን ሞት ይሞታል? ፋንታውን እንጂ! እ! ግን ያዝኑላቸዋል፡፡

አንዴ ከበአሉ ጋር ስለ አጋፋሪ ስንጨዋወት እንዲህ አለኝ "አጋፋሪ እንደሻው ሁላችንም ናቸው፡፡"

@Amharicbookstore



ያልከው ልቦለድ አጽመ ታሪኩ እንዲህ ነው፡፡ ያች ከሞት የምትሸሸው የአጋፋሪ እንደሻው ነብስ በአፄ ምኒልክ ዘመን ነበረች፡፡ በጃንሆይ ዘመን ወደ መጨረሻው አቶ አልዓዛርን ሆና ትፈጠራለች፡፡ እንግዲህ ያው ገፀ ባህሪ ናቸው ማለት ነው፡፡ ሁለቱን ለማገናኘት የጠለፍኩት ሐረግ አሁን ምን እንደሆነ ይጠፋኛል፡፡ እሱን ረጅም ልቦለድ ስጽፍ ምዕራፎቹ ራሳቸውን የቻሉ አጫጭር ልቦለድ ነበሩ፡፡ ምዕራፎቹ ደግሞ ተጠረቃቅመው አንድ ላይ ቢነበቡ ራሱን የቻለ ረጅም ልቦለድ ናቸው፡፡

ብዙዎቹ አጫጭር ልቦለዶች የፈጠራ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ በገሃዱ ዓለም ኑሮዬ የገጠሙኝ ናቸው፡፡ አሁን 'አምስት ስድስት ሰባትን' ውሰድ፡፡ እሱ መጽሐፍ ውስጥ 'አሮጊቷና እናት' እንዲጋጠሙኝ የጻፍኳቸው ናቸው፡፡ ሌሎቹ የፈጠራ ናቸው፡፡

ክምቡጠር? እሱማ ምናባዊ ፈጠራ፣ የመንፈስ ጨዋታ ነው፡፡ ለምሣሌ ኮተት ያልኩት አጭር ልቦለድ ውስጥ ጨዋታውን ውሻ ቢያስበው የሚል ሐሳብ በመንፈሴ መጥቶልኝ ነው የጻፍኩት፡፡ ያንን ሰው እንደተነጋገረው ብታደርግ አይታመንም፡፡ ውሻ መሆኑ ግን ለተዓማኒነቱ ያቀርበዋል፡፡ በዚያ ላይ ክምቡጠር የተጎነጫትን አልኩል አትርሣ...

አዎን፡፡ ሁሉቱም ላይ የኤሚል ዞላ ተከታይ ሆኜ ነው የምታገኘኝ፡፡ ድርሰቱን ሳልጀምር በፊት ከእውነታው ዓለም አያሌ ደብተር ሙሉ ማስታወሻ ወሰድኩ፡፡ በኋላ ቅርፅ እየሰጠሁ መጻፍ የእኔ ተግባር ሆነ፡፡ ማለትም ባህርያቱ እንደ መጡልኝ ድንጋይ፣ አሸዋ፣ ሲሚንቶን እያስማማህ እንደ ምትገነባው ማለት ነው፡፡

እዚያው መጽሐፍ ውስጥ እንደምታያቸው ናቸው፡፡ ስማቸውን፣ መልካቸውን፣ ለውጬዋለሁ፡፡ አንዳንዴም ለትረካው እንዲያመች የምጨምረውም የምቀንሰውም አለ፡፡ የትኩሳት ዋና ገፀባህሪ ባህሪም ደንበኛ ሰው ማን ነበር? መሐመድ አሲያያ፡፡

ማኑን አልፈጠርኩትም፡፡ የእውነት ሰው ነው፡፡ ማኑ መጥቶ ባህሪያምን ወደ ኢራን መውሰዱ ነው ፈጠራ የሆነው እንጂ ሌላው ሁሉ የሆነ እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ መሐመድን አስፈቅጄው በቃለ ምልልስ ማስታወሻ እየወሰድኩ ነው የሠራሁት፡፡

ሌቱም አይነጋልኝ ላይ ያሉት ባህሪያትም በሕይወቴ ውስጥ የገጠሙኝ ናቸው፡፡ የእነርሱ ማስታወሻ ብዙ ደብተር ፈጅቷል፡፡ እነዚህንም ልክ እንደ ትኩሳት መልክና ስም ቀያይሬ ተጠቅሜባቸዋለሁ፡፡

የትኩሳት መጽሐፈ የመጀመሪያው ርዕስ የሳጥናኤል ኮከብ ነበር፡፡ የእኔ አስተዳደግ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለነበር የመጀመሪያው

አብዮተኛ ለእኔ ሳጥናኤል ነው። ስለዚህ መጽሐፌን የሳጥናኤል ኮከብ አልኩት።

ከዚያማ የቀይ ኮከብ ጥሪ ሆነ። አወረድነው ወደ ምድር። ይህንን ርዕስ በዓሉ ግርማ ፈለገው። "ለእኔ ሥራ ቆንጆ ትመስላለች" አለኝ። 'take it!' አልኩት። እንኪንም የወሰዳት። ትኩሳት የበለጠ ርዕስ ሆነ።

እህ! ይህውልህ። በርናርድ ሾ ይመስለኛል ያላት። ለእኔም አባባሏ እውነት ናት። "በሃያዎቹ ዓመታት ዕድሜው አብዮተኛ ያልሆነ ሰው፣ ከአርባ ዓመታት በኋላ አብዮተኛ ሆኖ የቀጠለ ሰው፣ ሁለቱም ደደብ ናቸው" ይላል። ወደ 20 ዓመትህ አብዮተኛ ካልሆንክ ውስጥህ ምንም የለህም ማለት ነው። በቃ መቀለብ እንደ ከብት እየነዱህ መንገድህን መቀጠል ነው። 40 ዓመት ስትደርስ ግን ኦ! ያ ሁሉ ዓለምን ፈንቅለን ሰማይን ሰንጥቀን እናደርጋለን የሚለው ኃያልነት ይበርዳል፤ ትሰክናለህ።

ሁል ጊዜም ግለሰቦች አሉ። ወይም እ! እላይ ቤት (ወደ ሰማይ እየጠቆመኝ) የታቀደ ነገር ቢኖር እነርሱ ናቸው ሰበብ። አለዚያ በምድር ላይ ከሆንን ግለሰቦች ናቸው ምክንያቶቹ። ለጓደኛህ ታሪየለህ እኮ። አይታተምም። የዚያን ጊዜ ማስበው በማምት የልጅ ልጆቼ ያማትሙትና ብዙ ፍራንክ ያገኙበታል ብዬ ነበር የማምነው። ጓደኞቼ አነበቡትና ለምን ለብዙ ሰው እንዲዳረስ እኛ ኤዲት አናደርገውም? አሉ። እኔም 'ትኩሳት' ሆኖ አገኘሁት። እኛ ያሰብነውን ረጂም ዘመን ቆርጠው አሳጥረው አግዩን። አሁን የቀረው አስር ዓመት ቢፈጅ ነው። አንባቢው ይነግና ደራሲው እንደጻፈው እናንብበው ይላል። እንግዲህ የዚያን ጊዜ የልጅ ልጆቼ ያማትሙታል ያልኩት በእኔ ዕድሜ ታትሞ አየሁት።

የመጀመሪያውን ያላነበበ ሰው ስለማያውቅ ምንም አይመስ ለውም። በተለይ የባህራም የአገር ፍቅር ጠንካራ ስሜቱ ለጨዋነት ተብሎ መጽሐፉ በአርትኦት ቃላቱ ቢነካካም እንደ ነገሩ አንባቢ ጋ ይደርሳል።

ዋናው ገፀ ባህሪ ለእኔ ኤክስ አን ፕሮቨንስ ናት። ሁልጊዜም ኤክስ የትም አለችበት። እስዋ ነች ለእኔ ተወዳጅ ገጸ ባህሪ። በነገራችን ላይ ትኩሳትን አሁን አጥቼው እንጂ እንደገና ባነበው ደስ ይለኝ ነበር።

በሰላሳ ዓመት ልዩነት፣ እኔ ሌላ ሰው ነኝ ማለት ነው። ትኩሳትን አሁን ከታተመ በኋላ እንዴ አንብቤዋለሁ። ሌላ መጽሐፍ ባልፅፍም በቂ ነው የሚል ስሜት ነው ያማደረብኝ። "ቴክኒካሊ ያኔ አሪፍ ነገር ለይቼ ስለማላውቅ ሥራው አሪፍ መሆኑ አይገባኝም

@Amharicbookstore



ነበር። ግዙፉ ባህራም ነው። ቀጥሎ ነጋሪው ገፀ ባህሪ ነው። እሱ ደግሞ ደራሲ ነኝ እያለን ነው። ሐሳብ አልመጣልህ ሲለው ኤክስን ከፀጥታዋ ጋር ሲዞራት ያመሻል።

የመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ባህራምና ተራኪው አሜሪካኖቹን ሲያባርሯቸው የሸሹት ወደ ቀኝ በኩል ነበር። ባህራምና ተራኪው ግን ወደ ግራ ነው የሚሄዱት። ያን ጊዜ የፃፍኩት ሆን ብዬ አይደለም። እሱ ራሱ ነው ስነ ጥበባዊ መከፈቻ የሆነው። የትግላቸው ሁሉ ተምሳሌት ሆነ።

ፈረንሳይ አገር በሄድኩ ጊዜ ውቤ በረሀ ውስጥ ያማለፍኩትን ሕይወት የሚያሳይ ብዙ ማስታወሻ ይዤ ነው የሄድኩት። ለእኔ ከኑሮ ሁሉ ከባድ የምለው የገበሬን ነው። በዝናብ፣ በፀሐይ፣ በሀሩር፣ በውርጭ መልፋት አለበት። ከዚያ ቀጥሎ (እንዲያውም የሚብሰው) የሴተኛ አዳሪ ኑሮ ነው። ከማትፈልገው ወንድ ጋር ብዙ ጊዜ ትሄዳለች፤ ለእንጀራዋ ስትል። በጣም ያማዝናል። እዚያ ውስጥ ፍቅርም ስቃይም አለ። ይህ ሕይወት ነው ሌቱም አይነጋልኝ። መጽሐፉ የተጻፈው በፈረንሳይ ኤክስ አን ፕሮቫንስ በምትባል ትንሽ ከተማ ነው። ትኩሳትን ደግሞ ፈረንሳይ ማስታወሻ ይዤ አዲስ አበባ ውስጥ ጻፍኩት።

ትኩሳት ውስጥ ባህራም 'ፖዘቲቭ' በማሰብ ከፍቅር የተነሣ ነው አብዮቱን ማካሄድ የሚፈልገው። ሰባተኛው መልአክ ውስጥ ግን ከፍቅር ሳይሆን ከቂም በቀል የተነሳ ስርዓቱን ለማፈራረስ ነው። በኋላ እነ መንጌ በአገራችን እንዳደረጉት ማለት እኮ ነው።

ያሲን ኢራናዊ አይደለም። ሰባተኛው መልአክ ውስጥ ያለው ገፀ ባህሪ ያሲን አረብ ነው። እውነተኛው መነሻዬ ቬትናማዊ ነው። በኋላ ሳስበው ለእኛ አገር ሰው ቬትናም ይርቃል። እንደ ቋንቋ ማለት ነው። የቬትናም ሳይሆን የአረብ ጭንብል ሰጠሁት። ሰውዬው ግን እንዳለ ያው ነው።

አንድ ገፀ ባህሪ ኢራናዊ ነው። ምን ሆንክ? ባህራም ትልቅ ሰው ነው። በፊት ደግሞ ስናየው ኢራን ትልቅ መንፈሳዊ ሀብት ያመነጨች አገር ናት። ከእርሱ ጋርም ተገናኝቶብህ ነው" አለና ወፍራም ሣቁን ለቀቀው።

ለመጻፍ ደስ የሚለኝ? ቤቴ አልጋዬ ውስጥ ገብቼ ትራሴን ተደግፌ መጻፍ እመርጣለሁ። ያ ሳይሆን ሲቀር ሐሳብ ሲመጣ የትም ለመጻፍ እገደዳለሁ። በዚህ በኩል ችግር ቋለብኝም።

እ! ይህ ይለያያል። በታና ሁኔታውን አስቀድመህ አታውቀውም። ለምሳሌ ዶስቶዬቭስኪ የሚጥል በሽታ ነበረበት። መዳን

እንደማይፈልግ ይናገር ነበር፡፡ ምክንያቱም ሊጥለው ሲል ብልጭ የሚሉለት ውብ የፈጠራ ሐሳቦች አሉ፡፡ ድርሰት ልክፍት ነው፡፡ ይህንን ያህል ከበሽታም ጋር ያፋቅርሃል፡፡ እኔም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሐሳብ ብልጭ ቢልብኝም፣ በደንብ ሕሊናዬ መቅረጽ የሚጀምረው ጠዋት ጠዋት ነው፡፡ ሰዓቷ ጥሩና ፀጥ ያለች ነች፡፡ ለማብሰልሰልም ሆነ ከራሴ ጋር ለመወያየት ሰፊ ጊዜ ይኖረኛል፡፡

ቋንቋ ምንጩ? ማኅበረሰባችን ነዋ! እኔ የምጽፈው ሕዝቡ እንደሚያወራው ነው፡፡ አሮጊቷ «ምን ቂጥሽን ትቆያለሽ» ቢሉ እኔ ስፅፍ «ምን ቂጥሽን ትቆያለሽ? አሉ ብዬ ነው እንጂ 'ምን እዚህ ትሽከረመሚያለሽ? ታሽቃብጫለሽ' ብዬ አልጽፍም፡፡ ስለዚህ እነ ሳንሱር ይመጡና የይሉኝታ ይሉኝታ የማኅበረሰብህን አባባል አሳመርን ብለው ይገድሉታል፡፡ ሳንሱር ያው የውጪ ሰዎች ቢያነቡት ምን ይሉናል ብሎ እኮ ነው፡፡ የውጪ ሰዎች አሰፍስፈው 'ምን ይጽፋሉ?' ብለው የሚጠብቁን ይመስል፡፡ የራሳቸውን ጣጣ ማሳደድ ትተው የእኔን ችግር አያስተውሉም፡፡ ስለዚህ አንዱ ጠላቴ ሳንሱር ነው፡፡ ቀጥሎ ድህነትም፣ ስንፍናም፣ ግዴለሽነትም፡፡ እና እኔ ጽፌያቸዋለሁ፡፡ ጊዜያቸውን ጠብቀው ለኅብረተሰብ ይደርሳሉ፡፡ ይልገባው ካለም ቀረበት፡፡ እኔ እንደሆነ ደስ እያለኝ ነው የጻፍኳቸው፡፡ ለአንባቢዎቼ ቢደርሱ እጥፍ ይሆን ነበር ደስታዬ፣ በተረፈ መጻፌ ለእኔ በቂዬ ነው፡፡ ለእንጀራዬ የምፅፈው ጋዜጣ ላይ ነው፡፡ መጽሐፎቼን ግን ለእራሴ ፍላጎት ስል ነው የጻፍኳቸው፡፡

አንተም ገበሬን በገበሬነቱ፣ ሽሌንም እንደ ሽሌነቷ ማነጋገር አለብህ፡፡ አንተ ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን ልሣን ማን ከርክም አስተካክል አለህ? እንደተፈጠሩበት ኅብረተሰብ በነፃነት ሕይወታችውን ማሣየት ነው ግዴታህ፡፡ ሳንሱርን እርሳው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ዓለምን ያጥለቀለቀው ሳንሱር ባለመደረጉ ነው፡፡ አበሻ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ቢሆን ኖሮ የዳዊትና ኦሪዮን ፍጻሜ፤ የትዬለሌ ውሽማዎች ቁጥር አታነባትም ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የምወደው ከሥነ ጽሑፍ ውበቱ ጋር የሰውን ልጅ ከነጉድለቱ ስለሚያሳየኝ ነው፡፡ ተአምረኛነቱም ያስደንቅሃል፡፡

እኔ አንድም ቀን እታተማለሁ ብዬ ጽፌ አላውቅም፡፡ ነገር ግን ሕይወትን ከነቡትሯ እጥፋታለሁ፡፡ እኔና ጓደኞቼ እናነበዋለን፡፡ በዚህ ተነጋግረን ደስ እሰኛለሁ፡፡ ሌላው ሐና አለችልህ፡፡ እንደ ወረደ የጣፍኩትን ማታ ጋደም ብለን፣ ከንፏን አንተርሣኝ አነብላታለሁ፡፡ አንድ ጊዜ በጣም ተደሰተችና እቅፍ አርጋኝ፣ "You are my author" ብላ ሳመችኝ፡፡ 'የእኔ ድንቅ ደራሲ!' ማለቷ ነው፡፡ ለምንም ነገር

@Amharicbookstore



ስትናገር እንግሊዘኛ ነው የሚቀናት፡፡ ከዚህ በላይ ሽልማት ጠብቄ አላውቅም፡፡"

"እየህ በፊት...ሰዎች ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ሲሉኝ እንዲህ ያደርገኝ ነበር" አለኝ የመሰቅጠጥ አኳኋን እያሳየኝ፡፡ "በቃል መግለጽ ቢያስፈልግ ይዘገንነኝ ነበር ልልህ እችላለሁ፡፡ ደስ አይለኝም አጠራራቸው፡፡ ግን የእኛ ሰው ሲጠራህ ማንጠልጠያ ይወዳል፡፡ ተማሪ እገሌ፣ ነርስ እገሊት፣ ወታደር እገሌ ይልሃል፡፡ ለማኝ እገሌ አለማለቱ ግን ጨዋነት ነው፡፡ ደራሲ ብለው ለጠፉብኝ፣ እንጂ እኔ ደራሲ ነኝ አልልም፡፡ ሙሉ ደራሲ ነኝ አልልም፡፡ ድርሰት ሚስቴ አይደለችም፤ ውሽማዬ ነች፡፡

እኔ እኮ ጊዜውን አይቼ ነው የምራመደው፣ የምፅፈው፡፡ ተፈጥሮዬ እንደእዚያ ነው፡፡ ለምሳሌ በደርግ ጊዜ የማትፅፍባቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በተወሰነ ነገር ላይ በልኩ እንድትፅፍ ይፈቀድልሃል፡፡ ሕዝቡም እነርሱን ብቻ ነው እንዲያነብ የሚፈለገው፡፡ እኔ ሞኝ አይደለሁም ሌላ ነገር የምፅፈው፡፡ አሁን ግን በግምት ሳስተውል እንደልብህ መፃፍና መናገር ትችላለህ፡፡ አሁን የሚታዩኝን ለአንባቢዎቼ በተለይ ለወጣቱ መጻፍ እፈልጋለሁ፡፡ እኔ ዕድለኛ ሆኜ ያጋጠሙኝና ያነበብኳቸው መጽሐፍት ብዙ ናቸው፡፡ እነዚያን መጽሕፍት ከአዕምሮዬ እያወጣሁ ባካፍላችሁ ደስ ይለኛል፡፡ ይህንንም እያደረግኩ ነው፡፡

***

«ኃይለመለኮት መዋዕል ዘብሔረ ማጀቴ! ታትሞ የመነበብ ወግ ደረሰን፡፡ ዕድሜ ላንተና ለአረፋዓይኔ የውለታ ውለታ ነው»

ወንድምህ ስብሐት ለአብ

1981ዓ.ም

ኃይለመለኮት መዋዕል፦

«አምስት ስድስት ሰዓትን ለማሳተም ዋናው ትልቁ ሐሳብ አመንጪ አረፋዓይኔ ሐጎስ ነው፡፡ ምክንያቱም ከጋሼ ስብሐት ጋር በጣም ይቀራረባሉ በጣም ይዋደዳሉ በቅጡና በደንብ አሳምሮ ያውቀዋል፡፡ «ጋሼ ስብሐት ይኼንን ያህል የሥነ ጽሑፍ ሰው ሆኖ እያለ እንዴት አንድ መጽሐፍ እንኳን በስሙ ሳይታተም ይቀራል» እያለ በጣም ይቆጫል፡፡ «መታተም አለበት» ብሎ ወስኖ ከያሉበት እነዚህን አጫጭር ታሪኮች አሰባሰባቸው፡፡ ከእኔ ጋር ስንመካከር እኔ ከጉንጉን ያገኙትን ገንዘብ የተወሰነ አዋጣሁ፡፡ አረፋዓይኔም የራሱን ጨመረበትና እንዲ ልናሳትመው ወሰንን፡፡ ለደረሰው ለጋሼ ስብሐት አሳታሚ የሚከፍለውን መጠን 10 ፐርሰንት ልንከፍለው ወሰንን፡፡ 10ሺ ኮፒ አሳተምን፡፡ ይህ ድርሰቱ በሚፈጥረው ዝና ላይ መነሻ አድርገን ሌሎች ድርሰቶችንም ልናሳትምለት አቀድን፡፡ ሌሎች ሊያግዙን የሚችሉ ሰዎች

እናገኝ ይሆናል ብለን ተነጋግረን ነው ወደ ሥራው የገባነው፡፡ ስብስቦቹን ጋሼ ስብሐት እንዲያያቸው ተደረገና ስብስቦቹ በሙሉ የእርሱ ኦርጂናል ሥራዎቹ መሆናቸውን አንብቦ አረጋገጠልን፡፡ በሌ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡ ከመጀመሪያዎቹ ሕትመቶች አምስት ሺ ኮፒ ገደማ በደህና ሁኔታ ተሸጠ፡፡ የሽያጭ ሥራውን የሚያካሂደው ክብሩ ክፍሌ ነበር፡፡

መጽሐፉ 1981 ዓ.ም ነው የመጀመሪያው ሕትመት የወጣው፡፡ ቀደም ብዬ እንዳልኩት አምስት ሺ ከተሸጠ በኋላ ሽያጩ ቀጥ አለ፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ በገበያ ላይ ብዛት ያላቸው የትርጉም ሥራዎች ወጥተው ነበር፡፡ ይህ የትርጉም ሥራ ገበያውን ስለተቆጣጠረው በጋሼ ስብሐት ሥራ ላይ ተፅዕኖውን አሳረፈ፡፡ ይሁን እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ይፈልጉታል ተብሎ የተወሰነውን ሲገዙ የቀረውን ግን ዋጋ ተቀንሶ በአንዳንድ ብር ገደማ ተሸጠ፡፡ መጀመሪያም የመጽሐፉ አንድ ኮፒ ዋጋው ሶስት ብር ነበር፡፡ በመጨረሻ ላይ ለጋሼ ስብሐት የሚገባውን ከፍለነው እኔና አረፈዓይኔ 500 ብር አገኘን፡፡

ከእዚያ በኋላ ሌሎች ሥራዎችን መቀጠል አሰብን፡፡ ይሁን እንጂ 1983 ዓ.ም መጣ፡፡ ከዚህ በኋላ ሁላችንም እንደምናስታውሰው በጣም ከፍተኛ የጋዜጣና የመጽሔት ሕትመት ተጀመረ፡፡ የአንባቢውን ቀልብ ስለታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ያዘው፡፡ በዚህ ወቅት ምንም ዓይነት ሐሳብ ላይ የነጣጠረ መጽሐፍ ቢጻፍ ደራሲው የሚያነብለት ሰው ያገኛል ማለት አይቻልም፡፡"

***

፴፬

## ገፀ ባህርያቱ

በአሉ ግርማ ደራሲው የሚባለውን ሳይፅፍ የቀይ ኮከብ ጥሪን ደረሰ፡፡ ይህንን መጽሐፉን እያነበብን ተወያየን፡፡ በሁሉም ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንጨዋወታለን፡፡ በዛው ጨዋታ መካከል እምአእላፍ የተባለው ገጸ ባህሪ ተነሣ፡፡ እምአእላፍ ትልቅ መጽሐፍ የሚወጣው ባህሪ እንደሆነ ነገርኩት፡፡ እርሱም በደራሲ ላይ ሊፅፍ ያቆበቆበበት ወቅት ነበር፡፡ አንድ ቀን "እኔ በደራሲ ላይ ልፅፍ ፈልጌያለሁ ራሴን መነሻ ባደርግ ልክ አይመጣልኝም፡፡ ስለዚህ አንተን መነሻ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡ ፈቃደኛ ነህ ወይ?" አለኝ፡፡

"በጣም ጥሩ" አልኩት "ምክንያቱም በአሉ ነው በዚያን ጊዜ በጣም አንባቢ ያለው፡፡ የእኔን ሕይወት መነሻ አድርጎ ከፃፈ፣ በኋላ



የእርሱ አንባቢዎች በሙሉ እኔን ሊያነቡኝ ተዘጋጅተው ነው የሚጠብቁት፡፡ ስለዚህ በሐሳቡ ተስማማሁ፡፡ "

"እንግዲህ የሕይወት ታሪክህን ንገረኝ?" አለኝ በአሉ፡፡

አጫወትኩት፣ ደራሲውን ጻፈው፡፡ መጽሐፉ ወጥቶ እንዳነበብኩት የተጻፈው የእኔ ታሪክ ግማሹ ነው፡፡ የተቀረው የእራሱ የፈጠራ ውጤት ነው፡፡

"ከበዓሉ ሥራዎች እኔ የምወደው ሀዲስ ነው፡፡ በንሉ ኖሮ እሮማይ ቢሞት የእኔ ምርጫ ነው ያልከኝ? ትክክል!" እንደ ጥይት ጮኸ፡፡

ልክ ነህ፡፡ ድርሰት ልክፍት ነው፡፡ ባለበት መጠበቡን የሚተው አይመስለኝም፡፡ በአሉ ጎበዝ አዘጋጅ፣ ድንቅ ሚኒስትር ነበር፡፡ ከዚያ በመቀጠል ነው ደራሲነቱን የማደንቀው፡፡ አሪፍ ነበር፡፡ አሪፍ የምትለው እኮ ካንተ ሲበልጥ ነው፡፡ ተወው! ምንም አይደለም፣ ሞት እዳ ነው፡፡ እኛ እስካለን ጊዜ ድረስ እኛ ውስጥ ያለው በአሉ በሕይወት እንዳለ ይቆጠራል፡፡ 'ሁለት ሶስት በሆናችሁበት በመካከላችሁ አለሁ!' የሚለውን አባባል አስታውስ" አለኝ በተመስጦ እንጋገር፡፡ ከዚያም በረጂሙ ተነፈሰና ፀጥ ብሎ ቀረ፡፡ የዓይኑ ብርሃን ውስጤን የሚመረምር ይመስል አላላውስ አለኝ፡፡ ወጋችን በዓይኖቻችን ብቻ ሆነ፡፡ ውስጤ በፀጥታዬ ፀንቶ ያወጋነውን የኋሊት እየጠነጠንኩ አብሰለሰል ጀመር፡፡

"እ!" አለኝ ፈገግ ብሎ፡፡

ማታ ወደ አንድ ሰዓት ጀምረን የምናመሽባት አንዲት ግሮሰሪ ነበረች፡፡ የምንዝናናው በርሱ ቮልስ ዋገን መኪና ውስጥ ሆነን ነው፡፡ እንደ አጋጣሚው ቁጥራችን ከፍም ዝቅም ይላል፡፡ ፈቃደ አዘዘ፣ አስፋው ዳምጤ፣ ደበበ ሰይፉ አብረው የሚኖሩበት ጊዜ አለ፡፡ እንጨዋወታለን፡፡ ቦዩ የበአሉን መኪና ያውቃታል፡፡ እየሮጠ ይመጣል፡፡ አንድ ብር ጉርሻ ይሰጠዋላ!

እዚያ የሚመጣ አንድ ዓይነ ስውር የበአሉ ደንበኛ ነበር፣ ለእርሱም አንድ ብር ይመፀውተዋል፡፡ አንድ ምሽት በአሉ "ይሄ ሰውዬኮ ዓይነ ስውርም ለማኝም አይደለም፡፡ እኔን የሚሰልል የደህንነት አባል ነው" አለኝ፡፡

"እናቴን! ታዲያ ለምን ልክ ልኩን ነግረን አናባርረውም? የምን ብር መገበር ነው!?" አልኩ ገንፈል ብዬ፡፡

"ተው እንጂ! የማውቀውን ሰላይ ካባረርኩ እኮ የማላውቀውን ሰላይ ይተክሉብኛል" አለኝ፡፡

እንዲ! በቀይ ኮከብ ጥሪ ላይ ስንጨዋወት ገፀ ባህርያቱ እንዳሉ የፕሬስ ጋዜጠኞች ናቸው፡፡ ይህንን ተመልክቼ "ለምን ባህሪያቱን

@Amharicbookstore

በማይታወቅ መልኩ አትቀርፃቸውም? ግፋ ቢል የተፈጠረው ባህሪውና ጓደኞቹ ካወቁት በቂ ነው፡፡ አንተ ግን ስትቀርፅ ሁሉም ይኼኮ እከሌ ነው እስከሚሏቸው ለምን ታሳያቸዋለህ? ለወደፊቱ ግን መልካቸውን የአካላቸውን ቅርፅ ቀይረህ ብትጠቀም ጥሩ ነው አልኩት፡፡

"ልክ ነህ" አለኝ፡፡ በወቅቱ ስንነጋገር በአባባሌ እንዳመነበት እርግጠኛ ነኝ፡፡ በኋላ ግን ቀደም ብሎ እንደሚጠቀመው ኦሮማይ ላይም ስማቸው ብቻ ተቀይሮ መልካቸውና ጠባያቸው ግን እንኳን ለገፀ ባህርያቱ ለእኛ ለአንባቢዎቹ ወለል ብሎ ይታየናል፡፡ ያም ሥራው ችግር አመጣ" አለና ጥቂት ቆዝሞ ለራሱ እንደሚያወራ ሁሉ በለሆሳስ ድምፅ "በአሉ መልኩም፣ ቁመናውም ጠባዩም በጣም ያማረ ሰው ነበር፡፡ በአሉ ሞቶ ከሆነ 'አይገኝምና እንዳማሩ መሞት' የሚሉትን የአንዳንድ ጊዜ ሕግ ጥሶታል፡!

ቀደም ብዬ ፎቶግራፍ አስመስሎ ስለመቅረፅ ለበአሉ ነገርኩት ያልኩህን አስታውስ፡፡ ሌላው፣ ካሰኘህ ራስህንም እኮ መቅረፅ ትችላለህ፡፡ ግን መለዋወጡን አትርሣ፡፡ ለምሳሌ ሶመርሴት ሞምን ልጥቀስልህ፡፡ ሞም ተብታባ ነው፡፡ እና ምን ሆነ መሰለህ? ሞም ራሱ ዋናው ገፀባህሪ ሆኖ አይንተባተብም፣ ሲቀይረው በተቆለመመ እግር ያነክሳል፡፡ እንዲህም ይፈጠራል፡፡

ይኸውልህ ኧርነስት ሄሚንግወይ እንደ ሶመርሴት ሞም አንዳንድ ገፀ ባህሪያቱን ከገሃድ ዓለም ነው የሚወስዳቸው፡፡ ከነዚህ አንዱ በጣም ተናደደ፡፡ በሦስት ቀን ዕድሜ ውስጥ ሊገድለው እንደወሰነ መልዕክት ላከበት፡፡ ሄሚንግወይ ምን ደንታው፣ ትከሻውን ሰበቀ፡፡ ግዙፍ ነው፡፡ በባዶ እጁ ቢመጣ ይጨፈልቀዋል፡፡ ፍልሚያም ቢጠይቀው ያደገበት ነው፡፡ እጠብቅሀለሁ አለው፡፡ ጠበቀ፡፡ ሶስቱ ቀኖች አለፉ፡፡ ገዳይ አልመጣም፣ ተገዳይም አልገሰገሰም፡፡ አንድ ቀን ግን ተገናኙና ገዳይ ሚችን ይቅርታ ጠየቀው፡፡

ልቀጥልልህ፡ አንተ እኔን እየጠየክ እንደምትጥፈው ነው ፓፓ ሄምንግወይን የደረሰው ሰውዬ እየተከታተለ የጣፈው፡፡ ልዩነቱ የእነርሱ ግንዘብ እንደልብ ስለሆነ እስፓኝ፣ ድረስ እየበረሩ እየተዝናኑ ነው የጣፈው፡፡ ደራሲው ሆችነር ይባላል፡፡ ሲነግረን ሄምንግወይ አንድ ጓደኛ አለው፡፡ ወደፊት ሊሰራ ስለሚያስበው የፈጠራ ሥራ ሁሌ ያወራለታል፡፡ ያኛው ያደምጥና በሚቀጥለው ቀን ያችን ሐሳብ በጋዜጣ ይፅፋታል፡፡ ሲያበዛው ጊዜ ሄሚንግወይ ተናደደና "እንዳየሁህ እገድልሃለሁ!" ብሎ ላከበት፡፡ በበነጋው ያ ሰውዬ ውቅያኖስ ተሻግሮ ገለል አለ፡፡

@Amharicbookstore



እኔ ስጽፍ እያየሁ እየተከታተልኩ ገፀ ባህርያቱን እያስፈቀድኩ ስለሆነ ለድርሰት ሥራዬ የምጠቀምባቸው ችግር አልፈጠረብኝም፡፡ በ"ሌቱም አይነጋልኝ" ድርሰቴ ውስጥ ዋናው ገፀ ባህሪ ከንፈ አይቴን ያጋጠመው ብሎ አንድ ገጠመኝ አጫወተኝ፡፡ ደስ ብላኝ ስለነበር በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ጣፍኳት፡፡ በኋላ መጻሕፍትን ሳነብ ይህችው ገጠመኝ ማርክ ትወይን ድርሰት ውስጥ እንዳለች ተጥፋ አነበብኳት፡፡ የእኔ የአበሻ ስትሆን፤ የትወይን የአሜሪካ ከመሆንዋ በቀር ታሪኳ እንዳለች ያችው ነበረች፡፡ ሳይታወቀኝ 'unconsciously' ከማርክ ትወይን ሰረቅኳት፡፡

መዳፎቹን ወደፊት ዘረጋና "የምንጨዋወተው በሕይወት ዙሪያ ስለሆነ ለወደፊትም ለመፃፍ የምታስብ ወጣት ደራሲ ስለሆንክ ገፀ ባህሪያትን እየጨማመርን እናውጋ፡፡

አንዲት በዚያን ጊዜ የማውቃት ቆንጆዬ ልጅ ነበረች፡፡ ወፈር ያለች ደስ የምትል፡፡ የደርግ አባል ፍቅረኛ ነበራት፡፡ ከእርሱ ጋር ያሳለፈችውን ሕይወት ስታጫውተኝ በጣም ነው ያዘንኩት፡፡ ድሮ በሼክስፒር ሥራዎች ውስጥ ያነበብኳትን ጥቅስ ያስታውሰኛል፡፡ 'አክሊል የደፉ ጭንቅላት ምንጊዜም ተመችቷት አትጋደምም' ይልሃል፡፡ ያልኩህ ልጅ ቁንጅናዋ ብቻ ሣይሆን ተፈጥሮ ግልፅና ማራኪ ባህርይን ሰጥቷታል፡፡ ከእኔ ጋር ሸርክ ነን፡፡ ገጠመኞዋን ታጫውተኛለች፡፡ የደርግ አባሉ አንድ ቀን አቅፎዋት ይደሰታሉ፡፡

ሌላ ሰውዬ ደሞ ነበራት፡፡ «አንድ ቀን ከላዩ ላይ ሆኜ ወደታች ሳየው መልኩ አስቀያሚ ነው፡፡ አንሶላውን ሳብ አድርጌ ፊቱን ሸፈንኩና ደስታዬን ቀጠልኩ» አለችኝ፡፡ እንዲህ ዓይነት ልጅ ነበረች፡፡

የሚወስዳት ራሷ ቤት ነበር፡፡ 'አፓርተማ' ላይ ነው የምትኖረው፡፡ ወደቤት እንደገቡ ክፍሉን፣ በመቀጠል ደግሞ ቦርሳዋን ይፈትሻል፡፡ ከዚያም ሽጉጡን አውጥቶ ትራስ ስር አድርጎ ነው የሚያቅፈኝ ብላኛለች፡፡ ይህ ለእኔ በጣም አሳዛኝ ነው፡፡ ምናልባትም በጊዜው የሰማሁ ዕለት ውስጤ ሳያለቅስም አይቀር፡፡ ይህ የደርግ አባል ከመቶ ሃያ ንጉሦች አንዱ ነው፡፡ ከመሰሎቹ ጋር ቃላቸው ሁሉ ሕግ ሆኖ ስንትና ስንቱን ደምስሰዋል፡፡ ግን ፍቅረኛውን እንኳን ለማቀፍ ያለበትን ጭንቀት አየህልኝ?" አለና አማተበ፡፡

ይህች ገፀ ባሕሪ አድርገን የቀረጽናት የደርግ አባል ፍቅረኛ ቆንጆ ልጅ በፀረ አብዮተኝነት ታስራ ተፈትታ አገኘኋት፡፡ እቤቷ ይዛኝ ሄዳ ቡና አፍልታልኝ ስንጨዋወት "እንዴት ፈቱሽ?" አልኳት፡፡

"አራት የተለያዩ ባለሥልጣኖች ተደስተውብኝ ለቀቁኝ" አለቺኝ፡፡

ኃይለመለኮት መዋዕል፡-

«በአሉ ግርማ አሮማይን ለጋሼ ስብሐት አንብቦለታል። በአሉ ቮልስዋገን መኪና ነበረችው። እሷ ውስጥ እየተዝናኑ ነበር በየጊዜው ያነበበለት። የተናገረው ነገር አይረሳኝም። በአሉ ግርማ በአሮማይ መዝዝ ነው ደብዛው ጠፍቶ የቀረው። አንተ ጓደኛው ሆነህ ለብዙ ዓመታት እየተዋወቃችሁ እየተቀራረባችሁ መታረም የለበትን ሁሉ ማረም ነበረብህ። እኛ በአደባባይ መናገር ይቀተንን እሱ ተናገረልን። ለእኛ ግሩ ነው እሱን ግን አጣነው ለጊዜውም ቢሆን ለምን ተው አላልከውም? » አልኩት።

ቢቱዋ ትዝ ትለኛለች። ወደ ማጀቴ እየሄድን ሳለ ደብረሲና ዝቅዝቀት ላይ ልንደርስ የጣርማ በርን ዋሻ እንዳለፍን ቀንዷ ተራራ ታየኝ ። ተራራዋ በዳኛቸው ወርቁ አደፍርስ ድርሰት ውስጥ አለች። በሷ መነሻ ነው የበአሉንም ጉዳይ ያነሳሁበት። ይኼን ኢየወጋን ቆላ ወረድን። እሱም ሲመልስልኝ «120 ንጉሦች (የደርግ አባሎች) ባሉበት አገር 119ኙቹ ቢወዱልህ አንዱ ከመሀል ከጠላው ሊያጠፋህ ይችላል ይቆይ ብዬው ነበር» ብሎታል።

«በአሉ ግርማ ግን ከወቅቱ ፕሬዚዳንት ከመንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር ቅርርብ ስለነበረው እምነቱን በሳቸው ላይ የጣለ ይመስላል። ጋሼ ስብሐትም ሲያጫውተን ፕሬዚዳንቱ ስልክ ደውለው ሊጠሩትም ይችላሉ። አልያም በአሉ ደውሎ ይሄዳል። መጽሐፉንም አስነብቧቸዋል። በዚህ የተነሳ አደጋ እንደማይደርስበት ገምቷል። ውጤቱ ግን የተገላቢጦሽ ሆነ።

ይፍራታ ሄደን መካከ ላይ ቁጭ ብለን ልዩ ልዩ አርዕስቶች እያነሳን ስናወጋ ቆየንና ጋሼ ስብሐት በጀርባው ተንጋለለ። እኔም ጋደም አልኩኝ። «ምን እየየህ ነው?» አልኩት።

«ዳመና» አለኝ።

በነገራችን ላይ ጋሼ ስብሐት ደመና ማየት በጣም ደስ ይለዋል። እኔም አወዳለሁ። ቅርፁን እየለዋወጠ ሲሄድ እንቅስቃሴውና የሚፈጥራቸው ሥዕሎች ደስ ይሉኛል።

«በአሉ ግርማም ተፈጥሮን በጣም ይወዳል። እጅግ በጣም ያደንቃል። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም የምሽት ፀሐይ ስትጠልቅ ታፈዘው ነበር። ይኼኔ ተመለስ ብዬ እንደገና ወደ ጨዋታችን የሚመጣበት ወቅት ነበር» ብሎ ጋሼ ስብሐት አጫውቶኛል።

***

@Amharicbookstore



፴፫

## ተርጓሚዎቹ

አንደኛ ሳህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም፣ ሁለተኛ መስፍን አለማየሁ፣ ሦስተኛ ባሴ ሀብቴን ልጠቅስልህ እችላለሁ። አንብቤ የወደድኩላቸው እነዚህ ናቸው። በተለይ *ሲራኖ ደ ቤርገራክ በሚል ርዕስ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፈ አንድ ቴአትር አግኝቼ ከመውደዴ የተነሳ እንዲያነበው ለባሴ ሰጠሁት። የአማርኛ ትርጉሙ ከፈረንሳይኛው እኩል ድንቅ ነው። እሱ ፈረንሳይኛ ባያውቅም በማገርም የተለየየ የስንኝ ግልቢያ አለው፡ ልክ በፈረንሳይኛው ምት የሚሄድ ነበር አተረጓጎሙን ሳየው።

እንዴ? ምን ነካህ? የሲራኖ ደ ቤር ገራክ ቴአትር ገፀ ባህሪያት በግምት 50 ይሆናሉ። ያንን ሁሉ ተዋናይ እኛ አገር የት መድረክ ላይ ልታጫውታቸው ትችላለህ? ስለዚህ አይታይም።

እሱክ በመድረክ እንዲታይም እንዲታተምም አይደለም የፃፈው። ለራሱ ለግል ደስታው ነው የተረጎመው። እና እኛ ጓደኞቹ ደስታውን ተጋራነው።

ከበደ ሚካኤል ትምህርታቸው የፈረንሣይኛ ስለነበር የብዙዎቹ ሥራዎቻቸው ምንጮች የፈረንሣይ ቋንቋ ነበር። እንግሊዘኛም ያነባሉ። ሥራዎቻቸውን ስታይ ከእነዚሁ አገሮች የወሰዷቸውን ወደ አማርኛ ቋንቋ በማምጣት አስነብበዋል። መደነቅ ይገባቸዋል። በዘመናቸው ለነበረ ትውልድ በትክክል የተፈጠሩ ደራሲ ናቸው። አሁን ላለንበት ዘመን አንባቢ ግን እንጃ።

ሥራዎቻቸውን ተመልከት። ሞራል ይበዛበታል። የድሮው ትውልድ በጽሑፍህ ውስጥ ሞራል ጨምረህ ስታቀርብለት ፀጥ ብሎ ይቀበልሃል። ይኼኛው ትውልድ ግን 'Idea'ውን አንተ ትጽፍለታለህ፣ እርሱ ሞራሉን ያውቅበታል፣ ከፈለገ ይጨምርበታል፣ ወስዶ ያጣጥማል።

ማሞ ውድነህን እንዲያውም አላነበብኩትም፡፡ ይኸውልህ ኩራዝ አሣታሚ ድርጅት በምሠራበት ወቅት ከፈጠራ ሥራዎቹ እቁብተኞችንና እድርተኞችን እኔ ነኝ አርታኢ የነበርኩት፤ በእዚያ አጋጣሚ ነው እሱን ለማንበብና ከእሱም ጋር ለመወዳጀት የቻልኩት፡፡ በብዙ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተጨዋውተናል፡፡ ቀልድ ማውጋት ያውቅበታል፡፡ መንግሥት ላይ ግን ሁሌም ይነጫነጫል፡፡ አንዴ ጠይቀው «እኔ እንጃ፣ ሳስተውል መንግሥት ላይ ጉድለት አላጣም፤ ስለዚህ መንግሥትን ለማረም መነጫነጭ ደስ ይለኛል" ሳይለኝ አይቀርም፡፡

ከማሞ የማደንቅለት ብርቱ ጎኑ በማኅበራዊ ሕይወት ጥሩ ተሳትፎ አለው፡፡ ለምሣሌ አንድ የታወቀ ሥም ያለው ኢትዮጵያዊ ቢያርፍ፣ ማሞ ተሯሩጦ የቤተሰቡን ጡረታ ለባለቤቱና ለልጆቹ ማስከበር፤ ገንዘብ አሰባስቦ መርዳት፣ ልጆቹ የሚያጋጥማቸውን ችግር ፈትቶ ትምህርት ቤት ማስገባት ከማሞ ተግባሮች የማደንቀለት ነው፡፡ ደግሞ በሄደበት መሥሪያ ቤት በሩ ቀድሞት ወለል በሎ ተከፍቶ ይጠብቀዋል፡፡ እሱም ያውቅበታል አቀራረቡን፡፡ ለእኔም በአንድ ወቅት ችግር ላይ እያለሁ ደርሶልኛል፡፡

የትርጉም ሥራዎቹ እንደኔ ዓይነቶቹ በተፃፈበት ቋንቋ ለማንበብ ለቻደልነው ብዙም የማያስፈልጉን ቢሆንም፣ የቋንቋ ችሎታው ኖሯቸው መጽሐፉን ለማያነቡና በአንተ ዕድሜ ላሉት ወጣቶች የማንበብ ልምዱን እንዲያዳብሩ ጥሩ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ የሚያውቁትን ለአንባቢያን ለማዳረስ የጣሩ ብዙ የምትጠቅሳቸው ሰዎች የሉም፡፡ ቢኖሩም ከአውራዎቹ አንዱ ማሞ ነው፡፡ አንተስ አላነበብከውም?

ይኸውልህ፡፡ ሻምበል አፈወርቅን ስታነሣ አንድ ነገር ትዝ ይለኛል፡፡ አሮጌ መጽሐፍት ነጋዴዎች ጓደኞች አሉኝ፡፡ መደብራቸው ሄጄ ሳይ ለበርካታ ጊዜ የሻምበል አፈወርቅ ማኅተም ያለባቸው መጻሕፍት አጋጥመውኛል፡፡ ድንቅ፣ ድንቅ የሆኑ ሥራዎችን አንብበ ነበር፡፡ ባየኋቸው ቁጥር ሥራዎቹን ማሰቤን አስታውሳለሁ፡፡" አለና እንደማዘን ብሎ እጆቹን ወደፊት ዘረጋና "እንግዲህ የሚተካው ልጅ ሳይኖረው ቀርቶ፣ ወይም ወልዶ እንዳባቱ የማንበብ ፍቅር ሳይኖረው ቀርቶ፣ አልያም ሌባ ሠራተኛ ቀጥሮ መጻሕፍቱን እየሸጠ አንባብያን አካባቢ አድርሷቸዋል ስል አስባለሁ፡፡

"የሻምበል አፈጠርቅ ልጅ አልተማረም?" ጋሼ ጓጉቶ ጠየቀኝ፡፡

እንደ እዚያ ከሆነ የመጻሕፍትን ጥቅም ያውቃል፡፡ ለማንኛውም መጻሕፍት አይደለም ሞተህ፣ በሕይወት እያለህም በልዩ ልዩ መንገድ

@Amharicbookstore



ከእጅህ ወጥተው ገበያ ላይ ታገኛቸዋለህ፡፡ አንዳንድ ሰው ደግሞ አለልህ የመጻሕፍት ቀበኛ፤ እኔንም እንዲህ ዓይነት ሰው አጋጥሞኛል፡፡ አነሰ ቢባል አንድ አራት መጻሕፍት መንትፎኛል፡፡ አንዴ ይህ ሰው ቤቱ ምሳ ጋበዘኝ፡፡ እኔ ደግሞ መጻሕፍት ካየሁ እጄም ዓይኔም አያርፍ፣ ከመደርደሪያው ላይ እየገላለጽሁ ማየት ጀመርኩ፡፡ መጻሕፎቼን አገኘኋቸው፡፡ ስሜ በማርከር ተሰርዞ የእርሱ ስምና ፊርማ በመጻሕፍቱ ላይ ሰፍረዋል፡፡ አይቼ እንዳላየሁ በመሆን እነበሩበት መልሼያለሁ፡፡

ቢነቃስ? እሱ ግድ የለውም፡፡ እኔም መጻሕፍቶቼን ካነበብኩ በኋላ አልፈልጋቸውም፡፡ ምንም አልመሰለኝም፡፡ ምሣችንን በልተን፣ ተጨዋውተን ተለያየን፡፡

ሌላ ወጣት አርቲስት አለ:: በእንግሊዘኛ Shop lifter የሚባል ዓይነት አመል አለበት:: ሁሌም መጻሕፍቶቼን ይሰርቀኛል:: የሚደንቀው የሚሸጣቸው እኔ የማዘወትርበት መጻሕፍት መደብር ውስጥ ነው:: ለምን እንዲህ ታደርጋለህ ብዬው «ምን ሳድርግ አመሉ አለብኝ:: የግድ ልሰርቅህ ባሕሪዬ ያስገድደኛል:: አንተም የጠፉብህን መጻሕፍት መልሰህ እንድታገኛቸው አስቤ ነው የምትውልበት የምቀጣረው» ብሎኛል::

ራስን በራስ ማስተማር ብለህ ማሞን ስታነሳብኝ ጳውሎስ ኞኞ ትዝ አለኝ፡፡ እኔ ልብ ውስጥ ጳውሎስ ደፋር ነበር፡፡ አንዴ ምን አደረገ፣ የወሎ ሕዝብ መራቡን ሰማ፡፡ ያን ጊዜ በግልህ ምንም ማድረግ አትችልም ጃንሆይ እያሉ፡፡ ጳውሎስ ግን በሬዎች አረደና የተራበውን የወሎን ሕዝብ አበላው፡፡ ሰው በሌለበት ሰውዬው ጳውሎስ ሰው ሆኖ አየሁት፡፡

የሥነ ጽሑፍ ሥራዎቹን ካነሳን ዘንዳ፣ ለልጆች ጨዋታ ይፅፍ የነበረ ሰው በእኛ አገር የማውቀው አንድ ጳውሎስን ነው፡፡ አምዱ 'ይድረስ ለጋሼ ጳውሎስ' የምትል ነበረች::

ይኸውልህ፡፡ ጳውሎስ ደፋር፣ ራሱን በራሱ ያስተማረ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ሰው ነበር፡፡ ጳውሎስ ደፋሩን አሳይቼሃለሁ፡፡ ጳውሎስ ብዙውንም አስተዋልን:: ይህ ሰው ግን መሃን ነበር፡፡ ልጆችን እሱ ያስደሰት እንጂ፣ እሱ ከአብራኩ ባለማፍራቱ አዝናለሁ" አለና የጋሼ ድምፁ ሰለለ፡፡ እንባው ቅር አለ፡፡

አቤ ምኒልክ የሚል ታሪካዊ መጽሐፍ ጽፏል? አላነበብኩትም። እንዲያውም!" አለ ጋሼ "በማሪያም አምጣልኝ፡፡ ምኒልክ እኔ ውስጥ ሕያው ናቸው፡፡

ወደ ቀጣይ ጥያቄዬ በሳቅ ሰረገላ ተሸጋገርን፡፡ "የሣህለ ስላሴን ሺኒጋስ ቪሌጅ አንብቤያለሁ፡፡ በቃ፡፡

የዳኛቸው ወርቁን 'ዘ ሰርቲንዝ ሰን' በጣም አሪፍ ነበር ጅምሩ፤ ግን ዳኛቸውን ለምን በእንግሊዘኛ ለማንበብ እዳክራለሁ ብዬ ተውኩት፡፡

እንዴ? አደፍርስን ካነበብኩ በኋላ ዳኛቸውን በእንግሊዘኛ ላነበው እፈልጋለሁ እንዴ?" አለና ሎሚ "ይመስልሃል?! ዳኛቸውን ባላውቀው አነበው ነበር፡፡

እንዴት ነው የሁለቱም የቋንቋ ጉልበት? በማሪያም! ዘነበ፣ ጋዜጠኛ እየሆንክ ነው፡፡ እንደ ሚ.ጠ.ጠ. ጋዜጠኛ ጥያቄ አታብዛ...

"ጋዜጦች ላይ በእንግሊዘኛ ብዙ ጽፌያለሁ አይደለም እንዴ? ታዲያስ?" አሁንም ሎሚብኝ፡፡

"እህህህህ" ወፍራም ሳቁን ለቀቀው፡፡ "ግዴታ 'አክስፎርድ' መሔድ አለብን እንዴ? እነሣህለ ስላሴና ዳኛቸው ሄደውልናል፣ ውክልናውንም ለነርሱ ሰጥተናል" አለኝ ፈገግ ብሎ እያየኝ "የት ነን? ውል ማስያዝ ያንተ፣ ማጫወት የእኔ ነው፡፡ የፈለከውን ጠይቅ" አለኝ ኮቱን እያወለቀ፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ እያወጋኝ ይለብስና መልሶ ደግሞ ያወልቀዋል፡፡ ይህንን ሲያደርግ ንግግሩ ከአካሉ ጋር ነው፡፡ ሲበርደው ይደርባል፣ ሲሞቀው ያወልቃል ተነስቶ ቆሞ አካላቱን እንደማፍታታት እያደረገ በተመስጥኦ ያስተውለኛል፡፡

***

* ባሌ ሀብቴ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ የተረጐመው ሲራኖ ደ ቤርዤራክ በሰንዱ አበበ አማካኝነት 2000 ዓ.ም ለሕትመት በቅቷል፡፡

@Amharicbookstore



፴፮

# ንባበ ስብሐት

'አንድ አፍሪካዊ መንደር ውስጥ የሚኖር ሽማግሌ ሞተ ማለት፤ አንድ ትልቅ ቤተ መጻሕፍት ተቃጠለ ማለት ነው'

እምቦዋ

ፓሲፊክ ከዓለማችን ግዙፍ ውቅያኖስ ነው፡፡ ስለ ጥልቀቱ ሳይንቲስቶች በማይል፣ በፋቶ ሜትርና በኪሎ ሜትር ለጥራዝ ባበቋቸው ድርሳናት ውስጥ እማኝነታቸውን ገልጸዋል፡፡ ደራሲ ሉዊስ ጆንሰን 'ወተር' በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ በቃል ስለው ያሣዩናል፡፡

"አይቻልም እንጂ የሚቻል ቢሆን የዓለማችን የየብስ አካል ቁንጮ የሆነው ኤቨረስት ተራራ እንዲትም ድንጋይ ሳትናድ አንስተን በፓሲፊክ ውቅያኖስ ውስጥ ብናሰጥመውና የተራራውን አናት መርገጥ ብንፈልግ ሁለት ኪሎ ሜትር ወደታች መዋኘት ይኖርብናል፡፡" ሲሉ የዚህን ሰፊ ውቅያኖስ ጥልቀት ያሣዩናል፡፡

የስብሐት ገብረእግዚአብሔርን የንባብ ልምድ ለማወቅ ስንነጋገር ጥልቀቱ ልክ እንደ ፓስፊክ ውቅያኖስ ነው የራቀብኝ፡፡ የምፅፈው ስለ ደራሲ ነውና የማንበብ ልምዱን ስመረምር መጠየቅ ቀርቶ መማር ሆነብኝ፡፡ ምናባዊ ምጥቀቱ ራቀብኝ፡፡ በአያሌ ጥያቄዎች በመንፈሱ ውስጥ ዋኘሁ፡፡ እሱም ደስ እያለው አእምሮውን ከፈተልኝ፡፡ በአንደበቱም እያወጋ ዓለምን አዞረኝ፡፡ በዚህ ምዕራፍ የምታነቡት አስራ ዘጠኝ ዓመታት ስንተዋወቅ የበርካታ ከዕለታት አንድ ቀናት ቃለ ምልልስ ያደረኩለትን ስብስብ ነው፡፡

እንደ መታደል ቃለ ምልልሱ የተካሄደው ለመጽሐፍ ስለሆነ በጋሼ ሩቅ በሆነው ሕሊና ውስጥ ጠልቄ የጨለፍኩትን እንድጽፈው አማልክቱ ፈቀዱ፡፡ ዓለም አቀፍ የሥነ ጽሑፍ፣ ፍልስፍና፣ ሃይማኖታዊ... ንባቡን ስመረምር ጥያቄ ሆንኩ፡፡ ጋሼ መልስ ሆኖ ይኸውላችሁ!

"አፍሪካውያን ደራሲያን አፃራቸው የእንግሊዝ ወይም የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ስለነበሩ በገዢው ቋንቋ ነው እያነበቡ ያደጉትና

የሚፅፉት፡፡ እኛ አገር እንደ እዚያ ዓይነት ባሕል አልነበረም፡፡ አብዛኞቻችን የምንፅፈው በአማርኛ ነው፡፡ በእንግሊዘኛ የምንፅፍ ጥቂት ነን፡፡ በወጣትነቴ አማርኛ በምፈልገው መልኩ ሐሳቡን መግለፅ አያስችልም የሚል እምነት ነበረኝ፡፡ በዚህም ላይ ያስተማሩን እንግሊዘኛ ተናጋሪዎች መሆናቸውን አትርሣ፡፡

እኛ አናውቅም እንጂ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ወጣቱን ትውልድ በቅኝ አገዛዝ ጥበባቸው ይዘውናል፡፡ በኋላ ዳኛቸው ወርቁ አደፍርስን ፃፈ፡፡ እኔ ሳነበው በአማርኛ መፃፍ እንደሚቻል ገባኝ፡፡ ስለዚህ በእንግሊዘኛ የመፃፍ ሐሳቤን ተውኩት፡፡ በወቅቱ አስታውሳለሁ ሌቱም አይነጋልኝን በእንግሊዘኛ መጻፍ ጀምሬው ነበር፡፡ 65 የተተየበ ገጽ ላይ አቆምኩት፡፡

ይኸውልህ ሀ፣አ፣ሰ፣ፀ ሁለት ሁለት ናቸው፤ በእኛ ፊደል ውስጥ ያሉት፡፡ ሰለሞን ደሬሳ የአብሮ አደግ ዞኖበት ያለው እውነቱን ነው፡፡ ኮሌጅ ውስጥ ወጣቶች ሳለን እኔ ነኝ መጀመሪያ የምን የሀ ጋጋታ ነው? ዝም ብለን በአንዱ ሀ ፊደል እንጠቀም አልኩትና በአንደኛው ሀ ነበር የምፅፈው፡፡ እሱም መጻፍ ሲጀምር ልጅነትን ሲገጥም ከፊደሎቻችን አንዱን እየወሰደ ነው የፃፈው፡፡ እውነት ለካ እነዚህ ፊደላት ለግእዝ ሀቀኛ ፊደላት ነበሩ እንጂ በእኔ እምነት ለአማርኛው ትርፍ ሸክም ናቸው ነው፡፡

አንዴ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በኪነጥበብ ላይ በሁለት ቡድን ተከፋፍለን ክርክር ይደረጋል፡፡ እኔ መጀመሪያ ክርክሩ ውስጥ አልነበርኩበትም፡፡ አዘጋጆቹ ጓደኞቼ ስለነበሩ 'ይኸውልህ፣ *እነሌ ቀኑ ሲቃረብ ማስታወቂያ ተለጥፎ እንግዶች ከተጠሩ በኋላ እንቢ አለን፡፡ ስለዚህ አንተ በእርሱ ምትክ ብትካፈልስ'' አሉኝ፡፡ እሺ አልኩ፡፡

ርዕሱ? Art for art's sake ወይስ art for education መሰለኝ፡፡ ትዝ ይለኛል፡፡ በተሰጠኝ ርዕስ ስናገር ቆየሁና አቋርጬ ዳኛቸው ወርቁ እዚህ ይኑር አይኑር አላውቅም፡፡ ግን በአደፍርስ ልቦለድ ነብሴ እንዴት ደስ እንዳላት ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ አደፍርስን በማንበቤ በእንግሊዝኛ ጀምሬው የነበረውን ልቦለድ በአማርኛ ልፅፈው ወስኛለሁ፡፡ አልኩና ወደ ዋናው ርዕስ ተመለስኩ፡፡ የክርክሩ ጊዜ አለፈ፡፡ ከሰዓታት በኋላ አንድ የወንዳወንድ ቁመና ያለው ፊቱን ፈንጣጣ የወጋው ጎበዝ መጣና ጨበጠኝ፡፡ ዳኛቸው ወርቁ ሆኝ እልሃለሁ'' አለና ሣቀ፡፡

---------------

* መንግሥቱ ለማ፡ እንዳለ ጌታ ማዕቀብ ገጽ 122

@Amharicbookstore



ከልቤ ነው ይህንን ስልህ፡፡ ብዙ ጊዜ የምለው ነው፡፡ ዳኛቸው ወርቁ ማስተማር ብቻ ማይሆን አስደንቆኛል፡፡ በአደፍርስ መጽሐፉ፡፡ የሥነ ጽሑፍ ህግጋትን አበጥሮ ስለሚያውቅ፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጽሑፍ ጽፌ ለዳኛቸው ነበር የማሳየው፡፡ በግልፅ ነበር የሚያርመኝ፡፡ እሱም ጅምር ሥራዎቹን ያሳየኝ ነበር፡፡ አንድ ድንቅ የሆነች 'ኮሜዲ' ጽፎ ሦስት ምዕራፍ አነበበልኝ፡፡ እንዴት ነበር ያሣቀኝ! በቃ ይህ መጽሐፍ ሲያልቅ አደፍርስ ይረሳል ብዬ ነበር፡፡ ለማንም እንዳልናገር አስጠንቅቆኛል፡፡ ''ሐሳቤን ይሰርቁኛል'' ብሎ ኛል፡፡ ''እኔ ይህንን አባባል አላምንለትም ነበር፡፡ እሱ ስላለኝ ታዘዝ ኩትና ለማንም ተናግሬያት አላውቅም፡፡ ስለዚህም ለአንተም አልነግርህም፡፡''

ይህንን በዳኛቸው ወርቁ ላይ ያነሣነውን ጭብጥ ጋሼ ስብሐት ያለኝ በ1986 ዓ.ም ሚያዝያ ወር ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ሪፖርተሮች ቢሮ ውስጥ ቃለ ምልልስ ባደረግንበት ወቅት ነበር፡፡ ስለዚህ ወደ ሌሎቹ ጥያቄዎች ተሸጋግሬ ተወያየን፡፡

ዓመታት አለፉ፡፡ በሰኔ ወር 1991 ዓ.ም ቀርቀስ እኔ ቤት ተቀምጠን ከጋሼ ስብሐት ጋር ዳኛቸው ወርቁን አነሳነው፡፡ በዚህ ወቅት ዳኛቸው ዓይኑ አፈር ከለበሰ አምስት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ስመ ጥሩው ደራሲ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ኅዳር 22ቀን በ1987 ዓ.ም ነው፡፡

"አ! ትክክል!" አለኝ ጋሼ ስብሐት፡፡ እያብሰለሰለ ሲያዳምጠኝ አስተውለዋለሁ፡፡ "ይኸውልህ! አሁን ልነግርህ ይገባል፡ ዳኛቸው ለኔ ብቻ ነው እንደ ታላቅ ወንድሜ የሆነብኝ፡፡ ሌላ ቦታ ሰዎች ሲያነሱት ስሰማ በባሕሪው እሾህ ነው ይሉታል፡፡ አትንኩኝ ባይ ነው፡፡ ለእኔ ሲሆን ጽኄረዳ ነው የሚሆንልኝ፡፡ እጣችንና የኮከብ መግጠም በለው፡፡ እሱም የሚያየኝ እንደ ታናሽ ወንድሙ ነው፡፡ በዕድሜ እኩዮች ነን፡፡ ነግሬህ ይሆናል፡፡ ግን ከሚያመልጥህ ይህቺን ወሬ ባጫውትህ ይሻላል፡፡

አንድ ጊዜ ሥራ ፈታሁ፡፡ ከቁም ነገር መጽሐፔት እንደ ተሰናበትኩ ነው፡፡ ወደ ዳኛቸው ሄድኩና "ይኸውልህ ሥራ ፈታሁ፡፡ ሥራ እስከምይዝ ጊዜ ድረስ አንተ በወር ሃምሣ ብር ልታበድረኝ ትችላለህ ወይ?" አልኩት፡፡

"እሺ" አለኝ ሳያመነታ፡፡

ከዚያ በልደታ ቀን መሥሪያ ቤቱ እሔዳለሁ፡፡ ምሣ ይጋብዘኝና ሃምሣ ብሬን ይሰጠኛል፡፡ ያችን ይዤ ወደ ቤቴ፡፡ የጎደለኝን ከወንድሞቼ መሙላቴን አትዘንጋ፡፡ የዳኛቸው ልግስና 11 ወራት ቀጠለ፡፡ ከእዚያ ሥራ አገኘሁ፡፡ አንድ ስድስት ወር ሰርቼ የራሴን

ወጪ አስተካክልኩና ወደ ዳኛቸው ቢሮ ሄድኩኝ፡፡ ተጨዋወትንና 200 ብር አውጥቼ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩ፡፡

"ምንድነው ይኼ?!" አለኝ

"ባለፈው አስራ አንድ ወራት ካበደርከኝ ገንዘብ ይኼ ጥቂቱ ነው፡፡ ዛሬ ራሴን ስለቻልኩ መክፈል የምችለውን ነው ያመጣሁልህ" አልኩት፡፡

"ታዲያ በእኔና በአንተ መካከል ብድር አለን'ዴ?" ብሎ ብሩን ወደኔ ገፋው፡፡

ማን እንደነገረኝ አላውቅም፣ እንዲህ አልኩት "አሁን እኮ ዳኛቸው፣ ይህንን ገንዘብ ከወሰድኩት ሌላ ቀን ሲከፋኝ ወደ አንተ'ጋ መምጣት ላልችል ነው፡፡"

እሱም "እሺ አንተ ካልክ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን በእኔና ባንተ መኻል ብድር የሚባል የለም" አለና ሁለት መቶ ብሩን ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ወሰደ፡፡ እኔም በዚህ አጋጣሚ አረታሁት፡፡ በግድ ነው የተቀበለኝ፡፡

"ቆይ ከልቦለዱ ጭብጥ ዳኛቸው ይበልጥብናል" አለና ጋሼ ስብሐት ትዝታውን አከለበት፡፡" ከዕለታት በአንዱ ቀን ከተረት ሰፈር በቸርቺል ጎዳና እጓዛለሁ፡፡ በእዚያው መንገድ ላይ ከዳኛቸው ጋር ተገናኘንና ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ከዚያም ከላይ እስከታች አየኝና "ለምንድን ነው ራስህን ጣል ጣል የምታደርገው?" አለኝ፡፡

"እይ! ደህና ነኝ" ስለው፡፡

"ለጠላትህ ደስ እንዳይለው ራስህን ጠብቅ" አለኝ፡፡

"እንዴ? ዳኛቸው እኔኮ ጠላት የለኝም" ስለው፡

"ቢሆንም!" አለኝ፡፡

ይህች አባባሉ ነች በጣም የምትደንቀኝ፡፡

አንዴ እኔ አደፍርሰን ለሐና አነበብኩላትና በጣም ተደሰተች፡፡ ከእዚያም ስለ ዳኛቸው አወራንና መልክና ቁመናውን አብሰልስዬ ፈንጣጣ ጠቃጠቆ ያበዛበትን ፊቱን ሳስብ በሴት ዓይን ምን ይመስል ይሆን ብዬ በውስጤ አውጠነጠንኩና ሐናን "እንዴት ነው ዳኛቸው?" አልኳት፡፡

"አንተን ቀድሜ ባላፈቅር ዳኛቸውን አልምረውም ነበር" አለችኝ፡፡

ደስ አለኝ፡፡ ዳኛቸው በሴት ዓይን 'ራይት' አግኝቷል ማለት ነው፡፡ ዳኛቸው የሚከብደው ለእኛ ለወንዶቹ ነው እንጂ ለሴቶች የሚደነቅ ብቻ ሳይሆን የሚታቀፍም ሊሆን ይችላል፡፡ መልሰኝ ወደ ጥያቄህ፡፡

@Amharicbookstore



አሁን ወደ ልቦለዷ እንምጣ፣ እንዳልከው ከሞተ በኋላ ሃሳቧ አንባቢያን ሒሊና'ጋ መድረስ አለባት፡፡ ምንድናት መሰለህ? ታሪኳ ስትጀምር እናት ለማኝ ናቸው፡፡ አንድ ወንድ ልጅ አላቸው እየከፈሉ ያስተምሩታል፡፡ ኮሌጅ ተመርቆ አሜሪካ ሄደ፡፡ እዚያም ማስተርስ ዲግሪ ጭኖ ወደ አገሩ ተመለሰ፡፡ እናቱን በሰላም አገኛቸው፡፡

"እማዬ፣ አለፈልን እንግዲህ" ብሎ እንዲመቻቸው አደረገ፡፡ ቤተክርስቲያን ሊሳለሙ ሲሄዱ ዘንጠው ነው፡፡ 'ሁሉም በእጃቸው ሁሉም በደጃቸው' እንደሚባለው ሆነላቸው፡፡

አንድ ቀን ልጅ ባልታሰበ ሰዓት ወደቤቱ ይመለሳል፡፡ አንድ ነገር ሸተተው፡፡ ያንን ሽታ ልጅ ሆኖ በደንብ ያውቀዋል፡፡ ያደገበት የድርቆሽ ፍርፍር ነው፡፡ እናቱ ለምነው ከየቤቱ የሰበሰቡትን የእንጀራ ቁርስራሽ እቤት አምጥተው ያሰጡትና ይደርቃል፡፡ ከእዚያም ይወቀጥና ሲፈረፈር የራሱ የሆነ ጠረን አለው፡፡

ልጅ ወደ ማድቤት ሲሄድ እናቱ ድርቆሹን ፈርፍረው ሲሰሩ ያገኛቸዋል፡፡ ናፍቋቸዋላ! ልጃቸው በድንገት መድረሱ አስደነገጣቸው፡፡ ልጅም ተቆጣ፡፡ "ምነው እምዬ?! ምን አጥተሽ ነው ድርቆሽ ምትበይው?"

እናትም "እሺ ልጄ ይቅር በለኝ አይለምደኝም!" ብለው ልጃቸውን ይለምኑታል፡፡ ሰብሐት እየሣቀ "ሌላ ቀን እናት ቤተክርስቲያን ሄደው ባልተለመደ ሰዓት እቤታቸው ሲመጡ ልጅ ድርቆሹን ፈርፍሮ ለመብላት ሲዘጋጅ ያገኙታል፡፡

ይኸውልህ መነሻህ የትም ብትደርስ እንዴት እንደሚፈታተንህ አሣምሮ ያሣይሃል፡፡ በተለይ በዳኛቸው ጉልበት የቋንቋውን ጥልቀት አስብ፡፡ እነዚህን የጅምር ሥራውን ሦስት ምዕራፍ ያነበበልኝ ሶደሬ በመኪና ሄደን ነበር፡፡ ቆንጆ አበባዎች በግቢው ውስጥ ፈክተው ይታያሉ፡፡ "እስኪ እነዚህን አበቦች እየሞቅን አንብብልኝ" ስለው አሳሳቁ ሁሉ ትዝ ይለኛል፡፡

አንዴ ቆየሁ ቆየሁና፣ "እንዴት ነው፣ መጽሐፍህን የት አደረስካት? እኔ እኮ የመጣሁት የቀረውን ለማንበብ ነው?" አልኩት፡፡

ተናደደ፡፡ ወቅቱ ደርግ በቀይ ሽብር ወጣቶች መግደል የጀመረበት ጊዜ ነው፡፡ እኔ ወሬውን ሥራዬ ብዬ ስለማልከታተል አላወኩም፡፡

"ምን ትላለህ? እዚህ ከረጺ ወደዚህ አንድ ጉድጓድ ውስጥ አሥራ ስምንት ሬሣ ተቀብሮ ሲገኝ! አገራችን እንዲህ ጉድ ስትሆን እያየሁ ሰላምን ከየት አምጥቼ ነው የምፅፈው?" አለኝ።

እሱ ለመፃፍ ሰላም ይፈልጋል። አንዳንዶቻችን ግን እንዲያውም ከእሱም የባሰ እየተሰማን ሁለት ሦስት ቀን ሲዘገንነን ቆይቶ፣ ከዚያ እንደምንም ብለን አልኮል መጠጥ ጠጥተንም ቢሆን፣ መፃፍ እንቀጥላለን። ዳኛቸው ግን ነብሱ ስስ፣ በጣም ስስ ነው። አልቻለም። ከዚህ በኋላ 'ቴክኒካዊ' የሆኑ መጻሕፍትን ነው የፃፈው። ዘይቤያዊ አባባል፣ የአፃፃፍ ዘዴ ምናምን ነው የሠራው። የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ተቀጨ የምለው ዳኛቸው ያችን መጽሐፍ ባለመጨረሱ ነው ..." አለኝና ካቲካላውን ፉት ብሎ በውሃ ተጉመጥምጦ ዋጠ።

ቴዎድሮስ ቴአትርን ከአንድ ዓመት በላይ ተመልክቼዋለሁ!። ሁለት ሦስት አራት ምክንያቶች ይኖሩኛል። አንድ፣ ቴአትሩን የተጫወቱት ተዋንያን ቆንጆ ናቸው። ሁለት፣ አዚጋጁ አባተ መኩሪያ፣ ድንቅ አዘጋጀጀቱን ወድጄለታለሁ። ይህንን ታዲያ ሦስት ጊዜ ማየቱ በቂ ነበር። በዚያን ጊዜ የስድስት ወይም የሰባት ዓመት ልጅ የምትሆነው ዜና አለች። በጣም ያስደስታታል ቴአትሩን ማየት። ደግሞ በአጠቃላይ ተጨዋቾቹን አትርሳ። የማያልቁ ናቸው። በመጨረሻ ፀጋዬ መጣ አንድ ቀን። "ለምንድነው ይኸንን ቴአትር አንድ ዓመት ሙሉ ያየኸው?" አለኝ።

እኔ አሁን እንዳልኩህ ምክንያቴን ደረደርኩለትና፣ "እኔ እናቴን በጣም እወዳታለሁ። የአንተንም ቴአትር ሳይ እናትህን በጣም! በጣም! እንደምትወድ ያስታውቃል። አይደለም እንዴ?" አልኩት።

"አዎን እናቴን በጣም እወዳታለሁ" አለኝ ፀጋዬ።

ወንድ ተዋናዮችን አስመልክቱህ በሕይወትና ሥራቸው ላይ በደበበ እሸቱ፣ በፍቃዱ ተክለማርያምና ሥዩም ተፈራ... ጠዘተ ስለ እነርሱ ጥፌያለሁ። ከሴት አርቲስቶችስ አስናቀች ወርቁ፣ አርቲስቷንም፣ ዘፋኟንም ሴትዮዋንም ነው የምወዳቸው። አቤት አስናቀችን ወጣት ሆነህ ብታያት? እሷን ወጣት ሆኖ ማየት ፈተና ላይ መውደቅ ነበር። ልብህ በኃይል ይመታል።

ከውጪ ሰው ሲጠራኝ "Time out! መስዬ ስብሐት" ብዬ ስነሳ በእግሬ ነካ ያደረኩት የሻይ ብርጭቆ ከንብል አለና መደብ ላይ በተነጠፈው ብርድ ልብስ ላይ ተደፋ። "ጋዴሚት!" አልኩ ሳላስበው።

@Amharicbookstore



"ጋደሚት አይዘንሃወር!" አለ ጋሽ ፈገግ ብሎ።

"ኢንክሉዲንግ ቴክሳስ!" አልኩት።

"እ! አጫውቼሃለሁ?" አለኝ አሁንም እንደፈገገ።

"ይኸውልህ። ይህችን 'ጋደሚት አይዘንሀወር!' ያመጡዋት ኮርያ የዘመቱ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ናቸው። አሜሪካውያኑ ወታደሮች በአገራቸው በወቅቱ ፕሬዚዳንት የነበረውን እዚህ ብሽቅ አገር አዘመትከን ለማለት ሲዘልፉት "ጋደሚት አይዘንሐወር!" ይላሉ። ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች ከኮርያ ዘመቻ መልስ አዲስ አበባ መጥተው በውቤ በረሃ ሲደንሱ ጋደሚት አይዘንሐወርን ፋሽን አደረጓት።

ኢንክሉዲንግ ቴክሳስ? ቴክሳስ ደግሞ ከአሜሪካን ክፍለ ሀገሮች በፌዴሬሽን አልቀላቀልም ብላ በአንድ ከከብ ራሷን ለማስተዳደር የተፍጨረጨረች አገር ነች። በእዚያ አቋሟ ከመዋሃድ መገንጠልን በመምረጧ ነው እሷንም አክለው የሚዘልፏት።" አለና "ጋደሚት አይዘንሐወር!" አለ።

"ኢንክሉዲንግ ኤርትራ!" ስለው ሣቁን ለቀቀው።

እ? በአንድ ወቅት የተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የትምህርትና ባህል ማዕከል (ዩኔስኮ) ዳይሬክተር የነበረው እምቦዋ ነው። የምዕራብ አፍሪካ ተወላጅ ነው። የአገራችንን የታሪክ ቅርሶች አየና አደነቀ። እነ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ሌሎቹም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰው ልጆች የፈጠራ ቅርስነት እንዲመዘገቡ አደረገ። አጫውቼሃለሁ፣ በዚያን ዘመን ፈረንሣይ ቋንቋዋን ከቻልክ የዜግነት ዕድል በቀላሉ ትሰጥሃለች። እንግሊዝ ከሆነ ግን 'አይከነን!' ነው የሚልህ...

ይህ እምቦዋ ምን ይላል፣ "አንድ መንደር ውስጥ የሚኖር አፍሪካዊ ሽማግሌ ሞተ ማለት አንድ ቤተ መጽሐፍት ተቃጠለ' ማለት ነው'።

ያ ማለት እኔና አንተ አሁን የምናደርገውን ማለት ነው። ከማለፌ በፊት የማውቀውን ላቀብልህ ነው ቀጠሮ የተያያዝነው። ስንት፣ ስንትና ስንት ጊዜ እየተገናኘን አወጋን። በወዳጅነታችን መካከል ዓመታት ተቆጥረዋል። አንብበህ አልጨረስከኝም። እኔም እያቀበልኩህ ነው። አየህ አማልክቶቹ ሲፈጥሩን ያለምክንያት አይደለም። ምንም የማያባክኑት ነገር የላቸውም። ስሰጥህ ሳይከፋኝ እንዳቀብልህ፣ ስታነበኝ ደስ እንዲለኝ አድርገው አጣመዱን።" አለና ከርዕሰ ጉዳዮችን ወጣ። በሕይወት ላይ ያለውን ፍልስፍና እያከለባት ወደ ጉዳዮችን እንደሚመለስ ስለሚገባኝ በፀጥታ እከታተለዋለሁ።

"ቅድም ምሣ አብረን አልበላንም? የበላነው ምሣ በአካላችን ውስጥ በተለያዩ ክፍሎች ይከፋፈላል፡፡ ለነብሳችን ኃይልን፣ ለአካላችን ፀጉር፣ ጥፍር፣ ሥጋ ይሆናል፡፡ የተቀረው ይወገዳል፡፡ እዚህ አካላችን ውስጥ አስፈላጊውን ተግባር የሚያከናውኑ አሉ፡፡ እኔና አንተ ግን እየተዝናናን ነን፡፡ ያ ሁሉ ተግባር በሚከናወንበት 'ዩኒቨርስ' ውስጥ አንዱ አባል ነን፡፡ ምስጢሩ በማይገባን ተዓምር ውስጥ ነን፡፡ ስለዚህ የእኔ ተዓምር ማንንም አታስደነግጥም፡፡ ማንንም አታስበረግግም ደስ ትላለች" ከካቲካላዋ ተነነጨ፡፡ ውሃ ፉት ብሎ አፉን አባበሰና በሐሳብ ጭልጥ አለ፡፡

የሚለኝ ሲኖር ራሱ እንደሚያወጋኝ አውቃለሁ፡፡ ብጠይቀው ከምናብ ምጥቀቱ ተመልሶ ወደ እኔ ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ሐሳቡ እንዳይበታተን በፀጥታ በመከታተሉ ላይ ጸናሁ፡፡

"ኢትዮጵያ ስንል ነበር ምቦዋን አንስተን" ዓይኑን ሳያረግብ ቀና ብሎ አይቶ ጠየቀኝ፡፡

ኢትዮጵያን ስታስተውል የሚጠብቃት ሲመጣ የሚያጠቃትም አብሮት አለ፡፡ ለምሣሌ ግራኝ መሀመድ እያጠቃ እያለ ፖርቱጋሎች መጡ፡፡ ሙሶሊኒ ሊያጠቃት ሲመጣ እንግሊዝ ተባበረችላት፡፡ የተቀረውን ደግሞ አንተ መርምር፡፡

ምቦዋን ስናነሣ የእኛ ቤተ መጽሐፍቶች አዛውንቶቻችን ናቸው አላልንም? አንድ ቀን እኔ በፒያሳ በኩል በእንግሊዝ ቤተ መጻሕፍት ደጅ አልፋለሁ፡፡ በጣም ብዙ ልጆች ወደ ቤተ መጻሕፍቱ ገብተው ለማንበብ ተሰልፈዋል፡፡ በጣም አዘንኩ፡፡ ወጣቶቹ ማንበብ ፈልገው የሚነበብ አጥተው ነው ቆመው የሚጠብቁት፡፡ ማንበብ እየፈለጉ ደግሞ ተሰልፈው የሚያነቡበት ቤተ መጻሕፍት እንኳ ያጡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ወጣቶች በመላ አገራችን አሉ፡፡ እኔ ደግሞ ዕድለኛ ሆኜ ብዙ አንብቤአለሁ፡፡ በቃ ለእነዚያ መሰለፍ ላልቻሉ ወጣቶች ልፅፍላቸው ወሰንኩ፡፡ እግረ መንገድ አምዴን ጥሬስ ድርጅት ከፈተልኝ፡፡ ደስ እያለኝ ለወጣቶች የማውቀውን እየጣፍኩ አካፈልኳቸው፡፡ ለእንጀራዬ መጣፊያም እንደተጠበቀ ሆኖ፡፡

እሣሣቂ ከልብ ነው፡፡ ፍንድቅ ብሎ ሲንተከተክ ዓይኖቹ በእንባ ይሞላሉ፡፡ ለሚያየው ሰው በደስታ የሰራ አካላቱ እንዲዝናና የማድረግ ኃይል አለው፡፡ አፍጦ እያየኝ "የት ነን?"

"እሺ! At your service" አለኝ በትህትና፡፡ ከልቡ ነው፡፡ ፊት ለፊቴ ነው የተቀመጠው፡፡ "በጣም ጥቂት ያጋጠሙኝን ደራሲያን ነው ያነበብኩት፡፡ አምጣ ልጣፍልህ፡፡" አለኝ፡፡ ማስታወሻ ደብተሬን ሰጠሁት፡፡ ሲጽፍ በእግሊዘኛው መከተብ ይቀለዋል፡፡ "Wole Soyenka

@Amharicbookstore



" ብሎ ከፃፈ በኋላ ማስታወሻዬን እየመለሰልኝ "ከፀጋዬ ገብረ መድህን በላይ የምወደው ይመስለኛል፡፡ ምናልባትም የውጪ አገር ሰው ስለሆነ አብልጬው እንደሆን እንጂ የቋንቋ ጉልበቱም ሆነ የአፃፃፍ ስልቱ ፀጋዬ ከሶዬንካ ጋር ጉልበቱ አይተናነስም፡፡ አንዴ ሶዬንካ ሲናገር "እንግሊዞች ሲገዙን ቋንቋቸውን በግድ አስተማሩን፡፡ አሁን እንግሊዝኛ ቋንቋዬ ስለሆነ እንዳፈቀደኝ እጫወትበታለሁ፣ የፈለግኩትን አደርገዋለሁ፣ እገለባብጠዋለሁ እንደ አክሮባት" ብሏል፡፡ በአንድ ወቅት ከኖቤል ሽልማቱ በፊት ሌላ ሽልማት ሊሸልሙት እንግሊዝ አገር ጠርተውት ነው ይህችን ያለው፡፡

ሌላ Amos Tutwola የደረሣት The Palm Wine Drinkard የሚላት ሥራውን በጣም የወደድኩለት ነው፡፡ አዎ Tutwola የተማረው እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ ነው፡፡ መጽሐፉን ያረመለት አርታኢው አረፍ ነበር፡፡ የTutwola እንግሊዝኛ የራሱ እንድትሆን አድርጎ መጽሐፉን አረመለት፤ ነገር ግን እንግሊዘኛ ተናጋሪ ሆነው የአፍሪካን ባህል ለማያውቁ ግር እንዳይል ብቻ ነው አርታኢው በድርሰቱ ላይ ብዕሩን ያሳረፈው፡፡ አንዱ ባሕሪው ትዝ ይለኛል፡፡ "ዘ ፐርፌክት ጀንትልማን" ይባላል፡፡ በፓርቲ ላይ ሲዝናና ይታያል፡፡ በሁሉም ነገር ፍፁም ነው፡፡ ፐርፌክት ጀንትልማን ከፓርቲው ይወጣል፡፡ አንድ ቦታ ሲደርስ በር አንኳኩቶ ግራ እጁን አውልቆ "አመሰግናለሁ" ብሎ ያስረክባል፡፡ ይሄድ ይሄድና ሌላ ጋ እንዲሁ አንድ አካሉን እየነቀለ የተዋሰውን ሲያስረክብ በመጨረሻ ፐርፌክት ጀንትልማን የለም፡፡

ለካ ፐርፌክት ጀንትልማን የሆነው ከዚህ ሁሉ አገር አካል እየተበደረ ነው ሙሉና ረቂቅ ሰው ለመሆን የበቃው፡፡ የአንተ ዓይን ካማረችውና ቆንጆ ከሆነች ይበደርሃል፡፡ ከሌላ እግር፣ እጅ እያለ ፍፁም ሰው የሆነው፣ ሁሉንም ሲመልስ ደግሞ ዜሮ ይሆናል፡፡ ይህ ሳስበው ከሐበሻም 'ኢማጅኔሽን' ይርቃል፡፡

ጄምስ ጆርጅ ፊረዘር ጽፎዋት ያስገረመችኝን ልጨምርልህ፡፡ ይህ ደራሲ እየጻፈ ያለበትን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ በብሪቲሽ ኤምፓየር ሊያግዙት የሚፈልጉ ሐሳባቸውንና ልምዳቸውን እንዲያካፍሉት ደብዳቤዎችን ይፅፋል፡፡ መልስ ይልኩለታል፡፡ አንዷ አሁን የማጫውትህ ነች፡፡

ኬንያ ውስጥ ቺፍ ባላባት አለ፤ ታጅቦ ነው የሚሄደው፡፡ ትከሻው ላይ ጣል የሚያደርገው ባለ ኅብረቀለም እንደ ካባ ልብስ አለ፡፡ ትልቅ የኔጥ ልብስ ነው፡፡ ባላባትና አጃቢዎቹ ዛፍ ጥላ ሥር ያርፉሉ፡፡ አርፈው ሲያበቁ ጉዞ ጀመሩ፡፡ ብጣም ከራቁ በኋላ ባላባት ትዝ ሲለው መጎናፀፊያውን ረስቷል፡፡

"አንተ ካባዬን ረግጠህ፡፡ ማነው ሄዶ የሚያመጣልኝ?!" ሲል፣ አንዱ እየሮጠ ቅድም ወዳረፉበት ዛፍ ይሄዳል፡፡ ሲደርስ አንዱ እረኛ ወድቆ አግኝቶት ለብሶታል፡፡ በጣም ደስ ብሎታል፡፡ መልዕክተኛው እንዳየው "አንተ የባላባታችንን ካባ ነው የለበስከው?!" ሲለው እረኛው በድንጋጤ ክው ብሎ ሞተ፡፡

እየህ? በእነርሱ እምነት፣ አይደለም የባላባት ልብስን መልበስ፣ ጥላውንም መጠለል ለሞት ይዳርጋል፡፡ ይህቺ እምነትህ ገደለችህ ናት፡፡ በተልበት ከእምነትህ አዳነችህ እኩል ናት፡፡

አሁን ከምእራብ አፍሪካ ገፀ ባህሪ አንዱ በሰንበት ቀን የጓሮ አታክልቱን ሊከተክት ይወጣል፡፡ አንዴ ሲቆፍር "አይ!" የሚል የሕመም ድምፅ ይሰማል፡፡ ዞር ዞር ብሎ ቢያይ ማንም የለም፡፡ እንደገና ሲቆፍር "አይ!" ይላል ቅድም የሰማው ድምፅ፡፡ ገበሬው ከሚቆፍርበት ዞር ሲል "ምንድነው!? እሁድ እንኳን እረፍት የለኝም እንዴ? መጥተህ ትወጋኛለህ? ሂድ ከዚህ" ስትለው ይደነብርና ይሮጣል፡፡ ትልቅ አለት ላይ ዘሎ ይወጣና ቁጭ ይላል፡፡ ዓለቱ ደግሞ "የማነህ ቂጣም እኔ ላይ የምትወጣ! ውረድ ከዚህ" ይለዋል፡፡ ከዚያ ከዓለቱ ላይ ወርዶ ረዥም መንገድ ይሮጣል፡፡ ከፊቱ አንድ ሰውዬ አህያ እየነዳ ይመጣል፡፡ እያለከለከ ያጋጠመውን ይነግረዋል፡፡ አብዝኀቸው ያለው አህያ ጣልቃ ገብቶ "ለእኔ ነው የምትነግረኝ?!" አለው አህያው፡፡

አንዱ ወጣት ቱትሲ በአንድ ወቅት አጋጥሞኝ ያስገረመኝን ባህል ላካፍልህ፡፡ በወቅቱ ወጣቱ ከሁቱዎች ጭፍጨፋ ሸሽቶ ተሰዶ ነው ከአገሩ የወጣው፡፡ ይሄ የምነግርህ የቱትሲ ጭፍጨፋ የቆየ እኮ ነው፡፡ በቅርቡ የተደረገውን አምላክ የመጨረሻ ባደረገላቸው፡፡ ይህ ወጣት ቱትሲ ከእኔ ጋር የተዋወቅነው ዓለም ፐብሊክ ሪሌሽንስ እየሠራሁ ነው፡፡ ቱትሲው ቆንጆ አሜሪካዊት ጓደኛ አለችው፡፡ እሷ ፍቅር ይዟታል፡፡ እሱም ነገር ግን ያበሳጫታል፡፡ ለምን እንደሚያበሳጫት ጠየኩት፡፡ "ነጭ ሳበሳጭ አንጀቴ ይርሳል" አለኝ፡፡

በእኛ አገር አስተሳሰብ የቲማማተ የምትለው ዓይነት እምነት አለው፡፡ ክርስትና ለዓለም ሕዝብም ሆነ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ኮሎኒያሊስቶች አምጥተው የጫኑብን የእምነት ጣጣ ነው፡፡

"ይህቺ ሴት እኔን ላግባህ እያለች ትወተውተኛለች፡፡ እኔስ አልታደልኩም እንጂ እንደ ዘሮቼ ደንብና ባህል ማግባት ብችል ታላቅ እህቴ አለች፡፡ እሷን ነው ማግባት የመረጥኩት፡፡ እሷ ግን እኔን እንደ ወንድ አታየኝም" አለኝ፡፡

@Amharicbooksoe



እኔም እንዳንተው ጠይቄዋለሁ፡፡ በባህላቸው ነውር የለውም፡፡ በእኛ ባህል አንዲት ልጅ በጋብቻ ለመተሳሰር እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ የሥጋ ዝምድና እንዳይኖራችሁ ይከለከላል፡፡ ሳይንስም ይደግፈዋል፡፡

ለዚህ ቱትሲ ግን ይህ ዓይነቱ ባህል አይደገፍም፡፡ ወይም በእርሱ አመለካከት የኮሎኒያሊስቶቹ ተፅዕኖ ነው፡፡ ስለራሱ ሲያወራልኝ "አሁን እኔን ውሰድ፡፡ የአባቴ ወይም የአጎቴ የየትኛቸው ልጅ መሆኔን አላውቅም፡፡ ምክንያቱም አባቴ በሌለበት አጎቴ ከእናቴ ጋር ማደር መብቱ ነው፡፡ እኔም ወንድሜ ካገባ ሚስቱን እነሆ በረከት ብላት ደምብ ነው" እንዲህ ዓይነት ባህል አለ እልሃለሁ፡፡ የሰውን ልጅ በንባብና በመኖር ዓለም ስትመረምር እያወቅከው በሄድክ ቁጥር የማታውቀው እየላቀ ይሄዳል፡፡

ምን ትቀልዳለህ? ኮሌኒያሊዝም ከመፈጠሩም በፊት፣ ጥንት ጥንት ኢትዮጵያ ክርስትና ተቀብላ በምትኖርበት ጊዜ፣ የዛሬ ገዢዎቹ የጣኦት አምልኮ ውስጥ እንደነበሩ አያውቅም፡፡

ልክ ነህ! አፍሪቃውያን ምሁራን ፌደላውያን ይበዙባቸዋል፡፡ እኛማ እንዲያው ፌደላውያን ነን በባህላችንም፡፡ ኢየሱስ ፈሪሣውያንን ፌደላዊያን ነው ያላቸው፡፡ መኖርን አያሳዩንም፣ መጥቀስ ግን ያበዛሉ፡፡ ልብ ብለህ ስታስተውለው ይኸው አስተሳሰብ የሰው ልጆች ሁሉ ሆኖ የምታገኘውም ጊዜ አለ፡፡ ሩቅ ሳንሄድ እኛም አንድ ለምሣሌ እንጥቀስ፡

ፌሬንዚ የሚባል የሃንጋሪ ተወላጅ የሆነ ሲግሞንድ ፍሮይድ የሚያዝንለት ደቀ መዝሙር ነበረው፡፡ አንዴ ስለ 'ሳይኮአናሊስስ' ንግግርና ገለፃ ሊያደርግ ተጋብዞ ሄደ፡፡ አንድ የፍሮይድ ቲፎዞ "ዶክተር ፍሮይድ እንዲህ አላለም!" ሲል በረዥሙ እየጠቃቀሰ ተቃወመው፡፡ ፌሬንዚም እንዲህ አለ "አንድ ድንክዬ በጣም ትልቅና ረዥም በሆነ ሰው ትከሻ ላይ ቢቆም፣ ከተሸካሚው ይበልጥ ሩቅ ያያል፡፡"

በአጠቃላይ የአፍሪካ ደራሲያንን ፈጠራ ስንመረምር ከራሳቸው ከተፈጠሩበት አገር ሕዝብ ይልቅ የተጠቀሙባቸው በቅኝ ግዛት ገብተው ቋንቋቸውን በሁለተኛ ደረጃ ያስጠኑዋቸው ገዢዎቻቸው ናቸው፡፡ ያገራቸው ሰው ግን የበረከቱ ተቋዳሽ አልሆነም፡፡ ከዚህ አንጻር እኛ ዕድለኞች ነን፡፡ የእኛ አገር ደራሲዎች በአብዛኛው የተጠበቡት በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ በእንግሊዘኛውም የወከሉን የምናደንቃቸው ናቸው፡፡ የጨደፈቱን ለእናንተ ለወጣት ፀሐፍት እንተዋለን፡፡

ይኸውልህ፣ እኛ ለእዚያኛው ዓለም ሩቅ ስለሆን አንድ ሆነው ይታዩናል እንጂ አረቦችና ፔርሺያዎች አንድ ሕዝብ አይደሉም፡፡ እስልምና ግን አንድ አድርጎ ነው የሚያሳየን፡፡ ለምሳሌ ከዚህ ከመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ፐርሻ (ኢራን) ኢንዶ ዩሮፒያን Indo-european ናቸው፡፡ እንደ እንግሊዝ ነው ቆዳቸው የሚመደበው፡፡ ሥልጣኔያቸው በጣም ትልቅና ጥንታዊ ነው፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስም መወለድ በፊት የነበረው ሥልጣኔ የእነሱ ነው፡፡

በፍልስፍናው ሁለት ኃይል አለ ይሉሃል፡፡ አሁራማዝዳና አህሪማን፣ ሰናይና ከይሲ እንደማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ዘለአለም ውጊያ ላይ ናቸው፡፡ ደግሞ ጦርነቱ በነብረት የሚካሄድ ብቻ አይደለም፡፡ አንተም አለህበት፡፡ የለሁበትም ማለት አትችልም፡፡ ወይ በዚህ በኩል ወይም በወዲያኛው በኩል ነህ፡፡ አየኸው ወደ ሕሊናህ ሲመራህ ነው፡፡

እሱን ፍሬድሪክ ኒቼ ነው፤ ዛራቱስትራን ከፐርሺያ ወስዶ ለሚኖርበት ዓለም ፍልስፍናውን ያስተዋወቀው፡፡ እኔ ለምሣሌ አፄ ካሌብን ታሪካቸውን በመጠኑ ወስጄ ልቦለድ ባደርጋቸው እንደማለት ነው፡፡ ኒቼ ያደረገው ዛራቱስትራን ነብሱን ወሰደና 'ሱፐርማን' መሆን ነው አለ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ወይም በመንግሥት ትዕዛዝ አይደለም የምንመራው፣ በውስጣችን ትዕዛዝ ነው ይልሃል፡፡ ይህ ደግሞ ወደ 'ኤግዚስቴንሻሊዝም' ይወስደናል፡፡ እንግዲህ ደስ ወዳለህ መልሰኝ፡፡

ይኸውልህ ጨረቃና መስቀል ብለን ለያየነው እንጂ ሁላችንም የሚቀራረብ ሥርዓት እንዳለን ስታነብ ታውቀዋለህ፡፡ ልዩነቱ እኛ በአገራችን አይርበንም፡፡ በእሸዋው ዓለም የሚኖሩት ጥቂት ናቸው በቁጥር፡፡ ግን ረሀብና የውሃጥም አለባቸው፡፡ በተረፈ እንደ እኛ አንድ ዓይነት ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሰው ሁሉ ከኢንዱስትሪያል አብዮት በፊት ኑሮው አንድ ዓይነት ነበር፡፡

'አረቢያን ናይትስ' ማለት ድንቅ ሥራ ነው፡፡ ይህንን በምሣሌ ላስደግፍልህ፡፡ 'ስኮላር' እንሁን፡፡ ከአቴንስ ነው የምንነሳው፡፡ ሌላ ዴሎስ የምትባል ከተማ አለች፡፡ ሁለቱ ብቻ የሥልጣኔ ምንጮ፡፡ አንድ ላይ ስታረጋቸው ሶቅራጥስ፣ እና አፍላጦን (Plato) እና አሪስቶትል፣ የምንላቸውን ፈላስፋዎች ያስተዋውቁሃል፡፡ ያ የጭንቅላት ማሰብ ነው፡፡

ከፐርሻና ከእስራኤል የመጣው ሥልጣኔ በመንፈስ ማመን ነው፡፡ ጭንቅላት ሌላ፣ እምነት ሌላ፡፡ በሌላ አባባል ሐይማኖት ሌላ፣

@Amharicbookstore



ፍልስፍናና ሳይንስ ሌላ ይሆናል፡፡ አረቢያን ናይትስ ከዚህ በጣም የተለየ ነው፡፡ የአስማት ዘመን ይከሰታል፡፡ ያዚህ ታሪክ ገፀ ባህሪ እንዳንዴ ሱልጣን ሀሩን አልረሺድ ይሆናል፡፡ የታሪኩን አነሳስ ታውቀዋለህ፡፡ ሻህራዛድ ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊት ሌሊት ተረት እንደተናገረች ታስታውሰዋለህ አይደል?

ይህንን አረቢያን ናይትስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪ ሆኜ አነበብኩ፡፡ ገረመኝ ነው የምልህ፡፡ አንዳንድ ሰው ምን ያህል እንደሚያስገርምህ ነው ያስተዋልኩበት፡፡ እንግሊዘኛዋን ደራሲው ልክ እንደ አማርኛ ዘይቤያዊ አባባል እያመጠቀ ጣፋት፡፡ 'የለመኑትን የማይነሣ፣ የነገሩትን የማይረሳ' እንደዚህ፣ እንደዚህ ልክ የግጥም ልሣን ባለው መልኩ 12 ቅጽ አነበብኩ፡፡ ተርጓሚው ይህም አልበቃ ብሎት ሌላ 12 ቅፅ ጨመረበት፡፡

ይህ ቀደም ብሎ ያነበብኩት ከአረቦቹ ተርጉሞልን ነው፡፡ በኋላ ወደ ካይሮ ተጓዘ፡፡ ማታ ማታ የሚያወሩዋቸውን ተረቶች ሰብስቦ መዘገበ፡፡ The New Arabian Nights ብሎ ፃፋቸው፡፡

ደራሲው ሰር ሪቻርድ ኤፍ በርተን ነው ስሙ፡፡ 39 ቋንቋዎችን አጥርቶ ይናገራል ይፅፋል፡፡ እኔ አማርኛን እንደምፅፈውና እንደ ምናገረው፡፡ ያዝክ?

ከሕንድ ጀምሮ መካከለኛውን ምሥራቅ አሣምሮ ያውቀዋል፡፡ መካ ለእሕዛብ ክልክል ነው፣ ክርስቲያንና ነጭን ጨምሮ፡፡ በርተን ታዲያ አስበበት የሕንድ አገር ሼክ እገሌን ተመስሎ መካ መጣ፡፡ አነጋገሯን ሁሉ አጥንቷል፡፡ ተቀበሉት፡፡ መካ መዲና ውስጥ አይቶ መጥቶ ይህንንም ፃፈው፡፡ ይህም አልበቃውም፣ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ መጣ፡፡ በዚያን ዘመን ከመካ መዲና ቀጥሎ እስላም ላልሆነ ሰው የተከለከለች ቅድስት ከተማ ሐረር እኮ ነች፡፡

ሐረርም እንደመካው ሼክ እገሌ ሆኖ መጣ፡፡ ተቀበሉት፡፡ አሥራ አምስት ቀን አስተናገዱት፡፡ በኋላ ይህንንም ፃፈው፡፡ የመጽሐፉም ርዕስ FIRST FOOT STEPS IN EASTERN AFRICA ነው፡፡

እ.እ.እ! አንተ ሐረር ውስጥ ቤቱን ያየህለት ሰው አርተር ራምቦ ነው፡፡ እሱ ሚጢጢ ገጣሚ ነው፡፡ በአስራ ስድስት ዓመቱ አካባቢ መግጠም የተወ፡፡ ከፍሬንች የሃያኛው ክፍለ ዘመን አውራዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሐረር ውስጥ የእሱን ቤት ነው ያየኸው፡፡

በነገራችን ላይ፣ እንደገና ላስተካክልልህ፡፡ ኦመር ኻያም አረብ አይደለም፡፡ፔርሺያዊ ነው፡፡ በእንግሊዞች በኩል ነው የሚመጣልን፡፡

ከአረቦች ዘመናዊ ሥነጽሑፍ በጣም በጥቂቱ አንብቤያለሁ፡፡ በጣም የሚደንቅ ግብፃዊ ነው፡፡ ቶፊክ አልሀኪም ይባላል፡፡ The Fate

<u>of a Cockroach</u> ነው የምትለው ተውኔቷ፡፡ የበረሮዎች ዕጣ እንደማለት ነው፡፡ በረሮ ነው ዋናው ገፀ ባህሪ፡፡ በረሮው ባኞ ቤት ነው የሚኖረው፡፡ ገረዷ መጥታ ባኞውን እያፀዳዳች ትቆይና ቧንቧውን ትከፍታለች፡፡ የበረሮ ንጉሥ ለሆነ ጉዳይ መጥቶ ኖሮ፣ ገብቶ ባኞ ውስጥ ሲሰምጥ ታየዋለህ፡፡ ይህ የሁላችን እጣ ነው፡፡ ንጉሡ ነገሥት ሆነን እንቆይና ገረዲቱ ከተፍ ብላ ቧንቧውን ትከፍታለች፡፡ ገብቶሃል? ገረዲቱ እግዜሩ ነው ናቸው እኮ፡፡

ርዕሱን ረሣሁት እንጂ ቶፊክ የደረሰው ሌላ መጽሐፍም አንብቤያለሁ፡፡ ሕግ ያውቃል፡፡ የሆነ አገር ገዢ ሆኖ ያየውን ነው የደረሰው፡፡ ግብፅ ዘለዓለም ናት ይልሃል፡፡ ዓባይም አለ፣ ገበሬውም አለ፣ ፀሐይም አለች፡፡ ኑሮውም ያው ነው ይልሃል፡፡ የፈርኦንም ሆነ የማንም ዘመን ግብፅ ዘለዓለማዊ ናት ነው የሚልህ" ጋሼ ስብሐት አለና ፀጥ ብሎ ተነሣ፡፡ ይህንን ሲያደርግ ተመስጦ ቆሞ ነው፡፡ ዓይኑን ቡዝዝ አድርጎ እያብሰለሰለ "ጠይቅ" አለኝ ተመልሶ በዝግታ እየተቀመጠ፡፡

የነዑመር ኻያም አገር ደራሲያንን እናንሳ? ፐርሺያ እ! ቀደም ብሎ ስንጫወት ለያየናቸው እንጂ፣ አሁን የማወጋህ ከአረቦች ጋር አንድ የሚሆኑበትን ነው፡፡ እኛ ከእነርሱ በንባብ የወረስነው ፀጋ 'ሱፊዝም' ነው፡፡ ሌላው ታሪክ ነው፡፡ እገሌ እገሌን ወጋ፣ አገር ጠቀለለ፣ ሰፋ፣ ጠበበ ነው ሁልጊዜም ተጽፎ የምናገኘው፡፡ እነዚህ ሱፊዎች ግን ለሁሉም የሚዳረሱ ናቸው፡፡ እንዳጫወትኩህ እነጃፓንና ቻይና ዜን 'ቡድሂዝምን' እንደሚቋደሱት እነዚህም ብዙ የሚመሳሰሉበት አለ፡፡ ሁለቱም ዓለምን አይፈሯትምም፣ አይለማመጡዋትምም፡፡ አይጋፈጡም፡፡ ዝም ብለው ነው የሚኖሩት፣ እፍረት የለም ክብር የለም፡፡

አንድ ሱፊ ንጉሥ ሊሆን ይችላል፣ አታውቀውም እንጂ፣ ሌላው ሱፊ ግን ያውቀዋል፡፡ እርስ በእራስ ይተዋወቃሉ፡፡ ከእርሱ እኩል ሱፊ የሆነች ደግሞ የአንድ ገበሬ ገረድ ልትሆን ትችላለች፡፡ ቦታዋ ሂደቷ በእዚያ በኩል ነው የሚጠራት፡፡ አይመረመሬውን በትንሽ መስኮት የምታገኝበት ሽንኩርቷን እየከተፈች በማገልገል ነው፡፡ እነሱ በዚህ ረገድ ሩቅ የሄዱ ናቸው፡፡

ዑመር ኻያም ከሱፊዎቹ አንዱ ነው ይባላል፡፡ እንግዲህ እርሱ ሱፊ ነኝ አይልም፡፡ ሁኔታው ሁሉ ስታየው የሱፊዎች ነው፡፡ "ፔርሺያዎችስ የራሳቸው ቋንቋና ፊደል አላቸው ወይስ...?" አንተ! ጮኸብኝ፡፡

ልክ ነህ፡፡ አዝናለሁ፡፡ በዚህ ረገድ እውነተኛውን ታሪክ ልነግርህ እገደዳለሁ፡፡ መናገር ካስፈለገ በታሪክ በሥልጣኔ ከኢትዮጵያም

@Amharicbookstore



ይቀድማሉ፡፡ ከእነርሱም የወሰድናቸው ቃላትም፣ እፅዋትም፣ እንስሳትም አሉ፡፡ለመጥቀስ ዕፀፋርስ፣ ፈረስ ከዚያ ነው የመጣው፡፡ እንዲህ ስትል ሰው ሁሉ ለሰው ባለውለታ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡

ለእኔ ዑመር ካያምን በእንግሊዘኛ ያቀረበልኝ ደራሲ ኤድዋርድ ፊትዝጄራልድ ነው፡፡

አዎን! አሁን አረብኛ ከተማ ገብቶ ጎደፈ እንጂ ወርቅ የሆነ ቋንቋ ነው ይሉሃል፡፡ ሰውም ጭምር፡፡ ለምሣሌ ከባሕላቸው ልጥቀስልህ፡፡ በባህላዊው አረብ አገር አንዱ ቢያሳድደኝ ሮጬ አንተን የሙጥኝ ብል፣ ማንም አንተን ሳይገድልህ እኔን ዝንቤን እሽ አይልም፡፡ ጎሳህን ሳይፈጅ ደሞ አንተን አይነካህም፡፡ እንግዳ በአረብ ክቡር ነው፡፡ ምክንያቱም ተፈጥሮ ጨካኝ ናት፡፡ በሰው ልጆች ላይ ትጨክናለች፡፡ ውሃ የት እንደሚያገኝ አያውቅም፡፡ ግመሉ ሞቶበት እየተንፏቀቀ ነው የመጣው፡፡ እንግዳውን ተቀብለው በደንብ ያስተናግዱታል፡፡ ለሦስት ቀን ያበላ ያጠጣና እንዲያገግም ያደርገዋል፡፡

ከዚያ በኋላ ነው "ማነህ?" የሚሉት፡፡ "እገሌ ነኝ" ብሎ ዘር ማንዘሩን ይቆጥራል፡፡ አስተናጋጁ ደንግጦ "አሃ እኔና አንተማ የደም ጠላት ነን፡፡ በል እስከ ፀሐይ ጥልቀት ቶሎ ጥፋ" በቂ የእረፍት ጊዜ የወሰደው እንግዳ ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ የሰው ዘር እንዳይጠፋ መስተንግዶ መተሳሰሪያ ነው፡፡ የትም ብትሄድ ይህ ጥበብ አለ፡፡ አለበለዚያ የሰው ዘር አይኖርም ነበር፡፡ በነገራችን ላይ፣ ምንም ያልተቸገረ ጤነኛ መንገደኛም ቢመጣ እድንኳናቸው ለሦስት ቀን መስተንግዶ ይቀበሉታል፡፡

እህ! ቴክኖሎጂ መጣና የሰው ልጆችን ሥልጣኔ የመተዛዘንን ባሕል ሰርዞ በቁሳቁስ ተካው፡፡ አለች እኮ አንድ እንጉርጉሮ የራስህን አገር እሴት ቁልጭ አድርጋ የምታሳይህ፡፡

ሰው ባገሩ ሰው በወንዙ ቢበላ ሳር ቢበላ መቁመቁ፤
ይከበር የለም ወይ ማንነቱ ታውቆ፡፡

እነሱማ እስካሁን ድረስም ባሪያ ፈንጋዮች ናቸው፡፡ ድሮ በያፋ፤ ዛሬ በድብቅ ባሪያ ይፈነግላሉ፡፡ የእስልምና እምነት ተከታይ ሆነህ አረብ ባትሆንም ባሪያ አይደለህም፡፡ በሃይማኖት አንድ ከሆናችሁ በተወሰነ ደረጃ መብትህን ያከብራሉ፡፡ የሌላ እምነት ተከታይ ሆነህ ከተፈነገልክ ግን 'አቢድ' ነህ ልብ ማለት ያለብህ፣ አሁን በአረቡ ዓለም ሀብት ተገኘ እንጂ፣ የእውቀት ወይም የመንፈስ ፀጋ አይደለም" አለኝ ጭንቅላቱን በጣቱ እየጨቆመ፡፡ "ልክ እንደ ድሮው

ነው የሚያስቡት፡፡ እንደ ድሮው ነው የሚኖሩት፡፡ የቁስ ሥልጣኔ እንጂ የሕሊና ሥልጣኔ ላይ ስላልደረሱ፡፡ እገርህ ድረስ መጥተው ባይፈነግሉ፣ ተፈንጋዩ ሥራና ገንዘብ ፍለጋ እዚያው አገራቸው ድረስ ይጓዛል፡፡ እናም በሰው ልጅ ላይ ቢጨክኑ አይገርመኝም፡፡

አረብኛን አሥራ አምስት ቀን ተምሬዋለሁ፡፡ እንግሊዘኛ፣ አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ተናጋሪዎች ነበሩ ተማሪዎቹ፡፡ እኔ ትግርኛን፣ ትንሽ ግዕዝን፣ አማርኛን ስለምችል አረብኛ በጣም ቀላል ነበር፡፡

አረብኛ! ከበቂ በላይ፡፡ በሥነ ጽሑፍ ብትል፣ በሳይንስ፣ በሒሳብ በሰው ሥልጣኔ ታሪክ ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡ በተለይ ሥነ ግጥም፡፡ 'ፖወትሪ' የሚባለው ጥበብ እንደእነሱ የትም የለም፣ ነው የሚሉህ የሼክስፒር አገር ልጆች፡፡

The Way of Life ላኦ ትዙ ይልሃል፡፡ የሕይወት ጎዳና እንደ ማለት ነው፡፡ ላኦ ትዙን እና ኮንፉሽየስን ላሳይህ፡፡ ሁለቱ ናቸው የቻይና ዓይንና ህሊናዎች፡፡ በአንድ ዘመን ነው የኖሩት፡፡ ኮንፉሽዬስ ነው በአብዛኛው ቻይናን የቀረፃት፡፡ ሙሴ እስራኤልን ሥርዓት እንዳስያዘ፡፡

ላኦ ትዙና ኮንፉሽዬስ ተቃራኒዎች ናቸው፡፡ ለምሣሌ ሥነ ሥርዓት፣ ሕግ የሚሉት ጉዳይ ለላኦ ትዙ እርባናቢስ ነው፡፡ ኮንፉሽዬስ ወደ ላኦ ትዙ ሄደና "ምክር ልጠይቆት ነው?" አለው፡፡

"ምን ዓይነት ምክር?" አለ ላኦ ትዙ፡፡

አሁን እንግዲህ በደንብ ልብ በል፡፡ ላኦ ትዙኮ በጭራሽ ሥነ ሥርዓት አያስፈልግም ነው የሚለው፡፡ የገዢዎች ሥነ ሥርዓት ምንድነው? ማስመሰል ነው፣ ግብዝነት ነው አለው፡፡ ኮንፉሽዬስ ወደ ደቀመዛሙርቱ ተመለሰና በቀላሉ መንገር ስላልቻለ እንዲህ አለ፣

"አዕዋፍ ለመብረር፣ ክንፍ እንዳላቸው አውቃለሁ፡፡

. ዓሣዎችም ለመዋኘት ስንጥብ አላቸው፡፡

. አራዊትም ለመሮጥ እግር አላቸው፡፡

. ለባለ እግሮቹ ወጥመድ አለ፣

. ለዓሦቹም መረብ፤

. ለአዕዋፍም ቀስት አለ፡፡

. ለደራጉኖች ግን ምን አለ?

በዚህ ዕለት ላኦ ትዙን ደራጎን ሆኖ አገኘሁት፡፡"

ካረጀ በኋላ ላኦ ትዙ ብቻውን ከቻይና ግንብ ወጥቶ የእግር ጉዞ ጀመረ፡፡ በር ላይ ይጠብቅ የነበረው ዘብ በሕልሙ ስለ ላኦ ትዙ

@Amharicbookstore



አይቷል፡፡ ላኦ ትዙ በሩጋ ሲደርስ ነቃ፡፡ ተነስቶም ላኦ ትዙ ከመሄዱ በፊት ፍልስፍናውን እንዲፅፍ አሳሰበው፡፡ ላኦ ትዙም እሺ ብሎ በአምስት ሺ የቻይና ቃላት ይህችን መጽሐፍ ፃፈልን፡፡" መጽሐፉን አንስቶ አሳየኝ፡፡ በወቅቱ The Way of Life እያነበበ ነበር፡፡

ይኸውልህ ቡድሀ ደሞ ለአጭር ጊዜ ቻይና ውስጥ ነግሶ ነበር፡፡ ያን ጊዜ የተፃፈ ሞንኪ የሚል መጽሐፍ ነበር፡፡ የዚያን ዘመን የቻይና ዓብይ ልቦለድ ነው፡፡

በቡድሀ እምነት እንስሳም ሰውም ያው ፍጥረት ነው፡፡ እኔ ዛሬ ሰው ነኝ፣ ነገ ነብር ሆኜ ወደዚህ ምድር ብመጣ፣ በሚቀጥለው ዝንጀሮ እሆናለሁ፡፡ ሞንኪ በልቦለድ ውስጥ የተሰጠው ዓብይ ተልዕኮ የቡድሀን ወንጌል ከሕንድ ሰርቆ ወደ ቻይና ማምጣት ነው፡፡ በርካታ አደጋዎች ያጋጥሙታል፡፡ ሲያመልጥ 'እኔ ሞንኪ!' ይላል፡፡ በጣም አስቂኝ ነው፡፡ ዝንጀሮው ተሳክቶለት የቡድሀን ወንጌል ከሕንድ ሰርቆ ወደ ቻይና ይመለሳል፡፡ ቻይናዎች ደግሞ በእምነታቸው በእግዜር ይሳቃል እንዴ? እያሉ አይፈሩም፡፡ ይኼኔ ሳቅም የእግዜር አንድ መልኩ ነው፡፡

ሉ ሽሱንንስ? አላነበብክም? የካፒታሊስቱ ዓለም ሐያሲያን የኮሚንስቱ ዓለም ደራሲ ነው ይሉታል፡፡ እሱ ግን የሰው ልጆች ሕይወት ደራሲ ነው፡፡ ዘመኑ ግን በኮሚኒስቱ ጊዜ ስለታወቀ ጎራ ለዩለት፡፡ ለቅምሻ አንብቤዋለሁ፡፡ አሪፍ ነበር፡፡

ፐርል ባክንስ? በጣም እንጂ! አ! ሁለት ሦስት ሥራዎን አንብቤ ወድጄላታለሁ፡፡

የሕንድ ሥነ ጽሑፍ አንዳንድ ብቻ ነው ያነበብኩት፡፡ እንዳነበብኩት የሕንድ ዘር በአራት ነው የሚከፈለው፡፡ በሕንድ የእኔ ዘር አባል ካልሆንክ ሚሊዮን ጊዜ ብወድህ ልጄን አልድርልህም፡፡ ከፋፍለን እንዩቸው፡፡ ቀሳውስት ብራህሚን ይባላሉ፡፡ ብራሃማ ፈጣሪ አምላካቸው ነው፡፡ ብራሃማን እነሱ ናቸው መስዋዕት የሚያደርጉለት፣ አማኝንም ከፈጣሪ የሚያገናኙት፡፡

በመቀጠል ክሻትሪያ የንጉሥና የወታደር ዘሮች ናቸው፡፡ ከዚያም ቫይሲያ ሠራተኞች አሉ፡፡ ሁሉንም ዓይነት የእጅና የንግድ ሥራ የሚያከናውነው ይህ ሦስተኛው ዘር ነው፡፡ በመጨረሻ 'untouchables' የሚባሉ አሉ፡፡

'የማይነኩት' የሚባለው ዘር ሰገራ መጥረግ፣ ጥምብ ማንሳትና ይህንን የመሳሰለውን ቆሻሻ ሥራ ነው የሚሠሩት፡፡ አንዳቸውን ተጠግተህ ልንካህ ብትለው ደስተኛ አይደለም፡፡ አንተ ለሱ 'untouchable' ነህ፣ ብትነካው ታቆሽሸዋለህ፡፡ ሁሉም ዘር በሕንድ ያለበትን

ሁኔታና ደንብ ተቀብሎ ነው ለዘመናት የኖረው፡፡ በኋላ እንግሊዞች ገብተው ለአራት መቶ ዓመታት ገዙዋቸው፡፡ ለውጥ ተጀመረ ማለት ነው፡፡ ከዚያም ጋንድሂ መጣና "የማይነኩት" የሚባል ዘር የለም፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል ነው እንዲያውም የማይነኩት የእግዜር ልጆች ናቸው" ብሎ አስተማረ፡፡

ሕንዶች የተደነቁ ደራሲያን አሉዋቸው በእንግሊዝኛ አላጋጠሙኝም እንጂ፡፡ አንዷን ጥንት ያነበብኳትን ልንገርህ፡፡ ጦርነት ላይ ናቸው፡፡ እዚያም እዚህም ተሰልፈዋል፡፡ ዋናው ገፀባሕሪ አርጁና "በዚያ በኩልም የእኔ ዘሮች ናቸው፣ በእዚህ በኩልም የእነርሱ ዘር ነኝ፡፡ እዚህ ውስጥ እንዴት ብዬ ከዘሮቼ ጋር እዋጋለሁ?" ትልቁ ጭንቀት፡፡ እሱ ልብ አላለም እንጂ፣ የዚህ ጀግና ሰረገላ ነጂው እግዜርዬው ነው፡፡ እናም ይነግረዋል "ምርጫ የለህም፡፡ ሕይወትና ሞት ሆነህ መዋጋት አለብህ" አለው፡፡ የሕንድ ሃይማኖት አይፅናናህም፡፡ ጀግናው ተዋጋ፡፡ በጦርነቱም የእልቂት እልቂት ተፈጠረ፡፡ ይህንን አንብቤያለሁ፡፡ ሕንድን አንድ ታሪካዊ ፅዋ አንስተን እንሰናበት።

ላስታውስህ፡፡ ባንተ ዕድሜ ላሉ ወጣቶች ሩቅ ነው፡፡ ሕንድ ነን፡፡ ማሐቪራ የሚባል ሰው ነበር፡፡ እምነቱን ሲጀምር ራቁቱን መሄድ ጀመረና ሰው ተፋበት፡፡ እሱ ግን ቀጠለ፡፡ በቆይታም፣ "ፍጥረት ሆነው ለምን የእንስሳትን ሥጋ እበላለሁ?" አለ፡፡ ሥጋ መብላት አቆመ፡፡ ሲያስበው እፅዋቱም እትክልቱም ነብስ አላቸው፡፡

"በቃ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ አልበላም፡፡" አለና እግሩን አጣጥፎ ተቀመጠ፡፡ አለና መጅሊስ ላይ እግራቸውን አጣምረው እንደ ሚቀመጡት ጋሺም ተቀመጠ፡፡ "ሜዲቴሽን" እንደሚያደርግ የቡድሀ መነኩሴ ዓይኑን ገርበብ አድርጎ በአቀማመጡ ማሀቪራን አሳየኝ፡፡ "እዚያው ቁጭ እንዳላት ሞተ፡፡ የእሱ ፍልስፍና ስትቀጥል አፅዋፍን እንመግባቸዋለን፡፡ አንድ የማሀቪራ እምነት ተከታይ ሲሞት በቀጥታ ወደሚበለትበት ቦታ ያመጡታል፡፡ የሃ'ስት አራት ፎቅ ያህል ርዝመት ያለው የድንጋይ አምድ ነው፡፡ በላቹም እየበሉ ለአሞሮቹ ይጥልላቸዋል፡፡ ፍልስፍናዋ ስትሰነባብት ያ ማሀቪራ "እየሰበረ! ሰጠው ላሞራ!" ላይ ደረሰች፡፡" አለና ስቆ "እንዲህ ሆነ የቀብር ሥርዓታቸው፡፡

ከዓመታት በፊት በሕንድ የኢትዮጵያ አምባሳደር ባለቤት የነበረችው እትዬ መንበረ ስታጫውተኝ እንዲህ አለች፡፡ "ሁሌም ወደ ሥራዬ ስሄድ በብስክሌት ነበር፡፡ በዚያ መንገድ ሳልፍ አንድ ቦታ አለ አሮስቶ ይሸተኛል፡፡ አንድ ቀን እዚህ ገብቼ አሮስቶ እበላለሁ እያልኩ እወስናለሁ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ሞልቶልኝ እዚያ ቦታ ስደርስ ቢስኪሌቴን አቆምኩ፡፡ ጊዜ ነበረኝ፡፡ ጎራ ብዬ ያገኘሁትን

@Amharicbookstore



ሰው አሮስቶ መብላት እንደምፈልግ ነገርኩት፡፡" ሰውዬውም ግር አለውና "ተሳስተዋል፡፡ ይህ አካባቢ የማሀቪራ እምነት ተከታዮች የመጨረሻ መሰናበቻ ሥፍራ ነው፡፡"

ይሆናላ!! ሥጋው ተበልቶ አጥንቱ ይቃጠልና አመዱ ወንዝ ውስጥ ይበተናል" አለና ተነስቶ ቆመ፡፡

"እንደፈለክ" አለ እጆቹን እንደሚያቅፈኝ ሁሉ በሰፊው ከፍቶ፡፡ ኩቱን አነሣና ደረበ፡፡ መለዮውን አደረገ፡፡ ስለውጪው አየር አሰብኩ፡፡ ፀሐይ ጠልቃለች፡፡ ውጪው መብረድ ጀምሯል፡፡ ዝግ ብሎ እየተቀመጠ ቀጣይ ጨዋታውን ያጫውተኝ ጀመር።

"ፀሐይ እየጠለቀች ነው፡፡ ቡድሂስቱ መነኩሴ ሠአሊ ይህችን ነው መሣል! ብሎ ቀለሙን በሳር አጥቅሶ ቀና ብሎ ቢያይ ቅድም ያየው ውብ ቀለማትና ብርሃን አሁን የለም፡፡ ነቃ፡፡ 'ኢንላይትንመንት' አገኘ፡፡ ምንም ነገር የሚቆይ የለም፡፡ ሁሉም ቶሎ ያልፋል" አለና ሣቀ፡፡

"ቡድሐዝም ከሕንድ ተሻግሮ ወደቻይና ሲሄድ ተቀየረ፡፡ ክርስትና ከሌላው ዓለም ወደ እኛ አገር ሲመጣ የአበሲኒያ ሸማ ነው የለበሰው፡፡ እስልምናም እንዲሁ ከ'አረጂናሉ' በጣም በተለየ መልኩ ኢትዮጵያዊ ሆኖዋል፡፡ ምክንያቱም የእኛ ባሕል ሠፊና ግዙፍ ስለሆነ፣ ከማንም ባሕል የመጣ ሐሳብ ወስደን የራሳችን ፈጠራ እንጨምርበታለን እንጂ የእኛን ባሕል ሙሉ በሙሉ የመለወጥ አቅም አያኖረውም፡፡ ቡድሐዝም እንዲህ ነው የሆነው፡፡ ቻይና ግዙፍ ባሕል ስላላት የቻይናና የቡድሂዝም ነብስ ውህደት ሆነ፡፡ ቻን ይሉታል እነሱ...

ጃፓኖች ሁሉንም ነገር የሚወርሱት ከቻይና ነው፡፡ ከቡድሂዝም በፊት፣ ማለትም ከብዙ መቶዎች ዓመታት ቀደም ብሎ፣ ከቻይና አያሌ ባሕላዊ ስርዓቶችንና ሥልጣኔያቸውን ወስደዋል፡፡ ለምሣሌ ሥነ ሕንፃ፣ ፊደል አፃፃፍን፣ ሌላም ሌላም ሥርዓቶችን ወስደው የራሳቸው አድርገውታል፡፡ የቡድሂዝም እምነትንም እንዲሁ ነው የወረሱት፡፡

በጣም ብዙ ልዩነት አላቸው፡፡ የእኛ ፊደል ድምፅ አለው፡፡ የእነሱ ፊደል ሃሳብ ነው ያለው፡፡ ቤት፣ ውሃ... እያለ በስዕል ማመልከት፡፡ ቻይናና ጃፓን ቋንቋቸው በድምፅ አወጣጣቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ ማንኛውም የባዕድ ሰው ይለያቸዋል፡፡ ይህ ጃፓናዊ ነው ይህኛው ቻይናዊ ነው ልትላቸው ትችላለህ፡፡ በጃፓንኛ የተፃፈውን ቻይናዊው በቻይንኛ ነው የሚያነበው፡፡ አየህ፣ ማስተርጎምም አያስፈልግም፡፡ ጥቂት የሚጨማምሩት ይኖራቸዋል፡፡

የጃፓን 'ሀራኪሪ' በሲኒማ ነው ያየሁት፡፡ በእነርሱ ኅብረተሰብ ሎርድ አለ፡፡ ከእርሱ የበታቾች የሆኑ ሰዎች በተዋረድ አሉ፡፡ ከበላይህ ላለው ሰው መቶ በመቶ ነው የምትታዘዘው፡፡ ለምሳሌ እኔ ጃፓናዊ ሆኜ የሚያሳፍር ነገር ከደረሰብኝ ወይም በአንድ ጦር ግንባር በፍርሃት ተርበትብቼ ከሸሸሁ፣ አልያም አንድ ማኅበረሰቡ የማይፈቅድልኝን ነውር ነገር ካደረኩ፣ ራሴን መግደል አለብኝ፡፡ የበላዬ ከፈቀደልኝ የክብር ቦታ ተሰጥቶት ይቀመጣል፡፡ ሌሎቹም አባሎቻችን ክብ ሠርተው ይቀመጣሉ፡፡ የማምነው የልብ ጓደኛዬ አጠገቤ ይቆማል፡፡ እሰናዳለሁ፡፡ የሚጠጣም አይጠፋም፡፡ ሻምላዬን እመዝና ሆዴን ወግቼና ሁለት ጊዜ አማስዬ እሰናበታለሁ፡፡ ጓደኛዬም ስያፉን ይመዝና እንዳልሰቃይ አንገቴን ይቀላኛል፡፡ ቶሎ ይጨርሱኛል፡፡

ይህ ውርደት የደረሰበት ጃፓናዊ አለቆቹ እንዳይሞት ከከለከሉት ከሐፍረቱ ጋር እየተሸማቀቀ ይኖራታል እንጂ በገዛ ፈቃዱ በራሱ ላይ እርምጃ መውሰድ አይችልም፡፡ ይህንን ያህል ጥብቅ ነው የእነርሱ ባሕል፡፡

ይኸውልህ፡፡ አንድ ሎርድ ይኅዛል፡፡ ሌላ አነስተኛ ለእሱ ያደረ ሎርድ ሠፈር ይደርሣል፡፡ እዚያ ለማደር ይወስናል፡፡ በአጋጣሚ የቤቱ ጌታ የለም፡፡ ባለቤቱ ደግሞ ከመጠን በላይ ቆንጆ ነች፡፡ ወንድ ልጅ አይቶ የማይምራት ወይዘሮ ነች፡፡ እንደ ሎርድነቱ በበታቹ ቤት ተስተናገደ፡፡ ከዚያም ሊተኛ ሲሄድ፣ እቺን ሚስት መኝታ እንድትኀብኘው አዘዛት፡፡

"እሺ" አለችው፡፡ እንቢ አይባልማ፡፡ የመጨረሻውን መለኪያ ጨልጦ ወደ መኝታ እስከሚሄድ ቀድማው እሷ ገባች፡፡ እስከሚደርስ ያቺ ውብ ሴት ራሷን ገድላለች፡፡

እንቢ እንዳትለው መብቱ ነውና ለአክብሮት ያክል እሺ ማለት አለባት፡፡ በዚያ በኩል ደግሞ ፍቅረኛዋም ስለሆነ ባለቤቷን ክብሩን ከማስነካት ራሷን መስዋዕት ማድረግ ምርጫዋ ሆነ፡፡

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አውሮፕላን እያበረሩ ሄደው ጃፓኖች መርከብ ላይ የሚፈጠፈጡትን መስዋዕትነት 'ካሚካዚ' ይባላል፡፡ ወጣቶቹ መጀመሪያ ሲመለመሉ ሥልጠናው ካሚካዚ እንደሚሆን ያውቃሉ፡፡ ስለዚህም ጠላትን አጥፍቶ ለመጥፋት ወስኖ ነው የሚገባበት፡፡



በአሁኑ ጊዜ ጃፓን ካለችበት ዕድገት አኳያ 'ኒንጃ' ታሪክ ሆኗል፡፡ ቀደም ብሎ ግን እንበል ከአንድ ምዕተ ዓመት ብፊት፣ የኒንጃ አደገኛ እርምጃዎች የግለሰብ አይደሉም የኅሳ ሥራ ነው፡፡ ሥራ ከተባለ፡፡ ታላላቅ ሰዎቻቸው ሲጋጩ ወደ ኒንጃ በመሄድ ጠላቱን ለማስገደል ይዋዋላል፡፡ የተገዳዩን ቤት ማንነት በዝርዝር ለኒንጃዎች ያስረዳና ክፍያውን ይስማማሉ፡፡ ከዚያም ኒንጃዎች አስፈላጊውን ጥናት አድርገው የተገዳዩን ሰው አካባቢ በመውረር ይገድሉታል፡፡ ከዚህ በኋላ ነው ክፍያው የሚካሄደው፡፡ ካልከፈልክ ወዬውልህ፡ እናትህ ሆድ አትገባት!

አሁን በኮምፒዩተር ዘመንም የጃፓኖች ክብር ያው እንዳለ ነው፡፡ ሁለት ጃፓናውያን ነጋዴዎች ናቸው፡፡ ሳን ፍራንሲስኮ ወደብ በመርከብ ዕቃ ለማድረስ ይዋዋላሉ፡፡ በዚህ ቀን በዚህ ሰዓት እናደርሳለን ብለው ተስማሙ፡፡ እንዳሉት ሳይሆን ቀረና መርከብዋ ሁለት ሳምንት ዘግይታ ሳን ፍራንሲስኮ በመድረሷ ተዋዋያቸውን ይቅርታ ጠይቀው በራሳቸው ላይ 'ሀራኪሪ' ፈፀሙ፡፡ ከሩቅ ምሥራቅ እንመለስ ወይስ እዚያው እንቆይ?

ከጃፓኖች የመሰጠኝ ደራሲ አለ፡፡ ዩኪዮ ሚሺማ የሚባል ደራሲ ነበራቸው፡፡ የሃያኛው ክፍለ ዘመን ታላቁ የልቦለድ ደራሲያቸው ነበር፡፡ አራት ቅጽ ያለውን አንዱን ሥራ አንብቤያለሁ፡፡ ዋናው ገፀ ባህሪ በእያንዳንዱ ቅፅ ውስጥ አንድ ኑሮ ይኖራል፡፡ ከዚያ ከአራት ሕይወት ውስጥ በአንደኛው ሴት ሆኖ ተወልዶ ነው የምናገኘው፡፡ አራተኛ ቅፅ ውስጥ ወታደር ሊሆን ይወለዳል፡፡ የጃፓንን ንጉሥ በሙሉ ከበሬታ ገድሎ እሱም ሃራኪሪ ይፈፅማል፡፡

ደራሲው ዮኪዩ ሚሺማ ኑሮ ተሳክቶለት ሚሊዮኔር ሆኖ ውብና ማራኪ ሕይወት ኖረ፡፡ በሳሙራይ ወግ የታጠቁ የግል ወታደሮች ነበሩት በሄደበት የሚያጅቡት፡፡ በመጨረሻም፣ እኔ የፃፍኩት ጊዜ ማለፊያ ልቦለድ ሳይሆን፣ ሐቁ እሷ ናት ለማለት በሙሉ ሥነ ሥርዓት ሀራኪሪ ፈፀመ፡፡

አሁን በምናቡ የመጣውን ወግ ያወጋኝ ጀመር፡፡ "የእኔ ትውልድ ተማሪዎች በነበርን ጊዜ 'የእንግሊዝ ሳክሰን' ቅኝ ግዛት ዳርቻ ነበርን፡፡ ይሁን እንጂ የኤምፓየሩ አካል ነን፡፡ ብዙ ጊዜ ወደ እንግሊዝ ነው የምናየው፡፡ ከዚያ ነጥረን ወደ አሜሪካ ነው የምናነጣጥረው፡፡ ለምሣሌ እኔ ስወለድ ቦታዬ ትግሬ ይሁን እንጂ አስተሳሰቤ፣ አመለካከቴ በአጠቃላይ እንደ ሸሐል አገር አማራ ነው፡፡ ሕሊናዬ በአብዛኛው እንግሊዝ ነው፡፡ በወቅቱ ገንዘብ ስላልነበረኝ ሲኒማ

@Amharicbookstore

ለመግባት ዕድሉ አልገጠመኝም፡፡ ስለዚህ ማንበብ ብቻ ሆነ ዕድሌ፡፡ መጻሕፍትን ማንበብ ብቻ!...

ፍሮይድና ዶስቶዬቭስኪ የአንድ ዘመን ሰዎች አይደሉም፡፡ ዶስቶዬቭስኪ ነው ቀድሞት የኖረው፡፡ ቀድሞት ሲግሞንድ ፍሮይድ ኖሮ ቢሆን ኖሮ፣ ዶስቶዬቭስኪን አንድ አስተዋይ ሰው ቢያነበው፣ የፍሮይድ ፍልስፍና በደምብ ገብቶታል ብሎ ያስብ ነበር፡፡ ይሁንና እንጂ ከፈላስፋው ደራሲው ቀድሞ ስለኖረ የራሱን ፍልስፍና ደራሲው አስቲላለፈ፡፡

ሩሲያ ቆይታ እናድርግ! እንችላለን፡፡ ደስ እንዳለን መጓዝ መብታችን ነው፡፡ የምናብ ጨዋታ ድንበር አያግድህ፣ ፖለቲካ አይከለክልህ፣ ዓለምም ያንተ፣ አንተም የእርሷ ሆነህ ትቀጥላለህ፡፡ እኛም እንቀጥላለን፡፡ ዶስቶዬቭስኪን ሳነበው ወጣት ነበርኩ፡፡ ውስጤ ጥልቅ አለ፡፡ ልክ አበሻ ነው የሚመስልህ፡፡ ባሕላቸውና ወጋቸው እንዳለ የአበሻ ነው ሩሲያውያን፡፡ ከስም በስተቀር፡፡ በተለይ በወጣትነት ዕድሜ ዶስቶዬቭስኪ በጣም ኃይለኛ ነው፡፡ (Powerful) ለምሣሌ The Brothers Karamazov በተባለው በጣም ትልቅ ልቦለድ ውስጥ አራት ወንድማማቾች አሉበት፡፡ ሚቲያ (ዲሚትሪ) ስሜታዊ ነው፡፡ መብላት መጠጣት ሴት መሄድ:: የአባቱ ፍቅረኛ አለች፡፡ ከእስዋ ጋር ፍቅር ይዞታል፡፡ የእርሱ ታናሽ ኢቫን 'ኢንቴሌክችዋል' ነው፡፡ የእርሱ ተከታይ ደግሞ አሊዮሻ አለልህ፣ ንጹህ ክርስቲያን ነው፡፡ ቆንጆ ልጅ ነው መጽሐፉን ስታነብ ይህንን ልጅ ከልብ ትወደዋለህ፡፡ ከሁሉም ጋር ይፋቀራል፡፡ እሱንም የማይወደው የለም፡፡

ስሜርዲያኮቭ ደግሞ ከገረድ የተወለደ ነው፡፡ እንደ ዶስቶዬቭስኪ የሚጥል በሽታ አለበት፡፡ ኢቫን ይታመማል፡፡ ለሁለት ሳምንት ኃይለኛ ትኩሳትና ቅዠት ያጠቃዋል፡፡ በመጀመሪያ ለወጋችን አያያዝ እንዲያመቸን ትንሽ ስለ ሃይማኖት ገለፃ ላድርግልህ፡፡ 'ባክ ግራውንድ' ያስፈልግሃል!

እነ ማርቲን ሉተር መጥተው ፕሮቴስታንት እምነትን ካወጁ በኋላ፣ ካቶሊኮች ሲፃረሩዋቸው 'ካውንተር ሪፎርሜሽን' ጀመሩ፡፡ በተለይም ጀዝዊቶች በዚህ ረገድ መሪዎቹ ናቸው፡፡ ድንግላውያን ስለሆኑም ምንም ነገር ሐሳባቸውን አይሠርቀውም፡፡ ምንግዜም መንፈሳቸው ወደ እምነታቸው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ስፔን ውስጥ 'ኢን ኩዜሽን' ተቋቋመ፡፡ ...

እነ ማርቲን ሉተር ከተፍ ብለው አይደለም እንዴ የኤውሮፓ ክርስትናን ለሁለት ሰንጥቀው የከፈሉት? ሌሎችም ሳይበቅሉ ቶሎ



ማጥፋት ነው፡፡ ስለዚህ ኢንኩዊዚሽን የሚባል ፍርድ ቤት በፕሮግራም ከአገር አገር እየተዘዋወረ "ይፈርዳል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱም ተጠርቶ ይመጣል፡፡ ባንተ ላይ ክስ ለመመሥረት ሁለት ሰዎች በቂ ናቸው፡፡ ተከሳሹ ማን እንደከሰሰው አያውቅም፡፡ መርማሪዎቹ ተከሳሹን ሲመረምሩት ቶሎ ብሎ " አዎን ሠይጣን አሣስቶኝ ነው" ካለ፣ ንስሀ ይገባና " ይህን ያህል ቀን ጹም፣ መጽውት" ብለው " እግዜር ይፍታህ" ይሉታል፡ ዳነ፡፡ "ተነፋ!" ካልካቸው ግን በቆምክበት የእንጨት ክምር እሳት ይለኩሱብሃል፡፡ ይህ ኢንኩዚሽን ነው፡፡

ዋናው 'ዘ ግራንድ ኢንኩዊዚር' ነው፡፡ አስፈላጊ ሲሆን እርሱ ራሱ ሄዶ ይፈርዳል፡፡ አሁን የዶስቶዬቭስኪ ባሕሪዎች ጋ እንመጣለን፡፡ የዶስቶዬቭስኪ ምናብ ፍሬን የለውም፡፡ ይህ እንኳን አይታመንም ብለህ አትጠራጠርም፡፡ ማመንና መቀጠል ነው ያለብህ፡፡

ኢየሱስ ይመጣል በፈጠራ ጥበብ፡፡ ለግራንድ ኢንኩዊዚተሩ በግል ሲናገር ታየዋለህ፡፡ " እኔኮ ሳስተምር ወንድምህን እያሳደድህ አቃጥል አላልኩም፡፡ ይህ ምን ዓይነት ክርስትና ነው የምታካሂዱት? " ይላል፡፡

"አይ! ይኸውልህ እንግዲህ" ይለዋል ግራንድ ኢንኩዊዚተሩ ኢየሱስን "አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ መጥቼ ነበር የማቃጥልህ፡፡ ምክንያቱም አንተ ስርዓት አልበኛ ነህ፡፡ ሕዝቡ ደሞ ያለ ስርዓት መኖር አይችልም፡፡ እኛ ነን የሚፈልገውን የምናውቅለት" ሲለው ኢየሱስ ግንባሩን ስሞት ይወጣል፡፡

የፈረንሣይ አብዮት አንገት መቅያ ሥራ ፈትታ አታውቅም፡፡ ለ ኩንት ደ ጊዮቲን ነው የሠራት፡፡ሙሉ ስምዋ ማዳም ላጊዮቲን ነው፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው በጊዮቲን እንዲቀላ ተፈረደበት፡፡ ጊዮቲኗ ታድያ በዚያን ጊዜ ለብዙ ዓመታት ሥራ አቁማ ስለነበር ዝጋለች፡፡ ግን ሚቼን አልማሩትም፡፡ ከቢልጂየም መቅያ አስመጥተው አንገቱን ቀነጠሱለት፡፡

ዶስቶዬቭስኪ The Idiot ውስጥ አንዱ ባህሪ ጊዮቲንን አንስቶ "ቁምጥ እኮ ነው የምታደርግህ" ሲል ሌላኛው ከአፉ ነጥቆት "አሄሄ! እዚያ ታች አንገትህን አጋድመህ ስታየው የዘለዓለምን ያህል ነው የሚረዝምብህ" ይለዋል፡፡

አዎን፡፡ ቻርልስ ዲከንስን በኋላ አስታውሰኝ እጫውትሃለሁ፡፡ አሁን ሩሲያ ነን፡፡ እንዲያውም ዲከንስን ሩስኪዎች እንዴት እንደ ሚያዩት ላሳይህ፤ ዶስቶዬቭስኪ የዲከንስ ተፅዕኖ ነበረበት፡፡ ቶልስቶይ

@Amharicbookstore

ለዲከንስ ያለውን አድናቆት ሲገልፅ፣ በአንድ ምዕተ ዓመት አንድ ቻርልስ ዲከንስ ዓይነት ደራሲ ከአንድ በላይ አይፈጠርም ይለናል።

ይኸውልህ! አፃፃፉን ልብ ስትለው ልክ እንደ ሩሲያውያን ደራሲዎች እንባ በእንባ እኮ ነው የሚያደርግህ። የደሃውን ሕይወት አስመልክቶ ፃፈ። የእንግሊዝ ልዑላን፣ ልዕልታትና መኳንንቱ አነበቡት። ከእርሱ በኋላ ነው ድሆችን የመርጃ በጎ አድራጎት ድርጅት መመስረት የተጀመረው።

ዲከንስ በድህነት ውስጥ ነው ያደገው። ድህነትን አሣምሮ ያውቃታል። እናም ተጠበበባት። አንዳንዱ ሕይወትን ይኖራታል እንጂ አይገልፃትም።እንደ ዲከንስ ዓይነቱ ደግሞ ሁለት መቶ ዓመት ሙሉ ተነቦ አሻራውን እዚህች ምድር ላይ ትቶ እኔና አንተ መሃል እስከ መድረስ ይችላል ...

The Brothers Karamazov ለእኔ አልቋል። አንዳንድ ሀያሲያን አላለቀም ነው የሚሉት። ሲፅፍ በጣም ዝርክርክ ነው። በጣም! Crime and Punishment ብቻ ናት በቴክኒክ ያልተዝረከረከችው። ይሁን እንጂ ሥራው የሚጥምህ ዓይነት ሰው ከሆንክ እንኳንም ተዝረከረከ! እያልክ ነው የምታነበው። አሁን ደጅ ስወጣ ድንገት ዶስትዬቭስኪን ባገኘው:: ይህንን እነግረው ነበር።...

በአጠቃላይ ሥራዎቹ በጣም ኃያል ናቸው። ኑሮውን ቢታውቅለት ደግሞ ልብ ይነካል። የመከራ ሰው ነበር። በእሱ ዘመን ወጣት ጎረምሶች አብዮት እናስነሣለን ብለው ክበብ ነበራቸው። መሃላቸው ጆሮ ጠቢ ገባ። ተያዙ። ደራሲያችን በርሸና እንዲሞት ተፈረደበት። እሱና ሌሎቹ ሊገደሉ ከተወሰዱ በኋላ ነው የንጉሡ ነገሥቱ የምሕረት ቃል የተነገራቸው:: ምሕረት መጣለት። ወደ ቀዝቃዛው ኪስም ወደ ሳይቤሪያ በእስር እንዲቀጣ ተሻሻለለት። እዚያም አምስት ዓመት ታሰረ።

ለአንድ ጓደኛው የፃፈው ደብዳቤ ትዝ አለኝ። ለአንተም የመከራውን ዘቅ ያሣያሃል። "ይኸውልህ ያ የማያስቅም የማያ ነቀምጥ የማያጋድም በሽታዬ ተነስቶብኛል።" የኪንታሮት በሽተኛ ነበር። የሚጥል በሽታም አለበት?

እ! አጫውቼሃለሁ? እንደዚያም ቢሆን ሕመሟን ይወዳታል:: ኑሮው? ችስታ ነው። የአገሩ ልጅ ኢቫን ቱርጌኔቭ ከአጠገቡ አለ። ቱርጌኔቭ ጎበዝ ደራሲ ነው። ባለፀጋ ነው። መፃፍ ስለሚወድ ነው የሚደርሰው። አሣታሚ ባይኖርም በገዛ ገንዘቡ ማሳተም የሚችል ሰው ነው።

@Amharicbookstore



ሁለቱም ስዊዘርላንድ ሄደዋል። እዚያ ቁማር መጫወት ክልክል ነው የሚል ሕግ የለም። ዶስቶዬቭስኪ ደግሞ ቁማርተኛ ነው። ስለዚህ ገንዘብ ምንጊዜም ይቸግረዋል። ቁማርተኛ'ኮ አይበላም፣ ይበሉታል እንጂ።

በነገራችን ላይ The Gambler የተባለ ድርሰቱን በፊልም ነው ያየሁት። የተዋጣለት ነው። ደራሲው Gambler ነዋ። እንዲህ ነው እንግዲህ:: ዶስቶዮቭስኪ ከአሳታሚዎቹ ጋር ይነጋገራል። የታወቀ ደራሲ አይደል? በቅድሚያ ይከፍሉታል። በገንዘቡ ቁማር ይጫወትበታል። ከአሳታሚው ጋር የሚረካከቡበት ጊዜ ሁለት ሦስት ሳምንት ሲቀረው መፃፍ ይጀምራል። ለዚህ ነው ሥራው የሚዝረከረከው። ጊዜ የለውማ! የት ነን?

እ! ዶስቶዮቭስኪ ቱርጌኔቭ'ጋ ይሄድና ገንዘብ ይበደራል። ሁለት መቶ ሩብል። የሚከፍልባት ጊዜ አለፈች። ሁለት ወር አሳልፎ መጣ። ቱርገኔቭ ሳይናገረው፣ "እና ምን ይሁን ነው የምትለው?! ያንተን ሁለት መቶ ሩብል ሁለት ወር ባቆየው ምንድነው" ብሎ መጮህ። እየሳቀ "ይሄኔ ኮ ቱርገኔቭ ማበደሩንም ረስቶታል። እንጂ። ግን ተንጫንጮ ሰድቦት ሄደ።...

ውይ! በማርያም! ቱርገኔቭ እኮ 'gentleman' ነው። ምንም አላለውም። Crime and Punishment ውስጥ ራስኮልኒኮቭ ዋናው ገፀ ባህሪ ሶንያ ፍቅረኛው ናት። አባቷ ሰካራም ነው። ልክ ሲገባ ሚስቱ በጥፊ ቷ! ስታደርገው ይደርሳሉ። ምን ይላል መሰለህ "ስትመታኝ በጣም ነው የምደሰተው" ይልሃል። እየሳቀ "እና ዶስቶዬቭስኪን ታምነዋለህ። ሌላ ደራሲ ቢጽፈው አይታመንም። አቤት ደሞ ሲያስቅ!...

ስለ አባቱ አንዲት ነገር ብቻ ነው የማውቀው፤ የሕክምና ዶክተር ናቸው። ከከተማ ወጣ ያለ መንደር አላቸው። የዚያን ጊዜ ከባርነት መለስተኛ ነፃነት ያላቸው ሰዎች አሉ 'ሰርፍ' የሚባሉ። ሰርፍ የሆነ ሰው የመሬቱ ጌታ ሳያውቀው ማግባት አይፈቀድለትም። ሌላ ቦታ ሲሄድም ከጌታው ይለፍ ያስፈልገዋል። እያንዳንዱ ጌታ ያሉትን ሰርፍ 'Soul' ነው የሚላቸው። የዶስቶዬቭስኪ አባት ከእጁ አለንጋ አይለየውም። አንድ ሰው በአጠገቡ ሲያልፍ ስላላየው እጅ ካልነሣ ሾጥ ያደርገዋል። "እንዴት አባቱን እጅ አይነሳም?!" ሌላው በቅጡ እጅ ቢነሣም ሾጥ ይደረጋል። "እንዴት አባቱን ደፍሮ እጅ ይነሣል?!"

ዶስትዬቭስኪ ለኒኮላይ ጎጎል ያለውን ፍቅር ሲገልፅ "ሁላችንም ከጎጎል ካፖርት ውስጥ ነው የተገኘነው" ይላል። ካፖርቱ የሚለውን

አጭር ልቦለድ ማለቱ ነው፡፡ ጎጎል Dead Souls የሚል ልቦለድ አለው፡፡ እንዳያመልጥህ ካገኘህ አንብበው፡፡

ቺቺኮቭ ይባላል ባህሪው፡፡ ሞላጫ ነው፡፡ ባንክ ትሄድና አበድሩኝ ትላለህ፡፡ የሆነ ትልቅ ነገር ልትሠራ አስበሃል፡፡ በወቅቱ እዚያ "ምን ያህል Soul አለህ?" ይሉሃል፡፡ የሕዝብ ቆጠራ በየሰባትና አሥር ዓመቱ ገደማ ነው የሚካሄደው፡፡ ቆጠራ ሲያካሂዱ የእያንዳንዱ ባላባት Soul ስንት ናቸው? የሚያስተዳድሩዋቸው ከሃምሳ እስከ ብዙ ሺዎች ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ከቆጠራ በኋላ ቢሞቱም እስከሚቀጥለው ቆጠራ ግብር ይከፈልባቸዋል፡፡

የቺቺኮቭ ፕላን በሰረገላ እየዞረ አገሩን ያዳርሳል፡፡ አቀራረቡንም ያውቅበታል፡፡ ምን ያህል 'ሶልስ' እንደሞቱ ያጣራና፣ የሞቱትን ነብሳት ተደራድሮ ይገዛል፡፡ በደስታ ይሸጡለታል፡፡ በርካሽ ዋጋ፡፡ ከዚያም፣ በሰበሰባቸው ነብሳት መያዣነት ባንክ ሄዶ ይበደራል፡፡ በአጠቃላይ የጎጎል ራሺያ ቁልጭ ብላ ትታያለች፡፡ ሸፍጥ፤ ጥርጣሬ፤ ፍርሃት፤ ፍንትው ብሎ ይታይሃል" በረጅሙ ተነፈሰና በሐሳብ እልም አለ፡፡

እንግሊዝ መሬቷ ነው እንጂ ሚጢጢ ቋንቋዋ በጥበብ ዓለምን አጥለቅልቋል፡፡ቀደም ብሎም አጫውቼሃለሁ፡፡ ሼክስፒርን፣ ዲክንስን አንስተናል፡፡ አሁን ትዝ ያለኝ ዶክተር ሳሙኤል ጆንሰን ነበር፡፡ የመጀመሪያውን የእንግሊዝ መዝገበ ቃላት ያዘጋጀው ይህ ሰው ነው፡፡ አንዷን ቃል ላስታውስህ፡፡

0at በእኛ ቋንቋ አጃ ነው፡፡ ይህችን የእህል ዘር ሲተነትናት "በእንግሊዝ ፈረስ የሚበላው፣ በስኮትላንድ ሰው የሚመገበው እህል" ሲል ያሰፍራታል፡፡

የሕይወት ታሪኩን የጻፈለት ጓደኛው ቦዝዌል የሚባል የስኮትላንድ ተወላጅ ነው፡፡ የእንግሊዝ ንጉሥ ስኮትላንድን ወረረ፡፡ "ስኮትላንዶች ከመጠን በላይ በዙ!" አለና ቋሚ አዋጅ አስተላለፈ፡፡ አንድ ስኮትላንዳዊ ሲያገባ የሙሽሪትን ድንግል የሚወስደው አንድ እንግሊዛዊ ነው፡፡ እንግሊዛዊው የስኮትሽ ልጃገረዷቱን እነሆ በረከት! ካላት በኋላ ነው ሙሽራው የሚቀጥለው፡፡ ያዝክ?

ጆንሰን ደግሞ ተናጋሪ ነው፡፡ ከቦዝዌል ጋር ሲጨዋወቱ የሚያደንቃቸውንና 'ጂኒየስ' የሚላቸውን ሰዎች ይጠራለታል፡፡ ቦዝዌልም ልብ ብሎ አድምጧል፡፡ "እስካሁን አድንቀህ የጠራሃቸው ሰዎችኮ በሙሉ የስኮትላንድ ተወላጆች ናቸው" ሲለው፣



"የስኮትላንድን ሰው ሩቅ እናደርሰዋለን፣ በልጅነቱ ከያዝነው" አለው፡፡

ራሴላስን የፃፈው ለእናቱ ቀብር ነው እንዴ? 'ጋዴሚት!' እኔ ሊያሣክም ነበር የመሰለኝ፡፡ ለካስ መገነዣ ነው፡፡ ፅናታቸውን አደንቃለሁ የዶክተር ጆንሰንን..." አለ በተቀመጠበት እጅ እየነሣ፡፡

"እንግሊዝን ሸንቴን ሸንቼ ስመለስ ጨዋታችንን ልቋጭልህ?!" አለና ተነሣ፡፡ እዚሁ እንዲጠቀም ፖፖ' አቀረብኩለት፡፡ መሸቷል፡፡ አዳሩ እዚሁ 'ዙሉ ካስል' ውስጥ ከእኔ ጋር ነው፡፡

"እሺ አምጣው! በእውቀት ልሙላው" አለና ሣቀ፡፡

ጀርባውን ለእኔ ሰጥቶኝ ተጠናቅቆ እየተቀመጠ ዓይኑን ቡዝዝ አርጎ አስተዋለኝ፡፡ ምንጊዜም መፀዳጃ ቤት ደርሶ ሲመለስ ነብሱ አዲስ ሐሳብ ትፀንሳለች፡፡ ሐሳቧ ለእኔ የሚያጫውተኝ አልያም ለራሱ በማስታወሻው ላይ የሚይዛት ትሆናለች፡፡ እንዳልኩት ሆነ፡ "ይኼውልህ፡፡ አንዳንድ ሐሳብ አለች፤ አሁን ካልጻፍኳት ብልጭ ብላ ትጠፋለች፡፡ ማስታወሻዬን አቀብለኝ" አለ፣ ሰጠሁት፡፡ ከፃፈ በኋላ "እ?" አለኝ፡፡

እንግሊዞች ከሁሉ በላይ የምታደንቁት ገጣሚያችሁ ማነው ቢሏቸው፣ ሚልተን ይላሉ፡፡ ሼክስፒርስ? ሲባሉ፣ እሱማ የዓለም ነው ይሉሃል... ሼክስፒር አራተኛ ክፍል ድረስ ነው የተማረው፡፡ ቤን ጆንሰን ለሼክስፒር ሲጽፍለት "የእኔ ሼክስፒር፣ ትንሽ ላቲን፣ ከእዚያም ያነሰ ግሪክ የሚችለው" ሲል ያደንቀዋል፡፡ ሼክስፒር አረፈ፡፡ ከእዚያም በኋላ ሂሰኞች መጡ፤ አያሌ ጥርጣሬያቸውን አስነበቡን፡፡ ለምሣሌ የዘመኑ ንግሥት ኤሊዛቤት ጽፋቸው፣ ክብሯ ስላልፈቀደ ስሙን ለሼክስፒር ሰጠችው፡፡ ሌሎች ደግሞ ፍራንሲስ ቤከን (Bacon) የሚሉ አሉ፡፡ እሱ የመጀመሪያው ታላቅ ሳይንቲስት ስለሆነ፡፡ ቤከን በዘመኑ የነበረውን የሃይማኖት አስቸጋሪነት አልፈው አንባቢያንን በሳይንስና በሐይማኖት መሀል ያስለየ ምሑር ነው፡፡

በሼክስፒር ሕይወትና ማንነት ላይ ንትርኩ ይሄድ ይሄድና ካይሮ ውስጥ እያዝናና የሚኖር አንድ ይሁዲ 'ኮሜዲያን' ሼክስፒርን ያነሣና "ይህንን ሁሉ የፍቅርና የሙቀት ታሪክ እንዲህ ዓይነት በረዶ ምድር ላይ ተወልዶ መጻፍ አይቻልም፡፡ እንዲህ ዓይነት የፍቅር ግለት ሊገለፅ የተቻለው ሼክስፒር ፔርሺያዊ ሆኖ ነው" ይላል፡፡ በአጠቃላይ ሰው በስታቲስቲክስ ብታጠናው፣ ፎቶ ብታነሳው፣ ድምፁን ብትቀርፀው ያወከው ይመስልሃል እንጂ አታውቀውም፡፡ ሰው ራሱን የቻለ 'ዩኒቨርስ' ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ ሰውየው ሼክስፒር ተዓምረኛ ነው፡፡ ፐ! አድናቆትና ክብር ይገባዋል፡፡

@Amharicbookstore

ሼክስፒር ለንደን ከርሞ ወደ ስትራትፎርድ ይሄዳል፡፡ እቤቱ ሲገባ ሚስቱ ከአንዱ ጋር መርፌና ክር ሆነው ያገኛታል፡፡ ምንም አላላትም፡፡ ሼክስፒር ነቃ ሰውዬው፡፡ ሼክስፒር ልቡ የተሰበረው በልጁ ሞት ነው፡፡ ሐምኔት የሚባል በጣም የሚወደው ልጅ ነበረው፡፡ ይህ ልጅ በአምስት ይሁን በሰባት ዓመቱ ሞተበት፡፡ ቅስሙ ተሰበረ፡፡ ከዚህ በኋላ ነው እነዚያን ታላላቅ 'ትራጀዲዎች' የፃፈው፡፡ እውነትም ሼክስፒር የዓለም ደራሲ ነው፡፡..." አለኝና "አምጣ ማስታወሻዬን" አለኝ፡፡ ቀልጥፌ አቀበልኩት፡፡ ጻፈና ቀና ብሎ እያየኝ "ንጉሥ ሰለሞን ሺ 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች ነበሩት አይደለም? ልክ እንደሱ የእኛም ቆንጆ ሐሳቦች መዓት ናቸው፡፡ ስለዚህ ጋዜጣ ላይ አሰፍሬ ለአንባቢያን የማጋራው ሐሳብ ከጎበኘኝ እጽፈዋለሁ፡፡ ያን ያነበበኝ አንዳንድ ሰው ዕድለኛ ነው፡፡ እኔም በዚህ በኩል ዕድለኛ ነኝ... የቻርልስ ዲከንስን ላክልልህ?

ዲከንስ በየሳምንቱ በሚወጣ መጽሔት ላይ ነበር ብዙዎቹን ረጃጅም ልቦለዶቹን የጻፋቸው፡፡ በሳምንት፣ በሳምንት አንዳንድ ምዕራፍ ይጽፋል፡፡ የመጽሐፉ ርዕስ Little Dorit" ነው! የ'ፀባሕሪዋ ስምም Little Dorit" ነው! የሚባለው፡፡ ይህንን መጽሔት በፍቅር ብዙ ሺ አንባቢያን ተደስተውበታል፡፡

አንድ አየርላንዳዊ አንባቢው ነበር፡፡ ሰውዬው በጊዜው የታወቀ ደራሲ ነበር፡፡ ጎረቤቱ አንዲት ሴትዮ አለች፡፡ ደራሲው ቤት ካሰኛት ትመጣለች፡፡ አንድ ቀን መጥታ ስትጎበኘው ያለቅሳል፡፡ "ምን ሆንክ?" ስትለው፤

ደራሲው ምን አለ መሰለህ? "ቁጭ በይ አንቺንም ይመለከትሻል፡፡ ሊትል ዶሪት ሞተች፡፡" አላት፡፡ ልብ አድርግ፣ እርሱ ራሱ ደራሲ ነው፡፡ 'ቴክኒኩን' ምኑን ሁሉ ያውቃል፡፡ ያንን ያህል የደራሲን እንኳ መንፈስ ይዞ የማስለቀስ ኃይል ነበረው ቻርልስ ዲከንስ" አለና ረጂም ጢሙን ወደታች እየፍተለተለ ፈዞ ያየኛል፡፡ ዓይኑን እኔ ላይ ይትከለው እንጂ እይታው ወደ ውስጥ እንደሆነ አኳኋኑ ይገልፃል፡፡ ከረጂም ፀጥታ በኋላ "ራዳርህ የት ያመለክትሃል?

አንዳንድ ዓይነት ደራሲ የወለደውን ሁሉ ይወዳል፡፡ እንደ እናቱ ልጅ፣ እግዜር እንደሚሉት፡፡ ቻርልስ ዲከንስ የተባለው ደራሲ ሁልጊዜ አሁን የሚጽፈው መጽሐፍ ነው አሪፍ፡፡ የታተሙት ሁሉ አልፈዋል፤ በእሱ አስተሳሰብ፡፡ በጠየቁት ቁጥር "እንደዚህ ጽፌ" አላውቅም ይላል፡፡ እሱ ተናገረ እንጂ እኛም እኮ ስንፅፍ የሚሰማን እንደዚያ ነው፡፡ ምክንያቱስ በፊት የተጻፈው እኮ ሌላኛው እኛ ነው የጻፈው 'ራይት!' አሁን እኛ ደግሞ እንደዚህ ጽፈን አናውቅም ብለን ብናኾብ ጤናማ አንጀባ ነው፡፡ ይህ

@Amharicbookstore



ደራሲ እንጌ ለመብለጥ ሳይሆን ለመፍጠር ስለፈለግኩ ስለሚጥመኝ ደስ እያለኝ እጥፋለሁ፡፡

ሁለት ነን፡፡ አንዱ ከኅብረተሰብ፣ ከማኅበረሰብ ጋር የሚፋጠጠው እኔ የእነሱም እዳ አለብኝ፡ እነሱም የእኔ ዕዳ አለባቸው፡፡ ሥራ መብቴ ነው፡ የፖሊስ ጥበቃ መብቴ ነው፡፡ እንደዚህ እንደዚህ እኔ እና ማኅበረሰብ፡፡ ዞር እንልና ደግሞ እኔ ደግሞ ማኅበረሰብን ሳገለግል፡፡ መብቴን ስፈልግ አለ፡፡ መብቱን ስሰጠው ማለት ነው ደግሞ፡፡ እንዲህ ነኛ፡፡ ሁለቱም ነኛ፡፡ እንግዲህ አየህ ስትፅፍ ሁለቱን ሆነህ ነው፡፡ ስትቀሰቅስ ስለ ራስህ ስለሚሰማህ ብቻ የምትፅፈው ለምን መሰለህ? የእውነት ይህንን ጽፈኸው ከሆነ ማኅበረሰቡ መዋቅር ነው እንጂ፡ አባላቱ እንዳንተው ሰው ስለሆኑ እንደሚወዱት የተረጋገጠ ነው፡፡ 'ራይት!' ያንተ ተቃራኒ የሆኑ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህን እናልፋቸዋለን፡፡ ሁሉም ሰው ይውደድ አንልም፡፡ እንደ አንተ አይነት ጥቂረት የሚያስጠላት ሴት አለች፡፡ አይደል? Excite የሚያደርጋት አለች፡፡ አሁን ስም አንጠራም እንጂ፡፡

ፈረንሣይ በካርታ ስፋትዋ መጠነኛ አገር ነች፡፡ በታሪክ በሥነ ጽሑፍ፣ በሥዕል፣ በፍልስፍና፣ በአብዮት ስትል ውቅያኖስ የሆነች አገር ነች፡፡ እኔና አንተ የምናወራው በሁሉም ዓይነት ርዕስ ስለሆነ እኔም በቋንቋቸው ሳላነበብኳቸው የመጣልኝን ልስጥህ?

ይኸውልህ! መጀመሪያ ትዝ የታየኝ ጊ ደ ሞፓሳ ነው፡፡ ማስተርፒስ የሆኑ አጫጭር ልቦለዶችን አስነብቦናል፡፡ በእዚያኛው ዓለም በአጫጭር ልቦለዶች ዘርፍ አራት ቁንጮ ደራሲያን አሉ፡፡ ጊ ደ ሞፓሳ፣ አንቶን ቼሆቭ፣ ሶሞርሴት ሞም..." አለና በፍጥነት ስላልጠራቸው አራተኛው ደራሲ ጠፋው፡፡ ቆየና ትዝ አለው፡፡ "ኤድጋር አላን ፖ'ና ፍሎቤር የሚባል ሌላ ፈረንሣዊ ደራሲ አለ፡፡ አንድ ቀን ከጊ ደ ሞፓሳ ጋር ፓሪስ ውስጥ ክንድ ለክንድ ተያይዘው ይንሸራሸራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጨዋታ አለ፡፡ ፍሎቤር "እንዴት ነው ሴትን ልጅ የማቀፍ ጉዳይ?" ይለዋል፡፡

"እኔ በፈለግኩ ጊዜ ደስ ካለችኝ ሴት ጋር መተቃቀፍ እችላለሁ፡፡ ብትፈልግ ላሳይህ" አለና ጊ ደሞፓሳ ሽሌ ቤት ይዞት ገባ፡፡ እና ፍሎቤር ቁጭ ብሎ እየቆጠረ ጊ ደ ሞፓሳ ሰባቱን አከታትሎ ከተደሰተባቸው በኋላ ፍራንካቸውን ከፍለው መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ በዚያን ዘመን ቂጥኝ ገዳይ በሽታ ነበር፡፡ እንደኛ ዘመን ጉንፋን አልተባለም፡፡ ቂጢኝ ጊ ደ ሞፓሳን አመመው፡፡ በዚህ በሽታ አብዶ ሞተ..." አለና ድምጹ የነዘን ቃልት ያዘ፡፡

ምክንያቱም ዕድሜው ገና ነበር፡፡ ብዙ መጻፍ ይችል ነበር" ዓይኖቹ ዕንባ አቀረሩ፡፡ ቶሎ ለስላሳ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ

እንባውን አበሰ፡፡ ተረጋግቶ “ፍሎቤር የፍሬንች ስታይል ፋና ወጊ ታላቅ አርአያ ይሉታል፡፡ በአማርኛችን ሀዲስ ዓለማየሁ ቆንጆ ስታይል አይደለም ያላቸው?

ቀደም ብዬ ፈረንሣይኛን ገና ሳላውቅ በእንግሊዘኛ ሳነበው እንኳ እውነታቸውን ነው ብዬ ነበር፡፡ በኋላ በፈረንሣኛ ሳነበው እውነትም ሐያሲያኑ ጥሩ አይተውታል ነው ያሰኘኝ” አለና ቡትሌዋን አንስቶ አያት:: ካቲካላዋ አልቃለች፡፡ “It is enough for you?” አልኩ፤ መጨመር ከፈለገ ሮጬ ሄጄ አንድ ቡትሌ ገዝቼ ላመጣለት በፈለገ ስሜት፡፡

“ሂድ!” አለኝ በቀልድ “ሁለተኛ በዚህ lower class እንግሊዘኛ ስትናገር እንዳልሰማህ:: ለእንደኛ ዓይነቱ is it sufficient for you? ነው ማለት ያለብህ” አለና ሣቀ፣ በዕለቱ ጥርሴን አሞኝ ስለነበር ለሁለታችንም የሚሆን ያህል አረቄ ገዝቼ መጣሁ፡፡

ቁጭ ብሎ ሲያብሰለስል ደረስኩ፡፡ ለሁለታችንም ቀዳሁና ቡትሌዋን መሐላችን ሰይሜያት ተቀመጥኩ፡፡ በእንዲህ ያለ ወቅት ምንም ዓይነት ጥያቄ አላነሳም፡፡ እሱ ደስ ያለውን አንስቶ እንደሚያወጋኝ አውቃለሁ፡፡

“የት ነበርን?” አለኝ፡፡ አስታወስኩት::

ማርሴል ፕሩስት መጣልኝ፡፡ የጠፋውን ጊዜ ፍለጋ የሚል ልቦለድ አለው፡፡ ቤተሰቡ ሀብታም ናቸው፡፡ ይሁዲ ነው፡፡ አንዳንዴ ይሁዲ መሆን ጂንየስ ሳያደርግህ አይቀርም፡፡ ምናልባት ከሰዎች የበለጠ ጠንካራ የሚያደርጋቸው መገፋት መናቅ ስለበዛባቸው ሳይሆን አይቀርም፡፡ የቻሉት መከራ ብዛቱ!

አይሁድን እንዴ ሮማ፣ ሌላ ጊዜ ባቢሎን፣ ወይም ግሪክ ሁሉ ያሳድዳቸዋል፡፡ የሆነ ብረት ነገር አለ ውስጣቸው መንፈስ ጠንካራ የሚያደርጋቸው፡፡

ፕሩስት ስለራሱ ነው የሚጽፈው፡፡ ሲግምንድ ፍሮይድን አላነበበም፡፡ የኖሩበትን ዓመት ምሕረት አስተያይቼዋለሁ፡፡ እሱ በገዛ ራሱ እንደ ፍሮይድ ነው የሚያስበው” አለና ለራሱ እንደሚያወራ ሁሉ አፉን በመዳፉ ከድኖ “አይ! እረሣሁት መሠለኝ:: እንደገና ፕሩስትን የማነብበት ጊዜ ደረሰ ማለት ነው” አለና እኔን ፊት ለፊት እያስተዋለ “ተወው ደራሲውን ላጫውትህ፡፡ ማርሴል ፕሩስት ባሕሪውም እንደ ሥራው ለየት ያለ ነው፡፡ ምግብ ይወዳል፣ ወይን ጠጅ ይወዳል፣ ሴትንም በደንብ ይወዳል፡፡ ሴቶችን ጠንቅቆ ነው የሚያውቃቸው፡፡

@Amharicbookstore



በሽተኛ ነው፡፡ ስለዚህ በሕይወቱ ማለቂያ ላይ መኝታ ቤቱን በቡሽ አሽገው፡፡ ጣራውንም ግድግዳውንም ወለሉንም፡፡ አምስት ዓመት ሙሉ ከቤቱ ሳይወጣ! ብርድ እንዳይገባ፡፡

በወጣትነቱ ተደሰተ፡፡ ከፍተኛውን ማኅበረሰብ አየ፡፡ ‘በኤክስረይ’ ዓይኑ አጠናው፡፡ ሀብቱ አሁን በእኛ ዘመን ሚሊዮኔር እንደምንለው ዓይነት ነው፡፡ እናቱና ሴት አያቱ በጣም ነው የሚወዱት፡፡ ሴት አያቱ ሳይንቲስት ነበረች፡፡ ነፋሻማ አየር ሲኖር ካጋርት ሳትደርብ ዞር ዞር ብላ ነበር የምትመጣው፡፡ ፕሩስትን “ና! እንንሸራሸር” ትለዋለች፡፡

ሰባት መጻሕፍት ጻፈ፡፡ ዋና ገፀ ባሕሪው ፍራንሷዝ ናት፡፡ የርሱ ፈረንሣይኛ ደግሞ ውብ ነው፡፡ አቤት ዓይኑ ሲያይ፤ አይ አጨዋወቱ፣ አይ አገላለጽ፣ አቤት ፈረንሣኛውን ሲያውቅበት፤ እንደ እሱ ነው ቋንቋን ማወቅ፡፡ አንዳንዴ እየጣፈ የፍራንሷዝ አባባል ሲጠፋበት ብቻ ነው በብዙ ልብስ ተጀቡኖ እሷ ወደምትኖርበት ክፍለ ሀገር ሄዶ አጣርቶ ይመለስና እንደገና ታሽጎ ጽሕፈቱን ይቀጥላል፡፡

ታዲያስ?! ሁለት መቶውም ገፀ ባህርያቱ ሁሉ በሕይወት ያሉ ናቸው፡፡ የፓሪስን ሕይወት እንዳለች ነው ቁጭ የሚያደርጋት፡፡

Forget ሐያሲያን! ፒ! እኛ ከማርሴል ፕሩስት ጋር ነን፡፡ ጨዋታውንም ያውቅበታል፡፡ በእኛ አገር ‘ካፉ ማር ጠብ ይላል’ ብለን እንደምናደንቀው ዓይነት ሰው ነው፡፡ አንድ ቀን ተጋብዞ ወደ ግብዣው ቦታ ይሔዳል፡፡ በመስታወት ውስጥ አንድ ሽማግሌ ያያል፡፡ ቆም ብለህ ማነው ትላለህ አይደል? እሱም ተጠራጠረና ቆም አለ፡፡ ሽማግሌውን አየው፡፡ ያየውም እራሱን ነው፡፡ “ለካ እዚህ ጋ ደርሰናል” አለ፡፡

ስለ ኒቼ በቂ አላውቅም:: ከማስታውሰው ግማሽ ጎኑ የፖላንድ ሰው ነው:: ዕድገቱ ግን ጀርመን ነው:: በጣም Briliant ነው ከታላላቆቹ ፈላስፎች ከሚባሉት አንዱ ነው:: Existentialism የ21ኛው ክፍለ ዘመን ፍልስፍና ነው:: የዚህ ፍልስፍና አያቶች አንዱ ይህ ኒቼ ነው::

ይኸውልህ፡፡ እኔና አንተ ከዚህ ወጣን፡፡ አንተ ወደዚህ ስትመለስ አዳልጦህ ፍርጥ ሙትት ልትል ትችላለህ፡፡እኔም እንደ ዕንቁላል ተሰባሪ ነኝ፡፡ የቀድሞ ፍልስፍና፣ ሐቅ ምንድነው? ዘለዓለም ምንድነው? እግዚአብሔርስ? እያለ ነበር የሚመራመረው፡፡ ‘ኤግዚስቴንሻሊስቶች’ እንዲህ አሉ:: ተፈላሳፊው ማን ነው? ይህን የማወቅ አቅም አለው ወይ? ኗሪ ሰው ነው፡፡ መኖር ምንድነው? ማን እንደሆንን፣ ከየት እንደመጣን፣ ወዴት እየሄድን እንደሆነ ምንም የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ጨለማ ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ አብሰርድ

(absurd) ይሉታል፡፡ It is a tale told by an idiot Full of sound and fury. Signifying nothing ሲልህ ሼክስፒር ኤግዚስቴንሺያሊዝም ነው እኮ፡፡ ዛሬ ግን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አፍ አውጥቶ ተናገረና ኤግዚስቴንሺያሊዝም ፍልስፍና ሆነ፡፡ ስያሜውን የሰጠው ፈላስፋ ዦን ፖል ሳርት ነው፡፡

Existentialism በአጭሩ ምን መሰለህ? በፊት ፍልስፍና የሚያጠናው 'ኤግዚስት' ነው፡፡ 'ኤግዚስት' ማለት ምንነትህ እግዚአብሔር ምንድነው? ምንድነው ጥሩ፣ መጥፎስ ምንድነው? ምንድነው ሞራሊትስ? ሰው ምንድነው? ምንድነው? ምንድነው? ነው፡፡ ሲሉ Existentialism እሺ ያንን የሚያውቀው አዋቂው ማነው? 'ኤግዚስት' የማደርገው እኔ ነኝ፡፡ አይደለም? መጀመሪያ መሣሪያ እንውሰድ አረንጓዴ መነፅር ብታደርግ አረንጓዴ ይታይሃል ቀይ ብታደርግ ቀይ ይታይሃል? ጭንቅላታችንን ምን እንደሆነ ይመረምራል ዕውቀቱ ልክ ይሁን አይሁን ያኔ ነው የምታውቀው፡፡ ማነው ይኼ All I know is Existentialism ማለት የግለሰቡን ኤግዚስት ማድረግን ነው የምናጠናው፡፡

እሺ ደግሞ እንዲህ እንየው፡፡ የእኔ ኑሮ ምንድነው? አንድ ተሰባሪ ነኝ፡፡ በማንኛውም ጊዜ ይሆናል፡፡ በቃ ኮ ልታገኘኝ ትችላለህ፡፡ ሁለት ቋሚ አይደለንም፣ እርግጠኞም አይደለንም፡፡ ሌላው ሁሌም የምንኖረው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ትናንትም ነገም የሆነ ነገር አላቸው እኔ ውስጥ ትናንት ውስጥ ነበርኩበት ነገ ውስጥም እኖርበታለሁ፡፡ ማለት አሁን እዚህ እንደምታየው ኩባያ አይደለሁም» አለ፡፡ የሻይ ኩባያውን አንስቶ እያሳየኝ፡፡ « እኔ ግን ብፈልግ ወደ ልጅነቴ እመለሳለሁ፡፡ ከፈለግኩ እዚሁ ያለሁበት የወደፊቱን ለማየት እሞክራለሁ፡፡ አልያም የመጨረሻዋ ልጅ ደርሳ ስድራት ይታየኛል፡፡ እዚያ ውስጥ ካለሁ ሁሉም ጊዜ ውስጥ ነኝ፡፡ ሟች ነኝ፡፡ እና ደግሞ መሞት የማልፈልግ ነኝ፡፡ ከሁሉም የባሰ ምን አልባት ለጭንቅላቴ ማለት ነው፡፡ እኔ እንዲገባኝ እፈልጋለሁ፡፡ የፀሐይ፣ የተፈጥሮ፣ የእግዜሩ ምስጢር እንዲገባኝ እፈልጋለሁ፡፡ ሁሉንም እንዲገባኝ የሚያስችለኝ ኃይል የለኝም፡፡ በዚህ በኩል እኔ ውስጥ ያለው የማወቅ ጉጉት በዚያ በኩል አንድ ማወቅ የለም፡፡ ምንድነው የሚታወቅ? ይህ የእኔን ኑሮ Absurd ያደርገዋል፡፡

Absurd ውስጥ ነው የምንኖረው፡፡ አልቤርት ካሙ ወደ ተባለ ደራሲ ልውሰድህ፡፡ ይህ ፈላስፋ ነው 'የአብሰርድን' ምስጢር የገለጸልን፡፡ The Myth of Sisyphus የምትል ትንሽዬ መጽሐፍ አለችው፡፡ ብዙ ነገር በውስጧ አለ፡፡ ምንድነው በአጭሩ የምትለው፡፡ አሁን ያልኩት ጭብጥ ላይ ታተኩራለች፡፡ እንዲገባኝ እፈልጋለሁ አልችልም፡፡ ከየት መጣሁ? ለምን መጣሁ? ወዴት ነው የምሄደው? የኑሮ ዓላማው ምንም አይታየኝም it doesn't make sense,

@Amharicbookstore



ስለዚህ ለምን መኖር እቀጥላለሁ? ለምን ራሴን አልገልም፡፡ ምንድነው ይኼ 'አብሰርድ' ውስጥ ሆኖ መቀጠል፡፡ እ? ስል፡፡ እንዴ ለምን እራሴን እገላለሁ፡፡ እያለ ይቀጥልልናል፡፡

ደራሲው አልቤር ካሙ ስፖርት በጣም ይወዳል፡፡ በወጣትነቱ የትምህርት ቤቱ ግብ ጠባቂ ነበር፡፡ ዋና በጣም በጣም ይወዳል፡፡ ሁሌም እንደዋኘ ነው፡፡ በዚህ ላይ Fighter ነው፡፡ እንዲያውም 'ኤግዚስቴንሻሊዝም' ናት ልትላት ትችላለህ፡፡

ሕይወት አብሰርድ ትሁን እንጂ ይኸው እንደምታየው ነው፤ ደስ ብሎን ነው የምንኖረው፡፡ ቢገባንም መሞታችን ቢያናድደንም ይኸው ባለችው ጊዜ እስካሁን እየኖርን ነው፡፡ በቃ ቆንጆ አድርጌ እኖራታለሁ፡፡ አሪፍ አድርጌ እኖራታለሁ፡፡ የምኖራት ደግሞ እኔ እንደመሰለኝ ነዋ፡፡ ሲመስለኝ እንግዲህ አየህ እኔ አልቤር ካሙን ሆንኩ፡፡

አልቤር ካሙ ትውልዱ አልጄሪያዊ ነው፡፡ ሦስተኛ ትውልድ መሰለኝ፡፡ ግማሽ ጎኑ ስፓኒሽ ነው፤ በእናቱ በኩል፡፡

ጋዜጠኛም ነበር፡፡ ፈረንሣይ በዘመኑ አልጄሪያን የምታያት እንደ አካልዋ ነበር፡፡ ሌሎቹ አገሮች ግን እንደ ቅኝ ግዛትዋ ነበር የምትገዛቸው አልጄሪያ ግን አገራችን ናት ብለው ፈረንሣዮች ያስባሉ፡፡ በጣም ብዙ እንድትለማ አድርገዋታል፡፡ ብዙም ዓመታት አልጄሪያ ውስጥ ኖረዋል፡፡ ይህንን ሁሉ ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ፈረንሣዮች ከአልጄሪያ ይውጡ ሲባል አልቤር ካሙ በዚህ ሐሳብ አልተደሰተም፡፡ ምክንያቱስ ነብሱ ፈረንሣይ ናት፡፡ ግን አለ ሲጽፍ "ምንም አልጄሪያ ውስጥ መኖሩን ብንወደውም ውጡ ካሉን የእነሱ አገር ነውና መውጣት ነው ያለብን" ብሎ ጻፈ፡፡ ያኔ ሳንሱር የለም፣ ከንቲባው ይህንን ሲያነብ ከስሶ ያሳስረዋል፡፡ ስለዚህ ጓደኞቹ ገንዘብ አዋጥተው ወደ ውጪ አገር ሸኙት፡፡ ፖሊሶች ትዕዛዝ ሲደርሳቸው ፈልገው ፈልገው አጡት፡፡ የጓደኞቹ ፍጥነት ቀደማቸው፡፡ አየኸው አልቤር ካሙ ላመነበት ነው የሚቆመው ማለት ነው፡፡

ካሙ ቴአትር፣ አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድም ይጽፋል፡፡ ሲኖር ሲኖር አዶልፍ ሂትለር የጀርመን መሪ ሆኖ መጣ፡፡ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተቀሰቀሰ፡፡ ፈረንሣይ በ15 ቀን በጦርነቱ ድል ሆነች፡፡ ሃሜታው ምንድነው መሰለህ "እንደ ለንደን ፓሪስ ከምትወድምብን ይቅርብን ብለው ነው" ይሉናል፡፡ እነ ጄኔራል ደጎል "ፍራንስ አልተሸነፈችም እየተዋጋች ነው" አለኝ ይላል በቢቢሲ፡፡ እና ካሙ የኮሙኒስት ፓርቲ ትግል የሚል ጋዜጣ በሕቡዕ ጀመረ፡፡ ያኔ ለኮሚኒዝም አይደለም የሚዋጋው፡፡ ለፍራንስ ብሔራዊ ደህንነት ነው፡፡ ቢያዝ ይረሸኑታል፡፡ ከእነ ጄኔራል ደጎል ጋር ነው ሰልፉ፡፡ ለአገሩ ደህንነት ነው፡፡ ምንም ኤግዚስቴሻሊስት ቢሆንም ሰው ነው፡፡ ሰላም እንደመጣ እነ ቸርችል፡፡ ሩዝቬልት እና ስታሊን በአንድ ጎን

ሆነው 'አላይድ ፎርስን' አልመሰረቱም? ተቃራኒዎቻቸው ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ጃፓኖች ደግሞ አክሲስ ፎርስን መሠረቱ። ጦርነት ገጥመው የነሂትለር ቡድን ተሸነፈ። ከዚያ ሰላም ሲመጣ በጣም የተዋጣለት አረፍ ደራሲ ሆኖ ቀጠለ። 'ዘ ሚት ኦፍ ሲስፈስ' ምን ይለናል መሰለህ። እንዳየነው ካሙ ቅን ነው። For the good for the right የቆመው።

"ሲሲፈስ መሠረቱ የግሪክ ሚትዮሎጂ ቃል ነው። አየህ በጣም ይወዳት ነበር አማልክት። ኑሮ ከባድ ነው አይደለም። እንኖረዋለን። ዋናው ጥያቄ ልኑር ወይስ ልሙት አይደለም። ለመኖር ቆርጠናል አይደል? ስናየው ደግሞ ስቃ 'ሲሲፈስ' እኛ ነን። ለዘለዓለም አይደለም እንጂ. እኛም ኑሮን እናልፋለን። እኔ አሁን ሲሲፈስ ሲታየኝ እያለቀሰ ለእራሱ እያዘነ አይደለም። እዚያ ላይ እንደርሳለን። እኛም ኑሮአችንን እንደእዚያው ነው የምንገፋው። ማለት አልሞትም እኖራለሁ ነው መልሱ። የፍልስፍና ጥያቄ ነው የኤግዝስቴንሺያሊዝም!

ከአልቤር ካሙ ጋር እንቀጥል። ቀጥሎ ምን ይጽፋል The Rebel የተባለውን መጽሐፍ ጻፈ። ጥራዙ ወፈር ይላል። ይጥማል ሲያነቡት ይጣፍጣል።ብቻ እኔ በዘመኑ በበቂ ሁኔታ የአውሮጳን ታሪክ ስለማላውቅ አንዳንድ ነገሮች ካሙ ምን እንደሚል በቂ አልገባኝም እንጂ. ካነበብኩት ሸጊያ ቆንጆ መጽሐፍ ነው።

እዚያ ላይ ደግሞ ምን መሰለህ? መኖር መረጥን አይደለም? አብረን ነዋ የምንኖረው። ግለሰብ ሆነን ማኅበረሰብ ውስጥ ስንኖር 'ሲሲፈስ' አላልንም? እ ፈላስፋም ሆኖ አርቲስትም ሆኖ ዘመኑን ነው የሚያጠናው የሚሆነውም። አሁን እንግዲህ የካሙ ዘመን የሂትለር ዘመን ነው። የእስታሊን ዘመን ነው። የአብዮት ዘመን ነው። The Rebel ሰው እንደ አብዮተኛ። በእንግሊዘኛ in rebel ነው።

ምሰራፍ አንድ፣ ባሪያ መቼ ነው ጌታውን «እይ!» ብሎ የሚቃወመው? አብዮት ማለት ይህቺ እኮ ናት። ይህቺ ምሣሌ በግለሰብ ነች። ያኛው ደግሞ አብዮት በኅብረተሰብ ነው። እንጃ የመነው ቢቃን ባርነት በባሪያ ስንደምር ጌታው ሲጭነው ሲገርፈው ምን ሲለው ይችል ይችልና ከዕለታት አንድ ቀን ይገነፍላል። የሚገርመው የዚያን ዕለት ጌታው አልገረፈውም እኮ ሌላ ቀን የሚያደርገውን ብታይ መስቱን ነው የሚያወርድበት። በዕለቱ ግን ምን አልባት «ተነስ ውጣ!» ነው ያለው፣ የዚያን ዕለት። በቃ።

«አልወጣም!» ይላል ድንገት ባሪያው። አለቀ። ያ ሁሉ ተደምሮ ተደምሮ አብዮቱ'ጋ ደረሰ። ልክ ዕዋ ሲሞላ እንደሚፈስ ነው።



አልቤር ካሙ The Rebel እንዲህ ይልሃል። ሰው ራሱን የሚያጠፋው ትልቅ ነገር ስለደረሰበት አይደለም። ትንሽ ነገር ናት። በአብዛኛው ዛሬ የተንጠለጠለው ሰውዬ ጠዋት ለአደጋ የምታጋልጠው ትንሽ ነገር ነች። ለምሳሌ «ታዲያስ አሁሀ!» ይለው የነበረው ጓደኛው ዝም ብሎት አልፏል። ይህቺ ልትሆን ትችላለች ለሞት የዳረገችው።

«ታዲያስ! አሁሀ! መቼ ነው? አብረን እእእ ...» ብሎ ቢሆን ኖሮ ራሱን አያጠፋም ነበር።

የባሪያው እንደዚያው ናት። ጌትየው ያን ቀን በሰላም አልፎት ቢሆን ኖሮ ይቀጥል ነበር።

ካሙ ምን ሆነ መሰለህ? እኔ ያልኩትን ላክልልህ ካሙ በዘመኑ ፋሽን ነበር። ፍራንስ ስሄድ አልቤር ካሙ ፈላስፋው ዣን ፖል በዚያን ዘመን እነሱን ያላነበበው 'ኢንቴሌክችዋል' እና ወጣቶች አልነበርንም። መጻሕፍቶቻቸው በደንብ ይሸጡ ነበር። ሥራቸው አረፍ ብቻም አይደለም ፍልስፍናም ምርምርም ነው።

አልቤር ካሙ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ደግሞ ላሳይህ ።ይህንን አንተ ነህ የምታስተካክለው እዚህ ውስጥ» አለና በጣቱ ጭንቅላቱን ጠቆሞኝ ትረካውን በተመስጦ ቀጠለ «ካሙ የኖቬል ሽልማት በሥነ ጽሑፍ አግኝቷል። ዣን ፖል ሳርትም እንዲሁ ተሸልሞ ነበር ተቃወመ። እንዲህ አለ «እኔ የካፒታሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ሊሸልመኝ ክብሬ አይፈቅድም» ብሎ እምቢ አለ። እሱ ብቻ ነው የኖቤል ሽልማት አልቀበልም ያለው። ምክንያቱም እሱ ኤግዚስቴንሺያሊስት ብቻ አልነበረም። ኮሚኒስትም ጭምር ነው። ትግላቸው በየእራሳቸው ነው እንጂ. ሳርት የፍስልፍና መሪ ናቸው። ካሙ ደግሞ የፍልስፍናና በሞራል ወጣቱ ትውልድ ይቀበለው ይከተለው ነበር።

«ሲሪየስ' አርቲስት ነው። ምን? ማነው ይሁዲ? ምነው ባክህ? » ጮኸብኝ። «አሁን ስነግርህ ግማሽ አልጀሪያ ግማሽ ስፔን እያልኩህ? አዎን ዣንፖል ሣርትር ይሁዲ ነው። ሸውራራ ነው፣ አጭር ነው። ወፍራም መነፅር ያደርጋል። የሲሞን ደ ቦቪዋር 'ቦይፍሬንድ' ነው። እንዳይጋቡ፣ ጋብቻ የቡርዣዋ ፎርማሊቲ ነው። ስለዚህ መዋደድ ይበቃናል ብለው በፍቅራቸው ቀጠሉ። አብረው ኖሩ።

ሲሞን ደ ቦቪዋር ደራሲ ናት። ዘ ሰከንድ ሴክስ የሚባል መጽሐፍ ጽፋለች። የሴቶችን ትግል ፍልስፍና ጀምራ የመራቻቸው ነች። አሁንም የሴቶች ትግል ሲነሳ ሲሞን ደ ቦቪዋር ትነሳለች። እግዜርየው ታሪክ ሲሠራ ወንጀለኛውን አንድ ላይ ይሰበስብልሃል። እነ መንጌ እነ ምናምንን እነ ምናምንን አይተሃል። እነ ሂትለርን አይተሃል። ጀግኖችንም አንድ ላይ

ይሰበሰባል:: ታሪክን ስታይ አይገርምህም እንደዚህ ሲያደርግ? እነዚህ ሣርትና ቦቧቫር ግን ጀግና ለጀግና ናቸው::

አልቤር ካሙ ደግሞ የኖቤል ሽልማት ሲቀበል እንዲህ አለ:: «ክብር ይሰማኛል:: አመሰግናለሁ:: እንዲያም ሆኖ ይህ ሽልማት በእኔ እምነት የምትገባው ለጓደኛዬ ለአንድሬም ማርሎ ነበር» ብሏል::

አንድሬ ማርሎን ላሳይህ:: ማርሎ ዲፕሎማት ነው:: የደጎል ጓደኛ ነበር:: በስፔን የእርስ በእርስ ጦርነት ሕጋዊውን መንግሥት ደግፎ የተዋጋ ፓይለት ነበር:: እንዴት ዓይነት ቡድን እንደሆነ ላሳይህ እኮ ነው ይህን የማወራህ:: ኧርነስት ሄምንግዌም በስፔን ውጊያ ላይ የአንቡላንስ ሾፌር ሆኖ ተዋግቷል:: ለአደጋ እኩል ይጋለጣል:: እሱ ግን አይተኩስም:: እሱ ሌሎችም ስፔን የዘመቱ ቆንጆ ቆንጆ ሰዎች:: 'የጂኒዬሱ' ወገን በመጨረሻ ተሸነፉ::

ካሙ Moral standard አለው:: ማለት የቤተ ክርስቲያን ምናምን ምናምን አይደለም:: 'ኤቲይስ' መሆኑ እየታወቀ 'ሞራሊቲ' ማለት እንደ እሱ ነው:: እሱ እኔ በዚያን ጊዜ ስገልጸው የኢየሱስ ታናሽ ወንድም ይመስለኛል:: ለሰው ያላቸው ፍቅር ያላቸው ድፍረት ምንም አይፈሩም:: ሰተት ብሎ መሄድ ነው::

ቴአትር በጣም ይወዳል:: መጻፍ፣ መጫወት፣ ማዘጋጀትም:: የራሱ የቴአትር ክለብ አለው:: መጀመሪያ ቴአትሩን ፓሪስ ያሳይና ከዚያ ፈረንሣይን ይዞራሉ:: ምን አልባትም ፈረንሣይኛ ተናጋሪ አገሮች ላይ ሳይዘዋወሩ አይቀሩም:: ፓሪስ አሳይተው ሂዱ ማርሴ ይላቸዋል:: አንድ ዓይነት ችግር ሲያጋጥማቸው ይነግሩታል:: "መጣሁ" ይላቸዋል::

እና ከዕለታት አንድ ቀን የቴአትር ክለቡ ልኳቸው ወደ ደቡብ ፈረንሣይ መሰለኝ:: ተዋንያኑ ጓደኞቹም፣ ልጆቹም ናቸው:: እዚህ ከተማ እንገናኝ አላቸው:: ድንገት እመጣለሁ ባላለበት ከተማ ሄደና ተገኘ:: ሲተውኑ አየ:: «በሉ ደህና ሁኑ!» ብሎ ወደ ፓሪስ ለመመለስ ወደ ባቡር ጣቢያ ሄደ:: ትኬት አስቆረጠ:: ባቡሩ እስኪመጣ ይጠብቃል:: አንድ ጓደኛው ድንገት መጣ::

«ኤ! አልቤር!»

«ከሞቫ?»

«ምን እያረክ ነው?»

«ወደ ፓሪስ እየሄድኩኝ ነው:: የባቡር ትኬትም አስቆርጫለሁ::»

«ምን በባቡር አስኬደህ? እኔም ወደ ፓሪስ እየሄድኩ ነው ና በመኪናዬ ተሳፍረን እንሂድ» አለ::



በመኪና ሲሄዱ ሲሄዱ ወቅቱ ክረምትም አልነበረም:: መንገዱም የሚያዳልጥ አልነበረም:: መኪናዋ ከመንገድ ወጣችና ከዛፍ ጋር ተጋጨች:: ጓደኛው ምንም አልሆነም አልቤር ካሙ ለዘለዓለሙ ተሠናበተ፡፡ ካሙ ከሞት ጋር የነበረው ቀጠሮ እንዳያመልጠው የተላከ መልዕክተኛ ይመስላል፡፡ ፍልስፍናውም አሟሟቱም Absurd እንደሆነ ተሰናበተን::

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ከጀርመን ጋር አይደለም የምንዋጋው አይደል የምትለው ፈረንሣይ ሆነህ? ካሙን ስትሆን ግን Letters to German friend ብሎ ጻፈ:: እኔ በኋላ መጽሐፍ ሆኖ ነው ያነበብኩት:: በምን መጽሔት ውስጥ ይሁን እንጃ ብቻ በግልጽ እንዲደርስ አድርጎ ጻፈ:: እኛና እናንተ እኮ ጥል የለንም:: ሕዝብ ነን ቀጣይ ነን... ነው ነገሩ:: ለአገሩ ልጆችም ለእነዚያም ነው ነገሩ::... እንዴ? ከጀርመን ጋር ምናምን ምናምን አይደለም የምትለው:: ... እ ካሙ ነዋ እናትክን ብሎ ይቀጥላል::

አዎን እየተዋጋን ነው:: የምንዋጋው ከሂትለር ጋር ነው እንጂ ጀርመኖች እኮ እንደኛው ሰዎች ናቸው:: ለጀርመን ጓደኛዬ ነው የምጽፈው ይልሃል::... ብቻ ሃሳቡ እንደዚህ ነው:: የአገሩ 'የሞራል ስታንዳርድ' ተሸካሚ እንደማለት ነው:: ይኸውልህ እንግዲህ ከሂትለር ጋር ስንዋጋ ሌላውን አንረሳም We keep in touch ደግነቱ መልዕክቷ ጀርመን ደርሳለች::

አዎን፡፡ አንተ እስካልሰለቸህ መሸከም እስከቻልክ ላቀብልህ ወስኜ ነው የምሰጥህ፡፡ ጠይቅ የፈለግከውን፡፡

ባልዛክ ችስታ ነው፡፡ እዳ ይበዛበታል፡፡ ይሁን እንጂ ሠራተኛ አለው፡፡ ቁጭ ብሎ ይጽፋል፡፡ ሠራተኛው ዘብ ይቆማል፡፡ አንድ ሰው ሊጎበኘው ሲመጣ ገባ ብሎ ይነግረዋል፡፡ እሱም በጓሮ በር ሹልክ ይላል፡፡ መልክ ጥፉ ነበር? ኡ! እንዴት ዓይነት ስቃይ ውስጥ ነበር ባልዛክ!" አለ ጋሼ አዝኖለት፡፡

"ወደ ጀርመን እንሻገር? ገተ ነው የጀርመን ሥነ ጥበብና ባሕል አባት፡፡ ቋንቋቸው ለእንግሊዝ ቅርብ ነው፡፡ ትግርኛ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ያህል መቀራረብ አላቸው፡፡ ገተ ብጠቅስልህ፣ አስተዳዳሪ ነበር፣ ደራሲ ነበር፣ የመጀመሪያውን ሮማንቲክ የሚባለውን አብይ ልቦለድ በኤውሮፓ የፃፈ እሱ ነበር፡፡ በጣም የሚታወቀው ፎስት በሚባል ሥራው ነው፡፡ ፎስት ከጥንት ጀምሮ በጀርመን ውስጥ የታወቀ (ሌጀንድ) አፈታሪክ ነው፡፡

ዶክተር ፎስት የታወቁ አልኬሚስት ነበሩ፡፡ የኤልኬሚስት ዋና ፍለጋው እንደገና ወጣት የምታደርግህን ቅመም ማግኘት ነው፡፡ ትጠጣለች፣ ወይም ትጨሳለች ወይም ወዘተ፡፡ እሷን ፍለጋ ነው

@Amharicbookstore

የዶክተር ፎስት ምርምር፡፡ ቤታቸው መጻሕፍት ብቻ ነው፡፡ ሲመራመሩ፣ ሲመራመሩ፣ ለመኖር አንዲት ሰዓት እንኳን ሳይጫወቱ የግል ሕይወታቸውን ሳይኖሩ አረጁ፡፡

ይኼን ጊዜ ሜፊስቶፌሊስ ይመጣል፡፡ ሜፊስቶፌሊስ በማእረግ ከሳጥናኤል ቀጥሎ ሦስተኛው ደረጃ ላይ የሚገኝ ሰይጣን ነው፡፡ ቀላል ፍጥረት እንዳይመስልህ፡፡ አንዴ ምሽት ላይ ዶክተር ፎስት ከሽርሽር ሲመለሱ አንድ ጥቁር ውሻ ከፊታቸው ቀድሞዋቸው ይሄዳል፡፡ አልፈውትም ይሄዳሉ፡፡ ከኋላ ተከትሏቸው ቤት አብሯቸው ይገባል፡፡ መልኩን ይለውጥና ሜፊስቶፌሊስ እኔ ነኝ ይላቸዋል፡፡ ጃጅተው ማማረር የሚጀምሩባት ጊዜ ደርሳለች፡፡

"ወጣትነትህን ልመልስልህ እችላለሁ" ይላቸዋል፡፡

"መልስልኝ!" ይላሉ ዶክተር ፎስት፡፡

"ግና ኮንትራት ትፈርማለህ::"

"እፈርማለሁ::"

"ስትሞት ነብስህ የእኔ ናት!"

"እሺ!" አሉ ዶክተር ፎስት፡፡ ፈረሙ፡፡ በደማቸው ነው አጥቅሰው የፈረሙት፡፡ ወጣትነታቸውን ሰጥቶዋቸው ሜፊስቶፌሊስ የውል ሰነዷን ጠቅልሎ ይይዛል፡፡ ከእዚያ በኋላማ አብሯቸው ነው፡፡ የዓለምን ዝነጣና መደሰት እንደልብ ያመቻችላቸዋል፡፡ ዋና ዓላማው ኃጢአት እንዲሠሩለት ነው፡፡ እዚያ ደግሞ ከረምት ይበዛል አይደል? እ! ይጨፈግጋል አይደል? የፀደይ ፌስታ አለ፡፡ እዚያ ይወስዳቸዋል፡፡ ግሬቼን የምትባል ቆንጆ ልጅ አለች፡፡ ንፅህት ድንግል ናት፡፡ በሜፊስቶፌሊስ ተንኮል ቀስ እያለ ወጣቱ ፎስት ፍቅር ያስይዛታል፡፡በልጃገረድነትዋ ታረግዛለች፡፡ ወንድሟ የቤተሰቡን ክብር ለመጠበቅ ሲል ይገድላታል፡፡

ሜፊስቶፌሊስ ሁሌም ፎስት ኃጢያት እንዲሠራ መረብ ይዘረጋለታል፡፡ ፎስት ግሬቼንን ለመበቀል ሲል ከወንድሟ ጋር በሻምላ ይፋለማሉ፡፡ የሜፊስቶፌሊስ እገዛም ተጨምሮበት ወንድምየውን ይገድሉታል፡፡ ሁለተኛው ኃጢያት ሆነ፡፡

በመጨረሻም ወጣት ማርጀቱ አይቀርምና ፎስት አረጀ፡፡ ሞት መጣ፡፡ ይኼኔ ሜፊስቶፌሊስ ከተፍ ይልና "ይኸው ፈርመህ፣ ና እንሂድ!" ይላል:: ይኼኔ መላእክትና ሸይጣኖች ተባድነው የዶክተር ፎስትን ነብስ ለመውሰድ ይታገላሉ፡፡ ግሬትቼን በፍልሚያው መስክ ደረሰች፡፡ በእምዬ ማሪያም እርዳታ አሸንፋ የዶክተር ፎስትን ነብስ ይዘዋት ያርጋሉ፡፡

@Amharicbookstore



ተገርሞ "እንዴ! ምን ማለትህ ነው? ይህንን ነው ከገተ ፈጠራ የወደድክለት ትለኛለህ? እኔ ስተርክልህ እንደኮዛክ ነው ዝም ብለህ የኮመኮምከው?!"

በጋራ በኃይል ሣቅንና ትረካውን ቀጠለልኝ::

"አዎን፡፡ ኢኛዚዮ ሲሎኔ ይባላል፡፡ ጥልያን ነው፡፡ ኡ! እንዴት ልበልህ? Bread and Wine ይባላል መጽሐፉ፡፡ ኢየሱስ ይህ የእኔ ሥጋ ነው ይላል ኅብስቱን፤ ወይኑን ደሜ ነው ይላል፡፡ ርዕሱን ደራሲው ከእሱ ነው የወሰዳት፡፡ ይህንን ደግሞ የፃፈው ክርስቲያን አይደለም፣ ኮሚኒስት ነው፡፡ የፃፈልን የራሱን የሕይወት ልምድ ነው፡፡

እስተማሪ ነበሩን ይላል፡፡ የካቶሊክ ቄስ፡፡ አንድ የሚወዱት ተማሪ አለ፡፡ ኮሚኒስት ነው፡፡ ለእሳቸው ደግሞ በጣም አሪፍ ተማሪያቸው ነው፡፡ መምህሩ እሱ ከታገለ ምክንያት አለው ብለው አንድ ቀን ይጠይቁታል፡፡ ዓላማውን ዘርዝሮ አስረዳቸው፡፡ አመኑት፡፡ ከእዚያ የሙሶሊኒ ሰዎች ሲመጡ እኚህ ቄስ ይደብቁና ያድኑታል፡፡ ይህ ነው የብሬድ ኤንድ ዋይን ጭብጥ፡፡

በነገራችን ላይ፣ ኮሚኒዝምና ክርስትና አንድ ናቸው፡፡ ልዩነቱ ትንሽ ነው፡፡ ያውም ሰማይና መሬት!! ሃይማኖቱ ጽድቅ በሰማይ ቤት አለ ሲልህ፣ ፖለቲካው የብስ ላይ እናመጣታለን ይልሃል፡፡

በአንድ ወቅት በዓለም የታወቁ ደራሲያንን ጆዜፍ ስታሊን ጋብዞ ነበር? በአገራቸው የተነበቡ፣ ዝነኛ ደራሲያንን ወደ ሶቪዬት ሕብረት ጋበዘ፡፡ የኮሚኒዝምን ዕድገት እንዲያዩ፡፡ አንዳንዶቹ አደነቁለት፡፡ ብዙዎቹ ተሳስቷል አሉት፡፡ The God That Failed በሚል ርዕስ መጽሐፉ ተፃፈ፡፡ እስታሊን እግዚአብሔር ነኝ ሲል ቃጥቶታል፡፡ ግን የተሳሳተ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማሳየት ይህንን ጣፉ፡፡ ስንት እንደሆኑ አላስታውስም፡፡ ትዝ እንደሚለኝ ጆርጅ ኦረዌል፣ አልቤር ካሙ፣ ኢኛዚዮ ሲሎኔ፣ ሌሎችም የየራሳቸውን እይታ ጻፉ፡፡ ኮሚኒዝም በሐሳብ ነው፡፡ ሶቪዬት ኅብረት ያለው የድሮው ቄሳር ሌላ ልብስ ለብሶ ነው ይሉሃል፡፡

ወደ ላቲን አሜሪካ በደስታ እንሂድ! ሲሞን ቦሊቫር የሚባል ሰው ነበረ፡፡ አሁን ቦሊቪያ የሚባለው የደቡብ አሜሪካ አገር ለዚህ ጀግና መታሰቢያ ነው የተሰየመው፡፡ በእዚያን ዘመን ደቡብ አሜሪካ በሙሉ የስፓኝ ግዛት ነበር፤ ቋንቋውም ስፓኒሽ ነው፡፡ ከብራዚል በስተቀር፡፡ እናም ቦሊቫር ያስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሁሉ ነፃ አውጪ ነው፡፡ በጊዜው በፈረስ ነው ጦረኞች የሚጓዙት፡፡ እንደ ዛሬው ታንክ፣ ወታደራዊ መኪና የሚባል የለም፡፡ ስለዚህ ቦሊቫር

በፈረስ ሳምንት ድረስ ይጓዛል፡፡ እንቅልፉንም ኮርቻው ላይ እያሸለበ የተጓዘበት ጊዜ ነበር፡፡

የአርጀንቲናው ደራሲ የኖቤል ሽልማት አሸናፊ ጋብሪየል ጋርሲያ ማርኩዌስ ታሪካዊ ልቦለድ አድርጎ ጽፎት ነው ያስነበበን፡፡ ቦሊቫር ሁልጊዜም በፈረስ ከመጓዝ ብዛት የተነሣ ቂጡ መጅ አውጥቷል፣ ይልሃል ደራሲያችን በፀንፍ-የለሽ ምናቡ፡፡

ሲሞን ቦሊቫር የማይለየው ጓደኛ አለው፡፡ አብሮ አደጉ ነው፡፡ አሽከሩም ነው፡፡ አንድ ቀን አንድ ጎረምሳ መጥቶ ለሲሞን ቦሊቫር "እኔኮ በጦር ሜዳ የዋልኩ ጀግና ነኝ፡፡ እየኝ ሰድስት ቦታ ቆሲያለሁ አንዱም በጀርባዬ አይደለም" ብሎ ጠባሳውን አሣየው፡፡

"ኦ! ጥሩ ነው፡፡ ግን" ይለዋል፣ ቀኝ እጁ የሆነ ወዳጁን እየጠቆመ "ይኼ ጓደኛዬ ሰላሳ ዘጠኝ ቦታ አካላቱ ቆስሏል፡፡ አንድም ቀን ቆሴልኩ ሲል ሰምቼው አላውቅም" አለው፡፡

ቦሊቫር እያረጀ ሲሄድ እያነሰ፤ እያነሰ መሄድ አመጣ፡፡ ትልቅ የነበረው አልጋ እየሰፋበት ሲሄድ የሕፃን አልጋ ላይ እንደተኛ ነው የሞተው፡፡

የምትከተለዋ ትንቢት ራሷን የምትፈፅም ናት፡፡ በጥንት ዘመን ነጮቹ አሜሪካ ገና ሳይመጡ፣ ኳትዜልኮትል የተባለው የጥበብ አምላክ ሥልጣኔን፣ በሕግ መተዳደርን፣ ሽመናን፣ አንጥረኛነትን፣ እርሻን አስተምሯቸው ሲሰናበታቸው "እመለሳለሁ" ብሏቸው በመርከብ ነበር የሄደው፡፡

ፒዛሮ የተባለው እስፓኒሽ ጀዊሳ (የባህር ዘራፊ) ሦስት መርከብ ሙሉ ነጭ ሠራዊት ይዞ ሲመጣ ምን አሉ? "እንዳለው ይኸው፣ በመርከብ ተመለሰ አምላካችን ኳትዜልኮትል፡፡"

ሽብር መመሪያው የሆነው እርጉሙ ፒዛሮ "እንኳን ደህና መጣህ" ብለው ሊቀበሉት የመጡትን ኢንካ ንፁህን ሰዎች እዚያው ፈጃቸው፡፡ "ከአማልክት ጋር ማን ችሎ ይዋጋል?" ብለው ያመለጡት ለተረፉት ለኢንካ ሕዝብ የተሰራውን ጉድ ነገሩት፡፡ "አማልክትም ቢሆኑ ከወጉን ምርጫ የለንም እንዋጋቸዋለን" ብለው ተሰለፉ የኢንካ ወታደሮች፡፡ ግን አማልክትን ስትዋጋ እንደሚያሸንፉህ እያወቅክ ነውና ያለ ወኔ ነበር የተዋጉት፡፡ ድል ካደረጋቸው በኋላም ጨፈጨፋቸው፡፡ ያልፈጃቸውን በግድ በሰልፍ ክርስትና አስነሳቸው፡፡ በቤተ መቅደሳቸው የተከማቸውን ብዙ ወርቅ ዘርፎ ወደ አገሩ ሲመለስ ደሞ መርከቦቹ ሊይዙለት የቻሉትን ያህል ኢንካ ሰዎች ባሪያዎቹ ይሆኑ ዘንድ ለንጉሱ ገፀ በረከት አቀረበለት፡፡

@Alimabookstore



ፒዛሮ ተመልሶ ወደ ኢንካዎቹ አገር መጣ፡፡ ያለ የሌላቸውን በዝብዞ ሄደና በስፓኝ ውስጥ ወደር የሌለው የናጠጠ ሀብታም ሆነ፡፡ ዓለምን በመበዝበዝ ሀብታም ለሆኑ የፈረንጅ አገሮች ትክክለኛ ናሙና ነው...

ሌኒን ከሁሉ በላይ የሚወዳት አለች ላጫውትህ፡፡ ድርሰቷ የጃክ ለንደን ናት፡፡ <u>To build a Fire(?)</u> ታሪኩ የተመሰረተው በኤስኪሞዎች ኑሮ ላይ ነው፡፡ ኤኮኖሚያቸው ከእጅ ወደ አፍ ከመሆኑ የተነሳ፣ ራሱን የማይችል አንድ ሰው እንኳ ቢጠጋቸው ሊመግቡ አቅም የላቸውም፡፡ ይጓዛሉ፡፡ አንዱ ሸመገለና ራሱን መቻል አቃተው፡፡ ጎሳው ለሦስት ቀን የሚበቃውን ምግብ፣ ውሃና የሚያነደው እንጨት ትተውለት ጉዟቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ሦስቷን ቀን ይኖራታል፡፡ከዚያ ተኩላዎች መጥተው ሲበሉት ሲጮሁ ይሰማል...

ሌኒን ይህችን ታሪክ ከሁሉ በላይ ይወዳታል ስልህ?! ሌኒን ለማነው የቆመው? ጥቂቶቹ ብዙ፤ ብዙዎቹ ጥቂት ማግኘታቸው ልክ አይደለም ብሎ፡ አይደለም ሊታገል የተነሣው? ለብዙኃን መብት ቢታገል እውነት አለው፡፡ አገራችን ስንመጣ ደግሞ በአሉ ግርማ ሌላ ያጫወተኝ አለ፡፡

ከደቡብ ክፍለ ሀገሮች አንዱ ውስጥ ነው፡፡ ጎሳው ለመኖር በቂ የሆነ ፀጋ ከተፈጥሮ አላገኘም፡፡ አንዳቸው እንኳን ራሱን ችሎ ሊቀለብ አይችልም፡፡ ስለዚህ አባቱ ሲያረጅ ልጅዬው ያውቃል፡፡ ከእንግዲህ አቅሙ ከድቶታል፡፡ በቃ፡፡ ባይኖር ይሻለዋል ብሎ ልጅዬው ከኋላ መጥቶ አንገቴንና ጭንቅላቱን ይዞ በድንገት ይጠመዝዘዋል፡፡ እንቅሽ ይላል አንገቱ፡፡ ከእዚያ ይወጣና "ወይኔ አባቴ! አባቴ!" እያለ ይጮሃል፡፡ የምሩን ነው የሚያለቅሰው፤ ለመኖር የሚፈለገው ሁሉ በመታጣቱ ነው እንጂ ሊገለው ፈልጎ አይደለም፡፡ ደግሞ አባትዬውም አባቱን እንደ እዚያ አድርጎ ነው እዚህ የደረሰው፡፡

የሰው ልጆችን ባሕል በተለያየ አቅጣጫ እያሳየኝ፣ በፀጥታ እያዳመጥኩት የምናብ ጉዞዋችንን ቀጠልን፡፡ ጥቂት ቆዝሞ፣ ከካቲካላዋ ላይ ፉት ብሎ ውሃ ተጎንጭቶ፣ ለንፅፅር እንዲበጀን ሌላ ታሪክ ያጫውተኝ ጀመረ፡፡

"በሕንድና በቻይና ሰሜን በሁለቱ መሐል ከፍተኛ ቦታ ላይ ነው ቲቤት የምትገኘው፡፡ በበጋው ወቅት እንኳን የቲቤት ተራራዎች በበረዶ እንደተሸፈኑ ነው፡፡ ቲቤት ይበርዳል መሰለህ?! ሎብሳንግ ራምፓ ነው ያስነበበኝ፡፡

ከፍ እያልን ስንሄድ በኤለቬሽን ውሃ የሚፈላበት የዲግሪ ሴንቲግሬድ ብዛት እየወረደ ይመጣል፡፡ እኛ አገር ውሃ ለማፍላት 100 ዲግሪ ቢያስፈልግ፤ እንደ ቲቤት በጣም ከፍ ባለ ቦታ ላይ 90 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይበቃል እንበል፡፡

ከቲቤት ወርጄ ወርጄ እታች አገር ስደርስ ሻይ ፉት ብል የማቁሰልን ያህል ነው የፈጀኝ፡፡ እንግዲህ ቲቤት ከአገሩ ስፋት ማብቀል የሚችለው መሬት አስር ፐርሰንት ብቻ ነው፡፡ ሲበቅል ግን አሪፍ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ድህነት አለች፡፡ ድህነት ከመከፋቷ የተነሣ የት ደረስን መሰለህ?

እኔ ቲቤታዊ ነኝ፡፡ አንዲት ሚስት አግብቼ እርሻዬን አርሼ መኖር አልችልም፡፡ ስለዚህ ከተቻለ አምስት፤ እግዜር ከፈቀደም ስድስት፤ ሰባት ወንድማማች ሆነን አንዲት ሴት እናገባለን፡፡ አየህ የእኛ ሁሉ ትልበት ለአንዲት ጎጆ ብቻ ነው የሚበቃው፡፡

ጥጋብ ባለበት የሚያም 'ሳይኮሶማቲክ' የሚባል በሽታ አለ፡፡ ሳይኮ ማለት ነብስ ነው፡፡ ሶማቲክ ሥጋ ነው፡፡ ከነብሳችን የሚነሣ በሽታ ማለት ነው፡፡ ነብሰዬዋ ሕመም አለባት፤ ሥጋ ውስጥ በሽታ ታስድራለች፡፡ አሜሪካን ውስጥ ምቾት ስላለ የሆድ ጥያቄ ብዙም ስለማይኖር፤ ብዙው በሽታ ሳይኮሶማቲክ ነው፡፡

ጕርጊዝ ሲሜኖን ድንቅ ደራሲ ነው፡፡ ጠዋት ተነስቶ ነው ሁልጊዜ የሚፅፈው፡፡ ይፅፍ ይፅፍና ሄዶ እንዷን ተኝቶ ይመጣል፡፡ እንደገና ይፅፋል፡፡ ሚስቱ ደግሞ በፍቅር ትወደዋለች፡፡ ታምነዋለች፡፡ እርሱ ግን አትችይኝም ብሏት "በል ደስ ያለችህን እየቀፍክ ፃፍ" አለችው፡፡ በቀን ስንት ሴት እንደሚያቅፍ እንኳን እሷ እሱም አያውቅም፡፡ አይቆጥርማ! አየህ? እዚህ'ጋ ሰውየውን የምትመራው የተፈጥሮ ሕግ አይደለችም፡፡ ሕመሙ ነች፡፡ ይህንን ሕመም ሳይኮሶማቲክ እንለዋለን፡፡" አለና ጋሼ ስብሐት የዘረጋቸውን እግሮቹን ሰበሰበ፡፡ መደብ ላይ ረግቶ መቀመጥ አይችልም፡፡ ቁንጥንጥ ነው፡፡

"ከሌላ ባሕል ጋር ላስተዋውቅህ፡፡ በላቲን አሜሪካ በአማዞን ደን ውስጥ የሚኖር አንድ ዘር አለ፡፡ እነኚህ ሰዎች ያስገረመኝ ዓይነት ባሕል አላቸው፡፡ አንድ ቤተሰብ አምስት ስድስት ወንድ ልጅ ቢወልድ፤ የመጨረሻውን ልጅ ሴት ነሽ እያለ ነው የሚያሳድገው፡፡ እንደ ሴት አስፈላጊውን ሙያና ባሕሪ እየተማረ ልጁ ያድጋል፡፡ ለአቅመ ሔዋን ሲደርስ የሚድሩት ለሀብታም አባወራ ይሆናል፡፡ አየህ፤ ተፈጥሮ የሰጠችህንም ባሕሪ ባህል እንድትለውጥ የማድረግም ኃይል አለው፡፡

@Amharicbookstore



"የወሲብ አብዮት መቼ? እንዴት? እንደተነሳ እንመርምር ድንቅ ነው፡፡ ከንግሥት ቪክቶሪያ ዘመን እንጀምር፡፡ በዚያን ዘመን ወሲብ የሚባል ነገር የለም ሥነ ሥርዓት ከማጥበቃቸው የተነሣ "የፒያኖ እግር እንኳን እንዳይታይህና ወሲብ እንዳይቀሰቅስ ጨርቅ ያለብሱታል፡፡ አንድ ቀን ታድያ የንግስቲቱ ድንክ ውሻ ሱክ ሱክ እያለ ይገባና የኋላ እግሩን አንስቶ የፒያኖው እግር ላይ አይሸናም መሰለህ? ታላላቅ እንግዳ ሁሉ ሳቁ መጣ አመለጠው! "እኛን አላሳቀንም" አሉ ንግሥት ቪክቶሪያ፡፡

ወፎችና እኛ ሰዎች በአብዛኛው አንድ ለአንድ ነው እንድንኖር የተፈጠርነው፡፡ እንደ ካዛኖቫ ዓይነት ባሕሪያት ደግሞ አሉ፡፡ አንዲት ሴት ከአንዴ በላይ ማቀፍ እነሱ'ጋ ነውር ነው፡፡ በድጋሚም አይገናኙም፡፡ እሱ ሃያጅ ነው፡፡

ይህ የካዛኖቫው ግላዊ የወሲብ አብዮት ወደ አሜሪካ ተሻገረ፡፡ ልብ ብለን ስናስተውል ምን ጊዜም አዲስ ነገር በተጀመረ ቁጥር አሮጌው ይከላከላል፡፡ ግን ዘግይቶም ቢሆን አዲሱ መርታቱ አይቀርም፡፡ ጀምስ ጆይስ የፃፈው ታላቅ ልቦለድ በእንግሊዝ አገር እንዳይታተም ተከለከለ፡፡ እኔ ሳነበው ቢያንስ ሩቡ ገብቶኛል፡፡ ሶስት አራተኛው ባይገባኝም እንኳን ውብ ሆኖ ነው የታየኝ፡፡

እንዴት ማለት መልካም! በዚህ የተገነዘብኩት የአንዱን ደራሲ ሐሳብ ገብቶህ የራስህ ለማድረግ ብዙ መድከም አለብህ፡፡ አንተንም ጥሩ የሆነ የምናብ እድገት ላይ ያደርስሃል፡፡ 'የዩሊሲዝ' ገፀ ባህርያት አንዱ ብሉም ናቸው፤ በጣም አጠር ያሉ ሰውዬ ናቸው፡፡ ሚስታቸው በዕድሜ ታንሣቸዋለች፡፡ ቆንጆ ነች፡፡ የመጽሐፉ የመጨረሻው አርባ ገፅ የዚህችን ሴትዮ የሐሳብ ማንሰላሰል ነው የሚያወጋህ፡፡ ነጥብ የለም፤ ዐረፍተ ነገር የለም፤ አንቀፅ የለም፡፡ እንዳለ አንዱ አረፍተነገር አርባ ገፅ ሙሉ የሴትዮዋ ሐሳብ ነው፡፡ እንደ እዚያም ሆኖ አንባቢን የመያዝ ኃይል አለው፡፡ ኢንግላንድም አሜሪካም ውስጥ ብዙ ሀቡእ አሳታሚዎች ከብረውበታል በስውር እየተሸጠ፡፡ ጆይስ ሳንቲም አይደርሰውም፡፡

አሁን ደግሞ ጃስቲስ እ ዳግላስ መጣልህ፡፡ በእዚያን ወቅት የአሜሪካ ባሕል እንዲህ ዓይነት መጽሐፍ እንዲታተም አይፈቅድም፡፡ በጉዳዩ የሚቆጭ አንድ አሣታሚ አለ፡፡ ሳንሱር የለምና በይፋ አሣተመው፡፡ ተከሰሰ፡፡ ዳኛው ጀስቲስ እ ዳግላስ'ጋ ቀረበ፡፡ አነበቡት ዳኛው፡፡ የብያኔውን አባባል በእኔ ቃል ልግለፅልህ፡፡

"'ፖርኖግራፊ' ማለት ሆን ተብሎ በምርጥ ባለጌ ቃላት የሚፃፍ አንባቢው የሚያቅፈው ሲያጣ ለብቻው የሚደሰትበት ነው፡፡ 'ዩሊሲዝ' ግን የሕይወትን ሥዕል የሚያሳይ የሥነ ጥበብ ሥራ ስለሆነ

ፓርኖግራፊ አይደለም" በሕግ ተፈቅዶለት ታተመ። በዩኒቨርሲቲዎች የጀምስ ጆይስን ሥራዎች ማስተማር ተጀመረ።

ይህ ምን ያስተምረናል ብትል? እያንዳንዳችን በሥራ ክፍፍል ድርሻ ይነሳል። በየቦታው ጀግና አለ። ተመልከት፣ ጀምስ ጆይስ ፃፈ። አሣታሚው ደፍሮ ለንባብ አበቃው። ዳኛው ደግሞ በየኑ። ሥነ ጽሑፍም ነጻነቷን ተቀዳጀች።

የድሮዎቹን ደራሲያን የአሁኖቹ በፍፁም አይደርሱባቸውም። የአሁኑ ዘመን ደራሲዎች ሳየቸው በአጠቃላይ 'ዩኒፎርም' እየሆኑ ነው። የፋብሪካ እቃ ሊሆኑ ጥቂት ነው የሚቀራቸው። ይሁን እንጂ የትም ቢኬድ 'ጂኒየስ' ይወለዳል። ምክንያቱም ዓይን እንደሚኖርህ፣ የኅብረተሰቡን ሕይወት ፅፎ የሚያስቀር ዓይን የሆነ ደራሲ ይወለዳል። ሙዚቀኛ አለው፣ ዘፋኝ አለው፣ ደላላና አቃጣሪ እንዳለው ሁሉ፣ ሕዝቡ ሁሉም ነገር ይኖረዋል።

ኤውሮፓ ውስጥ የግሪክ ሥልጣኔ ነበር። በኋላ ሮማ ጠቀለለችው። ይህ ሲቀጥል፣ ሲቀጥል ክርስትና መጣ። የሮማ ኤምፓዬር ክርስቲያን ሆነ። ከዚያ ሁሉም የውበት ነገር ተከለከለ። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሆነ የሚነበበው። እሱም የተጻፈው በላቲን ነው። ይህ ዘመን ነው 'The Dark Ages' ወይም 'ጨለማው ዘመን' የተባለው። ምክንያቱም ምንም ነገር ማሰብ ክልክል ሆነ።

በላቲን እያልኩህ። እኛ አገር መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ በግዕዝ አይደል የተጻፈው? የምንሰማውም በግዕዝ ነበር። እንደሱ ሕዝቡ በላቲን ይሰማዋል። በኋላ ማርቲን ሉተር መጣና ወደ ጀርመንኛ ተረጎመው። ተወገዘበት። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዓይንህን ላፈር አለችው። ሒደቱ ግን ቀጥሎ ሌሎቹም እንደርሱ ዓይነት ሰዎች ወደየአገራቸው ቋንቋ ተረጎሙት።

አይዶለም! ይህ የጨለማው ዘመን እንደመጣ አረቦች በዚህ ጊዜ ታላቅ ተግባር አከናወኑ። የግሪክና የሮማ ሥልጣኔ ያፈራቸውን የጥበብና የሳይንስ መጻሕፍት ሁሉ ወደ ቋንቋቸው መለሱት። እነሆመር አዝማሪውን፣ እነ አርሲጣጣሊስ የሚባሉትን ፈላስፋ ሁሉ በቋንቋቸው የራሳቸው አደረጉ። በአረብኛ ተፅፎ ለዘመናት ቆየ። ከዚያ አውሮፓ ውስጥ ነጋ እንበል። የጨለማው ዘመን እያለፈ ሄደ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ መጻሕፍት ማንበብ ተጀመረ። በእዚያን ጊዜ ከአረብኛ ወደ ላቲን እየተተረጎመ መነበብ ጀመረ። በዚያን ጊዜ ምሁሩ አውሮፓ በሙሉ ላቲን ይናገራል። ያነባል፣ ይፅፋል።

በኋላ ሌላ ትውልድ መጥቶ ይህንን ከአረብኛ ወደ ላቲን የተተረጎመውን ሲያነቡት፣ ለምን የትርጉም ትርጉም እናነባለን?

@amharicbookstore



ቀጥታ ከግሪክ መተርጎም አለበት አሉ። ስለዚህ ግሪክና ላቲን ተምረው በቀጥታ ወደየቋንቋቸው አመጡት።

አዎን። አርቲስቶች የአውሮፓ ሀብት ሆኑ። እነ ሚኬላንጀሎ፣ ዳንቴ፣ ሊዮናርዶ ዳቪንቺ 'የሬነሰንስ' ዘመን ሰዎች ናቸው። አንድ ጨዋታ እዚህ ላይ ያስፈልገናል።

በተሃድሶ ዘመን ላይ የሆነ ነው። ጊርላንዳዮ የታወቀ የሥዕል መምህር ነው። ሚኬላንጀሎ ሥዕል መማር ይፈልጋል። አባቱ ግን ቆንቋና ስለሆነ ከፍሎ እንደማያስተምረው ያውቃል። ስለዚህ ወደ መምህሩ ሄደና "እኔ ያንተ ተማሪ መሆን እፈልጋለሁ። አባቴ ደግሞ ስስታም ስለሆነ እየከፈለልኝ መማር አልችልም። ስለዚህ አንተ እየከፈልክልኝ አስተምረኝ" አለው። ጊርላንዳዮ በጣም ስቆ "እሺ!" አለውና ሚኬላንጀሎ ትምህርቱን ጀመረ።

ጎበዝ ተማሪ ሆነ። ከእዚያም 'ዴስኩ' ላይ የተቀመጡትን የመምህሩን ኦርጂናል drawing ሥዕሎች አንድ በአንድ እየሰረቀ ወስዶ በመሳል፣ ኮፒዎቹን አስቀርቶ የመምህሩን ሥዕሎች ካነሣበት መለሰ። መምህሩም ይህንን አይቶ አንድ ቀን "ጥሩ ትስላለህ። ግን ኮፒዎችህን ውሰድና ኦርጅናሎቼን መልስልኝ" አለው።

ነቄ ተማሪ ተንቀቶባት ኖሯል! በዘመኑ የነበሩት ጳጳስ ሚኬላንጀሎን አስጠሩትና ሲስቲን ቻፕል (Sistine chapel) የሚባል ትልቅ ቤተመቅደስ ውስጥ ለሁለት ዓመት ያህል አዘኑበት።

ሚኬላንጂሎ በግድግዳውና በሲሚንቶ በተነነባው ኮርኒስ ላይ መሣል ጀመረ። የሚፈልገው ሁሉ ነገር ይቀርብለታል። ከእዚያ አካባቢ ብቻ መውጣት አይችልም። በተጨማሪም ዘበኛው ክፉ ነው። ያበሳጨዋል። በመጨረሻ ሥራውን አጠናቀቀ። ሊጎበኝ የመጣው ከሱ እኩል ታላቅ ሠአሊ ነው የሚባለው ቲሽያን (Titian) ተደንቆ ራሱን ስቶ ወደቀ። ተራው ሰው ቢሆን አድንቆ ነው ዝም የሚለው። እሱ ግን የጥበቡ ማስተር ስለሆነ ሕሊናው በተራ አድናቆት ብቻ መገታት ስላልቻለ ነው የወደቀው። ያ ሥራ ዛሬ፣ ቅርስ ሆኖ የዓለም ሕዝብ ወደ ሮማ ብቅ ያለ ሁሉ ይደሰትበታል።

ሥዕሎቹ የቅዱሳን ምስሎች ናቸው። ነብያትም መላእክትም ሸይጣንም በግድግዳም በጣሪያም ላይ ተሥለዋል። ቀንዳሙ ሸይጣን ግን ዘበኛው ነበር።

'ሮማንቲሲዝም' ሲመጣ የጨረቃ ብርሃን፣ የወፎች የማለዳ ዝማሬ ከሁሉም ነገር ይበልጣል ብለህ እንድታምን የሚያነሣሣ ስልት ነው። በሙዚቃም፣ በሥነ ጽሑፍም፣ በሥዕልም ሮማንቲሲዝም አለ።

ተገድበው ደግሞ ሶሻሊስት ሪያሊዝም ሲሉ ታስታውሳለህ፡፡ ሪያሊዝምን ስታይ በፈረንሳይ ስቴንድሃል "ቀይና ጥቁር" ብሉ ለስልጣን የተጠማ ጎረምሳ፣ ወይም ወታደር (ቀይ ዩኒፎርም) ወይም ቀሲስ (ጥቁር መለዮ ልብሱ) ሆኖ ዕድሉን መሞከር እንዳለበት ያሳያል፡፡ ከሁሉ ታላቅ 'ሪያሊስት' ደሞ ቶልስቶይ አለልህ፡፡
አዎን፡፡ በ'ሪያሊዝም' ያየኸውን ነው የምትገልፀው፡፡ በጨዋ ቋንቋ፡፡ በ'ናቹራሊዝም' ግለሰቦቹ በሕይወት እንደሚናገሩትና እንደ ሚገናኙት ትፅፋቸዋለህ ጨዋውን በጨዋ ቋንቋ፣ ባለጌውን ደግሞ በባለጌ ቋንቋ ሲናገር ትፅፈዋለህ፡፡ የዚህ መሥራች ኤሚል ዞላ ነው፡፡
ይህ ዘመን? እስካሁን ስናይ በቆየነው ዓይን ከሄድክ ምንም ላይ ያልረገጠ ጊዜ ነው፡፡ 'የኮምፒዩተርና ኢንተርኔት' ይሉታል፡፡ እዚህ ውስጥ እኔ አላዋቂ ነኝ፡፡ በሰው ልጅ ሕይወት አዲስ ዓለም ነው፡፡

ፓብሎ ፒካሶ ምን አለ መሰለህ? ሁላችንም ሬምብራንት ነው መሆን የምንፈልገው፡፡ ሙሉ ስሙ Rembrandt Harmaens- Zoon Ven Rijn ነው፡፡ ሬምብራንት የሳለው በአብዛኛው የገዛ ራሱን መልክ በመስተዋት እያየ ነው፡፡ ከወጣቱ ጀምሮ እስከ ሽማግሌው የሀዓሊያን ቁንጮ ድረስ፣ ጊዜ ያንን ፊት ሲለዋውጠው ያሳየናል፡፡ ልብ በል ስንጠበብ ብዛት አይደለም የሚያስፈልገው፡፡ ጥቂት ከጥሩ ጥራት ጋር፡፡ ለምሳሌ ዛሬ 'ከልጅነት' ድርሰትህ አንዷን ምዕራፍ አነበብክልኝ፡፡ የኖርከውን ነው የፃፍከው፡፡ 'ሪያሊስት' ሥራ ነው፡፡ ጥሩ እየሄድክ ነው፡፡
የሰው ልጅ ቋንቋን በመፍጠሩ ከእንስሳት በላይ ነው፡፡ ከመላዕክት በታች፡፡ አሁን የለበስካትን ልብስ ሌሎች ናቸው የሠሯት፡፡ ቋንቋንም ሌሎች ናቸው የፈጠሩት፡፡ ቋንቋን ከእናታችን ጡት ጋር አደግንበት እንጂ አንዷንም ቃል አልፈጠርናትም፡፡ የሰው ልጅ ጉልበቱ እዚህ ላይ ነው፡፡ እንደ ጉንዳን ቁጠረው፡፡ ሁሉም ጉልበትህ ናቸው፡፡ ጉልበታቸውም ነህ፡፡ እዚያው ውስጥ ነው የምንኖረው፡፡ ብቻዬን አይደለሁም፡፡
የማንም ሐሳብ የሰው ልጆች ሁሉ ንብረት ነው፡፡ ልዩነቱ እዚያ ውስጥ ያለው እኔ ውስጥ ላይኖር ይችላል፡፡ ነገሩ እንዴት አድርገህ አስተላለፍከው ነው፡፡ ልብስ ከየትም ቢመጣልን እንለብሳለን፡፡ ሐሳብም ድምበር አይከልለውም፡፡ ስለዚህ ሐሳብን እንዴት ተጠቀምክበት ነው እንጂ ሃሳብን ለምን ወሰድክ አይደለም፡፡

አዎን! ደራሲ ነብይ ነው፡፡ እንደ ደራሲው ይለያያል፡፡ አንዱ ታሪክ መልሶ ያስነብብሃል፡፡ ያለፈውን፣ አበው የኖሩትን፡፡ ሌላው

@amharicbookstore



የአሁን ጊዜ የምትለውን፣ የምታየው ግን የማታስተውለውን ያሜውትሃል፡፡ እያስገረመህ፡፡ ነብይ ደራሲ ደግሞ የወደፊቱን ይተነብያል፡፡ በምሣሌነት የምንጠቅሳቸው ሥራዎች አሉ፡፡ የሣይንስ ልቦለዶችን እንውሰድ፡፡ ይህ ድርሰት በደራሲው ምናብ ተፈጥሮ፣ ተጽፎ ከመታተሙ በፊት በምርምር ዓለም አይታወቅም፡፡ በፈጠራ ደራሲያኑ ይተነብዩና፣ ተመራማሪዎች በቁስ አካል ሥጋ አልብሰው እሴት ያደርጉታል፡፡ ሳይንቲስቱ ቶማስ አልፋ ኤዲሰንን እንውሰድ፡፡ አንባቢ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ሲናገር "እያንዳንዱ አሜሪካዊ ቤተሰቡንና አገሩን ይወዳል፡፡ የተረፈውን ፍቅር ለማርክ ትዌይን ይሰጠዋል" ሲል ለደራሲ ያለውን ፍቅር ይገልፃል፡፡
ለዛሬ እንደማሳረጊያ የምለው አለኝ፣ ኢየሱስ ያለው ነው፡፡ "ሁለት ሦስት ሆናችሁ በተሰበሰባችሁበት በመካከላችሁ እገኛለሁ፡፡" ይህ ምን ማለት መሰለህ? የሰው ልጅ ቋንቋ፣ ባሕል፣ ገንዘብ፣ ምርምር... ይህ ሁሉ ተሰጥቶታል፡፡ ይህም ሰው ሁሉ አብሮን እንዲኖርና ምንጊዜም በመካከላችን እንዲገኝ ያደርገዋል፡፡
ሁለት ሆነን ነው የምንነጋገረው፡፡ አንዱ አካላችን ከኅብረተሰቡ ጋር የሚነጋገረውና የእራሱ ዕዳ ያለበት ነው፡፡ እነርሱም የእኔ ዕዳ ያለባቸው፡፡ የእዚያ ማኅበረሰብ አባል ነኝ፡፡ ሥራ መሥራት መብቴ ነው፡፡ ጥበቃ መብቴ ነው፡፡ እያልክ ልትተነትነው ትችላለህ፡፡ አሁን እኔና ማኅበረሰብ ሆነን ዞር እንልና ደግሞ እኔ ማኅበረሰብን ማገለግል፣ መብቱን ሳከብርለት ታስተውላለህ፡፡ እኔ ሁለቱም ነኝ፡፡ ነብስህ ስትቀሰቀስ፣ ራስህ ስለሚሰማህ ብቻ የምትፅፈው ለምን መሰለህ? እውነትህን ፅፈኸው ከሆነ የማኅበረሰብ አባላት እንዳንተ ሰዎች ስለሆኑ ይወዱታል፡፡ አሁን የት ደረስን መሰለህ? ኪነጥበብ፣ ፍልስፍና ምናምን የሚለው የዲክሽነሪ ቃላት ነው እንጂ፣ እኛ ስንፅፍ ዝም ብለን የመጣልንን ነው የምንፅፈው፡፡ ምክንያቱን አናውቅም፡፡ በማናውቀው ምክንያት ሚች አምላክ እንድንሆን ተፈቅዶልናል፡፡ ሰው ሆኖ ቦታ የሌለው የለም፡፡ ሁሉም አለው፡፡ መወለዳችን ብቻ ምስክር ነው ቦታ እንዳለን፡፡ አሁን እኔ የትውልድ ምስክር ወረቀት አያስፈልገኝም፡፡ አሁን ደግሞ ልዝለልልህ...
ሐሲድ የሚባሉ አይሁድ አሉ፡፡ በጣም ነው የምወዳቸው፡፡ እነርሱ ደግሞ የእኛ ዘር ናቸው አይደል? ወደነቡድህ ስንሄድ ጎረቤት አገር ሄደን ተጋብዘን እንደመመለስ ነው፡፡ ሁልጊዜ እኛ የምንወስደው ከእስራኤል ነበር፡፡ ሐሲድ የሚሏቸው ከበቀሉ ቅርብ ጊዜ ነው፡፡ በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን፡፡ በአውሮፓ የሚኖሩ ስደተኛ እስራኤላውያን ናቸው ሐሲድነትን የፈጠሩት፡፡ ይህች የዛሬዋ

እስራኤል በእዚያን ጊዜ የለችም፡፡ አይሁድ እንደተበታተኑ ነው፡፡ 'Approximately' እግዚአብሔር ደግ ነው፡፡

የሙሴ እግዚአብሔር አለንጋ የሚይዝ ነበር አይደል? እነርሱ ግን ደጉን እግዚአብሔር ፈጠሩ፡፡ አሁን የዝብርቅርቅ ሰዓት ነው የማቀብልህ፡፡ At your service! With pleasure ..." አለና የፈለኩትን እንድጠይቀው ዕድሉን ሰጠኝ፡፡ ሞቅ ብሎታል፡፡ በዚህ ጊዜ እንደበቱ ተፍታቶ ያወጋል፡፡ የፈለገውን ያህል ቢጠጣ ሕሊናው ግን ሚዛኑን አይስትም፡፡ ይህንን ለበርካታ ጊዜያት ያስተዋልኩት ነው፡፡

ይኸውልህ እስራኤላውያን እንደ ክርስቲያን አይበተኑም፡፡ ምክንያቱም ዓለም ሁሉ ስለሚያጠቃቸው ሁልጊዜም አብረው ናቸው፡፡ ሲለያዩ ነው እንግዲህ እነዚህ ሐሲድ የሙሴ ተቃራኒ ሆነው የመጡት፡፡ እግዚአብሔር ደግ ነው፡፡ ቆይ እስኪ ላስታውስ" ረጂም ፀጥታ፡፡

እ!... ዝም ብዬ ልንገርህ አንዱን ጨዋታቸውን፡፡ አንድ በጣም ደደብ ሰውዬ ነበር፡፡ ከድድብናው የተነሣ ልብሱን ማውለቅ ያጨንቀዋል፡፡ አንድ ቀን ማታ ቁጭ አለ" የጨዋታችን ውል ጠፋበት፡፡ አተኩሮ እያየኝ "ምን እያልን ነው?

እ! ይሁዲ ደደብ ቢሆንም መጻፍና ማንበብ ይችላል፡፡ ልብሱን ሲያወልቅ ጨርቆቹን አንድ በአንድ መፃፍ ጀመረ፡፡ ጨረሰ፡፡ ተኛ፡፡ ጠዋት ተነሣ፡፡ የልብሱን ቅደም ተከተል ተፅፎ አገኘው፡፡ እርሱን ራሱን ግን ቢፈልግ ቢፈልግ አጣው ስላልተፃፈ...

"እዚህ'ጋ ነው መርፊስ ሎን ላጫውትህ የሚገባኝ:: መርፊ (Murphy) የአይሪሽ ስም ነው፡፡ ትውልዱ አሜሪካዊ ነው፡፡ የመርፊ ሕግ አንደኛው 'Whatever the situation you see might be, you do not understand it' ይልሀል፡፡ ብታይ የገባህ የመሰለህ አልገባህም፡፡ ሁለተኛው ሕግ If any thing can go wrong, it will ሊበላሽ የሚችል ነገር ካለ መበላሸቱ አይቀርም ይልሃል፡፡ ሦስተኛው የመርፊ ሕግ እንዲህ ይላል "የመርፊ ሕግ የሚሉት ነገር የለም::

ይኼውልህ፣ የአሁንዋ እስራኤል ከመፈጠሯ በፊት አይሁድ ማለት በጣም የተናቀና ዝቅ ተደርጎ የሚታይ ዘር ነበር፡፡ በጣም ተገፍተዋል፡፡ እሩቅ ሳንሄድ እነ ሒትለር ከመምጣታቸው በፊት ማንኛውም የምሥራቅ አውሮፓ መንግሥት በአገሩ ችግር ሲፈጠር አመፅ ሲቀሰቀስበት ወደ አይሁዶች ጌቶ ሰፈር ወታደሮች ልኮ አንድ ሰላሳ አርባውን አይሁድ ይፈጃል፡፡ የሕዝቡ ትኩረት ካአመፁ ወደ አይሁዶቹ እንዲዞር" አለ በእጁ በሐሳብ የፈጠረውን የአይሁድ ሰፈር ወደ ጎን እየሣየኝ፡፡

@Amharicbookstore



"በሲግሞንድ ፍሮይድ ላይ ስናወራ ስቃያቸው ምን ይመስል እንደነበር በቀልድ እያዋዛሁ አጫውቼሃለሁ፡፡ አሁንም ልጨምር ልህ፡፡ አገር አልባ ሰው ስታስብ፣ ስቃያቸው በደንብ የሚገባው ዘር ቢኖር አይሁድ ነው፡፡ አገር ከሌለህ ደግሞ ገንዘብንና ዕውቀትን አጣምረህ መያዝ አለብህ፡፡ ቢቻል ሁለቱን ካልቻልክ አንዱን፡፡ የትም ብትሄድ ወይ ለገንዘብህ አለበለዛም ለዕውቀትህ ሲሉ ያስጠጉሃል፡፡ በዚህ እንጂ ዓለምን የሙጥኝ ብለው አገር የመሰረቱት ሌላ ዘር ቢሆን እርግጠኛ ባልሆንም ይጠፉ ነበር፡፡ የሚያልቀው አልቆ የተረፉት የአሁንዋን እስራኤል የመሰረቱት በገንዘብና በዕውቀት ሀይል ነው፡፡ እና ድባቅ በሚመታ የጦር ድል! ዕውቀቱም ገንዘቡም የሌላቸው መአት የጠፉ ዘሮች በዓለማችን ላይ አሉ፡፡ ውሰድ ሬድ ኢንዲያንን፣ ሂድ አውሮፓ ጂፕሲ የሚባሉ ዘላን ዘር ነበሩ አገር የሌላቸው፡፡ አውስትራሊያ ብትሄድ የጠፉ አቦሪጅንስ የሚባሉ ዘሮች አሉ፡፡ በምን ተበልጠው ጠፉ ስትል ሁለቱ ቀደም ብለን የጠቀስናቸው ምትሀቶች ስለሌላቸው ይሆናል መልሳችን፡፡ ገንዘብና ዕውቀት ለማንኛውም የሰው ልጅ ተንቀሳቃሽ አገር ነው" ጋሼ ስብሐት ሲያወራ በእጁም፣ በዓይኑም፣ በትከሻውም፣ በሰራ አካላቱም ነው፡፡ "ቆንጆ እየመጣልኝ ነው፡፡ ልጨምርልህ!" አለኝ ተነስቶ ቆሞ እግሩን እያፍታታ፡፡

"በዚህ ረጂም ዓመታት በፊጀ የንባብ ጉዞዋችን አያሌ ፈላስፋዎች የሰሩትን ሥራ የማንበብ ዕድል ደርሶናል፡፡ ያንን ሩቅ ዘመን በፊደል አስማት አቅርበውልን ተደስተንበታል፡፡ ለእኔ ማንበብ ደስታን፣ መረጃን፣ ዕውቀትን ማግኛ ብቻ ሳይሆን በአንድ ነብስ ሁለቴ መኖር ነው፡፡ ስለዚህ የሩቆቹን ስትፈልግ ጠይቀኝ የማውቀውን አካፍልሃለሁ፡፡ አሁን ግን ኪርከጋር (Kierkegaard ) ትዝ አለኝ፡፡

ከኤግዚስቴንሺያሊዝም አያቶች አንዱ ተደርጎ የሚታይ ፈላስፋ ነው፡፡ እነ ዶስቶዬቭስኪ፣ ፍሬድሪክ ኒቼ፣ ብሌዝ ፓስካል ሌሎቹ አያቶች ናቸው፡፡ ኪርከጋር በቀጥታ በስሙ አይፅፍም፡፡ በተለያዩ የብዕር ስሞች ነው የፃፈው፡፡ ይህ ሰው አንዷ ፍቅረኛውን እንዲህ አላት፣ በእኔ አባባል ልንገርህ፡፡ "እኔ ዘሬ በዚህ ምድር ላይ እንዲቀጥል አልፈልግም" ኪርከጋር በስሙም፣ በዘሩም በዚህች ምድር ላይ መኖር አይፈልግም፡፡ እንዲህ ዓይነትም ሰው አለ፡፡ የነብስ ስቃይ ሲበዛብህ ዓለም ይህን ያህል ይዘገንንሃል፡፡ እንደ ይሁዲዎች ከሆንክ የመኖር መብትህን ታስከብራለህ፡፡ እያት የአሁንዋ እስራኤል የደረሰችበትን፡፡

በደንብ! ሎርድ በርትራንድ ራስልን አስታወሰከኝ" አለና እየተቀመጠ "እንግሊዛዊ ነው፡፡ ፈላስፋም የሒሳብ የመጨረሻ አዋቂም ነበር፡፡ አንደኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመር በዚህ ጦርነት ውስጥ መግባት የለብንም አለ፡፡ የሰማው የለም፡፡ ብቻውን ሰላማዊ ሰልፍ ወጣ፡፡ መንግሥትም ሆነ ሕዝቡ የሚያከብረውና የሚያደንቀው ቢሆንም ወንጀለኛ ተብሎ ለአንድ ቀን ታሰረ፡፡ የእንግሊዞች እምነት 'ብዙኃን ይመውኡ!' ነው፡፡

በርትራንድ ራስል አሜሪካን እየተዟዟረ ንግግር እንዲያደርግ ተጋበዘ፡፡ አሜሪካ እንዴ ባቡር ጣቢያ እንደደረሰ ሦስት ብዙ ገጽ ያላቸው ልቦለዶች ገዛና ባቡር ውስጥ ገባ፡፡ በጥቂት ሰዓት ጉዞ ሦስቱንም አንብቦ ጨረሳቸው፡፡ እዚህ ድረስ ፈጣን አንባቢ ነበር፡፡

ዓለም በቀዝቃዛው ጦርነት ተወጥራለች፡፡ በዚህ ላይ አሜሪካ ቬትናምን ወረረች፡፡ በርትራንድ ራስል ተነሣበት፡፡ አንድ ብቻውንም አይደለም፡፡ የኤግዚስቴንሽያሊዝም ፈላስፋ የሆነው ዣን ፓል ሳርትር አብሮት ተነሳ፡፡ ሁለቱ ስቶክሆልም ውስጥ በኖቤል ሽልማት አዳራሽ ወንጀል ችሎት ተቀመጡና አሜሪካን በሌለችበት ከሰሰው ፈረዱባት፡፡ የአንድን አገር ሉዓላዊነት ደፍራ ወረራ ማካሄዷ አለማቀፍ ሕግ አጥብቆ የሚያወግዘው ኢ ሰብአዊ ማናለብኝ ባይነት ነው፡፡ ያልአንዳች ድርድር በቀጥታ ጦሯን ከሰው አገር እንድታስወጣ በይነናል፡፡ ብዙዎቹ አሜሪካውያን ወጣቶች የሚሰጣቸውን መጠሪያ መቅደዳቸውን ቀጠሉ እስራት ቢሆንም ቅጣቱ፡፡ የአሜሪካ ወራሪ ሠራዊት የነሆቺሚንን የጫካ አርበኞች በናፓልም በምብ እንኳ ሊደቁስ ቢሞክርም ተሸንፎ አገሩ ገባ፡፡

እየተሰባጠረ ሲመጣ፣ ሰብጥርጥሩን እያሰባጠርክ አስተውለው፡፡ የፍልስፍናዎች ፍልስፍና፣ እንደ ወፍ በክንፍ የምትበር፣ እንደ ኤሊ ድንጋይ ለብሳ እንደ ጋራዎቹ ዕድሜ ያላት Solipsism ትባላለች፡፡ እኔ ብቻ ትላለች፡፡

አሁን እውነት እኔና አንተ ያለን ይመስልሀል? የለንም! እኔ ብቻ ነኝ ያለሁት፡፡ እኔ ብቻ፡፡ እነሂትለር እነስታሊን የሉም፣ ኖረውም አያውቁም፡፡ የእኔ ቅዠቶች የሚለብሳቸው መልኮች ናቸው፡፡ እኔ ግን አለሁ፡፡

ተኝቼ ስረሳቸው ደሞ የሉም ቅዠቶቼ፡፡ እኔስ አለሁ ወይ? ይህቺ ጥያቄ በመጠየቋ ብቻ እኔ ሳልኖር አልቀርም፡፡ ግፋ ቢል ጥያቄዎቼ በባዶው ውስጥ አጅበውኛል እንጂ፡፡ ማን ነኝ? ከየት መጣሁ? ወዴት እየሄድኩ ነው? በባዶው ውስጥ ብቻዬን ከምሆን 'ብርሃን ይሁን' አልኩ፡፡ ብርሃንም ሆነ፡፡

@Amharicbookstore



ኢማኑኤል ካንትን አስታወስከኝ፡፡ በፍልስፍናው ሊቃውንት አዲስ፣ ታላቅ የነሶቅራጦስ እኩያ ብለውታል፡፡ ይህንን ፍልስፍና ቀሳውስቱና የሃይማኖት አባቶች አልወደዱለትም፡፡ ግን ሐደቱን ሊገቱት አልቻሉም፡፡ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ሆኖ መፈላሰፍና መነበብ መብቱ ነውና፡፡ በሕጋዊ እስራት ሊያስቀጡት ባለመቻላቸው በሕገ ወጥ ቀጡት፡፡ ብዙዎቹ ውሻዎቻቸውን ጮክ ብለው ነው የሚጠሩት ኢማኑኤል ካንት! እያሉ፡፡ በነሱ ቤት እንግዲህ ያ የተረገመ ፈላስፋ መሆኑ ነው ጭራውን እየቆላ የሚመጣው፡፡

እ! ክርስቶስ ከ12 ዓመት እስከ 30 ዓመቱ የኖረው? የተለያዩ ግምቶች አሉ፡፡ አንዱ በጣም 'Serious' አይደለም፡፡ በጊዜው ግን እንደ ትልቅ ቁምነገር ይቆጠር ነበር፡፡ ሕንድ አገር ኢየሱስ እንደ ተማረ የፃፉ አሉ፡፡ ፋኪር ከሚባሉት ባሕታውያን፣ 'ሜዲቴሽን' ከሚሰሩ 'ጉሩዎችም' ጋር ኖሯል የሚሉም አሉ፡፡ በኋላም ወደ ታሪካዊ ተጨባጭ ሁኔታ እንመጣለን፡፡ ፈሪሣውያን፣ ሰዱቃውያን አሉ፡፡ ሁለቱም ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚጋጩ ናቸው፡፡ እዚህ'ጋ ደግሞ የቄሳር ሠራዊት መሪ አለ? ማነው ስሙ?

እ! ጲላጦስ አለ፡፡ ሌሎች ደግሞ ኤሲን የሚባሉ ከነ ጳውሎስ ፈሪሳውያን የባሱ አክራሪዎች አሉልህ፡፡ እስራኤላዊ ያልሆነ የባዕዳን ገገር ዘር ቢነካን ያረክሰናል ብለው ከነቤተሰቦቻቸው በኅብረት ተሰደዱ፡፡ በምድረ በዳው፣ 'Dead Sea' ወይም ሙት ባህር በሚሉት አካባቢ፣ ዋሻ ውስጥ ይኖሩ ጀመር፡፡ ምን እየሠሩ? እያመረቱ እንደሚመገቡ አላነበብኩም፡፡

ኢየሱስ የነሱ አባል ነበር፡፡ ከ12 እስከ 30 ዓመቱ፡፡ ለዚህም እንደ ማስረጃ የሚጠቀስ መዝገብ በቅርቡ ተገኝቷል፡፡ አንድ አረብ እረኛ አንድ ዋሻ ውስጥ ሲገባ፣ ረዥም ቅርፅ ያለው ጋን ዓይነት ነገር አገኘ፡፡ ጋኑ ታሽጓል፡፡ ከፍቶ ቢያየው ውስጥ ተጠቅሎ የተቀመጠ ብራና አለ፡፡ አረማይስጥ ቋንቋ የተፃፈበት ነው፡፡ የእነ ኢየሱስ ቋንቋ ማለት ነው፡፡እብራይስጥ የእዚያኔ አይነገርም፡፡እንደ አሁን የእኛ ግዕዝ፡፡

እረኛው ብራናዎቹን ለሂብሩ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ክፍል ኃላፊ ሸጠላቸው፡፡ ኢጋጣሚውን ደግሞ እየው፣ አያስገርምም? ዶክመንቶቹ ሲነበቡ ክርስትና ከኤሲን እምነት ጋር በጣም ይመሣሠላል፡፡ ኢየሱስ በእዚያ ዕድሜው እዚያ ነበር በቃል ወደ እውነቱ ያቀርበናል፡፡

የምሁሩ ጥናት ከምን ደረሰ? ብለን መጠየቅ እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ እስካሁን በቂ መርምሮ አላወጣም፡፡ የተቀሩት ብራናዎቹን ግን በአካባ

ቢው ዋሻዎች አሰሳ አድርገው ሰበሰቡዋቸው፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሰውዬ እየደበቀ ነው የሚባል በርካታ ነቀፌታ ተልከበታል፡፡ ግን ምን ታደርገዋለህ? መብቱ ነው፣ ንብረቱ አድርጎታል፡፡ ሲያደርሰኝ መርምሬ አትመዋለሁ ይላል፡፡ በቃ፡፡ አንድ ነገር ትዝ አለኝ አብራኝ ያረጀች ትዝታዬ ነች ላጫውትህ ይረባኛል ብሎ የሚያስባት ወግ ትዝ ካለቸው የሚያክልልኝ እንዲህ ብሉኝ ነው፡፡

"ስለ ሰብአ ሰገል ሰምተሃል፤ ወይም አንብበሃል? ስለ አራተኛው ሰብአሰገልስ? አሪፍ የፈጠራ ሥራ ነው፡፡ ይህንን ለእናቴም አጫውቻት ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ለአንተ ታዞልሃልና እህ! በለኝ፡፡

ከሦስቱ ጋር ነበር አራተኛውም አልማዙንም እንቁንም ወርቁንም፣ ሐሩንም፣ ከርቤውንም በሳጥን ሞልቶ የተነሣው፡፡ ያንን አዲስ ኮከብ እየተከተለ እጅ መንሻውን በግመል ጭኖ ጉዞ ጀመረ፡፡ ባሕር ላይ ማዕበል እንደሚነሣ ዓይነት፣ እዚህ በረሀ የአሸዋ ማዕበል ይነሣና አካባቢውን ድብልቅልቁን ያወጣዋል፡፡ አውሎ ነፋሱ አልፎ ዙሪያውን ቢመለከት አራተኛው ሰብአሰገል ብቻውን ነው፡፡ ጉዞው አዘገየውና ቤተልሔም ደርሶ ሕፃኑን እጅ ሳይነሣ ቀረ፡፡ ግን ምን ጊዜም ይፈልገዋል፡፡

ላሳጥርልህና፣ ሰውዬው ሲርበው ሲጠማው ከእዚያው ከእጅ መንሻው ላይ እየሸረፈ ፍለጋውን ይቀጥላል፡፡ የቅርብ ምሥራቅን ምድር ያዳርሳል፡፡ "ይኼን ጊዜ ጌታ የአሥር ዓመት ልጅ ይሆናል" ይላል እየፈለገው፡፡ ሲል አሥራ አምስት፣ ሃያ አምስት እያለ፣ እያለ ግምቱ ሰላሳ ሦስት እስኪ ደርስ ዕድሜውን ፈጀ፡፡ ኢየሩሳሌም ደረሰ አራተኛው ሰብአሰገል፡፡ ከተማው ጭር ብሏል፡፡ አንዱን ተጠጋና "ምነው ከተማዋ ዛሬ የተወረረች መሰለች?" አለው፡፡

«አልሰማህም እንዴ? ያ ኢየሱስ የሚባል ነብይ ሲሰቀል ለማየት ሕዝቡ ወደ ጎልጎታ ኮረብታ ሄደዋልኮ!"

እየሮጠ እተባለው ቦታ ደረሰ፡፡ ኢየሱስን ሰቅለውታል፡፡ እንዳየው አወቀው፡፡ ኢየሱስም ገርበብ ያደረገውን ዓይኑን ገልጦ አየው፡፡ አራተኛው ሰብአሰገልም፣ "ጌታ ሆይ፣ ይኸው እጅ ልነሣህ ከተነሣሁ ሰላሳ ሦስት ዓመት ሆነኝ፡፡ ስለዘገየሁ ይቅርታ፡፡"

"ወደታች እይ" አለው ኢየሱስ፡፡

ቢያይ አዲስ ሐር ለብሷል የወርቅ መጎናጸፊያውንም ደርቧል፣ ሳጥኑም አዲስ ነው፣ እሱም ራሱ ልክ የዛሬ ሰላሳ ሦስት ዓመት እንደነበረው ጎልማሣ ሆኗል!"

እናቴ ተቆጣችኝ፡፡ "የተፃፈለት ይበቃዋል፡፡ የምን ሌላ ታሪክ ተአምር መጨመር ነው?!" ብላ ነሰአችኝ አለ ፈገግ ብሎ እያየኝ፡፡

@Amharicbookstore



እንቀጥል፣ ከኢየሱስ ጋር ነን፡፡ እኛ በቋንቋችን ሰምተናት ኩኩ መለኮቴ የምንላት ርግብ አለች፡፡ የዛሬዎቹ ግሪኮች እንደኛው አገር እርቶዶክስ ክርስቲያን ናቸው፡፡ ርግቧን በቋንቋቸው ስትዘምር ሲሰሟት 'ዴካ እካቱራ!' ነው የምትለው፡፡ አስራ ስምንት ማለት ነው፡፡ ይህቺ ርግብ ሰው ነበረች፡፡ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ በዚያ ወበቅ እየተንገዳገደ፣ እየወደቀ እየተነሣ ሲሄድ፣ ከሚያጅቡት ሮማውያን ወታደሮች አንዱ አዘነለትና መንገዱ ዳር ቆማ ወተት ወደምትሸጥ እስራኤላዊት ሴት ሄዶ "አንድ ኩባያ ወተት ዋጋው ስንት ነው?" አላት፡፡

"አሥራ ስምንት ሳንቲም፡፡"

ኪሱን ቢዳብስ አንድ ሳንቲም ጎደለው፡፡

"ለዚህ ሰውዬ እንዲት ሳንቲም ብትቀንሺለት ይቆጭሻል? ኧረ በ17 ሳንቲም ያዋጣሻል፡፡"

"ዴካ እካቱራ" አለች፡፡

ወቴ በስድ ቋንቋው ረገማትና መንገዳቸውን ሲቀጥሉ፣ ቆመው ከሚመለከቱት መሀል አንድ አዛውንት አየ፡፡ "ና!" አላቸው በምልክት፡፡ መጡ፡፡

"ትንሽ መንገድ መስቀሉን ተሸከሙለት" አላቸው፡፡ ተቀብለው ተሸከሙለት፡፡ ፀደቁ፡፡ ያቺ አንድ ሳንቲም በጎደለ ወተት አልሸጥም ብላ እምቢ ያለችው ሴት ጌታ ሲሰቀል ወደ ርግብ ተለወጠች፡፡ እሷ ናት ማለዳ ላይ ግሪኮች 'ዴካ እካቱራ' ስትል የሚሰሟት፡፡

አንድ ቀን ይህቺ ርግብ "ዴካ እካቱራ" የማለት እልህ ከለቀቃትና "አሥራ ሰባት" ካለች ወደ ሰው ቅርጿ ትመለሳለች፡፡ ወይ የባሰ እልህ ይዟት ወተትዋ ላይ ዋጋ ብትጨምርና "አሥራ ዘጠኝ!" ብትል ግን ምፅአት ይሆናል፡፡ ሁላችንም እናልቃለን፡፡

ለኢየሱስ ክርስቶስ ጥልቅ ፍቅር አለኝ፡፡ የእኔን እምነት ልንገርህ፡፡ ኢየሱስን እስከ መስቀሉ ድረስ አምነዋለሁ፣ እከተለዋለሁ፡፡ ከዚያ ከሞት ተነሣ ሲሉኝ ማመን ያቅተኛል፡፡ ምክንያቱም እስካሁን አላወቅከኝም እንዴ? እኔ እኮ ቶማስ ነኝ፡፡» ጋሼ ስብሐት እንደ ቶማስ ተጠራጣሪ መሆኑን ሲገልፅልኝ እንደሆነ ገብቶኛል፡፡

"አስታውስ፣ ሙሴ ሕግ አመጣ፡፡ ኢየሱስ ነፃ አወጣን፡፡ ፍቅርም ጨመረበት፡፡ እንዳትረሳ፣ ሁልጊዜ ኢየሱስ የሙሴን ሕግ እንደ ተከተለ ነው የኖረው፡፡ በፍጹም የሙሴን ሕግ ጥሶ አያውቅም፡፡

"ሰዎቹ ወደ ኢየሱስ እየተንጫጩ መጡ፡፡ ሴትዮዋ ሸሽታ መጥታ እግሩ ላይ ወድቃ የሙጥኝ አለች፡፡ ዋናው ግባቸው እርሱን ማጥመዳቸው ነው፡፡ «ሙሴ ሴት ስታመነዝር ከተያዘች ትወገር ብሏል፡፡ አንተስ ምን ትላለህ?» አሉት፡፡

"ከእናንተ መሐል ሐጢአት የሌለበት የመጀመሪያዋን ድንጋይ ይወርውር" ብሎ ኢየሱስ መሬቱን በስንጥር ይጭራል፡፡ በአንዲት ጥያቄ ሁሉንም በጥርጣሬ ውስጥ ከተታቸው፡፡ ተለያዩ፤ ጥለዋቸው ሄዱ፡፡" አለኝና ጋሼ ሰብሐት አተኩሮ ያየኝ ጀመረ፡፡ እንባዎቹ ከአይኖቹ ውስጥ ፍልቅ ብለው በጉንጩ ላይ ተንኳለሉ፡፡ ለስላሳ ወረቀት ከኪሱ አወጣና እንባውን እየጠረገ "አይዞህ አትጨነቅ፡፡ ልክ የዛገ ጣራ እንደሚያፈስ አድርገህ እየው፡፡" አለኝ፡፡

ጋሼ ሰብሐት በዝምታ ለረጂም ደቂቃዎች ያህል ቆየና «አንቺ ሴት ከሳሾችሽ የታሉ? » ሲል ጠየቃት «አንድ ስንኳ» አለች፡፡

«በይ ድጋሚ እንዲህ ዓይነት ነውር አይልመድሽ» ብሎ አሠናበታት፡፡ «አላፈረሰም፣ የሙሴን ሕግ ቀጠለበት» እንባውን ጠራረገ፡፡

የጨዋታችን ርእስ በወላጅ እናቱ በእምዬ ማርያም ላይ አነጣጠረ፡፡ "ማሪያም ቧንቧ ነች፡፡ እኛንና ዘለዓለሞን አገናኘችን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ደራሲ ነው፡፡ እኛ የየብስ ደራሲያን ስንጠበብ በቃል ነው የምንፈጥረው፡፡ ኢየሱስ ግን በሰው ልጆች ሥጋና ደም ነው የሚጽፈው፡፡ ሲጥፍ፣ ሲጥፍ... ራሱ'ጋ ደረሰ፡፡ ተዋናይ አስፈለገው፡፡ ባሕርያቱን መረጠ፡፡ በቃ የዚህን ተውኔት ዋና ገፀ ባሕሪ እኔ ነኝ የምጫወተው አለና ወደ መድረኩ ወረደ..."

ኒኮን ካዛንትዛኪዝ ገጣሚ የልበለድ ፀሐፊም እና ሃይማኖተኛም ነው:: ገጣሚ ስልህ ደግሞ ሆሜር ከጻፈው አዲሴ ግሪከኛው የጥንቱን ዘመን የሚያክል ነው ጽሑፎች ታተመ:: አዋቂዎች የቋንቋ ብቃቱን ሲያዩት ከሆሜር እኩል ኒኮን ካዛንዛኪዝ ለዛ ጉልበት ዕውቀት ያለው ገጣሚ ነው:: ብዙ ሰው ነው:: በአንድ ቆዳ ውስጥ::

ሌላው ደግሞ አርቶዶክስ ክርስቲያን ነው:: የእውነት አማኝ ነው:: ምን ያህል ነው አማኝነቱ? በዓመት ሁለት ወር ዋሻ ውስጥ ገብቶ ሱባኤ ያደርጋል:: ልክ እንደ ድሮው ሰዎች:: መንኖ ሲወጣ ቆዳው ልክ እንደ ለምፅ ቁስል ሆኖበት ይህ እንግዲህ በድሮ ጊዜ እምነት ፃድቃን የሚገጥማቸው ነው ይባላል:: ነብሱ ሥጋውን ናቃትና ሥጋው እንዲህ ሆነች ዓይነት ነው፡ ለእኛ አይገባንም:: በኋላ ከዓለም ሰዎች ጋር ሲገናኝ ቆዳው እነበረበት ይመለሳል:: አንድ ጊዜ አንዲት 'ካውንተስ' የሆነች የተከበረች ወይዘሮ አየችው:: "ና" አለችው::

የገና በዓል ነው:: የገና በዓል ደግሞ ዋናው በዓል ነው:: ጌታችን የተወለደበት ነዋ::



«እንዴት ብቻዬን የገናን ራት እበላለሁ:: እያልኩ ስጠብቅ አንተ ከተፍ አልክ ና! አብረን የጌታን ልደት እናክብር» አለችው::

«እሺ!» ብሎ ኒኮል ካዛንዛኪዝ ተጋብዞ ገባ:: የገናን ራት ደስ ብሏቸው እየተጫዋወቱ በሉ:: ከዚያን በኋላ እሱ ወይም እሷ ከዚህ ዓለም በሞት እስኪለዩ ድረስ የገናን ራት አብሯት ነበር የሚበላው::

«ዘ ላስት ቴምፕቴሽን አፍ ክራይስት» ፊልሙን አይተኸዋል? እሱ ነው የጻፈው:: እንግዲህ እውነቱን ነው:: በመጨረሻ እየሱስ ተሰቅሎ ሸይጣን ቢመጣ:: ኖርክ እንደሰው ኖርክ! ሰይጣን ከውጪ የለም ራሱ ከውስጥ ነው:: መጽሐፉም ውስጥ እንደዚያ ነው እንደሚመስለኝ ከሆነ::

ሰው ሆኜ ተፈጥሬ እዚህ ደርሼ እንዴት እንደው አልኖርም:: እንደተሰቀለ መልኩን ብቻ ትቶ ሄደና ሰው ሆነ:: ወለደ፤ አሳደገና አባት ሆነ! ለካ 'ዘላስት ቴምፕቴሽን' ልክ አይደለም አለ:: 'ላስት ቴፕቴሽንን' አሸነፈ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሀሀ» ወፍራም ሳቁን ለቀቀው::

ዞርባ ዘ ግሪክን ማንበብ ይኖርብሃል:: ሰው መሆን ነው:: ተራኪው:: እንግሊዛዊ ነው የግሪክ ክልስ የእናቴን አገር ማወቅ አለብኝ ብሎ ይመጣል:: በጣም ዓይን አፋር ነው:: በቅርብ ነው የመጣው:: ወደብ ወርዶ ቡና ቤት ይገባል:: ዞርባ በራሱ ዓለም ለእኔ ልክ እንደ ቼ ጉቬራ ነው:: ዞርባ ግን ፍቅር ይዞ ይኸ መትረየስ ሆነ የያዘው::

ከመጠጡ ለራሱ እየቀዳ ነው፡፡ "እህ! ይኸውልህ" አለኝና ወደ ሌላ ምዕራፍ ይዞኝ ሄደ፡፤ "የሩቅ ምሥራቅ አባባል ነች፡፡ ሩቅ መሄድ የለብኝም፡፡ እዚህች አንዲት አሸዋ ውስጥ ሙሉ 'ዩኒቨርስ' አለ:: እነ ቡድሀ በአእምሮ በማሰብ ነው የሚሄዱት፡፡ ቡድሀ ማንም አያድንህም ይልሃል፡፡ አማልክቱም የሉም፡፡ የራስህ አምላክ አንተው ራስህ ነህ፡፡ እኔም አንተም ሁላችንም አምላክ ነን፡፡

አምላክ በአምሳሉ እንደፈጠረን አይደለም የተባልነው? ልክ ነህ፡፡ የነሱ አምላክ ግን ውቅያኖስ ነው፡፡ አንድ ቀን መጫወት አሰኘው፡፡ ከውቅያኖሱ አፈሰና በተነው፡፡ ተፈጥሮ ብቅ አለች፡፡ ሲንጠባጠብ አንድ ጠብታ ሰው ሆነ፣ ሌላው ጠብታ ጉንዳን... ቁጫጭም እንደማንኛውም ፍጥረት በዚህ ዓለም ላይ የመኖር እኩል መብት አላት፡፡ ለምን፤ ራሷ ከቡድሀ እኩል የውቅያኖሱ ጠብታ ነችና፡፡ ያዝክ?

"እ!" ተነሣ፡፡ ለሽንት መውጣት ፈልጓል፡፡ ነጠላ ጫማውን አጥመቻቸሁለት፡፡ ትከሻዬን ተመርኩዞ ተጫማ፡፡ ደገፍ አድርጌው ወጣሁ፡፡ የሽንት ቤቱን በር ከፍቼለት ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ውጪ

@Amharicbookstore

ቆሜ እያሰላሰልኩ እጠብቀዋለሁ፡፡ ሙሉ ጨረቃ ምድሪቱን በብርሃንዋ አድምቃዋለች፡፡ አንድ ትልቅ ኮከብ ከማዶ ሆኖ እንደ አንዳች ይንተገተጋል፡፡ በርቀት ሦስት ከዋክብት ይታያሉ፡፡ በፀጥታ እያስተዋልኩ አብሰለስላለሁ፡፡

የመታጠቢያ ቤቱ በር ሲከፈት ተንቋቋ፡፡ በሩ ተመልሶ ተጋጠመ፡፡ የጓሊት አጣምሬው የነበረ እጁ ጭምቅ ተደርጎ ሲያዝ ተሰማኝ፡፡ ጋሺ ነው "እንዲህ ጨረቃዋን ሳያት የነብዩ መሐመድ እውነት ይገባኛል" ሲል ያጫውተኝ ጀመር አጠገቤ ቆሞ ጨረቃዋን አንጋጦ እያያት "ጨረቃ እኮ ውብ ነች፡፡ ፀሐይን አረብ አገር ሆነህ እያት እስኪ? ስቃይ ነች! ታቃጥላለች፡፡ ጨረቃ ግን ልስልስ ውበትዋ ደስታ ነው የሚሰጥህ፡፡ በእንዲህ ያለ ሰዓት ነው ስለ ሃይማኖት ሳስብ ነቢዩ መሐመድ የሚገቡኝ፡፡ ክርስቶስም የሚገለፅልኝ፡፡"

ውጪው መብረድ ጀምሯል፡፡ ወደ ቤት ገባን፡፡ ነጠላ ጫማውን አውልቆ መደብ ላይ እየወጣ "ሰውየው ነብዩ መሐመድ'ጋ መጣና ይገላግሉኝ፡፡ የሃያ አራት ዓመት ልጄ እየደበደበ አስቸገረኝ" አለ፡፡

"ልጅህ ቅዱስ ቁርዓን ቀርቷል?" ሲሉ ጠየቁ፡፡

"አልቀራም" አለ ሰውዬው፡፡

"እንግዲያው ያሣደግኩት ግመል ረገጠኝ አትልም?" አሉት፡፡

በዓረብ አገር በረመዳን ወር ማታ ማታ የእንጨት ክምር እያነደዱ የግጥም ውድድር ይደረጋል፡፡ ፈረንጆች 'ካምፕፋየር' እንደሚሉት መሆኑ ነው፡፡ አንደኛው ውድድር ላይ ነብዩ መሐመድ ተገኝተዋል፡፡ የተለያዩ ድንቅ የሆኑ ረጃጂም ግጥሞች ይነበባሉ፡፡ አንድ ዓይነ ስውር ተነሣና ሁለት መስመር ብቻ አነበበ፡፡ ነብዩ በጣም ረክተው ካባቸውን ከትከሻቸው ላይ አንስተው ለዓይነ ስውሩ ደረቡለት፡፡ ያ ክቡር ካባ ወደ ልጅ ሲወረስ እስከ ዛሬ አለ፡፡ ግጥሟን በአማርኛ ልንገርህ::

እሷ ስትመጣ ይበራል
እሷ ስትሔድ ይጨልማል::

Jorge Luis Borges የሚባል የአርጀንቲና ደራሲ አለ፡፡ አጫውቼሃለሁ፡፡ በላቲን አሜሪካ ፈጠራ የአላህን ተአምር ላሳይህ ነው፡፡

የአጭር ልቦለዱ ዋናው ገጸ ባህሪ ሼኪ ናቸው፡፡ በሚመጡት ዓመታትና ዓሠርታት አላህን እንዴት እንደሚያገለግሉት እያሰላሰሉ ሲሔዱ ጦር ሜዳ ደረሱ፡፡ ከአንዱ ወገን ወደ ሼኪው ጦር ተወረወረ፡፡ ደረታቸውን ሊወጋቸው ሲል በልባቸው "አላህ አድነኝ፤

@Amharicbookstore



ገና አገልግሎቴን አልጨረስኩም" አሉ፡፡ ጦርዋ ባለችበት በአየር ላይ ቆመች፡፡ ሼኪው ወደ ጉዳያቸው ሄዱ፡፡ አላህን ሲያገለግሉ ረዥም ዘመን ኖረው ያቀዱትን ሁሉ ፈፀሙ፡፡ በልባቸው "ከእንግዲህ ውሰደኝ" ይላሉ፡፡ በቅፅበት ወደ ውጊያው ሜዳ ይመለሳሉ፡፡ ያች በአየር ላይ የነበረች ጦር እየሄደች ነው'ኮ፡፡ ቀድሞውንም አልቆመችም፡፡ ሼኪው ደረት ላይ ተሰካች፡፡ ተሠናበቱ፡፡

"Agnosticism" ጋ ደረስን፡፡ እግዜር ለመኖሩም በቂ መረጃ የለ፣ ላለመኖሩም በቂ መረጃ የለ፡፡ ስለዚህ ሊኖርም ይችላል፣ ላይኖርም ይችላል፡፡ በዚህ በኩል ደግሞ አይሁድ እስከ ፃፉት ድረስ ብሉይ ኪዳን እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ እስራኤል የተጓዙትን መንገድ አርኪዎሎጂስቶች አግኝተውታል፡፡ ስለዚህ እኔ የሙሴን ታሪክ አምናለሁ፡፡

አይሁድን ደግሞ በጣም የማደንቃቸው መጽሐፋቸውን ሲፅፉ ስለማይዋሹ ነው፡፡ ንጉስ ዳዊት አይደለም ከሁሉ ቅዱስ? ዳዊት ነው የገዛ ጄኔራሉን ሚስት ወሽሞ፣ ጄኔራሉን አስጠርቶ ለማጭበርበር፣ "ከሚስትህ ጋር ዕደር" ሲለው፤

"እኔ አላድርም:: የጦር ጓደኞቼን እዚያ ትቼ" ሲል፣ እንዲህ ያለ ወታደር ያውም ይሁዲ ያልሆነ፣ ያሳየውን ፅኑ ታማኝነት ታደንቅና፣ እዚያው በዚያው ዳዊትን ትንቀዋለህ፡፡ ደብዳቤ ፅፎ ለዋናው ጄኔራል "ተሰለፉና ስትጋጠሙ፣ ኦሪዮ ሲጋጠም አፈግፍጉ እየተዋጋ እንዲሞት" አለ፡፡ አፈገፈጉ፤ ሞተ፡፡ ይህን ይህንን የዳዊትን ጉድ አይደብቁም፡፡ ስለዚህ ሌላውን ሲነግሩህ ልታምናቸው ትችላለህ፡፡ በብዛት፡፡ ከኢየሱስ ወዲህ ያለው ግን ሌላ ጉዳይ ነው፡፡

እኔ ሙሴ ያደረገውን አምናለሁ እንጂ ከእግዜር ጋር የሚያወራው ወሬ ጥበብ ነው የሚመስለኝ፡፡ አንድ እምነት አለኝ፡፡ ልክ አንተ ተኝተህ "ኳ! ኮሽ!" ሲል የምታነቃህ ነገር አለች ዘበኛ ነገር፡፡ አንድ ሕዝብ ደግሞ ጥቃት ሲበዛበት የሚያበቅላት ጉልበት አለች፡፡ እሷ ሙሴ ነች፡፡ ወይም ማኦ ዜዶንግ፣ ወይም ፊደል ካስትሮ ወዘተ ነች፡፡ 'ማጂክ ትሪክ' ታውቃለህ?... እነዚያም ማጂክ ትሪክ ያውቃሉ፡፡ የፈርኦን ጠንቋዮችና ሙሴ ይዋጣላቸዋል፡፡ ልክ እንዳሁኑ ጦርነት ሚሳይል ፀረ ሚሳይል፡፡

ኢያሱ በውጊያው ድል ሊያደርግ ሲል ፀሐይ ልትጠልቅ ሆነ፡፡ "ቁሚ!" አላት፣ ቆመች፡፡ ይሄን ማመን ያስቸግረኝ ነበር፡፡ ደግነቱ፣ በዚያን ዘመን የነበሩ ቻይናውያን ኢያሱ ያቆማትን ፀሐይ

በአስትሮሎጂ ጥናታቸው ላይ መዝግበው መያዛቸውን የታሪክ ማስረጃ ያወጋናል፡፡

በዚሁ ርዕስ ስንጨዋወት አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ኤፍሬም ሐጎስ አብሮ አደጌ ነው፡፡ የሁለት ዓመት ታላቁ ነኝ፡፡ ልጆችም ሆነን በጣም እንዋደዳለን፡፡ እኔን ያሳደገኝ የእርሱ አባት እንደሆነ አጫውቼሃለሁ፡፡ ጋሼ ሐጎስ ሲኮረኩመን እኩል ነበር፡፡ ልጅ ሆነን የመዋደዳችንን ያህል አንዳንዴ መጋጨትም አለ፡፡ ኤፍሬም በተፈጥሮው 'ፋናቲክ' የምትለው ነው ባሕሪው፡፡ ለምሳሌ በዚህ ፊት ለፊት ባለው መንገድ ከሄደ ሁሌም በዚያው ነው የሚቀጥለው፡፡ ከፊት ለፊቱ የሆነ ነገር ገጭቶ ከመለሰው የት ነበርኩ አይልም፣ ይጠመዘዝና ይቀጥላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ባሕሪ በተለይ በእኛ ቤተሰብ ውስጥ በብዛት ይታያል፡፡

እንግዲህ እኔና ኤፍሬም አብረን ነው የታደስነው፡፡ አብረንም መጽሐፍ ቅዱስ ተምረናል፡፡ እሁድ እሁድ ነበር ያጠናነው፡፡ ከዚያ ተጠመቅን፡፡ መጀመሪያ ስንጠመቅ ሕፃን ነበርን፣ አናውቅም፡፡ አሁን ዳግማዊ ጥምቀት አውቀን ተጠመቅን፡፡ በእዚያን ጊዜ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ይዘን ፎቶ የተነሣነው፡፡

ኤፍሬም ቀጠለ፡፡ አንድ ቀን ሳይንቲስት ሆነ፡፡ ተነሳበት "እግዜር የለም፣ ዝም ብለው ነው፣ ወሬ ነው!" አለ፡፡

"እንዴ! ተው እንጂ ኤፍሬም፣ እርግጠኛ'ኮ መሆን አትችልም" አልኩት" አለ እየሣቀ፣ እሱ ግን በእርግጠኝነቱ ቀጠለበት፡፡

መብላት መጠጣት መዝናናት እና ቤት ማረፍ ሆነ የኤፍሬም ፕሮግራም፡፡ ሚ.ጢ.ጢ. መኪና አለችው፡፡ ጠጥቶ ሲነዳ የቆመ ትልቅ የጭነት መኪና ሥር ጥልቅ አለ፡፡ ክፉኛ ተጋጨ፡፡ ራሱን ሳተ፡፡ ቆይቶ ቆይቶ ሲነቃ ለካ በጭነት መኪናው ሥር ተሰንቅሯል፡፡

"መሞት ነበረብኝ" አለ፡፡ ያልሞትኩት እግዚአብሔር ስላለ ነው አለ፡፡ ለወጠ መንገዱን፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰባኪ ሆነ፡፡ እስካሁንም ኢየሱስ ያድናል እያለ እየሰበከ ነው፡፡

ሌላውን ትዝታዬን ልጨምርልህ፡፡ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከ20 እስከ 24 ዓመት ወጣት ሆኜ ማቴዎስ ጥግነህ የሚባል አምስት ዓመታት በዕድሜ የሚበልጠኝ ጓደኛ ነበረኝ፡፡ ከዶስቶዬቭስኪና ከሌሎች የሩሲያ ደራሲያን ጋር ያስተዋወቀኝ እሱ ነበር፡፡

ሩሲያና ኢትዮጵያ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንቀራረባለን፡፡ የዶስቶዬቭስኪ አገርና ሕዝብ ከእኔና ከማቴዎስ አገርና ሕዝብ ተመሳስሎ ይታየናል፡፡ ጎረምሣ ገፀ ባሕሪያቱ በአብዛኛው የእኛ ዓይነት ናቸው፡፡

@Amharicbookstore



እግዚአብሔር የለም፡፡ ሃይማኖት የሞት ፍርሃት መሸሻ ነው፡፡ እኛ ግን ሞትን እንፈራለን፡፡ ብንፈራም አይቀርልንም፡፡ ከፍርሃታችን ጋር እንፋጠጣለን እንጂ፣ ሰው በሃሳብ ወደ ፈጠረው እግዚአብሔር ሸሽተን የሙጥኝ አንልም፡፡ በተለይ ተፅዕኖ ያሳደሩብን የዶስቶዬቭስኪ ገፀ ባሕርያት ናቸው፡፡

አያሌ ዓመታት አለፉ፡፡ አንድ ቀን ሥላሴ ቤተክርስቲያን ሔድኩ፡፡ አንድ መነኩሴና ሁለት ምዕመናን ቆመዋል፡፡ ያወጋሉ፡፡ ከእነርሱ አንደኛው ጓደኛዬ ማቴዎስ ጥግነህ ነው፡፡ ሌላ ሽማግሌ ሰው መጥተው ትከሻ ለትከሻ ከተሣሣሙ በኋላ ሽማግሌው ማቴዎስን "ምነው ሰሞኑን አላየሁዎትም?" አሉት፡፡

"ግሸን ማሪያምን ልሳለም ሄጄ ነው" አለ ማቴዎስ፡፡ ሲጫወቱ ቆይተው እኔን አየኝ፡፡ መጣ፡፡ ትከሻ ለትከሻ ተሳሳምን፡፡

'ወይ ጊዜ! እውነትም ሰው እንዳስቀመጡት አይገኝም' አልኩ በልቤ፡፡ ጥላ ሥር ቁጭ ብለን ብዙ አወጋን፡፡ "ዶስቶዬቭስኪ ወጣቶች ሆነን አንብበን እግዚአብሔር የለም ስንል ኖረን አንተ የት አገኘኸው?" አልኩት፡፡

"ወደእሱ የሚወስድ መንገድ ብዙ ነው፡፡ እኔ የሄድኩበት Law of probabilityን ተከትዬ ነው፡፡ አንድ ትውልድ ብንቆጥረው ወንዱና ሴቱ እኩል ሆኖ እናገኘዋለን፣ ይላል 'የፕሮባቢሊቲ' ፅንሰ ሐሳብ፡፡ ሕዋውን ስናስብ ያ ሁሉ ሚሊዮን ጋላክሲ፣ ያ ሁሉ ቢልዮናት ከዋክብ በማይፋለስ ሕግ ይሽከረከራል፡፡

"ምድር የወረድን እንደሆነ ያ ሁሉ ሚሊዮናት የተለያየ የዕፅዋትና የእንስሳት ዘር አንዱ የሌላው ምግብ እየሆነ በማይበጠስ ቋሚ የብሉ ተባሉ ሰንሰለት እየሄደ ይገኛል፡፡

"ገላችን ውስጥ ገብተን እንደ ሐኪም ብልቶቻችንንና ግንኙነታቸውን የቆጠርን የዘረዘርን እንደሆነ ተአምር ሆኖ እናገኛለን፡፡ እህል በልተን ሰውነታችንን መገንባት ሌላ ተዓምር ነው፡፡ የሚያስተሳስረንና በኅብረት የሚያኖረን ቋንቋና ባሕልስ ከየት እንዴት መጣ? ውበቱስ?! ደግሞ ፕላኔቶቹ በፀሐይ ዙሪያ ሲሽከረከሩና የንጥረ ነገር ኤሌክትሮኖች በኒዩክልየስ ዙሪያ ሲሽከረከሩ አንድ ዓይነት ነው፡፡ ግዝፈትና ፍጥረት ይለያቸዋል እንጂ፡፡ ይኼ ሁሉ ተአምራት እንዴት ከባዶ አጋጣሚ ራሱን ሊገጣጥም ይችላል? አለኝ" የዓይኖቹ ብርሃን ውስጡን ዘልቀው የሚያስተውለኝ መሰለኝ፡፡

የአይመረመሬውን ትንግርቶች ብቻዬን ከእኔው ጋር ሳመነዥግ ጋሼም እንዲሁ በመንፈስ መጥቷል፡፡ አልቤር ካሙ ትዝ አለኝና ማወቅ እንፈልጋለን፣ እንመረምራለን፣ ባገኘን ባወቅን ቁጥር ርቀቱም ጥልቀቱም እየጨመረ ይሄዳል፡፡ እናም 'አብሰርድ' ያደርሰናል፡፡

"ከማቴዎስ ጋር ከብዙዎቹ ተአምራት ጥቂቶቹን እየተቀባበልን እየተገረምን ዘረዘርናቸው፡፡ የሁልጊዜው የሞትና የሕይወት ቅብብሎሽ የአክሮባትን ጥበብ ያስታውሰናል፡፡ በተቃራኒ ዖታዎች ተቆራኝተን የመዋደድ ተአምራትም አለ፡፡ ሰውነታችን በሽታን ሲከላከል ከጀርሞች ጋር የሚካሄደው ጦርነት፡፡ ይህ ሁሉ ተአምራት የአይመረመሬ አንዱ መልክ ነው፡፡ የዘመናዊው ማቴዎስ ወንጌል እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡

በጊዜ እየኖርን የፈተልነውን ሸማ በዘለዓለም ስንኖር እንለብሰዋለን፡፡ በሰማችን አሽብርቀን በዘለዓለም እንገናኛለን...

ረጂም ፀጥታ በመካከላችን ነገሰ፡፡ በፀጥታው ውስጥ የየእራሳችንን 'ዩኒቨርስ' እንመረምራለን፡፡ የታደልን እናየዋለን፡፡ ግን አናስተውለውም፡፡ የኑሮ ግጾታችን መኖርና ማለፍ ይሆናል፡፡ ሕይወት ነበርን በአፀደ ሥጋ፣ ከዕለታት አንዱን ቀን ደግሞ ሟች እንሆናለን እንደጥላ፡፡ እናልፋለን፡፡... እሱ እያዳመጥኩ መሆኔን ልብ ብሎ መዘፍያወጋኝ ጀመር፡፡

" መጽሐፍ ቅዱስን በፈጠራ አያሌ ደራሲያን ተጠበውበታል? በጣም ብዙ፡፡ በጣም! እየጫወትኩህ!! ልጨምርልህ፡፡ ከሳቅ ንጉስ ህምታችን ጋር ላስተዋውቅህ?

የእኔ ደራሲያን ጀግኖች ብዙ ናቸው፡፡ አንደኛው ማርክ ትወይን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን እንደገና ነው እንድታነብ የሚያደርግህ፡፡ ሔዋን ጨዋታውን ላውጋህ፡፡ ሔዋን የተከለከለችውን እፀበለስ በላች፡፡ "አዳም፣ ፈራሁ!" ትላለች፡፡

"ምነው?" ጠየቃት፡፡

"የተከለከለችውን ፍሬ በላኋት፡፡"

"ከወዴት ነው የቀጠፍሻት?" ጠየቀ አዳም፡፡

አሳየችው፡፡

«አንቺ በሌለሽበት ምን ይውጠኛል? እኔም በልቼ ልከተልሽ፡፡ አንቺ ሞተሽ እኔ ብኖር አላሳዝንሽም?» ሳይላት አይቀርም፡፡ የጋሼ ዓይኖች እንባ አቀረሩ፡፡ ለስላሳ ወረቀት ከኪሱ አወጣና ዓይኑንም አፍንጫውንም አባበሰ፡፡

"በዚህ ዓይነት እግዚአብሔርን ቀደሙ፡፡ ሞቱ!" ፈገግ ብሎ ሳቅም ለቅሶም በተቀላቀለበት ዓይነውሃ እያስተዋለኝ "ዘነበ፣ ላንተ ክር እየሣሣሁ ነው እንጂ እኛ የምንናገራት ቃል አንዷም መሬት ጠብ አትልም፡፡



የማርክ ትወይን ታላቅ ወንድም 'ዋይልድ ዌስት' ወደ ሚባለው የነጮቹ ሥልጣኔ ዳርቻ ሄደ፡፡ እዚያም የሚተኩሳት ጥይት መሬት ጠብ አትልም የሚባልለት ሰው ተዋወቀ፡፡

ሰውየውን፣ "አንተ የተኮስከው ጥይት መሬት ጠብ አይልም ይባላል፡፡ እስኪ እኛም አይተን አድናቆታችንን ለጋዜጣችን እንላክ ተኩስ" ይለዋል፡፡

"እሺ፡፡ ይህችን ዛፍ ታያታለህ? ግንዱ ቅርንጫፍ የሚሆንባትን መሀሏን ልምታልህ" አለና ተኮሰ፡፡ የትወይንን አለካክ አሁን እረሣዋለሁ፡፡ በእኔ ግምት ግማሽ የእግር ኳስ ሜዳ ያህል ርቃ የምትግጥ አንዲት ላም በጥይት ተመትታ ወድቃለች፡፡ እውነትም የሚተኩሳት ጥይት መሬት ጠብ አትልም፡፡"

ሎጫ ፀጉሩን በሁለት እጁ የኋሊት እያሸ አስተኛ፡፡ አንዳንዴ ሲያሰኘው ትንሽዬ ማበጠሪያ ከኪሱ ያወጣና ያበጥራል፡፡ አሁን ፊት ለፊቴ መደብ ላይ ተቀምጦ አፍጥጦ እየኝና "ብዙ አንብቤያለሁ፡፡ በንባብ ዩኒቨርሲቲዎች የክብር ዶክትሬት ዲግሪ የሚሰጡ ቢሆን ምንም አትጠራጠር ይህ ሽልማት ለእኔ ይገባኛል፡፡ አይገባኝም?!" ጠየቀኝ፡፡ ለሽልማቱ እንደሚመጥን መሰከርኩለት፡፡ ይኼንን ሲል ሚዛን ለማውጣት፣ ልክ ለማወቅ እንጂ ዶክትሬት ዲግሪውን ከማምለክ አይደለም፡፡ በሕይወቱ መጨረሻው ዓመት ላይ ጋሼ ስብሐት "ቢኤ ዲግሪህ የት ነው ያለው?" ስል ጠይቄው ነበር፡፡ ይህንን ስለው መጻሕፍት መደርደሪያው ላይ ጆርባውን ሰጥቶኝ ያሸውን መጽሐፍ እየፈለገ ዞር ብሎ እየኝና "ምን ያደርግልኛል?" አለኝ፡፡

ደነገጥኩ፡፡ ጥቂት አብሰለሰልኩና "እውነትም ለጋሼ ስብሐት ዲግሪ ምን ያደርግለታል?" ስል ወሰንኩ፡፡ መደንገጤን ሰላየ "ከፈለግክ ታናሽ ወንድሜ ዮሴፍ ጋ ሂድ ታገኘዋለህ" አለኝ፡፡ የንባብ ፍቅሩን በአንድ ዐረፍተ ነገር ሲቋጫት "ይህንን ሁሉ በማንበቤ? Enjoy አደረግኩ፡፡ ተደሰትኩ! በጣም ተደሰትኩ!"

***

*ከመጽሐፍ ጋር ከልቡ መሣቅ የሚችል የማውቀው ጋሼ ስብሐትን ነው፡፡ ይህ አኳኋኑ የርቀት ተመልካችን ግር ያሰኛል፡፡ በቅርቡ በአዲስ አበባ መስተዳድር ከበብ ምሣ ተጋብዞ ይመገባል፡፡ አንድ ባለሙያ ከርቀት አየውና "እህል ንጉስ አይደለም እንዴ?" ብሎ ተቆጣ፡፡ "እንዴት እህል ፊታቸው አስቀምጠው ከመጽሐፍ ጋር እየተሳሳቁ ይመገባሉ? ነውረኛ ሽማግሌ ናቸው" ብሎ ሲበሽቅ፣ ጋሼን የጋበዘው ጓደኛዬ ተቆጭውን "ጋሼ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ነው" ሲለው ከንዴቱ ጋብ ብሎ "እ! እሣቸውስ ከሆኑ ይገባቸዋል!" ብሎ የማሪያም መንገድ እንደተሰጠው አጫውቶኛል፡፡*

@Amharicbookstore

ጋሼ ስብሐት ፀጥ ያለ ቤታ ረጂም ጊዜ መቀመጥና ማንበብ ይወዳል፡፡ ጓሪቤቱ ከሆነ በኋላ የተነካዘባቸው ይህንኑ ባህሪውን ነው፡፡ ሁለት ሦስት መጻሕፍቶችን ይጀምራል፡፡ ያስደሰተውን በዕለቱ ሲያነብ ይውላል፡፡ ሲበቃው መፃፍ ይጀምራል፡፡ ማስታወሻ የሚፈልገውን ሃሳብ ሲያገኝ እዚያው መጽሐፍ ላይ ምልክት ያደርጋል፡፡

ጠዋት ቁርስ በልተን እንሰነባበታለን፡፡ ማምሻዬን እቤት ገብቼ ልጎበኘው ስሄድ ጭኑ ላይ ትራስ ደራርቦ ይፅፋል፤ ወይም ዘና ብሎ ያነባል፡፡ እንዳሞኘ ማንበቡንም ሆነ፤ መጻፉን ይተውና የዕለት ውሎዎቻችንን እናወጋለን፡፡ ያጋጠመው አስደናቂ ጉዳይ ካለ ወጉን ለእርሱ እተውለታለሁ፡፡ አንድ ጓደኛችን The Sign and the Seal ሊያመሰግነው ቃል ገብለት፡፡ "በማርያም! የግራሃም ሀንኮክን መጽሐፍ፣ እኔ ብሞት እንኳ አትንኩ ይመርቅሃል ቶሎ አምጣልኝ" አለው፡፡

ጓደኞችን ግን ቃለበላ ሆኑ፡፡ ወራት ተቆጠሩ፡፡ ጋሼም ሆነ ጠማቱ በምዬ ማርያም ስም መማፀናቸውን ዘነጉት፡፡ ሰሞኑን ፕሬስ ላይብረሪ መጽሐፍ ለመዋስ መደርደሪያዎቹን ሲቃኝ ይህንን መጽሐፍ አገኘሁት፡፡ይዞ ሊጋሼ ታላቅ ስጦታ እንደሚሆን ገምቼ ተዋስኩለት፡፡

እንደተለመደው ጀንበር ሲታዘቀዝቅ ልጎበኘው መጽሐፉን ይዤለት ሄድኩ፡፡ እየጻፈ ነበር፡፡ ስሰጠው ደስ ብሎት ተቀበለኝ፡፡ ገለጥ ገለጥ አደርጎ ቃኘውና "አቤ! አሁን ነበር ሁሌታም መሆን፡፡ ገንዘብ እንደልብ ቢሆን እፎይታ ዝግጅት ክፍል ደውዬ ለአሥራ አምስት ቀን ሥራ አልገባም እላቸው ነበር" አለኝ፡፡ ስለበላ ለመጽሐፉ ያለውን አምሮት ፍቅር አሣየኝ፡፡ በዚህ ጊዜ ለእፎይታ ጋዜጣና መጽሔት የሚሆኑ ወጎችን ይጽፋል፤ ሰባተኛው መልአክ የተባለ ድርሰቱን ለህትመት እንዲበቃ እያነበበ ያርማል፡፡ ይህንን በእርሱ ሕይወት ታሪክ ላይ የምጽፈውን መጽሐፍ አርትኦት እየገዘኝ ነው፡፡ ነባሱ በሥራ ብዛት ብትወጠርም የግራሀም ሀንኮክን ሥራ ማንበብ ጀመረ፡፡ ምክንያቱን ዘርዝሮ ባይናገረኝም አልኮል መጎንጨቱንም በዚያን ሰሞን ለጊዜው ትቶታል፡፡ ይህንን The Sign and the Seal መጽሐፍ 63ተኛ የልደት በዓሉን ስናከብር ከወዳጆቻችን አንዱ በስጦታ አበርክቶለታል፡፡

@Amharicbookstore

## ፴፯

## ለአንባቢያን ክብር…

እቤት እንደገባ አንድ ብርጭቆ ውሃ ጅው አድርጎ ጠጣና "እፎይታንና ውሃን ለድሃ ማን ሰጠብኝ? አሉ እቴጌ ጣይቱ!" አለን ጋሼ ስብሐት፡፡ የትና መቼ ይህን እንዳሉ ነገረንና ጨዋታችን እንደ ጨዋታነቱ ዘለለ፡፡



"ውይ! አቦይ ስብሐት በቀደም ትንሽ አሞዎት ተንበርክከው መፃፍዎ አቤት እንዳበሸቀኝ!" አለች ፀሐይ፡፡

እኔ ጋ ቆየት ያሉ ቁም ነገር መጽሔቶች አሉ፡፡ እዚያ ላይ እሱ የጻፋቸው ፅሑፎች ምናልባት አዲሱ ትውልድ ላያነባቸው ስለሚችል እነዚህን መጽሔቶች ለእፎይታ ዝግጅት ክፍል ልሰጥ እችል ነበር ብዬ አሰብኩና ይኼን ሃሳብ ሰነዘርኩ፡፡

"ሃሳብህ ጥሩ ነው፡፡ ግን ባለፈው ሳምንት በጻፍኩት ጽሑፍ ላይ ይቀጥላል ብዬ ነው ያቆምኩት፡፡ ስለዚህ አንባቢው ቀጣዩን ታሪክ ነው ማንበብ የሚፈልገው፡፡ አሁን ይኼን መጽሔት ብንልክ አንባቢዬን ያደነቃቅፈዋል፡፡ ደግሞ እኮ አንባቢው መታመሜን አያውቅም፡፡ ይሁን እንጂ እኔ እንደ ምንም ተቸግሬ ታሪኩን ልቀጥልለት ይገባል፡፡"

"ቢሆንም!" አለችና ፀሐይ ፊቷን ቅጭም አድርጋ፡፡ በዕለቱ ጋደም ብሎም ሆነ አረፍ ብሎ መጻፍ አልቻለም፡፡ ስለዚህ መሬት ላይ ትራስ ደልድሎ እላዩ ላይ በመንበርከክ የቡና ጠረጴዛ ላይ አስደግፎ የዕለቱን ሥራ ማከናወኑን በሃሳብዋ እያስተዋለች፡፡ አሁንም በቁጭት "ቢሆንስ አቦይ እንዴት ተንበርክከው ይጽፋሉ?" አለች አሁንም ከልብ እያዘነች፡፡

ጋሼ ፀሐይን ሰምቷታል፡፡ ሐዘንዋን እየተጋራ የመሥሪያ ቤቱን (እፎይታ) ሁኔታ ለማሳየት እንዲህ አጫወተን "ተስፋዬ ገብረአብ 'ኮምፕሌክስ' የሌለበት ሰው ነው፡፡ ነፃ ሰው ስለሆነ እኔን የሚመለከት ጉዳይ አጋጥሞት ልክ ለሌላ ሰው እንደሚያወጋ አጫወተኝ፡፡ የት አገር እንደሄደ ረሣሁት፡፡ በአንዱ መጽሐፍ መደብር ጎራ ብሎ ይመለከከታል፡፡ አንደኛው የመደብሩ ደንበኛ እፎይታ ጋዜጣ እንዳለ ጠየቀውና 'በረከት ብዕር' ከሌለበት ተወው!' ማለቱን ሰምቶ አጫውቶኛል፡፡"

እነዚህ አንባቢዎቹን ጋሼ ተንበርክኮ እስከ መጣፍ ያከብራቸዋል፡፡ እንዳለውም ከጥቂት ቀናት በኋላ ተሻለው፡፡ ማታ ማታ ዘና ለማለት ከካቲካላው መጎንጨቱን አሁን ደግሞ ጀምሯል፡፡

ልጁ ዜና መጥታ አብራው መኖር ስለጀመረች ሕመሙ አልከበደም፡፡ እኔና ፀሐይ ከሥራችን ስንመለስ እንጎበኘዋለን፡፡ ሕመሙን አቅልሎ በማየቱ ለወንድሞቹ መንገሩ አስፈላጊ አለመሆኑን ስለነገረን ለማንኛቸውም ትንፍሽ አላልኩም፡፡

"አብዛኛው አንባቢ የምታከብረው ቢሆንም የሚያሳዝንህም ያጋጥምሃል፡፡ በቀደም ዕለት በአለባበሱ የዘኈጠ፤ ሳምሶናይት ቦርሳ የያዘ አንድ ሰውዬ ቢሮዎችን መጣ፡፡ እግረ መንገድን አንድ ቅፅ ማሳተም እንፈልጋለን" አለኝ፡፡

"ጥሩ" አልኩት፡፡

"ከሕትመቱ ከሚገኘው ገቢ 60 ከመቶ በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቻችን እንሰጣለን፡፡ 30 ከመቶ ለአርሶ እንከፍላለን፡፡ ለኩባንያችን 10 ከመቶ ይበቃናል፡፡ 'ስፖንሰር' ሰላለን በገቢ አንጎዳም" በማለት እቅዳቸውን ነገረኝ፡፡

"ጥሩ ሃሳብ ነው "ብዬ ተስማማሁ፡፡

"ውል እንፈራረማ" አለኝ፡፡

"ደስ ይለኛል" አልኩት፡፡

"ከተወሰኑ ቀናት በኋላ እኔን ሰላላገኘኝ እፎይታ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ውሉን ትቶልኝ ሄደ፡፡ ወደ አምስት ገጽ ነው አነበብኩት በርካታ ነገሮች ያትታል፡፡ በአጠቃላይ ዓላማው እስካሁን ድረስ ለዓመታት በአማርኛም ሆነ በእንግሊዘኛ የጻፍኳቸውን ጽሑፎች፣ የፈጠራ ሥራዎች በሙሉ የዚህ ኩባንያ ንብረት እንደሆኑ ይገልጻል። እኔም በፊርማው ቦታ ላይ በትልቁ ኤክስ አደረግኩበት።"

@Amharicbookstore

## ፴፰

## 'ዴሴታንቴ'

ተፈጥሮ ከሰጠችህ ባሕሪያት ሲርብህ መብላትና መጠጣት የግድ ነው፡፡ እኔ ከተሰጠኝ ባሕሪያት በጣም የምወደው ፍርሃቴን ነው፡፡ የእኛ ዋና ሀብታችን ፍርሃታችን ነው ከስንትና ስንት ቀላልና ከባድ አደጋ የሚጠብቀን፡፡

በጣም ልዩነት አላቸው፡፡ ወጣት ሆነህ እርጅናን ስታየው አስቀያሚና አስደንጋጭ ነው፡፡ ውስጡ ስትገባበት ግን የራሱ የሆኑ እንደ ወጣትነት ደስ የሚሉ ነገሮች አሉት፡፡ ጤና፣ ምግብ፣ መጠለያ እስካላጣህ ድረስ በጣም አሪፍ ነው፡፡ አንዳንዴ ኡፍ! ያንን ሁሉ ትኩሳት አለፍነው! ዛሬ በረድ ብለን በሰላም መደሰት ነው፡፡ መጃጀት ጋ ስደርስ ደግሞ አስታውስህ ጠይቀኝ...



ከጥቂት ዓመታት በፊት አሣምሬ ነበርኩበት፡፡ እንደነበርኩበት የመጨረሻዋ ልጄ ምስክር ነች፡፡ አሁን ቀልድ "ሲወራ ካጋጠመኝ ደስ እያለኝ እሳተፋለሁ፡፡ ድርጊቱ ላይ ግን የለሁበትም፡፡

ሁላችንም ነብስ ውስጥ ይህ ያልከው ኬሚስትሪ አለ፡፡ ብሽቅ ሰው ሲመጣ ብሽቅ ትሆናለህ፡፡ ልክ ፈንጂ እንደታጠቀ ወታደር ማለት ነው፡፡ ጨዋና ሰላማዊ የነበርከው ሰው በአልሞትባይ ተጋዳይነት ብሽቅነትህን ትጠቀማለህ፡፡ በጣም ቆንጆ ሃሳብ ትውስ አለችኝ፡፡ ልንወለድ ስንል ገና ነብስ ሆነን እያለን መላዕክቱ ስንቆቻችንን ይሰጡናል፡፡ ይኸው ፍርሃትህ፣ ይኸው ድፍረትህ፣ ይኸው ፍቅርህ፣ ይኸው ቅናትህ... እንቀበላለን፡፡ እዚህ ከመጣን በኋላ (ወደ ምድሪቱ እያሣየኝ) ፍቅርህን ወላጆችህ ይቀሰቅሱታል፡፡ ስታድግ ቅናትህን የምትቀሰቅስ ትመጣለች፡፡ መናናቅህንም ጭምር፡፡ እንዳመጣጡ ነው የምንቀበለው... መከባበርንስ?

ያንተ ክብርህ ፍቅረኛህ ነች፡፡ ከአንተ ጋር ሆና አንዱ መጥቶ አንድ ነገር ቢል ዝም አትልም፡፡ ክብርህ ተነክቷል፡፡ በአገር ቤት ልጃገረድ ክብሯ ድንግሏ ነው፡፡ ሕግ ከሌለ ክብሯ የለም፡፡ ሚዜዎቹ አክብረው በፈረስ ተንከባክበው ያመጧትን ሙሽሪት ድንግሏ ካልተገኘ አዋርደው በአህያ ጭነው ወደ ወላጆቿ ቤት ይወስዷታል፡፡ ወንድን ልጅ "እናትክን!" ብትለው ነገር ተበላሸ፡፡ "እምዬን?" ይላል!፡፡ ክብሩ ተነካ፡፡ እናትን ያክል ክብር አዋረደ፡፡ ክብር በ'ስፖንዳ' ነጥሮ ይመጣል፡፡ በአጠቃላይ አንተ እንደበተ ቁጥብ ሆነህ ሌሎችን አክብር፣ አንተን ያከብሩሃል፡፡ ሰዎችን የምወዳቸው ከእኔ እኩል ሳከብራቸው ነው፡፡ ሳፈቅራቸው ነው፡፡

ሂትለር ሰው ነበር እንበል፡፡ ሁለት ዓይን ሁለት እግር ወዘተ፡፡ ኢየሱስ ግን በርግጥ ሰው ነበር፡፡ አይቻልም እንጂ ቢቻል እሱን መከተል ትልቁ ምርጫዬ ነው፡፡ ሰው ላልከው ግን ሰው የማይታወቅ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር እኩል ተዓምራዊ ፍጡር ነው፡፡ ሟች ከመሆኑ በስተቀር ችሎታውን እየው፡፡ መዓት ነው፡፡ ለወጥ ይልና ደግሞ የሰው ልጅን ወንጀለኛ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡ ጠቅለህ ስታየው፣ ብትፈልግ በወንጀል፣ ብትፈልግ በቅድስና ሰው የማይችለው ነገር የለም፡፡ እቺን ዓለም አይቷት፣ አይ! ይህንንስ አልፈልግም፣ ብሎ በቆንጆ መንገድ መሄድ የሚችል ሰው አለ፡፡ መርጦ ደግሞ በሞኝ መንገድ የሚሄድ አለ፡፡ ሁለቱንም መውሰድ እንችላለን፡፡ የሁለቱም ልጆች መሆን እንችላለን፡፡ እዚያ ውስጥ ነው ያለነው፡፡ መበላለጥ የለም፡፡

"ሰው ባለበት ሁሉ ወንጀል አለ፡፡ ከጥንት ጥንት ጀምረህ" በእጁ ሩቅ እያሳየኝ "ብትመረምር ይህንን ወንጀለኝነት ታስተውላለህ፡፡ በቅርብ Time መጽሔት ላይ ሳነብ አንድ ፕሮፌሰር በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ጥናት ማድረግ ጀመረ፡፡ አይጠ ሞገጦች በማርባት በየዕለቱ የኑሮ ሂደታቸውን መመርመር ያዘ፡፡ ጥቂት ነበሩ ጥናቱን ሲጀምር፡፡ ለአይጦቹ ምግብም፣ መጠጥም እንደልብ ያቀርብላቸዋል፡፡ ውሎ እያደር ቁጥራቸው ተበራከተ፡፡ ቀጥሎ ሥፍራ እየጠበባቸው ሄደ፡፡ ተጨናነቁ፡፡ እዚህ ዋጋ ወንጀል ይጀመራል፡፡ ቀደም ብሎ የነበረው ሰላም ደፈረሰ፡፡ አንዱ ሌላውን መንዘስ፣ ማቁሰል፣ መግደል ጀመሩ፡፡ ጥቂት በነበሩ ጊዜ በሰላም እየበሉ እየጠጡ ከሴት አይጦች ጋር ይዝናኑ የነበሩት ወንድ አይጦች አንዳንዶቹ ሰዶማዊ መሆን ጀመሩ፡፡ የኒውዮርክ ኗሪዎች ተምሳሌት ሆኑ፡፡ ወንጀልን በሕግ አስከባሪ ትከላከለዋለህ እንጂ አታጠፋውም፡፡"

ተከዘ፣ በረጂሙ ተነፈሰና አፍጠ አየኝ፡፡ በፀጥታ እየተከታተልኩት ነው፡፡ ዝግ ባለ ድምፅ "የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጀምሮ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ይፋጃል፡፡ ማዕበል፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ መቅሰፍቱ ብዙ ነው፡፡ ጦርነት ከነዚህ አንዱ ነው፡፡

አንዱ ይመጣና ጋንዲን እጅ ይነሣዋል፡፡ አፀፋውን ጋንዲ መለሰለት፡፡ ከዚያም ሽጉጥ አውጥቶ ተኩሶ ገደለው፡፡ የገደለበት ምክንያት ይኖረዋል፡፡ የትም ብትሄድ ጠንካራ እምነት ካለህ ጠላት ይነሳብሃል፡፡ ከኢየሱስ እንጀምር፡፡ ሊንከን፣ ኬኔዲ፣ ማልኮም ኤክስ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ሚሲስ ኢንዲራ ጋንድሂ፣ አንዋር ሣዳት... በእምነታቸው ኃያልነት ምክንያት የተገደሉ ናቸው፡፡

ኢየሱስ ላይ ሆኖ አየንና አምላክ ሰው ሆነ፤ ሰውም አምላክ ሆነ፡፡ ከዚያ በፊት ጁሊዬስ ሲዘር ሰው ነበረ፡፡ አምላክ ሆነ፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገር አለ፡፡ ሒትለር ደግሞ ሰው ሸይጣን ሆነ፣ ሸይጣንም ሰው ሆነ የሚባል ነው፡፡ እኔ አንዳንድ ጊዜ ማመን ያስቸግረኛል፡፡ በቲዎሪ ነው እንጂ እኔና ሒትለር ሰው ነን የምለው በማመን ደረጃ ግን አላስበውም፡፡ ሒትለር ሰው አይደለም ነው የምለው፡፡

ሌሚንግ የሚባሉ የዱር እንስሳ አሉ፡፡ ይረቡና ይበዛሉ፡፡ አገሩ ገደልማ ነው፡፡ ሌሚንጎች አካባቢው ለራሳቸው እስከበቃ ይዋለዳሉ፡፡ እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የእግዜሩ ተዓምር የሚታይህ፡፡ እነዚህ የዱር እንስሳት እርስ በእርስ መፋጀት አይፈልጉም፡፡ ሰው አይደሉማ! በራሳቸው፣ ሌሚንጐችን ምንም ሳይነካቸው፣ በሙሉ በመንጋ

@Amharicbookstore



እየጋለቡ ገደል ገብተው ያልቃሉ፡፡ ለዘር ያህል ጥቂቶች ይቀራሉ፡፡ ተዋልደው አሥር ዓመት ሲያልፍ ተባዝተው ያቺ መኖሪያቸው መጨናነቂያ ስትሆን ደግሞ ተረኞቹ እየተወረወሩ ገደል በመግባት ለተተኪው ዘር ቦታ ይለቁለታል፡፡

ያገኘሁትን ማንኛውንም መጽሐፍ አነባለሁ፡፡ ጀምሬ የምተወውም አለ፡፡ ወጣት በነበርኩ ጊዜ ማንበብ ከጀመርኩ መጨረስ አለብኝ ብዬ እራሴን አስገድድ ነበር፡፡ ለደራሲው ታማኝ የሆንኩ እየመሰለኝ፡፡ አሁን ግን ቀምሼ ካልጣመኝ እተወዋለሁ፡፡ አልፎ፣ አልፎ ለመረጃ ስል በትዕግስት አነባለሁ፡፡

በማንኛውም ሰዓት፣ በየትኛውም ቦታ፡፡ ግን ምረጥ ብትለኝ ገንዘብ በሽበሽ ቢሆን፣ ሁሉንም ነገር አድርጌ ምሣ በልቼ፣ ጥቂት ጫት ቅሜ፣ ምክንያቱም ጫት ትኩረቶችህን ይሰበስባል፡፡ ይኼንን የምልህ ለእራሴ ነው፡፡ አንዳንዱን ደግሞ ጫት ትኩረቱን ይዘበራርቅበት ይሆናል፡፡ የእራሴን ልቀጥል፡፡ ቆንጆ ጠጅ ወይም ቢራ ፉት እያልኩ ባነብ ገነት ውስጥ እንዳለሁ እቆጥረዋለሁ፡፡ ይህ ባይቻል፣ ጫጫታ ውስጥ ገብቼም ቢሆን፣ የትም ይሁን የትም ሊፍት እየጠበቅኩ እንኳን አነባለሁ፡፡

ጠጅ ቤት ልዩ ልዩ ነገር ያጋጥምሃል፡፡ አንዱ ምን አለኝ "ጠጅ እየጠጡ ማንበብ እንዴት ነው?" አለኝ፡፡ መልሴ ይኼንን ጊዜ የሚወሰነው ባለሁበት "ሙድ" ነው፡፡ ያኔ ጥሩ ስሜት ላይ ነበርኩ መሰለኝ፣ የታል ጠጅ እየጠጡ ማንበብ ክልክል ነው የሚል ማስጠንቀቂያ? አልተፃፈም አልኩት፡፡ ሳቅ አለና ተወኝ፡፡

አንዱ ግን ከወዲያ ማዶ ተነስቶ በማስፈራራት ከበላዬ ቆሞ "ምንድነው እዚህ ጠጅ እየጠጡ ማንበብ?!" ሲለኝ፣ ለእሱ ብቻ በሚሰማ ድምፅ 'እናትክን!' አልኩት፡፡ ወደ ሌላው ጠጪ ዞሬ ከፍ ባለ ድምፅ "ልብ አድርጉልኝ! ይኼ ሰውዬ እዚህ መጥቶ ያስቸግረኛል" አልኩ፡፡

"ተዋቸው እንጂ ያንብቡዋ" አሉት፡፡ "ኩምሽሽ ብሎ ሄደ፡፡ እኔ ግን የእራሴን ተፈጥሮ ሳውቀው እንዲህ ዓይነት ፍጥነት የለኝም፡፡" በዚያን ጊዜ የንባብ አምላክ፣ ወይም አድባር ደርሶልኝ መሆን አለበት

"ልክ ነው፡፡ እናንተ ከስራችሁ እስክምትመጡ እየተዝናናሁ ይህችን አነባለሁ" አለና የማርሻል ማክሉሀንን Understanding Media አሳየኝ፡፡ በመንደራችን አንድ ኮማሪት አለ፡፡ ሴትዮዋ ካቲካላና ምግብ በተመጣጣኝ ዋጋ ይሸጣሉ፡፡ ጋሼ ስብሐት ከእኔ ጋር በጉርብትና ለመኖር ወደ ቂርቆስ ሰፈር ሲመጣ ከዋለበት ውሎ የእኛ ቤት ዝግ ሆኖ ቢጠብቀው፣ የእኝህን ኮማሪት ቤት እንደ ሞቆያ እንዲጠቀምበት ጠቆምኩት፡፡ ከዕለታቱ

በአንዱ ቀን ከላይ የጠቀስነውን መጽሐፍ እያነበበ ከራሱ ጋር ይሳሳቃል። ይህ ሳቅ ኮማሪ;ቷን ረበሻቸውና "አንቱ ዳዊቱትን አይድገሙብኝ" ሲሉ ተቆጡ። የጢሙ መንዠርገግ፣ አዛሙንትነቱ በፈጠረባቸው ፍርሐት ሴትዮዋ መጽሐፍ እያነበበ ሳይሆን እየደገመባቸው እንደሆነ ነው የተገነዘቡት።

እሱም ሐሳባቸው በፍጥነት ገብቶታልና "እሜቴ እኔ እያነበብኩ ያለሁት የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ነው እንጂ ዳዊት እየደገምኩ አይደለም" አለና መለሰላቸው። ለእኛም ማምሻውን መጥቶ ገጠመኙን አውግቶ ሲደመድምልን "ሴትዮዋ ልክ ነበሩ። በተሰጣቸው ብርሃን ነው ያዩኝ፡፡ የማነበው ሌላ መጽሐፍ መሆኑን ስነግራቸው ተረጋጉ እንጂ መጀመሪያ ተሸብረው ነበር።"

በቅርቡ ኩኩሻ አሥራ አራት ዓመት ይሞላታል፡፡ አምስተኛ ክፍል ነች፡፡ የቁጥር ችሎታዋን ስታሳየኝና ስለአባቷ ምን ያህል እንደምታውቅ ስትገልጽልኝ "አባዬ፣ አንተ አሁን ኪድሪሊዮን መጽሐፍ አላነበብክም?" አለችኝ አለና ሳቁን ለቀቀው፡፡

መጀመሪያ አንተና እሷ ደግሞ የምትመሳሰሉበትን መንገድ ልንገርህ፡፡ ሁለታችሁም ጥያቄ ታበዛላችሁ፡፡

እኔ በአሁኑ ሰዓት የትምህርት ሚኒስትር ብሆን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የማዘዝ ሙሉ ሥልጣን ይኖረኛል አይደል? በዚህ ጊዜ አስፋው ዳምጤን እጠራውና ወጣቶችን ሥነ ጽሑፍ፣ ታሪክ፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና አስተዳደር አስተምር እለዋለሁ፡፡ ለእኔ አስፋው ሙሉ ቤተ መጽሐፍት ማለት ነው

እኔ መዝገበ ቃላት ውስጥ ብቁ የሚባል ሰው የለም፡፡ ሰውዬው እራሱ የሄደበትን መንገድ ዞር ብሎ አይቶ አረፍ ሄጃለሁ፤ ወይም እዚህ'ጋ መስተካከል ነበረበት ማለቱ መብቱ ነው እኔም እስካሁን የሄድኩትን በጣም ወድጄዋለሁ።

እንግዲህ ማስታወስ ያለብህ እኔ የምጽፈው ለራሴ፣ ለደስታዬ ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ደግ ነው፡፡ ለእንጀራዬ መጻፍ የለብኝም፡፡ ለእንጀራዬ እንደሆነ ሥራ አለኝ፡፡ ጋዜጣ ላይ መጻፍም ቢሆን እኔ እማየው እንደ እንጀራ ነው፡፡ ስለዚህ ደስ ያለኝን፣ አንባቢን ያዝናናል የምለውን ነው የምፅፈው፡፡ አሁን ለጊዜው ልልህ እችላለሁ፣ ከዚህ ውጪ አልፅፍም፡፡ ጊዜ የለኝም፡፡ ብዙ ጊዜዬን በማንበብ ነው የማሳልፈው፡፡ አንዳንዴም ጨዋታ፡፡ ጨዋታ ሲደራ አሁን <u>መጻፍ አለብኝ ብዬ ራ</u>ሴን አላስገድደውም፡፡ ጨዋታው ውስጥ

@Amharicbookstore



እገባለሁ፡፡ ሌላው ደግሞ፣ እኔ ተልእኮ አለብኝ ለዚህ ኅብረተሰብ የሚል እምነት የለኝም፡፡

በጣሊያንኛ አንዲት ቃል አለች፡፡ 'Dilettante' ሌሎች የፈረንጅ ቋንቋዎችም ተውሰዋታል፡፡ ትርጓሜዋ በጣም ባለፀጋ ሰው፣ "ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ" ያለው ነው፡፡ ይህ ሰው ፈጣሪ ነው፡፡ ደስ ባለው የኪነ ጥበብ ሥራ ይሣተፋል፡፡ ዛሬ ሥዕል ካሰኘው ሥዕል ይሥላል፣ ወይም ይፅፋል፣ አልያም ይጓዛል፡፡ የእኔም ነገሩ አሁን ሳያት በንባብ በሥነ ጽሑፍ ዓለም 'ዴሌታንቴ' ነች፡፡

***

## ፴፱

### ማኅበሩ

ፀጥታ በሁለታችን መካከል ሠፈነ፡፡ የየራሳችንን ሐሳብ እያብሰለሰልን ነው፡፡ በእዚያ መሐል "የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር አባል አልነበርኩም። እንዲያውም! እንዲህ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል፣ ብርሃኑ ዘሪሁን ቢሮው አስጠርቶኝ፣ "እንካ ይህንን ቅፅ ሙላ" አለኝ፡፡

"የምንድነው?" አልኩት፡፡

"የደራሲያን ማኅበር አባል እንድትሆን" አለኝ፡፡

"አልሞላም" አልኩት፡፡

"ለምን?" አለኝ፡፡

"እኔ ደርቱ እርስ በርስ በተረሻሸነ ቁጥር፣ የማላውቀው ሟችን ለመኮነን የድጋፍ ሰልፍ መውጣት አልፈልግም" አልኩት፡፡ ቅፁን መልሶ ወሰደና በጨዋነት አሰናበተኝ፡፡ ብርሃኑ ስገምተው ከእኔ የባሰ አይናፋርና ጭምት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ተነጋግረን አናውቅም፡፡ የተነጋገርንበትን ወቅት አስታውሳለሁ፡፡ ማዕበል የሚለው መጽሐፉን ሳነብ ከዘጠና አምስት ገጽ በላይ ፈቅ ማለት አልቻልኩም፡፡

አፃፃፉ አሪፍ ነው፡፡ ገረመኝ፡፡ ደራሲው እንዴት ፅናት ቢኖረው ያንን ሁሉ መከራ ተጋፍጦ ቢድርሰቱ ሊገልፀው ቻለ? ጥንካሬው አስደነቀኝ፡፡ እኔ ግን ያንን ሁሉ መከራ አንብቤ ልከተለው ትልቡቱ ሊኖረኝ አልቻለም፡፡ ተረታሁና አቆምኩ፡፡ እሱን አገኘሁና

አናገርኩት፡፡ እንዳልኩህ አይናፋር ነው፣ በቅጡም ፊት ለፊት ሳያየኝ አስገራሚውን ገጠመኝ ነገረኝ፡፡

ለዚህ ሥራው ጥናት ወሎ ሐይቅ የሚባል አካባቢ ለሳምንታት ቆይቷል፡፡ ሰዎች እያነጋገረ፣ ማስታወሻ እየያዘ፣ እዚያው ውሎ እያደረ፡፡ አንዴ አንድ ዝብሬ ቤት አድሮ የገበሬው ባለቤት ለቁርስ የጤፍ ቂጣ ትጋግራለች፡፡ ቂጣው በሰለ፡፡ ሴትዮዋ አምጥታ በእንቅብ ስታቀርብለት እጇን አየ፡፡ ደነገጠ፡፡ ሴትዮዋ ቆማጣ ነች! አማራጭ የለውም፣ ያቀረበችለትን በላ፡፡ አየኸልኝ? ለዚህ ሥራው ይህን ያህል መስዋዕትነት ከፍሎበታል፡፡

በኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር የሚገኙ ወዳጆቻችን ከዛኒጋባ ቤትህ የተሻለ ቤት እንዲኖርህ ጥረዋል?" ለማስታወስ ፀጥ ብሎ አብሰለሰለ፡፡ ከተመሰጠ ወጣና "አላስታውስም! አላስታውስም! አላስታውስም! በፍፁም ትዝም አይለኝም፡ ቤት እናሰጥህ ማለት ምን ማለት ነው?"

"ከምትኖርበት ዛኒጋባ ቤት አስወጥተው የተሻለ ምቾት በምታገኝበት ቤት ውስጥ እንድትኖር ማድረግ አስበው ነበር?" እንዲህ ዓይነት ነገር ተሞክሮ ነበር ነው የምትለኝ? እኔ ግን አላውቅም፡፡ ይህንን ነገር አስበው አድርገውት ቢሆን ኖሮ፤ እኔም ብሰማ አልረሳውም ነበር፡፡ አሁን አንተ ስታነሳብኝ ትዝ ይለኛል ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ አይድነቅህ ሁሌም የምንኖረው በሐሰትና በእውነት መካከል ነው፡፡

@Amharicbookstore

***

*በአብዮቱ ዘመን የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር በብሔራዊ ቴአትር አዳራሽ አንድ ስብሰባ ጠርቶ ነበር፡፡ በወቅቱም የሳንሱር ክፍል ኃላፊ በዚህ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ነበር፡፡ የወቅቱ የደራሲያን ማህበር ሊቀመንበር የነበሩት አቶ ማሞ ውድነህ "በዚህ ዓመት በርካታ መጻሕፍት ለህትመት በቅተዋል፡፡ ይህን ላደረገልን የሳንሱር ክፍል ማመስገን እወዳለሁ" ሲሉ ተናገሩ፡፡ ታዳሚዎቹ አጨበጨቡ፡፡*

*በወቅቱ ስብሰባውን ታድሞ የነበረው ጋሼ ስብሐት ድንገት ብድግ ብሎ "ሳንሱር ይውደም፡፡ ለእኔም አጨብጭቡልኝ!" አለና ቀጭ ማለቱን በወቅቱ እዚያው የነበሩት ክብሩ ክፍሌና ኃይለመለኮት መዋዕል አጫውተውኛል፡፡*



፴

# መልእክተ ስብሐት - ለፀሐፍት

... ይኸን ያህል ዋጋው በሥነ ፍጥረቱ
ትልቅ እንዳይመስልህ የሰው ልጅ በውነቱ
እየተሻሻለ ሁልጊዜ አድሶ
መፍጠር ይገባዋል ራሱን መልሶ...

ከበደ ሚካኤል
የቅኔ ውበት

ከጋሼ ጋር በዚህ ምዕራፍ ላይ ውይይታችንን ስንጀምር በፀብ ነበር፡፡ "አንጋፋ ደራሲ ነህ? ... " ብዬ ስጀምር "እሺ እንሂድ!..." አለኝ በቁጣ ስሜት፡፡ እንደ አንጋፋ ደራሲነትህ ለወጣት ደራሲያን የጉዞ ልምድህን ብታጋራቸው? ባልኩት አባባል አልተደሰተም፡፡ "በምን መልኩ?" አለኝ እንደተከሳተረ ወጣት ደራሲያንና አንባቢያንን ለማበረታት!

"ለምን ማበረታት ያስፈልጋል!" ጮኸብኝ፡፡

አንዳንዴ እንዲህ ቱግ የሚልበት ወቅት አለ፡፡ ባለፉት አያሌ ዓመታት ተገናኝተን ስንጨዋወት ድንገት ይቆጣል፡፡ እኔም በፀጥታ አሳልፈዋለሁ፡፡ ይህንን ማስተዋሌን አንድ ቀን አንስቼበት ትክክል እንደሆንኩና አባቱም ላይ ይህ አይነቱ ባህሪ እንደሚታይባቸው ታናሽ ወንድሙ ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር ይህንን ባህሪ እንደሚጋሩት አጫወተኝ፡፡ ወደ ዕለቱ ውይይታችን ተመለስን፡፡ በወቅቱ እንደተሰማኝ ለወጣት ደራሲያን አስፈላጊ መልዕክት ማስተላለፍ አለበት ብዬ በማመን በፅናት ገፋሁበት፡፡ "ወጣቱ ደራሲ ጎበዝ ከሆነ ራሱ እኮ ነው አንባቢያኑን የሚፈጥረው" አለኝ፡፡ ቁጣው አልበረደም፡፡

"ዛሬ ነገር አበላሸሁ" ስል በሆዴ አሰብኩ፡፡ ሃሳቤን አሰባስቤ ወደምፈልገው ርዕሰ ጉዳይ እስክገባ እንደ ፋታ ማግኛ እንዲሆነኝ አጠገቤ ያለውን ማንቆርቆሪያ አነሳሁና ሻይ ቀዳሁ፡፡ ስኒውን አማስልኩና አቀበልኩት፡፡ ተቀብሎኝ ፉት ብሎ የሻይ ብርጭቆውን መቀመጫው ላይ እያኖረ ተረጋግቶ ወደምፈልገው ርዕሰ ጉዳይ ሰተት ብሎ ገባልኝ፡፡

"ይኸውልህ፣ ልብ እንድትለው የምፈልገው ነው፡፡ እንዲህ ብለህ ጠይቅ፡፡ ሰዎቹም ማንበብ የሚፈልጉ ከሆነ ደራሲዎች ሞልተውላቸዋል፡፡ መጀመሪያ፣ ደራሲ መሆን ያስፈልጋል? ምንድነው የእኔ ስጦታ? ምንድነው የእኔ ችሎታ? ብሎ ወደዚያ ማዘንበል ነው፤ አንዳንድ ሰው ደራሲ ለመሆን አይደለም የተወለደው፡፡ እሱ የተወለደው ለሌላ ሙያ ይሆናል፡፡ ምን ያደርግለታል መፃፍ? ብዙ ደራሲዎች፣ እነ ሼክስፒርና እነ ቶልስቶይ፣ እነ ዞላ ወዘተርፈ ሌሎችም ብዙ ጥፈዋል፡፡ እና፣ ምንድነው የሚያመጣው ልዩነት? ያን ያህል አይደለም፡፡ ለሰውየው ግን መኖርና አለመኖሩ ደስ የሚለውን ሥራ መሥራትና አለመሥራቱ ልዩነት ያመጣል፡፡ እና መጀመርያ ደራሲ መሆን የሚያስፈልገው ለምንድነው? ያስፈልጋል? መኖር ነው ያለብኝ እንጂ ደራሲ መሆን አይደለም፡፡ አናፂ ሆኜ መኖር እችላለሁ፣ ኮርቼ! እጆቼ ከቻሉልኝ፡፡ ማንኛውም እንጀራ የሚያበላ ሥራ ቅዱስ ነው፡፡ ከደራሲነት እኩል፣ ከሠዓሊነት እኩል! ከሙዚቀኛነት እኩል፣ አናፂነት ግንበኝነት እኩል ነው፣ ልዩነቱ ለኪነጥበብ ይጨበጨብለታል፣ ይኼኛው አይጨበጨብለትም፡፡ ትንሽ ናት ልዩነቷ፣ ዋናው ቁምነገሩ ፍላጎትህን ማወቅ ነው፡፡

"ታዲያ ለምን አይተውትም ማንበቡን? ይኼኮ አግባብ አይደለም"፡፡ አሁንም ቁጣው ገነፈለ እኔም በፀጥታዬ ፀናሁ፡፡ እሱም ፋታ አገኘ፡፡ ቀጠለና "እያነበበ እያለ እንቅልፉ የሚመጣ ከሆነ ማንበብ አያስፈልገውም፣ በቃ፡፡ በግድ ማንበብ የለብህም፡፡ እገሌን አንብበሃል? ጥ! ምናምን! ሲባሉ ይሆናል ማንበብ ይኖርብኝ ይሆን'ዴ? እያሉ የሚደበሩት፡፡

የሰው ልጆች ማንበብና መጻፍን በቅርብ ጊዜ ነው የጀመሩት፡፡ መኖርን ግን ጥንት፣ ጥንት ነው፡፡ በሚሊዮን ዓመታት ነው የጀመሩት፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ መኖር እንጂ መጻፍና ማንበብ አይደለም፡፡

ባንተም እምነት በደንብ ብትሄድበት እንደዚያ መሆኑ አይቀርም፡፡ ለማወቅ ማንበብ? ከፈለግ ነዋ! የሚወድ ከሆነ ገብሬ የሚወደው ቅቅል ድንች ነው፡፡ ሄደህ አንተ ገብሬን ክትፎ ላብላህ? ብትለው ክትፎ ለእሱ ምንም አይደለም፡፡ ይለያያል፡፡ እንደዚህ ነዋ፡፡ ማንበብ ትወዳለህ እና ትቀጥልበታለህ፣ ወይ ስሜት አይሰጥህምና ትተወዋለህ፡፡ ለዚህ ነገር መጨነቅ የሚያስፈልገው አይመስለኝም፡፡

ይኸውልህ፣ ይኼ የእኔ እምነት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ከእኔ ተቃራኒ እየተናገረ ልክ ሊሆን ይችላል፡፡ ማንበብና መጻፍ የተያያዙ ናቸው፡፡ እንደ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡፡ መጀመሪያ አንተ ማንበብ ካላስፈለገህ መፃፍ ግዴታህ አይደለም፡፡ ማንበብ የማይወድ መጻፍ እፈልጋለሁ ቢለኝ አይገባኝም፡፡ ምንድነው



የሚጽፈው? ስለእንጨት የማያውቅ፣ የእንጨቱ ሽታ የሚከረከረው ሰው ወደ አናፂነት መግባት የለበትም፡፡ የማንበብ ልምድ ሳይኖረው የመድረስ ጉጉት ካለበት ፋሽን መስሎት ተሳስቷል፡፡ ንግድ አይደለም መጻፍ፡፡ የፍቅር ጉዳይ ነው፡፡ መፃፍ የሚወዱ ከሆነ፣ ተው ብትላቸው አይተውም፡፡ መጀመሪያ ግን "ማንበብ ትወዳለህ ወይ?" በለው፡፡ ከወደደ ማንበብ ደግሞ በቂ ነው፡፡ እየተደሰተ ከሆነ፡፡ ጻፉልኝ፣ አነባለሁ ብሎ መደሰት፡፡ ምን አለፋው? ሌላው ይረስለት እሱ እንደ መብላት'ኮ ነው፡፡ አንባቢያን'ጋ ስንመጣ ደግሞ ከምር ማንበብ የሚወዱት ከሙቶዎቹ አምስቱ ነፍሳቸው የደራሲ ነፍስ ናት፡፡ ከነዚህ ሁለቱ ወይም ሦስቱ በተለያየ ምክንያት መጻፍ አይችሉም፡፡ ወይ ውስጣቸው የሆነ የተነደበ ነገር አለባቸው፡፡ ብዙ ችግር ይኖርባቸዋል፡፡ አንድ ሁለቱ ይጽፋሉ፡፡ በቂ ነው! የተጻፈው ቢነበብ፡፡

አሁን የአማርኛው ሥነ ጽሑፍ በቂ አልተጻፈም፣ ምናምን ይባላል፡፡ ግን በቂ ተፅፏል፡፡ ማንበብ ለሚፈልግ፡፡ በብዛት እንደ እንግሊዘኛ 'Literature' ልዩ ልዩና በገፍ የለም፡፡ ይህንን አውቃለሁ፡፡ ከልብህ ከፈለክ ግን በአማርኛውም አለ፡፡ ከእንግሊዞች እኩል ነን፡፡ ከሌሎቹ ሁሉ እኩል ነን፡፡ ልዩነቱ የቴክኖሎጂ ነው እንጂ ነፍስህ ያው ነው፡፡ ሰው ነው፡፡ የቋንቋ አንዳንድ 'Concept' ማለት ንጥረ ሐሳብ እነሱ አሏቸው፡፡ ለምሳሌ ቴክኖሎጂ ውስጥ ካላደክ፣ አደን ሀገር ውስጥ ካደክ እነዚያ ቃላትና ሃሳቦች አይኖሩህም፡፡ ቴክኖሎጂ ውስጥ ያደገው ያንተ የአደን ቃላት አይኖሩትም፡፡ ብዙ ብዙ ይኖሩሃል አንተ፡፡ እሱ የማያውቃቸው ሐሳቦችም ቃላትም፡፡ ልዩነቱ የእሱ ስለሚያበላ፣ ሰውን ስለሚያስገድድ፣ ገበያ ስለሚወጣ ይደነቃል፡፡ እና አድጓል፣ ተራምዷል፣ ተራቋል ይባላል፡፡ ግን እዚያ ሄደው 'Primitive' የሚባለውን ሕዝብ ያጠኑ ሲነግሩን፣ ለካ ማንም 'Primitive' የለም፡፡ እኛ እዚህ ነን፣ እናንተ እዚያ ናችሁ፣ እነሱ እዚህ ... ማለት እኩል ሜዳው ላይ ነን፡፡ ማንም ወደፊት እየሄደ አይደለም፡፡ ሁላችንም ወደሞት ከመሄዳችን በስተቀር ሁሉቱም እና እያንዳንዱ የኑሮ ዓይነት ራሱን የቻለ ነው፡፡ ኋላቀርም አይደለም ተራማጅም አይደለም፡፡

እሱ የ'Classification' ጉዳይ ነው፡፡ ነገሮችን ለአእምሮዋችን እንዲመቸው መከፋፈል፡፡ በቴክኖሎጂና በሀብት ያደገውን አንደኛ ዓለም እንለዋለን፡፡ ሌላውን ሦስተኛ ዓለም እንለዋለን፡፡ ስናወራ ልዩነት ስላለውን ጂ ከልዩነቱ አንዳይነትነቱ በጣም ይበዛል፡፡ ልዩነቶቹ፣ እንግሊዙ በጣም የሚበሳጨው መኪናውን እየነዳ ይሆናል "እናቷን! ተጫወተችብኝ" ምናምን ይላል ፍቅረኛውን፡፡ ምድረ በዳ

@Amharicbookstore

ያለው የአፋር ጎረምሳ ደግሞ ግመሉን እየነዳ ነው የሚናደደው፡፡ ስለዚያች ብሽቅ ፍቅረኛው ነው የሚበሳጨው፡፡ የትም ብትሄድ ሰው ያው ነው፡፡

እኔ የማምነው እንዲህ ነው፡፡ የሰው ልጅ ፍጥረቱ አንድና እኩል ቢሆንም የተለያየ አዝማሚያ አለው፡፡ ለምሣሌ የፈረንሣይን አዝማሚያ ብትወስድ ሥዕል፣ ውበት፣ የመኖሪያ ነገሮች ይመርጣሉ፡፡ እንግሊዝ ጋ ስትሄድ ፍትህ ምናምን ይሉሃል፡፡ እኛ ጋ መጥተህ ስታስተውል ሥልጣኔያችን የቃል ነው፡፡ ለምሣሌ ቅኔ፣ ግጥም፣ ተረት፣ አግቦ፣ አሽሙር እያረግን በቃላቶቹ እንጫዋወታለን፡፡ እንግባባለን፡፡ ይህንን ልብ ብሎ የፃፈ የእኛ አበሻ ደራሲ ከሌላው ዓለም የተሻለ ቅድሚያ (አድቫንቴጅ) አለው፡፡ ቃላቱን እንደ ጥበብ ወስዶ ከተጠቀመበት ዕድለኛ ነው፡፡ ቃል ነው የእኛ ጥበብ፤ መግለጽ እስከፈለግህ ድረስ፡፡ መዝገበ ቃላትን ማገላበጥ አያስፈልግህም፡፡ ማኅበረሰቡ ራሱ ሲያወራ አድምጥ፡፡ በተለይ ያልተማሩት፣ በድሜ ገፋ ያሉት፣ አማርኛን እንደ እንዝርት ነው የሚያሾሯት፡፡ በጥቂት ቃል ብዙ ሲሉ ትሰማለህ፡፡ ይህንን ካጠናህ በቂ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ አዲስ ነገር የለም በኑሮ ውስጥ፤ ያንኑ ነው የምንደጋግመው፡፡ መውደድ፣ መጥላት፣ ናፍቆት፣ ምቀኝነት... ጥቂት ናቸው፡፡ የእነሱ መሰባጠር ነው የሕይወት ሂደቱ፡፡ ያንን መሰባጠር የእኛን ባህል ታለብሰዋለህ ማለት ነው፡፡ ልክ እንደ ሰዎች ቆዳ፡፡ ሌላው፣ አጥንቱ፣ ሥጋው፣ ደሙ ያው ነው የማንም ሕዝብ፡፡

ይኸውልህ አንድ ነገር አስታወስኩ፡፡ አንድ ቀን ደበበ ሰይፉ ቤት ሄድኩ፡፡ ደበበን ታውቀዋለህ? አዎ የዩኒቨርሲቲው መምህር፡፡ ሰላም ብዬው ቤቱ እንደገባሁ ምን እያደረግክ ነው? ስለው፤

"የአማርኛ መዝገበ ቃላትን ሰብስቤ ቃል በቃል እያጠናሁ ነው" አለኝ፡፡ ገርሞኝ "ለምን እንዲህ ማጥናት አስፈለገ?" አልኩት፡፡

"ወደፊት የድርሰት ሥራዎቼን በሙሉ የምሠራው በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ ስለዚህ የቃላት ጉልበቱን ጥልቅ ለማድረግ ይኸውልህ መዝገበ ቃላቱን ሁሉ ሰብስቤ አንድ በአንድ እየመረመርኩ ነው" አለኝ፡፡

እንግዲህ አንድ ወጣት ደራሲ፤ ደራሲ ነኝ ብሎ ካሰበ እንዲህም መዘጋጀት የግድ ነው፡፡

"ወጣቱ ደራሲ ጥሩ አድማጭ ከሆነ ሐሳቡን በአማርኛ ጥሩ አድርጎ መግለጽ ይችላል ብለህ ታምናለህ ነው ያልከኝ? ኮርቶ! እንዲያውም በቴአትሩማ እንግሊዘኛው ቃል የለውም፡፡ እስኪ አሁን ወይ ጉድ! እኔው ነኝና፤ እከከከከከ! ዘራፍ! በል እስኪ በእንግሊዘኛ፡፡



አ! ኸ! እንዲያውኮ! እያልክ ስትሄድ፣ የእዚህ ሁሉ ሀብት ባለቤት ነው የእኛ ደራሲ፡፡ ወደ ውጪው ስታይ ግን 'ቴክኖሎጂካል' እየሆኑ ሲሄዱ ያንን እየረሱት፣ እየረሱት ነው የመጡት፡፡ ቀደም ብሎ ብዙ ውብ አባባሎች ነበሯቸው፡፡ አሁን የኒቸውም፤ ቢኖሩም በመዝገበ ቃላት ተመዝግበው ይገኛሉ እንጂ አይጠቀሙባቸውም፡፡ ምክንያቱም የቴክኖሎጂው ሕይወትና መዋከብ አርግፈዋቸዋል፡፡ የእኛ ግን ገና ናቸው፡፡ በተለይ የአሁኑ ዘመን አማርኛ በጣም ጉልበተኛ ነው፡፡ ለቴአትር በጣም! ለልቦለድም ቢሆን ምንም አይጎድለውም፡፡ ቢጎድለው ደራሲ ነው እንጂ ሕዝብ አይጎድለውም፡፡ የሕዝቡ መከራ በቂ ነው፡፡ ደስታውም በቂ ነው፡፡ ይዘፍናል፣ መከራውን እየቻለ፡፡ ደግሞ ጻፍክ አልጻፍክ የራስህ ጉዳይ ነው፡፡ አንተ ነህ እንጂ ሕዝቡ መኖሩን ነው የሚያየው፡፡

ለአንዳንዱ ወጣት ደራሲ በቂ ነው፣ ላንዳንዱ አይበቃም፡፡ እንደ ሀዲስ ዓለማየሁ ለመፃፍ በቂ አለው፡፡ ገና በአማርኛ ለመፃፍ ያልተሞከሩ አፃፃፎች አሉ፡፡ አላስፈለጉማ፡፡ ገና ናቸው፡፡ ማስታወስ ያለብን፣ ሥነ ጽሑፍ የሕዝቡን ሕይወት ነው የሚያወራው፡፡ ማነፃፀር አይከፋም፡፡ መዋስ ጥሩ ነው፣ የሚረባ ከሆነ፡፡ ማስታወስ ያለብን ግን የራሳችንን ኑሮ ለመፃፍ አዲስ አበባ ውስጥ አድገህ ከሆነ ቃላት ያንሱሃል? አንድ ሁለት የታተሙ ይኖራሉ እነሱን ታነብና "ለካ እንደዚህ መፃፍ ይቻላል?" ትላለህ፡፡ በቂ ናት! ይህቺን እምነት ከያዝክ "እኔ ደግሞ የምፅፈው አለኝ፣ ምን ልፃፍ? ምንድነው የሚሰማኝ?" ብለህ ትፅፋለህ፡፡ እና ስለኖርክበት ኅብረተሰብ ስለሆነ አሳምረህ ትጽፈዋለህ፡፡ አያስፈልግህም መጣርና ከሩቅ ማምጣት (ቢቻል ጥሩ ነው) ደግሞም የተተረጎሙ አሉኮ፣ እነሱንም ማንበብ ይቻላል፡፡ የግድ በእንግሊዝኛ ማንበብ የለብህም፡፡ አሁን እነ ሲድኒ ሼልደንን አንብበህ፣ ሴራ፣ ምን ከምን ቀጥሎ ነው የሚመጣው? ከዚያስ ምን ሲነሳ ነው የትረካችን ክር የምትሸርበው?

ይህ እንዴት እንደሚታረም አላውቅም፡፡ ስለዚህ ወጣቱን ደራሲ፣ ስትፅፍ ሐያሲውን እርሳው ነው የምለው፡፡ ደስ እንዳለህ ተጠበብ፡፡ መዘነጥ አስበህ ስትለብስ ገንዘብ እንደልብ ካለህ አንተን ደስ ያለህን እንጂ እገሌን ደስ እንዲለው፣ እገሌ እንደሚለኝ እያልክ አትለብስም፡፡ ሞኝ ካልሆንክ፡፡ ደስ ያለህን ለብሰህ ስትሄድ ነው ለማብሰል የምትፈልጋትን ልጅ የምታገኛት፡፡ ስትፅፍም ደስ ያለህን ፃፍ፡፡ ደስ ያልከው ያነብሃል፡፡ እርሳው ሐያሲን፡፡ በነገራችን ላይ፣ ባላየኸው መንገድ የሚያሳይህ ሐያሲም ያጋጥምሃል፡፡ በራሴ ላይ ደርሶ "ፕ! ጎበዝ!" ብዬ ያደነቅኳቸው አንድ ሁለቱን ሐያሲን ማንበቤን አስታውሳለሁ፡፡

ቋንቋን ለማሳደግ እንግሊዘኛ ከሚነጋገሩ ጋር ማውራት፡፡ ደግሞ መጽሐፍ ውስጥ የሚደጋገሙ ቃላት አሉ፡፡ ደከመኝ ብሎ መተው አይደለም፡፡ 'Dictionary' መመልከት፡፡ ሁሉንም ቃላት አይደለም ማየት፡፡ ስታነብ አንዲት ቃል ታጋጥምሃለች፡፡ ያቺ ቃል ካልገባችህ ሙሉውም አይገባህም፡፡ እሷ 'Dictionary' ያስፈልጋታል፡፡ ሌላው ግን በግምት ገብቶህ ስለሆነ ማለፍ፣ ጋዜጣም ማንበብ፣ መጽሐፍም ማንበብ፡፡ በተለይ ሬዲዮ ማዳመጥ፣ ጥሩ ሬዲዮ ላለው BBC መከታተል፡፡ BBC እኮ Literature ያስተምርሃል፡፡ Story የሚነበብበት ጊዜ አለው፡፡ Classic፡፡ ሁሉ ነገር ፕሮግራማቸው ውስጥ አለ፣ በቀላሉ የምታገኘው፡፡ እሱን ይዘህ መከታተል፡፡ የእኛ መዝገበ ቃላት ሕዝብ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎችን እየጠየቅክ ነው ቋንቋህን የምታዳብረው፡፡

የእኛ ሥልጣኔ ቋንቋ ነው ብዬሃለሁ፡፡ ብቃል እንደመሆኑ፣ ወጣቶቹ የሚፅፉትን ስታነብ በጣም ትገረማለህ፡፡ በደንብ ስታውቀው እንዲህ ለመፃፍ ባልቻሉም ነበር፡፡ በትምህርት፣ በዕውቀት 'back-ground' ቢሆን ኖሮ አታምነውም፡፡ ነገር ግን የቃል ሥልጣኔ አባል ስለሆነ ቃልን ያውቃታል፡፡ በደሙ በናቱ ጡት ጠብቶታል ልልህ እችላለሁ፡፡ ነፃነት ብቻ ነው የሚፈለገው፡፡ ከሐያሲው በፊት ሳንሱር ነበር የምንለው፡፡ በእርግጥ ሳንሱር የፀሐፊው መቅሰፍት ነበር፡፡ ባይታተምም ልፃፍ የሚሉ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ሳንሱር ወዲያ ካልክ በኋላ፣ መጣልና ሐያሲ! ከሳንሱር በምንድነው የሚያንሰው? ልዩነቱ ሳንሱር ድርጅት ነው፣ ይኼኛው ግለሰብ ነው፡፡ የሃያ ሦስት ዓመቱን ደራሲ ከሃምሣ ዓመቱ ደራሲ ጋር አወዳድረህ መኮርኮም ሐሰ አይደለም፡፡ ሌላ ነገር ነው፡፡ የልጁን ዕድሜ፣ ጽሑፉን አስተያይተህ፣ በዚህ ምክንያት እዚህኛው ላይ አበዛኸው ወይም አሳነስከው፣ እዚህች ጋ ደሞ አሪፍ ሠርተሃል እያልክ ብታግዘው ወደፊት ምን ዓይነት ተስፋ እንዳለው ይታየዋል፡፡

ዘመኑ ለመፃፍ ይመቻል፡፡ የዚያኑ ያህልም እንቅፋቶች አሉ፡፡ ለመፃፍ አንዱ እንቅፋት ሕግጋት አውጪዎቹ ናቸው፡፡ መጀመሪያ ሲያስተምሩህ ዐረፍተ ነገር፣ ነጥብ፣ ሐረግ ያስፈልጋል፡፡ አናጢ ለመሆን ስታስብ መስመር ማስመር፣ መላግ፣ በመጋዝ መቁረጥ ያስፈልግሃል፡፡ የሚያስተምርህ አናጢ የሆነ ሰው ነው፡፡ መጻፍ ላይ ስትመጣ ሌላ ይሆናል ነገሩ፡፡ ፅፎ የማያውቅ ነገር ግን ሥነ ጽሑፍ እያነበበ ዲግሪ እያገኘ ይመጣል፡፡ አስተማሪው ይህንን አንብባችሁ እነዚህን ጥያቄዎች መልሱ እያለው ነው የተመረቀው፡፡ እሱ አይፅፍም፣ ፃፍ ብትለውም አይችልም፡፡ ምንድነው የሚችለው? ድሮ ትምህርት ቤት በተነገረው ሕግጋት እዚህ ወጣቱ ላይ መፍረድ፡፡



ያንን ሕግጋት ያወጣው ሌላ ኅብረተሰብ፣ በሌላ ሁኔታ፡፡ እሱን አምጥቶ እዚህኛው ላይ መፍረድ፡፡ እንበል" ጀምስ ጆይስ የዛሬ 60 እና 70 ዓመት የፃፈበትን ያመጣና ለምሣሌ የየሺጥላ ኮከብን መፅሐፎች አንስቶ የታል እንዲህ ያልከው? በዚያች በባዕድ መለኪያው እያየ እየመተረ ያብጠለጥለዋል፡፡ ወጣት ፀሐፊያን ደግሞ እነዚያን ነው የዕውቀት ምንጭ አድርገው የሚቆጥሯቸው፡፡ ለእኔ ይህ እንቅፋት ነው፡፡

ቀደም ብዬ ነግሬህ ይሆናል፡፡ ወጣት ፀሐፊ ሲጀምር ማንበብ፣ መረጃ መሰብሰብ፣ የሚኖርበትን ማኅበረሰብ ማስተዋልና ማድመጥ አለበት፡፡ መፃፍ ልጀምር እስኪል፡፡ ብልሃቶቹን፣ ሴራ፣ መቼት፣ ልብ ማንጠልጠል፣ ወዘተ እወቃቸው፡፡ መጻፍ ስትጀምር ግን እርሳቸው፡፡ አሁን አንተ ጸሐፊ እንጂ ኢቀቂር አጡጪ አይደለህም፡፡ ሐያሲ አይደለህም፡፡ በመፍጠር ላይ ነህ፡፡ በመፍጠር ላይ እያለህ ደግሞ አሃ! እንደ እገሌ ልፈጥር ነው እንዴ? ወይም እንደ እገሌ አልፈጥርም የምትል ከሆነ በመፍጠር ላይ አይደለህም፣ አእምሮህን በመረበሽ ላይ ነህ፡፡

ወጣት ደራሲያን በመጀመሪያ መጽሐፋቸው ውጤታማ ባይሆኑ ምንም መደንገጥ አያሻም፡፡ እንደገና መፃፍ፡፡ ወልደኸው ቢሆን ታሳድገዋለህ፡፡ ትከታተለዋለህ፡፡ ይኼኛው ግን ፃፍከው ታተመ በቃ፡፡ አለቀ፡፡ ከእዚያ ወዲያ መፅሐፉ ያንተ አይደለም፡፡ የኅብረተሰቡ ነው፡፡ ካወቀበት ሕብረተሰቡ ያነብበው ይደሰትበት፡፡ ካላወቀበት ቀረበት፡፡ የእዚያ ወጣት ድርሰት ለእኛ ኅብረተሰብ አይገባውም ማለት ነው፡፡

እሣታሚ ፊት ለሚነሳው ምሣሌ እንጥቀስላቸው፡፡ ሶመርሴት ሞም የተማረው ሕክምና ነው፡፡ በኋላ መፃፍ በለጠበትና ማከሙን ተውው፡፡ ሲፅፍ አሣታሚዎች ትንሽ ወረቀት ይልኩለታል፡፡ እንዲህ ትላለች፡፡ "የሰጡንን ጽሑፍ አንብበነዋል፡፡ ለጊዜው የማንፈልገው ስለሆነ መልሰንልዎታል፡፡ ሌላ ቢጽፉ ለማንበብ ፈቃደኞች ነን፡፡" እንደኛ አገር ነብስህን ከስጋህ በሚለያይ መልኩ አያስደነግጡህም፡፡

ሞም ሲፅፍ አሣታሚዎቹ ሪጀክሽን ስሊፕ ሲፅፉለት ወረቀቶቹ ተጠራቀሙ፡፡ ሞም ሳይታክት እየጻፈ እንዳያስትመለስ በተለያዩ ቦታዎች ሞከረ፡፡ አልሰመረም፡፡ ከተሳካለት በኋላ ሲናገር "አሳታሚዎች የላኩልኝን የመሰናበቻ ወረቀት አሰባስቤ የወንደላጤ ቤቴን ላሳምር ብል ግድግዳዎቹን ሙሉ ፀሙሉ ይሸፍንልኝ ነበር" ብሏል፡፡

ሞም ያለመታከት በመሥራቱ በኋላ የሚፅፈው ተለምዋ ሆነ፡፡ ግን ከጅምሩ አንድ ሁለቴ ሞክሮ "ኤጭ እንግዲህ የእንግሊዝ ሕዝብ

አይገባውም ዲዲብ ነው፡፡ ወደ ሕክምናዬ ልመለስ" ቢል ኖሮ ከሰሮ ነበር፡፡ እሱ ብቻ ሳይሆን መከሰራችንን አንወቀው እንጂ እኛም አንባቢዎቹ ከሰረን ነበር፡፡ እናም ቆም ችክ ብሎ መፃፉን ቀጠለ፡፡ ምክንያቱም እሱ የውቃላ እንደሚፅፍ፣ ደራሲ እንደሆነ፡፡ ከገቢየው ጋር እስከሚገናኝ ድረስ ታገሠ፡፡ በሃደት ተሣካለት፡፡ ስለዚህ ወጣት ደራሲዎች ከገቢየው ጋር እስከሚገናኙ መታከት የለባቸውም ነው የምለው፡፡

ቆየምን አንድ ወጣት ደራሲ "ምን ትመክረኛለህ?" ይለዋል፡፡ ስትፅፍ ሰሜትህ እቺን ሐረግ እንዴት ጣፍኳት! አይ እቺ ዐረፍተ ነገር ማማሯ! የምትላቸውን ሰርዛቸውና ሐሳቡን በሌላ ቃላት ፃፈው፡፡»

አለዚያ ቀንጆ የጻፈ እየመሰለው ይደጋግማቸዋል፡፡ ከአንድ መጽሐፍ በላይ አይነበብለትም፡፡ ጀማሪ ስለሆነ ይህ የፃፈው ታሪክ ለራሱ እንጂ ለአንባቢ የሚመጥን አይደለም፡፡ ቃላት ዐረፍተ ነገር እየለ ለራሱ ነው እየጻፈ የተማረባቸው፡፡ ረቂቁ ላይ መለማመጃውን ፅፎታል፡፡ ሕፃናት ልብ ብለህ ስታይ ጠርንት፣ ባልና ሚስት እየሉ ይጫወታሉ፡፡ የም ለአዋቂነት ሚና ልምምድ እየደረጉ ነው፡፡ ይኼንንም ሳይታሰብ የሚያደርጉት ነው፡፡

ጀማሪ ደራሲ ዋናው ነገር ራሱን አዘጋጅቶ መጀመር አለበት፡፡ አዎ! እንደመጣልህ ፃፍ፣ ስብሐት ቃላት አታብዛ፣ ዐረፍተ ነገር አታርዝም ብሎኛል ብለህ አትጨነቅ፡፡ ይህንን እየሰብክ ከፃፍክ እኔ እንቅፋት ሆንኩህ አጎደልኩህ ማለት ነው፡፡ መጀመሪያ ሲወጣ ዝም ብለህ የምትሄደውን የምትፅፈውን ትጨርስና ታነበዋለህ፡፡ አሁን ልምምድህን አጠናቀህል፡፡ ልክ እንደገበሬው ትመለስና ታርማለህ፡፡ ይኼ መነሻህ ነው፡፡ ወደፊት ለምትሠራው ታላቅ ሥራ መንደርደሪያህ ነው፡፡ ከሁለት ዓመታት በኋላ ትረሣዋለህ፡፡

ይህንን አፅንኦት ሰጥተን ብናስምርበት ደስ ይለኛል፡፡ አንድ ወጣት ደራሲ ማንበብ አለበት፡፡ ሳያነብ ምንድነው የሚፅፈው? ዝም ብሎ ቢፅፍ በኅብረተሰብ ላይ እየላገጠ ነው፡፡ ያ እንዳይሆን ግዴታ ማንበብ ይኖርበታል፡፡ ሲፅፍ ደግሞ ጀማሪ ስለሆነ ተፅዕኖ ይኖርበታል፡፡ ይህንን በእንግሊዘኛ ቢሆን 'ኢንስፓየር' ወይም ብርሃን መስጠት፣ ወይም ማሣየት፣ መንገድ መምራት ብንለው ይሻላል፡፡ የምትወደው ደራሲ ኢንስፓየር ያደርግሃል፡፡ ያ ተገቢ ነው፡፡ ተፅዕኖው ጊዜውን ጠብቆ ያልፋል፡፡ አያስጨንቅህ፡፡ ዕድሜ አለች፤ የተፅዕኖ ዕድሜህን አልፈልግም ብለህ ካሣለፍክ ተሳሳትክ፡፡ ትክክለኛው ተፅዕኖ ላንተ የሚያስፈልግህ መዋጮ ቀረብህ፡፡ መሣን ሆንክ ማለት ነው፡፡ ልትረጥብ ስትችል፡፡ ተፅዕኖ ቃሉ ደስ አይልም፡፡ ኢንስፓየር ባደረገህ ደራሲ መንገድ አልሄድም፣ በራሴ

@Amharicbookstore



መንገድ ብትል፣ ያንተ መንገድ ገና ነው፡፡ የታወቀውን መንገድ ሁሉ ሄደህ ከእዚያ በኋላ ነው አዲስ መንገድ የምታወጣው፡፡ የምትወዳቸውን ደራሲዎች ተከትለህ ብትፅፍ "ኤ! እንደ እገሌ መሰልህ" ቢሉህ መፍራት የለብህም፡፡ እንዲያውም እሱን መሰለ ጽሑፌ ብለህ መደሰት አለብህ፡፡ ዕድሜ አለ፣ ይመጣና እንድታራግፈው ያደርግሃል፡፡ ከዚያም የራስህን መንገድ መሄድ ትጀምራለህ፡፡ ደግሞ ከፈለግህ የራሴ መንገድ የምትለው የለም፡፡ በጣም ይመሳሰላል፡፡ ትንሽ ነው ልዩነቱ፣ ልክ እንደ አካላችን ነው፡፡ እስኪ እይ ሁለት ዓይን፣ ሁለት ጆሮ ሰላሳ ስንት ጥርስ ሁለት እጅ፣ ሁለት እግር፣ ስንል ልዩነቱ በጣም ትንሽ ነው፡፡

ሴቶቹም ወጣት ደራሲን አሁን ባነሣናቸው ሐሳባችን ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ነጥሊን እንይ ካልክ እንዲህ እልሃለሁ፡፡ ገና ስንፈጠር ጀምረን የሕይወታችን ዓለም ሴቶች ናቸው፡፡ ከተወለድን በኋላ ያጠቡናል፡፡ ቋንቋ ያስተምሩናል፡፡ ከቋንቋ ጋር አስተሳሰብ፣ ወግ፣ ባሕል፣ የሥነ ልቦና መሠረት የሚጥሉብን ሴቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በሕንድና በእኛ አገር ወንዶች የምንለብሰው የፈረንጅ ልብስ ነው፡፡ ሴቶቻችን ግን የሚለብሱት የባሕል ልብሳቸውን ነው፡፡ የትም አገር ብትሄድ ሴቶች ናቸው የባህልን ሒደት የሚቀጥሉት፡፡ ወንዶች ሌላ ነው ሥራቸው፡፡ ደግሞ ልብ ብለህ ብታስተውል ልጅን ከመውለድና ከማሳደግ የበለጠ ትልቅ ጥበብ የለም እኮ! አያበላም 'Best seller' አይደለም እንጂ ትልቅ ጥበብ ነው፡፡ ከጥበብም በላይ ነው፤ እውነተኛው ፈጠራ እሱ ነው፡፡ በእናቶቻችን አይተነዋል፡፡ ትልቁንም ሥራ የሚሠሩት እናቶቻችን ናቸው፡፡ ላይ ላዩን ግን እኛ ወንዶቹ ነን ነው የሚባለው፡፡

አንድ የአሜሪካኖች ዘፈን አለችልህ፡፡ እንዲህ ትላለች A man chases a girl until she catches him. እሱ አሳዶ የሚይዛት ይመስለዋል እንጂ እሷ ነች ተሳድዳለት ስታበቃ ዞራ ለቀም የምታደርገው፡፡ የሚጽፉትስ ስለምንድነው? ስለሰዎች ፍቅር አይደለም? ነውና! ስለ ሲ.አይ.ኤ፣ ኬጂቢ ውስብስብ ትግል አይደለም? ተወው! ወንዶች የፃፉት ይበቃናል፡፡ ሴቶቹ ባይጨመሩ ምንም አይደል፡፡ ትልቁን የሰው ልጅ የመፍጠር ጥበብ ቀድመውን ፈጽመውታል፡፡ ፍላጎቱ ያላቸው ሴቶች ደግሞ እንደ አጋታ ክርስቲን፣ ኤሚሊ ዲክንስንን... ይውሰዱ፡፡ የዲቴክቲቭ ታሪክን ለዓለም ካስከመከመ አራት ወይ አምስት ደራሲያን አንዷ አጋታ ክሪስቲ ነች፡፡

ዜና ልጄ? ደራሲ ትሆናለች ብያለሁ፡፡ ይኸውልህ፣ የእኔን ከፍቅር መነጨ አድርገህ ውሰድ፡፡ አንዳንድ ሥራዎቿንም አይቼ

ወድጃቸዋለሁ፡፡ ተቃራኒውን ደግሞ ልንገርህ፡፡ ሾፐንሀወር (Schopenhauer) የተባለ ፈላስፋ በ19ነኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነበር፡፡ ወላጅ እናቱ ደራሲ ነች፡፡ በዘመንዋ በጣም የምትነበብና የምትወደድ፡፡ እንዴ ልጅ ሆኖ ተጣሉና እንዲህ አላት "ልንገርሽ፣ ከዚህ በኋላ ዓለም አንቺን የሚያስታውሰው የእኔ እናት ስለሆንሽ ብቻ ነው" እንዳለውም ሆነ፡፡ ሾፐንሀወርን አሁን ስናነሳው የእናትየው ስም እንኳን ጠፍቶናል፡፡ የእርሱ እናት ስለሆነች ግን አስታውሰናታል፡፡ እግዜር ሌላ ያሰበላት ከሌለ ከአንድ ትውልድ በኋላ ስብሐት የሚታወቀው የዜና አባት እየተባለ ይሆናል፡፡ ኢንሻላህ!

አንድ ነገር ልጨምርልህ፡፡ ለወጣት ደራሲያን ታስፈልጋለች፡፡ አንድ ዓይነት ግጥም አለች 'limerick' ይሏታል እንግሊዞች፡፡ የብዙ ነገር ምንጮች ናቸው፡፡ ይህቺ 'ሊመሪክ' ሕግ አላት፡፡ በሚመስል ጀምረህ በማይመስል መጨረስ አለብህ፡፡ ለመሳቅ ነው እንጂ ሌላ ምንም ፋይዳ የላትም፡፡ እኔ አንዷን ግጥም በስድ ንባብ ልበልልህ፡፡ አንዷ ወጣት ደራሲ ትነሣለች፡፡ ልትፅፍ አኮብኩባ ባለች፡፡ መጀመሪያ ግን ማንበብ አለብኝ ትላለች፡፡ እንዲህ ነው የምትለው" አለ በተቀመጠበት እጁን ወገቡ ላይ አድርጎ በቁንጥ የጎንዮሽ እያየኝ "እ! ቶልስቶይን እንዴ እንኳን ሳላነብ እንዴት መፃፍ እጀምራለሁ? ቆይቻ፣ ከጆን ዶን ሥራዎች አንድ እንኳን ሳልቃኝ? ዓይኔ ስር ያለውን ቻርልስ ዲክንስን እንደ ፈጠራውን ሳልቀምስለት ምኑ ነው የሚገፋው? እንዴት ተደርጎ ከቪክቶር ሒጎ ጋር ሳልተዋወቅ? የሚገርም ነው፣ ኤሚሊ ዲኪንስንን ምንም አላስተዋልኩም፡፡ ከቼሆቭ አጫጭር ልቦለዶች አንዷን ብቻ ነው ያነበብኩት፡፡ ትል ትልና፣ ለካ ራሱ ሼክስፒርንም አላነበብኳቸውም! ትላለች" ያዝክ? ትውስ ሲላት ዘና ብላ ፈገግ ትላለች፡፡ እፎይ!

ቀድሞ ካነሳነው ሃሳብ ጋር በፍፁም አይጋጭም ምን ያጋጨዋል? ይኸውልህ፣ አንዳንዱ ብዙ አንብቦ ጥቂት ነው ላለበት ማኅበረሰብ ማቀበል የሚችለው፡፡ ሌላው ደግሞ ጥቂት ቢያይም አድቅቆ ያስተውላል፡፡ በዚያ ትልቡቱም ብዙ ያዋጣል፡፡ ለማንኛውም፡ ውይ! እንሌን ሳላነብ? እያልክ መጨነቅ ሳይሆን፣ የተወሰነውን አይተህ ነብስህ እንደ መራችህ መጓዝ ይሻላል ነው የምለው፣

ይኼውልህ፣ ወጣቱ መበላሸት ከፈለገ መበላሸቱ አይቀርም፡፡ እኔ ደግሞ እባክህን ተበላሽልኝ ብዬ የማበላሸው ወጣት የለም፡፡ ምን ስለማደርገው ነው የማበላሸው? እንደፈለገህ ኑር ስላልኩት ነው



ያበላሸሁት? እንደ መሰለው ይኑር፡፡ እንዲበላሽ ከተፈጠረ ይበላሽ፡፡ እኔ የለሁበት! ለነገሩ መምከርም በተፈጥሮዬ አልወድም፡፡ ምን ትመክረኛለህ ካላለኝ በስተቀር አልመክረውም፡፡ እንደገና ጠይቀኝ በአመላለሴ ካልረካህ?

Occupational hazard የሚባል 'አይዲያ' አለ፡፡ ወታደር በጥይት የመሞት፣ ሸሌ በኤድስ የመያዝ ዕድሉ አለ፡፡ እዚህ ሥነ ጽሑፍ ዓለም ውስጥ ስንገባም እንዲሁ አለ፡፡ "እኛ ወጣቶች ነን፣ ለምን መንገዳችንን አታሳየንም?" የሚሉኝ አሉ፡፡ አይደለም የእነርሱን የራሴንም መንገድ አላውቀውም፡፡ እየተጓዝኩ መንገዴን መለስ ብዬ ሳየው ነው ትንሽ ትንሽ የሚገባኝ፡፡ እና የማይቀር ነው፡፡ ይልቅ የሚጠሉን የሚስቁብን ባይኖሩ የሆነ የጎደለ ነገር አለ ትላለህ፡፡ ይህ የማይቀር ነው፡፡ ምንም ልናስብበትም አያስፈልግም፡፡ አይቶህ ለአንዳንዱ ደስ ትለዋለህ፤ ለአንዳንዱ ደግሞ ታስጠላዋለህ፡፡

እ! በነገራችን ላይ ማስጠንቀቂያ ልስጥህ፡፡ ደራሲንና ሴትን ልጅ ስታደንቅ እያየህ ይሁን፡፡ ደራሲውም ችሎታውን፤ ሴቷንም ልጅ ውበቷን ስታደንቅ የሚያስከራቸው አሉ፡፡ አንተ ግን የሚያስከራቸውንና የማያስከራቸውን እየለየህ መሆን አለበት አድናቆትህ፡፡ ምክንያቱም መልክህን ከረሱ በኋላም ሕይወታቸውን በሙሉ እንደሰከሩ የሚቀሩ አሉ፡፡ ይህ ነው ማስጠንቀቂያዬ፡፡

እንዳንተ ወጣት ጓደኞች አሉኝ የሚጥፉ፡፡ የሚፅፉት ወርቅ ነው ልልህ እችላለሁ፡፡ 'ጂኒየስ' ናቸው፡፡ ችግሩ ግን እኛ አገር ዓላማህን የሚረዳልህ ሀብት ያለው ሰው አታገኝም፡፡ ሀብታሞቹ አገር 'ኤጀንት' የሚባሉ አሉ፡፡ ድርሰትህን ትሰጠዋለህ፡፡ ያነብና ወስዶ ለአሳታሚዎች ይሰጣል፡፡ አንዱ እንቢ ቢል ወደ ሌላው ይወስዳል፤ ያሳያቸዋል፣ ያስተዋውቅሃል፣ የአንተ 'አይዲያ' ገብቶታል፡፡ ነገ ወጥተህ ታላቅ ደራሲ እንደምትሆንም ያውቃል፡፡ ለልዩ ልዩ አሳታሚ ድርጅት በመስጠት ይከታተላል፡፡ ያሳትማል፡፡ ለአገልግሎቱ የተወሰነ 'ፐርሰንት' ከመጽሐፉ ገቢ ይወስዳል፡፡ እኛ አገር ስትመጣ፣ እንኳን ሥነ ጽሑፍ ገብቶት 'ኤጀንት' ቢሮ መክፈት ይቅርና በቅጡ የሚያሳትም ድርጅት ያለው ያንን ያህልም ነው፡፡ አሁን አንተ ሚሊየነር ብትሆን! ስብሐት፣ አጋፋሪ እንደሻውን ጻፍ፤ ቅድሚያ ይህንን ያህል እከፍልሃለሁ ብለህ ካሽ አትሰጠኝም?

አምንሃለሁ፡፡ ገንዘቡ ያላቸው ሀብታሞች የሚነበበውን ወጣት ደራሲ ለማበረታታት ማድረግ ያለባቸው እንደእዚያ ነው፡፡ ዶስቶዬቭስኪን ያነበብነው እኮ እንዲህ ቅድሚያ ገንዘብ አሳታሚዎቹ እየሰጡት ነው፡፡ ነብሱን አውቀዋታል፡፡ 'ጂኒዬስ' ነው፡፡ ለትርፋቸውም ቢሆን፤ እኛም ያንን ድንቅ በረከት እንድንቋደስ

@Amaricbookstore

አደረጉን፡፡ እንኳንም ቅድሚያ ያበደሩት፡፡ የአበሻው አማታሚያም ወደፊት እንዲህ የሚያደርግ ይመስለኛል፡፡ ለአሁኑ ካደነቁህ፣ ድራፍት አብረሃቸው ከጠጣህ በቂያቸው ነው፡፡

ኡና ሙኖ የሚባል የዩኒቨርሲቲ መምህር ነበር፡፡ ስፔናዊ ነው፡፡ The tragic sense of life የምትል መጽሐፍ ደርሶዋል፡፡ በጣም ቆንጆ ነች፡፡ በጅምሩ ላይ የያዝኳት ሃሳብ እንዲህ ትላለች፡፡ አርቲስቶች፣ ደራሲዎችና የፊልም ተዋናዮች የዘላለም ሕይወት ጥማት አለባቸው፡፡ መሞት ስለማይቀር ቀሪው ስማቸው ነው፡፡ መመለከን እዚህ ጋ በቃኝ አይሉም፡፡ ይህንን በሸርሙጠችም ብትወስድ እንደ እዚያው ነው፡፡ አዲሷ ሸሌ ሌሎች አዳዲስ ወንዶች ናቸው የሚፈልጓት፡፡ ይሁን እንጂ የድሮዋ ሸሌ አዲሷን አትወዳትም፡፡ እሷ ብቻ ዘለዓለም ተፈላጊ እንደሆነች መኖርን ትፈልጋለች፡፡ ብዙዎቹ አርቲስቶችን እያቸው እስኪ በግል ስትጨዋወቱ፡፡ እገሌ ከተነሣ ያንቋሽሹታል፡፡ ካንቋሸሹ ደግሞ መድረኩ ላይ እነርሱ ብቻ ይቀራሉ፡፡ መድረኳ ባዶ ሆና እነርሱ ብቻ እንዲያበሩ ይፈልጋሉ፡፡ የዘለዓለም ሕይወት ጥማታቸውን በዚህ ይተኩታል፡፡ ስለዚህም ለወጣቶቹ ደራሲያንና አርቲስቶች እንዲቀጥሉ ይህችን የኡናሙኖን ጥበብ ነው የማቀብላቸው፡፡

አንዳንድ ደራሲያን የፃፉትን ሁሉ ይወዳሉ፡፡ ልክ እንደ እናት፡፡ አለልህ አጫውቼህ ይሆናል፡፡ ብደግመውም አሪፍ ነው፡፡ እንደ ቻርልስ ዲከንስ ዓይነት ደራሲ፡፡ ሁል ጊዜ በወቅቱ እየፃፈ ያለው መጽሐፍ ነው ስሜት የሚሰጠው፡፡ "እንደዚህ ቆንጆ ፅፌም አላውቅ!" እያለ ነው ሚፅፈው፡፡ ይህንን አባባል ቻርልስ ዲከንስ ቀድሞን ተናገረው እንጂ በጤና እየፃፍክ እየተጠበብክ ከሄድክ የሰው ልጅ የሚያስበው እንደ እዚያ ነው፡፡ ጤናማ ከሆንክ እገሌን ለመብለጥ ሳይሆን መፃፍ ስላለብህ ፃፍ፡፡ መጠበብ ያለብህ ሐሳብ ስለመጣልህ ነው የምትጥፈው፡፡

ቶልስቶይ ሲጥፍ ምኑም አይቀረውም፡፡ ናፖሊዮን ራሺያን ሲወር ፈረሱን፣ ጠሩን፣ አገር ምድሩን ሁሉ ያሳይሃል፡፡ ትዕግሥትንም ትማርበታለህ፡፡ ለምሣሌ የቶልስቶይ የፈጠራ ሥራ War and Peace በሩስኪ ስንት ገጽ እንደሆነ አላውቅም፡፡ በእንግሊዘኛ ከሺ ገጽ በላይ ነው፡፡ ያንን ድርሰት ባለቤቱ ሰባት ጊዜ በእጇ ጽፋ ገልብጣለች፡፡ አዎን ሰባት ጊዜ፡፡

ቪክቶር ሁጎን አስታወስከኝ በአንድ ወቅት አንደኛው ድርሰቱ ኅትመት ላይ እያለ እሱ ከፓሪስ ከተማ ለግል ጉዳዩ ወጥቷል፡፡

@Amharicbookstore



ባለበት ለአሳታሚው ሰውዬ ቴሌግራም ላከ፡፡ መልዕክቱ "?" ነች፡፡ አሳታሚውም "!" ሲል መለሰ፡፡

አንተ እንደእዚያ አስበህ ግብ ካለህ ሴትን ሳታቅፍ መኖዝ ትችላለህ፡፡ ግብም ሳይኖርህ ሴትንም ሳታቅፍ ዕድሜህ ቢረዝምልህ ምን ታደርግበታለህ? የእኔን ልንገርህ፡፡ ዓላማና ግብ ሲኖረኝ ነው የዕድሜዬን መርዘም የምፈልገው፡፡ አለበለእዚያ ግን ደስ ያለችኝን የምወዳትን ልጅ እያቀፍኩ ዕድሜዬ ያጠር፡፡

በእውነት፡፡ ወሲብን ጠብ እርግፍ አድርገው ትተው ታላቅ የሆኑ ሰዎች አሉ፡፡ የዚያኑ ያህልም እየተደሰቱ የሡሩና በሥራቸውም የተደነቁና የተከበሩ አያሌ ሰዎች አሉ፡፡ ለምሣሌ ጋንድሂን ውሰድ፡፡ በወጣትነቱ ወቅትና በጎልማሳነቱ ዘመን በወሲብ ይደሰት ነበር፡፡ ከዚያም እየበሰለ ሲሄድ ሴትን ማቀፍ ተወ፡፡ ወደ ታላቅ ተልእኮው አመራ፡፡ ይህ እንግዲህ ለአንዳንዱ በተለይ የሚፈቀድለት ነው፡፡ ያለበለዚያማ የሰው ዘር በሙሉ ወሲብን እርግፍ አድርጎ ቢተው ዓለም ባዶ ትሆን ነበር፡፡ እኔ ግን በራሴ በኩል ያለኝን አቋም አሳውቄሃለሁ፡፡

አሀ! ይኸውልህ:: ልክ መጣ:: ወጣቶቹን ዓይንና ጆሮ ሁኑ እላቸው ነበር:: ስለቋንቋ፣ ስለኅብረተሰብ፣ ስለአጻጻፍ ጠይቀኸኝ አካፍዬአቸዋለሁ:: አሁን የቀረኝ 'አይዲያዋ' ነችና እንዳልከው አንድ ልስጣቸው:: እኔ ወጣት ብሆን አባ ሆርን ነበር ረጂም ልቦለድ አድርጌ የምጽፋቸው:: አባ ሆር የእውነት ሰው ናቸው:: አባቴ ያውቋቸው ነበር:: እሳቸው ናቸው ስለ አባ ሆር ያጫወቱኝ:: አባ ትጓዥ ናቸው:: መንገድ ይወጡና ይቆማሉ:: ነጋዴዎች ሲያጋጥሟቸው ወዴት ናችሁ? ይላሉ:: ነጋዴዎቹ ይነግሯቸዋል:: እኔም ወደእዚያው ነኝ ብለው አብረዋቸው ይጓዛሉ:: አንድ ቦታ ደርሰው የተወሰነ ጊዜ ቆይተው ለውጥ ሲያስፈልጋቸው እንደገና ተነስተው ከተጓዦች ጋር ይነጉዳሉ::

በደንብ! ወጣቱ ደራሲ ግን ከምርጥ ምርጡ ላይ እያተኮረ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዘር አንድ ወግ ልንገራችሁ ቢለን በአንድ ቅጽ ብቻ ስለማይጨርሰውም ግዴታ ሌላ ቅጽ ይደግመናል ብዬ እገምታለሁ::"

በፈገግታ ያስተውለኛል፡፡ ሰዎችን በፈገግታ በሚያይበት ጊዜ ዓይኖቹ ፍቅርን ያመነጫሉ፣ ብሩህ ገፅ ይኖረዋል፡፡ ለወዳጆቹ የሚያስቅ ጉዳይ በሚያወራላቸው ወቅት ከወዳጆቹ ይልቅ ራሱን እያስፈነደቀት ነው የሚጫወተው፡፡ አሁንም በዚህ ስሜት ውስጥ ሆኖ "ዘነበ ቆንጆ ዕድል ነው ያገኘሁው፡፡ ደግሞ አይምሰልህ፡፡ እኔም እየተጠቀምኩ ነው፡፡ እኔ አንተን ሳስተምርህ እኔ ውስጥ ዝጎ

የነበረውን እየፈገፈገከኩ፣ ለራሴም እየተማርኩ ነው፡፡" ይለኛል በትልቅ እርካታ፡፡

***

## ፶፩

## ሃያሲያን

አሁን ወንድማችን አምስት፣ ስድስት፣ ሰባትን አምጥቶ እንድፈርምለት እንዳደረገኝ ሁሉ ከአንባቢዎቼ ጋርም እንገናኛለን፡፡ ወጣቶች፣ ጎልማሶች አዛውንቶች፣ አጋጥመውኛል፡፡ ይጨብጡኛል፡፡ አድናቆታቸውን ይገልፁልኛል፡፡ አንዷን ላውጋህ፡፡ ሲቲሆል ቁጭ ብዬ ያንተን ፀሐይ የምትመስል ልጅ መጣች፡፡ አኳኋንዋን ሳየው እንደ ወደደችኝ ከገጽታዋ ተረዳሁ፡፡ ተነሳሁና ሳምኳት፡፡ ተሳመችልኝ፡፡

"የምትጽፈውን ሁሉ አነበዋለሁ፡፡ የምትጽፈው ደግሞ እውነት ነው" አለቺኝ፡፡

"ጴንጤ ነሽ እንዴ?" አልኳት በግምት፡፡

"ነኝ" አለች፡፡

እየሀ ጴንጤዎች እንኳን ኒሻን ይሸልሙናል፡፡ በባሕሪዬ የአበሻ ቅሕትናም ሆነ ትዕቢት የለብኝም፡፡ ስለዚህ ቆንጆ ሐሳብ ጆሮዬ ስለሚሰማ፣ የምጽፈውም ቆንጆ የሆነው ለዚህ ይመስለኛል፡፡ ደግሞ ይህንን ስል መጻፍን አክብደህ እንዳታየው፣ ምንም ማለት አይደለም፡፡ ገበሬ ይበልጣል ቆንጆ የሚያበቅል፤ ሐኪም አለ፣ መምህር አለ... እያልክ ትሄድና በመጨረሻ ደራሲ ጋ ትደርሳለህ፡፡ ደራሲነት እኮ ጌጥ ነው፡፡ ውበት ነው፡፡

አዎን፤ አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል፡፡ ከእኔ ቤት የአምስት ደቂቃ መንገድ ሄጄ የምጠጣባት ቤት አለች፡፡ እቤቴ እህል ባልበላ እንኳን እዚያ እመገባለሁ፡፡ አንድ መልከ መልካም ሰው መጣ፡፡ በቀይ ፊቱ ላይ ጥቁር ጢም ያለው፣ መነጽር ያደረገ፡፡ ጠጋ አለኝና «ከርሶ ማወቅ ስለምፈልግ ነው» ብሎ መጠየቅ የሚፈልገውን ነገር አነሳ፡፡ ኮተታም ነው፡፡ እኔም ተገቢውን መልስ ሳይሆን የመጣልኝን

@Amharicbookstore



ሰጠሁት፡፡ «ድጋሚ ልጠይቅ» ሲል «ዝጋ!» አልኩት፡፡ አስታውስ የቤቱ እመቤት እኔን እየጠበቀችኝ ነው፡፡ ቹክ አለብኝ፡፡ «ተነፋ!» አልኩት፡፡ ቢመታኝ እንደሚያደቀኝ አውቃለሁ፡፡ ግን አካሉ ቁልል ሥጋ ነው እንጂ ነፍሲቱ የሆነ የጎደላት ነገር አለ፡፡ የመጠጥ ቤቱ ጠጪዎች ሊያግባቡን ሞከሩ፡፡ እኔ ፈቃደኛ አልሆንኩም፡፡ በሥነ ጽሑፍ ሥራዎቼ ላይ ተራ ዘለፋ ዘለፈኝ፡፡ በቃ ጠላሁት፡፡ አማላጅ ላከብኝ እንታረቅ ይቅር በሉኝ ብሎ በቀይታ ዘጋሁት፡፡ ተለያየን፡፡

ሌላ ቀን ተገናኘን፡፡ እኔ እንደነገርኩህ የአባቴ ዓይነት ባሕርይ ነው ያለኝ፡፡ እንደ ክብሪት ቱግ እልና ሲቆይ እረሳዋለሁ፡፡ የትናንት ቂም የለችም፡፡ ከእናቴም የወረስኩት አለ፡፡ ፀጥ ብሎ ማሳለፍ፡፡ መቼም ዞሮ ዞሮ ሁላችንም የአባትና የእናታችን ውጤት ነን፡፡ ሌላም የምንጨምረው ሥነ ልቦና አለ፡፡ ይቅር አልኩት፡፡ እርሱም ጥፋተኝነቱን አመነ፡፡ ታረቅን፡፡ ይህንን አስታውሳለሁ በጽሑፍ የተጣላኝን" አለና ተነስቶ ቆመ፡፡ ነጠላ ጫማ ተጫምቶ ለውሃ ሽንት ወጣ፡፡ እንደተመለሰ ነጠላ ጫማዋን አወለቀ፡፡ መደቧ ላይ ወገቡን ይዞ ቆሞ ወጉን ጀመረ፡፡ እኔ ከፊት ለፊቱ አንጋጥጬ እያየሁት አዳምጠዋለሁ፡፡ አካሉን እንደ ማፍታታት እያለ "ስትሸና ሳይቀር አሪፍ ሐሳብ ሊመጣልህ ይችላል፡፡ አሁን ባወጋነው ወግ ላይ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ያንን አሁን ትጠይቀኝ ይሆናል፤ ግን ሳንጠየቅ መመለስም መብታችን ነው፡፡ ሽባው ሰውዬ ባስኬት ቦል ተጫዋቹን እጅህን እንዲህ አድርገው እንደሚለው ነው፡፡ ለባለሂስ ምንም ቦታ አትሰጠውም፡፡ አንባቢህን ነው ማየት ያለብህ፡፡ አንባቢን የወደድኩትን ያህል አንዳንዶች ደግሞ አሉልህ፣ በእኔ ዕድሜ ውስጥ ሆነው የሚጽፉ፡፡ አንዱ ሌላውን ማሞገስም ሆነ፣ ማንቋሸሽ ያለ ነው፡፡ እየጠበቁህ ነው መንገድ ላይ፣ አገባንለት ሊሉህ፡፡ ለዚህች አንድ ገጠመኝ አለችኝ፡፡ እስከነታሪኳ ነው የምነግርህ፡፡ አንድ ነገር እግረ መንገድ ላይ ጻፍኩ፡፡ አንዱ በግል ጋዜጣ ላይ የሚሠራ ይከታተላል፡፡ ካው ቦይ ሲኒማ ላይ ጎበዙን ከገደልክ የእሱን ዝና ትወርሳለህ፡፡ እኔ ደግሞ ከእርሱ ጎበዞች መካከል አንዱ ነኝ፡፡ የአበሻን መሰሪነት አንተ ከእኔ እኩል የምታውቀው አይመስለኝም፡፡ በእኔ ላይ አጥላልቶ ጻፈ፡፡ አነበብኩት፡፡ ከጻፈው ሩቡን ያክል ትክክል ነው፡፡ በሱ ሽፋን ሶስት አራተኛው "እንነታረክ፣ ይዋጣልን" ነች፡፡ አሁን እሱ ምን እንደምመልስለት እየጠበቀ ነው፡፡ ሌላ አንባቢ ሳይገባው እሱ ብቻ ውስጠ ወይራዋን እንደሚያነባት አውቄያለሁ፡፡

"የማናውቀውና የማያውቀኝ ውሻ ቢጮህብን፣ መልሰን አንጮህ በትም፡፡ ሰው ነንና መንገዳችንን እንቀጥላለን፡ ከሐሳባችን ጋር በምናብ እየተጫዋወትን፡፡ እንደሚከተለው" ብዬ የዕለቱን ጽሑፌን